# የአሲምባ ፍቅር

በካሕሳይ አብርሃ ብስራት

አዲስ አበባ 2005 ዓ.ም.

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ህትመትና ስርጭት፡ ተስፋዬ ወልደዮሐንስ ሀይሌ

twoldeyohanes@yahoo.com

twoldeyohanes@gmail.com

+251-911433704

© ካሕሳይ አብርሃ ብስራት

የደራሲው ሙሉ መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

አስተያየት ለመስጠት የሚቀጥለውን አድራሻ ይጠቀሙ።

assimbafikir@yahoo.com





*ለሰማዕታቱ*

ሰማዕትነት የእምነትና የሃቅ እፁብ ዋጋ ነው። ስለሆነም በሰው ልጅ አቅም ሐውልት ማኖር ለሰማዕታቱ ያንሳቸዋል! የማያረጅ፣ የማይሸራረፍ ክብራቸውን በምንም መልኩ የማያጎድፍ፣ ፍፁም ዋጋ ያሻቸዋልና። ይህ መጽሐፍ የሐውልታቸው ምሉዕነት አካል ይሁን።

*መታሰቢያነቱ፡*

*በገጠርም ሆነ በከተማ ለሕዝብና ለሐገር ሲሉ የሕይወት መስዋዕትነት ለከፈሉ*

*የኢሕአፓ/ኢሕአሠ ሰማዕታት ይሁንልኝ።*

## በመጽሐፉ ዝግጅት የተሳተፉ

| | |
|---|---|
| አቶ መዝገበ ጥላሁን | የድምጽ ቅጅውን ወደ ጽሑፍ በመቀየር<br>የመጀመሪያውን ረቂቅ በማዘጋጀት |
| አቶ ነቢይ መኮንን | ስነ-ውበትና ይዘቱን ማጠናከር |
| ወ/ሮ ቆንጅት ብርሃን | አጠቃላይ ቴክኒካዊና ስነጽሑፋዊ<br>አደረጃጀትና ብቃት |
| አቶ አሥራት ከበደ | የፊደላት አጠቃቀም እርማት (ፕሩፍ ሪዲንግ) |





*መቅድም*

ከልብ በመነጨ ፍቅርና ቁርጠኝነት በለጋ ዕድሜዬ የጀመርኩት ጉዞ አቅጣጫውን የቀየረው ባላሰብኩት ሁኔታና ወቅት ነበረ። ማንኛውም ሰው በሁኔታዎች አስገዳጅነት ያላሰበበትንና አልሞ ያልመረጠውን ሕይወት እንደሚቀበል ሁሉ እኔም ዕጣ - ፈንታዬን ከተቀበልኩና በመራኝ ጎዳና መንጎድ ከጀመርኩ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ግን ለሐገርና ለሕዝብ የነበረን የጋራ ዓላማ አገናኝቶንና አፋቅሮን አብረን ብዙ ያሳለፍን ጓዶቼን ለአፍታ እንኳ የረሳሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። የሞቱለት ሕዝብና ቤተሰቦቻቸው ታሪካቸውን ያላወቁላቸውን ዕንቁ ወጣቶች ባስታወስኩ ቁጥር በፀፀት ከመሰቃየትና "አንድ ቀን!" ከማለት በዘኜ ባላውቅም ከፉከራ ለማለፍ ሳልችል ቆየሁ።

አንድ አጋጣሚ ግን ያን ፉከራዬን ዕውን የማደርግበትን ጉልበት ፈጠረልኝ። ወቅቱ ከሰባት ዓመታት በፊት ለሰስተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁበት ወቅት ነበር። እኔን ጨምሮ የአራት የኢሕአሠ ታጋዮችን ታሪክ አንድ ጋዜጣ ይዞ መውጣቱን ሰማሁ። ጋዜጣውን የሠጡኝ ከብሩ እና መዝገበ ጥላሁን ነበሩ። ታሪካችን በስፋት ተፅፎ ስመለከት የጸሐፊውን ፍላጎትና ጥረት ሳደንቅ በስንፍናችን ተናደድኩ፤ ታሪካችንን ለመፃፍ ሙከራ ሳናደርግ ያለፉትን ዓመታት አሰብኳቸው። መዝገበና ከብሩ ደግሞ ለዚህ የውስጥ ስሜቴ ማቀጣጠያ ይሆን ዘንድ ስሜታቸውን ገለጹልኝ፤ ታሪካችን ሳይፃፍ መቅረቱ እንደሚቆጫቸውና በጣም ትንሽ ብትሆን እንኳ ታሪክ ከባለታሪኩ አንደበት መስማት የቱን ያህል ሊያስደስት እንደሚችል ነገሩኝ። ወኔ ሰንቄ ወደ መኖሪያዬ ተመለስኩ:: በእርግጠኝነት ልናገር ከምችለው ከራሴ ታሪክ በመነሳትና የሌሎቹን በተለይም የተሠዉትን ጓዶቼን ታሪክ በማካተት ለመፃፍ በቁርጥኝነት ተነሳሁ። እነሆ ዕውንም ሆነ።

ይህን ታሪክ በመጽሐፍ መልክ ለማዘጋጀት ስወስን መነሻዬ ባሳለፍኩት አጭር የትግል ጊዜ የገጠሙኝን ሁኔታዎች፣ አብረውኝ የነበሩትን ታጋዮችና አንዳንድ

ተያያዥ አጋጣሚዎች በደንብ ለማስታወስ መቻሌን መተማመኔ ብቻ ነበር። ሆኖም ይህ መነሻ እንጂ መጽሐፍ ለመጻፍ እንደማያበቃኝ መጀመሪያውንም አውቀው ነበር። ምክንያቱም እኔ በሕክምና ሥራ የተሰማራሁ ባለሙያ እንጂ የሥነ ጽሑፍ ሰው አይደለሁምና ነው። እናም ያለኝን መነሻ ይዤ ቀሪውን ለማሟላት መንገድ መፈለግ ነበረብኝ። የመጀመሪያው ሙከራዬም ወዳጆቼን ማማከር ሆነ። ወዳጆቼም አበረታቱኝ፤ ቀስ በቀስም ሁሉም ነገር በሚፈለገው መንገድ መልክ መያዝ ጀመረ።

የመጀመሪያው ሥራ ታሪኩን በቅደም ተከተል በመቅረጸ-ድምፅ መያዝና ማሰባሰብ ነበር። ከዚያ ደግሞ ይህንን ታሪክ ወደ መጽሐፍ ለመለወጥ ታሪኩ ከተፈጸመበት ወቅትና ሁኔታ ጋር ትውውቅ ያለው/ያላት እና እምነት ሊጣልበት/ባት የሚችል/የምትችል የሥነ ጽሑፍ ችሎታ ያለው/ያላት ሰው መፈለግ ግድ ነበር። በደረሱኝ በርካታ ጥቆማዎች በመታገዝ ፍሊጋዬን ቀጠልኩና ነዋሪነቱ በአገር ቤት በሆነው በአቶ መዘገበ ጥላሁን ላይ ቀልቤ ዐረፈ። ተነጋገርን፤ ስምምነትም ላይ ደረስንና በድምፅ የተቀረጸውን ታሪክ አንድ ቅጅ ላኩሁለት። እነሆ ከብዙ ሥራ በኋላ ካሰብኩት በላይ እየተሳካ እዚህ ደረሰ።

ይህን ብዙ ጊዜ የፈጀብንን ረጅም ሂደት የተወጣነው ከአቶ መዝገበ ጋር ባደረግነው የጽሑፍ፣ የኢሜይልና የስልክ ግንኙነት ነው። የመጀመሪያው ረቂቅ እንዳለቀ፣ ሰራው የሚፈጥረው ስሜትና የመልእክቱ ብስለት በእኔና በጸሀፊው ዕይታ ብቻ የተለካ እንዳይሆን፣ በዚህ የትግል ታሪክ ውስጥ በቀጥታ የተሳተፉና ያልተሳተፉ ጥቂት ወዳጆቼ እንዲያነቡት በማድረግ አስተያየታቸውን ተቀበልኩ። ከታሪኩ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች የተካተቱበት ምክንያት ታሪኩ ለሌሎች ምን ዓይነት ትርጉምና ስሜት ሊሰጥ እንደሚችል ለመገመት እንዲቻል ነው። ከሞላ ጎደል የሁሉም አስተያየት ሥራውን እንድንገፋበት የሚያበረታታ ሆኖ አገኘነው። ሥራው ቀጠለና ታሪኩ ከተፈጸመ ከሦስት አሥርት ዓመታት በኋላ ለአንባብያን ዓይን ይበቃ ዘንድ በመጽሐፍ መልክ ታተመ።





ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ብዙዎች የኀደሉኝንና የማላገኛቸውን ተጨማሪ መረጃዎች በመስጠት ተባብረውኛል። ለዚህ ሥራ እውን መሆን የብዙ ወዳጆቼና የቀድሞ የትግል ጓደኞቼ ምክርና ማበረታቻ ጉልህ ድርሻ አለው። ስለዚህ በጥቅሉ ሁሉንም አመሰግናችኋለሁ ማለት ይገባኛል።

የመጀመሪያው ረቂቅ ከተጠናቀቀ በኋላ ሮባ፣ ጌራ፣ ዶክተር ተስፋ ዓለም ገብረ መስቀል፣ ዶክተር አዲስ ዓለም ባሌማ፣ ዶክተር ወልዱ ወለደኢየሱስ፣ አቶ ሙሉጌታ ከበደና አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ ረቂቁን በትዕግሥት አንብባችሁ ስለሰጣችሁኝ ጠቃሚ አስተያየቶች ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ሺፈራው የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠትና ከሌሎችም ለማግኘት እንድችል ስላደረገው ጥረት፣ እንዲሁም ማስረሻ ለሰጠችኝ መረጃ ሳላመሰግናቸው አላልፍም።

በመጨረሻም ለዚህ ሥራ ስል ቤተሰባዊ ጊዜያቸውን ለተሻማኋቸውና በሐሳብም ለደገፉኝ ለባለቤቴ ለሰምሃል ገብረ እግዚአብሔር ካሕሳይ እንዲሁም ለልጆቼ ለአሉላ፣ ለካሌብና ለናሆም ካሕሳይ ያለኝ ምስጋናና ከፍተኛ ፍቅር እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ።

ካሕሳይ አብርሃ ብስራት (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)

## መግቢያ

ይህ የትግል ታሪክ በአሥራ ዘጠኝ ስልሣዎቹ መጨረሻና በሰባዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ሲታገሉ ሕይወታቸውን የሰው ጓዶቼ ታሪክ ነው። በበኩሌ፤ እነዚህን ጓዶቼን መዘከር፣ እንዲሁም ቤተሰብና ዘመድ ወዳጆቻቸው እንዲኮሩባቸውና፣ ምን ዓይነት ልዩ ሰዎች እንደነበሩ እንዲያውቁላቸው፤ እስከአሁን አውቀው ከሆነም፣ ተጨማሪ ምስክርነቴ ያንን እንዲያጠናክርላቸው ለማድረግ መሞከር ግዴታዬ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ስለአለፉት ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን መሥዋዕትነትና እውነተኛ የወገን ፍቅር ስሜት፣ ቢያንስ የምናውቀውን ያህልና በምንችለው መንገድ መመስከር፤ አንዱ ሐላፊነታችን ነው። የራሳቸውን ኑሮ ጥለው፣ ለሌሎች ነጻነት ሲሉ መሥዋዕትነት የከፈሉ ኢትዮጵያውያንን፤ በተቻለንና ባለን አቅም ለመዘከርና ቢያንስ ስማቸው በታሪክ መዝገብ እንዲቀመጥ ለማድረግ፤ መጣጣር ተገቢ ነው። ለሌሎችም ስለሰው ልጅ ነጻነት በነበራቸው እምነት ለተሠዉ፤ እንዲሁም በተመሳሳይ ዓላማ የአካልና የአእምሮ ሰቃይ ለደረሰባቸው በሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን፤ ስለተቀበሉት ሰቃይና መከራ ያለንን ትልቅ ከብር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመግለጽ በማሰብ ነው፤ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው።

መጽሐፉ በግለ ታሪክ መልክ የቀረበ ሲሆን፤ የትረካ አድማሱ፣ እኔ እስከነበርኩበት ጊዜ ድረስ በነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) እንቅስቃሴና የትግል ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው። በዚያ እኔ በነበርኩበት የትግል ወቅት የብዙ ወጣቶችና ምሁራን ሕይወት ተቀጥፏል። አያሌ ጓዶች ለተበደሉና ፍትሕ ላጡ ወገኖቻቸው ተቆርቁረው በዓላማቸው ጸንተው ሕይወታቸውን ሠውተዋል። ግፍ ለደረሰባቸው ሰዎች ሲሉ በትግሉ ነበልባል ጋይተዋል፡፡ ያም ሆኖ፤ የትግል ጉዳይ ነውና፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ በሂደት፣ በአጋጣሚ ወይም በዕጣ-ፈንታ ከእዚያ እሳት ተርፈን፤ ሰላማዊ ኑሯችንን ቀጥለናል። ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናስብ ግን እኛ ተርፈን ስለነሱ መሥዋዕትነት ምንም





ለማድረግ ባለመቻላችን የአብዛኞቻችን ኅሊና የጥፋተኝነት ስሜት አያጣውም። በዚህ መሠረታዊ ምክንያት፤ እኔም የኅሊና እማራጮቼን ሳሰብ ቆይቼ፤ በመጨረሻ፣ የቻልኩትንና የማውቀውን በመጽሐፍ መልክ ባሳትመው የበለጠ ተመራጭ እንደሆነ ስለተሰማኝ፤ በግለ ታሪክ መልክ ልተርካቸውና ማንነታቸውን ላሳይ ተነሣሣሁ።

ባተኮርኩበት የጊዜ ክልል ውስጥ በተቻለ መጠን ሁሉን አካታች አድርጌ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ። በወቅቱ ከነበረው ታሪክ ውስጥ በቀጥታ የተካፈልኩባቸውን ሥራዎች፣ ያገኘኋቸውን ታጋዮች ታሪክና በዚያን ጊዜ የተፈጸሙ ሆነው ሲነገሩ የሰማኋቸውንና እንደገና ለማጣራት የቻልኳቸውን፤ አንዳንድ በጣም አስፈላጊ ሁነቶችንም ለማካተት ጥረት አድርጌያለሁ። ከዚህ ሌላ፤ በሠራዊቱ ውስጥና በተለያዩ ቁልፍ የትግል ሂደቶች ላይ ልዩ ቦታ አላቸው ብዬ የገመትኩዋቸውን ወቅቶችና ሰዎች በተቻለ መጠን ዘርዘር ባለ መልክ ለመግለጽና ጎላ ለማድረግ ጥሬያለሁ።

የእኔ ሙከራ ሌሎችንም ማነሣሻ ሊሆን ይችላል የሚል ተስፋ አለኝ። ብዙ ተመሳሳይ ሀገራዊ ጥቅም ያለው እውቀትና ታሪክ ይዘው ነገር ግን ዛሬ ነገ ሲሉ ትውስታቸው እየደበዘዘ፣ ዓላማቸው እየሳሳ፣ "ምን ይሻላል?" በሚል ከጊዜ ጋር ለሚታገሉ፤ ሕይወት ሳትቀድማቸው ይቀድሟት ዘንድ፣ የእኔ ትንሽ መጽሐፍ ሊያበረታታቸው፣ እውቀታቸውንና የሰማእታት ጓዶቻቸውን ታሪክ ለእኛና ለመጪው ትውልድ እንዲያካፍሉም ሊያግዛቸው ይችላል ብዬ አስባለሁ።

እርግጥ፤ ይህ ታሪክ የብዙ ታጋዮችንና የተለያዩ የትግል ወቅት አጋጣሚዎችን ስለሚያነሣ ደግም ክፉም ነገር ያለበት ነው። መልካሙ ለልጆቻችንና ለመጪው ትውልድ ምሳሌና አርአያ፤ ክፉው ደግሞ ለመጪው ጊዜ ማረሚያና መማሪያ ይሆናል፡፡ ታሪኩ የተጻፈበት ምክንያት፤ እናቱም አባቱም ይሄው ነው፡፡ ስለሆነም፤ በጭፍኑ የመካብና የማጣጣል መልክ ያለው እንዳይሆን የተቻለኝን ሁሉ አድርጌአለሁ። ድርጅታዊ ስሕተቶችንና ችግሮችን በወቅቱ አመራር ላይ የነበሩ

ወደፊት እንደሚያብራሩዋቸው እምነቴ ነው፡፡ የኔ ብርቱና ትሑት ፍላጎት በተጨባጭ የነበረውን እውነት መግለጽ ብቻ ነው ።

በስም አጠቃቀም በኩል ከታሪኩ ባሕሪይ ጋር በተያያዘ ሦስት ዓይነት የባለታሪክ ስሞች እናገኛለን። እውነተኛ ስሞች፣ የምስጢር ስሞችና የቅጽል መጠሪያ ስሞች ናቸው። ከእነዚህ አንዳንድ አባላት በሦስቱም ስሞች የሚታወቁ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ በአንዱ ወይ በሦስቱ ቅይጥ ስም ነው የሚታወቁት። ስለዚህ መጀመሪያ ላይ የማውቃቸውን ሁሉንም ስሞቻቸውን በማስቀመጥ፣ በቀጣዩ ታሪክ ውስጥ ግን በጣም የሚታወቁበት ነው ብዬ የገመትኩትን፣ አንዱን ወይም ድብልቁን፣ ተጠቅሜአለሁ። የተሠዉ ጓዶችን ስም ለታሪክ ምስክርነትና ለሚያውቋቸውም ወዳጆቻቸው ስል በተቻለኝ መጠን እውነተኛ ስማቸውን ከአባታቸው ስም ጋር ጠቅሼያለሁ፡፡ የአባታቸውን ስም ለማወቅ ያልቻልኳቸውን ደግሞ የራሳቸውን እውነተኛ ስም ብቻ ለመጠቀም ተገድጃለሁ። በሌላ በኩል ይህንንም ለማድረግ ባልተቻለበት ሁኔታ የምስጢር ወይም ቅጽል ስሞቻቸውን ብቻ መጠቀም ግድ ሆኖብኛል። በዚህ ጊዜም ቢሆን ግን እንዲሁ ከመተው በሚል ሌላ ማንነታቸውን መግለጫ መንገድ ሳገኝ ለማከል ሞክሬያለሁ።

ከዚህ የትግል ጊዜና ታሪክ ጋር ብዙ ትውውቅ ለሌላቸው አንባብያን ግራ እንዳይጋቡ በማሰብ፣ በተደጋጋሚ የሚመጡ ሜዳ-በቀል ቃላት፤ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳሉ ከተቀራራቢ ትርጉማቸው ጋር የተቀመጡ ሲሆን፣ በቀሪው ትረካ ውስጥ ግን በትርጓሜ ቃላት ይቀጥላሉ። የእነዚህ ቃላትና የትርጓሜያቸው ዝርዝርም በመጨረሻ ገጽ ላይ ተቀምጠዋል።

ስያሜዎችም አሉ። እንዲህ ዓይነት ስያሜዎች በመጀመሪያ ትርጉማቸው ተቀምጦም በታሪኩ ውስጥም በዚያው በሜዳ አጠራራቸው የተጠቀምኩባቸው አሉ - ለምሳሌ ጋንታ።





አንባቢ ሆይ! ታሪካችን ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም ትውስታውም ሰፊ ነው፡፡ የጠፋው ጠፍቶ፣ የተረሳው ተረስቶ፣ ለጊዜው በእጃችን ያለው ይዘገብ ዘንድ እኔ እነሆ የበኩሌን አዋጣሁ፡፡ ሌሎችም የበኩላቸውን ቢያክሉበት አንድ ቀን ከሞላ ጎደል ምሉዕ ታሪክ ይኖረናል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

መልካም ትውስታ! መልካም ንባብ!!

## ሰብአዊነትና መሥዋዕትነት

ከይመር ንጉሤ ጋር ያስተዋወቀኝ አጋጣሚ የተፈጠረው ሰኔ 27 ቀን 1968 ዓ.ም ወልዲያ ለተልዕኮ የወጣ አንድ የኢሕአሠ ሠራዊት ቡድን ወደ አሲምባ በተመለሰበት ዕለት የተፈጠረ የጦርነት አጋጣሚ ከይመር ንጉሤ ጋር አገናኘን። ሰኔ 26 ቀን ውድዬ ከሚባል ቦታ ትንሽ አርፈን መሸት ሲል ወደ ቆላ በመውረድ ወደ ጉራ ወርቄ አመራን። በዚህ ጊዜ በአካባቢው የነበረ በመንግሥት የታጠቀ የገበሬ ጦር ውጊያ ከፍቶብን ከባድ ችግር ላይ ወደቅን። በውጊያው ላይ የተወሰኑ አባሎቻችን ሲሞቱ፣ ከፊሎቻችን ደግሞ ተማርከን በገበሬዎቹ ጦር እጅ ወደቅን። በውጊያው ላይ ከወደቁት መካከል ሁለቱ ጓደኞቻችን በመጥረቢያና በጩቤ ሲገደሉ አንደኛው ደግሞ በጦር ተወግቶ ቆሰለ።

የውጊያው ወሬ ከመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጆሮ እንደ ደረሰ ወታደሮችና ነጭ ለባሾች ተላኩ። የተላኩት የደርግ ሰዎች አካባቢውን ማሰስ ጀመሩ። በአሰሳውም በገበሬዎቹ ከተማረክነው ውስጥ ሃያ ያህል የኢሕአሠ አባላት በቁጥጥር ስር ውለው ወደ አዲስ አበባ ተላኩ። አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ በተለያዩ እስር ቤቶች በምርመራ ሲሰቃዩና ከእስር ቤት እስር ቤት ሲንከራተቱ ቆይተው በመጨረሻ የመገደላቸው ዜና በመገናኛ ብዙኃን ተሰማ።

ከዚያ የኢሕአሠ ቡድን አባላት ውስጥ ከመአቱ በተአምር ተርፈን በሕይወት ለመመለስ የበቃነው በጣም ጥቂት እድለኞች ብቻ ነበርን። እኔን የማረከኝ ይመር ንጉሤ ነበረ። በሕይወት እቆያለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም፤ ተስፋ ቆርጬ ሁሉ ነገር ጨለሙብኝ። ያ ደግ ገበሬ ግን ነጻነቴን መልሶ፣ በደርግ ኃይሎች እጅ እንዳልወድቅ ከልሎና ደብቆ ወደምፈልግበት ቦታ እንድሄድ ሸኘኝ። በመጨረሻ ስንለያይ ግን ነጻነቴን ካለማመኔ የተነሣ የሚገባውን ምስጋና ሳላቀርብለትና በወጉ እንኳ ሳልሰናበተው ነበር የተለየሁት። ወደ አሲምባ ተመለስኩ፤ ትግሉም ቀጠለ።

በመጨረሻው የሁኔታዎች መለዋወጥ ባሰብኩት መንገድ ሳይሆን በራሱ መንገድ ወስዶ አሜሪካን ሀገር አሳረፈኝ። በአሜሪካን ሀገር ሕይወት ሌላ ገጽታ ያዘ፤

እንደገናም ትምህርት ቤት ገባሁ። ትምህርቴን በተሳካ ሁኔታ ጨርሼ በሙያዬ ሥራ ተቀጠርኩ። ትዳር መሥርቼና ልጆች አፍርቼም ጥሩ የቤተሰብ ሕይወት መምራት ጀመርኩ።

ሕይወት ቀጠለ፤ ለእነዚያ በሕይወት እስካለሁ በውስጤ ለሚኖሩት ሲጋራ ዓላማችን ለተሠዉት ጓደኞቼ የገባሁትም ቃል በአእምሮዬ ውስጥ ቦታውን እንደያዘ ነው። በዓይነ ኅሊናዬ ፍንትው ብሎ የሚታየኝ በኢሕአሠ ውስጥ ያሳለፍኩት ጊዜና አብረውኝ የነበሩት ጓዶች ትዝታ ብቻውን ታሪኩን ሙሉ እንደማያደርገውም አሳምሬ አውቀዋለሁ። ማሰባሰብ የነበረብኝ አንዳንድ አስፈላጊ መረጃዎች ነበሩ። ከእነዚህ አንዱ፣ ይመር ንጉሤ ስለሚባል አንድ የወሎ ገበሬ የመጨረሻ ሁኔታ ማጣራት ነበር። ታሪካችንን ለመጻፍ ያለኝ ቁርጠኝነት በጨመረ ቁጥር የይመር ንጉሤን ጉዳይ  የማወቅ ፍላጎቴ እያደገ ሄደ። ቦታው ድረስ በአካል ሄጄ ማጣራት እንዳለብኝ ወሰንኩ። ሌሎች ያልተጠናቀቁና በጣም አስፈላጊ መረጃዎችን ግን አሁን በሕይወት ካሉና በቅርብ በማገኛቸው ጓዶቼ አማካኝነት ማግኘት እንደምችል ተስምቶኛል። ስለዚህ ብዙዎቹን መረጃዎች በቦታው ከነበሩ የትግል ጓዶቼ ያገኘሁ ሲሆን እንደ ይመር ንጉሤ ዓይነት ጉዳዮችን ግን የግድ ኢትዮጵያ እንደገና በመመለስ ራሴ ቦታው ድረስ ሄጄ ከማረጋገጥ ውጪ አማራጭ አልነበረኝም።

ይመር ንጉሤ፣ እዚህ ለመድረሴ ትልቅ ውለታ ያደረገልኝ አንድ የወሎ ደግ ገበሬ ነበር።  ሁኔታዎች ሲመቻቹልኝ ይመርን ለመፈለግና ሌሎች በህሊናዬ ውስጥ ለሚጉላሉ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የኢትዮጵያ ጉዞዬን ማቀድ ጀመርኩ። ከመጀመሪያው ጉዞዬ በኋላ አሥራ ሦስት ዓመታት ቆይቼ ዕቅዴ ተሳካልኝና በ1997 ዓ.ም. እንደገና ወደ ኢትዮጵያ  ለመምጣት ዝግጅቴን አጠናቀቅሁ።

አሜሪካን አገር ከምኖርበት ከዴንቨር ከተማ ወደ ኢትዮጵያ ለመድረስ ሁለት በረራዎችን መውሰድ ነበረብኝ። የመጀመሪያው ከዴንቨር ወደ ዋሽንግተን





የሚያደርሰኝ ሲሆን ሌላው ከዋሽንግተን ወደ አዲስ አበባ የሚወስደኝ ነው። ወደ አዲስ አበባ የበረርኩት በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ነበር።

የመጀመሪያውን ጉዞዬን ጨርሼ ከዋሽንግተን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ተሳፈርኩ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ውስጥ ስገባ ሀገሬ የገባሁ ያህል ይሰማኛል፤ ትዝታዎቼ ይቀሰቀሱብኛል። በዚህ በረራዬም ብዙ ትዝታዎች ቢመጡብኝም፣ አእምሮዬን የተቆጣጠረው ያ የወሎው ትዝታዬ ነበር። ወሎ ውስጥ በተለይም ጉራ ወርቄ በሚባለው ቦታ ላይ የተፈጠረው አጋጣሚ ለብዙ ዓመታት ሲቆረቁረኝ የቆየ ታሪክ ነው። እያንዳንዱ ድርጊትና ቦታ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት እንደተፈጸመ ሳይሆን ልክ ዛሬ የሆነ ያህል ወለል ብሎ ታየኝ።

ከዴንቨር በተነሣሁ በሦስተኛው ቀን አዲስ አበባ ገባሁ።  አዲስ አበባ ገብቼ ለሁለት ቀናት እረፍት አደረግሁና በሦስተኛው ቀን ወደ መቀሌ አቀናሁ። መቀሌ ከዘመድ ወዳጆቼ ጋር ጥቂት ቀናት ካሳለፍኩ በኋላ በሁለተኛው ሳምንት ወደ ወሎ ሮቢት ለመሄድ ተዘጋጀሁ።

ራሱን ለአደጋ አጋልጦ ሕይወቴን ያዳነውን ያንን ደግ ገበሬ ሳላመሰግነውና በደንብም ሳልሰናበተው በመለየቴ ዘወትር ይቆጨኝ ነበር። ያንን ቁጭት ለመወጣት፤ ውለታውን መክፈል የማይቻለኝ እንደሆነ አውቃለሁ። ሆኖም ውለታውን መቼም የማልዘነጋ መሆኔን ለመንገርና የምችለውን ለማድረግ ነበር ወደ ወሎ ሮቢት ለመሄድ የተነሣሁት።  መኪና ከአንድ ጓደኛዬ  በትውስት አገኘሁ። ጓደኛዬ መኪናውን የሰጠኝ ከአዘጋጀልኝ አንድ ጎልማሳ ሹፌር ጋር ነበረ። የሁለት መቶ ሠላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ያለውን የወሎ ሮቢት መንገድ ለመጀመር ከሹፌሬ ጋር ከመቀሌ በጠዋት ተነሣን።

የመኪናው አሽከርካሪ ዕድሜው ከወጣትነት ያለፈ ጎልማሳ ሰው ሲሆን ንቁና ጨዋታ አዋቂ ነበረ። የተግባባነው መንገድ ከመጀመራችን በፊት ነው።  ጨዋታ አዋቂነቱ ወዳድነት ዝምታዬን ገፎ መንገዳችንን ሳላውቀውና ሳልሰለች እንድደርስ አግዞኛል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ጨዋታችንን የሚለኩሰው እርሱ ቢሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜና እስከመጨረሻው ድረስ ያወራሁት እኔ ነበርኩ። እርሱ የእኔ ወሬ በየአጋጣሚው ሲቋረጥ እንደገና ለማስቀጠል አንዳንድ ቃላት ይጥላል፤ ያልገባውንም ይጠይቃል፣ አለያም ደግሞ ግርምቱ ይገልጻል። በተረፈ መኪናውን እያሽከረከረ በተመስጦ ያዳምጠኛል።

ከመቀሌ ዉጥተን ማይ ነብሪን እስከናልፍ ድረስ ያንንም - ያንንም እያነሣን ስንጥል ከቆየን በኋላ ሹፌሬ "ወደ ወሎ ሮቢት የምትሄደው ምን ዓይነት ስራ ለመጀመር አስበህ ነው?" አለና ጠየቀኝ። ከአሜሪካ የመጣሁ መሆኔን፣ የምሠራው በፋርማሲ ባለሙያነት እንደሆነ አስቀድሞ አውቋል። ግምቱም ምናልባትም ከመድኃኒት ፋብሪካ ጋር የተያያዘ ሥራ ለመጀመር የሚያስችል ጥናት ለማካሄድ እንደምሄድ ነበር።

ከሥራ ጋር በተያያዘ ሳይሆን በግል ጉዳይ እንደምሄድ ነገርኩት። "አኻ ወሎ ሮቢት ዘመዶች አሉህ ማለት ነዋ! የቅርብ ቤተሰቦችህ ወይም ዘመዶችህ መሆን አለባቸው?" አለኝ። ምላሼን ሳይጠብቅ "የወሎ ሮቢት ሰው ነህ እንዴ?" በማለት አስከትሎ ጠየቀኝ።

"ኧረ አይደለሁም። ሮቢትን ያየኋት ከሁለት ሰዓታት በማይበልጥ ቆይታ ነው። ከዚያ በኋላም ተመልሼባት አላውቅም" አልኩት።

በመገረም ግንባሩን ኮስተር አድርጎ ተመለከተኝና ከፊቱ በተዘረጋው መንገድ ላይ አተኩሮ መንዳቱን ቀጠለ። የመኪናውን ማርሽ ቀንሶና ነዳጅ መስጫውን ረግጦ የሹፌርነት ችሎታውን በሚያሳይ መልኩ መኪናዋን በሚፈልገው ፍጥነት ውስጥ አስተካከለና "ታዲያ እኮ እዛ መቀሌ እያለን ከአሜሪካ የመጣኸው ወሎ ሮቢት ሰው ለመጠየቅ እንደሆነ በአግራሞት ሲያወሩ ሰምቼ እኔም ግራ ተጋብቼ ነገር። መቼም ሰው ዘመዱን ለመጠየቅ ከአሜሪካ ሲመጣ አንተ የመጀመሪያው እንዳልሆንክ አውቃለሁ። ብቻ አንዳንድ ሰዎች ሁሉን ማዳነቅ





እንደሚወዱ አሰብኩና ነገራቸውን ችላ ብዬ ተውኩት" አለና ከእኔ አንዳች ነገር ለመስማት መጓጓቱን በሚገልጽ ሁኔታ ተመለከተኝ።

አልመለስኩለትም። በራሴ ሐሳብ ውስጥ ገባሁና ዝም አልኩት። ሁለታችንም በየራሳችን ሐሳብ ውስጥ ሆነን በዝምታ መንገዳችንን ቀጠልን። እኔ ሀሳብ ውስጥ የሚመላለሰው ይመር ንጉሤ ነበር። "አሁን በሕይወት አገኘው ይሆን? ያኔ ምናልባት አርባ አመት ቢሆነው፣ ዛሬ የሰባ አመት ሽማግሌ ይሆናል" ብዬ አሰብኩ። እርጅና የተጫጫነውን ይመር ንጉሤን በዓይነ ኅሊናዬ ሳየው ቅር አለኝ። ትንሽ ቀደም ማለት እንደነበረብኝ አሰቤም ጸጸት ሸንቆጥ አደረገኝ። ደግሞ ለራሴ ይቅርታ ለማድረግ መንገድ ፈልጌ ሚስቱን እንደማገኛት ርግጠኛ ሆንኩና ራሴን አጽናናሁ። ያን ጊዜ ባለቤቱ በዕድሜ ከእርሱ በጣም እንደምታንስ ገምቻለሁ። "ደግሞ ልጆቹም ይኖራሉ፤ እነርሱ ባያስታውሱኝ እንኳ ለኔ እነርሱን ማግኘት ትልቅ ነገር ነው..." ሐሳቤ ከነይመር ንጉሤ ቤት ገብቶ አልወጣ ብሎኝ ሲዳክር የመኪናው መንገጫገጭ ከሐሰቤ አናጠበኝ። ዞር ብዬ ሾፌሩን ተመለከትኩት።

ሹፌሩ የመኪናውን መንገጫገጭ ከምንም የቆጠረው አይመስልም፤ በዝምታ እንደተዋጠ ከፊቱ መንገዱንና የመኪናውን መቆጣጠሪያዎች እየተመለከተ ይነዳል። ነዳጅ ሙሉ አድርገን ነው የተነሣነው። መኪናው ጥሩ ጉልበት ያለው፣ በደንብ የተያዘ ላንድ ክሩዘር ነውና ምንም የሚያሳስብ ነገር የለብንም። ለእንዲህ ዓይነት መኪና የአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ጉዞ ማለት ምንም ማለት እንዳልሆነ አውቃለሁ። ቢሆንም ግን መኪናው ሲዘልበት ሾፌሩ ይቅርታ ሊጠይቀኝ ይገባው ነበር፤ እርሱ ዞር ብሎም አላየኝ ግንባሩን ኮስትሮ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ መንዳቱን ቀጥሎአል። ዝምታዬ ስለከበደው ተናዶብኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ፤ ጨዋታ የለመደ ሰው እኮ ዝምታ እንደ ጨለማ ይከብደዋል።

ሐሳቤ ተመልሶ ወደ ወሎ ሮቢት ከነይመር ቤት ገባ። "እምባላጌ ደረስን፤ ሰባ ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘናል ማለት ነው።" አለና ከሄድኩበት በድንገት መለሰኝ። ቦታውን አላውቀውም፤ ዞር ዞር ብዬ ተመለከትኩ። ሾፌሩ ንግግሩን በመቀጠል

"አምባላጌን በፊት ታውቃታለህ? መቼም ታሪካዊ ከተማ ስለሆነች በስም የማያውቃት የለም" አለ። አንገቴን በመነቅነቅ የአዎንታ መልስ ሰጠሁት። እርሱ ግን አልተወኝም ዝምታውን ለመስበር እየታገለ ይመስላል። "ብዙዎቹ ትናንሽ ከተሞች እልፎ እልፎ ካልሆነ በስተቀር ይሄን ያክልም አልተለወጡም" አለ። እኔ እነይመርንና ከዚያው ጋር የተያያዙ ትውስታዎቼን ለማሰብ ስለፈለግሁ ምንም አስተያየት አልሰጠሁም። አሁንም ሌላ መኮርኮሪያ ርእስ በመፈለግ "መቼም አምባላጌ ሄደህ ባታውቅም ወደ ወሎ ሮቢት ስትሄድ፣ በዚሁ በኩል ነው የምታልፈው"አለኝ።

አሳዘነኝ፤ ደግሞም ዝምታው እንቅልፍ ሊያመጣበት ይችላል። ከትዝታዬ ወጥቼ ላጫውተው አሰብኩና "እኔ እንኳ በዚህ አልመጣሁም" አልኩት። በመናገሬ ይሁን በመልሴ ብቻ ነቃና ፈገግ አለ።

" እንዴ ምን ማለትህ ነው፣ ትቀልዳለህ?! ታዲያ በየት በኩል ሄድኩ ልትለኝ ነው?"

" እውነቴን ነው፣ በሌላ መንገድ ነው የሄድኩት?"

"በሌላ በኩል ደግሞ ምን መንገድ አለና ነው?"

"እይ በመቀሌ በኩል አይደለም የሄድኩት"

"እሺ መጀመሪያ የተነሣኸው ከየት ነው?"

"ከአዲግራት" አልኩት ከአሲምባ ላለማለት ፈልጌ። እስካሁን በዚህ በኩል ያለውን ታሪኬን ስለማያውቀው ለመሸሽ በመፈለግ።

ሰውዬው ግን የሚለቅ ነገር አይደለም። "ታዲያ በየት በኩል መጣህ? ደግሞስ ከአዲግራት ወሎ ሮቢት ድረስ ወደ ሁለት መቶ ሠላሳ ኪሎ ሜትር ተጉዘህ የመጣኸው ለሁለት ሰዓት ቆይታ ብቻ ነው ማለት ነው? ይሄ ዘመዴ ያልከውስ ሰው ይህን ሁሉ መንገድ ተጉዘህ መጥተህ እንዴት አላሳደረህም? ለመሆኑ ምን ያህል የቅርብ ዝምድና ነው ያላችሁ? ብቻ ሁሉም ነገርህ ግራ የሚያገባ ነው" አለኝ በመደነቅ እየተመለከተኝ።





"አዎን፣ ግራ እንደሆነብህ ይሰማኛል፤ ብነግርህም ሊገባህ አይችል ይሆናል። ልጠይቀው የምሄደውን ሰው ያወቅኩት በአጋጣሚ፣ ትውውቃችንም የሁለት ቀናት ነበር ብልህ ደግሞ የበለጠ አወሳስብብሃለሁ። እኔም ራሴ እንዴት እንደማስረዳህ ግራ ይገባኛል!" አልኩት ከምሬ።

"እሺ! ታዲያ ምን ቢያደርግልህ ነው፣ ከውጪ ሀገር ድረስ ልትፈልገው የመጣኸው? ለመሆኑ ምንድነው የሚሠራው?" ብሎ ተከታታይ ጥያቄዎችን ሰነዘረ።

"ገበሬ ነው! አንድ ደግ፣ ጀግና፣ ላመነበት የሚሞት፣ ተራ የወሎ ገበሬ!" አልኩት። ስሜቴን ከገጽታዬ ላይ የተመለከተ መሰለኝ።

"እውነትም ግራ የምታጋባ ሰው ነህ፤ የምትለው ሁሉ አልገባኝም! ለሁለት ቀናት ብቻ የምታውቀው አንድ ገበሬ፣ ግን ደግሞ ከአሜሪካ ድረስ መጥተህ የምትጠይቀው፤ ያውም ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ምን ማለት ነው? የምትናገረው ነገር በሙሉ የተለመደ ነገር አይደለም !!"

"አዎን ሊገባህ አይችልም ይሆናል፤ እንዳላስረዳህ ታሪኩ በጣም ብዙ ነው፤ በጣም ባጭሩ ልነግርህ አሰቤ ራሱ አጭሩም ለዚህ ጉዞና ግንኙነት ረዥም ሆነብኝ። በተጨማሪ ታሪኩን ለመረዳት እንደ ቅድመ ሁኔታ ማወቅ ያለብህ ነገሮች አሉ። ለዚህ ነው የምሸሸው፣ ወደሌላ ወደማታውቀው ነገር ውስጥ እንዳልከትህና አሁንም የበለጠ ግራ እንዳላጋባህ ፈርቼ ነው።"

"አንተ ሰውዬ! እኔን ለማሳበድ ተልከህ የመጣህ የመሰለኝ" አለና ራሱን እየነቀነቀ ፈገግ ብሎ በመኪናው የፊት መስታወት አሻግሮ መንገዱ ላይ አፈጠጠ።

ከፊት ለፊታችን ተዘርግቶ እየተጠቀለለ በመኪናው ስር ወደኋላችን የሚቀረው መንገድ ላይ ዓይኖቼን ተክዬ ቅዝዝ ብዬ ሳስብ ቆየሁና "በደርግ ጊዜ ኢሕአፓ የሚባል ድርጅት ታውቃለህ? ማለት የፖለቲካ ድርጅት?" አልኩት ሳያስበው። ደንገጥ ያለ መሰለኝ።

"እኔ በርግጥ ልጅ ነበርኩ። ግን ትዝ ይለኛል፤ አንድ የቅርብ ዘመዳችን ኢሕአፓ ነው ተብሎ ተገድሎ እናቴ ለቅሶ ከርማ እንደመጣችና ለረዥም ጊዜ የሐዘን

ልብስ አድርጋ እንደነበረ አስታውሳለሁ። ከዚህ ሌላ ያወቅኩት በሙሉ በወሬና በንባብ ነው። የእናቴ ሁኔታ ስለዚያ ወቅት የማወቅ ፍላጎቴን እንደኮረኮረው ነበር ያደግሁት፤ ዕድሜዬ እየጨመረ ሲሄድ ስለኢሕአፓ ብዙ ለማወቅ ሞከሬአለሁ። ደርግ በጣም የሚፈራ መንግሥት እንደነበረና ኢሕአፓ ደግሞ በጣም ጎበዝና ደፋር ወጣቶች እንዲሁም የተማሩ ሰዎች የነበሩበት ድርጅት መሆኑን ሰምቻለሁ"

"አዎን ልክ ነህ፤ በኢሕአፓ ስር ደግሞ በገጠር ወታደራዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ኢሕአሠ የሚባል ተቋም ነበረ። ይሄንንስ ታውቃለህ?" አልኩና ሌላ ጥያቄ አቀረብኩ።

"ኢሕአሠ ማለት አሲምባ የነበረው ጦር አይደል? የትግራይ ተወላጅ ሆኜ እንዴት አላውቅም? በሚገባ አውቃለሁ!" አለኝ።

"ይሄን ሳታውቅ ታሪኩን ብነግርህ ላይገባህ ይችል ይሆናል ብዬ ፈርቼ ነበር ጥያቄህን የሸሸሁት። ይሄን ያህል ካወቅህ ግን፣ ልፈልገው ስለምሄደው ጀግና ገበሬ ታሪክ ብነግርህ ልትረዳው ትችላለህ" አልኩት ለማረጋገጥ።

"አንተ ኢሕአፓ ነበርክ ማለት ነው?!" ለማወቅ የቸኮለ በሚመስል ስሜት ነበር የጠየቀኝ።

"አዎን! የኢሕአሠ አባል ነበርኩ"

"አኸ! አሁን ገባኝ፤ ኢሕአሠ ሆነህ የሠራኸው ወሎ ሮቢት ውስጥ ነበር ማለት ነው። አይደለም?" አለ እርግጠኛ መሆኑን ለማሳየት የሚፈልግ መሰለ። "ታዲያ ከአዲግራት ወደ ወሎ ሮቢት በየት በኩል መጣህ?" ጥያቄውን ቀጠለ ሾፌሩ።

ረፋድ ላይ ማይጨው ደረስን። ሮቢት ለመድረስ ወደ ዘጠና ኪሎ ሜትር ይቀረናል። እንደገና መንገድ ስንጀምር ታሪኩን እንደምነግረው ቃል ገብቼለት፣ መኪናችንን ከአንድ ሆቴል በር ላይ አቁመን ቁርስ ለማድረግ ወረድን።





ከቁርስ በኋላ ተመለስን፤ ሾፌሩ ጊዜ ሳያባክን መኪናውን አስነሥቶ ተፈተለከ። ልክ የማይጨውን ከተማ ለቀን ስንወጣ እየት አደረገኝ። "የቤት ሥራ እኮ ነው የሰጠኸኝ፤ ቁርስ እየበላን ሌላ ነገር ወደ አእምሮዬ ሊመጣ አልቻለም። ግራ ያጋባኝን የአመጣጥህን ምክንያት እስከማውቀው ቸኩያለሁ። መቼም እናንተ ኢሕአፓዎች ብዙ የሚገርም የችግርና የጀብዱ ታሪክ አላችሁ!" አለና ታሪኩን እንድጀምርለት ጎተጎተኝ።

"ታሪኩ በጣም ረጅም ነው። በአጭሩ ለመናገር ያህል"አልኩና ከየት እንደምጀምረው ግራ ገብቶኝ ጥቂት ዘገየሁ።

"ምነው ለመናገር ከበደህ እንዴ? ወይስ ደስ አላለህም? ደስ ካላለህም ብዙም አትጨነቅ!" አለኝ ቅሬታ ባዘለ ድምፅ።

"የሚያስጨንቅ እንኳ አይደለም፤ ከየት ብጀምር እንደሚሻል እያሰብኩ ነበር::" አልኩት።

"እንደሱ ከሆነስ እሺ" አለና እስቤ እስከምወስን ጊዜ ሰጠኝ።

"ዕለቱ ሰኔ 27 ቀን 1968 ዓመተ ምሕረት ነበረ..." ብዬ ከይመር ንጉሤ ጋር ያገናኘንን አጋጣሚ እተርክለት ጀመርኩ። ሾፌሩ በተመስጦ አዳመጠኝ። የይመር ንጉሤን ታሪክ ሰጨርስና ላሊበላ መገንጠያ ላይ ስንደርስ እኩል ሆነ። ሮቢት ለመድረስ አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ይቀራል።

"እንግዲህ የጓዳህለት ታሪክ ይሄው ነው" አልኩት።

ሾፌሩ በረጅሙ ተነፈሰና "እውነተኛ ታሪክ ሳይሆን ፊልም ወይም በመጽሐፍ ላይ ያነበብኩት ልብ ወለድ ነው የመሰለኝ" አለና ተመለከተኝ።

"እንግዲህ..." ላወራ የነበረውን ነገር ሳያስጨርሰኝ አቋረጠኝ።

"የሚገርመው ደግሞ የጊዜው ነገር ነው። ይሄ የሆነው በሰኔ ወር 1968 ዓ.ም አሁን ደግሞ ያው የሰኔ ወር 1998 ዓ.ም፤ ልክ ሠላሳ ዓመቱ!! ይሄን አሁን ማን ያምናል? በጣም ይገርማል!!" አለ። "እኔ የምልህ!" አለኝ ደግሞ ከእኔ መልስ

ሳይጠብቅ። "ለምን በመጽሐፍ መልክ አታወጣውም? ወይስ ሰው እንዲያውቅብህ አትፈልግም? እንደኔ ግን አሪፍ መጽሐፍ ይወጣዋል!" አለኝ።

"እንግዲህ ከተሳካ፣ ወደፊት እንደዚያ ለማድረግ እሞክራለሁ" አልኩት።

ወሎ ሮቢት እየደረስን መሆኑን ነገረኝ። ከዚያ በኋላ አልተነጋገርንም፤ ወደከተማው እስከንገባ ድረስ ሁለታችንም ከየራሳችን ሐሳብ ጋር ነበርን። እንዳለውም ወዲያውኑ ሮቢት ገባን።

ሮቢት እንደገባን "አውቶቡስ ተራውን ታውቀዋለህ?" አልኩት።

"በሚገባ እንጂ!" አለኝ።

"የዱሮው ይሆን ወይስ ተቀይሯል?" አልኩ ድግሞ።

"ኧረ ጥንትም ይኼው እንደነበረ ነው የሰማሁት" አለኝ።

"እባክህን ወደዚያ እንሂድ" አልኩት። ስሜቴ መለወጡ ለራሴም ታውቆኛል። ከጉራ ወርቄ ከይመር ንጉሤ ጋር መጥተን ወሎ ፈረስ አውቶቡስ የተሳፈርኩበት ቦታ ነው። ቅርብ ስለነበርን ወዲያው ደረስን። ሾፌሩ መኪናውን እንዲያቆም ነገርኩትና አቆመልኝ። አላማከርኩትም፤ ፈጠን ብዬ ወረድኩና ሰዎች መጠየቅ ጀመርኩ። ጥቂት ሰዎች "አናውቀውም" ሲሉኝ ፈራሁ፤ ይመር ንጉሤን ሳላገኘው እንዳልመለስ ሰጋሁ። አንድ በዕድሜ ገፋ ያሉ ሰውዬ ሳገኝ ደስ አለኝ። "አባቴ ይመር ንጉሤ የሚባል ሰው ያውቁ ይሆን?" አልኳቸው፡፡

"ወደዚህ ወደ ወርቄቶ ማርያም፣ ወደ ውድዬ በኩል ስሙን እሰማ ነበር" አሉኝ። በቅጡም ያመሰገንኩ አይመስለኝም፤ መኪና ውስጥ ገባሁና ወደ ውድዬ እንዲነዳ ነገርኩት። ከአስፋልቱ በስተግራ በኩል የሚያመራ መንገድ ይዘን ስንሄድ ወደ ገበያ የሚሄዱ አዛውንቶች አገኘንና መኪናችንን አቆምን። በዕድሜያቸው የገፉ የሀገር ሽማግሌ መሳይ ስለነበሩ ሊያውቁ እንደሚችሉ ገምተናል።

ይቅርታ ጠይቀን አስቆምናቸውና "እዚህ አካባቢ የሚኖር ሰው ብንጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?" አልናቸው። አንደኛው ሰውዬ "መሐመድ እባላለሁ፤





እዚሁ አካባቢ ነው ሀገሬ፣ እዚህ ወጣ ብሎ ይሄንን ጋራ ተሻግራችሁ ነው። ማንን ፈልጋችሁ ነው? ስሙን ታውቃላችሁ?" አሉን።

"ይመር ንጉሤ የሚባል ሰው" አልኳቸው

"ይመር ንጉሤ? ወይ ወንድሜን!" ብለው ጭንቅላታቸውን ይዘው ማልቀስ ጀመሩ።

ልቤ ስንጥቅ አለ። የሆነውን መጠየቅ አስፈላጊ አልነበረም፤ አውቄዋለሁ። እውነቱን መቀበል ግን አልፈለግኩም። ለመናገር መዘጋጀቴን ሳላውቀው ከአፌ "ምነው?" የሚል ቃል ሲወጣ በጆሮዎቼ ተሰማኝ።

"ይመር ንጉሤ እኮ ሞቷል!" አሉ።

"እንዴት ሆኖ?"

"በቃ እንዴት እንደሆነ አላወቅንም፣ ቀብርም ለመድረስ ጊዜው አልተመቸንም ነበርና አልደረስንም። ግን ይመር ንጉሤ ሞቷል" አሉና ቀና ብለው "በዚህ በኩል በመኪና ያስገባል፣። የክልል መኪኖች ሁልጊዜ ይመላለሱበታል። አገሩም ሰላም ነው። ወደ መንደሩ ብትሄዱ የበለጠ የሚነግሯችሁ ዘመዶቹን ታገኛላችሁ" አሉን። መኪናው ውስጥ እንዲገቡ ነገርናቸውና ባመላከቱን መንገድ መጓዝ ጀመርን። ጥቂት እንደሄድን አንድ የከተማ ሰው የሚመስል ሰው በእግሩ ሲሄድ አገኘን። መኪናውን እንዲያቆም ሾፌሩን ጠየቅሁትና "ወደየት ነው የምትሄደው?" ብዬ ጠየቅኩት መንገደኛውን።

" እዚህ ማዶ ጋራው አጠገብ ወዳለው ትምህርት ቤት ነው የምሄደው" አለ።

"ና ግባ እንሸኝህ" አልኩትና ይዘነው ሄድን። የተባለው መንደር እንደደረስን ብዙ ማጠያየቅ አላስፈለገንም። የይመር ንጉሤ ልጅ አግብታ በአካባቢው እንደምትኖር ተነገረን። ያገኘነው ሰው ልጅቱን አፈላልጎ ለማምጣት ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም፤ ይዟት ከተፍ አለ።

ልጅቱ ይመር ንጉሤን ትመስላለች፣ አባቷ ሲሞት እናቷ እርሷን እርጉዝ እንደነበረች፣ አባቷን በአካል እንደማታውቀው ነገረችኝ። "ልክ አባትሽን እኮ ነው የምትመስይው!" አልኳት ትኩር ብዬ እያየኋት።

"አዎን፣ ሁሉም ሰው እንደዛ ነው የሚለኝ" አለችኝ። ቀጥላ ደግሞ "እርሶ ግን አባቴን የት ነው የሚያውቁት?" ብላ ጠየቀችኝ።

"አባትሽን የማውቀው ድሮ - ድሮ! ከሠላሳ ዓመት በፊት ነበር። ከዛሬ ሠላሳ ዓመት በፊት እኔን አሳልፎ ላለመስጠት ቆራጥ አቋም የወሰደ ሰው ነበር። ጥላ ከለላ ሆኖ፣ ከሞት ያተረፈኝ ሰው ነው። እስካሁን ድረስ በሕይወት የቆየሁት በእርሱ ውለታ ነው። ያን ጊዜ ለደርግ አሳልፎ ሰጥቶኝ ቢሆን ኖሮ እንደሌሎቹ ጓደኞቼ እገደል ነበር። እናም እርሱንና እናንተን ቤተሰቡቹን ለመጠየቅና ውለታውን ያለመርሳቴን ለመንገር ነው የመጣሁት" አልኳት። ማልቀስ ጀመረች።

"አባቴ ጥሩ ሰው እንደነበረ ብዙ ሰዎች ይነግሩኛል። እኔ አላውቀውም፣ የሞተው ግን በመኪና አደጋ ነው" አለችኝ በለቅሶዋ መሐል። በእሷ ዕድሜ ስገምተው ይመር ንጉሤ ከሞተ አሥራ አራት አመት ይሆነዋል።

ያን ጊዜ ይመር ንጉሤ ማርኮ እቤቱ ሲወስደኝ ካየኋቸው ሁለት ሕፃናት አንዱ ወንድ እንደሆነ ትዝ ይለኛል፤ ሁለተኛውን ግን ተጠራጠርኩ። በአንዱ ልጀምር ብዬ "ታላቅ ወንድም አልነበረሽም እንዴ? እሱስ የት ነው የሚኖረው?" ብዬ ስጠይቃት እንደገና ማልቀስ ጀመረች።

"እሱም ሞቷል፣ ሁለቱም ወንድሞቼ ሞተዋል!" አለችኝ፤ ልክ እንደአዲስ ሐዘንተኛ እያለቀሰች።

"እናትሽስ አለች?" አልኳት የመጣው ይምጣ ብዬ።

"እናቴ እንኳ አለች" ስትለኝ ትንሽ ተንፈስ አልኩ።

"እናትሽን ልናገኛት እንችላለን? ወይስ እንዴት ነው?" አልኳት።





እናቷ ያለችበት ቦታ ሩቅና ለመኪናም የማይመች መሆኑን ነግራን እኛ ወዳለንበት ይዛት ብትመጣ የተሻለ እንደሚሆን ነገረችን። ተስማማን። ስልክ እንድትደውልልን ቁጥር ሰጠናትና "አባትሽን በሕይወት ላገኘው ባልችልም እናንተንም ቢሆን ትንሽ ልረዳችሁ እፈልጋለሁ" አልኳት። ጥቂት ገንዘብ ሰጥቻት "ለልብስና ለአንዳንድ ነገር መግዣ ይሆንሻል" ብያት ተለያየን። ወደወሎ ሮቢት ተመለስን።

በሦስተኛው ቀን ስልክ ደወሉልኝና እናቷን አነጋገርኳት። ታሪኩን ነግሬአት "ታስታውሽኛለሽ?" ብዬ ጠየቅኋት። ምናልባት እንደእኔ ያሉ ብዙ አስተናገደው ሊሆን ስለሚችል ላታስታውሰኝ ትችላለች ብዬ ተጠራጠርኩ። እርሷ ግን እያለቀሰች እንደምታስታውሰኝ ነገረችኝ። "ይመር ንጉሤ 'የት ገብቶ ይሆን? እምን ደርሶ ይሆን? ሀገሩ ገብቶ ይሆን ወይስ መንገድ ቀርቶ ይሆን?' እያለ ሁል ጊዜ ስለአንተ ያስብ ነበር። ወይኔ!! በሕይወት ኖሮ ቢሆን እንዴት ደስ ባለው!?" አለችኝ።

ስልክ የደወሉልን ከስልክ ማስደወያ ጣቢያ ሆነው ነበር። የስልክ ቤቱ ሠራተኛ ስልኩን ተቀበላትና ማንነቱን ከገለጸልኝ በኋላ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረበልኝ። "የኔ ወንድም ታሪክህን ሰምተናል! እዚህ አካባቢ ብዙ ሰዎች ሰምተው በጣም ተደስተዋል። ከሠላሳ ዓመት በፊት ውለታ ያደረጉልህን ሰዎች አስታውሰህ ለመጠየቅ የመጣህ መሆንህን ነው መንደርተኞቹ የነገሩኝ። ስለዚህ ሁለተኛ ጊዜ ስትመጣ ስልክ ቤት፣ ወይንም ፖሊስ ጣቢያ ብለህ ጠይቀህ ብትመጣ ደስ ይለናል። ስለአንተ አገሩ በሙሉ አውቋል፤ እስከታች እስከወርቄቶ ማርያም ድረስ ትላንትና የሚወራው ስለአንተ ነበረ። ብትመጣ ሕዝቡ እጅበ ወደ ውድዬ ይወስድሀል። እዚህ ከደረስክ አንተ የምትፈልገውን ሰው ቤት ማንም ያሳይሀል፤ በጣም ትልቅ ሰው ነሀ" አለኝ።

"አመሰግናለሁ፤ እንዳልከኝ አደርጋለሁ። እባክህን ልረዳቸው እፈልጋለሁና በሰጠኋቸው ስልክ እንዲደውሉልኝ ወይም በዚሁ አድራሻ እንዲጽፉልኝ በደንብ አስረዳቸው" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት።

## አንድ
## የሕይወት ኩርባዎች

*"ፀሐይ ስትወጣ፡ መንገዶች ሁሉ ወደ ልጅነት ያመራሉ"*

መቼም ማንኛውም ሰው የሕይወት መዞሪያ፣ መታጠፊያ ወይም መቀየሻ ኩርባዎች ይኖሩታል፡፡ አንዳንዶቹ አደገኛ ኩርባዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ መልካምና ሕይወትን ወደ ቀናው ጎዳና የሚመሩ ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከናካቴው ወዴት እንደሚወስዱ የማይታወቁ ብዙ የሚያለፉ፣ ብዙ የሚያስዳክሩ ይሆናሉ፡፡ የእኔ ኩርባዎች የገበሬ ቤተሰቦቼ ሕይወት፣ አሲምባ፣ ይመር ንጉሤና ድላይ ናቸው፡፡

የልጅነት አስተዳደግንና የትምህርትን ዓለም በአፍላው እንድቀምሰው ያደረጉኝ ናቸውና የሕይወቴን የመጀመሪያ ቅያስ ማበጀታቸው አጠያያቂ አይሆንም፡፡ አሲምባ ወድጄ፣ ፈቅጄ፣ ለትግል የገባሁበት የልጅነት ፍቅሬ ነው፡፡ ብስለትን፣ ፍርሀትና ድፍረትን፣ ሞትና ሕይወትን ገና በለጋ ዕድሜ ያሳየኝ የአሲምባ ኩርባ ነው፡፡ ይመር ንጉሤ ከሞት መንጋጋ ነጥቆ ያተረፈኝ፣ ልገድለው ስችል ሕይወቱን ያተረፍኩለት፣ ሕይወት የተቀያየርን፣ ቅን ሰው ነው፡፡ ድላይ የልጅነት ፍቅሬ ናት፡፡ የሕይወትን ዋጋና የሞትን አደጋ አውቅ ዘንድ፣ በፍቅር ሸማ ጠቅልላ የሰጠችኝ መቼም ከሕይወቴ ላወጣት የማልችል የጫካ ሕይወት፣ የተጋድሎ መከራ ፀጋ ናት፡፡ እነዚህ አራቱ እንደምን የሕይወት መዞሪያ ኩርባዎቼና አንጓዎቼ ሆኑ? ቢሉ የሚከተለው ታሪኬ ነው መልሱ፡፡

የተወለደኩት በትግራይ ክፍለ ሀገር፣ በአጋሜ አውራጃ፣ በዛላ አንበሳ ወረዳ ጥርቀ በሚባል ሥፍራ ነው። የዛላ አንበሳ ከተማ ከእኛ መንደር ሁለት ኪ.ሜ. ቢርቅም ወንዛችን ግን አንድ ነው። አባቴ አቶ አብርሃ ብስራት፣ እናቴ ደግሞ





ወይዘሮ ወለላ ረዳ ይባላሉ። ለቤተሰቦቼ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ስሆን፣ ከኔ በታች ሦስት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩ።

የአባቴ አባት፤ ቄስ ገበዝ ነበሩ፤ የቆሎ ተማሪዎችን የቤተክህነት ትምህርት ያስተምሩ ነበረ። እኔም ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሬ በፊት ከሚያስተምሯቸው ልጆች ጋር ተቀላቅዬ "ሀ...ሁ" የቆጠርኩት እርሳቸው ዘንድ ነበር። አያቴ በቤተክህነት ትምህርት የበለጠ እንድገፋ ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም ዛላ አንበሳ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለተከፈተ፣ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ከመግባት ሊከለክሉኝ ከበዳቸው። ስለዚህ ቀን ዘመናዊ ትምህርት እየተከታተልኩ ማታ ደግሞ የቤተ ክህነት ትምህርት እንድማር ተወሰነ።

ቅዳሜና እሑድ እንዲሁም በበዓላትና በክረምት ወቅት የዕረፍት ጊዜዬን የማሳልፈው አባቴን በማገዝ ነበር። ከብት በመጠበቅና በእርሻ ሥራዎች በመሳተፍ የአቅሜን ያህል ማገዝ ይጠበቅብኝ ነበር።

ከልጅነቴ ጀምሮ ስሰማ ያደግሁት ስለጦርነት ነበር። ቤተሰቦቼ፣ ጓደኞቼና መላው ማኅበረሰብ የሚያወራው የጦርነት ፖለቲካ ታሪክ በእኔም አእምሮ ውስጥ ቦታ ሳይዝ አልቀረም። አብዛኛው የዛላ አንበሳና አካባቢው ነዋሪ ወላጆቹ፣ አያቶቹና፣ ቅድመ አያቶቹ... በጦርነት ተወልደው ያደጉና በጦርነት ያረጁ ናቸው። እናም የዛላ አንበሳ ሕዝብ ስለጦርነት አውግቶ የማይጨርስ፣ ሰምቶ የማይሰለች የሆነው ሊረሳቸው የማይቻለው ከፉና ደግ የተቀላቀለባቸው፣ ጀግንነትና ፍርሀት የተሞላባቸው ብዙ የጦርነት ገጠመኞች ስለአሉት ነው። የዛላአንበሳ ነዋሪዎች፣ አሁንም ድረስ የጦርነት ጥላ ያልተለያቸው ድሀ ገበሬዎች ናቸው። ይህ ከጦርነት ጋር የተዛመደ ታሪካቸው ከመቶ ዓመታት በፊት የጀመረና ዛሬም ድረስ ያልተላቀቃቸው የቀን ተቀን ሕይወታቸው ክፍል ነው። ዛላ አንበሳ ትግራይና ኤርትራ ድንበር የሚጋሩባት ቁልፍ ቦታ በመሆኗ በነዋሪቿ የጦርነት ምንነት በተግባር የሚታወቅባት መንደር ነች። የሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን የዓለም አቀፍ የጦርነት ወሬዎችም እንኳ የመነጋገሪያ አጀንዳ የሚሆኑበት ጊዜ ነበር። ያ

ደግሞ በአዋቂዎች ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ በሕፃናቱም አእምሮ ውስጥ የራሱ ቦታ ነበረው። ለምሳሌ አራተኛ ክፍል እያለሁ የዐረቦችና የእስራኤል ጦርነት በሰፊው የሚወራበት ጊዜ ስለነበረ ዐረቦችና እስራኤሎች የሚዋጉበትን ምክንያት ማወቅ ለልጅነት አእምሮዬ ትልቅ የቤት ሥራው ነበረ። የዛላ አንበሳ አካባቢ የኤርትራ አዋሳኝ መሆን የኤርትራን የፖለቲካ ትኩሳት ለመለካት ምቹ ቦታም አድርጓታል። ከኤርትራ አማጽያን ጋር የተያያዙ ወሬዎችና ድርጊቶች ለእኛ ቅርብ ነበሩ።

***





በዘመናዊው ትምህርት ሰባተኛ ክፍል ስገባ በቤተ ክህነት ትምህርት ደግሞ ቅዳሴ ላይ ደርሼ ነበር። ሆኖም ዛላ አንበሳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰላልነበረ የቤተ ክህነቱን ትምህርት አቋርጬ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ለመቀጠል ወደ አዲግራት መሄድ ነበረብኝ። አዲግራት ከዛላ አንበሳ ሠላሳ አምስት ኪ.ሜ ስለምትርቅ እየተመላለሱ ለመማር አስቸጋሪ ነበር። ስለዚህ ለመጀመሪያ ግዜ ከቤተሰቦቼ መለየቴ ግድ ሆነ። አዲግራት በሚኖሩ ዘመዳችን ቤት እንድኖር ተመቻችቶልኝ አግአዚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብቼ መማር ጀመርኩ። የእናቴ አባት፣ አያቴ ደጃዝማች ረዳ በወር አስር ብር ተቆራጭ ስላደረጉልኝ ብዙም ሳልቸገር ሰባተኛንና ስምንተኛን ክፍል ተማርኩ። የመጣሁባት፣ የአዲግራት ከተማም ከጦርነት ጋር ያላት ዝምድና ከዛላአንበሳ ጋር የተመሳሰለ ነበር። የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ከጦርነት ጋር ያላቸው ትስስር ወደ ኤርትራ ድንበር እየተጠጉ በሄዱ ቁጥርና ቦታዎቹ ባላቸው ስትራቴጂያዊ ተፈላጊነት መጠን እየጠበቀ የመሄድ ባሕርይ አለው።

አዲግራት የጦርነት ከተማ ናት። የከተማዋ የጦርነት ታሪክ የብዙ ዓመታት እድሜ እንዳለው ለመረዳት ከተማዋን ማየት ወይም የኢትዮጵያን የታሪክ መጻሕፍት ማገላበጥ ብቻ ይበቃል። ጣሊያን ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት አዲግራት መግቢያና የመሸጋገሪያ መደራጃው፣ ለመውጪያው ደግሞ ለሽሽት መዘጋጃው ነበረች። በዚህም ከተማዋ በጦርነቶች ውስጥ ያላትን ቁልፍ ቦታ ወይም ስትራተጂያዊ አቀማመጥ እንደሚያመለክት እንረዳለን።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር መጋቢት 25 ቀን 1935 አዲግራት በጣሊያን ጦር ስር ከወደቀች በኋላ፤ የጣሊያን ጦር በደቡብ በኩል ወደ መቀሌ በመዝመት ዋና ጣቢያውን ያቋቋመው አዲግራት ላይ ነበር። የጣሊያን ጦር አድዋ ላይ ድል ሲመታ ደግሞ ከዐፄ ምኒልክ ጋር በተደረገው ድርድር ጄነራል አንቶኒዮ ባልዲሳር ለቆ እንዲወጣ የተደረገባት የመጨረሻ መሰናበቻው ከተማ አዲግራት ነበረች።

የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ የጦርነት ታሪክ ከውጪ ኃይል ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። የእርስ በእርስ ጦርነትም ታሪክ ብዙ ዓመታት ያስቆጠረና እስከዛሬም ድረስ ጥላውን እንዳጠላ ያለ ነው። ከ1990 ዓ.ም. የባድመ ጦርነት ተነሥተን ወደኋላ እስከ 1943 ዓ.ም. የመጀመሪያው የወያኔ አመጽ ድረስ ብቻ ብንቆጥር እንኳ አዲግራትና አካባቢዋ ያሳለፉት የጦርነት ሰቆቃ ከፍተኛ ነው። የኤርትራንና፣ ሌሎች የመንግሥት ተቃዋሚ ድርጅቶችን ጨምሮ በአካባቢው ሲንቀሳቀሱ ከአንድ ትውልድ ዕድሜ የሚበልጥና ሦስት መንግሥታትን ያስቆጠረ የጦርነት ታሪክ አሳልፈዋል።

አዲግራት የሚገኘው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተናግዳቸው ተማሪዎች የዛላ አንበሳን፣ የብዘትን፣ የአዳጋ ሐሙስን፣ የውቅሮንና የኤርትራ አዋሳኝ አካባቢዎችንም ያካትታል። ከተለያየ አካባቢ የመጣን መሆናችን ደግሞ ከትምህርት በተጨማሪ የተለያዩ ልምድና ባህሎችን ለመለዋወጥ እንድንችል ዕድል ሰጥቶናል። አዲግራት ውስጥ ከየኮሌጁና ከዩኒቨርሲቲ በዕረፍት ጊዜያቸው ወላጆቻቸውን ለማየት የሚመጡ ብዛት ያላቸው ተማሪዎችን ማግኘት የተለመደ በመሆኑም፣ ስለሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ በተለይም የመንግሥት ተቃዋሚ ስለሆኑ አስተሳሰቦችና ድርጅቶች፣ በደንብ እንድናውቅ አድርጎናል።

የመንግሥት ተቃዋሚ ድርጅቶችን ማንነት በቀዳሚነት ያወቅኩት አዲግራት ከመጣሁ በኋላ ነበር። አዲግራት ውስጥ የሚያውቁን የኤርትራ ተወላጆች ለእኔና ለጓደኞቼ የተለያዩ የፖለቲካ መጽሔቶችና በራሪ ወረቀቶች ይሰጡን ነበር። እኔ የፖለቲካ ጽሑፍ የሚባል ነገር መኖሩንም ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ያንጊዜ ነው። መጽሔቱ በትግርኛ ቋንቋ ነበር የተጻፈው። እኔና ጓደኞቼ ይህን መጽሔት ለመጀመሪያ ጊዜ ስንቀበል፣ ከሰው ገለል ያለ ቦታ መፈለግ ነበረብን። ከትምህርት ቤት ውጪ ጫካ ውስጥ ገብተን አነበብንና ለሰጡን ሰዎች መለስንላቸው። ጽሑፉን ስናነበው ልዩ ስሜት ነበር የተሰማኝ፤ ትግሉን





የመቀላቀልና ለውጥ የማምጣት ልዩ ስሜት! ከዚያ በኋላ የተለያዩ መሰል ጽሑፎችን የሚያመጡልንን ተጨማሪ ሰዎች ማግኘት ከባድ አልነበረም። የእነዚያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ደጋፊዎች አልያም አባላት የነበሩ ሰዎች መጽሔቶችና በራሪ ወረቀቶች ይሰጣቸው ነበር። ከእነርሱ መካከል ደግሞ ጓደኞቻችንም ሰላሉበትና ስለሚያምኑን እየሰጡን አንብበን እንመልስላቸዋለን።

በ1964 ዓ.ም. የስምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ አንድ ቀን ወደ ትምህርት ቤት ስንሔድ ፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ትምህርታቸውን አቋርጠው እየጮሁና ድናጋይ እየወረወሩ ስለወጡ ግርግርና ረብሻ ተነሣ። ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት ሲወጡ ያገኙትን የአንበሳ አውቶብስ መስታወት በድንጋይ እየሰባበሩ ሰላማዊ ሰልፋቸውን ቀጠሉ። በዚህ ጊዜ ከአዲግራት የጦር ካምፕ ወታደሮች መጥተው በከፈቱት ተኩስ ከተማዋ ተናወጠች። ሰልፈኞቹም በየአቅጣጫው እየሮጡ ተበተኑ። ግማሾቹ የሚሸሹት ወደወታደሮች ድንጋይ እየወረወሩና እየጮሁ ነበር።

እኔና የትምህርት ቤት ጓደኞቼም በተፈጠረው ረብሻ ግራ ተጋብተን በድንጋጤ መሸሽ ጀመርን። ኢትዮጵያ ሆቴል አጠገብ ጨረቃ ቤት የሚባል ቡና ቤት ነበረ። እየሮጥን ገባንና በየአልጋው ስር ተደበቅን። ወታደሮች በየቤቱና በየቡና ቤቱ እየገቡ ሲፈትሹ እኛንም ከተደበቅንበት እየጎተቱ አወጡን። ወታደሮቹ ትናንሾቹን ወደ ቤታችን እንድንሄድ ሲለቁን ትላልቆቹን ግን እየደበደቡ፣ እየገፈተሩና እየጎተቱ መኪና ላይ ጭነው ወደእስር ቤት ወሰዷቸው።

"ለምንድነው ተማሪዎች የረበሹት?" የሚለው ጥያቄ የዚያን ሰሞን የመወያያ ጥያቄ ሆኖ ሰነበተ።

"ዩኒቨርሲቲ ተረብሾ ተማሪ በሙሉ ትምህርት እንዲያቆም ስለተወሰነ ነው" አለ አንዱ ከሌላ ቦታ ወሬ የሚያገኝ ጓደኛችን።

“ለምንድነው ትምህርት እንዲቆም የተወሰነው?” የሌሎቻችን ጥያቄ ነበር።

“የኃይለ ሥላሴ መንግሥት አድሀሪ የፊውዳል መንግሥት ስለሆነ መቀየር አለበት ብለው ነው” አለ አንደኛው ጓደኛችን።

ሌላኛው ደግሞ “መሬት ለአራሹ መሰጠት አለበት ብለው ነው” አለ ቀጠል በማድረግ።

እኔ የገበሬ ልጅ ስለሆንኩ ከልጅነቴ ጀምሮ የማየውን ችግር ከተማሪዎቹ ረብሻ እና ከውይይታችን ጋር ለማዛመድ ሞከርኩ። ጭልጭል የሚሉ እውነቶች እየታዩኝ መጡ። ልጅ ሆኜ ከአባቴ ጋር ወደ እርሻ በምንሄድበት ጊዜ ያጋጠመን ነገር ትዝ አለኝ። አንድ ቀን ወደ እርሻ ለመሄድ ከሰፈራችን ወጣ እንዳልን ሰዎች ሲደባደቡ አየሁና “ለምንድነው የሚደባደቡት?” ብዬ አባቴን ጠየቅሁት።

“በመሬት ተጣልተው ነው።” አለኝ አባቴ።

“ለምንድነው በመሬት የሚጣሉት?” ጥያቄዬን አከታተልኩ።

“አንዱ በባለቤትነት የያዘውን መሬት ሌላው የኔ ነው ይላል፤ ኃይለኛው ከደሀው መንጠቅ ይፈልጋል። ርስት ሁልጊዜ የኃይለኛ መሬት ነው። ርስትን ኃያል ብቻ ነው የራሱ አድርጎ የሚያርሰው። እነዚህ ሲያለቅሱ የምታያቸው መሬታቸውን ኃይለኛው በጉልበቱ ነጥቋቸው ነው” አለኝ። ይሄን ከሰማሁ በኋላ እኛም ቤት መጥተው መሬታችንን ቢነጥቁን ምን ልናደርግ እንደምንችል እያሰብኩ በጣም ይጨንቀኝ ነበር።

እውነትም በአደግኩበት አካባቢ አንዳንዱ ሰፋፊ መሬት ይዟል። አንዳንዱ ደግሞ ያለው መሬት ትንሽ ነው፣ ያም ደግሞ ምርት በደንብ የማይሰጥ ሊሆን ይችላል። ታዲያ በዚህ ችግር ውስጥ ያሉ በርካታ ገበሬዎች ለሦስትና ለአራት ወራት ስደት መሄዳቸው የተለመደ ነበር። አንዳንዶቹ ከሄዱበት ሳይመለሱ በዛው ይቀሩና ለዓመታት ይጠፋሉ። እነዚያ ሰፋፊና ለም መሬት የያዙት ደግሞ ቤታቸው ሙሉ ነው። የተትረፈረፈ ንብረት ያላቸው ናቸው።





ስለዚህ አንዱ ሲተርፈው ሌላው ቤተሰቡን መመገብ አቅቶት ሲሰደድ ሳይ፣ “መሬት ለምን ለሁሉምእኩል አይካፈልም?” ብዬ ግራ ይገባኝ ነበር።

የማይረሳኝ ሌላም አንድ አጋጣሚ አለ። አባቴ ከመሬት ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤት ክስ ነበረው። በዚህ ክስ ምክንያት አዲግራት መጥቶ ተያይዘን ወደ አንድ ቤት ሄድንና በጓሮ በኩል አንኳኩቶ ለቤቱ ባለቤት ገንዘብ ሰጠው። ድርጊቱ ግራ አጋባኝ። “ለምንድነው ለዚህ ሰውዬ ገንዘብ የሰጠኸው?” ብዬ ጠየኩት አባቴን።

“ዳኛ ስለሆነ፣ እኔ የምፈልገውን እንዲያደርግልኝ ነው” አለኝ። ግራ በመጋባት አባቴን ዐይን ዐይኑን አየሁት፤ “እዚህ ሀገር ለዳኛ ገንዘብ ካልሰጠህ ምንም ነገር ማግኘት አትችልም፣ ስለዚህ ሁላችንም ጉቦ እየሰጠን ነው የምንኖረው” አለኝ አባቴ ጉዳዩ እንዲገባኝ።

“ሁሉም ሰው ጉቦ የሚሰጥ ከሆን ዳኛው ለየትኛው ያግዛል?” አልኩት።

“የሚፈርደውማ የበለጠ ገንዘብ ለሰጠው ነው” አለኝና “አየህ፣ የምሰጠው ወድጄ እንዳይመስልህ ይፈርድብኝና ያለኝን አጣለሁ ብዬ ከመፍራት ነው እንጂ ለእርሱ የምሰጠውን ገንዘብ ለአንተ ልብስ መግዣ ባደርገው በጣም ደስ ይለኝ ነበር። እንዲህ ካላደረግሁ ግን መሬቴን እነጠቅና የጠላት መጫወቻ እሆናለሁ” ብሎ አስረዳኝ። ከዚያ በኋላ ለረዥም ጊዜ ያንን ዳኛ እንደደመኛ ጠላቴ ቆጥሬው ባየሁት ቁጥር ውስጤ ይቆጣ ነበር። ስለዚህ የመሬት ችግር፣ የጉቦኝነትና የዳኝነት ማጣት ችግር እንዲሁም አስተዳዳሪዎች ሕዝቡ ላይ የሚያደርሱትን ስቃይ ስመለከት “ለምን?” የሚል ጥያቄ ከአእምሮዬ አልወጣ እያለ ከአቅሜ በላይ አስብ ነበር።

ቀስ በቀስ የተነሣው የፖለቲካ ጥያቄ ምንጩ እየታየኝ መጣ። እነዚያ በክረምቱ ወራት ከዩኒቨርሲቲና ከየኮሌጆቹ ለዕረፍት የሚመጡ ወጣቶች ደግሞ

መንግሥት መለወጥ እንዳለበት፣ መሬት ለአራሹ መሆን እንደሚገባው፣ ጉቦኝነትን ማስቀረት እንደሚያስፈለግ ሲያስረዱኝ ነገሩ የበለጠ ተገለጸልኝ። ወታደሮች እየተኮሱባቸው ሳይፈሩ የሚሰለፉት፣ ድንጋይ እየወረወሩ እየጮሁ የሚፎክሩት ተማሪዎች፣ የእኔን መሰል ቤተሰቦች ችግርና ብሶት ተሰምቷቸው መሆኑን ስረዳ ማድነቅ ጀመርኩ። እኔም እንደነሱ ለሕዝብ ጥያቄ የመታገል ስሜት አደረብኝ።

በዚያን ጊዜ ከሚነሡ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ የብሔር ጥያቄ ነበር።

የስምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ነበር፣ መምህር ሞገስ የሚባሉ የአማርኛ መምህራችን እያስተማሩን ሳሉ "መምህር ሞገስ፣ ለምንድ ነው ሰዋሰው የምናጠናው?" ብዬ ጠየኳቸው። መምህር ሞገስ ከት ብለው ሳቁ። "ሰዋሰው ማለት አማርኛ ማለት አይደለም እንዴ? ወይስ በአጠያየቄ ምን የተሳሳትኩት ነገር አለ?" ብዬ ደነገጥኩ። መምህር ሞገስ ግን ሳቃቸውን ሲጨርሱ "ዩኒቨርስቲ ለማለፍ ከፈለጋችሁ አማርኛ በደንብ ማወቅ አለባችሁ። አማርኛ ካላለፋችሁ ዩኒቨርስቲ ለመግባት አትችሉም።" አሉና ትንሽ ካመነቱ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል "የአማርኛ ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ነው። ቋንቋው ደግሞ ለሁላችሁም የኢትዮጵያ ተማሪዎች እኩል እንዳልሆነ ይታወቃል። አማርኛ ከወደቃችሁ ግን ሌሎቹን ትምህርቶች ብታልፉ እንኳ ዩኒቨርስቲ ለመግባት አትችሉም። አማርኛ የግድ መታለፍ አለባቸው ከሚባሉ ጥቂት ዋና ዋና የትምህርት ዓይነቶች አንዱ ሆኖ ስለተመደበ ነው። ይህ ደግሞ ትምህርት ሚንስቴር ያስቀመጠው ህግ ነው" አሉ፤ አሁንም ከፊታቸው ላይ ሳቃቸው እየታየ። አማርኛ በደንብ ካላወቁ ዩኒቨርስቲ አለመግባት ማለትና ለመውደቅ ምክንያት መሆኑ እንዳልገባኝና ግር መሰኘቴ የገባቸው ይመስለኛል። ሆኖም ሌላ ተጨማሪ ነገር አልተናገሩም። አሳሳቃቸው አንድ የተደበቀ ትርጉም እንዳለው ቢሰማኝም በወቅቱ ግን ዋና መልእክቱን ለማግኘት አልቻልኩም ነበር። በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ መካከል





ተወልደው፣ በአማርኛ አፋቸውን ፈትተው፣ አማርኛ እየተናገሩ ካደጉ ተማሪዎች ጋር እኛን ማወዳደር ምን ማለት ነው? እኛን፣ በአማርኛ ተናጋሪዎች መካከል ተወልደን ያላደግን ሰዎችን እኩል ማወዳደርና በውድድሩ ከተሸነፋችሁ ትወድቃላችሁ፣ ዩኒቨርሲቲም መግባት አትችሉም ማለትስ የቱን ያህል ትክክል ነው?... የሚሉ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ውስጥ ሲጉላሉ ቢቆዩም ፍትሐዊ እንዳልነበረ በትክክል የተረዳሁት ውዬ አድሬ ነው።

ከሌሎች ትምህርቶች የበለጠ አማርኛ እንድናጠና አስተማሪዎቻችንና ታላላቆቻችን ያስጠነቅቁን ስለነበረ ነው ጥያቄውን ያነሣሁት። ያኔ ምንም እንኳ አግባብነቱ ባይታወቀኝም፣ ከሌሎች ትምህርቶች በተለየ ለአማርኛ ብዙ ጊዜ ሰጥቼ ለማጥናት ተገደድጃለሁ። ዩኒቨርስቲ መግባት ካለብኝ አማርኛን የበለጠ ማወቅ ነበረብኝና ከሌሎች ትምህርቶች የበለጠ አማርኛ ማጥናት ያስፈልገኝ ነበር። "ብዙዎቹ አማርኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ የማይገቡት በአማርኛ ፈተና ስለሚወድቁ ነው" እየተባለ ይወራ እንደነበረ የተረዳሁት በኋላ ነው። አስተማሪዬ ከት ብለው የሳቁት፣ ጥያቄዬ ፖለቲካ ነክ ስለሆነና ምናልባትም እንደ መንግሥት ተቃዋሚ የሚያስቆጥር በመሆኑ ነው። መምህር ሞገስን ከብዙ ጊዜ በኋላ ሜዳ አግኝቼያቸዋለሁ። በኢሕአፓ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ታጋይ ነበሩ።

***

## የትግል ሕይወቴ ጅማሬ

*ሁለቱ መንገዶች*

ሁለት መንገዶች አሉ ወደ ጫካው የሚወስዱ
የተሄደበት ነው አንዱ
ያልተሄደበት ነው ሌላው ::
ያልተሄደበትን መረጥኩ
ብዙ እግር ያልረገጠውን::
የዓለምን መልክ የለወጠው
ያልተሄደበት መንገድ ነው!
ይሄኛው መንገድ ብቻ ነው! -

(ሮበርት ፍሮስት - The Road Less travelled}
ትርጉም ነቢይ መኮንን)

በ1967ዓ.ም ጥር ወር ላይ አዲስ ታጣቂ ድርጅት የመፈጠሩ ወሬ መናፈስ ጀመረ። "'ዓባይ ኢትዮጵያ' የሚባሉ ከውጪ ሀገር ተምረው ኢትዮጵያን ነጻ ለማውጣት የሚፈልጉ ሰዎች አዲ ኢሮብ መጥተው አሲምባ የሚባል ቦታ ሰፍረዋል" እየተባለ በሰፊው ይወራ ጀመር። እስከዚያን ጊዜ ድረስ የኤርትራ ድርጅት እንጂ "የኢትዮጵያ" የሚባል ሌላ ተቃዋሚ ድርጅት መኖሩን ሰምቼ አላውቅም። ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተነሣ የመንግስት ተቃዋሚ ድርጅት መቋቋሙን የሰማሁት በ1967 ዓ.ም መጨረሻ ሲሆን እንቅስቃሴ ከጀመረ ስድስት





ወራት እካባቢ እንደሆነው አወቅሁ፤ ይህ ድርጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት ነበር።

ከዚያ በኋላ ደግሞ "ግንባር ትግል ትግራይ" የሚባል የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት መኖሩንና በጀብሀ ስር ሆኖ ትግራይን ነጻ ለማውጣት በምባሶይራ አካባቢ እንደሚታገል ይወራ ጀመረ። የኢትዮጵያ ነፃ አውጪ ድርጅት ለሚባሉት "ዓባይ ኢትዮጵያ" የሚል ስም የሰጧቸው የኤርትራ ድርጅቶችና "ግንባር ትግል ትግራይ" ተብሎ ሲጠራ የነበረው ድርጅት ነው ይባል ነበር። ምክንያቱም "ታላቋን ኢትዮጵያ ለመመሥረት የሚፈልጉ ትምክህተኞች ናቸው" በሚል እምነት ሲሆን ነቀፌታቸውን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ስያሜ እንደነበረ ይታመናል። እኔና መሰል ወጣቶች ግን "የተማሩ ሰዎችና ከኢትዮጵያ ውጪ ሄደው ሠልጥነው የመጡ ናቸው..." መባሉ ከአሉታዊ ይልቅ አዎንታዊ ስሜት ስለፈጠረብን ልባችን ወደ ኢሕአፓ ያመዝን ነበር።

እኔና ታደሰ አጽብሐ የሚባል ጓደኛዬ ወደ ኢሕአፓ ለመሄድ በአደረብን ፍላጎት ጥናት ማድረግ ጀመርን። የሚገኙበትን ትክክለኛ ቦታ፣ እዚያ ለመድረስ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ፣ ብናገኛቸው ሊቀበሉን መቻላቸውንና አለመቻላቸውን... የመሳሰሉ አንዳንድ መረጃዎችን ካገኘን በኋላ ወደአሉበት ቦታ ለመሄድ ተስማማን።

መስከረም 27 ቀን 1968 ዓ.ም እኔና ታደሰ አጽብሐ በድቅድቁ ጨለማ ከዛላ አንበሳ ተነስተን፣ ኢሕአፓዎች ይገኙበታል ወደ ተባለው ወደ መነኩሲቶ አቅጣጫ መንገድ ጀመርን። ስንሄድ አድረን ረፋድ ላይ መነኩሲቶ ደረስን። መነኩሲቶ እንደደረስን ፍሰሐ ካሕሳይ የሚባል ቀደም ሲል አዲግራት ትምህርት ቤት የምናውቀው የአዲ ኢሮብ ልጅ አገኘን። ከሰላምታ በኋላም "ወዴት ነው የምትሄዱት?" ብሎ ጠየቀን ፍሰሐ። 'ዓባይ ኢትዮጵያ' የሚባሉት የኢትዮጵያ ነፃ አውጪ ድርጅት ሰዎች እዚያ አካባቢ መኖራቸውን ሰምተን ወደ እነርሱ ልንሄድ መሆኑን ነገርነው።

ፍሱሕ በጉዳዩ ላይ ጥቂት እንድንወያይበት ሐሳብ አቀረበልንና ተስማማን። ከመንገድ ትንሽ ወጣ ብለን ተቀመጥንና መነጋገር ጀመርን። "ለምንድነው የምትሄዱት? ወደእነርሱስ ለመሄድ ለምን መረጣችሁ?" አለን ፍሱሕ ጥቂት እንደማሰብ ብሎ። ያገኘነውን መረጃና የነበረችንን ትንሽ የፖለቲካ ዕውቀት ጠቅሰን ለመታገል ያለንን ስሜት ነገርነው። ምክንያቶቻችንን ካዳመጠን በኋላ በሐሳባችን ላይ መስማማቱን ገልጾልን የሚረዳን መሆኑን ነገረን። "እምነታችሁንና ሐሳባችሁን የማትቀይሩ ከሆነ እኔ አደርሳችኋለሁ" አለን ፍሱሕ በእርግጠኝነት። ባንነጋገርም ሁለታችንም ልናምነው አልቻልንም። ገጽታችን ጥርጣሬያችንን ይገልጽ ነበርና ሊያሳምነን ሞከረ። በጽሞናም ተነጋገርን። በመጨረሻም "አይዟችሁ ያሉበትን ቦታ አውቀዋለሁ። እኔም የእነርሱ አባል ነኝ" ሲለን በደስታ ተቀበልነው።

ፍሱሕ ካሕሳይ አዎ ወደምትባል ቦታ ወሰደን። አዎ ስንደርስ ንጉሤ ከሚባል ሰው ጋር አስተዋወቀን። (ንጉሤ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ የታወቀ ሽፍታ እንደነበረ ወሬውን ስንሰማ የነበረ ሰው ነው።) ንጉሤ በዕድሜው ወጣት ነበር፤ ጸጉሩ አጠር ያለ አፍሮ ሲሆን ቅቤ ተቀብቶታል። ፍሱሕና ንጉሤ ከእኛ ገንጠል ብለው በሳሆ ቋንቋ ተነጋገሩ። ጥቂት ቆይተው ወደእኛ ተመለሱና ለንጉሤ ወደ ኢሕአፓ እንዲያደርሰን አደራ ሰጥቶን ፍሱሕ ወደ መነኩሲቶ ተመለሰ።

ከንጉሤ ጋር ስንጓዝ ውለን አመሻሽ ላይ ከአዎ በስተደቡብ የምትገኝ አንዲት መንደር ደርሰን ንጉሤ ወደ አንድ ቤት ወሰደንና አዳራችንን እዚያ አደረግን። በጣም ደክሞን ስለነበረ ገና ዐረፍ ስል ነበር እንቅልፍ የወሰደኝ። የተኛነው መሬት ላይ ቢሆንም ቁርቋሬው አልተሰማኝም፤ ከጎን ጎኔ መገላበጤን እንኳ ሳላውቀው ነበር ሌሊቱ አልፎ ንጋት የሆነው። ከእንቅልፌ ስነቃ ከሴትዮዋ በስተቀር ሌላ ሰው በቤት ውስጥ አልነበረም። ከመኝታዬ ተነሥቼ ወደ ደጅ ስወጣ ታደሰና ንጉሤ ቀድመውኝ ተነሥተው እውጭ ነበሩ። አካባቢውን ቃኘሁት፤ በቁጥቋጦ የተሸፈነ ተራራ ከፊት ለፊቴ ተመለከትኩ፤ የአሲምባ ተራራ ነበረ። የአሲምባን ተራራ ለመጀሪያ ጊዜ





እየሁት። ያደርንበትን ቤትና የአሲምባን ተራራ የሚለያቸው ትልቅ ሸለቆ ከፊታችን ይገኛል።

ሴትዮዋ በጠዋት ተነሥተው ገንፎ ሠርተው ኖሮ ቤት ገብተን ቁርስ እንድንበላ ነገሩን። ከሴትዮዋ ገጽታ ላይና ከድምፃቸውም ውስጥ ሀዘኔታ ጎልቶ ይሰማል። በቃላት የገለጹት ነገር ባይኖርም ወዴት እንደምንሄድ የተረዱና የዕድሜያችን ለጋነት ያባባቸው መሆኑ ያስታውቃል። ገንፎውን ጥርግ አድርገን በላነው፤ እጅግ በጣም ጣፋጭ ገንፎ ነበረ። ሴትዮዋን አመስግነን ተሰናበትናቸውና እንደገና መንገድ ጀመርን። መሪያችን ንጉሤ በመንገድ የሚያገኛቸውን የሀገሩን ሰዎች እያጠያየቀ፣ ኢሕአፓዎች ማእቢኖን የሚባል አካባቢ መሆናቸውን በመስማቱ ወደ እዛው አቀናን። ማእቢኖን ስንደርስ ደግሞ ጋራቢኖ የሚባል ቦታ እንዳሉ ስለተነገረው ወደዚያ ይዞን ሄደ።

ከዛላ አንበሳ ከተነሣን ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ ጋራቢኖ ስንደርስ ጊዜው ከእኩለ ቀን አልፎ ነበር። ጋራቢኖ፣ ከአሲምባ በስተምዕራብ ወደ አዲግራት በሚወስደው መንገድ ላይ የምትገኝ መንደር ነች። ንጉሤ እንድንጠብቀው ነገረንና ብቻውን ሄዶ ጥቂት ቆይቶ ተመለሰ። ሲመለስ አንድ ሰው አብሮት ነበረ። ንጉሤ አብሮት ከመጣው ከግደይ ጋር አስተዋወቀን (የግደይ ትክክለኛ ስም ተፈሪ ብርሃኔ ነው)። "እንኳን ደኅና መጣችሁ" አለን ግደይ። አነጋገሩ ለዛና ጣዕም ያለው፣ የተረጋጋና በሳል፤ እንዲሁም የማስረዳት ችሎታ ያለው ሰው ነበር። ያነጋገረን በትግርኛ ቋንቋ ሲሆን ስለ ኢሕአፓና ስለሠራዊቱ እንዲሁም ስለትግሉ በዝርዝር አስረዳን።

ከግደይ ጋር ያደረግነው ውይይት አስደስቶኛል፤ ፍላጎቴን ለመግለጽም ቸኩያለሁ። የመጣነው ድርጅቱን ለመቀላቀል መሆኑን ነገርኩት። ግደይ ጥቂት አሰብ አደረገና "ጥሩ! ሐሳባችሁ ይኼ ከሆነ እንቀበላችኋለን፤ ውሳኔያችሁ ግን

የመጨረሻ መሆን ይኖርበታል።" አለን ዐይን ዐይናችንን እየተመለከተና መልሳችንን እየጠበቀ። ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ተውጠን ቆየን። ዝምታችንን ሲመለከት "ያልወሰናችሁ ከሆነ ደግሞ በእርግጠኝነት ስትወስኑ በሌላ ጊዜ መምጣት ትችላላችሁ" አለን።

"እኔ በበኩሌ ከናንተ ጋር ለመሆን ወስኛለሁና ወደኋላ አልመለስም" አልኩ የታደሰ ሁኔታ አጠራጥሮኝ።

ታደሰ አጽብሐ ልቡ ያመነታበት ይመስላል። "እይ እኔ ትንሽ ልቆይ። ጊዜ ስጡኝና ተመልሼ ብመጣ ይሻለኛል" አለ።

የታደሰ መልስ በግደይ ስሜት ላይ ሊፈጥር የሚችለው ለውጥ አሳስቦኝ ነበረ። በግደይ ገጽታ ላይ ግን ምንም የቅሬታ መንፈስ አልነበረም። ገረመኝ። ይልቁንም በማበረታታት ዓይነት "ጥሩ! አንተ ካልወሰንክ ምንም ችግር የለውም። ያመጣህ ሰው መልሶ ይወስድሀል። በአደራ ይዞህ እንደመጣ ሁሉ፣ በአደራ ወደነበርክበት ቦታ እንዲመልስህ ስለምንነግረው ያለ ችግር በሰላም ትገባለህ" አለው። ከጓደኛዬ ከታደሰ ጋር በመተቃቀፍ ተሰነባበትን፤ እርሱ ከንጉሤ ጋር ሲመለስ እኔ ደግሞ ከኢሕአፓ ጋር ልቀላቀል ጉዞዬን ከግደይ ጋር ቀጠልኩ።

***





ከግደይ ጋር እየተጨዋወትን ጥቂት እንደሄድን እርምጃውን ቀነስ አደረገና "ስምህ ማነው?" ብሎ ጠየቀኝ። ስንተዋወቅ የነገርኩትን ስም የዘነጋው መሰለኝ። "ካሕሳይ አብርሃ" ብዬ መለስኩለት።

"ከእንግዲህ በኋላ ግን ስምህ ካሕሳይ አይሆንም፤ የምትፈልገውን ሌላ ስም መርጠህ ትሰጠኛለህ። ከዛሬ ጀምሮ መጠሪያህ አዲስ የምታወጣው ስም ይሆናል፤ እውነተኛ ስምህን ለማንም መንገር የለብህም፤ ምስጢር መሆን አለበት። ሁላችንም እዚህ ያለነው የምንታወቀው በሌላ ስም ነው። ስለዚህ ከጓዶች ጋር የማስተዋውቅህ በአዲሱ ስምህ ይሆናል" አለኝ ግደይ።

ግራ ቢገባኝም የድርጅቱ ሕግ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ "አማኑኤል ይሁን" አልኩት በቀላሉ።

"መልካም ከአሁን በኋላ ስምህ አማኑኤል ነው" አለና ጥቂት ቆይቶ፤ "ድንገት የሚያውቅህ ሰው አግኝተህ ካሕሳይ ብሎ ቢጠራህ እንኳ "አቤት" ማለት የለብህም። 'ካሕሳይ ነህ' ብትባልም "አይደለሁም" ማለት ይኖርብሃል" አለኝ። አነጋገሩ ጥቂት ቢጠነክርብኝም ተቀበልኩት።

ትንሽ እንደሄድን አንድ ቤት ውስጥ ገባን። ግደይ በቤቱ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ጋር አስተዋወቀኝ። "አዲስ አባል ነው፤ ስሙ አማኑኤል ይባላል" በማለት ለሰዎቹ ነገራቸው። ሁሉንም ጨበጥኳቸው። በዚያን ጊዜ ከተዋወቅኳቸው መካከል ግደይ (ተፈሪ ብርሃኔ)፣ ሮብሌ፣ ጂግሳና ሓዋዝ (ውብሸት ረታ) ከራሽያ፤ ኃይሌ ቀጭኑ፣ ዘለአለም (ዘርአብሩክ አበበ) እና ፀሐዬ ከአሜሪካን፤ ጌራ ደግሞ ከአራት ጓደኞቹ ጋር ሱማሌ ውስጥ በእስር ላይ የቆየ፤ እንዲሁም አምሀ (አምሀ የሜዳ ስሙ ሲሆን በቅጽል ስሙ ጸጋዬ ደብተራው፣ እውነተኛ ስሙ ደግሞ ጸጋዬ ገብረመድኅን ይባላል) ከአዲስ አበባ ቢፓርቲው የተላከ፤ ሙሉ ብርሃን፣ ስብሐቱ፣ ሙሴ፣ ደበሳይና ኮመኒት ደግሞ ከአዲአሮብ የመጡ የአርሶ አደር ልጆች ነበሩ። ጋራቢኖ ያገኘኋቸው ሰዎች በድርጅቱ ውስጥ ምን ቦታ እንደነበራቸው ባላውቅም

ስተዋወቃቸው የተለየ ስሜት ተፈጥሮብኛል፤ ለሁሉም ትልቅ አክብሮት እንድሰጥ ያደረገኝ ስሜት!

ጸጋዬ ደብተራው ...

"ቀን በቀን ቁማር ተጫውቼ

ተበልቼ ገባሁ ተረትቼ፤

ምንኛ ዕድሌ በሰመረ

ዘውዱን ገልብጬ በነበረ።"

በሚለው ቅኔው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ይታወቃል።

በቦታው ያልነበሩት ብርሃነ መስቀልና እስክንድር እኔ ከመግባቴ ከጥቂት ወራት በፊት ለፓርቲው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ሄደው የነበረ ሲሆን ብርሃነ መስቀልን ከዚያ በኋላም አላገኘሁትም። ከእስክንድር ጋር ግን ጎንደር ላይ ተገናኝተናል። ስድስት የሚሆኑ አባላትም እኔ ከመድረሴ ቀድም ብለው በሐሳብ ልዩነት የተነሣ ወደ ደርግ መግባታቸውን ሰምቻለሁ። ሮብሌ እኔ ከገባሁ ከአንድ ወር በኋላ ወደውጪ ተላከ። ኮመኒት ከወራት በኋላ ከሠራዊቱ ለቅቆ ወደ ቤተሰቦቹ የተቀላቀለ ሲሆን ደበሳይ እስከመጨረሻው ከእኛ ጋር ዘልቋል።

ከትውውቁ በኋላ ምግብ ቀረበልኝ። የገበሬ ልጅ በመሆኔ የምግቡ ዓይነትም ሆነ አቀራረቡ የፈጠረብኝ ስሜት አልነበረም። ለእኔ ያንን ቡድን መቀላቀል የፈጠረብኝ ስሜት ከምንም በላይ ነበር፤ ኢትዮጵያን ለመታደግ ከቆመ ድርጅት ጋር መሰለፌ የፈጠረብኝ መንፈሳዊ ኩራት አጥለቅልቆኛል። ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር መሆኔን ለአፍታ እንኳ አላሰብኩትም፤ ለደስታዬም ወሰን አልነበረውም።

ያን ዕለት ከእኔ በኋላ ሁለት ቡድኖች ወደ ሥፍራው መጡ። የመጀመሪያው ቡድን ሀረጎት (ሀረጎት የአዲግራት ዘመቻ ጣቢያ አዝማች የነበረ መምህር ነበር)፣ አረጋይና ሓርነት የነበሩበት ነው። ቀጥሎ ደግሞ ሌሎች ከወሎ





የመጡ ሰዎች (የእነሺፈራው ቡድን) ደረሱና ቁጥራችንን ከፍ አደረጉት። እነርሱም ሺፈራው፣ ግርማይ፣ ወርቁ፣ አለሙና አሊጋዝ ነበሩ። ማታውኑ ወደ አዎ ለመሄድ ተነሣን፤ ምናልባትም እዚያ ቦታ የመጡት እነዚያን ቡድኖች ለመቀበል ይሆናል ብዬ አሰብኩና በዚህ አጋጣሚ እኔም እዚያ በመድረሴ ዕድለኛነት ተሰማኝ።

***

ጋራቢኖ አዲስ ለደረስነው እንግዶች ማር ቀረበልን። ኩሽክ የሚባል አንሶላ መሰል አቡጀዲ ጨርቅ ተሰጠን። ኩሽክ በርካታ አገልግሎት ያለው ጨርቅ ነው፤ ለፀሐይና ለብርድ መከላከያ፣ ለመኝታ፣ ለቁስል ማሰሪያ... ሲሞቱ ለከፈን ጨርቅነትም የሚውል እያንዳንዱ አባል ከአጠገቡ የማይለየው ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። ከሠራዊቱ ጋር ያሳለፍኩት የመጀመሪያው ሌሊት ቢጋራቢኖና በአዎ መካከል ነበረ። አካበቢው ተራራማ ሲሆን ያደርንበት ቤት በተራራው ወገብ ላይ ሆኖ በቁጥቋጦ የተሸፈነ ነው።'ለአዲሶቹ እንግዶች ለብቻችን ቤቱ ተለቀቀልንና ውስጥ አደርን። ነባር አባላቱ በሙሉ ያደሩት ውጭ ነበረ። በማግስቱ ጠዋት ወደ አዎ ተንቀሳቀስን፤ ጉዞው በሰልፍ ነበር። ለጥበቃ እንዲያመች መሣሪያ የያዙ ጓዶች ከፊትና ከኋላ በመሆን ሌሎቻችንን በመካከል አድርገውን ወደሰሜን፣ ወደ አዎ ጉዞ ሆነ። አዎ እንደደረስን ከውቅሮ፣ ከሁለት አውላሎና ከአካብባው አዲስ ሰዎች መጡ። እነሱም የአቢኢዮ፣ ነመራ፣ በርሄ (ሐጎስ በዛብህ)፣ ጀማል፣ አታክልቲ፣ ጸጋዬ (ሁለተኛው ጸጋዬ ማለት ነው)፣ ዘሚካኤልና ዳኔል (ፀጋይ ኪዳነ) ነበሩ።

ጸጋዬ አብርሃ ከእነየአቢኢዮ ጋር የመጣ አዲስ አባል ነው። በመጡበት ዕለት አስደንጋጭ የሆነ የጤና ችግር አጋጠመው፤ በደኅና ከቆመበት በድንገት ወደቀና ደጋግፈን አነሣነው። ለመቆም ቢሞክርም አልቻለም፤ ሁላችንም ተደናግጠን የምናደርገውን አጣን። እየቆየ ሲሄድ ደግሞ ጭርሱን መተንፈስም እየከበደው ተቸገረ። የጸጋየ የመተንፈስ ችግር እየባሰበት እንጂ እየተሻለው ሊሄድ አልቻለም።

በገጠር ባህል መሠረት የመተንፈስ ችግር ሲያጋጥም ወናፍ መጠቀም የተለመደ ስለሆነ ከአካባቢው ገበሬዎች ተጠይቆ ሁለት ወናፎች ተገኙ። ሁለቱ ወናፎች ተራ በተራ እየተቀያየሩ በአፉ አየር ለማስገባት ሙከራ ተደረገ። ስቃዩ እየጨመረ መሄድ እንጅ የመሻል ምልክት ለማየት አልተቻለም። ጸጋየ በሕይወት መቆየት የቻለው ለሦስት ቀናት ብቻ ነበር። እንደማይተርፍ ሲታወቅ ምንም እንኳ





ጸጋየ ባይሰማንም እያንዳንዳችን ተሰናበትነው። ወዲያውኑ ዐረፈና በዚያኑ ዕለት ተቀበረ።

የጸጋዬ ሞት የጣለብን የሐዘን ስሜት ከፍተኛ ነበረ፤ የሁላችንም ስሜት በሐዘን ክፉኛ ተጎዳ። ሁሉ ሰው ግንባሩን ቋጥሮ በዝምታ ተዋጠ። ልባችንን የሰበረው ሕመሙ በመጣበት ቀን ስለጀመረውና ምንም ዓይነት ህክምና ልናገኝለት ሳንችል በመቅረታችን ነበር። የጸጋዬን ስቃይ ለመቀነስና ሕይወቱንም ለማትረፍ የምንችለውን ሁሉ አድርግናል። ሆኖም ባህላዊውን የትንፋሽ መስጫ አፉ ላይ ማቆየቱ ስቃዩን መጨመር እንጅ ሌላ ጥቅም እንዳልሰጠው በማየታችን ወናፉ ሲቋረጥ እንደሚሞት ብናውቅም ማቋረጥ ግድ ሆኖብናል። እናም በግድም ቢሆን የጸጋየን ህልፈተ ሕይወት መፍቀዳችን ሐዘናችንን ያከበደው ይመስለኛል። ጸጋዬ ለእኔ በትግሉ ጅማሮ ላይ የተሰዋ የመጀመሪያው ሰው ሆነ። የመጀመሪያው ቡድን ወደአሲምባ ሲገባ ብንያም አዳነና ማህፉዝ የተባሉ ጓዶች በጉዞ ላይ እንዳሉ በኤርትራ በረሐ ውስጥ መሞታቸውን የሰማሁት ከዚያ በኋላ ነው።

***

በቁጥር እየጨመርን በጠቅላላ ወደ ሠላሳ ደርሰናል። የትግል ጓድነት የቃለ መሀላ ሥነሥርዓት ለመፈጸም ታሰበና አንድ አጭር ዝግጅት ተደረገ። ኃይሌ ቀጭኑ የቃለ መሃላውን ጽሑፍ አዘጋጅቶ ሰጠን። የጽሑፉ ሐሳብ፡

"እኔ ለሀገሬና ለኢትዮጲያ ሕዝብ፤ እስከ መጨረሻው ለመሥዋዕትነት ተዘጋጅቼና በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ስር ሆኜ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ እስኪወጣ እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ፣ በትግል ጎዳና እጓዛለሁ" የሚል ነበር። ቃለ መሃላው የተፈጸመው ጺጋየ በወደቀባት ቦታ አዎ ላይ ነበር፤ እያንዳንዱ አባል ተነሥቶ በአባላቱ ፊት በወታደራዊ ሥነሥርዓት በመቆም ቃለ መሃላውን ያነብና ሰላምታ በማቅረብ ወደቦታው ይመለሳል። ይህንን ቃለ መሃላ በፈጸምንበት ሰዓት በልቦናዬ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውና ልገልጸው የሚቸግረኝ ልዩ ስሜት ከዚያ ወዲህ በምንም አጋጣሚ ትሰምቶኝ አያውቅም። ለሕዝብና ለሃገር የመቆም ልዩ ኩራት ነበረ።

ቃለ መሃላውን በፈጸምን በማግስቱ የፖለቲካ ትምህርት መከታተል ጀመርን። የፖለቲካ ትምህርቱ ሲጀመር የማስታወሻ ደብተርና እስክሪብቶ ተሰጠን። ወቅቱ የመስከረም ወር መገባደጃ ላይ ነበረ። የተቀመጥነው ለእይታ ምቹ ከነበረ ቦታ ላይ ሲሆን ወርሃ መስከረም ለአካባቢው ያላበሰው ውበት ስሜትን የሚነካና ልዩ ድባብ ነበረው። ሜዳውና ተራራው፣ የእርሻ ማሳውና ወጣ ገባው፣ ወንዙና ሸንተረሩ ሁሉ በአደይ አበባና በለምለም ዕፅዋት ተሸልሞ ደምቋል። ያን ጊዜ በአካባቢው የተመለከትኩት ኅብረ ቀለምና የገጠር ገጽታ የጣለብኝ ግርምት ከዓይነ ኅሊናየ የማይጠፉ ትውስታዬ ሆነ።

የፖለቲካ ትምህርቱ የተጀመረው ስለኅብረተሰብ እድገት በሚያስረዳ ርእስ ነበር። ኅብረተሰብ ከጋርዮሽ ስርዓተ ማኅበር የጀመረና፣ የባሪያ አገዛዝ፣ የፊውዳል ሥርአተ ማኅበር፣ የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ወዘተ… እያለ በደረጃና በቅደም ተከተል እያደገ የመጣ መሆኑን ተረዳን። ለአንዳንዶቻችን የፖለቲካ ትምህርቱ





ፅንሰ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማነው ስለነበረ፣ በከፍተኛ ስሜትና ትኩረት ተመስጠን እንከታተለው እንደነበር አይረሳኝም።

ከዚያም በሀገራችንና በአካባቢያችን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ያተኮረ መረጃ ተከተለ። ተጨባጭ ሁኔታዎችን በተመለከተ ደርግንና የብሔር ጥያቄን ጨምሮ በወቅቱ ኢትዮጵያ ስለነበረችበት ሁኔታ፣ ስለድርጅቱ እንቅስቃሴና አካሄድ እንዲሁም በአካባቢያችን ስላሉ ሌሎች የታጠቁ ድርጅቶች መምህራችን ሐዋዝ ጠቃቀሰልን። ግንባር ገድል ትግራይ የተባለው ድርጅት 'አባይ ኢትዮጵያ' ብሎ የሚጠራው ኢሕአፓ በዚያ አካባቢ መቆየቱ እንደማያስደስተው ሐዋዝ ሲነግረን አባባላቸውንም ገለጸልን።

"ይህ ቦታ የትግራይ እንጅ የኢትዮጵያ አይደለም፤ እኛ ደግሞ የትግራይ ሰዎችና የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ነን። ስለሆነም በእዚህ አካባቢ መንቀሳቀስ የምንችለው እኛ ብቻ ነን፤ እናንተ መንቀሳቀስ የምትችሉት ሌላ የኢትዮጵያ ክልል ሄዳችሁ መሆን ይኖርበታል" እንደሚልና ከዚህም አልፎ "ከመሬታችን ውጡልን አለያ ግን ግጭት ሊፈጠር ይችላል" የሚል ዛቻ እንደሚሰነዝርም አብራራልን።

በተጨማሪም በምዕራብ በኩል ሽሬ ላይ የተመሠረተ ተጋድሎ ሐርነት ሕዝብ ትግራይ(ተሐሕት) የሚባል ድርጅት (በኋላ ሕወሃት የተሰኘው) እንዳለና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት የመፍጠር ፍላጎት መኖሩ ተገለጸ። የእኛ ድርጅት አብሮ ለመሥራት ንግግር የጀመረ መሆኑንና ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ያለው ድርጅት እንደሚመስልም ሐዋዝ ነገረን። ይህም ያን ጊዜ ኢሕአሠ በትግራይ ውስጥ መንቀሳቀስ ሲጀምር በአካባቢው ሁለት የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅቶች እንደነበሩ ያስረዳል።

በቅርብ ርቀት ላይ ከሚንቀሳቀሰውና "አካባቢያችንን ልቀቁ" እያለ ከሚያስፈራራው ግንባር ገድል ትግራይ ከተባለው ድርጅት ጋር ግጭት የማንሣት

ፍላጎት አልነበረም፤ እናም ድንገት መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአካባቢው ቢታዩ ላለመታየት ጥረት ማድረግና ማሳለፍ እንደሚያስፈልግ ተነግሮናል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ሌሊት ብረት የያዙ ሰዎችን እያየን ሳያስተውሉን እንዲያልፉ እናደርግ ነበር። የሚተላለፉትን ሰዎች ማንነት ባናውቅም አንዳንድ የምናያቸው ታጣቂዎች ጥሩ ጥሩ መሣሪያ የያዙና ዩኒፎርም የለበሱ ነበሩ። (በዚያን ጊዜ የእኛ ሠራዊት የነበረው ትጥቅ የተወሰኑ ክላሽን ኮቭና ሁለት ናቶ ጠመንጃዎች ብቻ ናቸው።)

መጠነኛ የሆነ ወታደራዊ ሥልጠናም እንድንወስድ ተደረገ። ሥልጠናው የተካሄደው ሰንገዴ የሚባል ለወታደራዊ ሥልጠና ምቹ መሆኑ በተጠና ቦታ ነበረ። አዲስ ዛህላይ ሠራዊቱን በተቀላቀለ በማግስቱ ሮባን ለመጠበቅ ከሰንገዴ በስተምሥራቅ ወደምትገኝ ኢጋም የምትባል ቦታ ሄድን። ከዳያ በምሥራቅ አቅጣጫ አድርገን ኢጋም ገባን። ኢጋም ወደሁለት አቅጣጫ የሚወስዱ መንታ መንገዶች አሏት። አንደኛው መንገድ የሰሜንን አቅጣጫ በመያዝ ወደ ዓዲጋ እንዲሁም ተራራውን ተከትሎ አይጋ ከዚያም ወደ ወራትሌ ይወስዳል። ሁለተኛው ደግሞ ወደ ሰንገዴ ያወጣል። ከሰንገዴ ሰሜናዊ ምሥራቅ የሚገኘው ዓዲጋ የሠራዊቱ የጥገና ሥራዎች የሚከናወኑበት ቦታ ነበር። ዓዲጋ ላይ ሬዲዮኖች፣ ሰዓቶችና የጦር መሳሪያዎች የጠገናሉ። ቦታው ከፍ ያለ በመሆኑ ዋርዲያ የቆመ ሰው ዳያ፣ እንዲሁም ሰበያና አካባቢው በሙሉ ግልጽ ብሎ ይታየዋል።

ኢጋም በነበርንበት ዕለት ቀደም ሲል ሜዳ የነበሩ ጓዶች ሜዳ ከመውጣቴ በፊት በቅርብ የማውቀውን አንድ አባል በጥያቄ ሲያስጨንቁት አየሁ። አጠገቤ የነበሩትን ምን ችግር እንደተፈጠረ ጠየቅሁና በሰላይነት ተጠርጥሮ መሆኑ ተነገረኝ። በሁኔታው ግር መሰኘት ብቻ ሳይሆን ቅሬታም ስላደረብኝ ነገሩን እያብሰለሰልኩ የመከፋት ስሜት ተፈጥሮብኝ ነበር። መከፋቴ ፊቴ ላይ በግልጽ ተንጸባረቀ። በራሱ





ፈቃድ ለትግል የመጣን ሰው ማስጨነቅና ማዋከብ ትክክል ያለመሆኑን እያሰብኩ ተናደድኩ።

በውስጤ የማብሰለስለው ነገር ስሜቴን ስላስጨነቀው ሐረጎት ምን እንደተሰማው ጠየቅሁት።ሐረጎትም በሁኔታው ቅር መሰኘቱን ነገረኝ። ጓዱ በመጣበት ዕለት ያደረው ከእኛ ጋር ስለነበረ ብዙ ነገሮችን አንሥተን ስንጫወት አጠራጣሪ ነገር አላየንበትም። ሜዳ ከመውጣቴ በፊት ከእኔ ጋር በነበረን ትውውቅ የሚታመን ልጅ ለመሆኑ አልተጠራጠርኩም። እናም ጠርጥረው በጥያቄ ሲያስጨንቁት ማየቴ ስሜቴን ነክቶታል።

ተረኛ ዋርዲያ ሆኜ በጥበቃ ቦታዬ ላይ ተከዝ ቁጭ ብያለሁ። የዋርድያ ሥራ ቀንና ሌሊት ይካሄዳል፤ እያንዳንዳችን ለአንድ ሰዓት ያህል ጠብቀን እንቀየራለን። ከእኔ ቀጥሎ ዋርዲያ የሚተካው ጸጋዬ ደብተራው ነበረ። በወቅቱ ለሁላችንም የሚዳረስ ጠመንጃ ስላልነበረን ዋርዲያ የምንቆመው አንዱን መሣሪያ እየተቀባበልን ነበርና የያዝኩትን መሣሪያ አስረከብኩት። ጸጋዬ ደብተራው ከቀየረኝ በኋላ ግን ተመልሼ ከሌሎቹ ጋር ለመቀላቀል ስላልፈለግሁ ለብቻዬ ነጠል ብዬ ተቀመጥኩ።

ጸጋዬ ደብተራው፣ የዋርድያነት ሰዓቱን ሲጨርስ ወደእኔ መጣና "ምነው አማኑኤል? ከሌሎቹ ተለይትህ ለምን ብቻህን ሆንክ? ከእነርሱ ጋር መሆን ይሻላል" አለኝ።

ብቻዬን መሆን እንደምፈልግ ነገርኩትና ሄደ። በጣም ቅር እንዳለኝና እንደከፋኝ አውቋል። ጥቂት ቆይቶ ዘላለም መጣ፤ ጸጋየ ስለሁኔታዬ የነገረው ይመስለኛል "እዚህ ለብቻህ ምን ታደርጋለህ?" አለኝ ዘላለም።

"ዝም ብዬ ነው፣ ይህቺ ቦታ ደስ ትለኛለች፣ ደግሞም ትሞቃለች" አልኩት።

"እስቲ እንጸዳዳና እንመለስ" አለኝና አብሬው ሄድኩ። ስንመለስ ከኔ ጋር ቁጭ አለና ጨዋታ ጀመረ "የት ነው ያደግከው?" አለኝ።

"ዛላ አንበሳ ነው ያደግኩት" አልኩት።

"ዛላ አንበሳ እኮ ዘመዶች አሉኝ" አለ ዘላለም።

"አንተ አማራ አይደለህ እንዴ? እንዴት ዛላ አንበሳ ዘመድ ይኖርሀል?" አልኩት።

ሳቅ አለና "እውነቴን ነው፣ ዘመዶች አሉኝ" አለ።

"እኔ ዛላ አንበሳ ውስጥ ሁሉንም ሰው አውቃለሁ። የአንተ ዘመዶች እነማን ናቸው?" አልኩት በመገረም። የማውቃቸውን ሰው ጠርቶ እኅቱ መሆናቸውን ነገረኝ።

"እንዴ፣ አንተ የማን ልጅ ነህ? እንዴት እሳቸው ያንተ እኅት ሊሆኑ ይችላሉ?" አከታትየ ጠየቅሁት።

"አባቴና እሳቸው የወንድማማቾች ልጆች ናቸው" ካለ በኋላ "ግን ዝም በል፤ ለማንም እንዳትናገር" አለኝ።

"እንዴ! አንተ ከየት ነው የመጣኸው? የማን ልጅ ነህ ታዲያ?" በማለት በጥያቄ አጣደፍኩት። ስለቤተሰቦቹ ማንነት ነገረኝ።

ሜዳ በገባሁ በሁለተኛው ቀን ግደይ እንደገና ለብቻዬ ስለሕይወት ታሪኬ በዝርዝር ጠይቆኝ እያንዳንዱን መረጃ እንደሰጠሁት ትዝ አለኝ። እናም ከዚያ መረጃ ተነሥቶ ዘላለምን እንዲያናግረኝ የላከው ይመስለኛል። ጸጋዬ ደብተራው እንደተከዝኩ በማየቱ ከግደይ ጋር ተነጋግረዋል፤ ግደይ ደግሞ





ያንን የሰጠሁትን የሕይወት ታሪክ መሠረት አድርጎ ዘላለም እንዲያነጋግረኝ ልኮታል። በተፈጠረብኝ ቅሬታ እንዳልጠፋ ሰግተው መሆን አለበት ብዬ ገመትኩ።

ከዘላለም ጋር ስለዘመዶቻችን አወራንና በትዝታ ጭልጥ ብለን ሰመጥን። ጨዋታችን እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሁለታችንም ስሜት እየሳሳ በመጨረሻ እስከመላቀስ ደረስን። "ከአንግዲህ እንዳይከፋህ፤ እኔ ወንድምህ ነኝ፤ የሚያስጨንቅ ወይም የሚያሳዝን ነገር ከገጠመህ ለእኔ ንገረኝ። ዘመድህ መሆኔን ግን ለማንም ሰው እንዳትናገር" አለኝና ተሰናብቶኝ ሄደ። በጣም ደስ አለኝ። ያን ቀን ዘላለም ባያናግረኝ ኖሮ የእውነትም የመጥፋት ሐሳብ እየጀማመረኝ ነበር ።

እጋም ላይ ለአንድ ቀን አድረን ወደ አይጋ አቀናን። እነሮባም በዚያው ዕለት ነበር አይጋ የደረሱት። ከሮባ ጋር ሁለት የሻቢያ አባሎችም መጥተዋል። ሮባን ሁሉም ሰው በደስታና በእልልታ አጅቦ ሲቀበለው በማየቴ ተገርሜ ማንነቱን ለማወቅ ቸኩዬም ነበር። ሮባን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በዚያን ቀን ነው። እኔ ሠራዊቱን በተቀላቀልኩበት ቀን ወደ ኤርትራ ሄዶ ስለነበር አልተገናኘንም። "አባ ሮባ ይባላል! ጓዳችን ነው፤! አለቃችን ነው! ተዋወቁት" ተብለን ተዋወቅነው። ሮባ ተመልሶ የመጣው ከአሥራ አምስት ቀናት ቆይታ በኋላ ይመስለኛል።

ሮባ መልኩ ጥቁር፣ ቁመቱ አጠር ያለና ቀጭን ነው። ንቁና ቀልጣፋ ሲሆን የለበሰው ቁምጣና የያዘው ክላሽን ከጎፈሬው ጋር ተዳምረው ግርማ ሞገስ ሰጥተውታል። ከአዲሶቹ አባላት ጋር ሲተዋወቅ ደስተኛ ነበረ። ሲናገር ደስ ይላል፤ ቃላቱ የፍቅር ስሜት አላቸው። ዕድሜው ትልቅ አይመስልም፤ እናም አለቃ የሆነበት ልዩ ተሰጥኦ ሊኖረው እንደሚችል ገመትኩ። በኋላ ግን በ1961 ዓ.ም ከባሕር ዳር አውሮፕላን ጠልፈው ከወጡትና በኋላም አልጄርስ ከገቡት ሰባት ተማሪዎች አንዱ እንደነበረ ተረዳሁ።

ሮባ በባሕሪው ነገር ማካበድ የማይወድና ወደመፍትሔ ማተኮር የሚቀናው ሲሆን፣ በአመራር ፈጣን ውሳኔ መስጠት የሚችልና በውጊያም ወቅት ጨበጣ ለመግባት የሚሽቀዳደም ደፋር መሆኑን የተረዳሁት ሜዳ ከቆየሁ በኋላ ነበር። ሮባ የሠራዊቱንም ሆነ የግለሰቦችን ችግር ቶሎ የሚረዳ፣ ከፍተኛ የማዳመጥ ችሎታ ያለውና ሁሉንም ሰው በፍቅር ለማሸነፍ የሚችል ባሕርይ ያለው ስለሆነ በሠራዊቱ በጣም ተወዳጆች ከሚባሉት የአመራር አባላት ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። በተዋወቅንበት ዕለት ያሳየን የፍቅርና የጓድነት ስሜት የፈጠረልን ርካታና ደስተኝነት አሁን ድረስ ይታወሰኛል።

ሮባ ከመጣ በኋላ በሁለት ጋንታ ተከፈልን። የመጀመሪያዋ ጋንታ፣ መሪ ሮባ፣ ምክትል ግደይ፣ እንዲሁም የፖለቲካ አስተማሪ ሐዋዝ ነበሩ። የሁለተኛው ጋንታ መሪ ደግሞ ጅግሳ፣ ምክትል ሮብሌ ሲሆን የፖለቲካ አስተማሪው ዘላለም ሆነው ተመደቡ። የአጠቃላይ ሠራዊቱ መሪ ሮባ ምክትሉ ደግም ጂግሳ ነበሩ። ሌሎቻችን በሁለቱ ጋንታ ውስጥ ስንደለደል እኔ፣ ጅግሳና ሮብሌ በሚመሩት ቡድን ውስጥ ተመደብኩ። ያ በተጠርጣሪነት በጥያቄ ሲዋከብ የነበረው ልጅም እነሮባ በመጡ ጊዜ "ነጻ ነህ" ተባለ።

ለጉዞ እንድንዘጋጅ ተነገረን። ጉዞው ወደ መነኩሲቶ ሲሆን የሄድነው በአይጋ በኩል አድርገን ነበር። መነኩሲቶ ሼቃ ንጉሤ የተባሉ በጣም ረጋ ያሉና ንግግር አዋቂ የሆኑ ሰው ቤት ገባን። ሼቃ ንጉሤም ጥሩ ዝግጅት አድርገው ተቀበሉን። ሼቃ ንጉሴ የኢሕአሠ አባላት የነበሩት የጋይምና፣ የዳዊት ሰዩም የቅርብ ዘመድ ናቸው።

መነኩሲቶ የሄድንበት ምክንያት ሮባ ከሻቢያ ያመጣቸውን መሣሪያዎች ለመውሰድ ነበር። እንደደረስን የተወሰኑ ጠመንጃዎችና ጥይቶች ላልታጠቅነው አባላት ታደሉን። ስንመለስ ከለአሳ ከመግባታችን በፊት ከረዳ አጠገብ ከሚገኝ





ኪንኪታ የሚባል ቦታ በሌሊት ገባን። ሊነጋጋ ሲል የደርግ ሰላይ መሆኑ የተነገረንን ኃይሉ ካሕሳይ የሚባለውን ሰው ቤት ከበብነው። የተወሰኑ አባላት ወደ ቤቱ ገብተው ኃይሉን አስረው ይዘውት ወጡ። ኃይሉ ቁመቱ ከሁላችንም የሚበልጥ፣ በጣም ረዥምም ነበር። እጆቹን ታሰረና ወደየት አቅጣጫ እንደሚሄድ እንዳያውቅ ደግሞ ዓይኖቹን ተሸፍኖ ወደ ሰንገዴ ይዘነው ሄድን። ኃይሉ ካሕሳይ ሰንገዴ ከደረስን በኋላ ውሳኔ ተሰጥቶበት በሠራዊቱ የተገደለ የመጀመሪያው ሰው ሆነ።

***

### *ዓዲ ኢሮብ*

የአዲ አኢሮብ ሕዝብ የመቻቻል፣ የእንግዳ ተቀባይነት፣የሕዝብና የታጋይ አንድነት ፍቱን ዓርአያ ነው፡፡ አዲ ኢሮብ በትግራይ ክፍለ ሀገር ሰሜን ምሥራቅ፣ በኢጋሜ አውራጃ፣ አዲግራት ከተማ በሰተምሥራቅ የሚገኝ፣ በአብዛኛው ተራራማ የሆነ ወረዳ ነው። የአዲ ኢሮብን ወረዳ በሰተሰሜን ደብረ መላ፣ በስተምሥራቅ ሀዶ፣ በደቡብ ምሥራቅ በኩል አፋር፣ እንዲሁም በደቡብ ሳዕሴዕና ሱብሐ፣ በምዕራብ በኩል ደግሞ ጉሎ ማከዳና በኤርትራ ግዛት ውስጥ የሚገኘው የአካለ ጉዛይ ወረዳ ያዋስኑታል። ከትግራይም ይሁን ከወሎ በኩል ካለው ለቀይ ባሕር በጣም ቅርብ የሚባለው፣ በአዲ ኢሮብ ውስጥ የሚገኘው ሰንገዴ የሚባለው ቦታ ነው።

የአዲ ኢሮብ፣ የደብረ መላና የሀዶ ነዋሪዎች የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው። የአዲ ኢሮብ ማኅበረሰብ አባላት ከዘጠና በመቶ በላይ የክርስትና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ የደብረ መላና የሀዶ ነዋሪዎች ግን በአብዛኛው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የአፋር ብሔረሰብ አባላትም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ፣ የተቀሩት ደግሞ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችና የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የቋንቋ ልዩነት ቢኖርም የአዲ ኢሮብ ባህሎች በብዛት ከላይኛው የትግራይ ሕብረተሰብ ጋር ስለሚመሳሰሉ፣ እርስ በእርስ ለመግባባት አይቸገሩም።

የአካባቢው ሰዎች እንደሚሉት ኢሮብ የሚለው ቃል የመጣው ኢሮባ ከሚለው ሲሆን ይህም በሳሆ ቋንቋ ወደ ቤት ግባ ማለት ነው። ስለዚህ የማኅበረሰቡ ስያሜ ምንጭ፣ የኢሮብ ሕዝብ እንግዳ ተቀባይ "ኑ ግቡ! ብሉ ጠጡ!" የሚል ደግና የዋህ ሕብረተሰብ ከመሆኑ ጋር ተያያዘ ነው። የአዲ ኢሮብ ማኅበረሰብ አባላት መልእክት የሚለዋወጡበት የሚስጥር ቋንቋ አላቸው። ያንን መልእክት የምስጢር ቃሉን የሚያውቅ ሰው ብቻ እንጂ ሌላ





ሰው ሊረዳው አይችልም።

አዲ ኢሮቦች ወንዱንና ሴቱን እንዲሁም ሕፃናቱን የሚያሳትፍ ማኅበራዊ ኑሮ አላቸው። እንደደጋው ክርስቲያን አክራሪነት አይታይባቸውም። ትንንሽ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር አብረው ማዕድ ይቀርባሉ፤ በጨዋታ ጊዜም ተከባብረው ይሳተፋሉ። ባህላዊ ጨዋታቸው ወኔን የሚነካ ነው። ከበሮ አመታታቸው ከዜማው ጋር የተዋሐደ በመሆኑ በጣም ያስደስታል። ከስድስት እስከ ስምንት በሚሆኑ ሰዎች ከበሮ በሚመታበት አንድ ዘፈን ላይ የሁሉም ከበሮ እኩልና አንድ ሆኖ ሲሰማ በጣም ያስደንቃል። የዘፈናቸውን ግጥሞች ቋንቋውን መስማት ለማይችል ሰው እንኳ ከዜማው እንዲሁም በእነሱ ላይ ከሚታየው ስሜትና ወኔ በመገንዘብ እንዲረዳው የሚያደርግ ጥልቀት አለው።

ኢሮብ ልዩ ልዩ ዕፅዋትና አበቦች የሚገኙበት ለም ቦታ ነው። በተለይ ከሰንገዴ በሰተምሥራቅ ከእንደሌ በረሐ ወረድ ብሎ ያለው ቦታ በሁሉም የዓመቱ ወቅቶች ልምላሜ የማይለየው ነው። የኢሮብ ማርና ቅቤ ከኢትዮጵያ ምርጥ የሚባል ነው። ማሩ ቆንጆ ስለሆነ ጠጃቸውም ልዩ ነው። ኢሮቦች ገበያ ሲወጡ ለደጋው ሕዝብ ማር፣ ቂቤና ወተት ካቀረቡ በኋላ ለራሳቸው ደግሞ እህል ሸምተው ይመለሳሉ።

አዲ ኢሮብ የተለያዩ ሀገራዊና ታሪካዊ የሃይማኖት ቅርሶች ያሉት ወረዳ ነው። ጉንዳጉንዴ የሚባለው፣ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀደምትና ታሪካዊ ገዳም የሚገኘው በሳዕሲዕ ወረዳ፣ ከአሲምባ ተራራ በስተደቡብ በኩል ሲሆን፣ ገዳሙ ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸውና ጥንታዊ ቅርስ የሆኑ የግእዝ መጻሕፍት የሚገኙበት ዝነኛ ገዳም ነው። አባቶች እንደሚሉት ይህ ታሪካዊ ገዳም በግራኝ መሐመድ ጊዜ ጽላተ ሙሴ ከአክሱም ወጥቶ ተደብቆ የቆየበት ገዳም ነው።

የኢሮብ ወረዳ ባህላዊ ከተማ በሆነችው አሊቴና ውስጥ የሚገኘው በኢትዮጵያ

የመጀመሪያው የሆነው የካቶሊክ ቤተክርስቲያ የተመሠረተው በ1840 ዓ.ም ሲሆን በቤተክርስቲያኑ ስር የተቋቋመ ዘመናዊ የሚሲዮን ትምህርት ቤትም አለ። ይህ ትምህርት ቤት በጣም የታወቀና ለአዲ ኢሮብና ለአካባቢው ሕብረተሰብ ልጆች ሩቅ የነበረውን የትምህርት እድል በቅርቡ በማስገኘት ከፍተኛ ድርሻ ያለውና ውጤታማ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ልጆች የዘመናዊ ትምህርት ዕድል በማስገኘት ብቻ ሳይሆን ከትግራይ ክልልም ጭምር ቀደምት ከሚባሉ ትምህርት ቤቶች አንዱ የሚባል ነው።

ይህ ትምህርት ቤት ከተመሠረተ ጀምሮ ነጻ የትምህርት እድል እየተሰጣቸው ወደሮም የሄዱ በርካታ የአካባቢው ተማሪዎች አሉ። ከእነዚህም ተማሪዎች መካከል ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች ሄደው በልዩ ልዩ የሞያ መስኮች ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል የቻሉ አሉ። ከእነዚህ መሀል ትልቅ ቦታ የደረሱ ብዙዎች ናቸው። ከቀደምት የኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል በዚህ የካቶሊክ ሚሽን ተምረው ከፍተኛ የትምህርት ዕድል ካገኙት አንዱ የኢሕአፓ መሥራችና የማእከላዊ ኮሚቴና የፖሊት ቢሮ አባል የነበረው ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ይጠቀሳል።

አዲ ኢሮብ ተራራማ፣ ጫካና በረሐማ ስለሆነ፣ እስከቅርብ ጊዜ ድረስብዙ የዱር እንስሳት፣ ነብሮች ጭምር እንደነበሩበት ይነገራል። አካባቢው ሁልጊዜ እርጥበት ስለማይለየው ከፍታው እየጨመረ ወደ አሲምባ ጫፍ እየተጠጉ በሄዱ መጠን ጫካው ጥቅጥቅ ያለ ደን ይሆናል። ከአዲ ኢሮብ ተራራዎች ትልቁ ከፍተኛ ቦታ የአሲምባ ጫፍ ነው። አሲምባ ማለት ቀይ አምባ ማለት ሲሆን የዚህ ተራራ ከፍታ 3250 ሜትር ነው። ከአሲምባ ተራራ ወደ ቀይ ባሕር አቅጣጫ፣ የመሬቱ አቀማመጥ እየቀነሰና እያቆለቆለ ሄዶ ከመሬት ወለል በላይ 150 ሜትር ድረስ ዝቅ ይላል። አሲምባ ከፍተኛ ቦታ





ከመሆኑ የተነሣ ሌሊት ሌሊት በጉም ይሸፈናል። በአሲምባ ተራራ ጫፍ ላይ በጣም ቀዝቃዛና የጠራ ንጹሕ ውኃ ያለው ጅረት አለ። ይህ ወንዝ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ይወርድና ከአሲምባ በታች የሚገኘውን የጉንዳ ጉንዴን ታሪካዊ ገዳም ያለማል።

ኢሮብ በተራራዎች የታጠረ ቦታ ነው። በምዕራብ ከደጋው በኩል ወደ ውስጥ ሲገባ በሰሜን በኩል የአይጋ ሰንሰለታማ ተራራ ይገኛል። የአይጋ ተራራ በወረአትሌ በኩል ወደ ምሥራቅ ተዘርግቶ እስከደንከል ይደርሳል። የማእቢኖን ተራራ ደግሞ በስተምሥራቅ በኩል የአሲምባን ተራራ ገጥሞ እስከ እንደሌ ይሄድና ደንከሌ ጫፍ ይደርሳል። የአይጋ ተራራ በደቡብ በኩል ካለው የማእቢኖን ሰንሰለታማ ተራራ በሚገጣጠምበት ቦታ ላይ ትንሽ ሸለቆ ይሠራሉ። በዚህ ሸለቆ ቀዳዳ በኩል ወደ ኢሮብ መግባት ይቻላል። በሁለቱ የተራራ ሸንተረሮች መጋጠሚያ ላይ በሚገኘው ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ ወንዝ በሁለቱ አፋፍ መካከል አድርጎ ወደ ምሥራቅ ይወርዳል። ተራራውና ሸንተረሩ ተሰልፎ ውበቱ ዐይን የመማረክ ስሜትን የማንበርከክ ኃይል አለው። የቦታው አቀማመጥ ለሽፍቶች በጣም አመቺ ስለሆነ፣ በዚያን ጊዜ ለመንግሥትም የሚያስቸግሩ ሽፍቶች አዲአሮብ ወደሚገኘው የአሲምባ ተራራ ጫካ ነበር የሚገቡት።

የኢሮብ ሕዝብ ውጊያ የማይፈራ፣ ያገኘውን ተካፍሎ የሚበላ፣ ያመነውን በፍጹም አሳልፎ የማይሰጥ፣ እስከተፈለገው ጊዜ ደብቆና ጠብቆ የሚያቆይ ሕዝብ ነው። የኢሮብ ሕዝብ ካመነ አመነ ነው። ለምሳሌ ዐፄ ዩሐንስ ከመንገሣቸው በፊት፣ ደጃዝማች በነበሩበት ጊዜ የመጀመሪያው ግዛታቸው ከአዲኢሮብ ጀምሮ እስከፉረስ ደጌ ቆላማው ቦታ ነበር። በዚህ የሽፍትነት ጊዜያቸው፣ የአዲኢሮብ ሕዝብ ደብቆ፣ ጠብቆ አቆይቷቸዋል። የአዲ ኢሮብ

ማኅበረሰብ የደበቀውን ምስጢር ማስወጣትም ሆነ ማግኘት አይቻልም። ጥብቅ ሕዝብ ነው።

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ የክልተ አውላሎም ሆነ የኢጋሜ ጀግኖች መደበቂያቸው አሲምባ ነበር። ስለዚህ የአዲ ኢሮብ ሕዝብ አሲምባን ምሽጉ አድርጎ ጣሊያንን እስከመጨረሻው የተዋጋ ጀግና ሕዝብ ሲሆን፣ በታሪክ የሚታወቀውም በጣሊያን ያልተገዛ ማኅረሰብ ተደርጎ ነው። በተጨማሪም የኢሮቦችን ጀግንነት ያስመሰከሩ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ የታወቁ ትውልዳቸው ኢሮብ የሆነ ብዙ ጀግኖች በታሪክ መዝገብ ተጽፈዋል።

ኢሮብ ተመሠረተ የሚባለው በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው፣ አነቀደማዊ ምንልክ ከእስራኤል ሲመጡ አብሮአቸው የመጣ ስምኦን የሚባል ሰው ነበረ ይባላል። የስምኦን ሚስት ዕሌኒ፣ የንጉስ ምኒልክ ሚስት እኅት ነበረች። አኩስም እንደገቡ ስምኦን የተወሰኑ አሽከሮችን ይዞ ወደ ክልተ አውላሎ ሄደ። ከክልተ አውላሎ ደግሞ ወደ አስመራና ወደ ኤርትራ አካለ ጉዛይ ሰራዬ ሲንቀሳቀስ ነበር። በተለይ በጸራእ፣ ክልተ አውላሎ ብዙ ጊዜ ተቀምጦ፣ ከትውልድ ትውልድ እልፎ ወረደ ምሕረት የሚባለው ተወላጅ ላይ ሲደርስ ሦስት ልጆችን ይዞ፣ ከሰባት መቶ ዓመት በፊት ኢሮብ ሰፈረ። ሦስቱ ልጆቹ ሀሰበላ፣ ኩመኒትና አልገዳ ይባላሉ። ሦስቱ የኢሮቦች ማኅበረሰብ ቤተሰቦች በእነሱ ስም ተሰይመው ተመሠረቱ የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው።

ሦስቱ ኢሮብ ከሚባሉት ሁለቱ አልገዳና ሀሰበላ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፣ ኩመኒቶች ደግሞ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሉም በጋብቻም ጭምር የተሳሰሩ ናቸው። አዲ ኢሮቦች ካቶሊክና ተዋሕዶ በሚባል የመከፋፈል ልዩነት አይታይባቸውም።

***





**ተአሊም**

«ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ

እንደሆቺሚኒ እንደቼጉቬራ

በዱር በገደሉ ትግሉን እንድትመራ»

ወደ ሰንገዴ ተመልሰን እንደመጣን፣ ተአሊም (ወታደራዊ ሥልጠና) ሊሰጥ እንደሆነ ተነገረን ። ሰንገዴ በአቀማመጡ ወጣ ገባ የሚበዛበት፣ ዙሪያውን ትናንሽ ኮረብታዎች ያሉበት፣ በመሆኑ ሥልጠና ለማካሄድ የሚመች ቦታ ነው። ሰንገዴ ለመጠጥና ለምግብ ማዘጋጃ የሚሆን በቂ ውኃና ለማብሰያም በቂ እንጨት ያለው ሥፍራ ነበር። ሥልጠናው ጠዋት በአስራ አንድ ሰዓት ይጀምራል፤ በሰሜን በኩል ያለውን ተራራ በሩጫ ወጥቶ መመለስስ ግማሽ ቀን ይወስድና እኩለ ቀን ላይ በስድስት ሰዓት የጠዋቱ ስልጠና ይቆማል። ከምሳ በኋላም ሥልጠናው ይቀጥልና አስራ ሁለት ሰዓት ያበቃል። ስልጠናውን የሰጡት ጌራ፣ ጂግሳ፣ አዲስ ዛህላይና ኃይሌ ነበሩ። በዚያን ወቅት በግደይ አሰልጣኝነት ስለፈንጂ አጠቃቀም ልዩ ትምህርት ተሰጥቶናል። ግደይ የፈንጂ ኤክስፐርት ስለነበረ ፈንጂ እንዴት እንደሚሠራ፣ ምን ዓይነት ቅመሞች እንዳሉት፣ እንዴት እንደሚፈነዳና ሌሎች ከፈንጂ ጋር የተያያዙ እውቀቶች ያገኘንበትን ሥለጠና ሰጠን። የሠራዊቱ አባላት በሥልጠና ላይ ስንሆን ጋንታ መሪዎቹ እየቀደሙ አካባቢውን ይቆጣጠራሉ።

ከአራት በኋላ እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ድረስ ተሸኪል (ደፈጣ) ይዘን እየጠበቅን እናመሻለን። ሶስት ሰዓት ከመሙላቱ በፊት መተኛት የተከለከለ ነበር። ለመኝታ ጊዜ አመራሩ ሁለት አባላት በአንድ ላይ ሆነን እንድንተኛ ይመድባል። አብሮ መተኛት ሙቀት ስለሚሰጥና ብርድ ለመቀነስ ስለሚያስችል እንዲሁም ለጥንቃቄም ሲባል ነው። ማን ከማን ጋር እንደሚተኛ የሚወስኑት መሪዎች ናቸው። "ተኙ" የሚለው ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ መተኛት የተከለከለ ነበር። እኔ የምተኛው ነመራ ከሚባል ጓድ ጋር ሲሆን ሁለታችንም አዲሶች ነበርን። እንቅልፋችን ከተፈቀደው ሰዓት ቀድሞ እየመጣ

እንቾገር ሰለነበረ ተደብቀን በፈረቃ ለመተኛት ተስማማን። ተቆጣጣሪያችን ጂግሳ ከመጣ ያልተኛው የተኛውን ይቀሰቅሳል።

ጂግሳ በየማማሸ ሰዓቱ እየመጣ መተኛታችንንና አለመተኛታችንን ይቆጣጠር ነበር። ጂግሳ በተፈጥሮው ንቁ፣ በጣም ጥሩ የወታደራዊ አቋም ያለውና ጠንቃቃ ሰው ነው። የጅግሳን ኮቴ ስንሰማ እንቀሳቀስና ያልተኛን መስለን እንታያለን። አዲሶች መሆናችንና የዕድሜያችን ገና አሥራ ሰምንት ዓመት አካባቢ መሆኑ ከሥልጠናው አድካሚነት ጋር ሲዳመር እንቅልፋችንን መቋቋም በጣም ይከብደን ነበር። ከሦስት ሰዓት በኋላ ግን ሌሊቱን እየተቀያየርን በተረኛ ዋርዲያነት ከምንጠብቀው በስተቀር ሌሎች የሠራዊቱ አባላት ይተኛሉ፤ ከማለዳው አሥራ አንድ ሰዓት እንደገና ወደ ሥልጠናው መሄድ የሁሉም ግዴታ ነበር።

በሕክምና ሞያ እንዲሠለጥኑ ለሚመደቡት አባላት ሥልጠናውን የሚሰጠው ጌራ ነበር። ጌራ በጣም ወጣትና መልኩ ቀይ ነበረ ሲሆን የስፖርተኛ ዓይነት ሰውነትም ነበረው። ጌራ ለሠራዊቱ የመጀመሪያው የጤና ባለሙያ እና ሌሎቹንም በጤና ሙያ ያሠለጠነ ሰው ነው። ከጤና ባለሞያነቱ በተጨማሪ ኤርትራ በቆየበት ጊዜ ባገኘው የጦር ልምድ የተካነ ጎበዝ ተዋጊና ታዋቂ የጦር መሪም ነበር። በፖለቲካ የነቃ ከመሆኑ ባሻገር ኤርትራ በቆየበት ጊዜ ትግርኛ ቋንቋ ተምሮ አማርኛና ትግርኛ አቀላጥፎ ስለሚናገር ከሠራዊቱ አባላትና ከሕዝቡ ጋር በቀላሉ መግባባት ይችል ነበር። ጌራ የሕክምና ሞያ ሥልጠና የወሰደው ከአራት ጓደኞቹ ጋር ጠፍተው ከኢትዮጵያ ለመውጣት ሲሞክሩ ሶማሊያ ውስጥ ታስረው ከተፈቱ በኋላ ነበር። ከእስር ሲፈቱ አብረው ከነበሩ የኤርትራ ተወላጅ ተማሪዎች ጋር ወደኤርትራ ከገቡ በኋላ በኢ.ፒ ኤል ኤፍ (ሻእቢያ) ዶክተሮች አማካኝነት ሠለጠኑ። ጌራ ጎበዝና ታታሪ አሠልጣኝ ከመሆኑም ሌላ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የሕክምና ርዳታ የሚያደርግልን እሱ ስለነበረ በቅጽል ስም ዶክተር እያልን እንጠራው ነበር ።

የሕክምና ባለያዎቹ በሥልጠና ላይ በነበሩበት ጊዜ መርፌ መውጋት የሚለማመዱት በእኛ ላይ ነበር። በዚህ ልምምድ ጊዜ ጸጋዬ ደብተራው በቅርብ ካለ ሌላ





ሰው እንዳይፈልጉ በመኪልከል በፈቃደኝነት ራሱን ለመለማመጃነት ያቀርብ እንደነበርና ብዙ ጊዜ በመርፌ መጠቅጠቁ አይረሳኝም።

ሰንገዴ በቅርበት ከሚገኘው ከቀይ ባሕርና በአካባቢው ካሉት ጋራዎች እርጥበት ስለሚያገኝና ከከፍታው ቦታ የሚወርደው ውኃ ስለሚያልፍበት ከዓመት ዓመት እርጥበት የማያጣና የማይደርቅ፣ ለም የሆነ መሬት ነው። ዙሪያውን በአካባቢው የሚኖሩ ከብት አርቢ ገበሬዎች ቢጋው ሲጠነከርባቸው ከብቶቻቸውንና በጥበቃ የሚያግዟቸውን ውሾቻቸውን ይዘው ወደሰንገዴ ይዘልቁና ሰነባብተው ይመለሳሉ። ሥልጠና ላይ በነበርንበት ወቅት ከብት አርቢዎች መምጣት እየጀምሩ ነበር። የከብት አርቢዎቹ ወደ ሥፍራው መምጣታቸው ያስከተለብን ስጋት አልነበረም።

ሆኖም በዚያኑ ሰሞን ቀስ በቀስ የሥልጠናው አባላት፣ ባልታወቀ ምክንያት በተቅማጥ በሽታ መጠቃት ጀመርን። ነገሩ ብዙ ቢያስጨንቀንም የበሽታውን መንስኤ ማወቅ ባ ለመቻሉ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ነበር። አዘውትረን የምንበላው በጋለ ድጋይ ( በቃጼላ) ላ ይ የ ሚጋገር ቂጣ ደግሞ አገጋገሩም ሆነ ምግብነቱ ለበሽታ አምጭ ተህዋስያን የማያጋልጥ ከመሆኑም ባሻገር በጣምአስተማማኝ የሚባል ስለነበረ በተከሠተው የጤና ችግር ግራ ተጋብተን የምናደርገው ጠፋን። የአካባቢው ገበሬዎችም ለዘመናት የሚጠቀሙበት የአገጋገር ዘዴ ሲሆን ተመሳሳይ የጤና ችግር ገጥሟቸው እንደማያውቅ መረጃዎች ተገኝተዋል።

በመጨረሻ በሁኔታው ግራ በመጋባት ችግሩን ለማጥናት እንዲቻል አባላት ሥልጠና ሄደን እስከንመለስ የተወሰኑ ጓዶች ምግብ በምናበስልበት አካባቢ ቀርተው እንዲከታተሉ ተደረገ። ፀሐዬ፣ ግደይ፣ ሐዋዝ፣ ዘላለምና ጸጋዬ ደብተራው እየተቀያየሩ በምንመገብበት ቦታ በመቆየት ምግባችንንም አዘጋጅተው ይጠብቁን ጀመር። በዚህ ሂደት የችግሩን መንስኤ ማግኘት ተቻለ። ለግጦሽ ወደ አካባቢው ከመጡት አርቢዎች ጋር የነበሩት ውሾች የሚጋገረው ቂጣ እየሸተታቸው እኛ ወደ ሥልጠና ስንሄድ የቃጼላ መጋገሪያውን ድንጋይ እንደሚልሱ ማወቅ ተቻለ። ከዚያ በኋላ ቂጣውን ከመጋገር በፊት ድንጋዩን በሚገባ ማጠብ ተጀመር፤ የጤና ችግሩም ተቀረፈ።

በሰንገዴ አካባቢ ሌላው የማይረሳው ከጤና ጋር የተያያዘ ችግር ደግሞ በዓመቱ የመጀመሪያ ወራት ላይ የቆላ ዝንቦች እየተፈለፈሉ የሚፈጥሩት ችግር ነበር። ዝንቦቹ በመጠናቸው ትላልቅ ሲሆኑ ተናዳፊዎችም ናቸው። የነደፉት አካል ወዲያውኑ ይቆስላል፤ ቁስሉ ደግሞ በቀላሉ የማይድንና አስቸጋሪ የቆላ ቁስል ስለሚሆን ይህን ችግር ለመከላከል የምንጠቀምበት ዘዴ አስቂኝ ነበር። መከላከያችን ዝንቡ ሲመጣ በሩጫ ጭምር ለመሸሽ መሞከርን ይጨምር ነበር።

ሰንገዴ ለአንድ ወር ቆየንና በጥቅምት ወር በ1968 ዓ.ም ወታደራዊ ሥልጠናው ተጠናቀቀ። ሥልጠናው ሲያልቅ ሰንገዴን ለቀን አዲ ኢሮብ ውስጥ ወደሚገኝ ወረአትለ ወደተባለ ቦታ ሄድን። ወረአትለ በበለስ የታወቀው ቦታ ነው፤ ጊዜውም የበለስ ወቅት ሲሆን፣ በለሱን በነጻ ለምግብነት መጠቀም ይቻል ነበር። (በለስ ከግንቦት ወር ጀምሮ እስከ ጥር ድረስ በአዲ ኢሮብ ውስጥ በብዛት ሊገኝ የሚችል፣ቁልቋል የሚመስል ለምግብነት የሚያገለግል የተክል ዓይነት ነው) በዚያ በወረአትለ የተፈጥሮ ሀብት የሚጠቀሙት የአዲኢሮብ ሰዎች ብቻ አልነበሩም። ከኤርትራ ከብቶቻቸውን ይዘው የሚመጡ ከብት አርቢዎች ጭምር ለሁለትና ለሦስት ወራት፣ በለስ እየተመገቡና ከብቶቻቸውን ግጦሽ እያሰማሩ ሰንብተው ይመለሳሉ።

ወረአትለ በከረምንበት ሰሞን አንድ ቀን ኃይሌ ቀጭኑ ሊያነጋግረኝ እንደሚፈልግ ነገረኝና ሄድኩ። በመጀመሪያ ስለ ሶሻሊዝምና ኮምኒዝም አስረዳኝ፤ አንዳንዱ በህዋስ ተሰብስበን ከተሰጠን የፖለቲካ ትምህርት ጋር ይመሳሰላል። ብዙ ነገር ካስረዳኝ በኋላ በመጨረሻ አንድ ያላሰብኩትን ጥያቄ አነሣብኝ። "በአምላክ መኖር ታምናለህ?"አለኝ።

በጥያቄው ደንግጬ ግራ ገባኝ። "አዎ! እኔ አምላክ በመኖሩ አምናለሁ" አልኩት ጥቂት ቆየት ብየ። "አምላክ አለ የምትል ከሆነማ ሶሻሊስት ልትሆን አትችልም" አለኝ መልሴን ሰምቶ።

እኔ፣ የቆሰ ገበዝ አያቴን መጽሐፍ ይዤ፣ ቤተክርስቲያን እየተመላለስኩና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታዊ ትምህርት እየተማርኩ ነው ያደግኩት። ከእሳቸው ጋር ቤተክርስቲያን





እየሄድኩ ሳድር፣ መጽሐፍ ቅዱስና ተአምራትን ሳነብ፣ ውዳሴ ማርያምና መልከ ማርያም ሁሉ ጨርሼ ወደ ቅዳሴ ልገባ ትንሽ ነበር የቀረኝ። ታዲያ አምላክ የለም ብዬ መልስ መስጠት እንዴት ልደፍር እችላለሁ? በመጨረሻ ግን እሱም ሁኔታዬን አይቶ የተረዳኝ መሰለኝ፡ "አይዞህ ምንም አይደለም። አምላክ አለ ብትልም ታጋይ መሆን ትችላለህ። የጠየቅኩህ፣ አቋምህን ለማወቅ ስለፈለግሁ ብቻ ነው" አለኝ።"በሌላ አትውሰድብኝ እንጂ እኔ በእግዚአብሔር አምናለሁ" አልኩትና በዚያው ተለያየን።

አልፎ አልፎ ሲያስለኝ ሰንብቻለሁ፤ እያደር ግን ሳሉ ትንሽ ጠንከር እያለብኝ ሄደ። ከሳሉ ጋር የተያያዘ ምንም የህመም ስሜት ስላልተሰማኝ ግን ችላ ብዬዋለሁ። በሌላ ቀን ኃይሌ እንደገና ጠራኝና ስለሚያስለኝ ችግርና በአጠቃላይ፣ ስለጤናዬ ጠየቀኝ። እኔም አንዳንድ ጊዜ፣እንደዚህ ብርድ ሲሆን እንደሚያስለኝ ነገርኩት።

"ሲያስልህ ከአክታህ ጋር የተቀላቀለ ደም ይወጣል?" ብሎ ጠየቀኝ።

"አዎ፤ አንዳንድ ጊዜ ከአክታዬ ጋር ደም ተቀላቅሎ ይወጣል" አልኩት።

"እንደዚህ ከሆነ የሳንባ ነቀርሳ ሊሆን ይችላል" አለና "ከዚህ በፊት፣ በዚህ ህመም ሐኪም ቤት ሄደህ ታክመህ ታውቃለህ?" አለኝ።

"በዚህ ዓይነት ህመም ሐኪም ዘንድ ሄጄ አላውቅም" አልኩት።

"ምናልባት የሳንባ ነቀርሳ ሊኖርብህ ስለሚችል፣ ለብቻህ መተኛት ይኖርብሃል፤ ውኃ የምትጠጣበት ኩባያም ለብቻህ ይሰጥሀል" አለኝ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ "አማኑኤል የሳንባ ነቀርሳ በሽተኛ ነው" ተብሎ ብቻዬን መተኛት ጀመርኩ። አንዳንድ ጊዜ አየሩ በጣም ሲቀዘቅዝ፡ አንድ ነጠላ ለብሶ ለብቻ ለማደር በጣም ይቸግር ነበር። አንዳንድ ጓዶች ደግሞ "እኛ በጥይት እንሞታለን እንጂ በሳንባ ነቀርሳ አንሞትም አባክህ ዝም ብለህ ከኛ ጋር ተኛ" ብለው አቅፈውኝ ይተኙ ነበር። ብቻዬን ስተኛ ግን በጣም እቸገር ነበር።

የአብሮ መተኛት ነገር ሲነሣ በተለይ ከጂግሳ ጋር ሳድር ደስ ይለኝ ነበር፤ ምክንያቱም የጂግሳ ጀርባ በጣም ይሞቃል። የፈለገው ብርድ ቢሆን የጂግሳን ጀርባ ተደግፎ ያደረ ሰው እንደሚሞቀው ስለሚታወቅ ሁላችንም ከጂግሳ ጋር ለመተኛት እንሻማ ነበር። በኋላ ከጌራ ጋር እንድተኛ ተመደብኩ። ጌራ የሕክምና ባለሞያ ስለነበር "አይዞህ አትፍራ፤ በሳንባ ነቀርሳ አምታለሁ ብለህ አትስጋ። ወደጓዶች እስተላልፋለሁ ብለህም አትሳቀቅ" እያለ ያጽናናኝ ስለነበር ትልቅ የሞራል ድጋፍ ሰጠኝና ተበረታታሁ። ከወረአትለ እንደተመለስን በቡድን ተከፋፍለን የሠራዊቱ ሕግና ደንብ ተነበበልን።

ያን ጊዜ እንታሪኩ፣ ያዲቴ፣ አብዲ፣ መገርሳ፣ ጃራ እና አማረ እንዲሁም ሌሎች መጥተው ብዛታችን ጨምሮ በርከት ብለናል። ጥቅምት አልፎ ወደ ኅዳር መጀመሪያ ላይ በሰቢያ በኩል ወደ መድአ ተንቀሳቀስን። መድአ እንደደረስን የሠራዊቱ አባላት ጥያቄ አነሡ። "ሥልጠና ወስደናል፣ ትጥቅም አግኝተናል፤ ከአሁን በኋላ ጠላት ያለበት ቦታም ድረስ እየሄድን ማጥቃት መቻል አለብን" የሚል ነበር ጥያቄው። ለዚሁ ጉዳይ ስብሰባ ተቀመጥን። በስብሰባውም መጨረሻ ሠራዊቱ አቅሙን ያገናዘበ የማጥቃት ርምጃ ሊወስድ እንደሚችልና ይህንኑ ውሳኔ ለፓርቲው ማሳወቅ እንደሚገባ ተወሰነ።

አንድ ቀን ቆሎ ምሸላ አካባቢ እያለን ከነበርሔ ጋር ቁጭ ብለን እየተጫወትን አብዲ እየሮጠ መጣና "ጓዶች! ጂግሳ እዚህ እኛ ውስጥ ከትግራይ ልጆች መሀል የጠባብ ብሔርተኛ አመለካከት ያላቸው ጓዶች ስላሉ፣ ተጠንቀቁ እያለ እያስፈራራን





ነው። ስለዚህ ችግር ላይ እንዳይጥላችሁ ተጠንቀቁ" አለን። ነገሩን እንደሰማን "ለምን ይህንን አለ? ከምን ተነስቶስ ተናገረ?" ብለን ሁላችንም ደነገጥን።

ሕግና ደንቡን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ነበር የምናነበው፤ ጂግሳ በማግስቱ መድአ የተባለ ቦታ ሆነን የሠራዊቱን ሕግና ደንብ ሲያነብ የአንድ አማርኛ ቃል ትርጉም ጠየቀን። በርሔ "አንተ እራስህ እወቀው እንጂ፣ አንተ ያላወቅከውን አማርኛ እኛ እንድናውቀው ለምን ትጠብቃለህ?" በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት። በርሔ እንዲህ ያለው፣ አብዲ ስለጅግሳ የነገረን ነገር ቅሬታ ስላሳደረበት ነበር። (በርሔ፣ እውነተኛ ስሙ ሀጎስ በዛብህ ይባላል፤ የአክሱም ልጅ ሲሆን፣ ከአጉላእ የመጣ የዩኒቨርስቲ ዘማች ነበረ። በሠራዊቱ አያ በርሔ በመባል የሚታወቅና ከሠራዊቱ ወታደራዊ መሪዎች አንዱ ለመሆን የበቃ ነው)

ጂግሳ ስለተሰማን ቅሬታ አላወቀም፤ በበርሔ መልስ ደነገጠ። በዚያ ላይ ሁላችንም ቅሬታ ስለነበረን በገጽታችን ላይ ይነበብ የነበረው መጥፎ ስሜት ነበር። "እንዴት እንደዚህ ይለናል? እኛ የፖለቲካ ብስለት ሳይኖረን ነው የመጣነው፤ ብዙዎቻችን አእምሮአችንን የከፈተው ንድፈ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠን የፖለቲካ ትምህርት ብቻ ነው። የብሔርም ሆነ ሌላ ድርጅት ውስጥ ተካፍለን አናውቅም፤ የምናውቀው ድርጅት ኢሕአፓ ብቻ ነበር። እንዴት ጠባብ ብሔረተኞች አለን?" በማለት እኛ ቅሬታ ተሰምቶናል፤ ጅግሳም የበርሔ አነጋገር ደስ ባይለውም ውይይቱን ቀጠልን።

ሕግና ደንቡ እየተነበበ ስነበትንና በዛው ደግሞ ስለሠራዊቱ የመንቀሳቀስ መብትም ተነሣ። ፓርቲው "ባላችሁበት ቆዩ፤ ምንም ዓይነት ወታደራዊ እንቅስቃሴ እንዳታደርጉ" የሚል ትዕዛዝ ማስተላልፉ ተነገረን። ይህም ፓርቲው ውሳኔውን እስኪለውጠውና እንድንንቀሳቀስ እስኪፈቀድልን መጠበቅ እንደሚኖርብን አስገነዘበን። ይህ ሁኔታ ብዙዎቻችንን ቅር አሰኝቷል፤ "እየበላንና እየጠጣን መንደር ለመንደር ለመዞር አልመጣንም። ትግል ማለት ሠራዊቱ ራሱን ሲችል፣ ጠላት ያለበት ቦታ ሄዶ ሲዋጋና ሲመታ ብቻ ነው" የሚል አመለካከት ስለነበረን ሁላችንም ቅሬታችንን አሰማን። ወዲያውኑ ውሳኔ ተላለፈና እንደሠራዊት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እርምጃ የሚወስድባቸው እንቅስቃሴዎች ማድረግ ጀመርን።

## ሁለት

## የመጀመሪያዎቹ ወራት

### የዳሎል ጉዞ

"ያለመሥዋዕትነት ድል የለም"

መድአ ላይ በተደረገው ስብሰባ እራሳችንን መቻል እንዳለብን ሐሳብ ቀርቦ ውሳኔ ተሰጥቶበታል። መሥዋዕትነት የሚያስከፍል ቢሆን እንኳን ችግራችንን ለመፍታት የሚያስችለንን ዕቅድ ነድፈን መንቀሳቀስ እንደሚገባን ብዙዎቻችን ተስማምተናል። ከፓርቲው ጋር ለመገናኘት የሚቻልበት መንገድ እስከሚመቻች ድረስ በራሳችን ውሳኔ ለመራመድና መሣሪያ፣ ገንዘብና፣ ሌሎችም ለሠራዊቱ የሚጠቅሙ ነገሮች ከጠላት ለማግኘት በተወሰነው መሠረት እንቅስቃሴ ተጀመረ።

ከሁለት ቀናት በኋላ ዳሎል ውስጥ በሚገኝ የመንግሥት ቀረጥ ሰብሳቢ ፊናንስ ፖሊስ ጣቢያ ላይ ያነጣጠረ ተልዕኮ ታቀደና ወደዚያው ለመሄድ ተዘጋጀን። እግረ መንገዳችንንም በአስፈላጊ ቦታዎች ሁሉ የቅስቀሳ ሥራ እየሠራን እንድንሄድ ተነገረን።

ጉዞአችንን የጀመርነው በሌሊት ሲሆን ያቀናነው ወደ ደገይቶ ነበር። ደገይቶ ከመእቢኖን በስተጀርባ ከሰበያ በስተደቡብ በኩል የሚገኝ ሥፍራ ነው። ደገይቶ ውስጥ በየነ አብርሃ የሚባል አደገኛ የመንደር ነጭ ለባሽ መኖሩን ሰምተን እርሱን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ነበር የሄድነው። እንደደረስን አገኘነውና በእስረኝነት ይዘነው ጉዞአችንን ቀጠልን። እንደበየነ ዓይነት ሰዎች ለትግሉ አደገኞች መሆናቸው ይታመናል። በየነ ግን ብዙም ሳይቆይ ጠፋብን። እስረኛው ያመለጠው ደበሳይ ዋርዲያ በነበረበት ሰዓት ስለነበረ ሁኔታው ሲመረመር ደበሳይና በየነ በሽፍትነት አብረው እንደነበሩ ታወቀ። እስረኛውን ሆን ብሎ እንዲያመልጥ





እንዳደረገ በደበሳይ ላይ ጥርጣሬ ቢኖርም ለመክሰስ የሚያስችል ተጨባጭ ማስረጃ አልነበረም።

በየነ ከተማ ሄዶ ጠላት ይዞብን ሊመጣ ይችላል ብለን ስላሰብን ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን። እናም በማግስቱ በአቅርቢያው ካለ ጋራ ላይ ወጥተን ዋልን። ወደ አመሻሽ ላይ በየነን እንደገና በቁጥጥር ስር ለማዋል ወደሚኖርበት መንደር ሄድን። የአካባቢውን ቤቶች አንድ በአንድ ብንፈትሽም በየነን ግን ልናገኘው አልቻልንም። በመጨረሻ ወደመኖሪያ ቤቱ ሄደን ንብረቱን ዘረፍነው፤ ከነበሩት ከብቶችና ከእህሉ ግማሹን ከፍለን ለሚስቱ በመተው እኩሌታውን ወሰድን። ከከብቶቹ መካከል አንዱን በሬ ለማረድ ፈለግንና ለመያዝ ሞከርን፤ በፍጹም አልተቻለም። በሬው ኃይለኛ ስለነበር አስቸገረን ከብዙ ሙከራ በኋላ በመሣሪያ ተመትቶ ወደቀና አርደን ሥጋውን ይዘን ሄድን።

ይህ ውሳኔ ፍትሐዊ ስለአልመሰለኝ ስሜቴን ነካው። ምናልባትም የገበሬ ልጅ ስለሆንኩ ይሆናል፤ የገበሬውን እህልና ከብቶች ከልጆቹ ቀምተን መውሰድ ትክክል መስሎ አልታየኝም። ሰውዬውን ፈልጎ ማግኘትና እንደገና ማሰር እንጂ ቤተሰቦቹን መዝረፍና ለድህነት ማጋለጥ ፍትሐዊ ያለመሆኑን ሳሰላስለው ከፋኝ። በዚያ ቤተሰብ ላይ የተደረገውን ነገር ወደ እራሴ ወስጀው ከአባቴ ቤት እህልና ከብት ተወስዶ ቤተሰቦቼ ለድህነትና ለችግር ሲጋለጡ ታየኝና ልቤ አዘነብኝ። ይህን ስሜት በውስጤ ከማውጠንጠን በስተቀር አውጥቼ አልተናገርኩትም።

***

ብዙውን ጊዜ የምንንቀሳቀሰውም በሌሊት ነበር። ጉዟችን ፈጣን እንቅስቃሴ ያለበትና ጥንቃቄ የተሞላበት የሽምቅ ተዋጊ እንቅስቃሴ ሆኗል። በዋልንበት አናድርም፣ ባደርንበትም አንውልም። በአብዛኛው ለአዳርም ሆነ ለውሎ የሚመረጠው ተራራማ የሆነ ቦታ ነበር። በእንዲህ ዓይነት ጉዞ ውሎ ካደረግን የተወሰኑ አባላት ተመርጠው ወደ አካባቢው መንደር ይላኩና ሕብረተሰቡን ሲያነጋግሩ ሌሎቻችን ቀኑን ተደብቀን ማሳለፍ ይኖርብናል።

ቅስቀሳ ለማድረግ፣ በሌሊት ተነሥተን ከአዲግራት በደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ በእዳጋ ሀሙስ በኩል ወደምትገኘው ሳዕሲዕ ወደትምትባል መንደር ሄድን። ሐረጎት በቅስቀሳ ሥራ ልዩ ችሎታ ነበረው። ጾታ፣ ዕድሜ እንዲሁም ማኅበራዊ ደረጃ ሳያግደው ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ማስተማርን ተክኖበታል። በምናርፍበት ጊዜ ሁሉ ሕዝቡ ሊገባው በሚችል መንገድ የፖለቲካ ትምህርት ሲሰጥ አይሰለችም። ሌላው የፖለቲካ ትምህርት የመስጠት ችሎታ የነበረው ግደይ ነበር። ሐረጎትና ግደይ ከገበሬዎች ጋር በጣም ከመግባባታቸው የተነሣ መምህር ሐረጎት፤ ልጅ ግደይ እየተባሉ ይጠሩ ነበር።

ሐረጎት በሚያስተምርበት ጊዜ ሕዝቡ የሚያዳምጠው በተመስጦ ነው። አንዳንዴ ከእርሱ ጋር በእሳት ዙሪያ ቆጭ ብለው በስሜት ሲያዳምጡት ሌሊቱ ይነጋ ነበር። ለጥበቃ ዋርዲያ እየተቀያየረ፣ እርሱ ግን ማንም ሳይተካው ከማኅበረሰቡ ጋር ሲወያይ የማደር ጥንካሬ ነበረው ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከቆየንበት አካባቢ ስንለቅ ነዋሪዎቹ ሲሰናበቱን ሐረጎትን በስስት እየተመለከቱት ተመልሶ እንዲያያቸውና እንዳይጠፋባቸው አደራ ይሉት ነበር።

ቀጣዩ ጉዟችን ከእዳጋ ሐሙስ በስተምሥራቅ ወደሚገኘው ወደ ሱብሀ ነበር። እራታችንን በልተን ሌሊቱን ቁልቁለቱን ወረድንና ከቆላማው ሰቢባ ደረስን። ከእሲምባ ወደ ዳሎል ለመሄድ የሚቀርበው ጉንዳጉንዴ ቢሆንም እኛ ግን





ሕዝቡን እየቀሰቀስን ለማለፍ እንድንችል ረጅሙን መንገድ ነበር የመረጥነው። ሰቢባ ሕዝቡን ከቀሰቀስን በኋላ ጥቂት እንደተጓዝን ወደ ቆላማው ቦታ መዳረሻ ላይ ከደጋ የመጣ ዝናብ ያዘን። ዝናቡ ከላይ ሲደበድበን ቁልቁል የሚወርደው የወንዝ ጎርፍ በየሥፍራው ከሚወርደው ውኃ ጋር ተዳብሎ መንገዳችንን አስቸጋሪ አደረገው። ጉዟችን የተራራውን እግር ተከትሎ በሚገኘው ጫካ ውስጥ ስለነበረ የፀሐይ ብርሃን አላገኘንም። በእርግጥ አስቸጋሪ ጉዞ ነበረ።

በዚያ ጫካ ውስጥ የነበሩ ለየት ያሉ ወፎች ግን በድምፃቸውና በውበታቸው የጉዞአችንን አድካሚነት አቅልለውልን ነበር። አስገራሚ የዝማሬ ድምፅ የታደሉት ውብ ወፎች በዚያ አካባቢ ብቻ የሚገኙ መሆናቸውን የተረዳነው በአካባቢው ካገኘናቸው ሰዎች ነበር። የአካባቢው ነዋሪዎች ሓዞ የሚባሉና ከአፋር ጋር የሚገናኙ ጎሳዎች ሲሆኑ የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። እነዚያ ሰዎች ከነፎቹ በልዩ ቀለማት የተዋቡት አንደኛው የወፍ ዝርያ "ሊላይ" እንደሚባልም ነገሩን። የሰዎቹ ቋንቋ ከሳሆ ጋር ስለሚቀራረብ የተግባባነው የአዲ ኢሮብ ተወላጅ በሆነው በደበሳይ አስተርጓሚነት ነበር።

የደበሳይ አገልግሎት በአስተርጓሚነት ብቻ የሚያበቃ አልነበረም፤ ሌላም ልዩ ችሎታ ነበረው። ከርቀት የማየት ችሎታው ከሁላችንም የተለየ ነበር። ከርቀት ሆነን በብዥታ የምናያቸውን ማናቸውንም ነገሮች ለማጥራት የሚጠራው ደበሳይ ብቻ ነበር። እርሱም በርቀት የሚታየውን ሰው ሴት ወይም ወንድ መሆኑን፣ መሣሪያ መያዝ አለመያዙን ጭምር በመለየት ችሎታው ያስደንቀናል። በዚያ ችሎታውም ብዙውን ጊዜ ከሻፌ ወይም አብሪ ሆኖ ይመደብ ነበር። (ከሻፌ ወይም አብሪ ማለት አካባቢውን ለመቃኘት ከሠራዊቱ ፊት ቀድሞ የሚሄድ ቡድን ነው።)

ከሰቢባ ተነሥተን ወደዳሎል የምናደርገውን ጉዞ ቀጠልንና ወደማታ አካባቢ ፈረስ ደጌ ደረስን። ፈረሰ ደጌ ትናንሽ ጎጆዎች የሚታዩበትና ኢሰቡ ተብሎ ይጠራ በነበረው የርዳታ ድርጅት የተሠራ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት

ቤት የሚገኝባት ትንሽ መንደር ነች። ነዋሪዎቿ የአርብቶ አደር ዓይነት የአኗኗር ዘይቤ ይታይባቸዋል። ቡርኩታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየነውና የቀመስነው ፈረስ ደጌ ውስጥ ነበር።

ቡርኩታ የቂጣ ዓይነት ነው። የሚጋገረው ሊጡ በእሳት የጋለ ድንጋይ ላይ ይጠፈጠፍና የጋለውን ድንጋይ መልሶ እሳት ውስጥ በመክተት ነው። ሊጡ በሁለቱም በኩል በእሳት ረመጥ መሀል ይቆይና ከድንጋዩ ሲላቀቅ የደርቀ ቂጣ ይሆናል። ቡርኩታውን ስንበላ በአሠራሩና በጣዕሙ እየተገረምን ነበረ። ገና አግራሞታችንን ሳንጨርስ ሰማዩ በደመና ተሸፈነና ጨላለመ፤ ወዲያውም ከባድ ዝናብ ጣለ። ጊዜው ቀን ቢሆንም መተያየትም አስቸጋሪ ሆኖብን ነበር። በጭጋግ የጠቆረው ሰማይ ገለጥ እስኪል ቆየንና ከጎጆዎቹ ወጥተን አዳራችንን ትምህርት ቤቱ ውስጥ አደረግን።

በማግስቱ ማልደን በመነሣት የዳሎል ጉዟችንን ቀጠልን። ሲነጋጋ አመቺ ቦታ ተመርጦ ለስብሰባ ተቀመጥን። ምስጢር ለመጠበቅ ሲባል የምንሄድበት ተልዕኮ እስከዚህ ስብሰባ ድረስ አልተነገረንም። በዚህ ስብሰባ ላይ ግን መድረሻችን ሳባ ሲሆን ዓላማውም እዚያ በሚገኝ የጨው ቀረጥ መሰብሰቢያ ጣቢያ ላይ እርምጃ በመውሰድ ለሠራዊቱ የሚሆን ገንዘብና መሣሪያ ይዘን መመለስ እንደሆነ ተረዳን።

ቦታውን የሚመራን አንድ አካባቢውን የሚያውቅ ሰው ይዘናል። ከዚያ በኋላ የነበረው እንቅስቃሴያችን በደርግ ኃይሎች ሊሰማ ስለሚችል፣ ጠላት እንዳይዘጋጅ ከሠፍራው እስከምንደርስ ድረስ የምንጓዘው ያለማቋረጥና በፈጣን እንቅስቃሴ ስለሚሆን በተቻለን መጠን በርትተንና ሞራላችንን አጠናክረን፣ ግዳጃችንን እንድንወጣ ተነገረን። የተልዕኮአችንን አፈጻጸም በተመለከተ በርካታ ምክሮች ተቀብለን ወደ ዳሎል በረሐ ዘለቅን።





ከላይ የሚወርደው የፀሐይ ዋዕይና ከአሸዋው ላይ ወደ ላይ የሚነሣው ሙቀት ልክ እንደ ቡርኩታው ከሁለት በኩል ያበስለናል። የምንጓዘው የደረቀ ወንዝ አሸዋማበይ ተከትለን ነበር። በወንዙ መልካ ውስጥ የሚታየው ደረቅ የአሸዋ ንጣፍ ቢሆንም አልፎ አልፎ ውኃ ያቆሩ ቦታዎችም ይገኙበታል፤ ውኃው በጣም ጨዋማ ነው።

በመንገዳችን ላይ አልፎ አልፎ ከምናገኛቸው ሰዎች አብዛኞቹ በግመል፣ በበቅሎና በአህያ ጨው ጭነው የሚመላለሱ ነጋዴዎች ነበሩ። የበረሐ ልምዳቸው ለመጠጥ የሚሆናቸውን ውኃ በስልቻ ሞልተው በከብቶቻው ላይ ጭነው መጓዝን አስተምሯቸዋል። መረጃ ለማግኘት ሰንል ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለን መሄድ ጀመርን። ከእነርሱ ጋር አብረን መሄዳችን ከመረጃው በተጨማሪ፣ ከውኃ ጥም አድኖናል።

ከሦስት ሰዓት በላይ አብረውን ከተጓዙት ነጋዴዎች ጋር የተጀመረው መግባባት እየጨመረ፣ በጫወታ እየተቀራረብን ስንሄድ ቀስ በቀስ ርእሳችን ወደ አካባቢው የጸጥታ ሁኔታና መንግሥት በአካባቢው ስላለው እንቅስቃሴ እየተቀየረ ሄደ። በሚገርም መልኩ ከነጋዴዎቹ አንዱ እጅግ ጠቃሚ የሆነ መረጃ በእጁ እንዳለ ነገረን። ይዞት የነበረውንም የፖስታ መልእክት አሳየን። ፖስታውን ከሰውየው ተቀብለን ለሠራዊቱ አመራሮች ሰጠናቸውና ከፍተው ተመለከቱት።

ፖስታው የተላከው በራሕሌ ወረዳ ከሚገኘው ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ሲሆን የመልእክቱ ይዘትም 'ወንበዴዎች ወደእናንተ አቅጣጫ እየመጡ መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ስለደረሰን፣ ምናልባት ድንገተኛ ጥቃት ሊጥሉ ስለሚችሉ ይህ ደብዳቤ ከደረሳችሁ ጀምሮ ጥንቃቄ አድርጉ። በተቻለን መጠን ተጨማሪ ኃይልና መሣሪያ ልንልክላችሁ እንሞክራለን' የሚል ነበር። ይህም ከእጋመ ወጥተን ወደ ሁለት አውላሎ ያደረግነው እንቅስቃሴ በደርግ ሀይሎች መታወቁን አመላከተ። ከሦስት ሰዓታት ለበለጠ ጊዜ ዝም ብሎ የተጓዘው ይህ ነጋዴ መረጃውን መጀመሪያ ያልሰጠን ሽፍቶች መስለነው ስለነበር ሳይሆን አይቀርም። በኋላ ግን

ማንነታችንንና ዓላማችንን ተረድቶ በእኛ ላይ እምነት በማሳደሩ ሊረዳን ወሰነ። መረጃው እንደተገኘ ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሩም ወታደራዊ ተልእኮውን በፍጥነት ለማካሄድ ወሰነ። በመሆኑም ስድስት ጓዶች፤ ማለትም ሮባ፣ ጌራ፣ ሓዲሽ ዛህላይ፣ አሊጋዝና፣ አረጋይ ያሉበት ቡድን በፍጥነት እንዲጓዝና ቀድሞ በመድረስ ዕቅዱን እንዲፈጽም ተመደበ። የቀረነው አባላት ከኋላ በደጀንነት እንድንከተልና ስንደርስ አስፈላጊ እገዛና ሽፋን እንድንሰጥ ተወሰነ። የቀዳሚው ቡድን አባላት ግልድም ታጥቀው፣ ግመሎችን እየነተቱ የጨው ነጋዴዎችን መስለው ገሰገሱ። እኛ ደግሞ ከኋላ እየተከተልን ጉዞአችንን ቀጠልን፤ የሠራዊቱ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር ሮባ ያመጣው መሣሪያም ሊያዳርሰን ባለመቻሉ ምክንያት ከኋላ ከተከተልነው መካከል መሣሪያ ያልታጠቅንም ነበርን።

ከፈረስ ደጌ ከተነሣን አሥራ ሁለት ሰዓታት አልፈዋል። ከምንጎነጨው ውኃ በስተቀር ያለምግብና ያለምንም ዕረፍት ነበር የተጓዝነው፤ በዚያ ላይ የዳሎል ንዳድ ሐዘኔታ የለውም። እኔ የድካም ስሜት ይታይብኝ ጀምሯል፤ ወደኋላ መቅረት አብዝቻለሁ። የነበርኩበት ጋንታ አዛዥ ጂግሳ መለስ ብሎ ሁኔታዬን ተመለከተና "አማኑኤል! አይዞህ ደርሰናል! ትንሽ ነው የቀረን፤ በርታ!!" ብሎ ሞራል ሰጠኝ። ያለኝን ጉልበት ሁሉ አሰባስቤ ከጓዶቼ እኩል መራመድ ጀመርኩ።

ቀድመው የሄዱት ጓዶች የፌናንስ ፖሊሶች ያሉበት ፍተሻ ኬላ ላይ ሲደርሱ የከፈቱት ድንገተኛ አውቶማቲክ ተኩስ ከኋላ ለነበርነው ተሰምቶናል። እኛ ስንደርስም ተኩሱ እንደቀጠለ ነበር። ጂግሳ፣ ከኋላ የነበርን ሰዎች ከመጀመሪያው ቡድን በስተግራ በኩል ከሚገኘው ጋራ ላይ እንድንወጣ አዘዘ። ጋራውን በፍጥነት ወጥተን ቦታ ቦታ ያዝን። ከጋራው ላይ ወደታች የተሰጠው የሽፋን ተኩስ የጣቢያውን ኃይሎች በማጥቃት አላፈናፍን ሳላቸው፣ መደናገጣቸውና መሸበራቸው ያስታውቃል።





ከኋላ ብዙ ደጋፊ ኃይል እንዳለ በመገመታቸው ይመስላል ብዙ መግፋት አልቻሉም።ፌናንስ ፖሊሶቹ መረታታቸውን ስናውቅ ገና እየተታኮሱ እያሉ የጂግሳን ትዕዛዝ ሳንጠብቅ ወደተኩሱ በሩጫ ሄድን። ጣቢያው አካባቢ ስንደርስ ወታደሮችእጃቸውን ሰጥተው መሣሪያቸውንም አስረክበው ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ሆኖ ደረስን። ትጥቅ ያልነበረን የተማረከውን መሣሪያ ታጠቅን። የተገኘውን ገንዘብና ንብረት ይዘን በመጣንበት ሁኔታ ተመለስን።

ሠራዊቱ ራሱን ለማጠናከር ከወሰዳቸው እርምጃዎች የዳሎል ወታደራዊ ተልእኮ የመጀመሪያው ተግባራዊ ክንውን ነበር። ተልእኮው ከአሊጋዝ መቁሰል በስተቀር ያለብዙ አደጋ ተሳካ። ያ ስኬት ከፍተኛ ኩራትና በራስ የመተማመን ስሜት አሳደረብን። የተሰማንን ደስታ በቃላት መግለጽ ያስቸግራል። ለአሊጋዝ በቅሎ ተገዛና እርሱ በበቅሎ እኛ በእግር ስንሄድ እየተቀላለድንና እየዘመርንም ጭምር ነበር።

በዳሎል ጉዞ በርካታ ንብረት አግኝተናል፤ እነዚህም ማስ ጠመንጃዎች፣ የሕክምና መድኃኒቶች፣ የግሉኮስ እሽጎችና በጥሬ ገንዘብ አስራ ስድስት ሺህ ብር ነበሩ። እኔም ግሉኮስ ምን እንደሆነ ያወቅሁት በዚያ ወቅት ነው ።

ያለዕረፍትና ያለምግብ ያደረግነው ፈጣን ጉዞ አድካሚ ነበረ። በመጣንበት መንገድ ተመልሰን ለግማሽ ሰዓት ከሄድን በኋላ፣ አቅጣጫ ቀይረን ቀኛችንን በመያዝ ለሰባት ሰዓታት በበረሐው ተጓዝን። ሆኖም የተገኘው የተሳካ ድል የፈጠረብን የደስታ ስሜት ድካሙን ሁሉ አጥፍቶት ሙሉ ኃይል ነበረን። ከመነሻችን ጀምሮ በአጠቃላይ ያለዕረፍት የተጓዝነው ለአሥራ ዘጠኝ ሰዓታት መሆኑ ነበር።

ከረዥሙ ጉዞ በኋላ አንድ ትንሽ መንደር ደርሰንና እንድናርፍ ተደረገ። ዕረፍት ከተደረገበት መንደር ሰዎች ጋር ለመግባባት ጊዜ አልወሰደብንም። አንደኛው መኖሪያ ቤት እንድንገባ ተመረጠልን። ነዋሪዎቹ አርብቶ አደሮች ናቸው፣ ያሸረጡት ግልድም ሲሆን እያንዳንዱ ወንድ ጠመንጃ ወይም ጎራዴ አለያም ትልቅ ጩቤ የታጠቀ ነው። በቂ ገንዘብ በእጃችን ስለነበረን ሠራዊቱን የተሻለ ምግብ

ማብላት በመቻሉ ሙከቶች እንዲሸጡልን ጠይቀን አመጡልንና ለማረድ ተዘጋጀን። ይሁን እንጂ ሰዎቹ ሙስሊሞች መሆናቸውን ስለተረዳን እቃዎቻቸው ተነካክተውባቸው እንዳይጸየፉና አብረውንም እንዲመገቡ በማሰብ ሙከቶቹን እነርሱ እንዲያርዷቸው ጠየቅን። እነርሱ ግን በገንዘባችን የገዛናቸውን ሙከቶች ራሳችን አርደን እንድንጠቀም ተከራከሩን። "እኛ እናንተን መምሰል፣ ከእናንተ ጋር መመገብ፣ እንደ ባህላችሁም መሆን ያስደስተናል፤ እናንተ እንደ ባህላችሁና ሀይማኖታችሁ አርዳችሁ አብረን በልተንና ተደስተን መለያየት እንፈልጋለን። ከእናንተ ጋር አንድ ሆነን ስለተግባባሁ ተጫውተን ከመሄድ የበለጠ የሚያስደስተን ነገር የለም" በማለት አጥብቀን ስንነግራቸው የተሰማቸው ልባዊ ደስታ እስከአሁን ይታወሰኛል።

ሙከቶችን አምጥተው አረዷቸውና አብረን አዘጋጅተን በላን። ልንሄድ ስንነሣ እዚያው አልተሰነባበትንም፤ የተወሰነ ርቀት ሸኙንና መልካሙን ሁሉ ተመኝተውልን፣ መርቀውን ተሰያየን። ጉዞአችንን አጠናቀን በሰላም አሲምባ ተመልሰን ገባን።

ትጥቃችን ተጠናከሯል፤ ሞራላችንም ቢሆን ከፍ ብሏል፤ የሌለን መሣሪያ መትረየስ ብቻ ነበር። ወደኋላ የመጡ አዳዲስ ጓዶችም ተጨምረዋል፤ እናም ተአሊም ተዘጋጀ። ሰንገዴ ቋሚ የወታደራዊ ሥልጠና ማዕከል እንዲሆን የተደራጀው ከዳሎል መልስ ነበር። በዚህ ጊዜ የተአሊም (ወታደራዊ ማሠልጠኛ) ሐላፊ ግርማይ ነበር። ይኼኛው ግርማይ ከመሥራቾቹ ጋር የመጣው ሳይሆን ከወሎ ከእነ ሽፈራው ጋር የመጣው ግርማይ ነው። ግርማይ ቋሚ አሠልጣኝ ነበረ። እኛም በአካባቢው በምንሆንበት በማንኛውም አጋጣሚ ጊዜያችንን የምናሳልፈው በወታደራዊ ሥልጠና የተለያዩ ልምምዶችን በማድረግ ነበር። ግደይ የሚያሠለጥነን የፈንጂ ሥልጠና ቀጥሏል፤ ግርማይ ደግሞ ካራቴና ጁዶ፣ ያለድምፅ ሰዎችን ማፈን፣ እንዲሁም ስለላና የመሳሰሉ ጠቃሚ ወታደራዊ ትምህርቶች ይሰጠናል።





እያደር አዲኢሮብን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠርነው፤ ከሕዝቡም በሚገባ ተዋወቅን። ገራይን፣ ኃይለ ማርያምን፣ በየነ ጉራን የመሳሰሉ የአዲኢሮብ ልጆች የሠራዊቱ አባላት መሆናቸው ከሕዝቡ ጋር ለመተዋወቃችን፣ ባህሉንና ቋንቋውን ለመላመዳችን ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ገራይና በየነ ጉራ ስንቅና ትጥቅ ነበሩ።

በተቻለን መጠን ራሳችንን ለመቻል ጥረት እናደርግ ነበር። ለምግባችን የሚሆነውን፤ ጥሬም ቢሆን፤ በገንዘባችን ገዝተን ለማቅረብ እንሞክራለን። ሕዝቡ ባለው አቅም ሁሉ ሊተባበረን ዝግጁ የነበረ ቢሆንም እኛ ግን ሕዝብን ላለማስቸገር የማናደርገው ጥረት አልነበረም። ሕዝብን ከማስቸገር ይልቅ ጾማችንን ማደርን እስከንመርጥ ድረስ እንጠነቀቅ ነበረ። የትግራይ ሕዝብ ለእኛ ድርጅት ያደረገው መሥዋዕትነት ግን ቀላል አልነበረም። ባለው አቅም ሁሉ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ከማቅረብ ወደኋላ ብሎ አያውቅም። ባንጠይቀውም ችግራችንን ያውቅልን ስለነበር ምግብና ውኃ ያቀርብልናል፣ የሚያስፈልገንን መረጃ ይሰጠናል፣ መንገድ ይመራናል፣ ውጊያ ላይ በምንሆንበት ጊዜ ቁስለኞችን በማንሣት ይንከባከባል ወዘተ፤ የትግራይ ሕዝብ ድጋፍ ተለይቶን አያውቅም። በዚያ ጊዜ የሕዝባዊ አርነት ትግራይ ድርጅት በአካባቢው መንቀሳቀስ ጀምሮ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሕዝብ ፊት ስንቀርብ አለመግባባቶች ይከሠቱም ጀምረዋል። ያለመግባባቱን በቀላሉ መፍታት ስንችል አንዳንድ ጊዜ ግን ችግሮች ይፈጠሩ ነበር።

***

## መሬት ለአራሹ

### "የጠፋው በግ ተገኘ"

መሬት መሬት፤ ለ - አራሹ

ለላብ አፍሳሹ፣

ሃገሩ ለባላገሩ፤

ተዋጉለት አትሽሹ

የላብ አደር መንግሥት የምትሹ

ተዋጉለት አትሽሹ

(ተማሪዎች ለመሬት ላራሹ ሲታገሉ ይዘምሩት የነበረ የትግል መዝሙር)

በ1968 ዓ.ም ኅዳር ወር መጀመሪያ አካባቢ ብዙ ወጣቶች ከዳሞ ወደ አሲምባ መጡ ። ዳሞ የሚገኘው በአድዋ አውራጃ ደብረ ዳሞ ተብሎ በሚጠራው ገዳም አካባቢ ሰብአ ዳሞ በሚባል ስፌ ወረዳ ውስጥ ነው። ወጣቶቹ ኤርትራ ውስጥ በላብ-አደርነትና በተለያዩ ሥራዎች ተሰማርተው የነበሩ ናቸው። በወቅቱ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች በጦርነት የአስመራ ከተማን በከበቡበት ጊዜ በርካታ ሕዝብ ተፈናቅሎ ነበረ። ከተፈናቃዮቹ ውስጥ ከፊሉ ወደ ትውልድ አካባቢው ሲገባ ከፊሉ ደግሞ ወደየድርጅቶቹ ተቀላቀለ። የትግራይ ልጆች የሆኑት ወጣቶችም ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ሲመለሱ ኑሮአቸውን የሚቀጥሉበት መንገድ መፈለግ ነበረባቸው። የአካባቢው ዋነኛ የሥራ መስክ ደግሞ ግብርና ነው። የሚያርሱት መሬት ጠይቀው ማግኘት አልቻሉም።

ወጣቶቹ ሌላ የሚተዳደሩበት መንገድ አጥተው ግራ ተጋቡ። በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሳሉ መሬት ለአራሹ መሆን እንደሚገባው የሚያምን ሠራዊት መኖሩን





ሲሰሙ ነበር ወደ እኛ የመጡት። አሲምባ እንደደረሱ ከዳሞ መምጣታቸውንና ችግራቸውን ተናግረው፣ መሬት እንድናካፍላቸው ጠየቁን። ሠራዊቱ ከዚያ በፊት ወደ ዳሞ ለመሻገር ተንቀሳቅሶ እንደማያውቅና ድርጅታዊ ሥራ ባልተሠራበትና ግንኙነት ባልተዘረጋበት አካባቢ መሄድ አስቸጋሪ እንደሚሆን ለማስረዳት ሞከርን። ወጣቶቹ ግን የሚቀበሉ አልነበሩም።

"ስለጸጥታው የሚያሳስባችሁ ነገር አይኖርም፤ እኛ አብረናችሁ አለን። የአካባቢው ተወላጆች ስለሆንን ሕዝቡንም ሆነ አካባቢውን እናውቀዋለን። ወደእናንተ የመጣነው መሬት ለሁሉም እኩል መሆኑን የምታምኑና ለዚያም የምትታገሉ መሆናችሁን በመስማታችን ነው" በማለት ተከራከሩን። "አይቻልም" ማለት አስቸጋሪ ፈተና ስለሆነብን ሙከራ ለማድረግ ተስማማን።

መንገዱን እነርሱ እየመሩን ጉዞ ጀመርን። ከዛላ አንበሳ ወደ አዲግራት የሚወስደውን ጥቁር አስፋልት ስንሻገር፣ እኛ መሣሪያ ይዘን እነሱ ደግሞ በትር፣ ጨቤና ፋስ ይዘው በግራና በቀኝ አጅበው ሽፋን ሊሰጡን ይጠብቁ ነበር። በመጀመሪያ የገባነው ከደብረ ዳሞ በስተሰሜን በኩል በምትገኝ አንድ መንደር ነው። ሕዝቡን ሰብስብንና ከመሬት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ካነሣን በኋላ "መሬት የሁሉም ስለሆነ መከፋፈል አለባችሁ" አልናቸው። በስብሰባው ላይ ሕዝቡን ያነጋገሩት የቅስቀሳ፣ የማስተማርና የማሳመን ልምድ ያላቸው እነ ሐረጎትና ግደይ ነበሩ። ሠራዊቱ እዚያ ቦታ የተገኘበትን ዓላማ ለመግለጽ ንግግር በተደረገበት ወቅት ሕዝቡ በጭብጨባና በእልልታ ተቀበለው። በዚያን ጊዜ የደብረ ዳሞ ገበሬዎች የተለያዩ የመሬት ችግሮች ነበሩባቸው። የመሬቱን ሲሶ ያህል የያዘው ገዳሙ ሲሆን ሀራኔ ተብለው የሚጠሩ የእያት የቅድመ አያት ወራሾች የሆኑ የመሬት ባለቤቶችም ነበሩ።

"እነዚህ ሰዎች ተወልደው ያደጉት በዚህ ቦታ ነው። ለመኖር ወደሌላ አካባቢ መሄድ ግድ ቢሆንባቸው ነበር የተሰደዱት። በሄዱበት አካባቢም ችግር ላይ ስለወደቁ መሄጃ ቢያጡ፣ ወደ ተወለዱበትና ወደ አደጉበት አካባቢ ከመመለስ ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም። "ያሳደገን ሕዝብ ጥሎ አይጥለንም" ብለው ቢመለሱም እዚህ ደግሞ ከእርሻ ሌላ የሚተዳደሩበት ሥራ የለም። ለማረስ ደግሞ መሬት ያስፈልጋቸዋል፤ መሬት ማግኘት አለባቸው። "አናውቃችሁም" እንዳትሏቸው፣ አሳድጋችኋቸዋል። "አርሰን እንብላ" ሲሉ የጋራ መፍትሔ መፈለግ እንጂ፣ መሬት መከልከል ትክክል አይሆንም። ልጆቻችሁ ናቸው። ስለዚህ መሬት አካፍላችኋቸው፤ አብራችሁ መኖር አለባችሁ" ሲባል ህዝቡ ተስማማ። ይህን የሚያስፈጽም የገበሬ ማኅበር ለማቋቋም ሸንጎ እንዲያደርጉ፣ ሊቀ መንበር እንዲመርጡና በጋራ ወስነው መሬት እንዲከፋፈሉ የቀረበላቸውን መፍትሔ በደስታ ተቀበሉ። ሠራዊታችን መሬት የማከፋፈል ሥራ የጀመረው በእንዲህ ያለው አጋጣሚ ነበረ።

ይህንን ፈጽመን ከዳሞ ወደ አሲምባ ስንመለስ አሲምባ አካባቢ ያለው ገበሬ ተመሳሳይ ጥያቄ ማንሣት ጀመረ። "እኛን አልፋችሁ ዳሞ፣ አድዋ ሄዳችሁ ልታካፍሉ የቻላችሁበት ምክንያት ምንድነው?" የሚል ወቀሳ አዘል ጥያቄ ተከተለ። የዳሞ መሬት የማከፋፈል ወሬ በአሲምባ አካባቢ ብቻ አልተወሰነም፤ የሌሎች አካባቢዎች ገበሬዎችም ጥያቄውን አስፋፉት።

ሠራዊቱ የብዙኃን ድርጅቶችን ማቋቋም የጀመረው ከዚህ በኋላ ነበር። ሕውሐትም የብዙኃን ድርጅቶችን ማቋቋም ስለጀመረ አንዳንድ መንደሮች ላይ መገናኘት ተዘወተረ። አንዳንዴ በመካከላችን ችግር ቢፈጠርም፣ ሰላማዊ መፍትሔ ለመስጠት ሙከራዎች ይደረጉ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሕዝቡ ለስብሰባ ይጠራና እንዲያስተዳድረው የሚፈልገውን ድርጅት እንዲመርጥም ይደረጋል። ድምፅ





የሚሰጠው ሁለቱም ድርጅቶች ባሉበት ሲሆን የአንድ ድምፅ ብልጫም ቢሆን የሕዝቡን ውሳኔ መቀበል ግድ ነበር። በዚህ ሁኔታ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ የማደራጀት ሥራ በሰላም እንዲፈታ ይደርግ ነበር። ኢሕአሠ በተቆጣጠራቸው በሁሉም ቦታዎች የመሬት ማከፋፈል ሥራ ተግባራዊ ተደርጎ ነበር።

***

## የጎንደር ሕክምና



ሚያዚያ 3/1968 ዓ.ም ጎንደር
ለህክምና በመጣሁ ጊዜ

....ፍፁም ነው እምነቴ

የትግሉ ነው ህይወቴ

ልጓዝ በድል ጎዳና

በወደቁት ጓዶች ፋና....

(የኢህአፓ መሪ መዝሙር)

"ፊልም የማየት ዕድል ሳይገጥመኝ በረሐ ገባሁ፤ ጎንደር አብሮ አደጌን አግኝቼው ሲኒማ ጋብዞኝ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ብገባ "የኢምፔሪያሊዝም ፊልም ሆኖብኝ ጥዬ ወጣሁ" የባለታሪኩ የግል ገጠመኝ

ታኅሣሥ ወር መጨረሻ አካባቢ ከአሲምባ በስተ ምዕራብ በሚገኙ አካባቢዎች የፕሮፓጋንዳ ሥራዎች ሠርተን ወደ አሲምባ ስንመለስ የጀብሃ የጸጥታ ምክትል ዋና ሐላፊ የነበረው ሃዲሽ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አንድ የኃይል መሪና አንድ ሐኪም ይዞ ወደ አሲምባ መጣ። ሃዲሽ ወልደ ጊዮርጊስ ቀጭንና ረጂም ጠቆር ያለና ጉንጮቹ በጺም የተሸፈኑ ናቸው። ሃዲሽ መልካም ሰው ሲሆን ከጀብሃ አመራር መካከል ኢሕአፓን የሚደግፍና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበጅ ድርጅት ነው ብሎ የሚያምን ሰው ነበር። የጀብሃው ቡድን የመጣበት ምክንያት ከኢሕአሠ ጋር በመነጋገር በአዲግራት ከተማ ውስጥ በነበረው የደርግ ኃይል ላይ የጋራ የጥቃት እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል ነበር። ጥቃቱ የሚደረግበት ጊዜ በገና በዓል ቀን እንዲሆን ተወሰነ። ዕለቱ የተመረጠውም በበዓሉ ምክንያት ወታደሩ ይዝናናል፣ ጠላት ይመጣብኛል ብሎም ስለማያስብ ይዘናጋል ተብሎ ስለተገመተ ነበረ። ሃዲስ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ፀሐዬ፣ ሮባና ጸጋዬ ደብተራው ከሕዝቡ ጋር





የሚያመሳስላቸው ልብስ ለብሰው ወደ አዲግራት በመሄድ በጦሩ ካምፕና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጥናት ሲያደርጉ ሰንብተው ተመለሱ።

አዲግራትን የሚያውቁና የአዲግራት ተወላጅ የሆንን የሠራዊቱ አባላት ደግሞ የከተማዋን ቁልፍ ቦታዎች የሚያመላክት ካርታ እንድንሠራ ተነገረን። ፖሊስ ጣቢያ፣ሆስፒታል፣ እስርቤት፣ ባንክ ቤትና ሌሎችንም አስፈላጊ ተቋማት የሚገኙበትን ሥፍራ የሚያሳይ ካርታ እንዲሁም ስለጦር ካምፑ የምናውቀውንና የምናስታውሰውን እየተነጋገርን በካርታው ላይ ለማስፈር እንድንችል ሰብቻችን ተለይተን ለሦስት ቀናት ሰነበትን። ያዘጋጀነውንም ካርታ አመራሩ ተወያይቶበታል።

አንዳንድ ጊዜ ሃዲሽ ወልደ ጊዮርጊስ ጀብሃ ኤርትራ ውስጥ ስለ ፈጸመው ጀብዱ፣አንዳንድ ቦታዎች ላይ ስላካሄዱት ወታደራዊ ተልእኮ፣ ለምሳሌ ባንኮች እንዴት እንደዘረፉ፣ መኪናዎች እንዴት ከከተማ ሲያወጡ እንደነበረ፣ የደርግ ሰላዮችን እንዴት አድርገው ሲገድሉ እንደነበር ያወራናል። ጀብሃ በስንት ሰዎች እንደተመሠረተና አሁን ያለበትን ሁኔታና የመሳሰሉ ነገሮችን ሲተርክልን ተመስጠን ነበር የምንሰማው። ሃዲሽ አማርኛና ትግርኛ አቀላጥፎ ይናገራል። "እኔ የሰላም ሰው አይደለሁም ፤ የትግል ሰው ነኝ ኤርትራ ነጻ ብትወጣም ፍልስጥኤምም ቢሆን ሄጄ እዋጋለሁ እንጂ ከኤርትራ ነጻነት በኋላ ቁጭ እልልም" ይል ነበር ሃዲሽ።

ብዙ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የአዲግራቱ ወታደራዊ ተልእኮ መሰረዙ ተወራ። አንድ የጀብሃ ኃይል ለዚሁ ጥቃት መጥቶ መነኩሲቶ እጠገብ (ኤርትራና ትግራይ ድንበር) መድረሱም ተሰምቶ ነበር። ጥቃቱ መሰረዙን የሰማነው በተባራሪ ወሬ ደረጃ ሲሆን ደርግ የእነርሱን ወደ አካባቢው መንቀሳቀስ በማወቁ እየተዘጋጀ ስለሆነ ገብቶ ለማጥቃት አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩን ነበር። በኋላ ላይ ሃዲሽ በጦርነት ላይ መሠዋቱን ሰምተናል፤ ከእርሱ ሞት በኋላ ከጀብሃ ጋር የነበረን ግንኙነት ጥሩ አልነበረም።

በጥርና የካቲት ብዙውን ጊዜ ያሳለፍነው ሕዝብ በማደራጀት፣ ብዙኃን ድርጅቶችን በማንቀሳቀስ፣ መሬት በማከፋፈልና በመሳሰሉ ሥራዎች ነበር።

ያን ጊዜ የጽሕፈት መኪና ስላልነበረን ክፍለ ዜና አልነበረም። የክፍለ ዜናው መቋቋም ግን አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። እናም አንድ ጋንታ የጽሕፈት መኪና ለማምጣት ተልእኮ ተሰጥቷት ወደ ውቅሮ ልትሄድ ተዘጋጅታለች። በዚህ ጊዜ፣ ሙሴና ሰለሞን የሚባሉ ከመነኩሲቶ መጥተው ከኛ ጋር የተቀላቀሉ ሁለት ኤርትራውያን ነበሩ። ለእነርሱ የኢሕአሠ ሠራዊት ወታደራዊ እንቅስቃሴ አለማድረጉ አላስደሰታቸውም ነበረ። እነዚያ ሰዎች እኔንና ዳዊት ወድቀሺን (ዳዊት ወድቀሺ፣ እውነተኛ ስሙ ብርሃነ በርሔ ይባላል) ስለሚያውቁንና ስለሚቀርቡን አንድ ቀን "እናንተ የማትዋጉ ከሆነ ወደሀገራችን መሄድ ይሻለናል፤ የኤርትራ ድርጅቶች ብዙ ጊዜ ውጊያ ስለሚውሉ ከእነሱ ጋር እንሰለፋለን" አሉን። ጥቂት እንዲታገሱ ብንነግራቸውም ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተው ጠፍተው ወደ አገራቸው ሄዱ። ያን ጊዜ የጀብሀና የእኛ ሠራዊት አመራሮች ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው። ታዲያ በዚያኑ ሰሞን ነበር ሀዲሽ ወልደ ጊዮርጊስ እኛ ዘንድ ሰንብቶ የተመለሰው። ጠፍተው የሄዱት ሰዎች ወደ ጀብሃዎች ሲሄዱ አስረው አቆዩአቸውና፣ "ከናንተ ሸሽተው የመጡ ሁለት ልጆች ስላሉ መጥታችሁ ውሰዷቸው" ብለው መልእክት ላኩ። እስረኞቹን ከነንብረታቸው ለእኛ ሠራዊት አስረከቧቸው። የመረመራቸው ኃይሌ ቀጭኑ ነበር፤ ለምርመራው የሚሆን ጉድጓድ አስቆፈራቸውና አስገባቸው። ጉድጓድ እንዲቆፍሩ የተደረጉት ለማስፈራራትና እውነቱን እንዲያወጡ ለማድረግ ነበር። ጉድጓዱን ቆፍረው ሲጨርሱ "ስትጠፉ ለማን ነግራችሁ ነበር?! የነገራችኋቸውን ሰዎች በግልጽ ካልነገራችሁኝ እዚሁ ትገደላላችሁ!" ብሎ አስፈራራቸው።





"የማንገደል ከሆነ እውነቱን እንናገራለን" ብለው "ለአማኑኤልና ለዳዊት ነግረናቸዋል" አሉት።

"ለእነርሱ ስትነግሯቸው ምን አሏችሁ?" የኃይሌ ቀጭኑ ተከታይ ጥያቄ ነበር።

"ጥቂት እንድንታገስ ነገሩን፤ እኛ ግን እንቢ አልናቸውና ሄድን። የምንጠፋበትን ቀን ግን አልነገርናቸውም" አሉት። ኃይሌም ከጉድጓድ አስወጣቸው። "አሁን ነጻ ናችሁ፤ መቆየት ካልፈለጋችሁም አትገደዱም" ተብለውም ወደ ሀገራችው ተላኩ። ድርጅቱን የሚለቁ ሰዎች ሠራዊቱ የሚቆጣጠረውን መሬት ለቀው በሰላም መውጣታቸውን ማረጋገጥ ግዴታ ነበር።

ዳዊት በዚሁ ጉዳይ የተነሣ ሂስ ቀረበበትና ወቀሳውን አመነ። በመሆኑም እርሱ የነበረበት ጋንታ አባላት የማተሚያ መሣሪያዎች ለማምጣት ወደ ውቅሮ ሲሄዱ፣ እሱ በቅጣት ትጥቅ እንዲፈታ ተወሰኖበት፣ ድስት እንዲሸከም ተደረገ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ውቅሮ የሄዱት ጓዶች ከአንድ ትምህርት ቤት ታይፕራይተር፣ ማባዣ፣ ገንዘብና ሌሎች ቁሳቁሶች ይዘው ተልእኳቸውን ሙሉ በሙሉ አሳክተው ተመለሱ። ክፍለ ዜና፣ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ቡድን ተመሥርቶ ጽሑፎችን ማተም የተጀመረው ከዚያ በኋላ ነበር።

እኔ በዚያን ወቅት ከዘላለምና ከሐዋዝ ጋንታ ጋር አሲምባ ቀርቻለሁ። ሐዋዝ መጣና "አንድ ጊዜ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ" አለኝ። ፈቃደኝነቴን ገለጽኩለትና አንድ ጥግ ይዘን ቁጭ አልን።

"ሙሴና ሰለሞን ወደ አገራቸው ሲሄዱ ነግረውህ ነበር?" ብሎ ጠየቀኝ።

"አዎ" አልኩት ሳላመነታ።

መልሴን እንደሰማ ኩትኩት ብሎ ሳቀና "ታዲያ ለምን አልነገርከንም?" አለኝ።

"አንደኛ ብረት ይዘው ይሄዳሉ ብዬ አላሰብኩም፣ ሁለተኛ ደግሞ ወደ አገራቸው መሄድ ከፈለጉ ምን ማድረግ ይቻላል? ብዬ ስላሰብኩ መናገሩ ጠቀሜታ ያለው አልመሰለኝም" አልኩት፣ ሐዋዝ አሁንም ይስቃል።

ሐዋዝ እንዲያነጋግረኝ የላከው ዘላለም እንደነበረ የተረዳሁት በኋላ ነው። የጋንታው የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ሐዋዝ ነበር። በደንቡ መሠረት ሊያናግረኝ የሚገባው ሐዋዝ በመሆኑ ዘላለም በቀጥታ ሊያነጋግረኝ አልቻለም። ሐዋዝና ዘላለም በጣም የሚቀራረቡ ጓደኛሞች ነበሩ፤ በኋላ ዘላለም መጣና "ምን አለ?" አለና ሐዋዝን ጠየቀው።

"እዎ! ነግረውኛል ብሏል፤ አምኗል።" አለው።

"አንተ የሞትክ! ደግሞ ታምናለህ እንዴ?! ልትቀጣ፤ ልትባረር፣ ጫን ሲል ደግሞ ልትገደልም ትችላለህ፤ ሰው ልከዳ ነው ብሎ ሲነግርህ ለድርጅትህ አታስታውቅም እንዴ? ድርጅቱ 'የዚህን ልጅ ነገር ምን እናድርግ? በሽተኛ እየተባለ እስከመቼ ድረስ በመገለል ይቆያል? ማሳከም ይገባናል።' እያለ ስለአንተ ይጨነቃል፤ አንተ ግን ስለድርጅቱ ግዴለህም" ብሎ በሐዋዝ ፊት ገሠጸኝ።

"በቃ አንተ ሂድ፣ እኔ አነጋግረዋለሁ" ብሎ ዘላለምን እንዲሄድ ካደረገው በኋላ ሐዋዝ በእንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ምን ማድረግ ይገባኝ እንደነበረ ዘርዘር አድርጎ አስረዳኝ። " 'እሄዳለሁ፣ እጠፋለሁ' የሚል ሰው ሲነግርህ፣ ለድርጅቱ ማስታወቅ አለብህ። የሚከዳ አባል መሣሪያ ይዞ ቢሄድ ይጎዳናል፣ ጠላት እጅ ገብቶ ምስጢር ሊያወጣ ይችላል፤ ለስለላ ያጋልጠናል። የሚከዳ አባል፣ ብዙ ችግር ሊያመጣ ስለሚችል ድርጅታችንን ለአደጋ ያጋልጣል። ስለዚህ የሚጠፋ ወይም የሚከዳ ሰው ካማከረህ ወይም ከተጠራጠርክ ለድርጅቱ ማስታወቅ አለብህ" በማለት በተረጋጋ መንፈስ አስረዳኝ።

ሐዋዝ በጣም ግሩም ሰው ነበር። በመጀመሪያም በነበርኩበት ጋንታ ውስጥ የተመደበልን የፖለቲካ ሐላፊ እርሱ ነበር። ወሎ እስከምንሄድ ድረስ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊያችን እርሱ ሆኖ ቆየ። ሐዋዝ፣ የተረጋጋ፣ አስተሳሰቡ





በጣም ሰፋ ያለና የበሰለ፣ ዘወትር ማንበብና መጻፍ የሚወድ ጓድ ነበር። ሁል ጊዜም አንድ መንደር ስንይዝ እርሱ በዛፍ ጥላ ስር ለብቻው ተቀምጦ የትንባሆ ማጨሻ ፒፓውን በትንባሆ ይሞላና ወይ ያነባል አለያም መጻፍ ይጀምራል። እያጨሰ ማንበብና መጻፍ ልምዱ ነበር። የሚሸከመው ሻንጣው ሁል ጊዜም በመጽሐፍ እንደተሞላ ነበር። የምግብ ጊዜ ሲደርስ ከንባቡ ወይም ከጽሑፉ ላይ እየተጠራ ነበር የሚመጣው። ሐዋዝ ሰውነቱ ግዙፍ ሲሆን የሚያበሩና የሚያምሩ ዓይኖቹ እንዲሁም ሰልካካ አፍንጫው መልከ መልካም፣ ከሚባሉት ጎራ ያስገቡታል። ጸጉረ ሉጫና ብዙ ጊዜ ፈገግታ የማይለው ነጻ ሰው ነበር።

***

የሠራዊቱ አመራር በመጋቢት ወር 1968 ዓ.ም መታከም እንደሚገባኝ ውሳኔ አሳለፈ። ተጠራሁና ሁለት አማራጮች ቀረቡልኝ። አንደኛው አማራጭ በጀብሀ በኩል ወደ ሱዳን መሄድና ከሰላ ታክሞ መመለስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እዚሁ አገር ቤት ውስጥ እንድታከም ሁኔታዎች ማመቻቸት ነበሩ። አስቤበት ምርጫየን እንዳሳውቅ ተነገረኝ። ዘላለምን አማከርኩት። አሁን ያለህ የፖለቲካ ንቃት በጣም ዝቅተኛ ነው። ሕክምናህ ምናልባትም ብዙ የሚያቆይ ሊሆን ይችላል፤ ብዙ ካቆየህ ደግሞ በትግሉ ውስጥ የበለጠ ድርሻ እንዲኖርህ እግረ መንገድህን የፖለቲካ ዕውቀትህን ማጎልበት ይኖርብሃል። ሱዳን፣ ከሰላ ብትሄድ የፖለቲካ ንቃትህን የበለጠ ለማሻሻል ያለው ዕድል ጠባብ ይሆናል። አገር ውስጥ ከታከምክ ግን ከሰዎች ጋር የመገናኘትና መጻሕፍት የማግኘት እድልህ ሰፊ ይሆናል፤ እናም እንብበህ የበለጠ አውቀህ ልትመለስ ትችላለህ፣ ስለዚህ አገር ቤት ይሻልሀል" አለኝ። እኔም ዘላለም ያለኝን ተቀብዬ አገር ውስጥ መታከም እንደምመርጥ ነገርኳቸው።

ለሕክምና የምላከው ወደጎንደር መሆኑ ተነገረኝና ዝግጅቱ ተጀመረ። በቅጫምና በቅማል የተወረረው ጸጉሬ ለሁለትና ሦስት ቀናት ዘመቻ ተደርጎበት ንጹሕ መሆን ቻለ። ሐዋዝ "የእድዋ ዘመቻ ጣቢያ ዘማች ተማሪ" የሚል ማኅተም ያለበት መታወቂያ ወረቀት፣ እንዲሁም ለመጓጓዣና ለአንዳንድ አስፈላጊ ወጪ የሚውል 150 ብር ሰጠኝ። ጎንደር ስገባ የማገኘው ሰው አለባቸው እንደሚባል፣ የምንገናኝበት የሦስት ቀናት ተለዋጭ የቀጠሮ ቀናትና ሰዓታት፤ የምስጢር ቃል እንዲሁም ቦታ ተነገረኝ። ከዚያ ብኋላ ከአሲምባ አካባቢ የሚሸኙኝ ሁለት ሰዎች ተመደቡልኝና የጎንደር ጉዞዬን ጀመርኩ።





ሸኚዎቼ ብዙት ለመድረስ ጥቂት እስኪቀር አብረውኝ ነበሩ። ከብዙት በኋላ አውቶብስ ተሳፍሬ ወደ ጎንደር መጓዝ እንዳለብኝ አውቄአለሁ። ብዙት ስሄድ የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለነበር አካባቢውን አላውቀውም፤ መጠየቅ ነበረብኝ። ብዙት ከተማ ከመግባቴ በፊት አንድ ወንዝ አገኘሁ። እጄንና እግሬን እየታጠብኩ ጥቂት ቆየሁና ራሴን አረጋግቼ፣ ቀስ ብዬ ወደከተማው ገባሁ። የገባሁት በከተማው በስተ ሰሜን ወደ እድዋ በሚወስደው ዋና መንገድ በስተምዕራብ በኩል ነበር። ወደውስጥ ዘለቅሁ፤ ከፊት ለፊት አንድ ጠላ ቤት አየሁና ወደዚያው አቀናሁ። ቤቱ ውስጥ በርከት ያሉ ሰዎች ነበሩ። ገብቼ ግራና ቀኝ ተመለካከቼ ተቀመጥኩና ጠላ አዘዝኩ። የቀረበልኝን ጠላ ፉት እያልኩ የት እንደማድር ሳሰላስል በሐሳብ ርቄ ሄጄ ነበረ። በድንገት ፖሊሶች ጠላ ቤቱ ውስጥ ገቡ፤ የመጡት በደጎና ያለመሆኑ ያስታውቃል።

ሆኖም ፖሊሶቹ እኔን ፈልገው ይመጣሉ የሚል ጥርጣሬ አልነበረኝም። ሳያቸው ግን ፈራሁ፤ የፈራሁት ጦሱ ለእኔም እንዳይተርፍ ሰግቼ ነበር። ግምቴ ግን ልክ አልነበረም፤፤ አንደኛው ፖሊስ "ናውጣ!" ሲለኝ ነበር እኔን ፈልገው መምጣታቸው የገባኝ። "ምን አደረግሁ? ምን ያጠፋሁት ነገር አለ?" ብዬ ተረጋግቼ ጠየቅኳቸው።

"ማንነትህና ከየት እንደመጣህ የማይታወቅ ስለሆነ ማንነትህን እስከናረጋግጥ ድረስ ወደ እስር ቤት ትሄዳለህ" ብለው ይዘውኝ ሲወጡ ቤቱ መከበቡን ተመለከትኩ። ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱኝ። እስር ቤት አስገብተውኝ ብዙም ሳልቆይ "ሽፍታ ተያዘ" የሚል ወሬ ተሰምቶ ኖሮ የከተማው ሕዝብ እኔን ለማየት ግልብጥ ብሎ መጣ። ከእስር ቤት ወደ ምርመራ ክፍል ተወስጄ የጣቢያው መቶ አለቃ በጥያቄ ያፋጥጠኝ ጀመር።

"ከየት ነው የመጣኸው?" አለና፣ መቶ አለቃው አፈጠጠብኝ።

“እንግዲህ እውነትህን ከሆነ፣ ተጠርተው ይመጣሉ” አለና ወደ አከስቴ ቤት መላከተኛ ላከ። አከስቴ ተጠርተው በአንድ በኩል ሲመጡ ባለቤታቸው ደግሞ በሌላ በኩል ከተፍ አሉ።

አከስቴ ሲያዩኝ “በኖርኩበት ሀገር እንዴት የእኅቴ ልጅ ይታሰራል?!” ብለው ጭንቅላታቸውን ይዘው ጮሁ።

“እትዬ ምስጋድ፣ በፍጹም የእርስዎ ዘመድ መሆኑን አላወቅሁም። ገና አሁን እኮ ነው የነገረኝ” አለ፣ መቶ አለቃው።

“በይ፣ አንቺ ወደቤት ሂጂ፤ ሁሉንም ነገር እኔ እጨርሳለሁ” አሉ ግራዝማችም ጥቂት ሲያዳምጡ ቆይተው ።

አከስቴ “በፍጹም እዚህ ትቼው አልሄድም ብለው አንገራገሩ። ግራዝማች እንደምንም ብለው አከስቴን አሳምነው ሸኟቸው። ከተሸኙ በኋላ ብዙም አልቆየንም ዋስትና ፈርመው አስፈቱኝና ወደ ቤታቸው ይዘውኝ ሄዱ።

እቤት ከገባን በኋላ ጥያቄዎቻቸውንና ጨዋታቸውን በሰፊው ቀጠሉ። የእኔ ሐሳብ ግን ጨዋታው ላይ አልነበረም። ምን ሰበብ ብፈጥር ላሳምናቸው እንደምችልና በሰላም ተለያይተን እንዴት አድርጌ የጎንደር ጉዞዬን እንደምቀጥል ነበር የማስበው። የሚያዋጣኝ እውነቱን መናገር ብቻ መሆኑን አመንኩበት። በጫወታ መሀልም ከበረሐ እንደመጣሁና በዓላማዬ መሠረት፣ ጉዞዬን መቀጠል እንደምፈልግ ነገርኳቸው። የሰሙትን ማመን አቃታቸው፤ ወደበረሐ ተመልሼ እንዳልሄድ ሁለቱም መከሩኝ። በሰላማዊ መንገድ ልኖር የምችልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻቹልኝ በመግለጽ ወደ መደበኛ ሕይወቴ እንድመለስ ለመኑኝ። “እኔ ከመንግሥት አስታርቅሀለሁ። በሰላም ትምህርትህን ብትቀጥል ይሻልሀል” እያሉ ደጋግመው ወተውቱኝ ግራዝማች።





“በጭራሽ አይሆንም፤ የተላከሁበትን ጉዳይ መፈጸም ይኖርብኛል። እናንተ ብቻ ለማንም አትናግሩ፤ እኔ ብዙ አላስቸግራችሁም። ነገ በጠዋት አውቶብስ ተሳፍሬ እሄዳለሁ” ብዬ ድርቅ አልኩ። እነሱም ሁኔታዬን አይተው እንደማልቀበላቸው አወቁ። የግዳቸውን በመሄዴ ተስማሙና “እንደመሰለህ” አሉ አከስቴ ዕንባቸውን እየጠራረጉ። ሌላ ቦታ እንደዚያ ዓይነት ችግር እንዳይገጥመኝና እንዳልያዝ በጣም መጠንቀቅ እንደሚገባኝ መከሩኝ።

ጠዋት ሁለቱም ተነሥተው፣ ስመውና መርቀው ሸኙኝና በሀጂ አብዶ አውቶብስ ተሳፍሬ ሽሬ ገባሁ። ከአዲግራት ሌላ የትም ሄጄ ስለማላውቅ፣ ሽሬ እንዳ ስላሴንም ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ያየሁት። ሽሬ ከአውቶብስ ከወረድኩ በኋላ አካባቢውን እየቃኘሁ ወዲያ ወዲህ ስል፣ አንድ ሱቅ አየሁና ገብቼ እቃ ጠየቅሁ። ባለሱቁ ግን ለጥያቄዬ መልስ የሚሰጥ መስሎ ጠጋ አለና “አንተ፣ ለዚህ ከተማ እንግዳ ነህ መሰለኝ? ይህን አውቀው ፖሊሶች እየተከታተሉህ ነውና የምትሄድበት ቦታ ሄደህ ዐርፈህ ብትቀመጥ ይሻልሀል” አለና አስደነገጠኝ። አመስግኜው፣ ከሱቁ ወጣሁ። እዚያው አካባቢ ወደአገኘሁት ሆቴል ገባሁና አልጋ ጠየቅሁ። “መታወቂያህን አምጣ” አለኝ አልጋ አከራዩ ከእግር እስከራሴ እየተመለከተኝ።

ሐዋዝ ያዘጋጀልኝን የዘማች መታወቂያ ሰጠሁት። አላጉላላኝም፤ የውስጤን ጭንቀት የተረዳልኝ መሰለኝ። የተከራየሁትን ክፍል አሳየኝና ገባሁ። የባለሱቁን ምክር እያሰብኩ ተመልሼ ሳልወጣ አደርኩ። በማግሥቱ በጠዋት ተነሥቼ ወደ አውቶብስ ተራው ሄድኩና ወደጎንደር የምጓዝበትን ትኬት አስቆርጬ እንደገና በሀጂ አብዱ አውቶብስ ተሳፍሬ ጎንደር ገባሁ። ጎንደርን ያየሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም፣ እዚያ የሚኖሩ እኅት እንዳሉኝ አውቃለሁ። ብዘትም ላይ ከጉድ የወጣሁት የአከስቴን እዚያ መኖር በማወቁ ነበር። ጎንደር ውስጥ እንዳገኘው የተነገረኝም ሰው በመኖሩ ለአደጋ የመጋለጤ አጋጣሚ ካለፍኳቸው ከተሞች የተሻለ እንደሆነ ተሰምቶኝ ትንሽ ዘና እንድል አድርጎኛል።

ከአውቶቡስ ተራው ወጣሁና በስተቀኝ በኩል ያለውን መንገድ ተከትየ ጥቂት ሄድኩ። የጎንደር ከተማ መታወቂያ የሆኑት ጃንተከል ዋርካና የፋሲል ግንብ ከፊት ለፊቴ ታዩኝ። እዚያው አካባቢ አንድ ሆቴል አገኘሁና አልጋ ያዝኩኝ። ጃንተከል አጠገብ ከመድረሴ በፊት በስተግራ በኩል አክሱም ሆቴል የሚባለውን ለምልክት ልብ ብዬ አይቼዋለሁ።

ጎንደር ውስጥ የመጀመሪያውን ምሽት ያሳለፍኩት ከተከራየሁት ሆቴል ሳልወጣ ነበረ። በሁለተኛው ቀን አለባቸውን ወደማገኝበት ወደ ኢትዮጵያ ሆቴል አመራሁ። ልክ በቀጠሮአችን ሰዓት ከሆቴሉ በስተግራ በኩል ጠበቅሁት፤ አለባቸው አልመጣም። የአጎቴ ሹራብ ቤት ያለው ከነበርኩበት ቦታ ፊት ለፊት ስለሆነ እንዳያገኙኝ መጠንቀቅ ነበረብኝ። ተመለስኩና ወደ አደርኩበት ሆቴል ገባሁ። አለባቸውን በመጀመሪያው ቀጠሮ ባለማግኘቴ ብዙም አልተደናገጥኩም፤ ብዙም ሳልጠብቀው ተመለስኩ። በሚቀጥለው ቀን ባለን ተለዋጭ ቀጠሮ እንደማገኘው ተስፋ አድርጌ ወደ ሆቴሉ ቡና ቤት ገባሁና ቁጭ አልኩ። ሆቴል ገብቼ ገና ተመቻችቼ ሳልቀመጥ ደግሞ የሆቴሉ አስተናጋጅ መጥቶ "ውጪ ሰው ይፈልግሀል" አለኝ።

"ማንን፣ እኔን?" ደንገጥ ብየ ጠየቅሁ።

"አዎን፣ አንተን!" አለኝ በእርግጠኝነት።

አሁንም ችግር ውስጥ ልገባ መሆኑ ተሰማኝ፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ገብቶኛል። የተለያዩ ሀሳቦች በአእምሮዬ ውስጥ ተተረማመሱ። የብዙት ፖሊሶች ወከባና የሸሬው ክትትል ተደቀኑብኝ። "እዚህም እየተከታተሉኝ ነው ማለት ነው?" አልኩ ለራሴ፤ ውስጤ ተረበሸ። ምናልባት አለባቸውን ስጠብቅ ከነበረበት የኢትዮጵያ ሆቴል ይሆናል ተከትለውኝ የመጡት የሚል ጥርጣሬ ያዘኝ። ምናልባትም ስለእኔ ያገኙት መረጃ ይኖር ይሆናል፤ ይህ ሁሉ አእምሮየን ያጣበበው በደቂቃዎች ውስጥ ነበር። የትም ማምለጥ እንደማልችል ተሰማኝ። ጨነቀኝ።





ለአፍታ ያህል አእምሮዬ በትክክል ማሰብ ሲችል ግን "ፖሊሶች ቢሆኑ እንዴት በመልእክተኛ ሊጠሩኝ ይችላሉ?" የሚል ስሜት ብልጭ አለልኝ።

ልጁን ቀና ብዬ ተመለከትኩት። እኔ ከሐሳብ ወደ ሐሳብ ስዋልል አስተናጋጁ ቆሞ መልሴን እየጠበቀ እንደነበር አላስተዋልኩም። እርሱም በሁኔታዬ ግራ መጋባት ሳያድርበት አልቀረም። ሆኖም በእርጋታ እየተመለከተኝ ነበረ። ኮስተር አልኩና "ማነው የሚፈልገኝ? ምን ዓይነት ሰው ነው?" ብዬ ጠየቅኩት።

"አንዲት ልጅ ናት የፈለገችህ" አለኝ በፈገግታ " ልጅቱ 'አሁን የገባውን ጠይም ቆንጆ ልጅ ጥራልኝ' አለችኝ። አሁን የገባኸው ደግሞ አንተ ነህ፤ ስለዚህ የምትፈልገው አንተን መሆን አለበት ብየ ገመትኩ። ለማንኛውም ወጣ ብለህ ብታጣራ ይሻላል" አለኝ - የሀፍረት ዓይነት ሳቅ እየሳቀ።

ተነሥቼ ወጣሁ፤ እውነትም አንዲት ጠይም ቆንጆ ልጅ በውጪ በኩል በሆቴሉ በር ጠርዝ ላይ ቆማ ወደውስጥ ትመለከታለች። ከሩቅ አይቻት አላወቅኋትም። መንፈሴ በሚገባ በመረጋጋቱ ግን ወደግቢው በር አመራሁ። አዲግራት የምታውቀኝ ልጅ መሆኗን ስትነግረኝ አስታወስኳት። ተሳስመን ጠበቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን። ጎንደር የምትኖረው በጋብቻ ይመስለኛል። ከቀጠሮ ስመለስ ሆቴሉ መግቢያ አካባቢ እንደደረስኩ ወደ እኔ እያየች "አንተ፣አንተ" ስትል አይቻታለሁ። እኔን ይሆናል ብዬ በፍጹም ስላልገመትኩ ነበር ዝም ብዬ ወደ ውስጥ የገባሁት። ከገበያ ወደቤቷ እየተመለሰች ይመስላል፤ ዕቃ የሞላ ላስቲክ አጠገቧ ተቀምጧል። ትንሽ ስናወራ በደንብ አስታወስኳት። ወንድሟንም አስታወስኩት፣ ሰለሞን ቀጄላ ይባላል።

"መቼ መጣህ?" ብላ ጠየቀችኝ።

"ትናንት" ብየ መለስኩ በአጭሩ።

"ታዲያ መቼ ላግኝህ? ምሳ ብጋብዝህ ደስ ይለኛል፤ ወዲያውም ቤቴን ታያለህ" አለችኝ።

"መቼ ይሻላል? ነገ ይመችሻል?" አልኳት በድፍረት።

"ነገ? እዎ ይመቸኛል"አለች ጥቂት አመንትታ

"ቢቃ! ነገ በዚሁ ሰዓት እዚሁ እንገናኝና ተያይዘን እንሄዳለን" አልኳት።

"በጣም ጥሩ" አለችና ተጨባብጠን ተለያየን።

በማግስቱ ያንን ሆቴል ለቅቄ ወደሌላ ሆቴል ቀየርኩ። ከአለባቸው ጋር እንድንገናኝ ከታሰበው ከኢትዮጵያ ሆቴል በታች ወደ አለው ምዕራብ ሆቴል ሄጄ ነበር አልጋ የያዝኩት። ምዕራብ ሆቴል ለሦስት ቀናት ቆየሁ። ከአለባቸው ጋር ወደተያዙት ተለቀጭ ቀጠሮዎች መሄዴን አላቋረጥኩም።

እርሱ ግን ሳይመጣ ቀረ። በመጨረሻው ተለዋጭ ቀጠሮ ሳጣው ተስፋ ቆረጥኩና ወደ አጎቴ ሹራብ ቤት ለመሄድ ወሰንኩ። ማንም እንዳያየኝ ስጠነቀቅ ያልነበርኩትን ያህል፣ አሁን ግን አማራጭ ስለሌለኝ ከአክስቴ ልጆች ውስጥ መዝገበ የሚባለውን ለማግኘት አሰብኩ። መዝገበ እዚያው ሹራብ ቤት ውስጥ እንደሚሠራ አውቃለሁ። ከእኔ ጋር ደግሞ በጣም እንግባባ ነበር። በመልክም እንደምንመሳሰል ብዙዎች ይነግሩን እንደነበረ ትዝ ይለኛል። የሚያመች ሰዓት ስመርጥ ቆይቼ ጥሩ በመሰለኝ ሰዓት ሄድኩ።

መዝገበ ሲያየኝ በጣም ደነገጠ "ከየት መጣህ? እንዴት መጣህ?" አለኝ እየተርበተበተ።

"ለጉዳይ ነው የመጣሁት። ለማንም ሰው ሳትናገር ከሥራ እንደወጣህ እንገናኝ" አልኩትና ያረፍኩበትን ነገርኩት። ከሥራ ሲወጣ መጣና ብዙ ስንጫወት ቆይተን ተሊያየን።

በሁለተኛውም ቀን መዝገበን ለብቻው ለማግኘት ወደ ሹራብ ቤቱ ስሄድ ከአጎቴ ጋር ተገጣጠምኩ። ሲያዩኝ ከመዝገበ ባልተናነሰ ደነገጡና ግራ ተጋቡ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "ምን ልታደርግ መጣህ?" ብለው ጠየቁኝ።





"አሞኝ፣ ለሕክምና መጥቼ ነው" አልኳቸው።

"እንግዲያውስ፣ እኛ ቤት ታርፋለህ" አሉኝ።

"ኧረ አልጋ ይገኛለሁ" አልኩ

"እንዴ! የእኛ ቤት እያለ? ለምንድነው ውጪ የምታድረው?" አሉ ቁጣ በተቀላቀለበት አነጋገር።

"በሽታዬ ተላላፊ ነው፤ የሳንባ ነቀርሳ ስለሆነና ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ ስለሚችል ውጪ ባድር ነው የሚሻለው" ስላቸው ደንገጥ አሉና ወደ መዝገበ ዞረው "በል ለማንኛውም እቤት ይዘኸው እንድትመጣ" አሉት። በማግስቱ ከመዝገበ ጋር አጎቴ ቤት ሄድኩና ምሳ በልቼ ተጫውቼ ተመለስኩ። ጎንደር ውስጥ ከመዝገበ ሌላ ሁለት ጓደኞቼንም አግኝቻለሁ። አንዱ ሰለሞን አርአያ የሚባል የአዲግራት ተማሪ የነበረና በኋላ አዲግራት ተመልሶ በቀይ ሽብር የተገደለ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደጀን አሰፋ የሚባል አብሮ አደጌ ነበር። ደጀን አሰፋ አሁን የአክስቴ ልጅ ባል ሆኗል።

ብዙውን ጊዜ ከደጀን ጋር አብረን እንውል ነበር። ሁኔታዬን ተጠራጥሮ "ወደ ሱዳን ለማለፍ ከፈለግህ ልተባበርህ እችላለሁ" አለኝ አንድ ቀን።

"ለሕክምና ነው የመጣሁት፤ እየተከታተልኩ ነው" አልኩትና ሐሳቡን እንዲቀይር አደረግሁት። ጎንደር ከገባሁ ሳምንት አለፈኝ። አለባቸውን እስከአሁን አላገኘሁትም። ሕክምናዬን ለመጀመር ወሰንኩና ሆስፒታል ሄጄ ካርድ አወጣሁ። የሆስፒታሉ ሠራተኞች እስኪደንቀኝ ድረስ በጣም ጥሩ በሆነ አቀባበል አስተናገዱኝ። ከዘበኛ ጀምሮ የሚገጥሙኝ ሁሉ ተንከባክበው አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽሙልኛል። ደስ አለኝ።

አልጋ በምይዝበት ሆቴል ከሦስት ቀናት በላይ አልቆይም፤ ቶሎ ቶሎ እቀይራለሁ። ቀን ከሆስፒታል መልስ አብዛኛውን ጊዜ ከደጀን ጋር ሻይ ቤትና ጠላ ቤት እየሄድን እንውላለን። ያን ጊዜ ለማስታወሻ ብለን ከደጀን ጋር አብረን የተነሣነው ፎቶ ግራፍ አሁንም በእጄ አለ። የምንውልበት ሻይ ቤት "ሰላም ሻይ ቤት" የሚባል ሲሆን የሚገኘው ከስልክ ቤቱ አጠገብ ነበር። እዚያ ሻይ ቤት የሚመጡት አብዛኞቹ ወጣቶች የፖለቲካ እውቀት ያላቸው ስለነበሩ እነርሱን ማዳመጥም ሆነ ከእነርሱ ጋር ስለ ዓለም አቀፍ፤ ስለሀገር አቀፍና ስለጎንደር የፖለቲካ ጉዳዮች መወያየት ያስደሰተኝ ነበረ።





ሕክምናዬን እስከምጨርስ ጎንደር በቆየሁበት ጊዜ ከሰላም ሻይ ቤት ሌላ ከደጀን ጋር የምንሄደው ወደ ጃንተከል ዋርካ ነበር። ከዋርካው አቅራቢያ የሚገኘው የወይዘሮ ሀዳስ ቤት የፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች ጠላ ለመጠጣት የሚገቡበት የታወቀ ቦታ ነበር። እኛም ከወታደሮቹ ጋር አብረን እንጠጣለን። ወታደሮቹ የታጠቁትን ዘመናዊ ማሽንገን ይዘው ይመጣሉ፤ ብዙዎች ኤርትራውያን ነበሩ። እነርሱ ተሰብስበው ጠላ እየጠጡ ይጫወታሉ፤ ይቀላለዳሉ፤ እኔ የታጠቋቸውን መሣሪያዎች እያየሁ እጎመጃለሁ። ከእነርሱ ጋር መጠጥ ስንገባበዝ ልቤ የሚመሰጠው በግብዣው ሳይሆን በሚይዟቸው ዘመናዊ አውቶማቲክ ጠመንጃዎች ነበር።

የሚያክመኝ ዶክተር፣ ራጅ እንድነሣ አዘዘልኝ። ከራጅ ክፍል የመጣውን ውጤት አነበበና ምንም ዓይነት የሳንባ ነቀርሳ ችግር እንደሌለብኝ የምሥራቹን ሲነግረኝ ተሰምቶኝ የነበረው ደስታ ዛሬም ድረስ አይረሳኝም። የምርመራ ፋይሌ ወደ መዝገብ ቤት ከተመለሰ በኋላ የካርድ ክፍሉ ሠራተኞች የተነሣኋቸውን የራጅ ፊልሞች "ይሄ ከሆስፒታል የማይወጣ መረጃ ነው፤ ለአንተ ግን ነጻ ለመሆንህ ማረጋገጫ እንዲሆንህ፣ ይዘኸው እንድትሄድ እንሰጥሃለን" በማለት ከመዝገብ ቤት አውጥተው ሰጡኝ።

***

ሁሉም ነገር በሰላም ተጠናቀቀና፣ የሆስፒታል ጉዳዬን እንደጨረስኩ ለመልስ ጉዞዬ ተዘጋጀሁ። ወደ አሲምባ የተመለስኩት በመጣሁበት መንገድ ቢሆንም መንገዱ ቀጥታ ነበረ። አዲግራት እስከምደርስ መኪና መቀየር አልነበረብኝም። ትልቅ ሻንጣ አልነበረኝም፤ ልብሶቼን የያዘውን አነስተኛ የእጅ ቦርሳ አንጠልጥያለሁ። አዲግራት ስገባ ፒያሳ ለመውረድ አልፈለግሁም፤ ፒያሳ የሚያውቁኝ ሰዎች ይኖራሉ። አውቶቡሱ ፒያሳ ከመግባቱ በፊት አውራጃው አስተዳደር አጠገብ የፍተሻ ኬላ ነበረ። ፍተሻ ኬላው ላይ ተፈትሼና ቦርሳዬንም አስፈትሼ ወደመኪናው ተመልሼ ሳልገባ በግራ በኩል ዋናውን የመኪና መንገድ ይዤ ከከተማው ወጣሁ። ከከተማ ስወጣ ተማሪዎች እያለን የማውቃቸውን ሁለት ልጆች አየሁ። ዘመድ ሞቶባቸው አስከሬን ከሆስፒታል አውጥተው እየሄዱ ነበር። እንዳያዩኝ ለመሞከር ስደናበር አዩኝ፤ ግን እርግጠኞች አልነበሩም፤ ተጠራጥረዋል። እኔ እንዳላየኋቸው በመምሰል መንገዴን ቀጠልኩ። በተደጋጋሚ እየዞሩ ያዩኛል። ያላወቅኋቸው መስዬ ወደኋላ ቀረት አልኩና፣ በመካከላችን ያለው ርቀት ሲረዝም ተስፋ ቆርጠው ሄዱ።

ከአዲግራት ከተማ እኩለ ቀን ላይ ተነሣሁና አመሻሹ ላይ ሰበያ ደረስኩ። ሰበያ የማውቀውና የከረምኩበት ቦታ ነው፤ ለአሲምባም በጣም ቅርብ ነኝ፤ ሰበያ ነጻ መሬት ስለነበረ ያለምንም ሐሳብ አደርኩ። ጠዋት ከሰበያ ተነሥቼ ቆሎ ምሽላ እንደደረስኩ የእኛን ሰዎች አገኘሁና አሲምባ ከሠራዊታችን ጋር በሰላም ተቀላቀልኩ። አሲምባ ስመለስ ከተላላፊ በሽታ ነጻ በመሆኔ ደስተኛ ነበርኩ። ያለምንም ሥጋት በአንድ ኩባያ መጠጣት አብሮ መተኛት ልዩ ስሜት ፈጠረልኝ። የጓዶች ጥያቄ ብዙ ነበር እኔም ያየሁትና ያወቅሁትን ያህል ከመመለስ አልቦዘንኩም።

***





እኔ ጎንደር በነበርኩበት ጊዜ፣ በመጋቢት ወር ውስጥ የተደረገ ጎላ ያለ ወታደራዊ ተልእኮ በአዲ አውአላ ፖሊስ ጣቢያ ላይ የተካሄደው ወረራ ነበር። ያን ጊዜ ሠራዊቱ መትረየስ አልነበረውም፤ መትረየስ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ሲታሰብ ተስፋይ ገብረ ሥላሴ በሰጠው ጥቆማ መሠረት የወረራው ዕቅድ እንደተነደፈ ጓዶች ነገሩኝ። ተስፋይ ገብረ ሥላሴ ትግራይ ውስጥ በሽሬ አካባቢ ተመሥርታ እንቅስቃሴ የጀመረች ጠርናፊት የምትባል ድርጅት አባል የነበረና ወደ አሲምባ መጥቶ ከኢሕአሠ ጋር የተቀላቀለ ሰው ነው። ተስፋይ፣ አዲ አውአላ ውስጥ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ሁለት መትረየሶች መኖራቸውን እንደሚያውቅ በመናገሩ ለጥቃት ርምጃው አስራ ሁለት ጓዶች ተመድበው እርሱም አብሯቸው እንዲሄድ ተደረገ። የተባለው ቦታ ሲደርሱ በሄሊኮፕተር መጥቶ ለሕዝቡ እንዲሰራጭ የተራገፈ ብዙ መሣሪያ መኖሩን ሰሙ። በዚህ ጊዜ ወደፖሊስ ጣቢያው በድንገት ገብተው ፖሊሶቹን ማርከው ተቆጣጠሯቸው። ከዚያም ያለውን መትረየስና፣ ተራገፈ የተባለውን መሣሪያም ጭምር ሰብስበው አንድ የጭነት መኪና በማስገደድ የተወሰነ ርቀት ድረስ ሄዱ። ከዚያ በኋላ አህዮች ተከራይተው ወደ ኤርትራ ድንበር በመጓዝ ጀብሃዎች ከሚቆጣጠሩት መሬት ገቡ። ጀብሃዎችም በጥሩ ሁኔታ ተቀበሏቸው።

የኢሕአሠ ቡድን ያመጣቸውንም መሣሪያዎች ጾረና፣ መነኩሴይቶ ድረስ ለማምጣት ቃል ገብተው፣ ቡድኑን በዚያው በኩል ወደ ጦር ሰፈሩ ሸኙት። ከጥቂት ጊዜም በኋላ መሣሪያዎቹን መነኩሲቶ ድረስ አምጥተው ለኢሕአሠ አስረከቡ።

***

# ሦስት

## ወልዲያ ደርሶ መልስ

### የግንቦቱ ስብሰባ

ግንቦት 1968 ዓ.ም መለስተኛ የእርማት እንቅስቃሴ የተካሄደበት ጊዜ ነበር። ለዚህ ስብሰባ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ዳዊት ስዩምና ብርሃነ እያሱን የመሳሰሉ የአመራር አበላት አሲምባ መጥተዋል። በዚህ ወቅት ከሻእቢያ ደግሞ ዶክተር ኢዮብ እና፣ መምህር ባራኪ የተባሉ የፖለቲካ ሐላፊዎች እንዲሁም ሌላ ሦስተኛ የሻእቢያ አባል ሰው ኢሕአሠን ለማነጋገር አሲምባ መጥተው ነበር። እነዚሁ ልኡካን እዚያ የተገኙበት አንዱ ምክንያት በሕወሐትና በኢሕአሠ መካከል በሚደረገው ንግግር ውስጥ የሽምጋይነት ሚና ለመጫወት ነበር። በዚያው ሰዓትም ኢሕአፓና ሻቢያ የኤርትራን ጥያቄን በተመለከተ አንድ ስምምነት አድርገው ስምምነቱም በአማርኛ፣ በትግርኛ፣ በእንግሊዘኛና በዐረብኛ እንዲሁም በሌሎች ሦስት ቋንቋዎች እንደተሰራጨ ይነገር ነበር።

የተካሄደው ስብሰባ ሁለት አጀንዳዎች ነበሩት። አንደኛው የእርማት እንቅስቃሴን የተመለከተ ሲሆን፣ ሁለተኛው አጀንዳ ደግሞ ኢሕአፓ ከኢ.ፒ.ኤልኤፍ/ሻእቢያ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ነበር። ስብሰባውን ለመምራት መድረኩ ላይ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና ግሩም ጌታሁን ተቀምጠዋል።

ስለእርማት እንቅስቃሴ የተነሣው ዋና ሐሳብ ፓርቲው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን ለሠራዊቱ አመራር ባለመስጠቱ፣ የሠራዊቱ እንቅስቃሴ ተገድቧል የሚል ነበር። የሠራዊቱ አመራር ሠራዊቱ "ለምንድነው የማንንቀሳቀሰው? ለምንድነው የማንዋጋው?" የሚል ግፊት እያደረገበት መሆኑን





በመግለጽ በዚህ ጉዳይ ላይ ፓርቲው ያለውን አቋም ግልጽ እንዲያደርግ ጠይቆ ነበር።

ተከትሎም "ፓርቲው ይህንን የወታደራዊ ክንፍ ምን ያህል ያምንበታል? ምን ያህል አስፈላጊ ነው ይላል? አስፈላጊነቱ የሚታመንበት ከሆነ ለምን በሰው ኃይልና በመሰሪያ ለማጠናከር አልተሞከረም? ለዚህ የትጥቅ ትግል የሚያገለግሉ ብቁ እውቀት ያላቸው ጓዶች ለምን ከከተማ ላይመጡም? በቂ ስንቅና ትጥቅ ስለሌለን እንዲሁም በአቅማችን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ውሳኔ ስላልተሰጠን፣ እንኳንስ በራሳቸው ተነሣሽነት ከየአካባቢው የሚመጡትን በድርጅታዊ ግንኙነት ከከተማ የሚመጡትንም ጓዶች ሠራዊቱን እንዳይቀላቀሉ እየከለከልን ስለሆነ ይህ ችግር እንዴት ይታያል?" የሚሉ ጥያቄዎች ተነሡ። ይህ በድርጅቱ በኩል የሚመጡትን ምሁራን ብቻ የመቀበል ሁኔታም ለሠራዊቱ ሁሉን አቀፍ መሆን ያለመቻል ምክንያት መሆኑን ብዙዎች ይጋራሉ።

ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ መልስ ሲሰጥ፣ በፓርቲው በኩል ሠራዊቱ አቅሙ በሚፈቅድለት መጠን የፈለገውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ መብቱ የተጠበቀ እንደሆነና ፓርቲው "ወታደራዊ እንቅስቃሴ እንዳታደርጉ" የሚል ትእዛዝ ለሠራዊቱ እንዳልሰጠ ተናገረ። በዚህ ጊዜ ጺጋዬ ደብተራው ትእዛዝ ተሰጠበት የተባለውን የጽሑፍ መረጃ ከእጅ ቦርሳው አውጥቶ ለዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ አሳየው። ዶ/ር ተስፋዬ ወረቀቱን ተቀብሎ ተመለከተና፣ ያሳየው መረጃ የፓርቲው ትእዛዝ እንዳልሆነ ለደብተራው ነገረው። ደብተራውም መልሱን ከሰማ በኋላ ወረቀቱን እንደገና አጣጥፎ ወደ ቦርሳው ከተተው።

ዶ/ር ተስፋዬ ከደብተራው ጋር ጨረሰና ወደ ተሰበሰቡት የሠራዊቱ አመራር አባላት ዞሮ፣ ፓርቲው ሠራዊቱን ለማጠናከር የቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ፣ ሠራዊቱ የተሟላ ሥልጠናና ትጥቅ እንዲያገኝ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚያገኘውን በር ሁሉ እንደሚያንኳኳ ገለጸ። እንዲሁም ትጥቅ በቅርብ ጊዜ እንደሚመጣም ቃል ገባ። እስከዚያው ድረስ ግን የሠራዊቱ አመራር

አቅም በሚፈቅደው መሠረት የሚያምንበትን ወታደራዊ ተልእኮ ለማካሄድ ሥልጣን እንዳለውና ከአሁን በኋላ እንደልብ ለመንቀሳቀስ የሚከለክል ምንም ነገር እንደሌለ በመግለጽ መልስ ሰጠ።

ከሠራዊቱ አመራር ጋር ስብሰባ በተደረገ በሁለተኛው ቀን ደግሞ ሠራዊቱ ለስብሰባ ተጠራ። በዚህ ስብሰባ ላይ ዶክተር ተስፋዬ የስብሰባውን ዓላማ ለሠራዊቱ ሲያስረዳ ከኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ. ጓዶች ጋር አብሮ ለመሥራት ስምምነት ላይ እንደተደረሰ አስታወቀ። ይህ ስምምነት ቢፓርቲው በኩል ስለኤርትራ ጥያቄ የተወሰደው ጊዜያዊ አቋም መሆኑን ጠቁሞ፣ የኤርትራ ጥያቄ የብሔርም ሆነ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ሳይሆን የነጻነት ጥያቄ ነው የሚል አቋም እንደተወሰደ ተናገረ። ኤርትራ አገር መሆኗን እናውቃለን። ግን ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ግዛት ለመያዝ አቅም ስለሌላት የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ለማለት ያዳግተናል። ብሔራዊ ትግል ነው እንዳንል ደግሞ ኤርትራ ከብሔር አልፋ እራሷን ችላ የነበረች አገር ናት። ፓርቲው የኤርትራን ችግር አጥንቶ በአጭር ግዜ ውስጥ መልስ እስከሚሰጥ ድረስ ለጊዜው የኤርትራ ጥያቄ የነጻነት ጥያቄ ነው እንጂ የብሔርና የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም የሚል አቋም እንዳለው አስረዳ። በመጨረሻም ይህንን የኤርትራን ጥያቄ በተመለከተ ከኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ. የመጡ ጓዶች እናንተን ለብቻችሁ ማነጋገር እንደሚፈልጉ ስለገለጹ ዛሬ ማታ ያነጋግሯችኋል። እናንተም ከፓርቲው ጊዜያዊ አቋም ተነሥታችሁ መልስ መስጠት ይጠበቅባችኋል አለን።

የተባለውም ስብሰባ ተጠራ። ዶክተር ኢዮብና መምህር ባራኪ እንዲሁም ተጨማሪ የሕዝባዊ ኃይልታት ተወካይ የሆነ ሦስተኛ ሰው መጥተው አነጋገሩን። ጥያቄዎቻቸውም "ስለኤርትራ ያላችሁ አቋም ምንድን ነው? ስለኤርትራ ትግልስ ምን ታውቃላችሁ?" የሚሉ ነበሩ። የተሰጣቸውም መልስ ያው ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ በሰጠን ማብራሪያ ላይ የተመሠረተ ነበር። (መምህር ባራኪ አዲግራት





ውስጥ አስተማሪ ስለነበር ስብሰባው ካበቃ በኋላ የአዲግራት ልጆችን ሰብስቦን ሲጫውት ያመሽ ነበር።)

ስብሰባው ከተደረገ ከጥቂት ቀናት በኋላ ደርግ "የራዛ ዘመቻ" በሚል አርሶ አደሮችን ከትግራይ ከወሎና ከሌሎችም ክፍለ ሀገሮች መልምሎ በኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ለመዝመት የጦር ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑ ተሰማ።

ጀብሀም ለራዛ ዘመቻ የመጣውን የደርግ ጦር አዲግራትን አልፎ ዛላ አንበሳ ሳይደርስ ለመምታት አቅዶአል። ሃዲሽ ወልደ ጊዮርጊስ ራሱ አንድ ባታሊዮን ጦር ይዞ እስከ ቀርሰበር ድረስ ዙሪያውን መሽገው ተዘጋጅተው መጠበቅ ይዘዋል። (ቀርሰበር ከአዲግራት ሰባት ኪሎ ሜትር ይርቃል)

አንደኛው የኢሕአሠ ቡድን ጂግሳ፣ ብርሃነ ወዲቀሺና የአቢኢዮ ያሉበት ቡድን፣ ከጀብሀዎች ጋር አድፍጧል። ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ወደ ጎእቶሎ በኩል ሰፍረናል። ለሦስት ቀናት ያህል በዚያ ሁኔታ እየጠበቅን ከቆየን በኋላ ጀብሀዎች መሽገውበት የነበረውን ስትራጂያዊውን የቀርሰበር ተራራ ለቀው ሄዱ። የለቀቁበት ምክንያት ለኢሕአሠ ግልጽ አልነበረም። እነርሱ ተራራውን በለቀቁ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ደርግ ሰባ በሚሆኑ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች ሠራዊቱን ከአዲግራት ጭኖ በማንቀሳቀስ የቀርስ በርን ተራራ በቀጥታ እንዲይዙ በማድረግ ያለምንም ችግር ዛላ አንበሳን ተቆጣጠረ።

በዚህ ጊዜ የደርግ ጦር በምድርባ አድርጎ ወደ አሲምባ እንዳይገባ ለመከላከል እንድንችል ወደ ምድርባ ተንቀሳቀስን። የራዛ ዘመቻ አራት ድርጅቶች ማለትም ኢሕአሠ፣ ሕወሃት፣ ጀብሀ እና ሻእቢያ በተጠንቀቅ የነበርንበት የጦርነት ሁኔታ ነበር። እኛ ምድርባ ላይ በመሸግን በሁለተኛው ቀን ስብሰባ ተደረገና "የደርግን የራዛ ዘመቻ በመጠበቅ ከሳምንት በላይ ቆይተናል። አሁን የራዛ ዘመቻ ጦር እኛን አልፎ ወደዛላ አንበሳ በኩል በማለፉ ትኩረቱ ወደ ኤርትራ ኃይሎች መሆኑን ተመልክተናል፤ የኤርትራ ድርጅቶችም ተዘጋጅተው እየጠበቁ ነው። ስለዚህ እኛን የሚመለከት አደጋ ስለሌለ ትኩረታችንን

ወደ ድርጅታችን ዕቅዶች ማድረግ ይኖርብናል። የድርጅታችንን ዕቅድ በተመለከተ የተደረገ ምደባና እንቅሲቃሴ በመኖሩ ወደዚያ እንሰማራለን" ተብሎ ተነገረን።

"በአካባቢያችን ጠላት ተከማችቶ እያለ እኛ ወደሌላ ቦታ ሥንሰማራ ቤዛችን ቢያዝስ?" የሚል ጥያቄ ተነሣ።

"ደርግ ቤዛችንን ሊይዘው አይችልም፤ ምክንያቱም የኤርትራ ድርጅቶች ለራሳቸው ደኅንነት ሲሉ ይከላከሉታል። ደርግ ግን አሲምባን ለመያዝ ሲል እነርሱን ትቶ ወደእኛ ይመጣል የሚል ግምት የለንም" ተባለ።

***





ከአሲምባ ቃሊም

"የጀግናማ ልቡ ጦሩ ብቻ አይደለም። የቁርጥ ቀን ሰው ነው፤ ብቻም አይደለም። ለዓላማው ሟችነት ብቻም አይደለም አለው እንጂ ፍቅር ድንቅ ሩህሩህነት የማይሞት ኃያል ሰው ሰብአዊ ሰውነት።።"

ከእርማት እንቅስቃሴ በኋላ የሠራዊቱ ቁጥር እየበዛ ሲሄድ ከፍተኛ የበላይ አመራሮች (ጠአኮ) የጠቅላይ አመራር ኮሚቴና የጠቅላይ ፓርቲ አመራር ኮሚቴዎች(ጠፓአኮ) የሚባሉ ሁለቱ ከፍተኛ የሠራዊቱ የአመራር ኮሚቴዎች ተመሠረቱ። ጠአኮ ወታደራዊ ከፍተኛ አመራር ሲሆን፣ ጠፓአኮ ደግሞ የፖለቲካ ጉዳይ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ነው። በዚህ መሠረት የጠፓአኮ አባላት ጌድዮን፣ ፀሐዩ፣ ጋይም፣ ታሪኩ ጋዙና ዘለቀ ሆኑ። የጠአኮ አባላት ደግሞ ሮባ፣ መዝሙር፣ ለምለም፣ አበጀ፣ ዳዊት እንድሪስና ጺጋዬ ደብተራው ሆኑ።

ሠራዊቱ በሦስት አሀድ፤ የትግራይ፣ የጎንደርና የወሎ ጦር ሰፈር ተብሎ ሲከፈል ሁሉም የየራሳቸው የበላይ ወታደራዊ መሪ እንዲኖራቸው ተደርጎ ተዋቀሩ። የትግራይ ወታደራዊ መሪ ጌራ፣ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ፀሐዩ፤ የጎንደር ወታደራዊ መሪ ጅግሳ፣ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊ ግርማይ ሲሆኑ፣ የወሎ ወታደራዊ መሪ ደግሞ ግደይ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ደግሞ ሐዋዝ ሆኑ።

አንድ ኃይል ሦስት ጋንታዎች አሉት። እያንዳንዱ ኃይልም ወታደራዊ መሪና ምክትል፣ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊና ምክትል ይኖራቸዋል። (ከእርማት እንቅስቃሴ በኋላ ደግሞ የፓርቲ ተወካይ የሚባሉ ተጨማሪ የፖለቲካ ሐላፊዎች አመዳደብ ተጨምሯል)።

አንድ ጋንታ በአማካይ ከአሥራ አምስት እስከ ሀያ የሚሆኑ አባላት ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ጋንታ የጋንታ ወታደራዊ መሪና ምክትል መሪ፣ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊና ምክትል ሐላፊ ይመደብለታል። የጋንታ ወታደራዊ መሪና ምክትሉ የጋንታዋን እንቅስቃሴ በሰዓት ለመምራት እንዲመቻቸው በቀንና

በሌሊት ሊታይ የሚችል የእጅ ሰዓት ይሰጣቸዋል። ጋንታዋ ስትንቀሳቀስ አባላቱ በመስመር ተሰልፈው ይሄዳሉ። በ ሰ ል ፉ ላ ይ ጋንታ መሪ ከፊት፣ ምክትል መሪው ደግሞ ከመካከል ይሆናሉ።

ሠራዊቱ ወደ ወሎና ጎንደር ለመሄድ ጉዞ የጀመረው በግንቦት ወር 1968 ዓ.ም ነበረ። እንደ ተለመደው ሁሉ ጉዞአችን በሌሊት ነበር። ጋንታ መሪና ምክትሉ ተራ በተራ እየተቀያየሩ የማደሪያ ሥፍራችንን ይቃኛሉ፣ የጸጥታ ሁኔታ በማጣራት ተረኛ ጥበቃዎችንም ይቆጣጠራሉ። ጋንታ መሪው የማታ የጥቢቃ ሐላፊ ሆኖ ካደረ በቀጣዩ ቀን ምክትሉ በተራው የጥበቃ ሐላፊነቱን ተረክቦ ይሠራል። የአስተኛኘታችንም ሁኔታ ሁልጊዜም እንደተከበረ ነበር።

አብሩክ ሲባል ሁሉም በያለበት ቦታ ቁጢጥ ይላል። አቀማመጡም ፊትና ኋላ በመሆን ከሁለት አቅጣጫ ለመመልከት በሚያስችል መልኩ ነበር። በምንም ሁኔታ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት አይፈቀድም። ይህም አሰላልፍ የመጨረሻ ተሰላፊ ወደ ኋላ ከፊት ያለው ደግሞ ወደፊት እንዲመለከት ሲያደርግ በመሐል ያሉት ደግሞ ግራና ቀኝ እንዲመለከቱ ያስችላል። ተረኛ የጥበቃው ኃላፊ ጥበቃ የሚቆምበትን አመቺ ቦታ ይመርጥና ያስታውቃል። ችግር ሲኖር ቶሎ እንዲገኝ ነው ያለበትን ቦታ የሚያሳውቀው። በየተወሰነ ሰዓት ጥቢቃዎች ስለሚቀያየሩ ቅይይሩና ሥራቸው በሚገባ እየተከናወነ እንደሆነም የሚቆጣጠረው የጥበቃ ሐላፊው ነው። ማለዳ ላይ የጋንታ መሪዎች ተነሥተው አካባቢውን ከተመለከቱና ሰላማዊ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ የጋንታው አባላት ለጉዞ እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ። ከጉዞ በፊት እቃ እንዳልተረሳ ከተረጋገጠ በኋላ ጋንታዋ መንቀሳቀስ ትጀምራለች።

በሐዲስ ዛህላይ የምትመራ አንዷ ጋንታ ትግራይ ቀርታ ከጀብሀዎች ጋር በመተባበር የአሲምባንና የአካባቢውን ቁልፍ ቦታዎች ለመከላከል ተመደበች። አምስቱ ጋንታዎች ጎእቶሎ እንደደረስን ማታውን ራት በልተን ከራት በኋላ ወደ





ሳዕሲዕ መጓዝ ጀመርን። እንደተለመደው ሁሉ እንቅስቃሴያችንን ላለማሳወቅ ለሊቱን በሙሉ ያለዕረፍት በጨለማ ነበር የተጓዝነው። የሠራዊቱ አመራር አባላት አብዛኞቹ ማለትም ሐዋዝ፣ ግደይ፣ ጂግሳ፣ ግርማይና ጸጋዬ ደብተራውም ጭምር ከእኛ ጋር መጥተዋል። አሲምባ የቀሩት ሮባ፣ ፀሐዬና ጌራ ብቻ ነበሩ። አምስቱም ጋንታዎች በሁለት ኣውላሎ፣ እዳጋ ሀሙስን ወደቀኝ ትተን፣ በእዳጋ ረቡዕ ወይም በስንአፌ አድርገን ወደ አጉላእ አመራን። ከሁለት ኣውላሎ፣ አንድ ገብረ ሚካኤል የሚባል አካባቢውን የሚያውቅ ነዋሪ በአባልነት ተመልምሎ ለመንገድ መሪነት ይዘነው ሄድን።

ሀይቅ መስሐል ስንደርስ አራቱ ጋንታዎች ወደ አጉላእ ሲሄዱ፣ እኔ የነበርኩባት ጋንታ ሀይቅመሳል እንድትቀር ተደረገች። የቀረነው አንድ ሕዝቡን ያስቸገረ ሽፍታ መኖሩን በመስማታችን እሱን ለመያዝ ነበረ። ሽፍታውን በቁጥጥር ስር አድርገን ለሦስት ቀናት የፖለቲካ ትምህርት እንዲሰጠው ተደረገና ትጥቁን አስፈትተን ለቀቅነው። አራቱ ጋንታዎች ያሉበት ቦታ ስንደርስ የአጉላእን ከተማ ተቆጣጥረውና የሄዱበትን ተልእኮ አሳከተው ጠበቁን።



ከአሲምባ ቃሊም የሰራዊቱ ጉዞ

አጉላእ እያለን አንድ ኢጋጣሚ ተፈጠረ። የጺጋዬ ደብተራው ሽጉጥ ጠፍቶ በከተማው ሁሉ ተፈልጎ ሳይገኝ ቀረ። ምንም ማድረግ ስላልተቻለ፣ መንገዳችንን ቀጠልንና ደስአ(እንደርታ ማለት ነው) ደረስን። "ጺጋዬ ደብተራው ሽጉጥ ጥሎ ለምን አይቀጣም?" የሚል ሹክሹክታ ይሰማ ጀመር። በሠራዊቱ ደንብ መሠረት አንድ አባል ማንኛውንም ዓይነት ንብረት ከጣለ ይቀጣ ነበር። ሁሉም እቃ በጥንቃቄ መያዝ ስላለበት እንኳንስ ሽጉጥን ያህል ትልቅ ነገር ኩሽከም የጠፋበት፣ ምጣድም ረስቶ የመጣ፣ደብተርም የረሳ ሳይቀር ይቀጣል። እንደጀማል መሣሪያ የባረቀባቸውና የተቀጡም ነበሩ። በመሆኑም ጺጋዬ ደብተራው ሽጉጥ መጣሉ ከተሰማ በኋላ "ለምን አልተቀጣም?" የሚል ጥያቄ ተነሣ። እኔም " እውነት ነው፤ ለምንድነው የማይቀጣው?" ብዬ አስተያየት ሰጠሁ። ወሬው ጺጋዬ ደብተራው ጆሮ ደረሰ። አጉላእን አልፈን አራጉሬ ወደምትባል ትንሽ ከተማ በመሄድ ላይ እያለን ጺጋዬ ደብተራው ጠራኝና ሄድኩ።

"ጺጋዬ ደብተራው ሽጉጥ ጥሎ ለምን አይቀጣም ብለህ ተናግረሀል እንዴ?" ብሎ ጠየቀኝ።

"አዎ ተናግሬአለሁ፤ ሁላችንም በእኩል የምንታይ ጓዶች ከሆንን መሣሪያ የባረቀበት፣ ኩሽከም የጣለ፣ ቦርሳም የጠፋበት ስለሚቀጣ ሁላችንም እኩል መሆን አለብን ብዬ ነው የተናገርኩት" አልኩት።

"አባባልህ ትክክል ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን ሐቅ መናገር ያስወነጅላል" አለኝ። ከዚያ በኋላ የተናገራት አባባሉ ሁሌም አትረሳኝም "አማኑኤል! ስታስበው ግን ማነው ቀጪ፣ ማነው ተቀጪ?" አለኝ። ከ ዚ ያ ደ ግ ሞ "በአኔ በኩል ችግር የለም። ነገር ግን ሁልጊዜ ሐቅ መናገር አያዋጣም። አንዳንድ ጊዜ አይቶም እንዳላየ ማለፍ መቻል አለብህ። ይህቺን ምክር እንዳትረሳ፣ እሺ?" አለኝ።





"እሺ" አልኩትና ልሄድ ስል ተያየንና ተሳሳቅን። ከዚያም አቀፈኝና ይቅርታ ተባብለን ተሳስመን መንገዳችንን ቀጠልን። ጺጋዬ ደብተራው መልኩ ቀይ፣ ቁመቱ ረዘም ያለና ቀጭን ነው። ጸጉሩ ሉጫ ሲሆን በላዩ ላይ ኮፍያ ያደርግበታል። ፊልድ ጃኬት ኮቱና ሱሪው በላዩ ላይ ብዙ ግዜ እንደቆዩ ያስታውቃሉ። ጺሙ እንደመነኩሴ ጺም ያደገ ነበር፤ ብቻውን ሲቆዝም ጺሙን እያፍተለተለ መጫወት ይወዳል። ዓይኖቹ ትናንሽ ናቸው። ማንገቻ ያለው የዓይን መነጽር ያደርጋል። ሲናገር ረጋና ዝግ ብሎ ሲሆን፣ በንግግሩ መካከል ቀልዶችና ተረቶች መጨመር ይወዳል። ቀልዶቹና ተረቶቹ ሁሉ ግን ከትግል ከጓዶችና ከቁም ነገር ጋር የተያያዙ ናቸው።

ጺጋዬ ግለኝነት የማያጠቃው፣ ከራሱ ይልቅ ለሌሎች ጓዶች የሚጨነቅና ቅድሚያ የሚሰጥ ነበር። ምግብ በምንመገብበት ጊዜ አንድ ሰው ምግቡን ቀድሞ ከጨረሰና ቅር ብሎት ከተመለከተ ጺጋዬ የራሱን ድርሻ ሲሰጥ ማየት የተለመደ ነበር። በበረሐ ውስጥ ከሚፈትኑን ችግሮች አንዱ የነበረው የልብስና የጸጉር ቅማል ነበር። መቼም ማከከን ተላምደነው እጃችን ሥራ ፈቶ አይቆይም።ችግሩ ጠንከር ሲልም ለማስታገስ እርስ በርስ መቀማመል የተለመደ ሲሆን ጺጋዬን ግን የሚያህለው አልነበረም። ጊዜ ኖሮት አንድ ሰው ሲያከ ካየ ዝም አይልም፤ ጠጋ ብሎ ይለቅምለትና እናት የልጇን እራስ እንደምትደባብስ ሁሉ እርሱም በደስታ ይደባብሳል። በተለይ ሰፋ ያለ ጊዜ ካለው እርሱ እንዲቀምለን ተራ የምንገባበት ወቅት እንደነበረ ትዝ ይለኛል። እሱ ግን አይሰለችም። የእርካታ ስሜት ነበር የሚታይበት።

እኔ የነበርኩበት ጋንታ መሪ ዘሚካኤል፣ ምክትል ጋንታ መሪ በርሔ፣ (ሀጎስ በዛብህ)፣ የፖለቲካ ሐላፊው ደግሞ ዘላለም ነበሩ። ሦስቱም የአመራር ሰዎች ለስብሰባ ተጠርተው፣ ሄደዋል። ጋንታዋን እንድመራ የተወከልኩት እኔ ነበርኩ። ከስብሰባ ሳይመለሱ ውለው አደሩና የነበሩበትን ቦታ ባለማወቃችን ወደየት እንደምንሄድ ግራ ገብቶን በደረስንበት መንደር አደርን።

ነፃነት ማንጁስ ዋርድያ በነበረበት ማለዳ ከራዛ ዘመቻ፣ ከእንትጮ ጠፍተው የሚመለሱ የታጠቁ ዘማቾች በአካባቢያችን ሲያልፉ ጠራና አሳየኝ። እኔ ደግሞ ፍሱሕ ገብራይንና መገርሳ አብረውኝ እንዲሄዱ ጠይቄ ሁሉንም ማረከናቸው። ትጥቃቸውንና ብረታቸውን ተቀብለን እቃችንንና ስንቃችንን አሸከመን፣ ከአቅማችን በላይ ሁለት- ሁለት ብረት ተሸከመን ስንሄድ እነዘሚካኤል ሲመጡ መንገድ ላይ አገኘናቸው።

"እነዚህ ከየት የመጡ ሰዎች ናቸው፣ ምን አድርገውስ ነው የያዟችኋቸው?" አሉን፡

"ማርከናቸው ነው" አልናቸው።

"መልእክት አልደረሳችሁም?" ብለው ጠየቁን። መልእክት እንዳልደረሰንና በግምት ወደፊት እየሄድን እንደነበረ ነገርናቸው። ጥቂት እንደተጓዝን ከሌሎቹ ጓዶች ጋር ተገናኘን። አመራሮቹ ስለማረከናቸው ሰዎች ጉዳይ ተነጋገሩና ብረቱ እንዲመለስላቸው ወሰኑ። ምክንያቱም በዚያን ወቅት ሁላችንም ታጥቀናል፤ እንዲያውም አንዳንዶቻችን ሁለት ብረት የያዝንም አለን። ጠመንጃዎቹም የድሮ ጠመንጃዎች ስለነበሩ ለሕዝቡ በመስጠት ለፖለቲካና ለመቀስቀሻ ብንጠቀምበት ይሻላል።

ለምርኮኞቹ ማስጠንቀቂያና ትምህርት ተሰጥቶ እንዲለቀቁ ተወሰነ። ብርሃነ ኢያሱ ጥሩ የፖለቲካ ትምህርት ሰጥቶ ብረታቸው እንዲሰጣቸው አደረገ። ውሳኔው ያልጠበቁት ስለነበረ ምርኮኞቹ ደስ አላቸው፤ በእኔ ሐላፊነት የተማረኩት ሰዎችም በሰላም በመለቀቃቸው ተደሰትኩ።

መቀሌን ወደቀኝ ትተን በቆላማው መሬት ገደል ገደሉን ይዘን መሄድ ጀመርን። ቆላው ውስጥ የእንደርታ አካል የሆነች ሸከት ወይም ደርጊአጀን የምትባል





የእርሻ መሬት ያለባት ከተማ አለች። እንደደረስን ቀን ላይ ሦስት ጋንታዎች የተሳካ ወታደራዊ ተልእኮ አካሂደው አንድም ጓድ ሳይቆስልባቸው ተመልሰው ተገናኘን። ይኼ ከሆነ ከአንድ ቀን በኋላ አምስቱ ጋንታዎች በሦስት ተከፈሉና ስምሪት ተደረገ። የሦስቱ ጋንታዎች ስምሪትም ዋጅራት፣ ሳምሬ እና እንጣሎ (እንጣሎ መቀሌ አጠገብ ያለች ትንሽ ከተማ ነች)ነበረ። በእነዚህ ሦስት ወረዳዎች በአንድ ቀን ወታደራዊ ተልእኮ እንድናካሂድ ነበር የታቀደው። ቀደም ሲል ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ሁለት ወረዳዎችን (አጉላእንና ሺከትን)ተቆጣጥረናል ።

እኔ የነበርኩት ዋጅራት ወረዳ ደቡብ ወደምትባል ከተማ በሚሄደው ቡድን ውስጥ ነበር። ቀኑን ሙሉ ተጉዘን ዋጅራትን አለፍንና አዲ ቀይሕ የምትባል ትንሽ መንደር ደረስን። መንደሯ ትምህርት ቤትና የቀይ መስቀል ሐኪሞች የሚሠሩበት ክሊኒክ አላት። ከአዲቀይህ በታች ራያና አዘቦ ነው። ከራያና አዘቦ አጠገብ መሆኒ የምትባል ቦታ ደረስን። ደቡብ ዋጅራትን አልፈን፣ ራታችንን በልተን እንደገና ተበገስ ተባለ (ተበገስ፣ ማለት ተንቀሳቀሱ ማለት ነው) ። ቀኑን ሙሉ ስንሄድ ውለን ሌሊቱን እንደገና ወደ ኋላ ተመለስንና ሊነጋጋ ሲል ዋጅራት አቅራቢያ ደረስን። መጀመሪያ ዋጅራትን አልፈን እንድንሄድ የተደረገበት ምክንያት የመንግሥትን ኃይሎች ለማዘናጋትና እንዲዝናኑ ለማድረግ ነበር። ዳዊት ወዲቀሺ፣ (ብርሃነ በርሔ) ሦስት ጓዶችን ይዞ ወደ ከተማ እንዲሄድና ፖሊስ ጣቢያው፣ የወረዳው ጽሕፈት ቤትና ሌሎች ቁልፍ ድርጅቶች የሚገኙበትን ቦታ እንዲያጣራ ተላከ። የቀረው ሠራዊት እንደገና ተበገስ ተባለና ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ አንድ ኮረብታ ላይ ወጥተን ሰፈርን። ከኮረብታዋ በስተቀኝ በኩል ቤተክርስቲያን አለ። ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ አንድንድ ሰዎች ይታዩናል። ለቅኝት የተላኩት ጓዶች የሚፈለገውን መረጃ ይዘው ተመለሱ፤ የቡድኑ ወታደራዊ መሪ ጅግሳ፣ መረጃውን በመጠቀም ዕቅድ አውጥቶ ስምሪታችንንና ተልእኮአችንን አስረዳን። በዕቅዱ መሠረት ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ተፈጸመ። ፖሊስ ጣቢያውን በቁጥጥር ስር አውለን የፖሊሶቹን ትጥቅ አስፈትተን መሣሪያዎቻቸውን

ወረስን። በተጨማሪም ዘመቻ ጣቢያውን ተቆጣጥረን ስንፈትሽ ለዘማቾች የተዘጋጁ ልብሶች አገኘንና ወሰድን።

ከኦፐሬሽኑ በኋላ ወደ ምዕራብ አፈግፍገን ወደ አንድ መንደር ገባን። አንዱ ጓድ ሲጋራ ለመለኮስ በአካባቢው ከሚገኝ ገበሬ ቤት ሲገባ በገበሬው ገጽታ ላይ የመረበሽ መልክ አየንበትና ግራ ተጋባን። ወደውስጥ የገባው ጓድ ሲጋራውን ለኩሶ ሲመለስ አንዲት የዐረብ ክልስ የምትመስል በጣም ቆንጆ ቀይ ልጅ እንዳየ ነገረን። ከአካባቢው ሴቶች የተለየ ውበት፣ ቅላትና ቁንጅና ስለነበራት ማንነቷን ለማወቅ ፈለግን። ስናጠያይቅም ልጅቷ የገበሬው ሚስት መሆኗን፣ ከዚህ በፊት በአካባቢ የነበሩ ዘማች ተማሪዎች ልክ እንደእኛው በውበቷ ተገርመው ፎቶ ለማንሣት ቢጠይቁት እምቢ እንዳላቸው ሰማን። የመረበሽ መልክ የታየበት ምክንያትም ሚስቱን የምንነጥቀው መስሎት በመፍራቱ እንደሆነ ነገሩን።

ዋጅራት ተልእኳችንን ካጠናቀቅን በኋላ ብዙ አልቆየንም። ወዲያውኑ ነበር ከተማውን ለቅቀን የወጣነው። እንደርታ አካባቢ ስንደርስ ዐረፍንና ሕዝቡ የሚበላና የሚጠጣ ይዞ ካለንበት ቦታ ድረስ በማምጣት በጥሩ ሁኔታ አስተናገደን። የእንደርታ ሕዝብ ብረት የያዘ ጀግና የሚያደንቅና የሚያከብር ሕዝብ ነው። እኛን የተመለከቱን ግን በጀግና ዓይን ብቻ አልነበረም። ብዙዎቻችን ወጣቶች መሆናችንና አቀራረባችንም በተለምዶ ከሚያውቁት የሽፍታ ባሕርይ የተለየ ስለነበረ ልዩ ስሜት ተፈጥሮባቸዋል። አንዳንዶቹ ሴቶች እልል ሲሉ አንዳንዶቹ ግን እያዩን ያለቅሱ ነበር። አንዳንዶቻችን ልጆች መሆናችንን ሲያዩ "እናቶቻችሁ እንዴት ይሆኑ ይሆን? እንኳን የወለዷችሁ እኛም እናለቅሳለን! እናንተ በረሐ ወጥታችሁባቸው ከቶውንስ እንዴት አድርገው ተኝተው ያድሩ ይሆን?" እያሉ አለቀሱ። በመጨረሻ ተሰናብተናቸው ለመሄድ ስንንቀሳቀስ ዳቦና ቆሎ በየነጠላችን ይቋጥሩልን ነበር። (የእንደርታ ዳቦ በጣም የታወቀ ነው።)





ከዚያ በኋላ የሄድነው ወደ ሀረቆት ነበር። ወደ ሳምሬና እንጣሎ ከተላኩት ጋንታዎች ጋር እዚያው ሐረቆት ላይ ተገናኘንና ለሦስት ቀናት ዕረፍት አደረግን። ሐረቆት በእንጣሎና በሳምሬ መካከል የምትገኝ ትምህርት ቤት ያለባት ትንሽ መንደር ናት። ሳምሬ ኮረብታ ላይ ያለች ከተማ በመሆኗ በጣም አደገኛ ቦታ ናት። ወደ ሳምሬ የሄደው ቡድን ሳምሬ ላይ ነግቶበት አንድ ላንድ ሮቨር መኪና አግኝተው አደጋ ላይ ከመውደቅ ለጥቂት እንደዳኑ ነገሩን። መኪናውን አስገድደው በቀጥታ ወደ ፖሊስ ጣቢያው በመግባት ነበር ችግር ሳይፈጠር ተልእኮአቸውን አጠናቀው የወጡት። እንጣሎ ለመቀሌ ቅርብ ነች፤ ወደዚያ የሄደው ቡድን ትልእኮውን ለማሳካት ባደረገው ሙከራ ተኩስ እንደተከፈተ አንድ የፈጥኖ ደራሽ ረዳት መጥቶ ነበር።

ፈጥኖ ደራሹ ከመድረሱ አስቀድሞ ግን ቡድኑ ተልእኮውን ጨርሶ እየወጣ ነበር። ከቡድኑ አባላት ቢኒያም ብቻ በጥይት ቆሰለባቸው። ብኒያም ሕክምና ማግኘት ነበረበት፤ ሐኪም ተከለ ብርሀን በቅሎ ገዝቶ ወደ አሲምባ ይዞት እንዲሄድ ተወሰነና ቁስለኛውንና ሐኪሙን እዚያው ትተናቸው መንገዳችንን ቀጠልን።

የፓርቲው ሰዎችና የሠራዊቱ አመራሮች የድርጅት ሥራ ነበራቸው። እነዶ/ር ተስፋዬ ደባሳይ እዚያ አካባቢ ነበሩ። ዶክተር ተስፋዬ ለአንዳንድ ጉዳዮች ወይም ለስብሰባ ካልሆነ በስተቀር ጋንታዎቹ ወዳሉበት አካባቢ አይጠጋም። ውሎና አዳሩ ገለል ያለ ቦታ ሲሆን ከተወሰኑ ጓዶችና ከአመራሮች ጋር ይገናኝ ነበር።

ከዕረፍታችን በኋላ ከሐረቆት ተነሥተን እምባላጌን ወደግራ ትተን ወደ ማይጨው አቅጣጫ ተንቀሳቀስን። ማይጨው የመድፈኛ ጦር ሰፈር አለ። ስለዚህ የሁለት ሰዓት ርቀት ላይ ሆነን ሐረጎት ሕዝቡን ሰብስቦ የቅስቀሳ ንግግር እያደረገ ነበር። ሁልጊዜም ምግብ የምንመገበው በፈረቃ ነው። አንዱ ቡድን ሲመገብ ሌላው በሥራ ላይ ይሰማራል። እነሐረጎት በቅስቀሳ ላይ እያሉ እኛ ምግብ እየበላን ነበር።

በምግብ ላይ እያለን በድንገት የክላሽን ኮቭ ጠመንጃ አውቶማቲክ ተኩስ ሰምተን እየተሯሯጥን ሄድን። ሐረጎት ስለያዘው መሣሪያ መግለጫ ሲሰጥ በድንገት ባርቆበት ነበር። የመድፈኛው ጦር ካምፕ የሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ ስለነበረ ወታደሮቹ ተኩሱን ሰምተው ሲተራመሱ ይታዩናል። ሐረጎትም "ጓዶች የእኔ ጥፋት ነው፤ አሁን ምንም አትናገሩ፣ በኋላ እቀጣለሁ፤ አሁን ግን ከሕዝብ ጋር ነኝ" አለ።

ከዚያ በኋላ በአካባቢው መቆየት አደገኛ ነበረና የያዝነውን ይዘን "ተበገስ" ተባለና አካባቢውን ለቅቀን ከጋራዎቹ በላይ ከአሸንጌ ሃይቅ በሰተ መእራብ ወደሚገኙት ተራራዎች ሄድን። በዚያው ጊዜ የተወሰኑ ጓዶች ጸጋዬ ደብተራውንና ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይን ወደከተማ ለመሸኘት ሄደው ነበር። እነርሱ እስኪመለሱ ድረስ የአሸንጌን ሐይቅ እያየን ጋራዎቹ ላይ የሁለት ቀናት ቆይታ አደረግን። እነርሱ ከተመለሱ በኋላ አምስቱም ጋንታዎች የምእራብን አቅጣጫ ይዘን ወደሰቆጣ ወረድን።

ሰቆጣ አካባቢ ተከዜ አፋፍ ላይ፣ አምስቱም ጋንታዎች አብረው ዋሉ፤ ከአሲምባ ሲነሱ በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት አመሻሽ ላይ ሁለት ጋንታዎች አዲስ የሠራዊቱ ጦር ሰፈር ወደሚመሠረትበት ወደ ጎንደር ይሄዳሉ። ያች ምሽት ልዩ ነበረች፤ መለያየት ሞት መሆኑን እያሰብን የተላቀስንባት ምሽት! ደም ወይም አብሮ አደግነት ሳይሆን ዓላማ ያሰባሰበንና በአንድ ድርጅት ጥላ ስር አስልፎ ያስተሳሰረን ወጣቶች ነበርን። ለአንድ ዓመት ያህል ሳንለያይ አብረን ቆይተናል፤ በጣም የምንግባባና የምንዋደድም ሆነናል። እንደ ወንድማማቾች ሆነን በመፈቃቀር ብዙ ነገር አሳልፈናል። ነገር ግን ላስተሳሰረን ዓላማ ስንል እንደገና መለያየታችን አይቀሬ ሆነ፤ መለያየታችን አስፈላጊ መሆኑን ብናምንም የሐዘን ስሜታችንን ግን ማስቀረት አልቻልንም። የምንሄደው እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ለሚያስከፍል ግዳጅ





መሆኑንም አሳምረን እናውቀዋለን። ሁላችንም መንገድ ላይ የሚያጋጥመንን እናውቅም፤ እንደገና ለመገናኘታችን እርግጠኞች አልነበርንም። ያን ስሜት በውስጣችን ይዘን ነበር እየተቃቀፍንና እየተሳሳምን የተሰነባበትነው።

መሪዎቻችን ጂግሳ፣ ግደይና ሐዋዝም ልክ እንደእኛው የመለያይት ስሜታቸውን ሲገላለጹ መመልከት ልብ ይነካ ነበረ። ዛሬ ላይ ቆመን ያንን ቀን ለማስታወስ ዕድል ያገኘን፣ ያች ቀን እንደፈራናት የእውነትም ለብዙዎቻችን የመጨረሻ የመሰነባበቻ ቀን መሆኗን እንመሰክራለን። በሕይወት ለቀረነው ሰዎች የዚያች ዕለት ትውስታ ከጉልምስናችን በኋላ እንኳ ልብን የመረበሽና ዓይኖቻችንን በዕንባ የመሙላት አቅሙ ጠንካራ ነው።

የሁለቱ ጋንታዎች መሪዎች ጂግሳ፣ ግርማይ፣ የአበኢዮና ዳዊት ወዲቀሽ ነበሩ። እነዚያ ጋንታዎች በሰሜን ተራራዎች በኩል አልፈው ጎንደር ውስጥ አዲስ የሠራዊት ጠቅላይ የጦር ሰፈር እንዲመሠርቱ ነበር የተላኩት። እንዲ፤ በዘሚካኤልና በበርሔ የምትመራው ጋንታ ደግሞ ከወልዲያ ወታደራዊ ተልእኮ የሚገኘውን ገንዘብ ይዛ ወደትግራይ የምትመለስ ነበረች።

ግደይና ሐዋዝ የሚመሩት የጦር ክፍል ደግሞ በወሎ ውስጥ አዲስ የጦር ማእከል የማቋቋም ተልዕኮ ነበረው። ከተለያየን በኋላ ሌሊቱን ሙሉ ስንሄድ አደርን። ከባድ ዝናብ እየጣለ ቢሆንም ለመጠለል ፈቃድ አልተሰጠንም፤ ያ ሁሉ ዝናብ እየወረደብን ዋግን አልፈን፣ ላስታ ላሊበላ አካባቢ ደረስን። ሲነጋጋ በተራራዎች በተከበበች ሜዳ ላይ በምትገኝ መንደር ዐረፍንና ጉዟችንን ቀጠልን። ዋድላ ደላንታን ወደቀኝ በኩል ትተን፣ የአሲምባን አካባቢ ተራራዎች የሚመስል ቦታ ተመለከትን። ስንመለስ አዲስ የጦር ሰፈር እንድናቋቁም የተመረጠው ቦታ እዚህ ተራራማ ሰፈር እንደሆነ ተነገረን። ቦታው ወሎ ውስጥ ሲሆን ስሙም

ዋድላ ድላንታ ይባላል፤ ለበጌምድር ቅርብ ከሆነው ከጋይንት አውራጃ በስተሰሜን በኩል ይገኛል።

ሰኔ 24 ቀን 1968 ዓ.ም. ለአዲስ የጦር ሰፈር የተመረጠውን ቦታ በፍጥነት አልፈን፣ ወደማታ አካባቢ ቃሌም ወረዳ ገባን። ቃሌም ለወልዲያ በጣም ቅርብ ናት። አመሻሽ ላይ ከላስታ የመጨረሻው ተራራ ያለባት ቦታ ላይ ዕረፍት ተደረገ። በምናርፍባቸው ቦታዎች ሁሉ ለእያንዳንዱ ጋንታ ቁልፍ ቦታ ይመረጣል። ለጋንታችን የተመደበውን ቦታ ይዘን ትንሽ ዐረፍ እንዳልን ዘሚካኤል መጣና የስድስት ጓዶችን ስም ጠራ። የተጠራነው አማኑኤል፣ ፍሱሕ ገብራይ፣ ጁሊያኖ፣ በርሔ፣ ገረመስቀልና ኃይለ ሥላሴ ከበደ ነበርን። "በግማሽ ሰዓት ውስጥ ጠመንጃዎቻችሁን ወልውሉና ተኙ!" አለን ዘሚካኤል። ስድስታችንም የተባልነውን አደረግን። ሲመሻሽ ጋንታችን ተነሥታ ወደ ቃሌም አካባቢ ወረድን።

ቃሌም ስንደርስ ከሌሎቹ ጋንታዎች ጋር ተገናኝተን ተሰባሰብን። እኛ ቃሌያ ስንገባ ወርቁና አሊጋዝ የላስታ ሰዎች ዓይነት ኩርፊያ፣ ለብሰውና ጋቢ ደርበ ሲመጡና ሲደባለቁ አየኋቸው፤ ለጥናት ወይም ለመረጃ ተልከው እን ገመትኩ። መጀመሪያ እኛ ቀን ተኙ ተብለናል፤ በኋላ ደግሞ የወርቁንና የአሊ ዛን ሁኔታ ስመለከት ከበድ ያለ ነገር እንዳለ እርግጠኛ ሆንኩ። ነገር ግን ሁልጊዜም ምስጢር ለመጠበቅ የሚወሰድ ጥንቃቄ በመኖሩ እስከአሁን ድረስ ተልእኳችን ምን እንደሆነ ገና አልተነገረንም።

ቃሌም ደርሰን ከሕዝቡ ጋር ስንገናኝ፣ ዘላለም "እኛ ፖሊሶች ነን። የመጣነው ግብር ለማስከፈል ስለሆነ የገበሬ ማኅበሩን ሊቀ መንበር ጥሩልን" አላቸው። ሰዎቹ ግን አላመኑትም "ምናችሁም ፖሊስ አይመስልም፤ እንዴት ፖሊስ ነን ትላላችሁ?" የሚል ጥያቄ አነሡ።





"እኛ የፊናንስ ፖሊሶች ነን። ግብር ለመሰብሰብ ነው የመጣነው" ብለው መከራከር ሲጀምሩ፣ የሰዎቹ ጥርጣሬ እየተባባሰ ሄደ። በሌላ በኩል ደግሞ እኛ " ብረት ጠርጋችሁ ተኙ" የተባልነው ስድስታችን ተጠርተን ቀድመን ወደፊት እንድንሄድ ተነግሮናል። ከሌሎቹ ሁለት ጋንታዎች በተመሳሳይ ተመርጠው ከመጡት ጓዶች ጋር በጠቅላላው አሥራዘጠኝ የምንሆን ተሰበሰብን። ግደይና ሐዋዝ መጥተው አሥራ ዘጠኛችን አባላት ያለንበት ቡድን የሚሠማራበት አንድ ወታደራዊ ዕቅድ መኖሩን ነግረውን፣ ስለዕቅዱ ዓላማና አፈጻጸም በዝርዝር አስረዱን።

ዕለቱ ሰኔ 25 ቀን 1968 ዓ.ም ሲሆን የምንሄደው ወደወልድያ ከተማ ነበረ። ከተማ ከገባን በኋላ ዋና ዒላማችን ባንክ ቤቱ እንደሆነ ተገለጸልን። ወደ ከተማ የምንገባው በሁለት ተከፍለን ነው። አንደኛው ቡድን ቀጥታ ወደ ባንክ ቤት የሚሄድና የገንዘብ ዘረፋ የሚያደርግ ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ከአውራጃው ፖሊስ ጣቢያ ፖሊሶች ለእርዳታ ወደ ባንክ ቤቱ እንዳይመጡ ባሉበት ቦታ የሚያስቀር ቡድን ነበር። የዚህ ቡድን ዓላማ ወደፖሊስ ጣቢያው መግባትና መቆጣጠር አይደለም። ፖሊሶቹ ከጣቢያው እንዳይወጡ ከሩቁ በመተኮስ ባሉበት እንዲቆዩና ለእርዳታ ወደ ባንክ ቤቱ እንዳይመጡ ማድረግ ብቻ ነበር። ወደ ባንክ ቤቱ ከተላከው ቡድን ውስጥ ዳንኤል፣ የባንክ ቤቱን ዘበኛ በተቻለ መጠን ድምፅ ሳያሰማ እንዲያፍን ነው። ከታገለው ግን ሽጉጡን እንዲጠቀም ተነገረው። (ዳንኤል፣ የውቅሮ ልጅ ሲሆን፣ እውነተኛ ስሙ ጸጋዬ ኪዳኔ ነው። )

የገንዘብ ዘረፋው ከተከናወነ በኋላ ሁለቱም ቡድን በአንድ ላይ ወደ ቃሊም በመመለስ ከቀሪዎቹ ጓዶች እንድንቀላቀል ነበር የታሰበው። እኔ የተመድብኩት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ከሚሄደው ቡድን ጋር ነበር።

እንዴት እንደምንሰማራና ምን እንደምናደርግ ከተነገረን በኋላ ሌሊቱን ሙሉ ስንጓዝ አድረን ከተማው አካባቢ ደረስን። ወልዲያን እየተጠጋን እያለን አኩለ ሌሊት ገደማ የከተማው መብራት ድርግም ብሎ ጠፋ። በስተግራ በኩል ያለውን ጋራ ለመውጣት አንዱን መንደር ስናልፍ የመንደሩ ውሾች በብዛት ሆነው ይጮሀሉ። መንገዳችንን ቀጠልንና ዳገቱን ወጥተን ኮረብታ ላይ ደረስን። የወልዲያ ከተማ ስራችን ሆና ትታየናለች። እዚች ኮረብታ ላይ ሰፍረን ቀጣዩን ትእዛዝ ስንጠባበቅ ሁለት ሰዓት ያህል ለሚሆን ጊዜ ቆየን።

ግደይና ሐዋዝ ወደፊት ቀድመው ሄደዋል። ለሁለት ሰዓታት ያህል ቆይተው ተመለሱና "ወታደራዊ ተልእኮው ተሰርዟል ስለዚህ ወደነበርንበት ቦታ እንመለሳለን" አሉን።

"ይሄን ሁሉ መንገድ ከትግራይ አንድ ወር ሙሉ ደክመን ተጉዘን፣ ቤዛችን በራዛ ዘመቻ፣ ይወረር አይወረር ሳናውቅ ጥለን መጥተን፣ አንዴት አሁን ተመለሱ ትሉናላችሁ?!"ብለን ማንገራገር ጀመርን።

"የለም መመለስ አለብን። አሁን የምታነሡት ሌላ ጥያቄ ነው። ለምን እንደተመለስን ሌላ ጊዜ እናብራራለን። አሁን ግን እዚህ መቆየት ስለሌለብንና ለደኅንነታችን አደገኛ ስለሚሆን አሁኑኑ በመጣንበት መመለስ አለብን" አሉ።

"መመለሱን እንመለስ፤ እንዴት በመጣንበት መንገድ እንመለሳለን?" የሚል ጥያቄ ቀረበ። ሐሳብ መለወጥ ግን አልተቻለም። በመጣንበት መንገድ ስንመለስ፣ ሞራል የመነካት ስሜት በመፈጠሩ፤ በአብዛኞቻችን ገጽታ ላይ የመረበሽና የድካም ሁኔታ ይታይ ጀመር። የመልስ ጉዞ ጀምረን ሲነጋ ሲል ዕረፍት የማድረግ ፍላጎት ተንጸባረቀ። "ከትላንት ጀምረን አልተኛንም፤ ደክሞናል ስለዚህ ትንሽ ማረፍ አለብን" አልን።





"አይሆንም" አሉ መሪዎች።

ብዙዎቻችን ስለተናደድን፣ እምቢተኛነት እየጎላ መጣ። ከዚያም አልፎ፣ "የራሳችሁ ጉዳይ! ዞር በሉ" በማለት ስሜት ከፊሉ ቁጭ ማለት ጀመረ።

መሪዎቻችን ምንም ማድረግ እንደማይችሉ አውቀዋል፣ ስለዚህ ወደፊት አልፈው ሄደው የነበሩ ጓዶች እንዲመለሱ ተደርጎ፣ ለአንድ ሰዓት እንድናርፍ ተደረገና እንደገና ጉዞ ሆነ። የሁለት ቀናት መንገድ ሸፍነን ሰኔ 26 ቀን ኪቃሌም ፊት ለፊት ካለው ትልቅ ተራራ ላይ የሚጠብቁን ጓዶች ወዳሉበት ቦታ ደረስንና ተቀላቀልን። እንደደረስን ወደከተማ ሄደን የነበርነው አሥራ ዘጠኛችን ለሁለት ተከፍለን ምግብ በላንና እንድንተኛ ሆነ።

ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ሲሆን ፊት ለፊታችን ካሉ መንደሮች የጡሩንባ ድምፅ መሰማት ጀመረ። እኛ ግን ያለማቋረጥ የሚሰማው የጥሩንባ ድምፅ ምክንያት ምን እንደሆነ አላወቅንም። ጥሩንባ የሚነፋው ጦር እንዲሰበሰብ መሆኑ የታወቀው በኋላ ነበር። ከወልዲያ በአንድ ኮሎኔል የሚመራ ፈጥኖ ደራሽ፣ ከላሊበላ፣ ከደሴና ከአካባቢው ህዝብ የተውጣጣ ጦር አሰባስበው ሊወጉን ወደ ነበርንበት ቦታ እየመጡ ነበር። ቃሌም ላይ ተሰብስበው የአገሩን ወጣትና የጎበዝ አለቃ ከደርግ ጋር እንዲሰለፍ ቀስቅሰዋል።

ተኝተን የነበርነው አሥራ ዘጠኛችን በእንቅልፍ ላይ እያለን ተኩሱ ተከፍቶ ኖሮ ጓዶች ወደተኛንበት ቦታ መጥተው ቀሰቀሱን። የነበርንበትን ጋራ ከመጀመሪያውም የእኛ ዋርዲያዎች ይጠብቁት ስለነበረ ከላይ ሽፋን እየሰጡን ወደጋራው ወጥተን ተቀላቀልንና አብረን መከላከል ጀመርን።

የነበርነው ጥሩ ገዢ መሬት ላይ ቢሆንም እየተከላከልን እንድናፈገፍግ መመሪያ ስለተሰጠን በቅርባችን ወደነበረው ቤተክርስቲያን አቅጣጫ ስናፈገፍግ እነርሱ እኛ ይዘነው የነበረውን ጋራ ያዙት። እንደገና ከነበርንበት ቤተክርስቲያን

አካባቢ "አፈግፍጉ" ተባልንና ወደ ቤተክርስቲያኑ በስተኋላ በኩል አፈገፈግን። እነርሱ እኛ የለቀቅነውን ቦታ ያዙና አጠገባችን ደረሱ። ከዚያ በኋላ ግን "ይሄ የመጨረሻ ምሽጋችን ነው፤ ከዚህ አንለቅም" ተባለ። ምክንያቱም እንደኛ እነርሱ ብዛት አላቸው፣ ሁለተኛ የያዝነው ቦታ በግራም በቀኝም በኩል ገደል በመሆኑ በየትም በኩል ሊመጡ አይችሉም። ከበስተጀርባችን በኩል አንድ ተለቅ ያለ መንደር አለ። ያላቸው አማራጭ ፊት ለፊት መግባት ብቻ ነበረ። በቀኝና በግራ በኩል ሊከቡን ከፈለጉ የገደሉን ቁልቁል ወደታች ወርደው እንደገና ረዥሙን ዳገት መውጣት ይኖርባቸዋል፤ ያ ደግሞ የሚሞከር አልነበረም። ለዚያ ነበር አዋጊዎቹ ሐዋዝና ግደይ ይሄ "የመጨረሻ ምሽግ ነው" ብለው መርጠው ከዚያ ላለመልቀቅ የወሰኑት።

እዚያው እንደመሸግን መታኮስ ቀጠልን። ይመጣሉ፤ እንመታቸዋለን፤ ይመለሳሉ። እንደገና ለመምጣት ይሞክራሉ፤ ስንተኩስባቸው ይመለሳሉ። በዚያ ሁኔታ እንደቆየን አንዳንድ ጓዶች ቀስ በቀስ ጥይት መጨረስ ጀመሩ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደግሞ ብዙ ጓዶች ጥይት እየጨረሱ መጡ። ጥይት የጨረሱ ጓዶች ወደኋላ እንዲሄዱ ተደረገ።

እነዘላለምና ጴጥሮስ በስተኋላ በኩል ያለውን ትልቅ መንደር ሕዝብ ሰብስበው ለማግባባት እየሞከሩ ነበር። ጴጥሮስ (እውነተኛ ስሙ ተስፋዬ ደሳለኝ ሲሆን፣ከአሜሪካን አገር መጥቶ ሠራዊቱን የተቀላቀለ አማርኛና ትግርኛ በደንብ መናገር የሚችል ነበር።)

በመጨረሻ ያለንበትን ምሽግ፣ በግማሽ ክብ ቅርጽ ይዘን የመከላከል ተኩስ ላይ ሆንን። ሐዋዝ በስተግራ በኩል ግደይ በስተቀኝ በኩል ሆነው ሁለቱም እያስተባበሩ ያዋጋሉ። ጥሩ ጥሩ መሣሪያ የያዙና ጥይት ያልጨረሱ ጓዶች ወደፊት ሲያልፉ፣ ጥይት የጨረሱት ደግሞ ወደኋላ እንዲሄዱ መደረጉ እንደቀጠለ





ነው። እኔ ያለሁት ከሐዋዝ አጠገብ ነበር። ለሁለታችን የምትበቃ አንድ ጉድጓድ አግኝተን እዚያች ጉድጓድ ውስጥ ገብተን መታኮሳችንን ቀጥለናል። ሐዋዝ የያዘው ካርባይን፣ እኔ የያዝኩት መሳሪያ ደግሞ ኤም ዋን ጠመንጃ ነበር። ሐዋዝ ጥይት ጨርሷል፣ አንዳንድ ጊዜ የኔን ጠመንጃ እየተቀበለኝ ይተኩሳል። በስተቀኝ በኩል ግደይ በያዘው ክላሽን ከእነአሊጋዝ ጋር ሆኖ ሲታኮስ ይታየኛል። አንዳንዴ ግደይ ከሐዋዝ ጋር ለመመካከር መሬት ለመሬት እየተሳበና እየተንከባለለ ወደእኛ ይመጣና ተመልሶ ይሄዳል። የማፈግፈግ እንቅስቃሴ እናድርግ ወይስ እንቆይና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ይማከራሉ። "እየመሸ ስለሆነ፣ የመጨረሻችንን ምሽግ ከለቀቅን ሊከተሉን ይችላሉ፣ የደከሙና ጥይት የጨረሱ ጓዶች ስላሉን፣ እስከመጨረሻ ድረስ ወደዚህ እንዳይመጡ እዚሁ ሆነን ነው መከላከል ያለብን" ሲባባሉ ይሰማኛል። በመጨረሻ "እስኪመሽ እንጠብቅና እነሱ ቀድመው ካፈገፈጉ እኛም እናፈገፍጋለን" የሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ።

ብዙም ሳይቆይ ግን ወደ እኛ በኩል የያዙትን ጋራ ትተው ወደ ሜዳማው ቦታ ሊወጡ ብቅ - ብቅ ያሉ ወታደሮችን እየመታን ቁስለኞቻቸውንና የሞቱትን አባሎቻቸውን እንኳን ለማንሣት እናስቀርብ አልናቸው። በጣም ስለተቀራረብን ለማንሣት በሚመጡበት ጊዜ ስለምንተኩስባቸው በጣም እንደተቸገሩ ማወቅ ችለናል። በዚህ ሁኔታ ትንሽ ሞከሩና ማፈግፈግ ጀመሩ። የነበሩበትን ጋራ ለቀው መጀመሪያ እኛ ወደነበርንበት ቤተክርስቲያን አፈግፍገው እንደተመለሱ ግደይ ወደ ሐዋዝ መጣ። "አሁን እያፈገፈጉ ናቸውና ምን ብናደርግ ይሻላል" አለው።

"ቀድመው ካፈገፈጉ እኛም ማፈግፈግ እንችላለን፤ ከኋላ ካሉት ጋር ተነጋግረን ቶሎ ብለን ከዚህ ቦታ መውጣት ይኖርብናል" አለው።

አንዳንዶቻችን ደግሞ "እነሱ እያፈገፈጉ ስለሆነ የቆሰሉትና የሞቱትን ሰዎቻቸውን መሣሪያ ለምን ሄደን አናመጣም?"አልን።

"የለም አይሆንም! ማንም ሰው ከምሽግ እንዳይወጣ! ካላችሁበት እንዳትንቀሳቀሱ!! ከአሁን በኋላ ወደኋላ እንጂ ወደፊት የሚባል ነገር አንሄድም!!"አሉን። ወዲያውኑ ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመርን። ከኋላ በኩል የነበሩት አነብርሃን ኢያሱ፣ እነዘላለም፣ ለተሰበሰቡ ሰዎች የቅስቀሳ ንግግር እያደረጉ ነበር። ከሁለት አውላሎ ይዘነው የመጣነው አባል ጭንቅላቱን በጥይት ስለተመታ ጓዶች ከሰዎቹ ጋር ሆነው ይዘውት ነፍሱን ስቶ ያጣጥራል። ከዚህ በኋላ ጊዜ አልፈጀንም፤ ጓድ ገረሚካኤልን ሁላችንም ተራ በተራ ወታደራዊ ሰላምታ እየሰጠነው ተሰናበትነውና ሕዝቡ እንዲቀብረው ትተን ቁልቁል ወደታች መውረድ ጀመርን። ቁልቁለቱን ወርደን ሌሊቱን በሙሉ ስንጓዝ አደርን። ወደ ምሥራቅ በኩል አንድ ትልቅ ድልድይ አጠገብ ደረስን። ለመሻገር የተወሰኑ ጓዶች ሄደው ድልድዩን እስኪፈትሹት ድረስ የቀረነው ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ዐረፍ አልን። ፈታሾቹ ጠላት አልፎ እንዳልቆየን ካጣሩ በኋላ በፍጥነት ተሻገርን እንደ አስር ደቂቃ እንደቆየን፣ አንድ ጦር የጫነ መኪና ከወልዲያ መጥቶ ሲያልፍ አየን። ከዚያም ከድልድዩ ፊት ለፊት በቅርበት ካለው ተራራ ላይ ወጥተን ዕረፍት አደረግን።

ያንን ጦርነት ግደይና ሐዋዝ በሚገባ ነበር የመሩት። ብዙ ተሞክሮ ያላሳለፍን፣ ያን ያህል የረባ ትጥቅና ሥልጠና የሌለን ብንሆንም፣ በኮሎኔል ከሚመራ፣ በደንብ ከሠለጠነ፣ ከታጠቀና ከተደራጀ፣ እንዲሁም በሚሊሺያና በገበሬ ኃይል ከሚታገዝ ጦር ጋር ለዚያውም በቁጥር ጥቂት ሆነን ለአራት ሰዓታት ተዋግተን መመከታችን እስካሁን ድረስ እንደተአምር ያስደንቀኛል።





በተለይ አዋጊዎቻችን ግደይንና ሐዋዝን በጣም ነበር ያደነቅኋቸው። ምክንያቱም የሚያደርጉትን ነገር በሙሉ እየተመካከሩ ግንባር ቀደምሆነው ሲመሩ አይቻለሁ። በተለይ ግደይ እየተታኮሰ አንዴ በሱ በኩል ያሉት ሽፋን እየሰጡት፤ አንዴ እኛ ሽፋን እየሰጠነው፤ ወደሐዋዝ መጥቶ ይነጋገርና እንደገና ወደ ነበረበት ምሽግ ወደ እነአሊጋዝ ተመልሶ ሄዶ ነበር የሚዋጋው። አሁን ተመልሼ ሳስበው ያ የተሻገርነው ድልድይ ለወልዲያ ብጣም ቅርብ ነው። ከቃሌም የበለጠ ቅርብ ሲሆን ሜዳማ ነው። የመጣውን ጦር አሳለፍነውና ካረፍንበት ተራራ ተነሥተን ለስድስት ሰዓታት ወደ ምሥራቅ ያለዕረፍት ተጉዘን ውድዬ የሚባል ቦታ ላይ እንደገና ዕረፍት አደረግን። ከውድየ አጠገብ ወቀቶ ማርያም አለ።የነበርንበት ውድዬ የሚገኘው፣ ከወልዲያ በስተሰሜን ከወሎ ሮቢት በምሥራቅ በኩል ነው።

ሰኔ 26 ቀን 1968 ውድዬ ሰንደርስ እኩለ ቀን ሆኖአል፤ እዚያ ዐረፍንና ሕዝቡን አነጋግረን አስተባበርንና የሚበላና የሚጠጣ ሰጡን። አንዳንድ ጓዶች እንደደከሙ ነበሩና ዕረፍት ያሰፈልግ ነበር።

እኔና ፍሱሕ ገብራይ ምግብ ለመፈለግ ሄደን፣ አንድ ገበሬ አገኘን። የገበሬው አለባበሰና አነጋገሩም ጭምር ከተማ ቀመስ ይመስላል። እንደ አካባቢው አለባበስ ግልድም አድርጎ ከላዩ ላይ ግን ኮት ለብሷል፤ ጥሩ ጠመንጃም ይዟል። እኛ ምግብ ሰናሰባስብ፣ እርሱም እገዛ አደረገልን። ከዚያ በኋላ ገበሬው ፣ ለያዘው መሣሪያ ጥይት እንድሰጠው ጠየቀኝ፣ ልሰጠው ብፈልግም የእርሱ ጠመንጃ አልቀበል አለ። እሱ ጥይት ልሰጠው ስለሞከርኩለት ደስ ብሎታል። እኔ ደግሞ እገዛ ስላደረገልን ብሰጠው እደሰት ነበር። መጨረሻ ብዙ እንደሞከርኩና እንዳልሆነልኝ ሲያይ በጣም አመሰገነኝ "ጋሼ! በቃ ተወው፤ በሙከራህ ብቻ ሚሊዮን ጥይት እንደሰጠኸኝ ነው የምቆጥረው፤ ሌላ ጊዜ ስትመለስ ግን የኔ ዓይነት መሣሪያ የሚበላውን ጥይት ይዘህልኝ እንድትመጣ" አለኝና በዛው ተሰነባብተን ተለያየን።

***





**ጉራ ወርቄ**

*«....ቢሰበር አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ*

*ላዲስ ስርዓት ልምላሜ*

*ፍፁም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ህይወቴ*

*ልጓዝ በድል ጎዳና በወደቁት ጀግኖች ፋና...»*

*የኢሕአሠ መዝሙር*

ውድዬ ዐረፍ ብለን አመሻሽ ላይ ጉዞ ጀመርንና አንድ መንደር አደርን። በማግስቱ ሰኔ 27 ቀን በሌሊት ተነሥተን ጉዞአችንን ወደምስራቅ አቅጣጫ ቀጥለን ወደ ጉራ ወርቄ አመራን። ሜዳውን ጨርሰን ወደ ተራራው ለመድረስ ትንሽ ሲቀረን ነበር የሁካታ ድምፅ የተሰማን። ድምፁ እየቀረበ ሲሄድ ሁኔታውን ለማጣራት ስንሞክር የገበሬ ታጣቂ ሚሊሻዎች ከኋላችን እየተከተሉን መሆኑን አወቅን። ታጣቂዎቹ እየቀረቡን፣ መጥተው፣ አጠገባችን ሲደርሱ የመጀመሪያውን ተኩስ ከፈቱ። ተኩሱ ከተከፈተ በኋላ፣ ዘላለም በታጣቂዎቹ የተማረከ የመጀመሪያው ጓድ ሆነ። የዘላለም እውነተኛ ስም ዘርዓ ብሩክ አበበ ይባላል።

ሌሊቱ የለቀቀ ቢሆንም ፀሐይዋ ገና አልወጣችም። ከኋላችን እየተከተሉን መተኮሳቸውን ሲቀጥሉ፣ ከኋላ የነበርነው የምላሽ ተኩስ መስጠት ጀመርን። እንደአጋጣሚ እኔ የነበርኩባት ጋንታ ከበስተኋላ በኩል ነበረች። መሪዎቹ ግደይ እና ሐዋዝ ወደፊት አልፈዋል። እኛ ከኋላ ያለነው የመከላከል ተኩስ ሰናደርግ ወደፊት ያሉት ጓዶች ደግሞ ከፊት ለፊታቸው የነበረውን ተራራ ወጥተው ቦታ ለመያዝ በፍጥነት ይጓዙ ነበር። የእኛን ጋንታ ከፊት ሆነው የሚመሩት ጓዶች የቀደሙት ቡድኖች የሄዱበትን የቀኝ አቅጣጫ ስተው በተቃራኒው ወደ ግራ አቅጣጫ አምርተው ነበረና ሳናውቀው ኃይላችን ለሁለት ተከፈለ። ሐዋዝና ግደይ እሥራ

አምስት ጓዶችን ይዘው ቀድመዋል። እየተታኮስን ወደፊት ብንፈጥንም የቀደሙትን "በየት በኩል ነው የሄዱት?"ይላል - ከፊት ያለው አንዱ የጋንታችን አባል።

" በቀኝ በኩል የሄዱ መሰለኝ" ይላል ሌላው።

"ታዲያ እናንተ ለምን ወደግራ ሄዳችሁ?" በማለት ከኋላ ያለው አባል ይጠይቃል።

"ወደዚህ የመጣነውማ ተኩሱን ተከትለን ነው" ይላል -ከፊት ያለው።

"ታዲያ ምን ይሻላል? ሰዎቹ እኮ ተጠግተውናል?" ሌላው ግራ በመጋባት ይናገራል።

ወደፊት እየሄድንና ወደኋላ እየዞርን እንተኩሳለን፤ ደግሞ ወደፊት ለመፍጠን እንሞክራለን። ወደፊት ብንፈጥንም ቦታ ይዘው ለመጠበቅ ከቀደሙት ጓዶች ጋር ስለተለያየን የሚገጥመንን አላወቅንም። አደጋ ላይ መሆናችን ግልጽ ነበር። በአንዳንዶቻችን ላይ የመረበሽና ግራ የመጋባት ስሜት መታየቱ ጨመረ። ከአመራሩ ጋር ምንም ግንኙነት ማድረግ በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ስለገባን፣ አንድ መላ ካልተገኘ ወይም እነርሱ መነጠላችንን በቶሎ አውቀው ሊያገኙን ካልሞከሩ ሁሉም ነገር በጨለማ እንደመዳከር ሊሆን ነው። የኃይል አመራሮቹ ሐዋዝና ግደይ ከፊተኞቹ ጋር ቀድመው በመሄዳቸው ያለአመራር መሆናችንን አውቀናል።

በአንድ በኩል እርስ በርሳችን እየተነጋገርን፣ በሌላ በኩል እየተኮሰ ለሚከተለን ሕዝብ አልፎ አልፎ የተኩስ ምላሽ እየሰጠንና እየተከላከልን የእውር ድንብር ጉዟችንን ቀጠልን። ከትንሽ ጊዜ በኋላ የበለጠ ችግር ውስጥ መግባታችንን ያወቁ ይመስል ተኩሳቸው እየጨመረና እየበረታ መጣብን። በዚህ





ጊዜ ከፊት ለፊታችን ምሽግ በመያዝ ለመከላከል ተገደድን። ቦታ ይዘን ፊት ለፊት መታኮስ ስንጀምር ቀስበቀስ እየተከበብን እንደሆነ ተረዳን።

መከበባችንን ካወቅን፣ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ብርሃነ እያሱና ተስፋዬ ደስአለኝ ተኩስ አቁመን ከሕዝቡ ጋር እንድንነጋገር ሐሳብ አቀረቡ። በዚህ ጊዜ ከእኛ ውስጥ ጥይት ያለቀባቸውና ወደፊት ያስቀደምናቸው ጓዶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በመታኮስ ላይ የነበርነውና ወደኋላ የቀረነው አሥራ ሁለት ብንሆን ነው።

ብርሃነ እና ተስፋዬ "እኛ እናንተን የምንወጋ ሰዎች አይደለንም፤ የእናንተ ወገኖች ነን፤ ተጋዳዮች ነን" እያሉ ለማግባባት ሙከራ ጀመሩ። ከሚከተሉን መካከል ከፊት ያሉት ተኩስ እያቆሙ መነጋገር ሲጀምሩ ግማሾቹ ግን ውስጥ ለውስጥ እየተሽሎኮሎኩ ወደ እኛ እየተጠጉ እንደሆነ አየን። በጣም ሲጠጉና እየቀረቡን ሲመጡ-እንደገና ከመታኮስ ሌላ አማራጭ አልነበረንም።

ተስፋዬና ብርሃነ ፊትለፊት ወደነበሩት ሲሄዱ ከበስተ ጀርባችን ያሉት ጥይት ያለቀባቸው ጓዶቻችን በአጥቂዎቻችን እጅ ገብተው ኖሯል። ውስጥ ለውስጥ የመጡት ደግሞ ጥሰው መሐላችን ገቡ። ዘሚካኤል ከድካሙ የተነሣ የያዘውን ክላሽን መሸከም አቅቶት ጣለና ሰውነቱን ስቶ አጠገቤ ወደቀ። ጁሊያኖ ጥይት ጨርሶ ስለነበር ራሱን ስቶ የወደቀውን የዘሚካኤልን ክላሽን አንስቶ መታኮስ ጀመረ። እኔ ከዘሚካኤልና ከጁሊያኖ መካከል ሆኜ እተኩሳለሁ። ጁሊያኖም ብዙ አልቆየም፣ አንዱ ገበሬ፣ ከበስተጀርባው መጥቶ ጭንቅላቱን በመጥረቢያ ፈለጠው፤ ደሙ እንደ ኃይለኛ የምንጭ ውኃ እየፈለቀ ከአናቱ በላይ እየተረጨ መፈንጣጠቅ ጀመረ። ከዚያም ደሙ እየተንዠቀዠቀ ወርዶ በደሙ ሲታጠብና ተሽከርክሮ ሲወድቅ አየሁት። አጠገቡ የነበረው መገርሳ፣ ጥይት አልቆበት ባዶ ቀፎ ጠመንጃ ነበር የያዘው። የፈነከተውን ሰውዬ በያዘው የካርባይን ቀፎ ወርውሮ

መታውና ግብ ግብ ተያያዙ፤ በግብ ግቡ መሐል "ጁሊያኖ!! ጁሊያኖ!!" እያለ ይጮህል።

ጁሊያኖ በጣም እንደተጎዳ ባውቅም የመገርሳ ጩኸት የበለጠ አስደነገጠኝ። ዞር ብዬ ስመለከት፣ ያ! ሁላችንም በጣም የምንወደው ጁሊያኖ መሆኑን ገና ያወቅሁ ይመስል ሰንባ በዕንባ ሆንኩ። በሆዴ ጁሊያኖ! ጁሊያኖ! እያልኩ ድምፅ በሌለው ለቅሶ በውስጤ መብሰልሰ ጀመርኩ።ወዲያውኑ ደግሞ ጁሊያኖ ከወደቀበት ባሻገር ወደ አስር ሜትር ርቀት ላይ የበለጠ አስደንጋጭ ነገር ተመለከትኩ፤ አሊጋዝን ከተፋላሚዎቻችን አንዱ በጩቤ ወግቶ ጣለው። የወጋውን ሰው ደግሞ አንድ ጓድ በጥይት መታው። ምድሯ ቀውጢ ሆናለች! ሁላችንም በጭፍን ራሳችንን ከመከላከል ውጪ ምን ማድረግ እንደምንችል ለማሰብ ጊዜ አላገኘንም።

እኔ ተሰፋ መቁረጥ ውስጥ ብገባም እስከመጨረሻው ለመታኮስ ወሰኛለሁ። ምንስ አማራጭ ነበረኝ? የትኞቹን መከላከል እንዳለብኝ ግራ ገብቶኛል፤ መካከላችን እየገቡ ጨበጣ መግጠም የጀመሩ ገበሬዎች ብዙ ሲሆኑ ከፊት ለፊታችን ያሉትም እንዲሁ በርካታ ነበሩ። ወደ ግራና ቀኝ ገልመጥ፣ ገልመጥ በማለት ወደፊት ለማተኮር ወስኜ ጠመንጃዬን ደገንኩና ልተኩስ ስል ከጀርባዬ የኮቴ ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ። ለማረጋገጥ ዞር አልኩ፤ አንድ ግዙፍ ሰው ከእሾህማው ጫካ ውስጥ ዘሎ ወደ እኔ ሲመጣ ተመለከትኩ። ሰውየው ሽምግል ያለ ገበሬ ነበር። ጠመንጃዬን ልተኩስ ከደገንኩበት በኋላ አመንታሁና ተውኩት። ዙሪያዬ የነበረው ድርጊት ምንም ተስፋ እንደሌለን ያሳያል። ያነጣጠርኩበትን ገበሬ ያለ ምንም ጥቅም እንደምገለው በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ማሰቤን ሳስታውሰው ዛሬም ይገርመኛል። ሌላ ተጨማሪ ነፍስ ማጥፋት ዋጋ የሌለው እርምጃ መሆኑ ተሰማኝ። እኔ በመተኮስና ባለመተኮስ መሀል ሳመንታ ሰውየው አጠገቤ ደርሶ





ጭንቅላቴ ላይ ሰፈረብኝ፤ ተያይዘን ወደቅን። ራሴን ለመከላከል ምንም ፋታ አልነበረኝም።

"ጥይት አልጨረስክም፣ እየተታኮስክ እንደነበርም አይቻለሁ ታዲያ ለምን አልተኮስክብኝም?" ብሎ ጠየቀኝ።

"እንኳንም አልገደልኩህ!" አልኩት ድንገት። የተናገርኩትን ሲሰማ ገርሞት "ምን ማለትህ ነው?" አለኝ፤ በያዘው ገመድ በተኛሁበት እጆቼን ለማሰር እየተዘጋጀ።

"አንተ ምናልባት ሚስትና ልጅ እንዲሁም ሌሎችም የምታሳድራቸው ብዙ ሰዎች ሊኖሩህ ይችላሉ፤ እኔ ግን የማሳድረው ቤተሰብ የለብኝም። ብትገለኝም እንኳ አንድ ብቻዬን ነኝና ግድ የለኝም። አንተን ብገድልህ ልጅህና ሚስትህ ሊቸገሩ ይችላሉ። ስለዚህ እኔ አንተን ከምገድልህ፣ አንተ እኔን ብትገድለኝ ይሻላል" አልኩትና ከወደቅኩበት ተነሣሁ። ማሰሩን ተወና አጠገቤ ቆሞ ይጠብቀኝ ጀመር።

እኔና ሌሎች ጓዶች ምርኮኛ ሆንናል፤ ልባችንን የሰበረው ግን የጁሊያኖና የአሊጋዝ መጨረሻ ነበር። ዞር ስል የጁሊያኖ አስከሬን ከፊት ለፊት ወድቋል። ሁኔታው ከቁጥጥራችን ውጭ ሆኖብን ግማሾቻችን ሬሳውን እየሳምነው ማልቀስ ጀመርን፣ ሌሎቹ ደግሞ ጭንቅላታቸውን በሁለት እጆቻቸው ይዘው ይጮሃሉ። ማራኪዎቻችን ለቅሶአችንንና ሐዘናችንን አልተቃወሙም።

ኡ..ኡ..፣ እያልን ለጁሊያኖ እያለቀስን መቃብሩን ስንቆፍር አንዳንዶቹ ገበሬዎች አገዙን። ገና የጁሊያኖን ቀብር ሳናጠናቅቅ ደበሳይ ደግሞ በጦር ተወግቶ ኖሮ ደሙ በጀርባው እየፈሰሰ ተመለከትነው። የደበሳይ ሰውነት ግዙፍ ነው፤ እንኳን አንድ ሰው ሁለትና ሦስት ሰዎችም የሚጥሉት አልነበረም። እነሱም በሰተጀርባ በኩል በጦር የወጉት በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ደም በጣም ስለፈሰሰው ተንገዳገደና ወደቀ። የሚገርመው ከወደቀ በኋላ እንደምንም ተነስቶ ለመቆም መሞከሩ ነበር። ግን አቃተው፤ ትንሽ ቆየና ተንገዳገዶ ተመልሶ ወደቀ።

ሦስት ጓደኞቻችን ወድቀውብናል። ጁሊያኖና አሊጋዝ ደግሞ ተሠውተዋል። አሊጋዝ ከእኛ ትንሽ ራቅ ብለው ከነበሩት ጓዶች ጋር ስለነበረ እነርሱ ቀበሩት።

ጁሊያኖን እየጮህን ስንቀብረው ሰዎቹ የለቅሷችንና የሐዘናችንን መራርነት ተመለከቱና በጣም አዘኑ። በዚህ ጊዜ ነበር ከዚያ! ውድዬ ካገኘሁትና ጥይት ልሰጠው ሞክሬ ካልተሳካለት ሰው ጋር የተያየነው። ጠመንጃውን አውርዶ ወደሰማይ እየተኮሰ ወደእኔ መጣ። "ይሄን ጎበዝ አላሲዝም!! ይህን ጎበዝ ሁሉ ደክሞ በነበረ ጊዜ ለሠራዊቱ ምግብ ሲሰበስብ አግኝቼው ጥይት እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት። የያዘውን ጥይት ሁሉ ሞክሮልኝ የሚሆነኝ በማጣቱ ሌላ ጊዜ ሊያመጣልኝ ቃል የገባልኝ ሰው ነበርና ባለውለታዬ ነው። ስለዚህ መሄድ ወደሚፈልግበት እሸኘዋለሁ እንጂ አላሲዘውም!!" እያለ መፎከሩን ቀጠለ። የማረከኝ ሰው፤ ይመር ንጉሤ ደግሞ "እይ ግዴለም እኔም አላሲዘውም። ሊገድለኝ ይችል ነበር፣ ግን አልገደለኝም። ለምን እንዳልገደለኝ ስጠይቀው የሰጠኝ መልስ ልቤን ነክቶታልና እኔም ለማንም አሳልፌ አልሰጠውም። በፍጹም አታስብ፤ አብረን እንወስደዋለን እንጂ ምንም አይሆንም" አለና ሁለቱ ሰዎች ሌሎች ጥቃት እንዳያደርሱብኝ ከለላ ሆነው እየጠበቁኝ ግማሽ ቀን ያህል ተጉዘን ውድዬ ገባን።

መንገዱን ሁሉ ጁሊያኖና አሊጋዝ እፊቴ እየተደቀኑብኝ ሐዘኑ አልወጣልህ ብሎኝ ነበር። ጁሊያኖ በውጊያ ጊዜ ጎበዝና ደፋር፣ ለሕይወቱ የማይሳሳ፣ ለጓዶቹ የሚሠዋ ተወዳጅ ጓድ ነበር። እድገቱ ኤርትራ ሲሆን በኤርትራ ውስጥ የታወቀ ቦክሰኛ እንደነበር ሰምቻለሁ። ጁሊያኖ የሚለውን ስም ያወጣለት ሮባ ነበር። ጁሊያኖ ያለው መልኩና ቅላቱ ጣሊያናዊ ስለሚመስል ሳይሆን አይቀርም። በሲኒማ የገጸ ባሕሪ ስሙ፣ ሪንጎ፣ በመባል የሚታወቅ ጁሊያኖ ጄማ የሚባል ዝነኛ የጣሊያን ተዋናይ እንደነበረም አስታወስኩ። ሮባ ይህን ተዋናይ የቱን ያህል እንደሚያውቀው ርግጠኛ ባልሆንም ቅጽል ስሙን ያወጣለት ከዚህ ዝነኛ የጣሊያን ተዋናይ ለማመሳሰል ሊሆንም ይችላል ብዬ አሰብኩ።





አሊጋዝ የቦረና ልጅ ሲሆን ደሴ የወይዘሮ ስኂን ትምህርት ቤት ተማሪ ነበረ። (እውነተኛ ስሙ እርቀው በላቸው ነበር።) ዳሎል በሄድን ጊዜ ቆስሎ ስለነበር ለመልስ ጉዞ በቅሎ ገዝተንለት ነበር። እኛ በእግር እርሱ የፀሐይ ኮፍያ አድርጎና በበቅሎ ላይ ሆኖ ነበር የምንጓዘው። በዚያም የተነሣ ቅጽል ስሙ ምኒልክ ሆኖ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። በቅሎዋ ደግሞ ከእኛ ጋር አሲምባ እስከቆየችበት ጊዜ ድረስ አሊጋዝ እየተባለች በእርሱ ስም ትጠራ ነበር። አሊጋዝ በተለይ ከዳሎል ተልእኮ ጋር በተያያዘ የማይረሳ ትዝታ አትርፎ ነበር።

***

ወድዬ ስንደርስ ሕዝብ ሲከተለን ቆይቶ ይመር ንጉሤ መንደር እንደደረስን የደስታ ተኩስ ይተኩሱ ጀመር። ይመር ንጉሤ ምርኮኛ ይዞ የመጣ ጀግና፤ ተብሎ ነበር በተኩስና በእልልታ የታጀበ ደማቅ አቀባበል የተደረገለት። እርሱ ግን ፈገግ ከማለት ውጪ የተለየ የጀግንነት ስሜት አልታየበትም።

ይመር ንጉሤ ግቢ እንደገባን አብረውን የመጡት የአካባቢው ነዋሪዎች ቀስ በቀስ እየተሰናበቱ ሄደው ብቻችንን ስንቀር "አይዞህ ምንም እንዳትፈራ!" አለኝ። ወደቤት ውስጥ ስንገባ አምስትና ስድስት ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚሆናቸው ሁለት ሕጻናት ልጆቹን አየኋቸው። ባለቤቱ እንግዶቹን ሸኝቶ ወደ ውስጥ እስከሚገባ እየጠበቀች ነበርና ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች። እንድቀመጥ ጋበዘኝና "እንግዲህ ቤትህ ነው፤ ምንም የሚያስጨንቅ ነገር የለም" አለኝ። በግድግዳው ዙሪያ የተሠራው መደብ አጎዛ ተነጥፎበታል፤ አጠገቤ ባለው ግድግዳ ሥር ከመደቡ ላይ ተቀመጥኩና ወገቤን ግድግዳው ላይ ደገፍ አድርጌ ዐረፍ ለማለት ሞከርኩ። ይመር እንቅስቃሴየን ሁሉ በጥሞና ይመለከታል፤ ድካሜንና ጉዳቴንም የተረዳው ይመስላል። ወደ ሚስቱ ዞር ብሎ "እስቲ የሚበላ ነገር ስጪው" አላት። የምበላውና የምጠጣው ቀርቦልኝ ከቀማመስኩ በኋላ ነፍሴ ትንሽ መለስ አለች።

ከምግብ በኋላ ይመር ጨዋታ ጀመረ። ለሚስቱ ስለሆነው ሁሉ ሲያጫውታት በመገረም ሰረቅ አድርጋ ተመለከተችኝና ፈገግ አለች። ትንሽ ካወራን በኋላ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ደጃፍ እየወጣ "ና! የምታድርበትን አሳይሀለሁ" አለኝ። ተከተልኩት። ከዋናው ቤት እልፍ ብሎ የምትገኝ ትንሽ ጎጆ ቤት ውስጥ ገባንና መኝታዬን አሳየኝ። ከመኝታዬ ላይ ዐረፍ አልኩ፤ እርሱ ግን እንደቆመ የሆነ ሐሳብ እያሰላሰለ መሆኑ ያስታውቃል። "አይዞህ፣ ሁሉንም ነገር ለእኔ ተወው። ምንም ሳትሰጋ ቢደንብ ተኛና ስለወደፊቱ ደግሞ ነገ እንማከራለን" አለኝ በትኩረት እየተመለከተኝ። በዙም ሳይቆይ ተሰናብቶኝ ወጣ።





ይመር ንጉሤ ከወጣ በኋላ ተቀምጬ ብዙ ቆይቻለሁ፤ በባዶው ቤት ውስጥ በትካዜ ተውጬ ቆየሁና ጋደም ለማለት ሞከርኩ። ጀርባዬ መሬት ቢነካም፣ የወደፊት ዕድሌም ተስፋ እንዳለው ቢሰማኝም እንቅልፍ እምቢ አለኝ። ሰውነቴ በድካም የደቀቀ ቢሆንም የገጠመኝን አደጋና የተመለከትኩትን አሰቃቂ ትርኢት እውነትነት በመቀበል ራሴን ማረጋጋት አቃተኝ። ዓይኖቼ በጨለማው ውስጥ ፈጠው የዕለቱን ውሎ እንደፊልም መመልከታቸውን ቀጠሉ፤ አእምሮዬ ተበጠበጠ። ጁሊያኖ... አሊጋዝ... ደበሳይ... ጭንቅላቴ የደነዘዘ መሰለኝ፤ ሰመመን ውስጥ ገባሁ።

በሰመመኑ ውስጥ የማየውና የምሰማው የቀኑን ትርምስ ነበረ። የተኩሱ ድምፅ ሊያደነቁረኝ የደረሰ ይመስለኛል፤ ጆሮዎቼን በሁለት እጆቼ ያዝኳቸው። ደግሞ ከጓዶቼ ጋር ስንሸሽና ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ውስጥ ገብተን ስንጠፋፋ፣ የማደርገው ጠፍቶኝ ስወራጭ፣፣ ለመጥራት ስሞክር ድምፅ ማውጣት አቅቶኝ ከንቱ ጩኸት እየጮህኩ እጨነቃለሁ። ከሩቅ ደግሞ "ወይኔ ጁሊያኖ! ወይኔ ጁሊያኖ!" የሚል ድምፅ ይሰማኝና ዞር እላለሁ። አንዱ ገበሬ ጁሊያኖን በመጥረቢያ ሲመታውና አንገቱ ተቀንጥሶ እየተንከባለለ ወደገደል ሲወርድ ይታየኝና ራሴን ይዤ እንደደነዘዝኩ ብዥ እያለብኝ ደበሳይን አየዋለሁ። ከጀርባው የገባው ጦር በደረቱ ወጥቶ ሲንገዳገድ... ሊወድቅ ሲል... "ኡ..ኡ.." ለማለት ስሞክር ድምፄ አልወጣ ብሎኝ ልቤን ሲጎትተው በላብ ተዘፍቄ ብንን አልኩ።

ከተጋደምኩበት ተነሥቼ ቁና ቁና እየተነፈስኩ ቁጭ አልኩ። ነቅቼም የምቃዥ መሰለኝ። ግን ቅዠት አልነበረም ሁሉም ነገር እውነት ነበር። ጁሊያኖ ሞቷል ቀብረነዋልም፤ "ደበሳይስ ግን ይተርፍ ይሆን? ኧረ በጭራሽ! ምንስ ግዙፍ ቢሆን ያ ሁሉ ደም ፈስሶት እንዴት ይተርፋል? በዚያ ላይ ደግሞ በጠላት እጅ ነው የነበረው፤ አይ አይተርፍም! በፍጹም አይተርፍም!" እላለሁ ለራሴ። ተቀምጬ በቁም ቅዠት ስንገላታ ረዥሙ ለሊት አልገፋ ብሎኝ ስጨነቅ ቆየሁ፤ እንደገና ቀኑን የማላየው መሰለኝ። ነገር ግን ወዲያውኑ የወፎች ጫጫታ

ተሰማኝ። "እፎይ" አልኩ ሳላስበውም ያንን ረዥም የስቃይ ሌሊት ያነጋውን ፈጣሪ አመሰገንኩ።

ሰኔ 28 ቀን ጠዋት ሆነ። ከአደርኩባት ትንሽ ጎጆ ቤት ወጣሁ፤ የጠዋቱ ቀዝቃዛ አየር ሰውነቴን ሲዳስሰው ጉልበት የሰጠኝ መሰለኝ። ግቢው ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያልኩ አካባቢውን ማጥናት ጀመርኩ። የይመር ንጉሤ ቤት የተሠራው ተራራ ጫፍ ላይ ነው። ከፊት ለፊት ሰፈሩና አደባባዩ ቁልጭ ብለው ይታያሉ። ከበስተጀርባው በኩል የዱር እንስሳት የሚያኖር ጥቅጥቅ ያለ ደን ሲሆን በግራና በቀኝ በኩል ገደላ ገደል ነው።

ሕዝብ ሸንጎ የሚሰበሰብበት ትልቅ ዛፍ ያለበትን ሜዳ ግቢው ውስጥ ሆኜ አሻግሬ ተመለከትኩ። ወደ አደባባዩ የሚያደርስ ኮሮኮንች የመኪና መንገድ አለው። ትንሽ ቆይቶ የመኪና ድምፅ ሰማሁ። አንድ የፖሊስ መርሰዲስ የጭነት መኪና በኮረኮንቹ መንገድ ላይ ሲመጣ አስተዋልኩ። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ፖሊሶቹ የላኩት ሰው ወደ ይመር ንጉሤ ቤት መጣ። የፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች በይመር እጅ ምርኮኛ መኖሩን ሰምተው እንዲያስረክብ ሊጠይቁ መምጣታቸውን መገመት ከባድ አልነበረም። ወዲያውኑ ወደ አእምሮዬ የመጣው የማምለጫ አቅጣጫዬን መምረጥ ነበርና ግራና ቀኙን ማየት ጀመርኩ። የይመር ንጉሤ ቃል ደግሞ በአእምሮየ ውስጥ ተመላለሰ "ለማንም አሳልፌ አልሰጠውም!" ነበር ያለው። ቃሉን እንድማያጥፍ ልቤ ተቀብሎታል።

ይመር ወደእኔ መጣና "አንተን ፍለጋ እንደመጡ ርግጠኛ ነኝ። ለማንኛውም ወደ ጓሮ ዘወር በል፤ ሆኖም በጭራሽ ሊያሳስብህ አይገባም፤ ገድዬዋለሁ እላቸዋለሁ። ቤቱን የመፈተሽ አዝማሚያ ካሳዩኝ ግን ወደሰማይ እተኩሳለሁ፣ የተኩሱን ድምጽ ሲሰማ ደግሞ መንደሩ በሙሉ መሣሪያውን ይዞ ይወጣል እንጂ፣ እኔን አሳልፎ አይሰጠኝም። ፖሊሶቹም ባህላችንን አሳምረው ስለሚያውቁ አይታኮሱም፣ ወደመጡበት ይመለሳሉ። አይዞህ!" ብሎኝ ሄደ። ሲመለስም ልክ





እንዳሰበው መሆኑንና "ገድየዋለሁ" ሲላቸው ምንም ሳያንገራግሩ እንደተቀበሉት ነገረኝ።

ከሰዓት በኋላ ደግሞ ሌላ ነገር አስከትሎ ከተፍ አለ። ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ እረኞች የሚመስሉ ሁለት ልጆች መጡ።"እንደምን ዋላችሁ፣ እዚህ ቤቶች" ብለው ሰላምታ ሰጡና ግቢ ገብተው፣ ይመር ንጉሤን ሊያነጋግሩ እንደሚፈልጉ ተናገሩ። ይመር ሲወጣ ከቤቱ ወደታች ይዘውት ወረድ ብለው ለብቻው አነጋገሩትና አብረው ተመለሱ።

አጠገቤ ሊደርሱ ሲሉ፣ ይመር ንጉሤ ነጠል ብሎ ወደእኔ መጣና "አማኑኤል! የአንተ ሰዎች ሊያነጋግሩህ መጥተዋል፤ ምንም አትፍራ አነጋግራቸው" አለኝ። ልጆቹን አነጋገርኳቸው።

"የመጣነው አንተን ለማየት ነው፣ ጤንነትህ እንዴት ነው?" አለኝ፣ አንደኛው።

"እኔ ደኅና ነኝ፣ እናንተ እነማን ናችሁ?" አልኳቸው።

"እኛን በግል አታውቀንም። የመጣነው ግን አንተን ፍለጋ ነው" አለኝ ሁለተኛው።

"እንዴት እኔን ፍለጋ ልትመጡ ቻላችሁ፣ ማን መሆኔን በምን አወቃችሁ፣ ማንስ ልኳችሁ ነው?" በማለት ጥያቄዎች አከታተልኩ።

"ድርጅታዊ ተለኮ ነው የተሰጠን፤ ይመር ንጉሤን አነጋግረነዋል። ማገዝ የምንችለው ነገር ካለ ብለን ነበር አመጣጣችን" አለኝ ሌላው።

"ይመር ንጉሤን ምንድነው ያነጋገራችሁት?" አልኩ በሐሳቤ በርካታ ነገሮች እየተመላለሱ ።

"ዋናው ነገር ይመር አሳልፎ እንደማይሰጥህ ቃል መግባቱ ነው" አሉኝ። ይመር የእነዚህን ልጆች ማንነት እንዴት ሊያውቅ እንደቻለ ገርሞኛል። ይመር ንጉሤ ምንም ችግር አልፈጠረብኝም፤ ማታም በሰላም አሳድሮኛል። እነዚህን ሰዎች ግን አላውቃቸውም። የደርግ ሰላይ ሊሆኑ፣ ወይንም ሌላ ዓላማ ሊኖራቸው ይችላል።

አሳዳሪዬ ግን በእኔ ላይ መጥፎ አመለካከት እንደሌለው አውቄ ተማምኜበታለሁ። ታዲያ እነዚህ ሰዎች ምን ያደርጉልኛል?" ከራሴ ጋር ነበር የተነጋገርኩት። እነዚህ ልጆች ማንም ይሁኑ ማንም እኔ የይመርን ሐሳብ መከተል እንደሚኖርብኝ ወሰንኩ።

"አይ፣ እኔ እናንተን አላውቃችሁም! ምንም የማናግራችሁም ነገር የለኝም! ላነጋግራችሁም ፈቃደኛ አይደለሁም!" አልኳቸው ኮስተር ብዬ።

ውሳኔዬን ከሰሙ በኋላ እርስ በእርሳቸው በዓይኖቻቸው ሲነጋገሩ አየኋቸው። ነገራቸው አላማረኝም፤ አሁን ደግሞ የበለጠ ቀፈፉኝ። "ምን ሊያመጡብኝ ነው" ብዬ ራሴን እያዘጋጀሁ ነበር። የሚቀጥለውን እርምጃቸውን እያሰላሰልኩ የሁለቱንም እንቅስቃሴ በትኩረት እከታተላለሁ። አንደኛው ግልድሙን ገለጥ ሲያደርግ አየሁና አቋቋሜን አስተካክዬ ተመቻቸሁ። ከግልድሙ ውስጥ ያወጣው ግን እኔ የገመትኩትን ሳይሆን፣ የማኦ ሴቱንግን ትንሽ ቀይ የኪስ መጽሐፍ ነበር።

መጽሐፏን አውጥቶ ምንም ቃል ሳይናገር አሳየኝና ምን ዓይነት ስሜት ሊፈጥርብኝ እንደሚችል ለመመልከት ጠበቁ። አሲምባ እያለሁ ይህችን መጽሐፍ በአንዳንድ ጓዶች እጅ አይቻታለሁ። ገና ያቺ መጽሐፍ መሆኗን ሳረጋግጥ መላ ሰውነቴን ወረረኝ። ዓይኖቼ በዕንባ ተሞሉና ሳላስበው ጉንጮቼ ላይ ሲወርድ ተሰማኝ። ስሜቴ ፈንቅሎኝ ማልቀስ ስጀምር መጽሐፉን የያዘው ልጅ ጠጋ ብሎ ትከሻዬን አቀፈኝ። አቀፍኩት፤ ገና መገናኘታችን ይመስል ተሳሳምን። ከሁለተኛውም ጋር እንዲሁ ተቃቀፍንና ተሳሳምን። ከዚያ በኋላ በአዲስ ጓዳዊ መንፈስ ተማምነን መነጋገር ጀመርን።

ይመር ይህ ሁሉ ሲሆን በመገረም ከመመልከት በስተቀር ጣልቃ አልገባም፤ ይመር ንጉሤ ደርግን በጣም እንደሚጠላ ከመስማቴ በስተቀር የኢሕአፓ ደጋፊ መሆኑን ለመጠርጠር የሚያስችል ምልከት አላገኘሁም። ያን ዕለት ደርግ በራዛ





ዘመቻ እንዲሳተፍ እንደጠየቀውና አልዘምትም ማለቱን ነገረኝ። በጣም የሚገርመው ይመር ንጉሤ የራዛ ዘመቻን ለመዝመት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከአካባቢው አንድም ሰው ወደ ዘመቻ ሳይሄድ መቅረቱ ነበር።

"ሰውየው ወደ አገርህ አሳፍሮ እንደሚሸኝህ ነግሮናል። ነገ ወደ ሮቢት ቢያሳፍርህ ለመሄድ ተዘጋጅተሃል? ትችላለህስ?" አሉኝ። "አዎ፣ እችላለሁ" አልኩ።

"በጣም ጥሩ ነው" አሉኝ። ለጉዞ የሚያስፈልገኝ ዝግጅት መኖሩን ነገሩኝ፤ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት በመሞከር ላይ እያለሁ ጸጉሬን መላጨት እንደሚኖርብኝ ተነገረኝ። ጸጉሬን ላጭተው ቅቤም ቀቡኝ። ከዚያ በኋላ የሚነግሩኝን ሁሉ ያለጥያቄ መቀበል ያዝኩ። ከይመር ጋር ተነጋገሩና ልብሶች አመጣልኝ፤ የአካባቢው የባህል ልብስ ነበረ። ግልድም እንዴት እንደሚገለደም ለመጀመሪያ ጊዜ ዓየሁ። በግልድሙ ላይ የሚደረበውም ጋቢ የተለየ አለባበስ ነበረው፤ ሁሉንም በሚገባ አለማመዱኝ። "ከዚህ አካባቢ እስከምትወጣ እንደዚህ ተመሳስለህ ራስህን ካልለወጥክ ብዙ ችግር ሊያጋጥምህ ይችላል፤ አለባበስህም ጥርጣሬ የሚፈጥር እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልግሃል" አሉኝ። ለመሳፈሪያ የሚሆነኝን ገንዘብም ሰጡኝ።

በጣም አመሰገንኳቸው፤ እነርሱም መልካም ዕድል እንዲገጥመኝ ተመኝተውልኝ ተሰነባበትንና ተመልሰው ሄዱ። (ከእነዚህ ሁለት ወጣቶች አንደኛው፣ አበበ ተፈራ የሚባል ሲሆን በወሎ ዘመቻ አብሮን የነበረና በሕይወት የተረፈ እንዲሁም፣ በኋላ ላይ ኃይል ሦስት ሆኜ የኃይሏ የፖለቲካ ሐላፊ የነበረው የሺፈራው ታላቅ ወንድም እንደሆነ ከቆየሁ በኋላ አወቅሁ።) እነርሱ በሔዱ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ይመር ንጉሤ መጥቶ "ና እንሂድ" አለኝ።

"የት ነው የምንሄደው?" አልኩት፤ ወደወሎ ሮቢት የምንሄደው ሌሊት ይሆናል ብዬ ገምቼ ሆኖም ድንገት ለመሄድ እንድዘጋጅ ሲነግረኝ ግራ ተጋባሁ።

"ዛሬ እዚህ ማደር የለብህም። የደርግ ሰዎች እዚህ መኖርህን አውቀዋል፤ ጠዋት መጥተው ጠይቀው ቢሄዱም እንደገና ሊመጡብን ይችላሉ? " ሲለኝ በጣም ደነገጥኩ። ይኼን ስጋቱን እስካሁን አልነገረኝም ነበር።

"ታዲያ አሁን ወዴት ነው የምንሄደው?"ብዬ ጠየቅኩት እንደገና።

"አሁን የምንሄድበት የባለቤቴ ቤተሰቦች ሀገር፣ ለወሎ ሮቢት ቅርብ ነው። እዚያ ሄደን እናድርና በጠዋት ወሰጄ አውቶብስ አሳፍርሀለሁ" አለኝ።

በመጀመሪያ ከይመር ጋር ከሆንኩ ምንም እንደማልሆን ሙሉ እምነት አድሮብኝ ነበር። አሁን ይህን ሐሳብ ሲያመጣ ግን ከፍተኛ ስጋት ተሰማኝ። እሱን ተጠራጥሬው አልነበረም፣ ምናልባት ፖሊሶቹ እንቅስቃሴያችንን እየተከታተሉ ከሆነ፣ መንገድ ላይ ሊይዙን ይችላሉ የሚል ጥርጣሬ ገብቶኝ ነው። ያ ከሆነ ደግሞ አደጋው በእኔ ሕይወት ብቻ የሚመጣ ሳይሆን፣ ለይመርም ሕይወት የሚያሰጋ ይሆናል። ይህንን ስጋቴን ለይመር መናገር ስለከበደኝ ዝም አልኩት።

መንገድ ስንጀምር እየመሸ ነበር። ከቤት ተነሥተን መንደሩን ለቀን እስከንወጣ ድረስ የተለመደውን የእግር መንገድ አልተከተለም፤ አሳቻ መንገዶችን እየተጠቀመ እንደነበር ተገንዝቤአለሁ። ይመር በዚያ ግዙፍ ሰውነቱ መሣሪያውን ታጥቆ በንቃትና በጥንቃቄ ከፊት ከፊቴ ሲራመድ በአቋሙ እየተገረምኩ ነበር የምከተለው።

ከመንደሩ ብዙ ከራቅን በኋላ መደበኛውን መንገድ ይዘን መሄድ ቀጠልን። መንገዳችን የማታ ጉዞ ስለነበረ፣ የምንሄድበትን አቅጣጫና ያለፍናቸውን ቦታዎች ለማወቅ አልቻልኩም። በጭፍን ይመርን ከመከተል ውጪ አማራጭ አልነበረኝም።





ከኋላው እየተከተልኩት በሆነ አጋጣሚ ችግር ሊፈጠር ቢችልና እኔን አሳልፎ ላለመስጠት ሲል አንድ ነገር ቢሆንስ? የሚል ሐሳብ በአእምሮዬ መመላለስ ጀመረ:: እቤት ጥለናቸው የመጣነው ባለቤቱንና ሁለቱ ሕፃናት ልጆቹን አስቤ በጣም ጨነቀኝ። የእኔ ህይወት እንዴ አደጋ ውስጥ የወደቀና የወደፊቱም ዕጣዬ ያልለየለት ስለሆነ፣ ለሚመጣብኝ ማንኛውም ነገር ተዘጋጅቻለሁ። ከቻልኩ ለማምለጥ መሞከር፣ አለያም ሞትንም ቢሆን መቀበል ግዴታዬ መሆኑን አምንበታለሁ።

የምናልፍበትን ቦታ ሁሉ በጥንቃቄና በንቃት እየተመለከተ እንደሚጓዝ አስተውያለሁ። ስለእኔ ደኅንነት በጣም እንደተጨነቀና ካሰበው ግብ ሳያደርሰኝ የሚመለስ ሰው እንዳልሆነም አውቄያለሁ። ብቻ በዚህ መካከል... እያልኩ ስለ እርሱ ደኅንነት በማሰብ ነበር አእምሮዬ የተወጠረው። ያሰበበት ቦታ በሰላም ብንደርስ እንኳ፣ እዚያ ስላለው የፖሊሶች ሁኔታ ምንም አላውቅም።

ፖሊስ ጣቢያው ከምናድርበት ቤት ጎረቤት ቢሆንስ፣ በቤቱ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ ባይኖር እንኳ፣ ምናልባት የመምጣታችን ወሬ ተሰምቶ ችግር ቢፈጠርስ፣ እኔ ለሀገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ ነኝ። እርሱም ቢሆን እንደ ጉራ ወርቄ፣ ጎረቤቶቹን ተማምኖ ለማስፈራራት የሚችልበት ሁኔታ የሚኖረው አይመስለኝም፤ ሐሳቤን ግን ለይመር አልነገርኩትም።

እኩለ ለሊት ገደማ ሲሆን ከባለቤቱ ቤተሰቦች ቤት ደረስን። ግቢው ውስጥ ከመግባታችን በፊት ምንም ስጋት እንዳያድርብኝ በድጋሚ ነገረኝ፤ ማለዳ ማንም ሰው ከመንቃቱ በፊት አውቶብስ ተራ እንደምንሄድና እንደሚያሳፍረኝ ለማስተማመን እየሞከረ ነበር። "ምንም ችግር ቢፈጠር ማንኛውንም ኃይል ለመከላከል የሚያስችል በቂ ጥይት አለን" አለኝ ደግሞ የመጣው ቢመጣ ቃሉን ለማክበር ያለውን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ።

ይመር እንዳለውም በሚቀጥለው ቀን ማንም ሰው ሳይሰማ፣ ድምፃችንን አጥፍተን ለመውጣት በማለዳው ተነሣን፤ ይመር ግልድሙን ሳገለድም አገዘኝና መሳሪያውን ይዞ ፊትና ኋላ ሆነን ወደ አውቶብስ ተራ ሄድን።

***





ከወሎ ሮቢት አሲምባ

"የጀግና ሰው መልኩ ሁለት ብቻ ነው፤

አንድ ፊት መሥዋዕት በአንድ ፊት ድሉ ነው፤

የሁሉም ማሰሪያ ማተቡ ብቻ ነው ።"

ከይመር ንጉሤ ጋር አውቶብስ ተራው ወደሚገኝበት ወደ ከተማው እየተቃረብን ስንመጣ ምን ሊያጋጥመን እንደሚችል እያሰላሰልኩ ሰውነቴ እንደገና መሸበር ጀምሯል። ፖሊስ ወይም ሌላ የመንግሥት ሰላዮች ቢያጋጥሙን በእርሱ ከመተማመን በስተቀር ምን ማድረግ እንደምችል እያሰብኩ አማራጮቼን በአእምሮዬ እያሰላሰልኩ ሳለሁ ነበር አውቶብሱ ተራ የደረስነው።

ከተማ ከገባን በኋላ ፖሊስ ባያጋጥመንም ሰው በሙሉ የታጠቀ ስለነበር ከበደኝ። የሚያገኙት ሰዎች በሙሉ ለእርሱ የአክብሮት ሰላምታ ይሰጡትና እኔን በጥርጣሬ ይመለከቱኛል። የእነርሱን ዓይነት ልብስ ብለብስም የማኅበረሰቡ አባል አለመሆኔን በማወቅ በአትኩሮት እያዩኝ ስለ ጉራ ወርቄ ጦርነት ይጠይቁታል።

አውቶቡስ ተራው አካባቢ ስንደርስ ከዋናው መንገድ በስተምዕራብ በኩል ወደሚገኝ አንድ ጠላ ቤት ገባን። ውስጥ የነበሩት ሰዎች ይመርን በሰላምታ ተቀበሉት። እሱም ሰላምታቸውን በመመለስ እንደየሁኔታው ያናግራቸዋል። ሰላምታው የበዛው የጉራ ወርቄ ወሬ በስፋት ተሰምቶ ሊሆን እንደሚችል ገምቻለሁ፤ ይመር ግን ወሎ ሮቢት ውስጥም የሚታወቅ ሰው እንደሆነ ተረዳሁ።

ቦታ አግኝተን ተቀምጠን ትንሽ እንደቆየን ከፊታችን ከተቀመጡት ሰዎች አንደኛው ጠላውን ጎንጨት አድርጎ መልሶ ካስቀመጠ በኋላ ወደእኔ ተመለከተና "ከትላንት ወዲያ የሆነውን ሁሉ እኮ ሰማን። ይኼ ነው እንዴ የማረከው ኮበሌ?" ብሎ ጠየቀው

"አይ ይኼ እንኳን እረኛዬ ነው። ምርኮኛየንማ ገድየዋለሁ" ብሎ በመኮሳተር ተመለከተው። እኔ ሰው መግደል ያን ያህል እንደቀላል ነገር መነገሩ እየገረመኝ ነበረ፤ ሰውየው የሰማውን ማመኑን ተጠራጥሬአለሁ።

ይመርም ሁኔታውን ተገንዝቦታል "ይኼ እረኛዬ ነው። ዘመዶቼን ስለናፈቀ፣ ወደሀገሩ ልሸኘው ነው ያመጣሁት" እለና የበለጠ ለማሳመን ሞከረ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ አስተማሪዎች የሚመስሉ ሰዎች ወደጠላ ቤቱ ገብተው እኔና ይመር ከነበርንበት አቅራቢያ መደቡ ላይ ተቀምጠው ነበር። ሰውየውና ይመር የተነጋገሩትን ካዳመጡ በኋላ "ይኼ እረኛህ ወደሀገሩ ሲሄድ መልእክት የሚያደርስልን ከሆነ እንዴ እናነጋግረው?" ብለው ይመርን አስፈቀዱት። ይመር ፈቃደኝነቱን ገለጸላቸውና ወደውጭ ይዘውኝ ወጥተው፣ በአቅራቢያ ወደነበረ ሻይ ቤት ወሰዱኝ። ማን እንደነገራቸው ባላውቅም ስለእኔ የሚያውቁ መሆናቸውን ተረድቻለሁ። ሻይና ዳቦ አዘውልኝ በልቼ ስጨ ርስ ትንሽ አወሩኝና "አይዞህ! ይሄ ደግሞ ለአንዳንድ ነገር ይጠቅምሀል" ብለው ገንዘብ ሰጡኝ። ልክ ይህንን በማውራት ላይ እያለን ወደ መቀሌ የሚሄደው የወሎ ፈረስ አውቶብስ ጡሩምባውን እያስጮኸ መጣ። አውቶብሱ መምጣቱን ስሰማ "የየት መኪና ይሆን?" አልኳቸው ሰዎቹን።

"መቀሌ ነው" አለኝ አንደኛው ቀልጠፍ ብሎ።

ከመጣደፌ የተነሣ ወደ ይመር እንኳ መለስ ብዬ ሳልሰናበተው ወደ አውቶብሱ በሩጫ ሄጄ ተሳፈርኩ። ይመር አውቶብሱ መምጣቱን ሲሰማ ይመስለኛል ከጠላ ቤት ወጥቶ በዓይኖቹ አሻግሮ ሲፈልገኝ አየሁት። በመስኮት በኩል አንገቴን አውጥቼ "ደኅና ሁን!" በማለት ተሰናበትኩት።

***





አውቶብሱ ሞተሩን አስጮኸና ተንቀሳቀሰ፣ የልቤ ምት ሲጨምር ተሰማኝ። በሐሳቤ በመንገድ ሊያጋጥመኝ ስለሚችል ችግር ሳውጠነጥን ቆየሁና "የሚገጥሙኝን ችግሮች አልፌ ተመልሼ አሲምባ እገባ ይሆን? ለመሆኑስ ስንት ጓዶች ይህ ዕድል ገጥሟቸው ይሆን?" ወደሚል ሌላ ሐሳብ ገባሁ። ዕድሉ ያልገጠማቸውና ከመጀመሪያውም ለከፉ አደጋ የተጋለጡ ጓዶቼን ሳስብ፣ ያሳለፍነው የጦርነት ትርኢት በዓይኔ ላይ መጣ።

የሰዎች ጩኸት፣ የጁሊያኖና የአሊጋዝ አሟሟት፣ በደበሳይ ጀርባ የገባው ጦርና የተንዘርቀዘርቀው ደሙም ፤ የአሊጋዝ አወዳደቅ፣ የጁሊያኖ ሬሳ ላይ ተደፍተን ስንላቀስ" ጁሊያኖ!! ጁሊያኖ!!" የሚል ጩኸት እየተሰማኝ፣ በሃሳብና በታዜ ጭልጥ አልኩ። አውቶብስ ውስጥ መሆኔንና በማላውቃቸው ሰዎች መካከል መሆኔ ሁሉ ተዘንግቶኛል። በግምባሬ ላይ መፍሰስ የጀመረው ላብና የዓይኖቼን ቋት ሞልተው ዱብ ዱብ የሚሉት የእንባ ዘለላዎች ምን ዓይነት እንግዳ ስሜት ውስጥ እንደነበርኩና ምን ያህል ራሴን መቆጣጠር እንዳቃታኝ ይናገሩ ነበር። ድንገት ወደ ኅሊናዬ ተመለስኩና ደነገጥኩ፤ ሰዎች ሁኔታዬን ልብ እንዳይሉ ከፊቴ ያለውን መቀመጫ በሁለት እጆቼ ይዤ ጭንቅላቴን በእጆቼ መካከል ቀበርኩት። ስሜቴ ቀዝቀዝ እስኪልና ገጽታዬ መለስ እስኪልልኝ በዚያ ሁኔታ እንደተደፋሁ ቆየሁ።

አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው የከተማ ሰው የቅቤዬ ሽታ ሳይስማማው ቀርቶ ይመስለኛል ወንበሩን ትቶ ከቢጤው የከተማ ሰው ጋር ተዳብሏል። ያለሁት ለብቻዬ መሆኑ ተመችቶኛል። መኪናው ፍጥነቱን እየጨመረ ነበር። በመስኮት የሚታየኝ ተራራ፣ ሸንተረርና ሜዳው እንዲሁም ዛፎቹ ሁሉ ወደ ኋላችን እየተፈተለኩ ይጠፋሉ። ዞር ብዬ በስተቀኝ በኩል ባሉት ወንበሮች ላይ የተቀመጡትን ሰዎች ተመለከትኩ። አንዳንዶች እርስ በርሳቸው ያወራሉ። ከመስኮቱ ጥግ የተቀመጡ አንድ ሽምግል ያሉ ሰው አንገታቸውን ወደኋላ ዘንበል አርገው እንቅልፍ ሸለብ አድርጓቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ እንደእኔው ሁሉ በራሳቸው ሐሳብ ውስጥ ገብተው

ወደኋላ የሚወረወረውን የገጠር ትእይንት እያዩ ቅዝዝ ብለዋል። ከኋላዬ ባለው ሁለት መደዳ ወንበሮች ላይ ስድስት ባላገሮች የቤተሰብ ጫወታ ይዘው ሐዘን በተቀላቀለበት ስሜት ያወራሉ። ከሴቶቹ አለባበስ ለለቅሶ እንደሚሄዱ ገመትኩ።

ድንገት አውቶብሱ ፍጥነቱን ቀነሰና ቆመ። የደረስንበትን ቦታ ለመለየት ቀና አልኩና አጠገቤ ባለው መስኮት ቃኘት አደረግኩ። ከመኪናው ፊት የፍተሻ ኬላ መኖሩን አየሁ፤ ጥቂት ወታደሮች ከዳር ቆመው ሹፌሩን እያነጋገሩት ነበር። "የመጀመሪያው ፈተና" አልኩ በልቤ። የተለየ አጋጣሚ ካልተፈጠረ በስተቀር የያዝኩት አንድ በእጅ የሚንጠለጠል የልብስ ቦርሳ ብቻ ሲሆን በውስጡም ምንም እስጊ እቃ የለበትም። ግን ምን ይታወቃል? አንዳንዴ በማያውቁት ሀገርና በማያውቁት ሰው መሀል በመገኘት ብቻ የሚያጋጥም ችግር አለ። "ሆነም ቀረ ወርዶ መፈተሽና የሚመጣውን ማየት ነው" አልኩና ከፊቴ ያሉትን ሰዎች ተከትዬ ለፍተሻ ወረድኩ።

ከፊት ለፊቴ አንድ የሃምሳ አለቃ ማዕረግ ያለው ፈታሽ ቆሟል። ራመድ ብዬ አጠገቡ ስደርስ፤ ለመፈተሽ ሁለት እጆቼን እንደማንሳት አደርግሁ። "ዞር በል፣ ግማታም" አለኝና አፍንጫውን ይዞ ወደኋላው ሸሸ። የራሴን ቅቤ ረስቼው ግራ ገብቶኝ ነበር፣ ወዲያውኑ ግን አለባበሴና የተቀባሁት ቅቤ ትዝ አለኝ። ተመልሼ ወደ መኪናው ውስጥ ስገባ ደግሞ ሌላው ፈታሽ ወታደር ከመኪናው ውስጥ ሆኖ ግራና ቀኝ እየቃኘ የተሳፋሪዎችን እቃዎች ዳበስ አድርጎ ወዳገኘበት ቦታ ይመልሳል።

ለፍተሻ ያልወረዱ ባላገሮችና ሴቶች ጫወታቸውን አቁመው የሚፈትሸውን ወታደር ይመለከታሉ። ሴቶችና የባላገር ወንዶች እንደማይፈተሹ የሰማሁት ቆይቼ ሲሆን የሚፈተሸው የከተማ ሰው ብቻ መሆኑን ተገነዘብኩ።





መጀመሪያ አጠገቤ የነበረው ሰው ተመልሶ መጥቶ ከወንበሩ ጫፍ ላይ ተቀመጠና ወደ እኔ እየተመለከተ ፈገግ በማለት የማግባባት ፊት ካሳየኝ በኋላ "ከየት ነው የመጣኸው?" ብሎ ጠየቀኝ። እንዲህ ዓይነት ጥያቄ የሰላምም የጨዋታ ፍለጋም ሊሆን ይችላል፤ እኔ ግን ደስ አልልህ አለኝ።

"ከወሎ ሮቢት" አልኩት።

"አሀ! ወሎ ሮቢት?"አለና ዝም አለ።

የተጠራጠረኝ ስለመሰለኝ "አንድ አስተማሪ ወንድም ነበረኝ፣ እሱን ፍለጋ ነው የመጣሁት" አልኩ ሳይጠይቀኝ።

የኔን መልስ ችላ ብሎ፣ ባሻገር ያለውን ጓደኛውን ማነጋገር ጀመረ። "ሰሞኑን፣ እዚህ አካባቢ እኮ የብርሃነ መስቀል ሰዎች ተይዘዋል ይባላል" አለው።

"እውነትህን ነው? መቼ ነው እባክህ?" ብሎ ጠየቀው።

"ሰሞኑን" አለውና እንደገና ወደ እኔ ዞር አለ። ሰምተሀል ወይ? ይሁን፣ አንተም የእነርሱ ሰው ነህ ለማለት ይሁን አልገባኝም። እንዳልሰማ ሰው በዝምታ አሳለፍኩት። እሱ ግን በዋዛ ሊለቀኝ የፈለገ አይመስልም።

"አልሰማህም እንዴ?" አለኝ፣ ተኮር አድርጎ እየተመለከተኝ።

"እኔ እንጃ! ምንም አላውቅም" አልኩት። መልሴን ስላሳጠርኩበት ወይም ከፊቴ የጠረጠረው ነገር ይሁን አልገባኝም። "ቅድም በሐሳብ ተመስጬና የነበርኩበትን ዘንግቼ፣ በላብ ተጠምቄ ሳለቅስ አይቶኝ ይሆን እንዴ የጠረጠረኝ?" ብዬ አሰብኩ። የመንግሥት ነጭ ለባሽም ሊሆን ይችላል፤ ብቻ በሁኔታው ምቾት

እንዳልተሰማኝ እሱም ሳይገባው አልቀረም። የእኔ አነጋገር አላጠግብ ብሎት ቅር እንዳለው ያስታውቃል። ያ ሰው ችግር ይፈጥርብኛል ብዬ ፈርቼው ነበር።

ሰውየው ከጓደኛው ጋር ሲነጋገር እንደተረዳሁት የጭነት መኪና ያለው ይመስለኛል። የመጣውም መኪናውን ለመከታተል እንደሆነና ማይጨው ላይ እንደሚወርድ ለጓደኛው ሲነገረው የሰማሁም መስሎኝ ነበር። እርሱ ግን አሁንም ከእኛ ጋር እየሄደነው። ጓደኛው ማይጨው ለምን እንዳልወረደ ሲጠይቀው መኪናው አልፎ መሔዱን ስለሰማ እየተከተለው እንደሆነ ነበር የመለሰለት። የጓደኛውን ጥያቄ ከመለሰ በኋላም ቀስ እያለ ወደ እኔ ዞሮ ሊያነጋግረኝ ደጋግሞ መሞከሩን አስታወስኩ። እኔ ደግሞ ሆነ ብዬ የምሰጠው አጭር መልስ ብቻ ነው ። አንዳንዴም አዎን፣ ወይም አይደለም ለማለት አንገቴን እያወዛወዝኩ በምልክት ብቻ እመልስለታለሁ። የሚያደርገው ግራ ሲገባው፣ ይተወኝና እንደገና ወደ ጓደኛው ይዞራል።

ደግሞ እርእስቱን ለውጦ ስለ ወያኔ ማውራት ጀምረ። "ሰሞኑን እኮ የትግራይ ተጋዳዮች፣ ሰሮ ላይ በደርግ ጦር ላይ ከባድ ጉዳት አደረሱ" አለ።

"እውነትህን ነው?" አለ ጓደኛው። ለወሬው ጉጉት ኖሮት ሳይሆን፣ እንዲሁ መልሱን በመጠበቅ እየተመለከተው እንደሆነ ስላየ ብቻ ነበር የተናገረው።

ይህንን ስሰማ ይኼ ሰውዬ ማንነቴን ጠርጥሮ፣ ለማወጣጣት በአዲስ አቅጣጫ እየመጣ ነው አልኩ በልቤ። የወያኔ አባል መሆኔን ማወቅ እንደፈለገ ገብቶኛል። ሌላ ችግር ውስጥ ሳይከተኝ በጊዜ ለመላቀቅ መቀሌ ከመድረሳችን በፊት ለመወርድም አስቤ ነበር። መንገድ ላይ ወርጄ ግን የት እገባለሁ? ከእርሱ ጋር እንዲሁ እንደተፋጠጥን ሳላውቀው መቀሌ መዳረሻ ላይ የሚገኘው ካምፕ ደርሰን ለፍተሻ ቆምን።

ከማይጨው በኋላ ለፍተሻ የቆምነው መቀሌ መግቢያ ላይ ነበር። ከማይጨው የፍተሻ ተሞክሮዬ ትምህርት ስላገኘሁ መቀሌ ፍተሻ ጣቢያ ላይ





ከመኪና አልወረድኩም። ፍተሻው የሚመለከታቸው ከተማ ቀመስ መንገደኞች፣ አጠገቤ ሆኖ ይጨቀጭቀኝ የነበረ ሰውዬና ያ አውቶብስ ውስጥ የተግባባው ጓደኛው እየተንሾካሸኩ ከመኪና ወረዱ። እኔ ግን ያው እንደገበሬ ስለለበስኩ ባለፈው ፍተሻ ላይ እንደገጠመኝ "ግማታም" የሚል ጸያፍ ቃል እንድዳይመጣብኝና ፍተሻው እንደእኔ ዓይነቱን ባላገርና ሴቶችን ስለማይመለከት ከተቀመጥኩበት አልተንቀሳቀስኩም። ሆኖም ሰውዬው ከሩቅ እየታየኝ ስለነበር በዓይን እየተከታተልኩት ነው። የወረዱት መንገደኞች ተመልሰው ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ መኪናው እንደገና ሞተሩን አስነሥቶ ጉዞ እስኪጀምር ድረስ አፎይታ አላገኘሁም ነበር።

ያ ጨቅጫቂ ሰውዬም በደባልነት ተቀምጦበት ወደነበረው ወርንበር ተመልሶ ሄዷል። ሐሳቡን ከእኔ ላይ አንሥቶ አጠገቡ ካሉት ሰዎች ጋር ማውራት ጀምሯል። ለማዘናጋት የፈጠረው ዘዴ ከሆነም፣ ችግርም እንኳ ቢያመጣ መቀሌ አውቶብሱ ሲቆም የሚመጣ ነው የሚሆነው። ከፍተሻው በኋላ ብዙም አልቆየንም፤ አውቶብሱ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ መቀሌ አውቶብስ ጣቢያ ገብቶ ቆመና ተሳፋሪዎቹ መውረድ ጀመሩ። ገልመጥ ብየ ሰውዬውንና አካባቢውን ተመለከትኩና ወደመጨረሻ ከቀሩት መንገደኞች ጋር ተቀላቅዬ ወረድኩ።

መቀሌንም እንደሌሎቹ ከተሞች ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነበር። አውቶብስ ተራው ውስጥ ሆኜ "አዲሊስ ሆቴል" የሚል ጽሑፍ ይታየኛል። ወደዚያ በመሄድና ባለመሄድ መሃል ሳመነታ በግቢው ውስጥ ያሉ ቦዘኔዎች፣ ሸርጤን ለማየት የፈለጉ ይመስል ከበበው ይጎነታትሉኝ ጀመር። ባላገርነቴን ዓይተው መቀለጃ ሊያደርጉኝና ሊስቁብኝ ፈልገዋል፣ ወይም ደግሞ ገንዘብ ሊሰርቁኝ እያመቻቹኝ ነበር። በያዝኩት ረዥም በትር ለማስፈራራት ስሞክር እየተሳሳቁ ይበተኑና እንደገና ተመልሰው ይከብቡኛል። በመጨረሻ ግቢው ውስጥ በጥበቃ ላይ የነበሩ ሚሊሺያዎች ደረሱልኝ። "ባላገር አይታችሁ አታውቁም? ዞር በሉ!!" ሲሏቸው ተበታተኑ።

መቀሌን ስለማላውቃት፣ ከአውቶብስ ተራው ወጥቼ፣ በየት አቅጣጫ መሄድ እንዳለብኝ ገና አልወሰንኩም። እግሬ በወሰደኝ አንዱን መንገድ መርጬ ጉዞዬን ቀጠልኩ። የሄድኩበት መንገድ ግን አንድ በወይን ተክል ቅጠሎች የታጀበ ግቢ አጠገብ ሲደርስ ቆመ። ግቢው በወታደሮች የተከበበና በመትረየስ የሚጠበቅ ነበረ። ልቤ ድው ድው አለብኝ። አስፈሪውን ግቢ ወደግራ በኩል ትቼ በፍጥነት በመታጠፍ ስሄድ መንታ መንገድ ላይ አወጣኝ። ዞር ስል በአንዱ አቅጣጫ ትልቅ የመኪና መንገድ ታየኝ፣ ትንሽ ተንፈስ አልኩ። አውራ መንገዱን ይዤ ወደፊት መጓዜን ቀጠልኩ፤ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከተማውን ለቅቄ እየወጣሁ መሆኔን በግራና በቀኝ ያሉት መስኮች ነገሩኝ።

ገጠር ውስጥ በመግባቴ ሕይወቴ ከአደጋ እየራቀ መሄዱ ተሰምቶኝ እፎይ ስል፣ ረሃብ ይሞረሙረኝ ጀመር። ገረመኝ፤ በስጋት ውስጥ በነበርኩባቸው ደቂቃዎች ውስጥ በፍጹም ያልነበረ ረሃብ ከየት መጣ ሳልለው ሲያንገበግበኝ መሳቅም አሰኘኝ። ምግብ ወሎ ሮቢት የበላሁ ነኝ። መቼም የገጠር ሰው አይጨክንም ብዬ አሰብኩና አቅራቢያየ ሰው ባገኝ ብዬ አካባቢውን አማተርኩ። አንዲት ሴት በራቸው ደጃፍ ላይ ጎንበስ ብለው የሆነ ነገር ሲያገላብጡ አየሁ። ሳላመነታ ጠጋ አልኩና "ማደሪያ የሌለኝ፣ ለሀገሩ እንግዳ ነኝ..." ብዬ ገና ንግግሬን ሳልጨርስ ቀበል አድርገው፤ "አነጋገርህ ግን እንዳለባበስህ የገበሬ አይመስልም" አሉኝ።

ከዚያም ትኩር ብለው ሲያዩኝ ቆዩና ግራ ቀኛቸውን ካጣሩ በኋላ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብለው "እዚህ አካባቢ ነጭ ለባሾች አሉ፣ እንደአንተ ዓይነቱን ጸጉረ ልውጥ ካገኙ፣ ይዘው ወደ ወህኒ ቤት ነው የሚወስዱት" አሉኝ። ወህኒ ቤት ያሉት ቀደም ሲል ያለፍኩት የሚጠበቀው ግቢ እንደሆነ ገመትኩ። ደጃፉ ደርሼ እጃቸው ውስጥ አለመግባቴ ተአምር ነው ብዬ አሰብኩ።





ሴትዮዋ ማስጠንቀቂያውን ነግረውኝ ለራሳቸውም ለመጠንቀቅ እየፈለጉ እንደሆነ ስለታወቀኝ ወደቤት እንድገባ ሲጋብዙኝ ገረመኝ። ቀልጠፍ ብዬ ወደ ውስጥ ገብቼ ዐረፍ እንዳልኩ፣ ትኩስ እንጀራ አምጥተው ነጠላዬ ላይ አስቀመጡልኝና "በል አሁን እንዳይዞህ ቶሎ ከዚህ አካባቢ ጥፋ" አሉኝና ቀድመው ወጥተው፣ አካባቢውን ተመለካከቱና እንድወጣ ምልክት ሰጡኝ። እኔ አመሰግኜአቸው ስሄድ እሳቸው ደግሞ በጭስ የሞጨመጩ ዓይኖቻቸውን በመዳፋቸው ጀርባ እያሻሹ ያሰፉት እንጀራ እንዳይቃጠልባቸው፣ እየተቻኮሉ ተመልሰው ገቡ።

አደጋ ላይ መሆኔ ተሰምቶኛል፤ ፈጥኜ አካባቢውን መልቀቅ እንደሚያስፈልገኝም ርግጥ ነበር። የምሄደው ግን እግሬ ወደመራኝ የእውር ድንብሬን ነበር። መድረሻየን ለመገመትም ሆነ አቅጣጫዬን ለማስተካከል የሚያስችለኝ ሁኔታ አልነበረኝም። በዚህ ሁኔታ የተከተልኩት መንገድ ወደአልተጠበቀ ጫፍ ወስዶኝ ከወንዝ አፋፍ ላይ አደረሰኝ። ወንዙ የሚወርደው በትልቅ ገደል ላይ ነው፤ መሻገር የማይታሰብ ነበር። በመጣሁበት መንገድ ተመልሼ በመጀመሪያ ሳልፍ ወዳየሁት አንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለማደር ወስኜ ወደዚያው አመራሁ። ጥርጣሬየ ከፍተኛ ስለነበረ ማንንም ሰው ለመጠየቅ አልደፈርኩም፤ ቤተክርስቲያኑን ከማግኘቴ በፊት ግን አንድ ጅምር ቤት በማየቴ ሐሳቤን ለወጥኩ።

በቤቱ አጠገብ አጠና፣ ድንጋይ፣ ለመምረጊያ የተዘጋጀ ጭቃ እንዲሁም ሌሎች ለግንባታ የሚሆኑ የተለያዩ ነገሮች እዚያና እዚህ ተበታትነው ይታያሉ። ሠራተኞቹ የሉም፣ ነገር ግን አካፋና ዶማ የመሳሰሉት የግንባታ መሳሪያዎቻቸው፤ በቤቱ ውስጥ ትቀምጠዋል። እዚያ ጅምር ቤት ስደርስ ቀኑ መጨላለም ጀምሮ ነበር። ከዚያ በኋላ ሠራተኞቹ እንደማይመጡ እርግጠኛ ሆንኩና ገብቼ አንዱ ጥግ ቦታ መርጬ ለመተኛት ተመቻቸሁ። ከመተኛቴ በፊት ግን ሴትዮዋ የሰጡኝ እንጀራ ትዝ አለኝ፤ በእርግጥ ረሐቤ ሁሉ ጠፍቷል፤ ቢሆንም ግን ለመብላት መሞከር እንዳለብኝ አውቃለሁ፤ ደረቁን እንጀራ ቆረስ አድርጌ ወደ አፌ አስገባሁና ገና

ማላመጥ ስጀምር ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ፤ ማላመጤን አቁሜ ማዳመጥ ጀመርኩ። አዎን- የተሰማኝ የጅቦች ጩኸት ነበር።

በአቅራቢያው ካለው ወንዝ የሚወጡ ጅቦች ናቸው ብዬ ገመትኩ። እውነትም የድምፁ አቅጣጫ ከወንዙ በኩል መሆኑ ያስታውቃል። በነጠላዬ የተቋጠረውን እንጀራ ወዲያ ጥየ፣ ጅቦቹ ከመጡ መከላከያ ለመሥራት ወዲያ ወዲህ ማለት ጀመርኩ። .ቤቱ መዝጊያ አልተገጠመለትም፤ ስለዚህም ውጪ ያሉትን ድንጋዮች ማምጣት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነበር። ከአሁን አሁን ጅቦቹ ደረሱብኝ እያልኩ በመሳቀቅ ድንጋዮቹን እስከ ወገቤ ከፍታ ድረስ አደራርቤ በሩ ላይ ቆለልኩ። የጅቦቹ ድምጽ እየቀረቡ መምጣታቸውን ይነግረኛል፤ በዚያ ፍጥነት ግን አጠገቤ ይደርሳሉ ብየ አልገመትኩም። ነገር ግን ወዲያውኑ ደርሰው፣ ቤቱን ከበቡት። ጩኸታቸው ቤቱን ያንቃንቀው እስከሚመስለኝ ድረስ ከባድ ነበር። የሰው ጠረን ሸትቷቸው ሊሆን እንደሚችልና በየትኛውም ደቂቃ ድንጋዩን ሊገፉት እንደሚችሉ እየጠበቅሁ በፍርሃት ተጨነቅሁ። የጭንቅ ሌሊት ደግሞ አያልቅም፤ ለሊቱን ሙሉ ዓይኖቼ ፈጠው ጅቦቹን እየተጠባበቅኩ አንዲት ደቂቃ እንኳ ለመተኛት አልቻልኩም።

ወደ ሌሊቱ መገባደጃ ላይ ጩኸታቸው ቀነሰና ቀስ በቀስ ድምፃቸውም እየራቀ ሄደ። እፎይ አልኩ። ከተቀመጥኩበት ጥግ ተነሥቼ ውጭውን ተመለከትኩ፤ ማለዳው ለዓይን ገልጦ ወገግ ማለት ጀምሯል፤ ወደ ደጅ ወጣሁ። ሊያዘልቅ የሚችለውን የመንገድ አቅጣጫ ረጋ ብዬ ለማጣራት ሞከርኩ። ገና መንጋቱ ስለሆነ በአካባቢው ሰው አይታይም። የተሻለ አማራጭ የመሰለኝን አንደኛውን አቅጣጫ ይዤ ወደሰሜን በኩል ስሄድ የመኪና ድምፅ ሰማሁ። ርምጃዬን ፈጠን አደረገሁና ድምፁን ወደሰማሁበት ገሰገስኩ፤ ሳላስበውም አውራ መንገድ ላይ ደረስኩ። የወጣሁበት ቦታ የፍተሻ ኬላ መሆኑን ያወቅሁት ግን ተከታትለው





የቆሙ መኪናዎችን ስመለከት ነበር። የፍተሻውን ኬላ ወደግራ ትቼ በቀኝ በኩል ወደ በረሐው አቅጣጫ በሚወስደው መንገድ ሄድኩ።

ውስጤ በአዲስ ተስፋ ተሞልቶ ከየት እንደመጣ ባላወቅሁት ኃይል እየገሰገስኩ እንደርታን አልፌ ሐይቅ መስሐል ገባሁ። ወደ ወልዲያ ስንሔድ ያረፍንበት ቦታ ስለነበረ ገና ሳየው አስታወስኩት። ትክክለኛውን የመንገዴን አቅጣጫ ስለለየሁት በራስ መተማመኔ ተመለሰልኝ ውስጤም በደስታ ተሞላ።

ተረጋግቼ ወደራሴ በመመለሴ ይመስለኛል ሐይቅ መስሐል እንደገባሁ ረሐቡ አገረሸብኝ፤ ካልተመገብኩ ጉዞየን መቀጠል አልችልም። ስለዚህ በቅርብ ወደአየሁት አንድ ሻይ ቤት ለመግባት ወሰንኩ። ልገባ ስል ግን ዮሐንስን አየሁት፤ ዮሐንስን ወደወሎ በሄድንበትም ጊዜ አይቼዋለሁ። ዮሐንስ ቀድሞ አዲግራትም እያለሁ የማውቀው ልጅ ነው፤ ልክ ሲያየኝ ወደ እኔ መጣና "ይቅርታ አንተ ካሕሳይ አይደለህም?" ብሎ ጠየቀኝ። በንግግርና፣ አንገቴን በመነቅነቅም ጭምር "አይደለሁም" አልኩት። ግራ በመጋባት ትቶኝ ሔደ።

"እፎይ!" አልኩ በቀላሉ በመገላገሌ ደስ ብሎኝ። ዮሃንስ ግን እንደገና ተመልሶ መጣ። "አንተ ካሕሳይ አብርሃ አይደለህም? እንዴት አይደለሁም ትለኛለህ? በአለፈው ወር እንኳ በዚህ በኩል አልፋችሁ አልነበረም?" ብሎ አጥብቆ ጠየቀኝ።

"አይ እዳዬ ይሄ ደግሞ ምን መዘዝ ሊያመጣብኝ ይሆን?" አልኩ ለራሴ። ከሄደ በኋላ በመመለሱ፣ የሆነ ነገር እስቦ መሆን አለበት የሚል ጥርጣሬ ፈጥሮብኛል። "ይኼ ሰውዬ አላውቅህም ሲሉት ዝም ብሎ አይሄድም? ምን ፈልጎ ነው እንዲህ አልለቅ ያለኝ?" እያልኩ ከራሴ ጋር ተሟገትሁ።

የሚፈልገው ነገር እንዳለው ቢገባኝም ምን ሊሆን እንደሚችል ግን መገመት አልሆነልኝም። ዱሮ ሳውቀው በከፉ ሊያስጠረጥረው የሚችል ባሕርይ አልነበረውም። በወቅቱ በተፈጠረው ሁኔታ ግን ሊለወጥ የማይችልበት ምክንያት ማግኘት አቃተኝ። ድንገት ለአደጋ ቢያጋልጠኝ ብዬ ለመዘጋጀት እየሞከርኩ ነበር።

በሐሳብ ውስጥ ሆኜ ለሁለተኛ ጥያቄው መልስ እንዳልሰጠሁት ትውስ ሲለኝ ፊቴን ኮስተርተር አድርጌ ልቆጣ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ሁኔታውን ላለማካረር ብዬ በትሕትና "የኔ ወንድም፣ ተሳስተሀል። እኔ አንተ የምትለው ሰው አይደለሁም" አልኩትና በቆመበት ጥዬው ሄድኩ።

እርሱ ግን አሁንም አልለቀቀኝም፤ እየተከተለኝ እንደሆነ በኮቴው ድምፅ ይታወቀኛል። ወደኋላ ዞር ብዬ በግልምጫ አነሣሁት፤ አልሄደም። ከባድ ችግር ውስጥ እየገባሁ እንደሆነ ውስጤ እየነገረኝ ነው። የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ቆም አልኩና አፍጥጬ እየተመለከትኩት "የኔ ወንድም አላውቅህም፣ አታውቀኝም፣ እኔ አንተ የምትለው ሰው እንዳልሆንኩ ነገርኩህ፣ ታዲያ ለምን አትተወኝም!?" አልኩት።

መልሴን እንዳልሰማ ችላ ብሎ "የጠየቅኩህ ለሌላ ነገር አይደለም፣ ለራሳችሁ ጉዳይ ነው" አለኝ ካልፈለግህ መሄድ ትችላለህ በሚል ስሜት። ደንገጥ አልኩ፤ ምን እያለኝ እንደሆን ለመገመት አእምሮየን በፍጥነት እንዲያስብ እያስጨነቅሁት ነበር። ለጥቂት ደቂቃዎች ሁለታችንም ዝም አልን።

"ብዙም እንድትጨነቅ አያስፈልግም፤ ቢኒያም የሚባል ቁስለኛ ጓደኛችሁ እዚህ መደበቁን ልነግርህ ነው" አለኝ።

በጣም ደነገጥሁ፤ "አይደለሁም" ብየ የካድኩትን "ምን?!" በማለት ጮህኩ። ዮሐንስ የስሜቴን መለዋወጥ ሲመለከት ፈገግ አለ። ፈገግታው አናደደኝ።

የቢኒያምን ስም ስሰማ የታወሰኝ፣ ሲቆስል ከሐኪም ተክለ ብርሃን ጋር ጥለነው መሄዳችን ነበር።

"አሁን ታዲያ የት ነው ያለው?" ብዬ ጠየቅኩት።

"ያለበትን ቦታ ላሳይህ?" አለና ከበፊቱ ለየት ባለ ስሜት ጠየቀኝ፤ ፈቃደኝነቴን ገለጽኩለትና ወዳለበት ቦታ ይዞኝ ሄደ። ቢኒያምን ያገኘሁት ያለረዳት መንቀሳቀስ በማይችልበት ሁኔታ ላይ ነበር።





ብንያም አለባበሴ ተቀይሮ ሲመለከት ችግር እንዳለ ገብቶታል፤ ምን እንደተፈጠረ ጠየቀኝ። ሁሉንም ነገር አጫወትኩት። ራሱ ያለበትን ሁኔታ ረስቶ፣ በነገርኩት ታሪክ አዝኖ ያለቅስ ጀመር። እርሱን ማጽናናት ቀላል አልነበረም፤ በኋላ ግን እንደምንም አረጋጋሁትና ስለእርሱ ጉዳይ መነጋገር ቀጠልን።

እንደተረዳሁት፣ ተክለ ብርሃን እዚያ ድረስ ይዞት መጥቶ፣ ከዚህ ወዲያ ማጓጓዙ ስለቸገረው አንድ ቤት ውስጥ ደብቆት ወደ አሲምባ ሔዷል። "አሁን ታዲያ እዚህ ጥለኸኝ ልትሔድ ነው?" ብሎ ጠየቀኝ ብዙ ከተጨዋወትን በኋላ።

ወዲያውኑ አንድ ሐሳብ መጣልኝ "እዚህ ቦታ ብዙ ስለቆየህ ለደኅንነትህ ጥሩ አይሆንም። ቦታ ብንቀይር ይሻላል" አልኩት።

እዚያው ሐይቅ መስሐል ውስጥ ፊታውራሪ ምኡዝ የሚባሉ ወደ ወያኔ የገቡ ሰው ነበሩ። እናም "በዚህ በኩል ስናልፍ ሕዝቡ ስማቸውን ጠርቶ "ፊታውራሪ እናንተጋ ነው የገቡት?" ብሎ ሲጠይቀን ትዝ አይልህም?" አልኩት ቢንያምን። ለፖለቲካ ፍጆታ ስንል ፊታውራሪ ምኡዝ 'እኛ ጋ ናቸው' እያልን ማለፋችንን አስታወስኩት። እርሳቸው ትውልዳቸውና ኑሮአቸውም ሐይቅ መስሐል ነበር፤ ቤተ መንግሥት የሚመስል ቤት ነበራቸው። ወደእርሳቸው ቤት እንድንሄድ ነበር ብንያምን የጠየቅሁት።

"ጓዶች እንደሆንን እንነግራቸውና ተመልሰን እስከምንወስድህ በአደራ አብረሃቸው እንድትቆይ እንጠይቃቸዋለን" አልኩት። ብንያም ተስማማልኝ። ዮሐንስና ሌሎችን የሚተባበሩን ገበሬዎች ተጨምረው ቢኒያምን በበቅሎ ይዘነው ሔድን። ፊታውራሪ ቤት ስንደርስ በጣም መሽቶ ነበር፤ በተባባልነው መንገድ አነጋገርናቸውና ብንያምን በአደራ ሊደብቁልን ተስማሙ። ደስ ተሰኘሁ፤ በቀጣዩ ቀን ጠዋት ቢኒያምን ተሰናበትኩና የአሲምባ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

ከመቀሌ ከተነሣሁ በኋላ ሁለት ቀናት ጨርሼ ሦስተኛውን ጀምሬዋለሁ፤ አጋሜ ወረዳ ልገባ የሰዓታት ጉዞ ይቀረኛል። ጉዞዬ አላለቀም፤ ጥቂት እንደሄድኩ፣ ቆም ብዬ ወደ ሰሜን ምሥራቅ በኩል ተመለከትኩ። ልቤ ወከክ ብሎ የተከፈለ

መሰለኝ፤ ዓይኖቼ በዕውን የተመለከቱትን ልቤ መቀበል አቃተው። የማየውን እውነት ውስጤ መቀበል አቅቶት እንገራገረ። "ይህ ህልም ነው ወይስ እውን? እውነት በሕይወት ተመለስኩ ማለት ነው? ብዙ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ውስጥ ይመላለሳሉ። በደንብ እንዲታየኝና ልቤ አምኖ እንዲቀበል፣ ከፍታ ቦታ ላይ ወጥቼ ለመመልከት አሰብኩና ወደዚያው ሄድኩ።

በኮረብታው ጫፍ ላይ ቆሜ ስመለከት፣ የደስታ ስሜት ውስጤን አናወጠው። ደስታየን መቆጣጠር አቃተኝ፤ እግሮቼም የተብረከረኩ መሰለኝ። ዓይኖቼ ፈጥጠው ያን ትንግርተኛ የናፍቆቴን ዳር፣ የበረሐ ቤቴን፣ የጓደኞቼን መሰብሰቢያ፣ የዓላማዬ መሠረት የሆነውንና፣ ብዙ ጊዜ የወጣሁትንና የወረድኩትን የአሲምባን ተራራ ከጥግ እስከ ጥግ ተመለከቱ። አሲምባ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉ ተራሮችም በደንብ ታዩኝ። በማዬው ነገር የበለጠ እርግጠኛ እየሆንኩ ስመጣ ውስጤ በስሜት ሲቃ ተይዞ እውነቱን ለመቀበል ተገደደ። እምን ወደቤቴ ለመዳረሴ እርግጠኛ ስሆን ሆድ ባሰኝ፣ ከቁጥጥሬ ውጪ ዕንባየ በግራና ቀኝ ጉንጮቼ ላይ ኩልል እያለ መውረድ ጀመረ። በጸጥታ አነባሁ! አሲምባንና ጓዶቼን ተወልጄ ካደግሁበት ቀዬና ከቤተሰቦቼም የበለጠ ማፍቀሬ እየገረመኝ አለቀስኩ።

አሲምባ ደርሼ፣ ሁሉን እስከምረዳ ቸኮልኩ፤ የእነዚያን መጨረሻቸውን ያላወቅሁትን ጓደኞቼን ወሬ እስከምሰማ ጨነቀኝ። አሲምባ ቀርተው የነበሩት ጓዶችስ የወሎ ጉዞአችንን መጨረሻ ሰምተው ከሆነ ምን ብለው ይሆን? እስከአሁን ሰምተው ካልሆነስ እንዴት ብየ ይሆን የምነግራቸው? ምናልባት ከዚያ መአት ወጥተው ከኔ ቀድመው አሲምባ ለመርዶ ነጋሪነት የበቁ ጓዶች ይኖሩ ይሆን? ከሌሉ ግን መርዶ ነጋሪው እኔ መሆኔ ነው። ታዲያ ለጓዶቼ የወንድሞቻቸውን መርዶ እንዴት ነው የምነግራቸው? የጁሊያኖን አሟሟት ሲሰሙ ምን ይሉ ይሆን? የደበሳይንስ ነገር? ወይኔ ደበሳይ! ያ ሁሉ ደም ፈሶት ይተርፍ ይሆን? እኔ እንጃ! በፍጹም አይመስለኝም። ግን ምን ይታወቃል? የደበሳይ ሰውነት ግዙፍና





ጠንካራ ስለሆነ ይተርፍ ይሆናል። እነዚያ ሁሉ የተማረኩ ጓዶች ዕጣ ፈንታስ ምን ሆኖ ይሆን? መቼም ገበሬዎቹ ማንነታቸውን ካወቁ በኋላ ይገድሏቸዋል የሚል ግምት የለኝም። ነገር ግን ፈጥኖ ደራሾች ይመር ንጉሤ ዘንድ መጥተው እንደነበረ ሁሉ እያንዳንዱ ምርኮኛ አለበት የተባለ ገበሬ ቤት እያሰሱ መሄዳቸው አይቀርም። ገበሬዎቹ ሁሉ እንደ ይመር እንገታቸውን ይሰጡላቸዋል ለማለት ከባድ ነው። ስለዚህ አብዛኞቹ በደርግ እጅ መውደቃቸው አይቀርም። ደርግ ደግሞ የኢሕአፓን ስም እንኳ ሲሰማ ቀልቡን ነው የሚስተው።ከደርግ እጅ በምንም መንገድ በሕይወት ይወጣሉ ብሎ ማሰብ የማይሆን ነው። እቤት! ቢያንስ ለተልዕኮው ከወጣነው ውስጥ እኩሌታው ያህል ሳይማረክ አይቀርም። በዚህ ዓይነት ከሙቶ የማያንሱ ጓዶች በአራጁ በደርግ እጅ ገብተው ሞት የማይቀርላቸው ሊሆን ነው? ለዚያውም የእስር ቤቱን ምርመራና ስቃይ ሳይቀምሱ መሞት አይኖርም። ወይኔ ወንድሞቼ!!

ስለከተማው ኢሕአፓ አላውቅም፤ ኢሕአሠ ግን ይህን ሁሉ ጀግና አጥቶ እንደገና ኢሕአሠ ይሆናል ማለት የማይመስል ነው። እነ ግደይ፣ ሐዋዝ፣ ዘላለም፣ ደበሳይ .... እንዲህ እያሰላሰልኩ ከኮረብታው ጫፍ ላይ ቆሜ በዕንባ እየታጠቡ ወደ አሲምባ አሻግሬ ተመለከትኩ። እንደ በድን ሆኛለሁ። ከሐሳቤ ስባንን ጉልበቴ እየተብረከረከ መቆም እንዳቃተኝ ታወቀኝ። ወደ ቆምኩበት መሬት ላይ ሸብረክ ብዬ ቁጭ ስል ሐዘኔና እልሄ ተባብሶ፣ ሳግ እየተናነቀኝ አነባሁ።

ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ አላወቅሁትም፤ በኋላ ግን ራሴን ለማጽናናት ሞከርኩ፣ መንገዴን መቀጠል፤ መራራም ቢሆን እውነቱን ማወቅ ይኖርብኛል። እንደገና ጉዞ ጀመርኩ። ተስፋ በውስጤ ሲያንሰራራ ተሰማኝ፤ ሐዘኔም በረድ አለ። "አሲምባ ተመልሼ መጣሁልሽ!" አልኩ የአሲምባ ተራራ ይሰማኝ ይመስል! እንደገና እንደተወለድኩና በጣምም ዕድለኛ እንደሆንኩ እየተሰማኝ ሰውነቴን አዝሎት የነበረው ድካም ጥሎኝ ጠፋ፤ ርምጃዬም መፍጠን ጀመረ። በሕይወቴ ከአሲምባ ተራራ ጋር በተያያዘ እንዲህ አይነት ልቤን የነካ ጥልቅ ስሜት

ውስጥ የገባሁት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ሁለቱንም ጊዜ የአሲምባን ተራራ እያየሁ የተፈጠረቡኝ የስሜት መረበሾች ስለሆኑ ሕይወቴን ሙሉ የአሲምባን ተራራ ሳስብ ሁለቱም አጋጣሚዎች አብረው ይታወሱኛል።

አጋሜ አውራጃ ከመድረሴ በፊት የሁለት ሰዓት መንገድ ሄጄ፣ እዳጋ ሮብዕ ወይም ሰንአፌ ደረስኩኝ። ቦታውን ወደ ወሎ ስንሄድም በደንብ ልብ ስላልኩት አሁን በሚገባ ነው ያስታወስኩት። እዚያ ያሉትም ሰዎች ተጋዳይ መሆኔን አውቀዋል። ሳነጋግራቸው "ተጋዳዮች እዚህ አካባቢ ስለአሉ ያሉበትን ቦታ እናሳይሀለን" አሉኝ።

"የማን ተጋዳዮች ናቸው?" አልኳቸው።

"አታስብ፣ የእናንተ ተጋዳዮች ናቸው" አሉኝ።

የተባሉትን ተጋዳዮች ሔጄ አየኋቸው። አንድ በወያኔ ክፍለ ሕዝብ ውስጥ የሚሠራ ልጅ አገኘሁ። ጥርሰ ፍንጭትና መልካም ገጽታ አለው። ጥሩ አቀባበል አደረገልኝ፤ "አንድ የእናንተ ጓድ፣ ከእኔ ጋር አርፍዶ አሁን በቅርብ ነው ከዚህ የሄደው" አለኝ።

"ማን ይባላል?" አልኩት።

"ተከለብርሀን የሚባል ነው"

"እባክህን አስጠራልኝ" አልኩት።

ተባበረኝ፤ ሰዎችን ጠራና "በዚህ በታች በኩል የወረደ አንድ ተጋዳላይ አለ፣ የእናንተ ሰው እዚህ ይፈልግሃል በሉና ጥሩት" አላቸው።

ተከለብርሃን እስኪመጣ ልጁ በክብርና በፍቅር አስተናገደኝ። አንድ ሻይ ቤት ይዞኝ ገብቶ ምግብ በመጋበዝ የረሀቤን ጥያቄ አስታገሰልኝ። ስለእኛ የሰሙትን ሁሉ አጫወተኝ። ወልድያ ባንክ ዘርፈዋል፣ብዙ ቦታዎችም መትተዋል፣ ሲባል ሰምተዋል። "ብዙ ከተማዎችን እንዳዳረሳችሁ፣ እንደርታም እንደነበራችሁ ሰምተናል" እያለ አጫወተኝ። በዚያ መሀል ተከለብርሀን ተመልሶ መጣ፤ ልጁን አመስግኜውና፣





በጣም ጥሩ ሰው እንደሆነ ነግሬው፣ ተሰናበትኩትና ከተከለብርሀን ጋር የአሲምባን አቅጣጫ ይዘን መጓዝ ጀመርን።

ለተከለብርሀን የሆነውን ሁሉ ነገርኩት፤ መሪር ሐዘን አዘነ። በኋላ ሽጉጥ ሰጠኝና ታጠቅሁ። የታጠቅሁት ሽጉጥ ደግሞ በራስ መተማመኔን ሙሉ በሙሉ መለሰልኝ። ከተከለብርሃን ጋር ሰአሲእ ገብተን አደርንና በሌሊት ተነሥተን ጉዞአችንን ወደ ሱርከሶ ቀጥለን ሰደይቶ የሚባል ቦታ ላይ የአሲምባ ጓዶችን አገኘን። የአመጣጤን ሁኔታ ሲሰሙ በጣም ደነገጡ።

በደፈናው ምን ዓይነት አደጋ ውስጥ እንደገባንና እኔም ዕድል አጋጥሞኝ ለመመለስ እንደቻልኩ ስነግራቸው ሊያምኑኝ አልቻሉም። በጉጉት፣ አንገታቸውን አስግገው ዓይኖቻቸውን አፍጥጠው፣ አንዲት ቃል እንኳ እንዳታመልጣቸው በጥያቄ እያዋከቡ፣ የነገርኳቸውን መልሰው እያስደገሙኝ ሲያስለፈልፉኝ ቆዩ። አንዱ ጉንጮቹን በእጆቹ ደግፎ "ጉድ" ይላል፣ ሌላኛው ጭንቅላቱን ይዞ "ወይኔ ጓዶቼ" እያለ ይጮሀል፣ ሌላው እጆቹን ጨብጦ በእልህ ምድሪቷን በእግሩ ይቀጠቅጣል። ብቻ ሁሉም ስሜታቸውን በተለያየ መንገድ ይግለጹ እንጅ ዓይኖቻቸው ከእኔው ላይ አልተነቀሉም። እንደምንም ወሬዬን ለማሳጠር ሞከሬ በመጨረሻ የአመራሩ አባላት የት እንዳሉ ስጠይቃቸው ባህኩላ መሆናቸውን ነገሩኝ።

ባህኩላ ፀሐዬ፣ ሮባንና ጌራን አገኘኋቸው። ባህኩላ አጋሜ አውራጃ ውስጥ ከአዲግራት ወደ አሲምባ በሚሄደው መንገድ ላይ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ምን እንደተፈጠረ ጠይቀውኝ ስለሆነው ሁሉ ነገርኳቸው። መጀመሪያ በድንጋጤ ደንዝዘው ነበር የሰሙኝ፣ በኋላ ግን ስሜታቸው ተነክቶ ለቅሶ፣ በለቅሶ ሆኑ። በተለይ ሮባና ፀሐዬ እንዴት ሆነው እንደነበር አሁን ድረስ በዓይኔ ላይ ይታየኛል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉም ስሜታቸውን

ተቆጣጥረው ምን እንደተፈጠረና እንዴት እንደተበታተንን፣ ዝርዝር ጥያቄዎች እየጠየቁኝ የረሳሁትን እያስታወስኩ እንደገና ዘርዝሬ ነገርኳቸው።

***





**ከወሎ መልስ**

በ1968 ዓ.ም ሐምሌ ወር የመጀመሪያ ሳምንት ከሻእቢያ ጋር በመተባበር እንትጮ ላይ ጥቃት ተሰንዝሮ ነበር። እንትጮ በአዲግራትና በአድዋ መካከል የሚገኝ ትልቁ የመንግሥት ጦር ካምፕ የሚገኝበት ሥፍራ ነበር። በዚያ ተልእኮ ላይ የተሳተፉት እኛ ወደወሎ ስንሄድ ከሮባና ከጌራ ጋር አሲምባ ቀርተው የነበሩት ጓዶች ሲሆኑ እጅግ የተሳካ ተልእኮ ነበር። በርካታ የጦር መሣሪያ የተገኘበት ውጤታማ ዘመቻ ሆኖ አልፏል።

የእንትጮው ተልእኮ ተሳክቶ ጓዶች ብረት ይዘው ከተመለሱ፥ በኋላ ነበር እስከናገግም ድረስ እንክብካቤ ይደረግልን ዘንድ ውሳኔ ተሰጠው። በዚያው በሐምሌ ወር አጋማሽ ላይ ወደ ከልአሳ ሄጄ አቦይ ገብራይ ቤት እንድገባ ተነገረኝ። ቤቱን ሠራዊቱ እንደ ቤተ መጻሕፍትም ይጠቀምበት ነበር። በዚያን ወቅት እዚያ ቤት የተገናኘነው ስድስት ስንሆን ሁላችንም ከወሎ ተልእኮ ቀድመን የተመለስን ነበርን። በወሎ ተልእኮ በተፈጠረው ችግር የጓዶቻችንን ስቃይና ሞት ተመልክተን፣ እኛም በምርኮ ቆይተን ከዚያም ወደ አሲምባ ለመመለስ ባሳለፍነው ውጣ ውረድ የአእምሮና የአካል ጉዳት ደርሶብን ነበር። በአካላችን ላይ ከደረሰውና ማንም ከሚያየው ጉዳት ይበልጥ መንፈሳዊ ጉዳቱ እጅግ ከባድ ነበር።

እኔ ከነበረብኝ የአካል ድካም በላይ ያሳጣኝ የነበረው የሰውነቴ መክሳት ነበረ። ቀድሞ ከነበረኝ አቋም በጣም ተለውጫለሁ፤ ሰውን በሚያስደነግጥ ሁኔታ በአጽሜ ነበር ያለሁት። ሁላችንም የስነልቦና ችግር ነበረብን። ቀን በሐሳብ፥ ማታ ደግሞ በቅዠት ከመሰቃየት መዳን አልቻልንም፤ ጉዳታችንም እንዲህ በቶሎ ሊጠፋ የማይችል ጠባሳ ሆኖብናል። ከደረሰብን የአእምሮና የአካል ጉዳት እንድናገግም አንድ ተንከባካቢ ነርስ ተመድቦልናል።

የሚያሳስበን፣ የአእምሮ ዕረፍትና እንቅልፍ የነሳን፣ ሌላው ችግር፣ መጨረሻቸውን ያላወቅነው ጓዶቻችን እጣ ፈንታ ነበር። ምናልባትም እንደ እኛ የመመለስ እድል የሚገጥማቸውም ሊኖሩ ይችላሉ። በዛው መጠን ደግሞ

በማራኪዎቻቸው ከፉ እርምጃ የተወሰደባቸውና በደርግ መንግሥት እጅም የወደቁ እንደሚኖሩ ሰናስብ ሐዘናችን ይበረታል። በውጊያው ላይ ከአርሶ አደሮች ጋር ፣ የደርግ ጦርም ነበረበት፤ እኛ ተማርከን በአርሶ አደሮች እጅ የነበርነው ደርግ በየቤቱ ሲያፈላልግና አካባቢውን ሲያስስ እንደነበር እናውቃለን። ስለዚህ መጥፎ አጋጣሚው እንደሚያመዝን ሰለምናውቅ ነበር ሕልማችንንና ቅዥታችንን ድብልቅልቅ አድርጎብን መረጋጋት ያቃተን።

በእዚህ ሁኔታ እያለን፤ ደርግ የጀመረው የራዛ ዘመቻ አበቃ። በራዛ ዘመቻ በተካሄደው የመከላከል ውጊያ ከጀብሀ ጦር ጋር በቅንጅት የተካፈሉ ጥቂት የኢሕአሠ ጋንታዎች የተሰጣቸውን የጥበቃና የግዳጅ ተልእኮ ጨርሰው ተመለሱ። ሁሉም ወደ ሠራዊቱ መደበኛ እንቅስቃሴ ገባ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ጀብሃ ከራዛ ዘመቻ ውጊያ በምርኮ ከተገኘው የጦር መሣሪያ ለኢሕአሠ የሚሰጥ መኖሩን በማሳወቅ ሰዎች እንዲላኩ የሚጠይቅ መልእክት መጣ። ከኢሕአሠ አመራሮች አንዱ ፀሐዬ ወደ ነበርንበት የአቦይ ገብራይ ቤት መጥቶ እኔና አስመሮንምን ጠርቶ ለብቻችን አነጋገረን "ሁለታችሁም ለጀብሃ የሚደርስ መልእክት ይዛችሁ መነኩሴይቶ ትሄዳላችሁ" አለንና በፖስታ የታሸገ ደብዳቤ ሰጠን። ጸጋዬ መትረየስና ሌሎች የጦር መሣሪያዎችንና ጥይቶችንም እንደሚሰጡን ነገረን። በተጨማሪም "በተለይ መትረየሱን እንዴት እንደምትጠቀሙበት፣ በደንብ እንዲያሳዩዋችሁ ጠይቃችሁ እንድትረዱ ይሁን" ብሎ አስጠነቀቀን።

ወደ መነኩሴይቶ እንድንሄድ ስንታዘዝ ገና ሰውነታችን አልተመለሰም ነበር። አስመሮም ኤርትራ ተወልዶ ያደገ፣ ቤተሰቦቹ ግን የትግራይ ተወላጆች ስለሆኑ ከኢሕአሠ ጋር ለመታገል በራሱ ፈቃድ ከኤርትራ የመጣ ነበር።

በተሰጠን ትእዛዝ መሠረት ጉዞአችንን በተከታዩ ቀን ጠዋት ጀመርን። በመንገዳችን ላይ ድንገት የወልዲያ ወሬ ተነሣና ሐዘኑ ከውስጤ አልወጣ ብሎ





ስለሚያስቸግረኝ ስለጁሊያኖ አወራሁለት። አስመሮም ከጁሊያኖ ጋር እንደሚተዋወቅ አጫወተኝ።

አሰመሮምና ጁሊያኖ ኤርትራ ተወልደው ያደጉ ሲሆኑ፤ ጓደኞቻቸው ወደ ኤርትራ ድርጅቶች ለመደባለቅ በረሀ ሲገቡ እነርሱ ደግሞ ወደትግራይ መጥተው ከኢሕአሠ ጋር ተቀላቀሉ። አስመሮምና ጁሊያኖ አብሮ አደጎች ብቻ ሳይሆኑ በጣም የሚቀራረቡ ኢሕአሠም ከገቡ በኋላ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የማይለያዩ ጓደኛሞች ነበሩ። ጁሊያኖን በቅርብ አውቄው፣ በሞቱ የተሰማኝን ሐዘን እያሰብኩት፣ አብሮ አደጉ አስመሮም ስለአብሮ አደግነታቸ ሲያጫውተኝ የቱን ያህል ትልቅ ሐዘን እንደተሸከመ ተረዳሁለት።

የጉዟችን መዳረሻ ወደሆነው መነኩሴይቶ ስንገባ የአካባቢው የጀብሃ አስተዳዳሪዎች የት እንደሚገኙ ጠይቀን ሼካ ንጉሥ የሚባሉ ሰው ቤት መሆናቸውን ተረዳንና፣ ቤቱን ፈልገን አገኘነው። ሼካ ንጉሥም ለጀብሃ ሐላፊዎች ደብዳቤ ይዘን እንደመጣን መለእክት ተላከባቸው ዕለቱን እዚያው እንድናድር አድርገው በሚቀጥለው ቀን ከመነኩሴይቶ በስተምሥራቅ በኩል የሚገኘውን ቢሮዋቸውን በምልክት ነግረውን ሄድን።

እኔና አስመሮም ከወሎ ስንመለስ የአካባቢውን ሰው ለመምሰል የተላጨነው ጸጉራችን ገና በደንብ አላደገም። የጸጉራችን መላጨት በአጽም የቀረውን ሰውነታችንን አጋንኖ ጣረ ሞት አስመስሎናል። እኩለ ቀን ላይ ጀብሀ ቢሮ ስንደርስ፣ አሥር የሚሆኑ የጀብሀ አባሎች መጥተው ተዋወቁን። ከሁለቱ አመራሮች አንደኛው ስመረ ይባላል። በዚያን ጊዜ የዚያች የአዋሳኝ ወረዳ የደኅንነት ሐላፊ ነበር። ሁለተኛው የአመራሩ አባል አማኑኤል ይባላል። በወረዳው የታወቀ የጀብሀ ካድሬ ነው። ሁለቱ አመራሮች ራሳቸውንና ሐላፊነታቸውን ካስተዋወቁን በኋላ ነበር የተላከውን ደብዳቤው የሰጠናቸው።

ሌሎች አመራሮችና አባላትን ከተዋወቅን በኋላ ወደግቢው ይዘውን ገቡ። በግቢው ውስጥ ከሁለት የትግራይ ድርጅቶች አባላት ጋር ተገናኘን።

ዝርዝሩን ባላውቅም ምናልባት እነርሱም በራዛ ዘመቻ ከጀብሀ ጋር በመተባበር ስለተሳተፉ ከተማረኩ መሣሪያዎች ወይም ሌሎች ድጋፎችን ለመቀበል የመጡ ይሆናሉ ብዬ ገመትኩ።

ከሁለቱ ሰዎች አንደኛው በዝምድናም በጓደኝነትም በቅርበት የማውቀው ነበር። ደጀኔ ተሰማ ይባላል፤ እንደተያየን ተቃቅፈን ሞቅ ያለ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ 'እንዲህ በአጽምህ የቀረኸው ምን ሆነህ ነው? ታመህ ነበር እንዴ?' አለኝ ደንግጦ። በሐዘን ስሜት ከእግር እስከራሴ እየተመለከተኝ አንገቱን ነቀነቀ። ደጀኔ ያንጊዜ የመጣው የትግራይ ነጻ አውጪ ከሚባል (ወያኔ አይደለም) ድርጅት ነበር።

ከደጀኔ ጋር ትንሽ ከተጨዋወትን በኋላ ወደ ዋናው ቤት ገባን። እዚያም ሌላ እንግዳ መኖሩን ተመለከትን። አብረውን ያሉት የጀብሀ ሰዎች ሲያስተዋውቁን፡ "እሱ ከትግራይ ሕዝብ ሐርነት ተጋድሎ (ወያኔ) የመጣ ነው፤ መለስ ይባላል " አሉና እኛንም አማኑኤልና አስመሮም እንደምንባል ነገረውት እጅ ለእጅ ተጨባብጠን ሰላምታ ተለዋወጥን። ያን ጊዜ የተዋወቅነው መለስ፤ በኋላ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር የሆኑትና በቅርብ ጊዜ በሞት የተለዩት መለስ ዜናዊ ነበሩ።

በምሳ ሰዓት ጥሩ ምግብ ቀርቦልን እየተጨዋወትን በልተን ስንጨርስ የጀብሐ መሪዎች እዚያው እንደምናድርና በሚቀጥለው ቀን መሣሪያ ወደሚቀመጥበት ቦታ እንደምንሄድ ነገሩን። ከደጀኔ ጋር ለመጨዋወት ጊዜ እንደሚኖረኝ አስቤ ደስ አለኝ። በኋላ ግን ደጀኔ ሳይሰናበተኝ መሄዱን ሰምቼ ተገረምኩ። ስንገናኝ ሞቅ ያለ ሰላምታ በመለዋወጣችን በዚህ ዓይነት እንለያያለን ብዬ አላሰብኩም። ከዚያ በኋላ ከደጀኔ ጋር እስከመጨረሻው አልተገናኘንም።





ያን ዕለት የቀረውን ጊዜ በሙሉ ያሳለፍነው ከመለስና ከጀብሀ ሰዎች ጋር ነበር። የወያኔ አባል የሆኑ ተጋዳዮችና በርካታ መሪዎች አውቅ ነበር፤ ብዙዎችን በአካል ሌሎቹን፣ ደግሞ በዝናና በወሬ ደረጃ ስማቸውን ሰምቻለሁ፣ መለስን ግን ያየሁትም ሆነ ስሙን የሰማሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

መለስ የለበሰው የዘማቾች ካኪ ዩኒፎርም ሲሆን አንድ በርሳ ሙሉ መጽሐፍ ይዟል። ሰውነቱ ጠንካራ፣ ከመካከለኛ ሰው ትንሽ አጠር ያለ ቁመት ያለው፣ ክብ ፊትና ንቁ ዓይኖች ያሉት ሰው ነው። መለስ ጨዋታና ቀልድ የሚያውቅ፣ ኃይለኛ ተከራካሪ፣ በውይይት ጊዜ ፊቱን ቅጭም የሚያደርግና የሚመሰጥ እንደሆነ በዛን ቀን ቆይታችን አስተውያለሁ።

ቀኑ ሲመሽ ሁላችንም ተሰብስበን ስንቀመጥ የፖለቲካ ውይይት ተጀመረ። ዋናው የውይይት ርእስ ኢሕአፓና ወያኔ በኤርትራ ጥያቄ ላይ ባላቸው አቋም ላይ ያተኮረ ነበር። የኢሕአፓ አቋም፣ 'የኤርትራ ጥያቄ የነጻነት ጥያቄ ነው እንጂ፣ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም" የሚል ሲሆን የወያኔ ደግሞ "የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው" የሚል ነበረ።

እኛ ኢትዮጵያ ራሷ በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ያለች ሀገር፣ ሌላን ሀገር በቅኝ ግዛት ለመያዝ የሥርዓቱም ባሕርይ እንደማይፈቅድም ሆነ፣ አቅሙም እንደሌላት አስረዳን። ቅኝ ግዛት በዋነኝነት የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር የመስፋፋት ባህሪይ ጋር የተያያዘ መሆኑን ተናገርን። መለስ የጠቀሳቸው መረጃዎችና ነጥቦች ትክክለኛና ተያያዥ መረጃዎች እንዳልሆኑ ለማሳየት ሞከርን። ዶ/ር ተስፋየ ደበሳይ በመራውና የሻቢያ ሐላፊዎችም በተገኙበት በግንቦቱ ስብሰባ ላይ ተወያይተን ስለነበረ የጠራ አቋም በመያዛችን አሁን ለምናደርገው ክርክር ጥሩ መሠረት ሆነን።

መለስ ብዙ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችንና የተለያዩ የርእዮተ ዓለም ትንተናዎችን ለመስጠት ቢሞክርም እኛ የምናውቀው አለመሆናችን ስለገባው፣ በዚያ በኩል ብዙ ለመግፋት የተመቻቸ ሁኔታ አላገኘም። ነገር ግን ብዙ ጥልቀት ያላቸው ርእዮተ ዓለማዊጽሑፎችን እንዳነበበና ሰፊ የእውቀት አድማስ እንደነበረው ሁላችንም ተገንዝበናል።

የውይይታችን አቀራረብና መከራከሪያ ነጥቦች፤ በየአቋሞቻችን ላይ የነበረን እርግጠኛነት፤ ስንከራከር በዝምታ የሚያዳምጡትን የጀብሀን ታጋዮች እንዳስደመመ ከሁኔታቸውና አልፎ አልፎ ከሚያነሡት ጥያቄ ተረድተናል።

የምንከራከረው እኔና አስመሮም ከአንድ ወገን፣ መለስ ደግሞ ብቻውን ስለነበር ውይይታችን አድካሚ ሳይሆንበት አልቀረም። እርሱ ግን እንዲህ በቀላሉ ደክሞት የሚተው ሰው አልነበረምና እኛን ለማሳመን ብዙ ደከመ። በመጨረሻም ከሀሳብ መደጋገም በቀር አዲስ ነገር እያለቀብን ሲመጣ፣ "ብሬይን ወሽድ (brain washed) ስለሆናችሁ፣ እናንተን ማሳመን አይቻልም"አለ።

የመጨረሻ አቋማችን "የኤርትራ ጥያቄ የነጻነት ጥያቄ ስለሆነ መፍትሔውም በኤርትራ ሕዝብ በሚደረግ ነጻ ሬፈረንደምሊወሰን ይገባዋል" የሚል መሆኑን ገልጸን ውይይቱ በዚሁ አበቃ። ከዚህ በተጨማሪ የምሽቱ በጣም መግፋትም ለውይይቱ መቋረጥ ምክንያት ሳይሆን አልቀረም።

ኤርትራውያኑ ግራ የገባቸው ይመስላሉ። እኛ የምንነጋገረው ቋንቋ በተለይም የአስመሮም ትግርኛ የእነርሱን ቋንቋ ዓይነት መሆኑና የእነርሱን ትግል ጉዳይ ያን ያህል በጥልቀት ማወቃችን ገርሟቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የእኔና የአስመሮምን የሰውነት ጉዳት እያዩ በጣም አዝነውልናል። እኛ ግን ወሎ ስለደረሰብን እስቃቂ አደጋ ለማናችውም አልነገርናቸውም።





በመጨረሻ የበለጠ ያስደነቃቸው ጉዳይ ተከሠተ፤ ሦስታችንም ኩሽኮቻችንን በጋራ አንጥፈንና ለብሰን መተኛታችንን ማመን አቅቷቸው ነበረ። የተለያየ አቋም ያላቸው ድርጅቶች አባላት፣ ምናልባት የማንግባባበትና በከፉ የሚያስተያዩን ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉን አውቀው ይሁን ሳያውቁ፣ ብቻ ተማምነን አብረን በመተኛታችን በጣም ተገረሙ። የተለያዩ የኤርትራ ድርጅቶች አባላት የሚገናኙበትና አብረው የሚያድሩበት ሁኔታ ሲያጋጥም እንኳን ተቀራርበው ተኝተው አያውቁም፤ ተራርቀው በከፍተኛ መጠባበቅና በጥንቃቄ እንደሚያድሩ ነገሩንና በእኛ የእርስ በእርስ መተማመን ከመገረምም በላይ ብስለታችንን እንደሚያሳይ ጠቁመውን ወጡ። ከዚያም በግራዬ በኩል አስመሮም፣ በቀኝ በኩል መለስ ሆኖ፣ መደዳውን ለጥ ብለን አደርንና ሦስታችንም ማልደን ተነሣን።

የጀብሀ ሰዎች በነገሩን መሠረት መሣሪያው ወደተቀመጠበት ቦታ ወስደውን መሣሪያዎቹን ሰጡን። መሣሪያዎቹን ስንረካከብ የፈረምኩት እኔ ስሆን፣ በአጋጣሚ ከጀብሃ ወገን የፈረመው ሰው ስሙ አማኑኤል ነበር። በአጋጣሚው እየሳቀ "እናንተ ኢሕአፓዎች እውነተኛ ስማችሁን ሳይሆን የውሸት ስም እንደምትጠቀሙ አውቃለሁ። በዚህ ፊርማ ላይ ያሉትም ሁለት አማኑኤሎች ቢሆኑም፣ እኔ እውነተኛው አማኑኤል፣ አንተ ግን የውሸት አማኑኤል መሆንህ መታወቅ አለበት" አለኝና ሳቅን። በታዘዝነው መሠረት የመትረየሱን አጠቃቀም በዝርዝር እንዲያሳዩን ጠይቀን አስረዱን። የተሰጡንን ሌሎቹንም መሣሪያውዎችና ጥይቶች ይዘን ተመልሰን ለሐላፊዎቻችን አስረከብን።

እኔና አስመሮም መነኩሴይቶ ሄደን ከመጣን በኋላ ከወሎ የተመለስነው ጓዶች ቁጥር አሥራ ሁለት ደረሰ። ወደ ወልዲያ ከሄድነው ሃምሳ አራት የሠራዊት አባላት ሠላሳ ሁለት ጓዶቻችንን አጣን። ዕድለኞች ሆነን የተመለስነው፣ እኔ፣ በርሔ፣ ነጻነት ማንጁስ፣ መገርሳ፣ ሽፈራው፣ ወርቁ፣ ጀማል፣ ፍሡሕ ገብራይ፣ ዕቁባይ፣ አስመሮምና ሌሎች ሁለት ተጨምረው (ከወሎው አጋጣሚ ከተረፍነው

አንደኛው ወደ ሠራዊቱ ሳይመለስ ወደቤተሰቦቹ የሄደ ነው) ፣ በተለያየ ጊዜ ነበር አሲምባ የገባነው።

ሁላችንም በየራሳችን መንገድ የተመለስን ቢሆንም ብዙ ኢጋጣሚዎቻችን ተመሳሳይ ነበሩ። በዕድልና በአጋጣሚ፣ እንዲሁም በገበሬዎችና በወልዲያ የድርጅታችን ሰዎች ድጋፍ ነበር የተመለስነው። ሽፈራው፣ ወርቁ፣ ጀማልና መገርሳ ሲመለሱ ያጋጠማቸውን ሁኔታ ሽፈራው እንደሚከተለው አጫውተን። ወርቁ ሲማረክ ከሽፈራው ጋር አብረው ነበሩ። ወርቁ የተያዘው እግሩን ተመትቶ ሲሆን ለያዘው ገበሬ "የቀበርነው ገንዘብ አለ" ብሎ ነገረውና ገበሬው ገንዘቡን ፍለጋ ሲሄድ ወርቁ አመለጠውና እየተንፏቀቀ ሄዶ አንድ ቤት ገባ።

የቤቱም ሰዎች አዝነው አሳደሩት፤ ከዚያም የራያ ልብስ አልብሰው ወልዲያ ድረስ ሸኝተውት ተመለሱ። ወልዲያ እንደደረሰ አንድ የድርጅት አባል የሆነ ሰው አግኝቶ ቤቱ ደብቆ አስቀመጠው። አንድ ቀን የተደበቀበት ቤት በደርግ ኃይሎች ተከበበ። ወርቁም "አለቀልኝ" ብሎ ተስፋ ቆረጠ በሩን ከፍቶ ታጣቂዎቹን አናገራቸው። የቤቱን ባለቤት እንደሚፈልጉ ሲነግሩት ወደውጪ ወጣ ማለቱን ነገራቸው። ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ሳይጠይቁት ሲሄዱ ማመን አቃተው። እንዳይጠረጥሩ ያደረጋቸው የለበሰው የራያ የባህል ልብስ ነበር ። ከዚያ በኋላ ወርቁ እዚያ መቆየት እንደማይኖርበት ወስኖ ወዲያውኑ በጓሮ በኩል በአጥር ዘሎ ጠፍቶ ሄደ።

ሽፈራው ደግሞ የማረኩት ገበሬዎች ቤት ቆይቶ በእረኝነት መሥራት ጀምሮ ነበር። ሰዎቹ ሚስትም እንደሚድሩት ቃል ገብተውለት እስከመጨረሻው እነሱ ጋ ሊያስቀሩት ተስፋ አድርገው ነበር። ነገር ግን ልክ እኔ የነበርኩበት ሰፈር እንደመጡት ሽፈራው የነበረበትም መንደር የደርግ ወታደሮች ለአሰሳ





መጥተው ነበር። ሰዎቹ ይህን ሲሰሙ ጎተራ ውስጥ ደበቁት፤ ከዚያ በኋላ ግን በአካባቢ መቆየቱ ለሽፈራው ስጋት ስለሆነበት አሳዳሪዎቹን ወደ ቆቦ እንዲወስዱት ጠይቋቸው ተስማሙለት። ቆቦ ሲደርስ ጠላ ቤት ገብቶ ቁጭ እንዳለ አንድ መምህር አግኝቶ እንዲተባበረው ጠየቀው። ሰውየው እቤቱ ወሰደው። መምህሩ ቤት ተደብቆ እያለ አበበ ከሚባል የኢሕአፓ ሰው ጋር ተገናኘ። ሽፈራው ጀማል በምርኮ ያለበትን ቤት ስለሚያውቅ ለድርጅቱ ነግሮ ጀማልን እንዲያስለቅቁት ከአበበ ገንዘብ ተቀብሎ ላከላቸውና ጀማልን አስለቀቀው።

ሺፈራው ወልዲያ በ ድርጅት ሥራ መሳተፍ እንደጀመረ በአካባቢው አንድ የቆሰለ ጓድ መኖሩን ሰማ። ለማጣራት ባደረገው ሙከራም ቁስለኛው ወርቁ ሆኖ አገኘው። ወዲያውኑ ግን የሺፈራው ማንነት በአካባቢው የደርግ ባለሥልጣኖች ጥርጣሬ እየፈጠረ ጥያቄ ማስነሣት ሲጀምር ወደ አሲምባ ለመመለስ ወስኖ ተነሣ። መንገድ ጀምሮ አላማጣ ሲደርስ ጀማል፣ ወርቁና መገርሳም ወደ አሲምባ ለመመለስ ጉዞ ጀምረው ኖሮ አገኛቸው። በዚህ ሁኔታ ነበር አራቱ በአንድ ላይ አሲምባ ተመልሰው ለመግባት የቻሉት።

እኛ ዕድል ገጥሞን በተለያየ መንገድ ስንመለስ መመለስ ካልቻሉት ውስጥ ሀያ የሚሆኑ ጓዶች ደግሞ በገበሬዎች ጦር ተማርከው በደርግ ሠራዊት እጅ የወደቁ ነበሩ። በኋላ እንደታወቀው፣ እነዚያ ጓዶች "ዓላማችሁን ለውጣችሁ ከመንግስት ጋር ከተሰለፋችሁ በምሕረት ትለቀቃችሁ፤ሥልጣንም ይሰጣችኋል" ተብለው ተለምነው ነበር። በቀረበላቸው ጥያቄ ተስማምተው ከእስር በመፈታት አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ሁለት ከፍተኛዎች ውስጥ በካድሬነት ተመድበው ከነበሩት ከሁለቱ በስተቀር ሌሎቹ ያን ከማድረግ ይልቅ ሞትን የመምረጥ ቆራጥ ውሳኔ ያደረጉ ጀግኖች ነበሩ። በመጨረሻ በከፍተኛ ምርመራ ሲሰቃዩና በየእስር ቤቱ ሲንከራተቱ ቆይተው በኢሕአፓነት ተከሠው እንደነርሱ ከተሰቃዩ ሌሎች ሶስት እስረኞች ጓዶቻቸው ጋር በጥቅምት ወር 1969 ዓ.ም. ተገደሉ። ከእነርሱ

ጋር ተቀላቅለው ከተገደሉት ውስጥ የኢሕአሠ ነባሩ ታጋይ፣ የጸሎተ ሕዝቅያስ ወንድም ይትባረክ ሕዝቅያስ ይገኝበታል።

በዚያን ወቅት ደርግ የረሸናቸው ጓዶች በጠቅላላው ሀያ ሦስት ሲሆኑ እነሱም፦

1. ተፈሪ ብርሃኔ፣
2.ውብሸ ት ረታ፣
3.ተስፋዬ ደሳለኝ፣
4.ዘርዓ ብሩክ አበበ
5.ፈለቀ ወልደ ሰንበት፣
6.ጸጋዬ ኪዳኔ፣
7.ኃይለ ሥላሴ ከበደ፣
8.መሐሪ ተፈራ፣
9.ኪዳኔ አጽብሀ፣
10.ሐጎስ ብሩ ፣
11.ሽፈራው ተካ፣
12.ጋሹ ገብሩ፣
13.ዓለም እንግዳ፣
14.ደበሳይ ካሕሳይ፣
15.ልዑል ሰገድ እምዴ፣
16.ተስፋዬ ኃይሉ፣
17.ይትባረክ ሕዝቅያስ፣
18.ታደሰ መኮንን፣
19.ተወልደ ብርሃን ሰዩም፣





20.ሙሉጌታ ሱልጣን
1.ዳንኤል ደምሴ፣
22.ኪዳኔ መኩሪያ፣
23.ጥላሁን መኩሪያ ነበሩ።

ይህም ለወሎ ተልእኮ ከወጣነው 54 አባላት ከሃያ የሚበልጡ ጓዶች የት እንደደረሱ ያለመታወቁን ያሳያል።

በወሎው ተልዕኮ ሳቢያ መሥዋዕትነትን ከከፈሉ ወጣቶች አብዛኞቹ በእምነታቸው ጥንካሬ፣ በውጊያ ልምድና ችግሮችን በጽናት በማለፍ የሚታወቁ ናቸው። ድርጅታዊ ዓላማዎችን ለማሳካት ሕይወታቸውን ለመስጠት ለደቂቃ የላመነቱ ቆራጥ ጓዶች ነበሩ። ከእነርሱ መካከል አብሬያቸው በቅርብ ከመሥራቴ የተነሣ በጭራሽ የማልረሳቸው ይገኙባቸዋል። እኔ ኢሕአሠን ስቀላቀል መጀመሪያ ያነጋገረኝና በዚያን ጊዜ ኢሕአሠ ከነበሩት ጥቂት አባላት ጋር ያስተዋወቀኝ ግደይ (ተፈሪ ብርሃኔ) ስለነበር የማልረሳው ልዩ ትዝታ አለብኝ። ግደይ የሠራዊቱ ከፍተኛ ወታደራዊ አመራር አባል የነበር። እንደነ ጅግሳ ራሺያ የተማረ ከዚያም በፍልስጥኤሞች ሠልጥኖ የመጣ ፣ በቀላሉ የማይተካ ጓድ ነበር። ሐዋዝ (ውብሸት ረታ) ደግሞ የኃይል የፖለቲካ ሐላፊ የነበረ፣ አንባቢና ከፍተኛ ብስለት የነበረው፣ ከፖለቲካ ሐላፊነቱም በተጨማሪ ጎበዝ አዋጊና ተዋጊ የነበረ ጓድ ነበረ። ደበሳይ ካሕሳይ ፣ በጦር ተወግቶ ዓይኄው ስለነበረ ዛሬም ምስሉ ከዓይኔ ላይ አልጠፋም፣ ብዙ ደም ከፈሰሰው በኋላ ተርፎ ነበር በደርግ እጅ ወድቆ ለመገደል የበቃው።

የወሎ ተልእኮ ባስከተለው አስከፊ መዘዝ፣ አመራሮቹ በጣም እንደተጸጸቱና ከፍተኛ ሐዘን እንደወደቀባቸው እናውቃለን። ተልእኮው ለምን ለከባድ ችግር እንደተጋለጠ፣ ይህን ሁሉ አደጋ ለምን ሊያስከትል እንደቻለ፣ በአጠቃላይ የማን ጥፋት እንደነበረ ፓርቲውና ወታደራዊው አመራር ምክንያቶቹን

በዝርዝር አጥንተው መልስ ይሰጡበታል ተባለ። መልሱም መጀመሪያ የሚደርሰው ለዚያ ቡድን አባላት እንደሚሆን ተነግሮን ነበር።

እንኳንስ ጥናታዊ ውጤት ልናገኝ የወሎ ተልእኮ ጉዳይ ከዚያ ወዲህ ተነሥቶ አያውቅም፤ እንደተከደነ ቀረ። ምናልባት አመራሩ የችግሩ ምንጭ ራሱ ጋ መሆኑን አውቆ ይሆናል፤፤ እውነቱን አውጥቶ ስሕተትን በአደባባይ ለመቀበል አባላት በአመራሩ ላይ ያላቸውን እምነት እንደሚቀንስ ታስቦ ሊሆን ይችላል። በአመራር ላይ እምነት ከሌለ ደግሞ በትንሹም በትልቁም ነገር ላይ ማንገራገር ያስከተል ይሆናል። ይህ ሁሉ ከግምት ያለፈ አይደለም፤ ነገር ግን ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ሁኔታው ያሰከተለውን መንፈሳዊ ጉዳት ከመባባስ አላዳነውም። በተለይም ከወሎ ተልእኮ በሕይወት የተረፍነው አባላት ከጠባሳው ጋር አብረን እንድንኖር ሆነናል።

የኢሲምባ አመራሮች የነበሩት ሮባና ፀሐዬ እንዲሁም ሌሎቹ በወሎ ከደረሰብን የአእምሮ ጉዳት እንድናገግም የቻሉትን ያህል ሞክረዋል። በመጨረሻ የማገገሚያ ጊዜያችን አበቃና ተመልሰን ወደየምድባችን ገብተን ትግላችንን እንድንቀጥል ተነጋግረን ተሰማማን። ከዚያ በኋላ ለሦስት ወራት ያህል በክፍለ ሕዝብ ማለትም ሕዝብን በማደራጀትና በመቀስቀስ ሥራ ካገለገልኩ በኋላ ሠራዊቱ ተቀይጦ አዲስ ምደባ ተደረገና ኃይል ሦስት ው ስ ጥ ገባሁ።

***





# አራት

## ኃይል ሦስት

### ክፍለ ሕዝብ

በትጥቅ ትግል የማምነው ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ለሚታገሉ ሰዎች ብቸኛ መፍትሔ ሲሆን ነው፡፡ በዚህ እምነቴ እስከመቼም እገፋበታለሁ

ቼ ጉቬራ- ኩባን ለቆ ወደ ኮንጎ ሲሄድ ለቤተሰቡ የጻፈው ደብዳቤ

ከወሎ ከተመለስን በኋላ ወደ ኃይል ሦስት ከመመደቤ በፊት ለጥቂት ወራት በክፍለ ሕዝብ ተመድቤ ሠርቻለሁ። መጀመሪያ አዲ ኢሮብ አካባቢ ለአንድ ወር ያህል ከዚያ ደግሞ በኢድዋ አካባቢ ነበር የቆየሁት። በአዲሱ ምደባ መሠረት ሕዝብ ውስጥ ገብተን የመቀስቀስና የማደራጀት ሥራ ላይ ከተሰማራነው ጓዶች መካከል፣ ጴጥሮስ፣ ኤልያስ፣ ሰባጋድስና ሐጎስ ይገኙበታል።

እየተዘዋወርን ቅስቀሳ በማድረግና የብዙኃን ድርጅቶችን በማቋቋም ውጤታማ ሥራዎችን እየሠራን ቆየን። በአካባቢው የሚገኙትን የከተማም ሆነ የገጠር ሕዝብ እየሰበሰብንና ሕዝቡ በሚያከብራቸው በዓላት ላይ እየተገኘን፣ ስለመብት፣ ስለኢኮኖሚ ጥያቄ፤ ስለመደብና የብሔር ጭቆና ድርጅታችን ስለነበረው አመለካከት እናስተምር ነበረ። እኛም ከሕዝቡ ጎን ተሰልፈን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ እስከሚሆን ድረስ እንደምንታገል እንናገር ነበር።

በዛላ አንበሳ አካባቢ በሠራሁበት ወቅት አንድ ቀን ከጴጥሮስ ጋር እያለን በአካባቢው የወያኔ ካድሬ የነበረው አርአያ ወደእኛ መጥቶ "አንድ የአማርኛ ተናጋሪ የሆነ የከተማ ሰው እኛ ዘንድ መጥቷል። ምናልባት ከእናንተ ጋር ለመቀላቀል መጥቶ ተሳስቶ ወደእኛ የገባ ስለመሰለኝ እንድታነጋግሩት ፈልጌ ነው"

አለን። በሐሳቡ የምንስማማ መሆኑን ስንነግረው ሄዶ ሰውዬውን ይዞት መጣ። ሰውየው ቀይ፣ መካከለኛ ቁመትና ደልዳላ ሰውነት ያለው ነበር።

ሰውየውን ከካድሬው ዞር አድርገን ስለማንነቱና ስለ አመጣጡ ጠየቅነውና፣ ስለ እኛ ድርጅት ዓላማና ኀብረ ብሔር ድርጅትነት አስረዳነው። ወዲያውም ለእርሱ የሚሆነው በብሄር ላይ የተመሠረተው የትግሬኛ ተናጋሪዎች ድርጅት የሆነው ሕወሐት ሳይሆን ኀብረ ብሔር የሆነው የእኛ ድርጅት ኢሕአፓ መሆኑን ከጴጥሮስ ጋር እየተፈራረቅን አስረዳነው።

እርሱ ግን ስለ ኢሕአፓ በደንብ እንደሚያውቅና ወደዚህ የመጣው ከወያኔዎች ጋር ለመቀላቀል መሆኑን ነገረን። ሁላታችንም በጣም ተገረምንና ሰውየው የሰጠንን መልስ እልፍ ብሎ እየጠበቀን ለነበረው ካድሬ ለአርአያ ነገርነው።

አርአያ በከፍለ ሕዝብ ሥራ ላይ ካጋጠሙኝና ከማከብራቸው ጥቂት በሳል የወያኔ ካድሬዎች አንዱ ነበረ። የጋራ ጉዳዮች ሲያጋጥሙን ተባብሮ ለመሥራት የሚመችና ጥሩ ሐሳብ ማምጣት የሚችል ሰው ነበረ። ከዚህ ሌላ እኛም የምናቀርበውን ሐሳብ በቀላሉ የሚረዳ፤ ለሁለቱም ድርጅቶች የጋራ ጥቅም የሚያስገኝ ነገር ላይ ለመተባበር የማያመነታና በራሱ የሚተማመን ሰውም ነበር። ለዚህም ነው የእርሱን ሐሳብ ያለምንም ጥርጣሬ ተቀብለን ሰውየውን ለማነጋገር የወሰንነው።

አርአያ መልሳችንን ከሰማ በኋላ "ምናልባት ቀድሞ ወደ እኛ ስለመጣ ወደ እናንተ ለመግባት ፈርቶ ይሆናል። በዚህ በኩል ምንም እንዳይሰጋ እነግረዋለሁና እንደገና በደንብ አነጋግሩት፤ እስከምትጨርሱ ድረስ እጠብቃችኋለሁ" ብሎ ለብቻው ትንሽ አነጋገረውና መልሶ ወደ እኛ ላከው።

አርአያ የተጨነቀው ሰውየው ወደ እነርሱ ቢመጣም የትግሬኛ ተናጋሪ ስላልሆነ ከመግባባትም ሆነ ከዓላማ አንጻር ሊቸገር ይችላል ብሎ ነበር። "አይቻልም" ብሎ እንዳይሸኘው ደግሞ ብዙ መንገድ አቋርጦ ለመታገል





የመጣን ሰው በአይሆንም ብቻ መመለስ በጣም ከብዶታል። ስለዚህ ለማሳመን የተቻለንን ሁሉ ጥረት እንድናደርግ ተማጸነን።

አርአያ እንዳለው ሰውየውን ደግመን አነጋገርነው። እነርሱ ጋ ምን ችግር እንደሚገጥመው፣ ፣ ለአንድ አማራ ትግራይን ነጻ የማውጣትን ትግል ዓላማዬ ብሎ መቀበል አስቸጋሪ እንደሚሆን፣ የእኛ ድርጅት ግን ከየትኛውም ብሔር የመጣን ታጋይ ሊቀበል እንደሚችልና ለእርሱ ከኢሕአሠ የተሻለ አማራጭ እንደሌለው አስረዳነው።

ሰውየው በእርግጠኝነት ከወያኔ ጋር ሊታገል ስለመጣ ወደሌላ ወደማንኛውም ድርጅት እንደማይቀላቀል ገለጸልን። እኛም በጣም ተገርመን ለዚህ ውሳኔው መነሻው ምን እንደሆነ ጠየቅነው። መልሱን ሲነግረን ደግሞ የበለጠ ገረመን።

"እኔ ከከተማ ስመጣም ስለሁለቱም ድርጅቶች ሰምቻለሁ። ነገር ግን 'ወያኔዎች አማራ አይወዱም፣ አማራ ካገኙ ይገድላሉ' ሲሉኝ፣ 'ውሸት ነው እንዲህ የሚያደርግ ድርጅት ሊኖር አይችልም ብዬ ስከራከር 'እኔ ወደ ወያኔዎች እሄዳለሁ ከገደሉኝ የእውነትም ያላችሁት ልክ ስለሆነ ለሁሉም ደፍራችሁ ተናገሩ። እኔን ከተቀበሉኝና ካልገደሉኝ ግን የእናንተ መረጃ ተራ ወሬ እንደሆነ ታውቃላችሁ' ብዬ ነው የመጣሁት። ስለዚህ ነው ከእነርሱ በስተቀር እናንተ ጋ አልገባም ያልኳችሁ" አለን።

ብዙ ሞክረን ስላቃተን አርአያ ወደሚጠብቀን ቦታ ሄደን ፣ የሰጠንን መልስ ነገርነው። አርአያም ምንም ማድረግ ባለመቻሉ በጣም ቅር እያለውና ከእነርሱም ጋር ቢቀጥል ሊኖር የሚችለውን ችግርና የዓላማ አለመጣጣም ገልጾልን ተሰናብቶን ሰውየውን እንዳመጣው ይዞት ተመለሰ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ያ አርአያ ያመጣው ሰው ከወያኔዎች ጋር ሆኖ እየታገለ እንደሆነና ከተራ ታጋይነት አልፎ ከፍ ባሉ ሐላፊነቶች እየተመደበ በመሥራት ላይ መሆኑን ተረድቻለሁ። ኢሕአድግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም ወንድወሰን የሚባለው የገንዘብ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣን ያ ሰው መሆኑንም ሰምቻለሁ።



ሕዝብ ውስጥ ገብተን የመቀስቀስና የማደራጀት ሥራ ስናከናውን





በክፍለ ሕዝብ ሥራ ላይ ምድርባ እያለሁ፣ ከኢሕአሠ ጋር ለመቀላቀል በእኛ በኩል ወደ አሲምባ ለመሄድ የመጡትን አርባ የሚደርሱ የአየር ወለድ አባላት ከሕዝቡ ጋር ሆነን ተቀበልናቸው። የአየር ወለድ አባላቱ በሙሉ ግሩም የሆነ ወታደራዊ ቁመና ነበራቸው። ሁሉም ዘመናዊ ኤም ፎርቲን ጠመንጃ ታጥቀው ከእነወታደራዊ የደንብ ልብሳቸው ሲታዩ ልዩ ድባብና ግርማ የተላበሱ ነበሩ። በተለይ ለእኛ በኢሕአሠ ውስጥ ለምንገኝ አባላት የእነርሱ ወደእኛ ድርጅት መግባት፣ በድርጅታችን እንድንኮራ፣ በአቋማችን እንደንተማመንና እንድንጸና የሚያደርግ መንፈስ እንድንላበስ አድርጎን ነበር።

እነዚያ ደርግን ከድተው በኤርትራ መሬት ከጀብሀዎች ጋር የቆዩትን አየር ወለዶች የእኛ ሰዎች ከኤርትራ ወደ አሲምባ ይዘዋቸው ሲሄዱ ነበር እግረመንገዳቸውን እኛ በነበርንበት ቦታ ያረፉት ።

ምድርባ ላይ ሰንጋ ታርዶላቸው ከእነርሱ ጋር አብረን እየበላንና እየጠጣን ውለን፣ እነርሱ ወደ አሲምባ ለመሄድ ሲነሡ እኛም ወደየሥራችን ተሰማራን። ያን ጊዜ እነዚያን የአየር ወለድ አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያቸው ከብዙዎቹ ጋር በቅርብ ለመተዋወቅና አብሮ ለመሥራት ዕድል አገኛለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም። ሆኖም ግን አብዛኞቹ በኢሕአሠ የትግል ታሪኬ እጅግ የምወዳቸው የማከብራቸውና አብሬ ክፉ ደግ የተካፈልኳቸው ውድ ጓዶች ሆነውኛል። እነሱም፤

1. ሌተናል ኮሎኔል ዓለማየሁ አሰፋው
2. ሌተናል ብርሃኑ ኡርጌ
3. ሌተናል አያልሰው
4. ሌተናል ፍጹም አብርሀ
5. ሕብስቱ
6. አያሌው
7. በዕደማሪያም
8. ዘውዴ
9. ጌትነት
10. ጌታሁን
11. መኮንን
12. ብንያም
13. ታዬ ቶላ
14. ግርማ ቺኪ
15. ግርማ በልሁ
16. ወንድማገኝ
17. አከሊሉ
18. ዓለማየሁ ሊቁ
19. ተኮላ
20. መሰሉ
21. ጳውሎስ
22. መኮንን ኢታሙ
23. ባንጃው
24. ሥራብዙ





25. ነጋሽ
26. ኪሩቤል
27. ደፋሩ
28. መኮንን ደጀኔ
29. ንጉሡ
30. ተሰማ
31. ዘሪሁን
32. ሙሊሳ
33. አሰፋ
34. ትእዛዙ
35. ሙሉ ዓለም ዘውዱ
36. ቅመሙ
37. ምስግናው
38. በቆዬ ናቸው።



ሌተናል ኮሎኔል ዓለማየሁ (አበጀ ) ሌተናል ብርሃኑ ኡርጌ ሌተናል አያልሰው ሌተናል ፍጹም አብርሀ አምሳ አለቃ ሕብስቱ(ከግራ ወደ ቀኝ)

በ1969 ዓ.ም ከመስከረም ወር ጀምሮ ለጥቂት ወራት ደግሞ በጉሎ ማከዳና በዳሞ ወረዳዎች ውስጥ በዚያው በክፍለ ሕዝብ፣ ሥራ እየተንቀሳቀስኩ ነበር። ጥቅምት 14 ቀን ዳሞ ውስጥ በሚገኘው የደብረ ዳሞ ገዳም፣ የአቡነ አረጋዊ ዓመታዊ በዓል የሚከበርበት ቀን ነው። ይህ በዓል በሚከበርበት ዕለት በቦታው ተገኝተን የቅስቀሳ ሥራ ለመስራት ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ለመሄድ በአንድ ቀን ቀደም ብለን ተነሣን።

የአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የሚገኘው ደብረ ዳሞ ተራራ ላይ በሚገኘው ገዳም ነው።በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ አረጋዊ የተመሠረተው የደብረ ዳሞ ጥንታዊ ገዳም በመካከለኛው ትግራይ ከአዲግራት በስተምዕራብ አቅጣጫ ይገኛል። ገዳሙ ከመሬት ወለል በላይ 2216 ሜትር ከፍታ ባለው ደብረ ዳሞ ተብሎ በሚጠራው ተራራ ስም የተሰየመ ነው።

በተራራው አናት ላይ የ25 ሜትር ከፍታ ያለው ኮረብታ ይገኛል። ኮረብታው ዙሪያውን ቀጥ ያለ ዳገት ስለሆነ በእግር መውጫ መንገድ የለውም። የሚወጣው ከቆዳ በተሠራ ወፍራም ገመድ (ጠፍር) ወገብ ላይ ታስሮ ከኮረብታው አናት ላይ በሚገኙ መነኩሴዎች እንድ በአንድ እየተጎተቱ ነው። ኮረብታው አናት ላይ 400 በ1000 ሜትር ስፋት ያለው አምባ ይገኛል። የአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያንና ገዳሙ የሚገኙት በዚህ አምባ ላይ ነው።ደብረ ዳሞ ገዳም መግባት የሚፈቀደው ለወንዶች ብቻ ነው።

የገዳሙ መሥራች የሆኑት አቡነ አረጋዊ ከዘጠኝ የእምነት ጓደኞቻቸው ጋር ከሶሪያና ከአካባቢ ሀገሮች መጥተው ወደ ትግራይ እንደገቡ ታሪክ ይናገራል። እነዚህ ዘጠኝ ቅዱሳን ወይም ወንጌላውያን አባ አረጋዊ፣ አባ





ጸንጠሌዎን፣ አባ አፍጼ፣ አባ አሌፍ፣ አባ ገሪማ፣አባ ጉባ፣ አባ ሊቃኖስ፣ አባ ጽሕማና አባ ይምአታ ይባላሉ።

ዘጠኙም በትግራይ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት አቋቁመዋል። ከእነዚህ መካከል በአባ ገሪማ የተመሠረተው፣ በሰሜን አድዋ የሚገኘው የአባ ገሪማ ገዳም አንዱ ነው። አባ ሊቃኖስና አባ ጸንጠሌዎን፣ አክሱም የሚገኘው የጸንጠሌዎን ገዳም መሥራቾች ናቸው። በታሪካዊዋ የትግራይ ከተማ የሀ የሚገኘው ገዳም ደግሞ የተመሠረተው በአባ አፍጼ ነው። በእነዚህ ወንጌላውያን የተመሠረቱት ገዳማት በትግራይ ውስጥ በጣም ታዋቂ ከመሆናቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ገዳሞች የተመሠረቱባቸው ወረዳዎች ጭምር የሚጠሩት በስማቸው ነው። አባ አፍጼና አባ ገሪማ ወረዳዎችን ለዚህ አባባል እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

እኛም በክብረ በዓሉ ዕለት በጊዜ ደረስንና መዛሙር ዳሞ ገብተን ከገዳሙ ስር አደርን። ለቅስቀሳ ስራችን ስንንቀሳቀስ፣ በሐዲስ ዛህላይና በናደው የምትመራው ኃይል አምስት ጸጥታውን ለማስከበር ስለምትመጣ ምንም ስጋት እንደማይኖርብን ተነግሮናል። ከጥዋት ጀምሮ ሰው መጉረፍ ጀምሯል። በየዓመቱ እንደተለመደው የደብረ ዳሞ ገዳም ከትግራይ አካባቢዎችና ከኤርትራ በመጡ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ተጨናነቀ። ከገጠር ብቻ ሳይሆን ከየከተማውም የሚመጣው ሕዝብ ብዙ ነው። ኃይል አምስትም በጥዋት በቦታው ደርሳለች። ከእኛ ኃይል በተጨማሪ ሕወኃቶችም የተወሰኑ ኃይሎችና የኪነት ቡድናቸውን ይዘው መጥተዋል። ከእነርሱ የኪነት ቡድኑ አባላት መካከል ባህታ ገብረሕይወትና ብዙአየነ ዘገየ ይገኙባቸዋል።

የኃይል አምስቱ የፖለቲካ ሐላፊ ናደው (ዓባይ አብርሃ) እንደደረሰ ገዳሙ ወደሚገኝበት ኮረብታ ላይ ለመውጣት ወሰነ። እኔም ናደውን አጅቤ

እንድወጣ በመመደቤ ሐዲስ ዛሀላይ ደኅና ጠመንጃ መርጦ ሰጠኝና ከናደው ጋር አብሬ ለመውጣት ተዘጋጀን። በዚህ ጊዜ ኃይል አምስት የያዘችው የማጭድና መዶሻ ምስል ያለው ትልቅ ቀይ የሠራዊቱን ዓርማ ባንዲራ ስለነበረ እሱም ተሰጠኝና በወገቤ ዙሪያ ደጋግሜ ጠምጥሜ ያዝኩት።

ዋናው ታቦት ያለበት ቤተክርስቲያን የሚገኘው ለመውጫ የሚሆን የእግር መንገድ በሌለው የኮረብታ አምባ ላይ ስለሆነ ወደ አምባው የሚወጣው በጠፍር፣ ወገብ ላይ ታስሮ ከላይ ባሉት መነኮሳት እየተጎተቱ ነው። እኔ ተራዬ ደርሶ ለመውጣት ስዘጋጅ ጠመንጃ ይዤ ልወጣ መሆኑን የተመለከቱ ሰዎች፣ "ጠመንጃ ይዘህ ወደገዳም መውጣት ስለማትችል ይቅርብህ" አሉኝ። በአካባቢው ባህል ጠመንጃ ይዞ መንቀሳቀስ እንግዳ አይደለም። ሆኖም እንደኔ ጠመንጃ ይዞ በገመድ እየተጎተተ ለመውጣት የሞከረ ሰው ከዚያ ቀደም ስላላጋጠማቸው ነበር "እንዴት መሣሪያ ይዘህ ለመውጣት ትሞክራለህ?" ብለው ያንገራገሩብኝ። እኔ ደግሞ ትእዛዝ መፈጸም ስለነበረብኝ፣ "ግዴለም ምንም አታስቡ" በማለት መሣሪያ እንደታጠቅኩ በገመድ ወገቤን አስሬ እየተጎተትኩ ወጣሁ፣ ናደውም እንደዚሁ ተከትሎኝ ወጣ። እኔ ገዳሙ የሚገኝበት ኮረብታ ላይ ስወጣ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር።

ታቦቱ ሲወጣ በቀሳውስቱና በሃይማኖቱ አባቶች በቀዳሚነት ይታጀባል። ከቀሳውስቱ ኋላ ደግሞ ሕዝቡ ይከተላል። ታቦቱ እንደወጣ በወገቤ ላይ ጠምጥሜ የያዝኩትን የሠራዊቱን ዓርማ ፈታሁና እያውለበለብኩ ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለን አብረን ቤተክርስቲያኑን መዞር ጀመርን። በመካከል ናደው ወደ ኋላው ዞር ሲል አንድ ያልጠበቀው ሰው ተመለከተና " አማኑኤል፣ አማኑኤል!" ብሎ ጠራኝ።





እኔና ናደው ጎን ለጎን ሆነን ነበር የምንሄደው። ናደው መሣሪያ አልያዘም። እኔ ደግሞ መሣሪያ የተሰጠኝ እርሱን ለማጀብ ስለሆነ የምሄደው ግራና ቀኙን እያጣራሁ ነበር። ስሜን ሲጠራ በተጠንቀቅ ቀና ብዬ ተመለከትኩት። እርሱም "በስተጀርባህ ያለውን ሰው ተጠንቀቀው" አለኝ። ወደኋላ ዞር ብዬ ስመለከት ምንም አጠራጣሪ ሁኔታ ያለው ሰው አልታየኝም። ግራ ገብቶኝ እንደገና ፊቴን ወደእርሱ አዞርኩና ግራ በመጋባት ስመለከተው አይቶ "ከኋላችን ያለው ሰው ዋና የወያኔ ሰው ስለሆነ ጥንቃቄ አድርግ" አለኝ።

እንደገና ወደኋላ ዞሬ አየሁ። አንድ ረዥም ገበሬ ብቻ ነው ከኋላዬ ጎላ ብሎ የሚታየኝ "አዎ! እርሱ! ከኋላህ ያለው! አረጋዊ በርሔ የሚባለው ቀጣፊ ነው። እንዳይጠጋህ ተጠንቀቀው" አለኝ የዓይኖቼን አቅጣጫ ተመልክቶ።

አረጋዊ በርሔን በስም ገናና መሆኑን እንጂ በአካል አይቼው አላውቅም። ስለዚህ እንደገና ወደ ኋላዬ ዞር አልኩና አተኩሬ ተመለከትኩት። ረዥም፣ ጠይም፣ ትላልቅ ዓይኖችና፣ ቀጥ ያለ አፍንጫ ያለው ነው፤ የገበሬዎች ዓይነት አለባበስ ለብሷል።

አረጋዊም የእኔን መጠንቀቅ አየና "ብጻይ፣(በትግሪኛ ጓድ ማለት ነው) ተው እንጂ አትሳደብ ነውር ነው።" አለው።

ናደውም መለሰና "አንተ አጭበርባሪ ሌባ፣ የትግራይን ሕዝብ እያደናገርክ መኖር የለመድክ! ለምንድነው፣ ሐቀኛ ለመምሰል የምትሞክረው - እ ? በትግራይ ሕዝብ ስም ለመነገድና ለማጭበርበር ነው?። ደግሞ ገበሬ ለመምሰል ነጠላ ደርበህ፣ ንጹሕ ሰው ይመስል፣ በሕዝብ መካከል ታቦት አጅበህ ትዞራለህ። ሌባ! አሁንም ደጋግሜ ልክ ልክህን እነግርሃለሁ። ቀጣፊ፣ አስመሳይ ሌባ !!" እያለ እየደጋገመ ሲደበው።

አረጋዊ ናደው እንደማይተወው የገባው መሰለኝ፤ ከነገሩ ለመሸሽ ዞር ብሎ ከእኛ ርቆ ሄደ። ናደው፣ አረጋዊ ከሄደም በኋላ ታቦቱ ገብቶ ከገዳሙ ወደታች እስከንወርድ ድረስ "ይሄ ቀጣፊ! አጭበረባሪ! ሌባ!" እያለ መሳደቡን አላቆመም። መጨረሻ በጠፍር ታስረን እንደወጣነው ሁሉ ተራ ጠብቀን ከኮረብታው ላይ ታስረን ቁልቁል ወረድን። እኔም የተሰጠኝን ጠመንጃ ለሓዲሽ አስረከቤ ከጓደኞቼ ጋር ተቀላቀልኩ፣ ከናደውም ጋር ተሰነባበትንና ተለያየን። ናደው ስንለያይም ፊቱ እንደተጨማደደ ነበር።

በዚያ ሕዝባዊ አገልግሎት ላይ እያለን ከወያኔ አባላት ጋር ስንገናኝ ባለመግባባት ችግሮች የሚፈጠሩበት ጊዜያት ነበሩ። ከወያኔ ካድሬዎች ጋር ስንገናኝ አብዛኛውን ጊዜ የሚነሣው ጥያቄ "ከብሔርና ከመደብ ጥያቄ የትኛው ይቀድማል?" የሚለው ርእስ ሲሆን፣ አንዳንድ ብስለት ያላቸውና ለውይይት ዝግጁ የሆኑ የወያኔ ካድሬዎች ሲያጋጥሙን በአቋም ባንተማመንም ውይይታችን በመግባባትና በሥነሥርአት በማካሄድ በጥሩ መንፈስ እንለያይ ነበር። ከሌሎች ደግሞ በጭቅጭቅና በንትርክ ጊዜ ፈጅተን እንዲሁ እንለያያለን።

በዚያ ጊዜ ሕዝቡን ማስተማር ብቻ ሳይሆን እኛም ከሕዝቡ አስተያየትና ጥያቄዎች ብዙ ትምህርት አግኝተናል። የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ሕዝብ እንደሆነ በሚገባ አውቀናል። ከዚህም በተጨማሪ የሕዝቡ የትግል መንፈስና ንቃት ወደር የማይገኝለት ነበር። ከሕዝቡ ጋር ስንወያይ የብሔርም ሆነ የመደብ ጭቆና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ችግሮች ስለሆኑ ለሁለቱም ጥያቄዎች በመታገል ነጻነትን ማምጣት እንደሚያስፈልግ ነበር የምንገልጸው። ሕዝቡን ከሚያምታቱት ነገሮች አንዱም ኢሕአሥና ወያኔዎች በኤርትራ ጥያቄ ላይ ያላችው ልዩነት ነበረ፤ እንደማገኘውም የኢትዮጵያ ክፍል ሁሉ የትግራይ ሕዝብም የኤርትራ ጥያቄ እጅግ ያሳሰበው ነበር። በአጠቃላይም በእኛና በወያኔዎች መካከል የነበረው ልዩነት የትግራይን ሕዝብ የሚያስጨንቀው ጉዳይ ነበር።





"ሁለታችሁም ልጆቻችን ናችሁ፤ ለምን ልዩነታችሁን በር ጋታ ተነጋግራችሁ አትፈቱትም፣? ለምንስ ተስማማታችሁ በአንድነት አትታገሉም?" እያሉ ይጠይቁን ነበር።

እኛ ሁለቱም ጥያቄዎች መመለስ እንዳለባቸው እንናተምራለን። ስለዚህ ሕዝቡ የመደብ ጭቆና ብቻ ሳይሆን የብሔር ጭቆናም እንዳለበትና እነዚህ ጥያቄዎች እስኪመለሱ ድረስ መታገል እንዳለበት እንናገራለን፡፡ በአንጻሩ እኛም ከትግራይ ሕዝብ ብዙ ትምህርት አግኝተናል። የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ያለው ኩራት ስለሀገር ፍቅር የበለጠ እንድንረዳ አድርጎናል። የትግራይ ሕዝብ ታጋይ በመሆኑ ከትግል ልምዱም ብዙ ትምህርት አግኝተናል።

ከዚህ ሌላ የድርጅታችንን አሠራር አስመልክቶ ግራ የሚገቧቸውን አንዳንድ ነገሮች ይጠቁሙንም ነበር። ለምሳሌ "ድርጅታችሁ በከተማ ደርግን እንደሚያጣድፈው እንሰማለን፤ እዚህ በገጠር ውስጥ ግን ብዙ ፍጥነት የላችሁም። የፖለቲካ ቅስቀሳ ብቻ እንጂ ወታደራዊ ንቅናቄ ብዙ አታደርጉም። ለምንድነው? የከተማውና እዚህ ያለው ድርጅታችሁ አንድ አይደሉም ወይ? ከተማ የሚሰጠው መመሪያና እዚህ ገጠር የሚሰጠው መመሪያ የተለያየ ነው ወይ?" የሚሉ ጥያቀዎችንም ያነሡ ነበረ።

ውሎ አድሮ የምንደርስበት ቦታ እየሰፋና ሥራው እየተፋጠነ ሲሄድ የከፈለ ሕዝብ ሥራችንም በዚያው መጠን መፍጠን ነበረበት። ስለዚህም ኃይሎች ከሚሰፍሩበት ቦታ ራቅ እያልን መሄድ ጀመርን። በእጃችን የነበረው ትጥቅ ግን በጣም ትንሽና በጥራትም ዝቅተኛ ስለነበረ ለአደጋ ለመጋለጥ ቅርብ ነበርን። አንዳንዴ የምንይዛቸው መሣሪያዎች፣ የማይተኩሱ ሽጉጦች፣ እንደልብ የማይሠሩ አልቤን ወይም ካርባይን ጠመንጃዎችም ነበሩ። ችግሩን በሚመለከት ከሰዓሲዕ ትንሽ ወጣ ብሎ በሚገኝ ዳላ በሚባል ቦታ ሁላችንም ተሰብስበን ተነጋገርን። ራቅ

እያልን በሄድን መጠን ችግሩ አሳሳቢ እየሆነ፤ ለጠላትም የመጋለጥ ዕድላችን እየሰፋ መሆኑን ገልጸን ደኅና መሣሪያዎች እንዲሰጡን መጠየቅ እንደሚገባን ወሰንን። በሁለተኛው ቀን የብዙሃን ድርጅት አባላት በሙሉ ከአመራሩ ጋር ለመወያየት ወደ ዳውሃን ሄድን።

ከአመራሩ ጋር በተደረገው ስብሰባ የፖለቲካ ኮሚሣሮች እንዲሁም ከአመራር ሮባ ተገኝቶ ነበር። ከእኛ በኩል ደግሞ እኔ፣ ጀሚላ፣ (ጀሚላ የመጀመሪያዋ የኢሕአሠ ሴት ጓዲት ስትሆን እውነተኛ ስሟ መድፈሪያሽ በላይ ይባላል) ጴጥሮስ፣ ስባጋድስ፣ ኤልያስ፣ ሐዲሽ በየነ፣ሐጎስና ይስሐቅ ነበርን። እነሮባም ችግራችንን አዳመጡና ሁኔታዎችን በተቻለ መጠን ለማሻሻል እንደሚሞክሩ ነግረውን ተለያየን።

በዚያን ጊዜ በአጋጣሚ የደረስነው ሠራዊት የመቀየጥ ምደባ የተደረገበት ጊዜ ላይ ስለነበረ፣ ስብሰባው ካቢቃ በኋላ የእያንዳንዱ ጓድ ምድብ ተነገረ። ሁሉም ምደባውን ሲያውቁ እኔ ብቻ አልተነገረኝም። "አንተ ምድብህ አልታወቀም፤፣ ጾረና የነበረ አንድ ጓድ ወደሌላ ቦታ ስለተመደበ ጾረና ላይ የአንድ ሰው ቦታ ይኖራል፤ ስለዚህ አንተ ምናልባት ወደ ጾረና ትሄድ ይሆናል" ተባልኩ። በማግስቱ ሁሉም ወደየምድባቸው ሲሄዱ እኔ ከአመራሩ ጋር ቆየሁና በሁለተኛው ቀን ለቅስቀሳ ሥራ ሄዳ የነበረችው ኃይል ሦስት ስትመለስ ወደ ኃይል ሦስት ተመድበሀል ተብዬ ከእነሱ ጋር ተቀላቀልኩ፡፡





**የበጌምድር ጉዞ**

በ1969 ዓ.ም በጥቅምት ወር ኃይል ሦስት የፖለቲካና የፕሮፓጋዳ ቅስቀሳ ለማድረግ ወደ አድዋ አካባቢ ተንቀሳቀሰች። የኃይል ሦስት መሪ ኃይሌ ቀጭኑ፣ ምክትሉ ጌትነት ሲሆኑ፤ የኃይሉ የፖለቲካ ሐላፊ ደግሞ ሽፈራው ነበር። ጌትነት ከኃይል ምክትል መሪነቱ በተጨማሪ እኔ የነበርኩበት ጋንታም መሪ ነው። የነበርኩባት ጋንታ ምክትል መሪ እኔ ስሆን የጋንታዋ የፖለቲካ ሐላፊ ደግሞ አብደላ ሆነ። (ከሺፈራው ጋር በወሎ ተልእኮ ላይ አብረን ስለነበርን በደንብ እንተዋወቃለን።) ወደ ገርሁ ስርናይ ለመሄድ ከዳሞ መንገድ ይልቅ የኤርትራን መሬት አቋርጦ ማለፍ በጣም ስለሚቀርብ በዚያው በኩል ሄድን።

ወደ ኤርትራ መሬት ስንገባ ባለፍንባቸው አካባቢዎች ያገኘናቸው የኤርትራ ነዋሪዎች በጥሩ ሁኔታ ነበር የተቀበሉን። የኤርትራ ድርጅቶች "የኢትዮጵያ መንግሥት ቅኝ ገዥ ነው!" እያሉ ሲቀሰቅሱ እንደነበር ስለምናውቅ፣ እኛ ደግሞ "የኢትዮጵያ ታጋዮች ነን! የደርግን መንግሥት በመቃወም ነው በረሐ የገባነው!" ብለን ራሳችንን ስናስተዋውቃቸው በቀላሉ ለማመን ይቸገራሉ ብለን ፈርተን ነበር። እነርሱ ግን ልክ እንደልጆቻቸው አድርገው ተቀብለው አስተናገዱን። በተለይ አንዳንድ የተማሩ ሰዎችን ስናገኝ ስለኢሕአፓ ከማወቃቸው በላይ "ዲሞክራሲያ ካላችሁ ስጡን" እያሉ ይጠይቁን ነበር። በሕዝቡ አቀባበልና ለእኛ በነበረው አመለካከት ሁላችንም በጣም ተደነቅን።

ኃይል ሦስት የኤርትራን ምድር አቋርጣ ወደ አድዋ ከዘለቀች በኋላ በጉሎ ማከዳ፣ ዳሞ፣ እንዲሁም አድዋ አካባቢ እየተተዘዋወረች የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ስትሠራ ቆይታ ወደ አሲምባ ተመለሰች።

በ1969 ዓ.ም በጥር ወር ከአድዋ እንደተመለስን፣ ወደ በጌምድር እንደምንሄድ ተነገረን። የምንሄድበት ምክንያት በጌምድር ላይ ለሚገኘው

ሠራዊታችን መትረየስ ለማድረስና እዚያ የሚገኘውን የሠራዊቱን ኃይል ለተወሰነ ጊዜ እንዲጠናከር ለማድረግ ነበር።

ወደ ጎንደር ስንሄድ በኃይሏ ውስጥ ከነበርነው ጎንጂን የማያስታውስ ማንም የለም። ጎንጂ በጣም ተግባቢ፣ ተጫዋችና በክፉም ሆነ በደግ ጊዜ የሆነ ገጠመኝ እያነሣ የሚያስቀንና የሚያዝናናን ተወዳጅ ጓድ ነበር። ከጎንጂ ሌላ የማስታውሳቸው አሰፋ ባዩ፣ ጀማል፣ ስዩም፣ መኩሪያ፣ ከበደ አሊና ሌሎችም በወታደራዊውም ሆነ በፖለቲካው ጥሩ ልምድና ብስለት ነበራቸው።

ወደጎንደር የምንሄድበት አቅጣጫ የተከዜን ወንዝና በረሐውን አቋርጠን እንደሚሆን አውቀናል። እንትጮ ላይ ትልቅ የወያኔ የጦር ሠፈር እንዳለ ስለሚታወቅ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግም ይጠበቅብን ነበር። በእኛ ድርጅት በኩል በአካባቢው ምንም ዓይነት የፖለቲካ ሥራ አልተሠራበትም። ብዙም እንቅስቃሴ ለማድረግ ዕቅድ የለንም። ኃይሏ የታዘዘችው በተከዜ በረሐ አቋርጣ ወደጎንደር እንድታልፍ ብቻ ነበር።

የተከዜ ተፋሰስ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው።፣ አብዛኛውን የኤርትራን ምዕራባዊ ወሰን የሚያሰምር፣ በጥልቀቱ ከአፍሪካ አንደኛ የሆነ የወንዝ ሸለቆ ያለበትና በረሐ ነው። ይህ ጥልቀቱ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እስከ 2000 ሜትር ይደርሳል። ተከዜ ወንዝ ላስታ ከሚገኘው ካጭን ተራራ ይነሣና የምዕራብንና የሰሜንን አቅጣጫ እየያዘ በትግራይና በኤርትራ አድርጎ ወደሱዳን የሚገባ ወንዝ ነው።

የተከዜ በረሐ የራሱ የሆነ የጦርነት ታሪክም ያለው በረሀ ነው። በ1929 ዓ.ም.የካቲት በሁለተኛው የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ አርበኞች መሸሸጊያ ነበር። በዚያኑ ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች፣ በኢጣሊያ





የአየር ኃይል በመርዝ ጋዝ ያለቁትም፣ ወደ ተከዜ በረሀ እያፈገፈጉ ባሉበት ወቅት ነበር።

የዚህን ወንዝ ሸለቆ ተከትሎ የተዘረጋው በረሀ በጣሊያን ጊዜ የአርበኞች ከለላ እንደሆነ ሁሉ፣ ወያኔዎችም ከደርግ ኃይል ከለላ እንዲሆናቸው የጦር ሰፈር መሥርተውበታል። እኛ ደግሞ ወደ ጎንደር ለመሄድ የተነሣነው ይህንን የተከዜን በረሐ ሰንጥቀን በማለፍ ነበር። በተከዜ በረሐና በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች በወያኔ ሠራዊት ስር በመሆናቸው፣ ስለእኛ የሚኖራቸው አመለካከት የተዛባ መሆኑ የታወቀ ነው። በእኛ ድርጅት የፖለቲካ ሥራ ያልተሠራበት አካባቢ ስለሆነ እዚያ ስንደርስ ጥሩ አቀባበል ይጠብቀናል የሚል ግምት አልነበረንም። በመሆኑም ኃይላችን ስትነሣ በቂ የሥነ ልቦና ዝግጅት አድርጋለች። በዚህ ምክንያት ወደተከዜ ስንጠጋ እኔ ትግሪኛ ተናጋሪ ስለሆንኩ፣ የኃይሏን ምክትል መሪ የጌትነትን ሬድዮ እንድይዘው ተደረገ።

ሬድዮ ይዤ በትግሪኛ ስነጋገር የአካባቢው ልጆች ሰምተው "ሐቡይ ኩርኩር፣ሐቡይ ኩርኩር" (ትልቁ የአማራ ውሻ) እያሉ እየሳቁብኝ ይከተሉኝ ጀመር። ነገሩ በጣም የሚያበሳጭ ቢሆንም ዓላማችንን ብቻ በማሰብ ልጆቹ ቢቀበሉም ባይቀበሉም በትግሪኛ እውነቱን ለማስተማር እየሞከርኩ እንደምንም በትዕግሥት አለፍኳቸው።

መንገዳችንን ቀጥለን ወርኢ በረሐ ገባን፤ የወርኢ በረሐ በትግራይ ውስጥ የሚገኘው ትልቁ በረሐ ነው። ከትግራይ ሦስት አውራጃዎች ማለትም ከአጋሜ፣ ከአድዋና ከተንቤን አውራጃዎች አቋርጠው የሚመጡ ወንዞች የሚገናኙበትና ወደተከዜ የሚገቡበት ቦታ ነው።

በረሐውን እያቋረጥን ስንሄድ፣ አንድ የወያኔ ኃይል እየተከተለን እንደሆነ አወቅን። አካባቢው እነሱ የሚንቀሳቀሱበት ቦታ በመሆኑ መምጣታችንን

ሰምተው እንቅስቃሴያችንን እየተከታተሉ ነበር። እነርሱ ስለእኛ ሊያገኙ የማይችሉት መረጃ ቢኖር ለምን አላማ እንደመጣን ማወቅ ብቻ ነው።

የወያኔ ኃይል እንደምትከታተለን ስለተረዳን፣ በተቻለን መጠን ከበስተጀርባ ያሉ ጓዶች ኮቴያችንን እያጠፉ ዳናችንን በማሳሳት በተለየ አቅጣጫ የሔድን እንዲመስል ለማድረግ ሞክረናል። ከወያኔዎች ኃይል ጋር አንዳንዴ ፊትና ኋላ፣ አንዳንዴ ደግሞ ግራና ቀኝ፣ እየሆንን መንገዳችንን ቀጠልን። ወደ ተከዜ በረሐ ገብተን የምናቋርጥበትን አቅጣጫ እንዳያውቁ የበስተግራውን አቅጣጫ የምንይዝ አስመስለን በቀኝ በኩል አቋርጠን ለማለፍ ነበር የፈለግነው።

እንደዚያ በድብብቆሽና በጥንቃቄ ተጉዘን፣ ወደ አመሻሹ ላይ ተንቤን አውራጃ ውስጥ በምትገኝ ወርቅ እንባ በምትባል ትንሽ መንደር በኩል ብቅ ስንል ትከታተለን ከነበረችው የወያኔ ኃይል ጋር ፊት ለፊት ተገናኘን። "ማነህ ቁም! ማነህ ቁም!" እየተባባልን፣ ተፋጠጥን። ሁለታችንም ማንነታችንን ለማረጋገጥ ስለፈለግን፣ ሁለት ሁለት ሰዎች እንድንልክ ተስማምተን ሰዎቹ ቁልቁለት ላይ ወርደው አንዱ የሌላውን ማንነት አረጋገጠ። በኋላ የምንጓዝበትን አቅጣጫ ለይተን ስምምነት ተደረገና ፍጥጫው በሰላም ተፈታ።

በዚህ መካከል "በአንዳንድ የፖለቲካ አቋሞቻችን ላይ ውይይት ብናደርግስ?" የሚል ሐሳብ መጣ። ሐሳቡ ከማን እንደመነጨ አላስታውስም እንጂ የሁለታችንም ወገን በሐሳቡ ተስማማ። ከሁለታችንም ጋንታዎች ሁለት ሁለት ሰዎች ዋርዲያ እንዲቆሙ ተደረገ። አንደ አጋጣሚ ውይይቱ የተካሔደበት እኔ የነበርኩባት ጋንታ የሰፈረችበት ቦታ ስለነበር፣ የእኛን ጋንታ ዋርዲያ የምቆጣጠረው እኔ ነበርኩ።

በዚያ ሐላፊነቴ ማድረግ የሚገባኝን ጥንቃቄ ሳስብ ከዚህ በፊት ከወያኔዎች ጋር ሰበያ ላይ ተሰብስበን እያለን የተፈጠረው አጋጣሚ ታወሰኝ። ልክ እንደአሁኑ ከእነርሱም አንድ ከእኛም አንድ አባል ለዋርድያነት ተመድበ ሁለት





ሁለት እየሆኑ ነበር ዘብ የሚቆሙት። ከእነሱ ዋርድያ የተመደበው አባል የያዘው ጥሩ መሣሪያ ሲሆን የእኛ አባል ግን የያዘው አሮጌ ማስ ጠመንጃ ነበር።

ውይይቱ እየተካሄደ እያለ፣ ጠመንጃ ባረቀና የተኩሱ ድምፅ ተሰማ። በዚህ ጊዜ በተፈጠረው መተራመስ ቤት ውስጥ በርታ የነበረችው ኩራዝ ጠፋችና በጨለማ ተዋጥን። ሁላችንም ሲጋት ውስጥ ገባን። ጨለማው በፍጹም የማያስተያይ ስለነበረ ውስጥ ያለነው ሁላችንም የምንይዘውና የምንለቀው ጠፍቶን ግራ በመጋባት ተደነባበርን።

ለዋርድያ የቆሙት የእኛና የእነርሱ ጓዶችም ምን እንደተፈጠረ ስላላወቁና ለእርምጃ መዘጋጀት ስለነበረባቸው ሁለቱም መሳሪያቸውን ደግነው አንዱ በአንዱ ላይ ሲያቀባብሉ፣የማስ ጠበንጃ የያዘው የእኛ ዋርድያ ማቀባበያውን ሲስበው ሊሠራለት አልቻለም። የእነርሱ ዋርድያ ግን የያዘው መሣሪያ ጥሩ ስለነበረ ወዲያው አቀባብሎ ደገነበት። የእኛ ዋርዲያ ዓይኖቹ ፈጠው የሚያደርገው ግራ ገባው። ሁልጊዜም በእንደዚህ ዓይነት ድንገተኛ ሁኔታ ላይ ፈጥኖ የመወሰን ችሎታ የነበረው ጂግሳ፣ እንደምንም ብሎ ከጨለማው ቤት ውስጥ ዘሎ ወጣና ባትሪ አግኝቶ ሲያበራ፣ የእኛ ዋርድያ ግራ ተጋብቶ እንዳለ ደረሰለትና ሁለቱንም አረጋጋቸው። ከዚያም ላምባዲና አመጣና አብርቶ በስበሰባው የነበሩት እንዲረጋጉ በማድረግ ተራ በተራ ወጥተው ችግሩ በዚያው አለፈ። ምን እንደተፈጠረ ከተጣራ በኋላ ሁሉም ተመልሰው ገቡና ኩራዝ በርቶ ውይይቱ እንደገና ቀጠለ።

ከዚያ አጋጣሚ በመነሣት ለዋርድያ የሚቆመው የእኛ ጠባቂ ጥሩ ጠመንጃ እንዲታጠቅ ማድረግ እንደሚገባኝ አሰብኩ። ስለዚህ ለተረኛው ዋርዲያችን፣ ኤም ፎርቲን ጠመንጃ እንዲይዝ አድርጌ ዋርድያዎቹ ሲለዋወጡ ጠመንጃውን ለቀጣዩ ተረኛ ዋርዲያ እየሰጠ ሰዎቹ ብቻ እንዲለዋወጡ አደረግሁ።

በውይይቱ ከሌሎችም ከእኛም ጋንታዎች የፖለቲካ ብስለትና የንግግር ችሎታ ያላቸው አባላት መጥተው እንዲካፈሉ ተደርገዋል። በውይይቱ የተካፈሉት አስር ያህል ሲሆኑ የሁለቱ ጋንታዎቻችን የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎች ኪዳኔና

ገላውዲዮስም ተካፍለዋል። እኔ ጸጥታውን የመቆጣጠር ሐላፊነት ስለነበረብኝ ወጣ ገባ እያልኩና ወደ ዋርድያ መቆሚያ ቦታ ደረስ መለስ እያልኩ ነበር በውይይቱ ላይ የሚሰጡ ሐሳቦችን የምሰማው።

በሁለቱም ወገን ብስለት ያላቸው አባላት ስለተካፈሉ የየራሳቸውን ትንታኔዎች ሰጥተውበታል። ከእነርሱ በኩል ተወያይ የነበረው የኃይሉ የፖለቲካ ሐላፊ አነጋገሩና አገላለጹ የሰውን ጆሮ የመያዝ ችሎታ ነበረው። ሰውየው ነገር የማይደጋግም፣ ከተነሣበት ነጥብ የማይወጣና በረጋ መንፈስ ሐሳቡን መግለጽ የሚችል መሆኑን ስመለከት፣ ወያኔዎችም እንደዚያ ዓይነት በሳል ፖለቲከኛ የነበራቸው መሆኑ አስገርሞኝ ነበረ። የዚያ የፖለቲካ ኮሚሳር አነጋገርና ሐሳቡን ያቀረበበት መንገድ ከዚያ በፊት ከወያኔ ካድሬዎች ከማውቀው አቀራረብ የተለየ ነበር።

ኮሚሳሩ ሲያስረዳ ደርግ በዚያን ጊዜ አውጥቶት የነበረው የመሬት ለአራሹ አዋጅ፣ ገበሬውን ለጊዜውም ቢሆን የሚያማልልና የደርግንም ማንነት የሚሸፍን ጭንብል ስለሆነ፣ ሕዝቡን በደርግ ላይ ለማነሣሣት የብሔር ጥያቄን ማስቀደም ጠቃሚ እንደሆነ ገለጸ። የብሔር ጥያቄን በማስቀደም የትግራይን ህዝብ ከዳር እስከዳር ማነሣሣት እንደሚቻልና ይህም በወቅቱ ከነበረው የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት ትግሉን ለማጠናከር በጣም የሚጠቅም ወሳኝ የታክቲክ ጥያቄ እንደሆነ አስረዳ። ይሁን እንጂ አለ ኮሚሳሩ "አሁን ባለንበት ሁኔታ፣ የብሔር ጥያቄን ማስቀደም እጅግ ቢጠቅምም፣ መሠረታዊውና ዋናው ጥያቄ ግን የመደብ ጥያቄ ነው። የብሄር ጥያቄ በታክቲክ ደረጃ የተነሳ ጥያቄ ነው። በድርጅታችን ስትራተጂ ዋናውና መሠረታዊው ጥያቄ አሁንም የመደብ ጥያቄ ነው" አለ።

እኔ ከወያኔ አባላት ጋር በተለያየ ጊዜ የመገናኘት ዕድል ስለነበረኝ የአንዳንዶቹን ለመደብ ትግል ምንም ያህል ቦታ ያለመስጠት ዓይቻለሁ። ይህ አዲስ የሰማሁት መከራከሪያ ነጥብም እውነት ቢሆን ኖሮ በተግባር ሊታይ የሚችል ፍንጭ





እንኳ ማየት ነበረብን እያልኩ ከራሴ ጋር እነጋገራለሁ። ወይንም ደግሞ ኮሚሳሩ ያነሳው ሐሳብ የእርሱና የአንዳንድ አመራሮች ሐሳብ ሆኖ በሌሎች ገና ተቀባይነት ያላገኘና በተግባር ያልሠሩበት አቋም ሊሆን እንደሚችልም ገምቻለሁ።

ሰውየው ንግግሩን በመቀጠል "የእኛ ድርጅት አቋም ይህ መሆኑን እናንተም ታውቃላችሁ። ስለዚህ እኛን ጠባቦች በማስመሰል፣ የብሔር ጥያቄ በመደብ ትግል ውስጥ የሚፈታ ነው እያላችሁ ሕዝቡን እያወናበዳችሁ አትከፋፍሉብን" ብሎ ማሳሰቢያ ሰጠ።

ሁሉንም ያስማማው ነገር ለውይይት መቀመጥና ለመነጋገር መቻል መልካምና ጠቃሚ የፖለቲካ ባህል ጅምር መሆኑ ነበር። ውይይቱ በጥሩ መግባባት ተካሒዶ ተመሳሳይ የውይይት መድረክ እየተፈጠረ በየጊዜው ቢካሔድ የሚደገፍ እንደሆነ ስምምነት ላይ ተደርሶ ስብሰባው አበቃና፣ የሁለታችንም ኃይሎች በየፊናችን ለመሔድ ተለያየን።

የጎንደር ጉዟችንን ቀጥለን ወደ ተከዜ ጫፍ የሚወስደውን አቅጣጫ ይዘን በተከዜ በረሐ አፋፍ ላይ የምትገኝ ሀምባራ የምትባል መንደር ተቃረብን።

***

ወደ መንደሯ ከመግባታችን በፊት የኃይሉ ወታደራዊ መሪ ኃይሌ ቀጭኑ፣ ሽፈራውና ጌትነትን ጠራቸውና፣ ሦስቱ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ተመካከሩ። በምክክራቸው መሠረት በኃይሏ ውስጥ ያሉት ሦስት ጋንታዎች የሚገቡበትን ዕቅድ ነገሩን። አንደኛዋ ጋንታ ከአመራር አባላቱ ፊት ፊት እየቀደመች እንድትሄድ፤ ሁለተኛዋ ጋንታ ከኃይሌ ቀጭኑ ጋር ያሉ የአመራር አባላትን አጅባ ወደ መንደሩ እንድትገባ፤ ሦስተኛዋና እኔ የነበርኩባት ጋንታ ደግሞ መትረየሱን በመያዝ ከመንደሩ በስተጀርባ በሚገኝ አንድ ተራራ ላይ ወጥታ ቦታ እንድትይዝ ታዘዘች።

ቦታችንን እንደያዝን፣ ብረት የያዙ ሰዎች ከቤተክርስቲያን አካባቢ ውር-ውር ሲሉ ከነበርንበት ከፍታ ላይ ሆነን ተመለከትን። “ሽፍቶች ናቸው ወይስ ወያኔዎች ቀድመው መጥተው ነው?” እየተባባልን ስንጠያየቅ ከቆየን በኋላ እውነቱን ተረዳን። በአካባቢው ብዙ ታጣቂዎች ያሉት አንድ የመሬት ከበርቴ መኖሩን፤ በዚያን ሰዓት ደግሞ ሰውየው ያለው ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደነበረና ታጣቂዎቹም እርሱን የሚያጅቡ መሆናቸን የመንደሯ ነዋሪዎች ነገሩን። ከትንሽ ጊዜ በኋላ አሽከሮቹ፣ ማንነታችንን ለማጣራት እኛ ወደነበርንበት ቦታ መጡና ጠየቁን። የኢሕአፓ ሠራዊት እንደሆንን ስንነግራቸው፣ ጉዳት እንደማናደርስ አምነው ተመለሱ። እስከማስታውሰው ድረስ ለምን እንደሆነ ባላውቅም ባላባቶቹ ከእኛ ጋር ውጊያ ገጥመው አያውቁም።

ኃይሌ ቀጭኑና ሌሎች አመራሮች አብራቸው ያለችውን ጋንታ ይዘው ወደ መሬት ከበርቴው ቤት ገብተዋል። ሰውዬው ከቤተክርስቲያን ተጠርቶ ወደቤት እንዲመጣ አስላኩበት። ሲመለስም ለኃይሌ ቀጭኑና አብረውት ለነበሩት ጓዶች ግብዣ አደረገላቸው። የመንደሩ ነዋሪዎች ደግሞ እኛ ወደነበርንበት ቦታ መጥተው “እናንተ የእውነት ተጋዳዮች ከሆናችሁ ይሄንን ሰውዬ ለምን አትይዙትም? ማን እንደሆነ አታውቁም እንዴ? ፊታውራሪ አበራ ጣሰው የሚባለው፣ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበረ የሰለሞን ጣሰው ወንድም ነው!(ሰለሞን





ጣሰው በሰሜን ተራራዎች አካባቢ ብዙ መሬት የነበረው የመሬት ከበርቴ ነው) እርሱ እኮ መንደሩን ያስቸገረ፣ሴቶችን የሚደፍር፣ የድሀ ሀብትና ንብረት በኃይል የሚቀማ፣ የመሬት ከበርቴ ነው! ለምንድነው እርሱንና አሽከሮቹን የማትይዟቸው?” በማለት ጥያቄ አቀረቡ። እኛ የሰውየውን ማንነት ከነዋሪዎቹ ከሰማን በኋላ የግብዣው ነገር ግልጽ አልሆን አለን። ሰዎቹ ያቀረቡትን ጥያቄ በማንሣት ምን ማድረግ እንዲሚገባን የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊያችንን አብደላን ጠየቅኩት።

አብደላም “እኛ በዚህ ጉዳይ ላይ ትእዛዝ ስላልተሰጠን ዝም በሏቸው” አለኝ-በቸልተኛ አስተያየት እየተመለከተኝ።

“እንዴት ዝም በሏቸው ትላለህ? ወይ ሂድና ስለሁኔታው አመራሮችን ጠይቃቸው” አልኩት።

“ለምን ትጨቀጭቀኛለህ?! እኔ ሳልታዘዝ ምንም ማድረግ አልችልም!!” በማለት ቱግ አለብኝ።

“አንተ የፖለቲካ ሐላፊ ሆነህ እንዴት እንደዚህ ትላለህ? በረሐ የወጣኸው ለሕዝብ መብት ለመታገል አይደለም እንዴ? ታዲያ የምንቆመው ከሕዝብ ጋር ነው፣ ወይስ ከወንጀለኛ ጋር ነው? ቢያንስ ለማጣራት እንኳ አንሞክርም እንዴ?” ብዬ ወጥሬ ስይዘው። በመካከላችን ጸብ ሊነሣ ሆነ። ተፋጠጥን፤ የቀረን ነገር መሣሪያችንን ማቀባበል ነበር። መከረራችንን ሲመለከቱ ሌሎቹ መሐል ገብተው አለያዩን። ባይገላግሉን ኖሮ ግን አንድ ከፉ ነገር መፈጠሩ አይቀርም ነበር።

እኔ የገበሬ ልጅ ስለሆንኩ ፍትሕ ማጣት ምን ያህል መጥፎ ነገር እንደሆነ አውቃለሁ። አባቴ የነገረኝንና ያየሁትን አስታወስኩና በዚያን ወቅት ደግሞ ከሕዝብ ጎን መቆም ስላልቻልኩ፣ እልህ ያዘኝ። በረሐ የወጣሁበት ዋና ዓላማም ይሄ ነበር፤ ምንም ማድረግ ስላልቻልኩ በጣም በግኛለሁ። የጋንታዋ መሪ ጌትነት ከእኛ ጋር ስላልነበረ ሐላፊነቱ የኔ ነው። መወሰን የሚችለው ግን የጋንታዋ የፖለቲካ ሐላፊ ስለሆነ የእርሱ ምላሽ ደግሞ የግዴለሽነትና ከዓላማችን የሚያርቀን ሆኖ ስለታያኝ አልተዋጠልኝም።

ከእርሱ እንደተለየሁ የሰውየው አሽከሮች ውጪ ለነበሩ አባላት፣ ምግብ እያዞሩ ነበርና ወደ እኛም ጋንታ ይዘው መጡ። ምናልባት ያመጡት ምግብ ከመንደሩ ነዋሪ በማስገደድ የተሰበሰበ ሊሆን ይችላል ብዬ ስላሰብኩ አሽከሮቹን አመናጭቄ ከአመጡት ምግብ ጋር እንዲመለሱ አደረግኳቸው።

የጋንታዋ አባላት የአብደላ መልስ ስላልተዋጠልን ተቃውሞአችንን ለመግለጽ አኩረፍን፣ የሰውየው አሽከሮች ያመጡልንን ምግብ አንበላም ብለን መመለሳችንን፣ የመንደሩ ነዋሪዎች ሲያውቁ፣ በአቋማችን ተደስተው በገዛ ፈቃዳቸው፣ ከየቤቱ ምግብ አሰባስበው ይዘውልን መጡ። ምግቡን ስንበላ ሁሉ አብደላን በነገር እያበሸቅን ሕዝባዊ ድጋፍና የግፈኞች ድጋፍ እንደዶሮ ወጥና እንደሽሮ የጣዕም ልዩነት አላቸው እንባባል ነበር። እርሱ ግን አንገቱን ቀና ሳያደርግ ዝም ብሎ ነበር የሚበላው። ምናልባትም በሠራው ሥራ ተጸጽቶ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።

ሀምባራን ለቀን ስንወጣ ያለፍነው በአበራ ጣሰው ደጅ ላይ ስለነበር እያንዳንዳችንን እየጨበጠ "ደኅና ሁኑ አይዟችሁ!" እያለ ተሰናበተን።

***





በተከዜው ጉዟችን ላይ የአየር ወለድ አባል የነበረው፣ ሙቶ አለቃ ፍጹም ገና ከዳሞ መንቀሳቀስ ስንጀምር አንሥቶ የጋንታ አመራሮችን ለብቻችን እየሰበሰበ አንዳንድ የወታደራዊ ሥልጠናዎችን ይሰጠን ነበር። ጅዶ፣ ካራቴ ፣ ድምፅ በሌለው መሣሪያ መጠቀም፣ ጠላትን በማፈን ማስቀረት፣ ለተወሰነ ጊዜ ትንፋሽን መሰወር፣ እንዲሁም የሰወርነውን ትንፋሽ መመለስና የመሳሰሉትን አስተማረን። የሙቶ አለቃ ፍጹም፣ ጠንቃቃ፣ ጥሩ የሆነ ወታደራዊ እውቀትና አቋም የነበረው ጓድ ነበር።

ከሀምባራ ተነሥተን ስንጓዝ ውለን አንድ ቦታ አደርንና ተከዜን በጠዋት ለመሻገር በሌሊት መንገድ እንድንጀምር ተደረገ። ምንአልባትም በረሐማ የአየር ሁኔታ በመሆኑ ፀሐይዋ ከማበርታቷ በፊት ቁልቁል ወርደን ዳገቱን ስንወጣ እንዳንደክም ተብሎ ይመስለኛል። ደን የበዛበትን አካባቢ አለፍንና እስኪነጋ ድረስ ተጓዝን። ወደ ተከዜ ወንዝ ስንጠጋ አብደላ ከእኔ በፊት ያልፍ ስለነበር መነጋገር ጀመርን። በአበራ ጣሰው ምክንያት ብዙ ተጨቃጭቀን የነበረበት ሁኔታ ገና ስላልበረደልኝ ሆነ ብዬ እንደገና አነሣሁበት።

"የእኛ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎች ለሕዝብ ነው የምንቆመው እያላችሁ ታስተምራላችሁ። እናንተ ግን ሕዝብ ሲጮህ ዝም ትላላችሁ። ከፊውዳሎች ጋር አብሮ መሆን ምንድነው ስንል ዝም እንድንል ታደርጉናላችሁ። ዓላማችሁን ምን ያህል እንደምታውቁት ያጠራጥራል" እያልኩ የተቋጠረ ብሶቴን አወረድኩበት። እርሱ መናደዱ ቢያስታውቅም ምንም መልስ አልሰጠኝም። መልስ ስላልሰጠኝ ደግሞ የበለጠ ተናደድኩና ሌላ ማናደጃ መንገድ መፈለግ ጀመርኩ። "ሌላ ደግሞ ልንገርህ፤ እናንተ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎች ወያኔ ጠባብ ነው፤ በመደብ ትግልም አያምኑም ትላላችሁ። ትናንትና ግን 'በመደብ ትግል እናምናለን' ሲሉ ሰማናቸው ..." ብዬ ተናግሬ ሳልጨርስ፣ ዝም ብሎ የነበረው አብደላ አንገቱን ቀና አድርጎ መናገር ጀመረ።

"አንት እኮ፣ መጀመሪያም ተሳስተህ ነው ወደ እኛ የገባኸው!" አለኝ፡፡ ያንን የተናገረው የትግራይ ልጅ ስለሆንኩ መሆኑን አውቄዋለሁ።

“እኔ ተሳስቼ አልገባሁም፣ አንተ ነህ የተሳሳትከው” አልኩትና ትንሽ ተጨቃጨቅንና እኔም እርሱም ስሜታዊ እንደሆንን ተለያየን።

ከዘንዶ፣ ከእባብና ከአዞም እንድንጠነቀቅ እየተነገረን ተከዜን ተሻገርን። መጀመሪያ ዋና በደንብ የሚችሉ የተወሰኑ ጓዶች አሰሳ ካደረጉና አካባቢውን ዞረው ካጣሩ በኋላ ነበር ሌሎቻችን የተሻገርነው። ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ጓዶችም ወደ ዳገት ላይ ወጥተው ሽፋን ሲሰጡን በስተጀርባም በኩል እንዲሁ ሌሎች ጓዶች ተመድበው ተጠንቅቀን ነበር ያለፍነው። የተራበ ዘንዶ በመንገዳችን ላይ እንድነበረ የሰማሁት በኋላ ነው። እኔ አላየሁትም። በአካባቢው የነበረ አንድ አዳኝ ዘንዶው ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ በማየቱ ለጓዶች በስተቀኝ በኩል ዘንዶ መኖሩን በመንገሩ “ተጠንቀቁ” የሚለው መልእክት እየተላለፈ እኔ ዘንድ ደረሰ። ከእኔ በፊት የነበረው ታደሰ የሚባል ሐኪም ግን ዘንዶውን አይቶታል። የመጨረሻ መስርእ(የሰልፉ መጨረሻ) ላይ ስለነበርኩኝ እኔ ስደርስ ዘንዶው ቦታውን ለቅቆ ሄዶ ነበር።

ቀኑን ሙሉ ስንሄድ ውለን ወደ ማታ ላይ ጸለምት ወረዳ ውስጥ አጨር ገባን። አጨር እንደገባን ከበጌምድር ጓዶች መጀመሪያ ያገኘነው አባ አያሌው የሚባል የከፍለ ሕዝብ አባል ነበር። አባ አያሌውን በአካባቢው ላይ የሚሠሩ አራት የሚሆኑ ብረት የያዙ ገበሬዎች አስከትሎ አገኘነው። በሁለተኛው ቀን ጡርሰጌ ገባን። መግባታችንን ሲሰሙ የበጌምድር ጋንታዎች በሙሉ ወደ እኛ መጡ። ብዙ ሽፍቶች ይዘው ነበር። ከሽፍቶች የነጠቋቸው ከብቶችም ነበሯቸው። በመሆኑም በሬዎች አረዱልንና ከጎንደር ጓዶች ጋር ስንቀላቀል በትልቅ ድግስና በመዝሙርም ቢታጀበ ሞቅ ያለ መስተንግዶ ነበር። ከዘመርናቸው መዝሙሮች ውስጥ “ኢንተርናሲዮናል፤ የዓለም ሠራተኞች ተባበሩ” የሚለው መዝሙር፣ በትግርኛ፣ በአማርኛና፣ በኦሮምኛ ተዘምሮአል። እያንዳንዱ ሌላ ቋንቋ የሚችል ጓድ በቋንቋው ይዘምራል። በዚያም ምክንያት የቅልቅላችን በዓል የደመቀ ሆነ። በዚያ





ዓይነት ሁኔታ ለሦስት ቀን ከቆየን በኋላ በጉዞ የደከመውን ሰውነታችንን በደንብ አሳርፈን ታደስን።

ከቅልቅሉ ዕረፍት በኋላ መጀመሪያ የተንቀሳቀስነው ወደ ዲማ ገበያ ነበር። ዲማ ገበያ ሄደን ሀገር ያስቸገሩ የተባሉ ሽፍቶችን ያዝንና በቁጥጥራችን ስር አቆይተን ከሦስት ቀናት በኋላ ችሎት (ትሪቢዩናል) ተቋቁሞ በሽፍቶቹ ላይ የዳኝነት ውሳኔ ተላለፈ። ዳኝነቱ ዲማ ላይ እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያት የቆላውን ምድር ከደጋው ጋር የሚያገናኝ ትልቅ ገበያ ስለሆነና ብዙ ሕዝብ ስለሚሰበሰብበት ነበር። እያንዳንዱ ሽፍታ ወደ ገበያው ተወስዶ ግርፋት የተወሰነበት ተገርፎ፣ በይቅርታ የሚታለፈው፣ በሕዝብ ፊት ምሕረት ጠይቆ፣ አብዛኞቹ ተለቀቁ። የተቀሩት ከባድ ወንጀል የፈጸሙ የተባሉትን ደግሞ ከእኛው ጋር አስቀርተን ይዘናቸው ሄድን።

አዲ ሰላም ገባን፤ ከአዲስ ሰላም እንደታለፈ በስተምዕራብ በኩል ገደልና ጫካ ነው። እሱን አልፈን ወደ ግልቤና ሄድን። ግልቤና እንደደረስን ሞት ተፈርዶባቸው የነበሩት ሽፍቶች ፍጻሜ ሆነ።ከግልቤና ቀጥሎ ጉዞአችን ወደ ድልበዛ ነበረ፤ ድልበዛ የበየዳ ሥላሴ ዋና ከተማ ናት። ከግልቤና ተነሥተን በጣም ብርዳማ የሆነ አንድ መንደር አደርን፤ ብርዱን ለመከላከል ሌሊቱን ሙሉ እሳት እያነደድን ነበር ያደርነው። በሌሊት ተነሥተን ለሰባት ሰዓታት ያለማቋረጥ ተጉዘን ራስ ዳሽን ተራራ ፊት ለፊት በስተደቡብ በኩል ያለውን ተራራ ወጥተንና ወርደን አፋፍ ላይ ደረስን።

የራስ ዳሽን ተራራ ጫፉ በጉም የተሸፈነ ነው። ይህ ተራራ በከፍታው ከኢትዮጲያ ትልቁ ተራራ ከአፍሪካ ሦስተኛ ሲሆን ከፍታው ከ4550 ሜትር በላይ ነው። የራስ ዳሽን ሌላው መጠሪያው ራስ ደጀን ይባላል። የሰሜን ተራራ ፓርክ የሚገኘው በዚህ ክልል ውስጥ ነው። በዚህ ፓርክ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ እነ ዋልያ አይቤክስ፣ ገላዳ ባቡንና የሰሜን ቀበሮ የሚገኙበት ቦታ ነው።

የተራራው ሰሜናዊ ክፍል በተከዜ ገባሮች የተሸረሸረ ነው። በስተምዕራብ በኩል ደግሞ ሌላው የ4510ሜትር ከፍታ ያለው የባቱ ተራራ ይገኛል።

አፋፍ ከደረስን በኋላ ከተራራው ቤታች ወርደን ድልበዛ በቀን ደረስን። ወደ ከተማው ስንገባ የፖሊስና የወረዳው ባለሥልጣኖች በከተማው ውስጥ አልነበሩም። መምጣታችንን አስቀድመው ሰምተው ስለነበረ ሸሽተው ሄደዋል። የወረዳ ገዢው ግራዝማች ናደው በዛው እንደወጡ ወደ ኢዲዩ መቀላቀላቸው ይነገራል። ወታደሮቹ ግን የሄዱት ወደ ጃንአሞራ እንደሆነ ሰማን። ከተማው ውስጥ ለሁለት ቀናት ቆይተን የቅስቀሳና የማደራጀት ሥራ ከሠራን በኋላ ወደ ጃንአሞራ በኩል ሄድን። ጃንአሞራም እንዲሁ ለሁለት ቀናት የፖለቲካ ቅስቀሳ አደረግን።

ከሕዝቡ መካከል ሌሊት እየተሰበሰቡ እኛን ለመውጋት የሚማከሩብን መኖራቸውን ስለሰማን በጥንቃቄ ነበር የምንንቀሳቀሰው። እኛ ወሬው ቢደርሰንም እነርሱ አንድ ነገር እስካላነሱ ድረስ በእኛ በኩል ምንም ላለማድረግ ወስነን ሁኔታውን በሰላም አለፍነው።

ጃንአሞራን ወደቀኝ ትተን እስላምጌ፣ የሚባል ቦታ ደረስን። ዕለቱ የገበያ ቀን ነበረ፤ በጠዋት ስንገባ በየቦታው ድንኳን ተተክሎ ለቀስተኞች ያሉበት ለቅሶ ቤቶች ተመለከትን። ምክንያቱን ስንጠይቅ ባለፉት ሁለትና ሦስት ቀናት ውስጥ የደርግ መንግሥት በጎንደር ከተማ ተማሪዎችን ስለረሸነ፣ ልጆቻቸው የሞቱባቸው ቤተሰቦችና ዘመዶቻቸው ሐዘን ተቀምጠው እንደሆነ ነገሩን። ወሬውን ስንሰማ በጣም ነበር ያዘንነው። እስላምጌ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድ ሆነው የሚኖሩበት መንደር ነው።

ከእስላምጌ ከወጣን በኋላ፣ ወደመና ወንዝ ስንወርድ በከብት እርባታ የሚተዳደሩ አርብቶ አደሮች አገኘን። ከእነርሱ ላይ ፍየሎች ተገዙና ታረዱ፤ ዐረፍ ብለን ምሳችንን በመብላት ላይ እያለን፣ ሬዲዮ የያዙ ጓዶች ከቢቢሲ ሬድዮ





ጣቢያ ዜና ያዳምጡ ነበር። አዲስ አበባ ቤተመንግሥት ውስጥ ተኩስ እንደሚሰማና፣ ደርጎች እርስ በራሳቸው እንደተጨራረሱ ሲናገር ሰምተው፣ የሁላችንንም ልብ አቆሙት። የኢትዮያጵያ ሬድዮ ስንከፍት "ከመንግሥት የተሰጠ መግለጫ ስላለን እንደደረሰን በምሽቱ ፕሮግራማችን እናቀርባለን" ይላል። እውነቱን እስከንሰማና መጨረሻውን እስከናውቅ በጣም ጓግተን ቀኑ አልመሽ አለን። የተባለው ሰዓት ደርሶ የኢትዮጵያ ሬድዮ ስንሰማ ተፈሪ በንቲና ሻምበል ሞገስን ጨምሮ ልዩነት የነበራቸው ሦስት የደርግ አባላት በመንግሥቱ ኃይለማርያምና በደጋፊዎቹ እንደተገደሉ ተገለጸ። የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቡድን የደርግን ስልጣን ጠቅልሎ በእጁ አደረገ ማለት ነው እየተባባሉ አንዳንድ ጓዶች በድርጊቱ አደገኛነት ላይ ይወያዩ ነበር።

በማግስቱ ረቡዕ በጃንአሞራ በኩል አድርገን የመናን ወንዝ ተሻግረን ወደ ሐሙሲት ለመሄድ ተነሣን። በጫካ ውስጥ ስናቋርጥ የሚዳቆዎች መንጋ አገኘንና ሁላችንም ለማደን ተሯሯጥን። አንድ ሁለቱን ገድለን ቆዳቸውን ገፈፍንና፣ ስጋቸውን ይዘን፣ ወደሚቀጥለው መድረሻ ቦታችን ሄድን። ነገር ግን የደረስንበት አካባቢ ነዋሪዎች ወግ አጥባቂና ጿሚ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የሚበዙበት መሆኑ ስለተነገረን ስጋውን አሽገን ማሳደርና በነጋታው ጠዋት መብላት ግድ ሆነ።

ረቡዕ ስንጓዝ ውለን ሐሙስ ዕለት ሐሙሲት ደረስን። ከተማዋ ሐሙሲት የተባለችው ሐሙስ ቀን የሚውል ትልቅ ገበያ የሚገኝባት ቦታ ስለሆነች ነው። ሐሙሲት ስንገባም ወረዳ ገዢውም ሆነ ፖሊሶች በከተማው ውስጥ አልነበሩም። ስለዚህ ምንም የሚያሰናክል ኃይል ስላሊጋጠመን ተረጋግተን ሰተት ብለን ገባን። ዕረፍት ስናደርግ በአደን ያገኘነውን ስጋ ጠብሰን ለመብላት በቅርበት ባገኘነው አንዱ ቤት ጎራ ብለን ብረት ምጣድ እንዲያውሱን ጠየቅናቸው። "በአካባቢው ስለማትታወቁ ተጠንቀቁ" የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን ስለነበር ባለፍንባቸው ቦታዎች ሁሉ በምናደርገው ግንኙነት ችግር እንዳይፈጠርብን እንጠነቀቅ ነበር።

እንዲሁም ማኅበረሰቡ በእኛ ላይ ያለው ግምት ስለማይታወቅ ከጥላቻ ጋር የተያያዙ አስተያየቶችም ሊያጋጥሙን እንደሚችሉ እየገመትን ራሳችንን አዘጋጅተን ነበር።

ምጣዱን እንዲያውሱን የጠየቅንበት ቤት ያገኘናቸው ሴት የመደናገር ስሜት ነበረባቸው። "እናንተ እነማን ናችሁ?" ይላሉ ብለንም ገምተን ነበር። ምንም ጥያቄ አላቀረቡም፤ሴትዮዋ እያዘጋጀን የነበረውን ስጋ ተመለከቱና ከበራፋቸው፣ ወደሜዳው ወጥተው "አምጡት እኛ እንጠብስላችኋለን" አሉን።

እኔም "ብረት ምጣዱን ከሰጣችሁን እንደትልቅ ርዳታ ነው የምንቆጥረው፣ ለመጥበሱ ግን እናንተን ማስቸገር አንፈልግም" ብዬ ምጣዱን ብቻ እንዲያመጡልን ጠየቅኳቸው።

"ኧረ በጭራሽ አይሆንም! ትግሉ የሁላችንም አይደለም እንዴ? ይቺን እንኳ እናግዛችሁ እንጂ?" ሲሉን ሁላችንም ተደናግጠን መተያየት ጀመርን።

ከአነጋገራቸው ማን መሆናችንን ብቻ ሳይሆን ዓላማችንን ጭምር በደንብ እንደሚያውቁ ገባን። አነጋገራቸውን ስንሰማ በአንድ በኩል ግራ መጋባት በሌላ በኩል ደግሞ በውስጣችን ትልቅ ደስታና ኩራት እየተሰማን፣"ምንድነው ነገሩ? እንዴት ሊሆን ቻለ?" እየተባባልን መልስ የሌለው ጥያቄ መጠያየቅ ጀመርን።

*"ማን ነገረህ?*

*ወፍ ነገረኝ"*

*"እረኛ ምን አለ..."*

መልሱን ያገኘነው ትንሽ ቆይቶ ከመጣ እረኛ ከሚመስል ወጣት ልጅ ነበር። የልጁ መኖሪያ ምጣድ ከተዋስንበት ቤት ጎረቤት ነበር። የሚኖርበት ቤትም የጓዶች ቤት መሆኑን ነገረን። ከእርሱ ጋር በገበሬ አካባቢ ለቅስቀሳና ለማደራጀት ሥራ ከጎንደር የመጡ ሦስት ጓዶችም አብረው ይኖራሉ። ይህን





ስንሰማ ሙሉ ነጻነት ተሰምቶን ከእነርሱ ጋር ስንጫወወት በማደራችንም ስለአካባቢውና ሌላም ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን ሰጡን።

***

## አርባያ

*'ሥህተት ሥራ፡፡ እንደገናም ተሳሳት፡፡ ግን ያለፈውን ስህተትህን ኢይነት ደግመህ አትሥራ፡፡*
*(የአበው አባባል)*

ከሐሙሲት በኋላ ኃይሏ ለተለያየ ወታደራዊ ተልእኮ በሁለት እንድትከፈል ተደረገና በሁለት አቅጣጫ ተሰማራን። ኃይል ሦስት በሁለት ተከፍላ ከጎንደር ጋንታዎች ጋር በመሆን፣ በአርባያና በእብናት ለተሰጣት ተልዕኮ የተንቀሳቀቸው ጥር 29 ቀን ነበር ።

በኃይል ሦስት ሥር ከነበሩት ሦስት ጋንታዎች ውስጥ ሁለት ጋንታዎችና ከበጌምድር አንድ ጋንታ ወደ እብናት፤ በኃይል ሦስት ስር የነበረ አንድ ጋንታ እና ከጸለምት አንድ ጋንታ ተጨምሮለት ሁለት ጋንታዎች ደግሞ ወደ አርባያ እንድንንቀሳቀስ ተመደብን።

በጌትነትና በእኔ የምትመራው ጋንታ የተመደበችው አርባያ ሲሆን፣ በዳዊትና በኃይለ ማርያም የምትመራ የጎንደር ጋንታ አብራን ነበረች። ለእብናቱ ተልዕኮ በዋና አዛዥነት የተመደበው ግርማይ ነበር። በፍሱሕና በሰቦቃ የሚመሩት ሁለቱ ጋንታዎች ደግሞ እብናት ተመደቡ። ለእብናት ሦስት ጋንታ የተመደበው ከአርባያ የበለጠ ርቀት ስለነበረው ይመስለኛል። ወደ አርባያ የተመደቡት አጠቃላይ ዋና አዛዥ ኃይሌ ቀጭኑ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊ ጌዲዎን ሆኑ። እብናት የተመደቡት አጠቃላይ አዛዥ እስከንድር የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊ ደግሞ ሺፈራው ነበር፡፡

ሌሊቱን ሙሉ ተጉዘን አርባያ ስንደርስ ጨለማው እየገፈፈ መንጋት ጀምሮ ነበር። መንገድ ላይ እያለን ዳዊት የሚመራት ጋንታ ከፊት ቀድማ ትሄዳለች። የእኔ ጋንታ ደግሞ ከኋላ ነበረች። አንድ ወንዝ ስንሻገር ዳዊት ከጋንታው ወጥቶ





ወንዙ አጠገብ ይጠብቀኛል። ከዳዊት ጋር አብሮ አደግ ስለሆንንና በጣም ስለምንቀራረብ እንደሚጠብቀኝ ስመለከት ምን ሆን ብዬ ደንግጬ ነበር። ስደርስ "ምነው ዳዊት ምን ሆንክ?" ብዬ ጠየቅኩት።

"እኔ የዛሬ ተልዕኮ ነገር ምንም ደስ አላለኝም" አለኝ። ለግማሽ ሰዓት እያወራን አብረን ከሄድን በኋላ ወደጋንታው ወደፊት ቀደመና ተለያየን።

ከተማው ከመግባታችን በፊት አንድ ተራራ አለ። ከተራራው ቀጥሎ ሰፊ ሜዳ ይገኛል፤ ተሻግሮ የአርባያ ከተማ ነው። ከተማው ከመድረሳችን በፊት ትንሽ ዕረፍት ወሰድን። በእረፍቱ መካከል አመራሮች ተሰበሰብንና ምን መደረግ እንዳለበት ወሰንን። ምክንያቱም ወደ ከተማው አካባቢ መድረስ የነበረብን ሳይነጋ በሌሊት ነበር። ከተነሣንበት ቦታ ያለውን ርቀት ለመገመት ስላስቸገረን፣ ምቹ ባልሆነ ሰዓት ነበር የደረስነው። ቀን በከተማው አቅራቢያ መዋሉ አደገኛ ስለሚሆን አምሽተን ለመግባት መወሰን የሚሞከር አልነበረም። ባለፍንባቸው ቦታዎች መታየታችን የማይቀር ስለነበረ መምጣችን በከተማው የደርግ ኃይሎች ይሰማልና አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል በሚል ስጋት አደረብን።

"ተልዕኮው ቢሰረዝ ይሻላል" የሚል ሃሳብ ቀረበ። ኃይሌ ቀጭኑና ጌዲዎን ግን አልተስማሙም፤ "አይሰረዝም ቀንም ቢሆን መግባት አለብን" አሉ።

"መምጣታችን በመንግሥት ሰዎች እንዳይሰማ ለማድረግ አንችልም፤ በጣም በመራቃችን ደግሞ ደጀን ስለሌለን የከፋ አደጋ ሊፈጠር ይችላል" የሚል አስተያየት እንደገና ተሰጠ።

"ቀኑን እዚሁ ውለን መረጃ እንዳይሾልክ እስከማታ ድረስ ከሰፈሩ ሰው እንዳይወጣ እናግደዋለን" አሉና ኃይሌና ግዲዎን ውሳኔያቸውን እንደማይቀይሩ ገለጹ።

ከዚያ በኋላ የጋንታ አመራሮች ለብቻችን ተሰብስበን ተነጋገርን። ሁላችንም በአመራሩ ውሳኔ እንደማንስማማ፤ ስሕተቱ የተፈጸመው መጀመሪያ

እነሣሣችን ላይ በመሆኑ በትክክለኛው ሰዓት አለመድረሳችንና መታየታችን መሆኑን ተስማማን። መረጃው ለደርግ ኃይሎች በዚህም በዚያም ብሎ መድረሱ ስለማይቀር ከፍተኛ ችግር መፈጠሩ እንደማይቀርም ተማመንን። ሁላችንም የጋንታ አባላት ጥሩ ስሜት የለንም። ትእዛዝ ስለሆነ እንጂ የማያምኑበት እንደሚበዙ ማሳወቅ፤ እንዲሁም ከደጀን ርቀን በመምጣታችን መዘዙ የከፋ እንደሚሆን ያለንን ስጋት እንደገና በመግለጽ አመራሩን ማሳመን እንደሚኖርብን ተስማማን።

ይህንኑ ሐሳብ በመያዝ ከጎንደርም ሆነ ከአሲምባ የመጡት አብዛኞቹ አባላት በተልዕኮው መቀጠል ላይ ያላቸው እምነት የተሸረሸረ መሆኑንና በውሳኔውም ቅሬታ እያሰሙ ስለሆነ ተልዕኮው ተሰርዞ ብንመለስ ተመራጭ እንደሚሆን ነገርናቸው።

"ይህን ሁሉ ርቀት ተጉዘን እዚህ ከደረስን በኋላማ እንዲሁ አንመለስም" አሉ።

በመካከል አሰፋ ባዩ ተነሣና "እኔ ቄስ መስዬ ከተማ ልሂድና አጣርቼ ልምጣ" ብሎ ሃሳብ አቀረበ። አሰፋ በዕድሜው ገፋ ያለና ጢማም ስለሆነ እንደቄስ ለብሶና ጠምጥሞ ራሱን ለማመሳሰል በቀላሉ እንደሚችል ያውቃል። ሐሳቡ ማንም ሳይጠራጠረው መምጣታችን መሰማት አለመሰማቱን አጣርቶ ለመምጣት ነበር። እኛም ይህ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ተሰምቶን ነበር። ነገር ግን ሁለቱም የእርሱንም ጥያቄ ሳይቀበሉት ቀሩ።

ያን ጊዜ እኔ ተነሣሁና "በዚህ ውሳኔ የወሎውን ስህተት በመድገም ወሎ እንደአስጨረስናቸው ጓዶች እዚህም ጓዶቻችንን እንዳናስጨርሳቸው። ከጥቅሙ ጉዳቱ በልጦ ድርጅቱንም የበለጠ የሚጎዳ እንዳይሆን፤ ያልተመጣጠነ መሥዋእትነትና እልቂት እንዳይፈጥር እንጂ ማናችንም ብንሆን መሥዋዕትነቱን ፈርተን አይደለም። ስለዚህ እንደገና አስባችሁበት ብትወስኑ ይሻላል" አልኩ።





ሌሎችም በእኔ ላይ ተመሳሳይ ሐሳብ ጨመሩና እንደገና እንዲያስቡበት ጠየቅናቸው።

ኃይሌ ቀጭኑና ጌዲዎን ግን በምንም መንገድ ተልዕኮው እንደማይሰረዝ አስረዱ። በመጨረሻም ጌዲዎን "ይህ እርምጃ ለፓርቲያችንም ሆነ ለጎንደር ሠራዊት የወደፊት እንቅስቃሴና ተሰሚነት ትልቅ ጥቅም ስላለው ሊሰረዝ አይችልም። የሚከፈለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ከፍለን ይህን ተልዕኮ ማሳካት አለብን" አለና በእንግሊዝኛ "After all war is politics" (ጦርነት ማለት እኮ ፖለቲካም ማለት ነው) ብሎ ደመደመ። በውሳኔያቸው መጽናታቸውን ነግረውን ምንም ማድረግ ሳንችል ተለያየን።

በትእዛዙ መሠረት ለመፈጸም የአካባቢው ሰው እንዳይወጣ ሙከራ ለማድረግ ተሰማራን። እርብ ቀን ተደብቀን እስኪመሽ ዋልን፤ ሌሊቱንም ጥበቃው ቀጠለና የካቲት 30 ቅዳሜ ሌሊት ቀደም ብለን በተልእኮው መሰረት ወደከተማው ተንቀሳቀስን::

በዕቅዱ መሰረት በዳዊት የምትመራው ጋንታ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንድትገባ፤ ሌሎች ደግሞ ከፖሊስ ጣቢያ በስተግራና በስተቀኝ በኩል ሆነን እንድንገባ ነበር። በመጀመሪያ ወደ ከተማ ስንገባ ሁላችንም አንድ አንድ እንድንተኩስ ተነግሮናል። ምክያቱም ብዙ መሆናችንን አውቆ ከተማው ውስጥ ያለው የደርግ ኃይል እንዲረበሽና እንዲደናገጥ እንደሆነ ተነገረን።

በመጀመሪያ ወደ ከተማው እንደገባን በነበረው የተኩስ ልውውጥ ምትኩ ተመታና ተሠዋ። ወደ ከተማው ከገባን በኋላ እነዳዊት በፖሊስ ጣቢያው አድርገው ወደ ወረዳው አስተዳደር ግቢ ሔዱ። በዳዊት የምትመራው ጋንታ የወረዳው አስተዳዳሪ ያለበት ቤት ለመግባት ያደረገችው ሙከራ ከባድ የመከላከል ተኩስ ስላጋጠማት ችግር ሆነ። ስለዚህ ዳዊትና የተወሰኑ ጓዶች አጥሩን ዘለው ገብተው ሲታኮሱ ዳዊት አድብቶ ወደ አለበት ቤት ተጠጋና የያዘውን የቻይና ስሪት ቦንብ በመስኮት በኩል ወደ ውስጥ ወረወረባቸው፤ ቦንቡ ግን ከሸፈና ሳይፈነዳ

ቀረ። በዚህ ግዜ ዳዊት እየሮጠ ተመልሶ በአጥር ዘሎ ሊወጣ ሲል፣ በሁለት ጥይት ተመታና ወደ ግቢው ውስጥ ወደቀ። ከዳዊት ጋራ ግቢው ውስጥ የነበሩ ጓዶች አጥሩን ዘለው ወጥተው የዳዊትን መመታትና ቆስሎ ግቢው ውስጥ ብቻውን መቅረቱን ነገሩን።

ስለዚህ የሁለቱም ቡድን ጓዶች በሙሉ አንድ ላይ ተሰብሰብን ጥሰን ለመግባት ወሰንንና ሁላችንም እየተኮስን ወደ ውስጥ ሆ! ብለን ከገባን በኋላ ዳዊትን ይዘነው ወጣን።

ከዚያም ሁለት ቁስለኞችንና፣ የምትኩን አስከሬን ይዘን ከከተማው በመውጣት ላይ እያለን ከየቦታው የሚመጣ የተኩስ ድምፅ መሰማት ጀመረ። ተኩሱ ከከተማው ውስጥ ብቻ ሳይሆን በከተማው ዳርቻዎች ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጣ ነበረ። ከከተማው ስንወጣ ተመልሰን እንድንሰባሰብ የተነጋገርንበት ቦታ ስንደርስ ተኩስ በከፈቱብን የአካባቢ ታጣቂ ገበሬዎች ተይዞ አገኘነው። ቦታውን ለማፈግፈጊያ ለመጠቀም እንደማንችል ስንገነዘብ በሁለተኛ አማራጭነት ወደተቀመጠው ሁለተኛ የመሰባሰቢያ ቦታ ለመሄድ ወሰንን።

በጌትነት የምትመራው አንደኛዋ ጋንታ አንድም ጓድ ሳይሠዋባቸው ግዴታቸውን ፈጽመው አልፈዋል። ከጌትነት ጋር ወደፊት የቀደሙት ከኋላ በኩል የነበሩት እንዲያልፉ ሽፋን በመስጠት የጠላትን ኃይል በዘዴ አልፈው በስተቀኝ ያለውን ጋራ ይዘው ለተወሰኑ ሰዓቶች መሽገው ተታኩሱና ቀስ በቀስ እያፈገፈጉ ቦታውን ለቀው ለመውጣት ቻሉ።

እኔ ከነበርኩባት በኃይሌ ቀጭኑ ከምትመራው ጋንታ ውስጥ ቀድመው ወደ ማፈግፈጊያው ቦታ ሲሔዱ፣ ያልጠበቁት የገበሬ ታጣቂዎች ተኩስ የገጠማቸው እነኃይለ ማርያም የተቀነባበረ መከላከል አድርገው ጥሰው በማለፍ ሲወጡ ሁለት ጓዶች ተሠውባቸው።





እኛ ከእነዳዊት ኋላ ሆነን፣ በአንድ መርሰዲስ የፖሊስ የጭነት መኪና ተከልሎ ያለፈ እስረኞችን የሚጠብቅ አንድ ፖሊስ አግኝተን ከእርሱ ጋር ስንታኮስ አጠገቤ የነበረው ዓለማየሁ ሊቁ እግሩን ተመታና ቆሰለ። እኛ ፖሊሱን ማርከን ዓለማየሁን ይዘን በመመለስ ላይ እያለን ነበር ትእዛዙን የሰማነው። በጣም ደነገጥን። ተእዛዙም አባላት የቆሰሉትንና የተሰዉትን ጓዶች በነበሩበት ትተው እንዲያፈገፍጉ የሚገልጽ ነበር። ዓለማየሁ ሊቁ አጠገቤ ነበር የተመታው፤ የጋንታ መሪ የነበረው ዳዊት ወዲቀሽ ደግሞ በጣም የምወደው አብሮ አድጌ ነው። እነዚያ ሁለት ጓዶች አደጋ ላይ ወድቀው ባሉበት ኃይሌ ቀጭኑ የቆሰሉ ጓዶችን ትቶ የመሸሽ ትእዛዝ ሲያመጣ ተናደድኩ።

በትእዛዙ ሁላችንም ግራ ተጋብተን ነበር። "እንዴት ቁስለኞችን ትታችሁ ውጡ እንባለለን?" ብለን ሁላችንም እርስ በእርስ መነጋገር ጀመርን። ትእዛዙን ተቀብለው ቁስለኞችንና የተሰው ጓዶችን ጥለው የተመለሱ ጓዶች ደግሞ ስሜታቸው ተነክቶ የሚያደርጉት ጠፍቷቸዋል እየጮሁ በእልህ ያለቅሳሉ። ጀማል ደከሟል፤ በትእዛዙ መሠረት ግን አብረውት የነበሩት ጥለውት ሔደው ነበርና እኔ ከኋላ ስደርስ መሄድ አቅቶት አገኘሁት። ደጋግፌ እንዲራመድ ለማድረግ ሞከርኩ፤ ጫማው እግሩ ላይ ሊረጋ አልቻለም። ጫማውንና እግሩን በኩሽክ አስሬ አነሳሁትና ሽንጣውንም ተሸክሜ ላተርፈው ቻልኩ።

ድልድል የሚባል ጓድ ደግሞ በሁለት ጥይት ተመትቶ ደሙ የፈሰሰውን ጓድ ያደቴን ይዞ ለመውጣት ይታገላል። ያደቴ "እየደረሱ ስለሆነ አንተን እንዳይዙህ እኔን እዚሁ ተወኝና ሂድ፤ እኔ ደክሜአለሁና አልተርፍም። ስለዚህ አንተ ከእኔ ጋር መሞት የለብህም ሂድ " እያለ ይለምነዋል። ድልድል ግን "አብረን እናመልጣለን፣ አለያም አብረን እንሠዋለን እንጂ፣ ጥዬህ አልሄድም" ብሎ እምቢ አለው። በመጨረሻ የገበሬዎቹ ታጣቂዎች ደረሱባቸውና ሁለቱም እየተታኮሱ አብረው ተሠው።

እኔ ከጀማል ጋር ከኋላ መቅረቴን ያዩ ጓዶች፣ "አማኑኤል ጀማልን ይዞ ለመምጣት ወደኋላ ቀርቷል እንዴት ጥለናቸው እንሔዳለን?" ብለው ትዕዛዙን ጥሰው ሲጠብቁኝ ደረስኩና ተገናኘን። እኔ ስደርስ ኃይሌ ቀጭኑ በጣም ተረብሾ ካርባይኑን በደንብ መያዝ አቅቶት ነበር። "በጣም ስለተረበሸና ራሱን መቆጣጠር እየተቸገረ ስለሆነ፣ በግድ ካላስቆምነውና ካላረጋጋነው ሁላችንንም ሊያስጨርሰን ነውና ምን እናድርግ?" ተባብለን ከጓዶች ጋር ተነጋገርን። ኃይሌን ለማስፈራራት ኃይለ ቃል ተናገርኩትና ጠመንጃ ደገንኩበት። እርሱም ዝም አለ።

ከውጊያው ከወጣን በኋላ ሦስቱም ጋንታዎች ለየብቻቸው ነበሩ። እኛ ቀኑን ሙሉ ስንጓዝ ውለን ወደ ማታ አካባቢ ዕረፍት አደረግን። ለመልስ መሰባሰቢያ በመጀመሪያ የተመረጠው ቦታ ሳይሆን ቀርቶ ስላለፍነው ወደ ሁለተኛው አማራጭ መሰባሰቢያ ወደ ማክሰኘት ነበር የምንሄደው። ማክሰኘት ስንደርስ ግን ከእኛ ጋር የነበሩትን ሳይሆን ከእብናት የተመለሱትን ጓዶች አገኘናቸው።

ወደ እብናት የተላኩት ጓዶች ተልእኳቸውን አሳክተው ሲመለሱ፣ እነ የመቶ አለቃ ፍጹም አንዲት የዜና ማዳመጫ ሬድዮ ረስተው መምጣታቸውን አስታወሱ። የመቶ አለቃ ፍጹም፣ ተካልኝ፣ ግደይና ሙስጠፋ ሬዲዮኗን ለማምጣት ተመልሰው ሄደው በዚያው ቀሩባቸው። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ወታደራዊ መሪው ግርማይ እና እንግዳ የቅስቀሳ ንግግር ለማድረግ ሕዝቡን ሰብስበው እንደቆሙ፣ ሌሎቹ ጓዶች ራቅ ብለው መሄዳቸውን በመመልከታቸው ከሕዝቡ መካከል የተወሰኑ ገበሬዎች ግርማይንና እንግዳን ለመያዝ እንቅስቃሴ አደረጉ ። እንግዳ እንቅስቃሴውን በመረዳቱ ሲያመልጥ ግርማይን ያዙት። እንግዳ ለግርማይ ሽፋን አልሰጠውም ወይም ለሌሎች ጓዶች ጥሪ ለማድረግም አልተኮሰም። ሌሎቹ ጓዶች የሚያውቁት ነገር ቢኖር ግርማይና እንግዳ የፖለቲካ ትምህርት እየሰጡ እንደሚከተሉ ብቻ ነበር። የግርማይንና የእንግዳን አደጋ ላይ መውደቅ





ከሰሙ በኋላ እነመቶ አለቃ ፍጹምም ስለቀሩባቸው፣ ሁሉም ነገር በደኅና ተጠናቀቀ ከተባለ በኋላ ስድስት ጓዶቻቸውን ጥለው ወደማክሰኝት መጡና ከእኛ ጋር ተገናኙ።

ከሐሙሲትና፣ ከማክሰኝት ጓዶችን አግኝተን የሦስተኛው መሰባሰቢያ ወደተባለው አርባ ጩጓር ሄድን። አርባ ጩ ጓር ስንደርስ ከወዲያም ከወዲህም እየመጡ ብዙ ጓዶች ለመሰባሰብ ቻሉ። በለሳ አካባቢ ገጠር ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ጓዶችም መጥተው ነበርና ተሰባስበን ወደ ጸለምት ጉዞ ቀጠልን። በጥበበ ይሚመሩ ጥቂት ካድሬዎች ግን በለሳ ቀርተዋል።

በአገው ምድር በኩል ወደ ጸለምት ለመሄድ ድልበዛ ስር ሲደረስ ሁለት አማራጮች አሉ። አንደኛው በተከዜ በኩል በረሐውን ማቋረጥ ነው፤ ይህ መንገድ ረዥም በመሆኑ አንድ ሳምንት ይወስዳል። ምግብ ለማግኘትም አስቸጋሪ ነው። ሁለተኛው አማራጭ በድልበዛ በኩል መሄድ ነበር፤ ከአገው ምድር ድልበዛ በሁለት ሰዓት መግባት ይቻላል። ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ግልቤና በአንድ ሌሊት ይደረሳል። ግልቤና ከተገባ ደግሞ ጸለምት ማለት ነው፤ በሁለትና በሦስት ቀን መግባት ይቻላል። በጣም አቋራጭ መንገድ ነው። አመራሩ ግን የተከዜን አቅጣጫ መረጠ። "ለምን አስቸጋሪውና ረዥሙ መንገድ ተመረጠ? አቋራጩ ይሻላል" በሚል ጭቅጭቅ ተነሣ።

አመራሩ ግን "ፊታውራሪ ናደው ወደ ኢዲዩ ገብተው ስለሸፈቱ ከእርሳቸው ኃይል ጋር ሌላ አላስፈላጊ ግጭት ውስጥ ልንገባ እንችላለን። እርሱ ያለው ኃይልም ምን ያህል እንደሆነ ስለማናውቅ ፖሊሶችም አብረው ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ በተከዜ መንገድ መሄድ ይሻላል" አለ።

ቀደም ሲል በገባንበት ውጊያ ውስጥ አመራሩ ብዙዎቻችንን ስላላስደሰተን፣ ሞራላችን ተነክቶ ነበር። ስለዚህም ብዙዎቻችን ውሳኔያቸውን ለመቀበል ስላልፈለግን ማጉረምረም ተጀመረ።

"የእናንተን ሐሳብ አልተቀበልነውም። ባለፈውም ቢሆን ራሳችንን አዳንን እንጂ በእናንተ አመራር ያገኘነው ነገር ስላልነበረ አሁንም የሚመጣውን ችግር እራሳችን እንዳመጣጡ እንወጣዋለን" በማለት እምቢ ብለን ተነሜነጭን።

ቆየት ብሎ በድምፅ ብልጫ ይወሰን የሚል ሐሳብ መጣ ። ያን ጊዜ ንትረኩ በጋንታ አመራሮችና በኃይል አመራሮች መካከል ሆነ። ውይይቱን የሚመራው የኃይል ሦስቱ የፖለቲካ ሐላፊ ሺፈራው ነበር። "ውሳኔያችንን በድምፅ ብልጫ ማሳለፍ ትክክል አይሆንም። በእኛ ላይ ቅሬታ እንዳላችሁ አውቀናል። ወቀሳውንም ይሁን ሌላም ችግር ወደ ጦር ሰፈራችን ከተመለስን በኋላ እንፈታዋለን" በማለት እያለሳለሰን መጣ።

በድምፅ ብልጫ ከተባለ የጋንታ አመራሮች ድምፅ ነው የሚበልጠው። ነገር ግን በሠራዊቱ ደንብ አመራሩ ያለውን ተቀብለን ቅሬታችንን በኋላ ነው ማቅረብ ያለብን። እኛም ይህን አጥተነው ሳይሆን ጭቅጭቅ የፈጠርነው በብስጭት እልህ ውስጥ ገብተን ነበር። በመጨረሻ ሺፈራው ስሜታችን ገብቶት ከአግባባንና ካበረደን በኋላ የድምፅ ብልጫው ቀርቶ የአመራሩን ውሳኔ በመቀበል በመረጡት መንገድ ተጉዘን፣ በጸለምት ወረዳ የሚገኝ ፍየል ውኃ የሚባል መንደር ደረስን። ፍየል ውኃ ላይ ሁለት ቀናት የወሰደ ስብሰባ ተደረገ። በኃይል አመራሩ ላይ የተነሣው የኃይሌ ቀጭኑ እና የእንግዳ ድክመት ነበር። "ለግርማይ መያዝ ተጠያቂው ማነው?" በሚል እንግዳ ላይ ወቀሳ ተሰነዘረ። እንግዳ ለቀረበበት ክስ መልስ ሲሰጥ እልህ ይዞት ያለቅስ ነበር።

ውይይቱ ሲጀመር ቃለ ጉባኤ እንዲያዝልን ጠይቀን ስለነበር፣ የተነሡት ወቀሳዎችና ሐሳቦች በሙሉ ተመዝግበው ስብሰባውን ጨርሰን ጸለምት ገባን። ጸለምት ከገባን በኋላ ነበር ወደ እብናት ከሄዱት ጓዶች መካከል መጨረሻ ላይ የቀሩትን የስድስቱን ጓዶቻችንን ጉድ የሰማነው።

***





ሬዲዮ ለማምጣት የሄዱት የእብናት ጓዶች አራት ሆነው ሬድዮዎ ይዘው የሙቶ አለቃ ፍጹም የተማረከውን መኪና እየነዳ ሲመለሱ፣ መኪናዋን መንገድ ላይ ጭቃ ይዘባቸው ለማውጣት ሲሞክሩ ቀኑ እየመሸ ሄደ።

በእነግርማይ ላይ ስለተፈጠረው ችግር ሳያውቁ፣ በጭቃ የተያዘችውን መኪና ለማውጣት በመታገል ላይ እያሉ ግርማይን ይዘው የሚመለሱት ገበሬዎች ያገኟቸዋል። ገበሬዎቹ ማንነታቸውንና ጥቂት መሆናቸውን ሲያዩ እነሱንም ለመያዝ እንቅስቃሴ በማድረግ ተኩስ ከፈቱባቸው። እነፍጹም፣ ከለላ ይዘው መታኮስ ከጀመሩ በኋላ ፍጹም ተመትቶ ቆሰለ። ሙስጠፋ፣ ግደይና ተካልኝ ጥቃቱ እየበረታባቸው ሲመጣ እየተታኮሱ ማፈግፈግ ጀመሩ። ገበሬዎቹም እየተከታተሉ በተኩስ አጣደፏቸው። ሙስጠፋ መሳሪያ ሳይዝ ባዶ እጁን ስለነበረ ተኩሱ ሲባባስ በገበሬዎቹ እጅ ወደቀ። ወዲያውኑ እንደያዙት ተረባርበው ከደበደቡት በኋላ ራሱን ስቶ ሲወድቅ ሞቷል ወይም አይተርፍም ብለው በወደቀበት ጥለውት ሄዱ።

የቀሩት ግደይና ተካልኝ ብቻ ነበሩ። ግደይና ተካልኝ እየተታኮሱ በማፈግፈግ በአቅራቢያቸው ወዳገኙት ቤተ ክርስቲያን ገብተው ቤተ መቅደስ ውስጥ ገቡ። በሀገሩ ባህል ቤተ መቅደስ ውስጥ ገብቶ መተኮስ ነውርና ኃጢአት ነው። ስለዚህ ገበሬዎቹ በቤተ ክርስቲያን ላይ ላለመተኮስ ከበው ለማደር ወሰኑ። ምክንያቱም የሚበሉትና የሚጠጡት አጥተው ሲደክሙ እራሳቸው እጃቸውን እንደሚሰጡ በማመናቸው ነበር።

ውድቅት ላይ ሁለቱም ድምፅ ሳያሰሙ በቤተ ክርስቲያኑ አጥር ሾልከው ለማምለጥ ቻሉ። ካመለጡ በኋላ አብረው ተጉዘው ጸለምት ገቡ። ገበሬዎቹ ሙስጠፋ ሞቷል ብለው ጥለውት ከሄዱ በኋላ ራሱን እንደሳተ ቆየ። አጋጣሚ ሆነና በገበሬዎች መካከል የሚሠራ የኢሕአፓ ካድሬ ከወደቀበት ቦታ

እንሥቶ ወደ ቤቱ ወሰደው። በገበሬው ውስጥ የፖለቲካ ሥራ ከሚሠሩት ካድሬዎች ጋር ግንኙነት አይኑር እንጅ ስለሠራዊቱ በሥፍራው መገኘት ያውቁ ስለነበር ነው ሙስጠፋን ወደቤቱ ሊወስደው የቻለው። በጓዶቹ እጅ ሆኖ ለአንድ ወር ያህል ሕክምናና እንክብካቤ ሲደርግለት ቆይቶ ሙስጠፋ ሊያገግም በመቻሉ ጸለምት ተመልሶ ታሪክ ለመናገር በቃ።

መቶ አለቃ ፍጹም ግን አልቀናውም፤ እስከመጨረሻው ድረስ ተፋልሞ ሕይወቱን ሊያተርፍ አልቻለም። ቢሆንም ብዙ ጉዳት ካደረሰ በኋላ ነበር ከፉኛ ቆስሎ አቅም ያጣው። እንደማይተርፍ ሲያውቅ በመጨረሻው ሰዓት ላይ የያዘውን መሣሪያ እንዳይጠቀሙበት ፈታቶ፣ ቃታውን ሁሉ አወላልቆ ከወረወረ በኋላ ወድቆ ተዘረረ።

ገበሬዎቹ ብቻውን ያን ያህል ተከላክሎ ስለተዋጋቸውና ጉዳት ስላደረሰባቸው ከተሰማቸው ጥላቻ ይልቅ ጀግንነቱ አስደነቃቸው። ስለዚህ "ጀግና" ብለው አስከሬኑን በክብር ተሸከመው በቅርባቸው ወደሚገኘውና ሁለቱ ጓዶች ወደተሸሸጉበት ቤተ ክርስቲያን ወስደው ቀበሩት። የመቶ አለቃ ፍጹምን አስከሬን ገበሬዎቹ አጅበው ሲቀብሩት ሁለቱ ጓዶቹ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደተሸሸጉ የቀብር ሥርዓቱን ተመለከቱ። በዚያ ተልእኮ የተሰዉት ጓዶች አጠቃላይ ቁጥር አሰር ነበር።

ወደ ጸለምት ከተመለስን ከጥቂት ቀናት በኋላ እኛን ለመተካት የመጣችው ኃይል አምስት ገብታለች ሲባል ሰማን። ምናልባት አመራሮቹ ተገናኝተው ይሆናል እንጂ እኛ አላየናቸውም። ኃይል አምስት ግን እንደ ኃይል ሦስት ወደ አሲምባ የመመለስ ዕድል ሳታገኝ እስከመጨረሻው ጎንደር ቀረች።





ጸለምት በገባን በማግስቱ ኃይል ሦስት የበጌምድር ተልዕኮዋን ጨረሰችና ወደ አሲምባ ለመመለስ ተንቀሳቀስን።

***

## ወታደራዊ ፍርድ ቤት (ትሪቢዩናል)

ትሪቢዩናል የሠራዊቱ ከፍተኛው የጦር ፈርድ ቤት ነው። ኃይል ሦስት ወደ አሲምባ ከተመለሰች በኋላ በአርባያ ተልእኮ ላይ ስለ ነበሩ ችግሮች እንድናስረዳ የኃይል ሦስት አባላት ዳሮ በሚባል ቦታ ለሦስት ቀናት ተሰብሰብን። ስብሰባውን የሚመራው ጂግሳ ነበር። ከጂግሳ በተጨማሪ ዘርኡ ከህሸንም ሙሉ ስብሰባውን በታዛቢነት ተከታትሏል። ነገር ግን እስከመጨረሻው ድረስ ምንም ቃል ሳይናገር በዝምታ ነበር የሚመለከተው።

ስብሰባው በተጠናቀቀ በማግስቱ የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይን የመታሰቢያ ቀብር ሥነ ሥርዓት ለማስፈጸም ዝግጅት እየተደረገ ነበር። እኔና ሌሎች አሥራ አምስት አባላት ተመረጥንና ለግማሽ ሰዓት ያህል ስለወታደራዊ ሥርዓተ ቀብር ሥልጠና ተሰጠን። በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ብዙ ሕዝብ የተገኘ ሲሆን፣ በወታደራዊ ሥነ ሥርዓት የታጀበ ቀብር ተካሄደ። እንዲሁም ከአካባቢው የመጡ ሰዎች ሐዘናቸውን በለቅሶ ይገልፁ ነበር:: ከሠራዊቱ አባላት መካከልም ብዙዎቻችን እያለቀስን ነበር ሥነ ሥርአቱን የፈጸምነው።

በማግስቱ በአርባያ ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንደሚሰጥ ጂግሳ ነገረን። ለሦስት ቀናት በተደረገው ስብሰባ ላይ እኔን በሚመለከት ምንም ዓይነት ሂስ አልቀረበም ስሜም ስላልተነሣ የሚመለከተኝ ጉዳይ እንደሌለ ተማምኜ ነበር የስብሰባውን ውጤት የምጠባበቀው። ስለ ፍየል ውኃ ስብሰባ ሂስ ቢኖር እንኳ የሚያስመሰግንና አዎንታዊ አስተያየት እንጂ ሌላ ነገር እንደሌለ ተማምኛለሁ። ምክንያቱም አርባያ የተማረከውን የፖሊስ አባል እኔና ሱሌማን ነበርን የማረክነው። ጀማልንም ቢሆን ከወደቀበት አንሥቼ ሕይወቱ እንዲተርፍ ያደረግሁት እኔ ነበርኩና እነዚያን ውጤቶች አስቤ ነበረ የተማመንኩት።

ከምሳ ሠዓት በኋላ ወደ አመሻሹ ላይ ጂግሳ በአርባያ ተልእኮ ላይ ውሳኔ እንደተሰጠ ነገረን። በውሳኔው መሠረት ኃይል መሪው ኃይሌ ቀጭኑ፣ የፖለቲካ





ጉዳይ ኃላፊው ሽፈራውና ምክትል ጋንታ መሪ አማኑኤል፣ በሐላፊነት እንደምንጠየቅ ተናገረ። በጆሮዬ የሰማሁትን ማመን አቃተኝ። የሰማሁት ውሳኔ እርግጠኛ መሆኑን አእምሮዬ ሲቀበል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ምናልባት በስሕተት ስለሚሆን በኋላ የሚያስተካክሉት ይሆናል ብዬ ራሴን አጽናናሁ:: በመጨረሻ ግን ክሱ የምር ሆነና እየከረረ ሄደ።

ያን ዕለት ማታ የምክትል ጋንታ መሪ ተቆጣጣሪነት ተራ የእኔ ስለነበረ፣ ተግባሬን ለመወጣት ስነሣ ሐላፊነቴን ከአየር ወለዶች ጋር ለመጣው ለጓድ መሰሉ እንዳስረክብ ተነገረኝና ሰጠሁ፤ የምክትል ሐላፊነቱን ቦታ እርሱ ተረከበ። በሁለተኛው ቀን ደግሞ ወደ ሰበያ ስንሄድ መንገድ ላይ ጌትነትና ሌሎች ሁለት ጓዶች አብረውኝ ነበሩ። "አማኑኤል ወደፊት" ተብየ ተጠራሁና ብረት እንዳወርድ ተነገረኝ። ኤም ፎርቲን ጠመንጃዬን አሰረከቤ ወደ ፍሱሕ ገብራይ ጋንታ እንድዘዋወር ተደረገ። ፍሱሕ ገብራይ "አይዞህ ምንም አትሆንም መረበሽ የለብህም ፤ጭንቀትም እንዳይሰማህ" እያለ ሊያጽናናኝ ሞከረ። ለሁለት ሳምንታት ከእነ ፍሱሕ ገብራይ ጋንታ ጋር ቆየሁ። አንድ ቀን የቅስቀሳ ሥራ ሠርተን ስንመለስ እንደገና ተጠራሁና ወደ ሰንገዴ መውረድ እንደሚኖርብኝ ተነገረኝ።

በዚህ ጉዳይ አጣሪ ኮሚቴ እንደተቋቋመ ሰምተናል። የአጣሪ ኮሚቴ አባላት አሰፋ ባዩ፣ መኩሪያና ከበደ አሊ እንደሆኑም ተወርቷል። መኩሪያ ደግሞ እኔን አይዞህ ብሎኝ ነበር። አጣሪው ኮሚቴ መጀመሪያ ስራውን ሲጀምር ለምን አማኑኤልን አስገባችሁት ብሎ ጠይቋል። ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሩ ደግሞ "እኛ አንድ ጊዜ ወታደራዊ ፍርድ ቤት (ትሪቡናል) አቋቁመናል፣ ሌላውን የሚወስኑት የተሰየሙት ዳኞች ናቸው፤ እናንተ የሚጠበቅባችሁ የተሰጣችሁን ዝርዝር አጣርታችሁ ማቅረብ ነው። አመራሩ ደግሞ የወሰነውን ለትሪቢዩናል ያቀርባል። እኛ ትሪቢዩናሉን አቋቁመን ለማንቀሳቀስ የማንችል ከሆነ ለምን በአመራር ሐላፊነት ላይ ተቀመጥን?" በማለት ተከራከሩ። ስለዚህ ሦስታችንም ለትሪቢዩናል ወደ ሰንገዴ ወረድን።

ሰንገዴ ሆነን የእኔና የሽፈራው ሥራ ተአሊም ላይ ለነበሩ አባላት የኩሽክ አዘገጃጀት ማሳየት ነበር። ከዚያም በተጨማሪ አንዳንድ ማወቅ ያለባቸው ነገሮች እናወያያቸዋለን፡፡ ኃይሌ ቀጭኑ ከእኛ ጋር ብዙ አይቀላቀልም በአብዛኛው የሚቀመጠው ለብቻው ነበር።

ለዳኝነት የተመረጡት በገለብ ዳፍላ የሚመሩ የትሪቡናል አባላት አምስት ነበሩ። ገለብ ዳፍላ አመራሩን ወክሎ በበላይነት የተመደበ ሲሆን እኔን ያነጋገረኝ ደበሳይ ነበር። መጀመሪያ ሦስታችንም ተከሳሾች ወደ ትሪቢዩናሉ ስንቀርብ ዳኞቹ "መከሰስ የሚገባቸውን ትታችሁ፣ መከሰስ የማይገባቸውን ጓዶች አስገብታችኋል" በማለት ክሱን አንቀበልም ብለው ነበር። "መከሰስ የማይገባው ማነው?" አለ አመራሩ፡፡ "አማኑኤል መግባት የለበትም፣ ነገር ግን ጓድ አርነት መጠየቅ ነበረበት ምክንያቱም አርነት የከፍተኛ አመራሩ ወኪል ሆኖ ነበር ከኃይል ሦስት ጋር የሄደው" የሚል መልስ ሰጠ አጣሪ ኮሚቴው።

በእኔ ላይ የቀረቡብኝ ክሶች ሁለት ናቸው። አንደኛ በብሔር ጥያቄ ላይ ያለው አቋሙ አጠራጣሪ ነው የሚል ሲሆን። ሁለተኛው ደግሞ ችግሮቹ በተፈጠሩበት ወቅት ከሥነ ሥርዓት የወጣ ጠባይ ወይም የአናርኪዝም ባሕርይ አሳይቷል የሚል ነበር።

የሥርዓት አልበኝነት ጠባይ አሳይቷል የተባለበት ምክንያት በአርባያው ጦርነት ላይ ለኃይሌ ቀጭኑ ያሳየሁትን የንዴት መንፈስና መሳሪያ ማቀባበል ነበር። የጠባብ ብሔረተኛነትና አጠራጣሪ አቋም የተባለው ደግሞ ከጋንታዬ የፖለቲካ ሐላፊ ከአብደላ ጋር ከወያኔ ኃይል ጋር (በተንቤን አውራጃ) የተደረገውን ውይይት አንስቼ በተናገርኩት መሆኑ ነበር።

አብረን ትሪቢዩናል ከቀረብነው ሁለቱ ሺፈራውና ኃይሌ ቀጭኑ የተመሠረተባቸው ክስ፣ ሺፈራው ላይ ሁለት፣ ኃይሌ ቀጭኑ ላይ ደግሞ ሶስት ክሶች ነበሩ። ትሪቢዩናል ለመቅረብ ስንሄድ ኃይሌ ቀጭኑ "እንድታውቅልኝ የምፈልገው





ነገር፣አርባያ ላይ በተነጋገርነው ነገር እኔ አልከሰስኩህም፤ ኃይሌ ቀጭኑ ከሰሰኝ ብለህ እንዳታስብ" አለኝ።

ሽፈራውም የተጠየቀው፣ የኃይሏ የፖለቲካ ሐላፊ ሆኖ እያለ ያልተፈቀደ ውጊያ በመፍቀድና፣በዚያም ውስጥ በመካፈል የሚል ነበር። እንዲሁም ኃይሌ ቀጭኑ የኃይሏ ወታደራዊ አዛዥ ሆኖ ያልተፈቀደ ውጊያ በማካሔድ፣ በመሳተፍና ከጦር ሜዳ በመሸሽ የሚሉ ሦስት ክሶች ተጠየቀ። ክሶቹን ከሰማን በኋላ ጠበቃ ያስፈልገን እንደሆን ተጠየቅን። ሺፈራውና ኃይሌ ቀጭኑ ጠበቃ እንደማያስፈልጋቸው ሲናገሩ፣ ለእኔ ግን ጠበቃ እንደሚመደብልኝ ተገለጸልኝ።

በዚያው ሰሞን፣ ደበሳይ መጣና፣ "ካሳሁን (ኢያሱ ዓለማየሁ) ሊያነጋግርህ ወደ ሰንገዴ ስለመጣ ሕክምና ወደሚሰጥበት ጣቢያ እንሄዳለን" አለኝ ። ኢያሱ ዓለማየሁ በ1961 ዓ.ም ከእነርባ ጋር የኢትዮጵያ አየር መንገድን አውሮፕላን ከባሕር ዳር ከጠለፉት ሰባት ተማሪዎች አንዱ ሲሆን የኢሕአፓ መሥራችና የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነው።

ደበሳይ "እኛም ነግረነዋል፣ አንተም ሁሉንም ነገር ሳትደብቅ ንገረው" አለኝና በተጨማሪ አንድ ማስጠንቀቂያም ሰጠኝ። "ገለብ የኃይሌ ቀጭኑ አጎት መሆኑን ታውቃለህ? ስለዚህ ገለብ ፊት ስለ ኃይሌ ቀጭኑ በምትናገርበት ጊዜ መጠንቀቅ አለብህ፤ኃይሌ ቀጭኑ እንዴት ተደናገጠ እንደነበረ፣ ምን ተእዛዝ እንደሰጠ...፣ ስትናገር ካልተጠነቀቅክ ገለብ ሊናደድብህ ይችላልና ተጠንቀቅ" አለኝ።

ወደማታ ላይ ሕክምና ጣቢያ አብረን ሄደን ኢያሱን አገኘሁት። እርሱም ስለ ታሪኬ ጠየቀኝና፣ እንዴት ወደበረሐ እንደወጣሁ፣ ስለ ወሎ ዘመቻ፣ ጎንደር ለሕክምና ሄጄ እንዴት እንደተመለስኩ፣ የበጌምድርን ሁኔታና ከኃይሌ ቀጭኑ ጋር የነበረን አለመግባባት ከምን እንደመጣ፣ ሁሉንም ምንም ነገር ሳልደብቅ ነገርኩት። በዚህን ጊዜ ገለብ ከእኛ ጋር ነበረ፣ ደበሳይ የነገረኝን ማስጠንቀቂያ ይገርለሁ። እርሱን ግምት ውስጥ አስገብቼ ሁሉንም ዝርዝር አድርጌ ለኢያሱ አብራራሁለት። ኢያሱም ካዳመጠኝ በኋላ"አይዞህ ሁኔታውን ሁሉ ሰምቼዋለሁ፣ አጥንቼዋለሁም፣ እንደገና

በደንብ እናየዋለን፣ ስለዚህ ምንም እንዳትረበሽ፣ የመጨነቅና የመከዳት መንፈስ እንዳያድርብህ፣ አይዞህ ምንም አትሆንም" ብሎ አበረታታኝና ተለያየን።

በማግስቱ እኔና ሽፈራው ሁልጊዜ የምንቀመጥባት ቦታ ላይ ሆነን፣ ደበሳይ እና ደሳለኝን አገኘኋቸው። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "አሁን ጥሩ ጠበቃ እያፈላለግንልህ ነውና አታስብ" አሉኝ።

በተከታዩ ቀን ከሽፈራው ጋር በምናድርበት ቦታ ተቀምጠን እያለን ቀይ፣ አጠር፣ ወፈር ያለች አንዲት ሴት ከደበሳይና ከደሳለኝ ጋር አየሁ። እነርሱ በሥልጣና ሐላፊነት ቦታ ላይ ያሉ ስለሆኑ፣ እሷም ከሁኔታዋ የሆነ ሐላፊነት እንዳላት ታስታውቃለች። ምናልባት የፖለቲካ ሐላፊ ሳትሆን አትቀርም ብዬ አሰብኩ። ማን እንደሆነች ግን አላወቅኩም፣ ያየኋትም ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ምናልባት በቅርቡ ከከተማ የመጣች የፓርቲ አባል ትሆን ይሆናል።

በሁለተኛው ቀን እንደተለመደው ከሽፈራው ጋር ሆነን ያች ሴት ወደእኛ መጣችና "አንዴ ለብቻህ ላነጋግርህ እፈልግሀለሁ" ብላኝ አብረን ሄድን። ቦታ መርጠን ከተቀመጥን በኋላ ሰላማዊት እንደምትባል ነግራኝ ራሷን ስታስተዋውቃኝ፣ እኔም ራሴን አስተዋወቅኳት። ለምን እንደፈለገችኝ ስላላወቅሁ ተረብሻለሁ።

መረበሼ ከገጽታዬ ላይ ሳይታይ አይቀርም፤ ወዲያውኑ ወደ ዋናው ጉዳይ ገባች። "የፈለግኩህ ትሪቢዩናል በቀረብክበት ጉዳይ ላይ ላናግርህ ነው" ብላ ጀመረችና ፈገግ አለች። ፈገግታዋ ደስ የሚልና የማረጋጋት ኃይል ያለው ነበር። ገና ዋናውን ጉዳይ ሳታነሣ በፈገግታዋ ብቻ ለጥሩ ነገር እንደመጣች የነገረችኝ ይመስል ያደረብኝን የጥርጣሬ መንፈስ አባረረችልኝ። "ትሪቢዩናል በቀረብክበት ጉዳይ ላይ ለአንተ ጠበቃ እንድሆንና እንድረዳህ ተጠይቄ እሺ ብያለሁ፤ ስለዚህ ነው ወደአንተ የመጣሁት። በዚህ ከተስማማህ፣ ከአሁን በኋላ ወደ ትሪቢዩናል የምትቀርበው ከእኔ ጋር ወይም በእኔ በኩል ይሆናል። ከሚመለከታቸው አካላት





ጋር ሁሉ አንተን ወክዬ የማነጋግርልህ እኔ እሆናለሁ" ብላ መስማማቴን በመጠየቅ ዓይነት ተመለከተችኝ።

እኔም ከመጀመሪያው ጠበቃ እንደሚቆምልኝ ተነግሮኝ ስለነበረ ይህንኑ ገለጽኩላት። መስማማቴን ካረጋገጠች በኋላ ከክሱ ጋር ስለተያያዙና ስለሌሎችም ስለተካፈልኩባቸው እንቅስቃሴዎች ምንም ሳልደብቅ እውነቱን ዘርዝሬ እንድነግራት ጠየቀችኝ። በጥያቄዋ መሠረት ሁሉንም ነገር በዝርዝር ስነግራት በማስታወሻ ላይ እየጻፈች በጽሞና አዳመጠችኝ።

እዚህ ችግር ውስጥ ከገባሁ በኋላ ሁሉንም ነገር የማማክረው፣ የማምነውና አጠገቤም ያለው ሺፈራው ስለነበረ፣ ያጋጠመኝን አዲስ ነገር ለእርሱ ነገርኩት። ሽፈራው ምን ማድረግ እንዳለብኝ በመጠቆም፣ አይዞህ በማለትና ሞራሌ ዝቅ ሲልም በማጽናናት የረዳኝ ብቸኛ አማካሪዬ በመሆን በዚያ የችግር ጊዜ ትልቅ ውለታ ጥሎብኛል። ከሰላማዊት ጋር ስለተነጋገርነው ነገር ሳማክረውም ሁሉንም ነገር ገልጬ ማስረዳቴን ደግፎ የረሳሁት ካለም እያስታወስኩ ጨምሬ እንድነግራት አጠንክሮ መከረኝ።

ሰላማዊት ጠበቃዬ ከሆነች በኋላ በየቀኑ እንገናኝ ጀመር። ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ለእኔ ጉዳይ ስትንቀሳቀስ ብቻ ሳይሆን፣ ለራሷም ጉዳይ አንዳንድ ቦታ ስትሄድ አብሬያት እንድሄድ እየጠየቀችኝ ቅርርባችን በጣም እየተጠናከረ ሄደ።

አንዳንዴ ዝርዝር ነገር ሳወራ ረዥም ሰዓት ብቆይም እንኳ ምንም ሳታቋርጠኝ በትዕግሥት የማዳመጥ ችሎታዋ እስከዛሬም ያስገርመኛል። ልክ እኔ ንግግሬን ከጨረስኩ በኋላ ፈገግ ትልና ከዚያ መናገር ትቀጥላለች። ይህ ጠባይዋ ከእርሷ ጋር በማወራበት ጊዜ ስናገር እንዳላመነታና በራሴ እንድተማመን አድርጎኛል፡፡ ምንም ሳላስብ ያየሁትንና የሰማሁትን ነገር ሁሉ እንድናገርና ነጻነት እንዲሰማኝም ረድቶኛል። ስለ ወሎ ሳወራት ዘመዴ ከሆነው ከዘላለም ጋር ከልጅነት ጀምሮ እንደሚተዋወቁ ነገረችኝ። ወሎ ተይዞ በመንግሥት እጅ በመውደቁ

የተሰማትን ሐዘን ገለጸችልኝ። እኔ ለዘላለም ዘመዴ መሆኑን አልነገርኳትም፣ በራሷ መንገድ ከሌላ ቦታ ነበረ መረጃውን ያገኘችው።

በትሪቢዩናሉ ፊት ቆማ፣ በእኔ ክስ ላይ አሳማኝ ነጥቦች አንስታ ስትከራከር፣ የመናገር ችሎታዋን፣ የፖለቲካ ልምዷንና በራስ መተማመኗን ተመልክቼ አደነቅኳት። ደበሳይና ደሳለኝ "ጠበቃ የሚሆንልህ አስተማማኝ ሰው እያፈላለግን ነው" ያሉኝ እውነታቸውን እንደሆነ ተረዳሁ። ያቆሙልኝ ጠበቃ እውነትም ያለምንም ጥርጥር ጎበዝና አስተማማኝ ነበረች። በደንብ ተዘጋጅታ ነበር የቀረበችው።

በመጨረሻዎቹ ቀናት ሰላማዊት ትሪቢዩናሉ ላይ የቀረበችው ብቻዋን ነበር። ስለዚህ ምን ምን የመከራከሪያ ነጥቦችን እንዳቀረበች ነገረችኝ። "በብሔር ጥያቄ ላይ ያለው አቋሙ አጠራጣሪ ነው" ስለሚለው ክስ ያቀረበችውን ስትነግረኝ አቋሙ አጠራጣሪ ነው የተባለው፣ እውነት ያለመሆኑን የሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች ማቅረብ እንደሚቻል እንደገለጸችላቸውና ዋና ዋናዎቹን ጭብጦች እንዳስረዳች ነገረችኝ። አጠራጣሪ አቋም ቢኖረኝ ኖሮ፣ በቀደምትነት ሠራዊቱን ከተቀላቀልኩበት ዕለት ጀምሮ ድርጅቱን ጥለው የሄዱ የተለያዩ አባላት አብሬያቸው እንድጠፋ ጠይቀውኝ የሁሉንም ጥያቄ እንዳልተቀበልኩ በአመራሩ ጭምር የሚታወቅ መሆኑ በድርጅቱ ላይ የነበረኝ ጠንካራ እምነት የሚያረጋግጥ እንደሆነ አስረድታለች። አጠራጣሪ አቋምና የጠባብ ብሔረተኝነት ስሜት ቢኖረኝ ኖሮ፣ ለሕክምና ብቻዬን ጎንደር ስላክ በዚያው ለመቅረት ወይም ከብሔረተኛ ድርጅቶች ጋር ለመቀላቀል የሚከለክለኝ ነገር እንዳልነበረ ግን እንዳላደረግኩት ምክንያቱም ድርጅቴን ስለምወድና በዓላማዬ የጸናሁ ለመሆኔ አንድ ማረጋገጫ እንደሆነ ጠቁማለች። ከዚያ በተጨማሪም ከወሎ በተመለስኩበት ጊዜም ለመቅረት ወይም ለመክዳት ምንም የሚያግደኝ ነገር እንዳልነበረም ገልጻለች።





ከዚያ ድካምና መሥዋዕትነት ከበዛበት አጠያያቂ ተልእኮ በኋላ እንኳ በእምነቴ እንደጸናሁና ወደ ሌላ ለመሄድ ሳላመነታ ብቻዬን ብዙ ችግር አልፌ የተመለስኩ በመሆኔ፣ በትግሉና በድርጅቱ ላይ ምን ያህል እምነት እንዳለኝ፣ ምናልባትም እምነቱ ከብዙዎቻቸው የሚበልጥ ቢሆን እንጂ እንደማያንስ የሚያመለክት መሆኑንም ተናግራለች። ከዚያም ሌሎች ትንንሽ ዝርዝር ያቀረበቻቸውን መከራከሪያዎች ጨምራ በደንብ አስረግጣ እንዳስረዳቻቸው ነገረችኝና ስሜቴን ለማወቅ ትመለከተኝ ጀመር። ያቀረበችው ማስረጃ ትክክለኛ ስሜቴን ስለገለጸው በጣም ደስ እንዳለኝ ነገርኳት።

"ሌላ ደግሞ ሳልነግርህ የዘለልኩት አንድ ነጥብ አለ። የጠባብ ብሔረተኛ አመለካከት አለህ የተባለው ትክክል አይደለም። የእውነት ቢኖርህ እንኳ ሊጠየቅ የሚገባው የራሱን ዓላማ በትክክል ለማስረዳትና ለማሳመን ያልቻለው ራሱ ፓርቲው እንጂ፣ የአንተ ችግር ሆኖ ሊታይ እንደማይገባና ይሄ ክስ አንተን በምንም መንገድ ሊያስጠይቅህ እንደማይችል ገልጬላቸዋለሁ" ብላ ነገረችኝና ወደሁለተኛው ክስ መልስ አለፈች።

ሁለተኛው ክስ፣ ከሥነ ሥርአት የወጣ ጠባይ ወይም የአናርኪስት ባሕርይ አሳይቷል፣ የሚለው ሲሆን ስለሰጠችው መልስም "ይህንን ባሕርይ ያሳየኸው፣ የሠራዊቱን ደንብ ባለማወቅ ወይም በንቀት እንዳልሆነ፤ ቦታው ላይ በተፈጠረ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመሥርተህ የሠራዊቱን ክብር በሚጠብቅና የትግል ጓዶችህን ከአላስፈላጊ መሥዋዕትነት ለመከላከል በመፈለግ እንደሆነ መረዳት እንዳለባቸው ነው የነገርኳቸው" አለችና ቀጠለች። "ሌላው ሠራዊት ለበለጠ አደጋ በማይጋለጥበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑን አምኖ፣ ባዶ ሜዳ ላይ ለጠላት ተጋልጠው የነበሩ ጓዶችን ሌሎች ጥለዋቸው ሊሄዱ ሲሉ ለራሱ ሕይወት ሳይሳሳ የጓዶችን ሕይወት ማትረፉ ሊያስሾመው እንጂ ሊያስከስሰው አይገባም ብያለሁ። በውጊያው ላይ በሌሎች ሕይወት ላይ ያልተጠበቀ አደጋ ሊያደርስ ይችል የነበረውን የፖሊስ አባል ከሌላ ጓደኛው ጋር ሆኖ መማረኩንም አትርሱ፣ የታየበት

ስሜታዊነት ደግሞ ለሠራዊቱና ለጓዶቹ ካለው ፍቅር የመነጨ እንጂ በአመጻኝነትና ሥርዓት ካለማክበር አልነበረም። እንደሚታወቀውም ከእንደዚያ ዓይነት ጠባይ ጋር የሚያያዝ ተግባር ታይቶበት ስለማይታወቅ የአናርኪስት ባሕርይ አሳይቷል ሊያሰኝ አይችልም ብያቸዋለሁ። ስሜታዊነት ቢታይ እንኳ በጊዜው የነበረው አመራር በተሳሳተ አካሄድና ከዚያ በፊት ከሚታወቀው የአመራር ልምድ ጋር የማይጣጣም ስለነበረ ነው። በዚህ በኩል ደግሞ አመራሮቹ እንደተከሰሱበት ልብ እንዲሉ ጠቁሜያለሁ፣ የሚሳሳላቸው ጓዶቹን ለማዳን በመፈለግ የተፈጠረን ስሜት አናርኪዝም ነው ብሎ መፈረጅ ስሕተት መሆኑን በተገቢው መንገድ አስረድቻቸዋለሁ" በማለት ነገረችኝ።

ንግግሯን በጽሞና እያዳመጥኳት ሳለሁ ጉዳዬን የቱን ያህል የራሷ ጉዳይ እንዳደረገችው እያሰብኩ በራስ የመተማመን መንፈሴ ከፍ ሲል ተሰማኝ። አዲስ ነገር ካላመጡ በስተቀር ነጻ እንደምወጣ ትልቅ ተስፋ አደረብኝ። ሰላማዊትም ስሜቴን ለመረዳት ለሁለተኛ ጊዜ አተኩራ ፊቴን አየችኝና " እንዴት ነው? ምን ይመስልሃል?" ብላ ጠየቀችኝ።

"በጣም ነው ደስ ያለኝ። ከገመትኩት በላይ ጥሩ አድርገሽ ነው ያስረዳሻቸው። ጠበቃ እንዲቆምልኝ መጠየቄ ትክክል ነበረ፤ ጉዳዩን ራሴ ባስረዳ ይህን ያህል ልገልጸው እንደማልችል ርግጠኛ ነኝ። በጣም አመሰግናለሁ!" አልኳት።

"አይዞህ፣ ነጻ እንደምትወጣ እርግጠኛ ነኝ። ምንም የሚያሰጋ ነገር ስለሌለ እንዳትጨነቅ" በማለት አበረታትታኝ ተሰናብታኝ ሄደች።

ሰላማዊት ሰው የመቅረብ ችሎታዋ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደብኝም። የማዳመጥ ችሎታዋ፣ ታጋሽነቷ፣ ትኩረቷ፣ ጓዳዊ ፍቅሯና የአክብሮት አስተያየቷ ተጨማምረው ማንም እንዲያደንቃት የምታስገድድ ሴት ነበረች። ስትናገር የድምጽዋ ልስላሴ፤ ውስጥ ድረስ ሰርስረው የማየት ኃይል ያላቸው ዓይኖቿ፤ ምክንያታዊ ገለጻዋ መስጠኝ "ምን ያህል የበሰለች ብትሆን ነው?"





እያልኩ ሁሌ እንዳስብ ያደርገኝ ነበር። ይሄን ሁሉ የምገምተው ስለእርሷ ከሌላ ሰው የሰማሁት መረጃ ሳይኖር፤ ከተዋወቅን ጀምሮ በጥቂት ቀናት ቆይታችን ካየሁት እውነት ብቻ ተነስቼ ነው፡፡ የጸሎተ ባለቤት እንደሆነች ያወቅኩት እንኳ ቆይቼ ነበር፡፡

እየተቀራረብን ሄደን የበለጠ ስንግባባ ብቻዋን ስትሆን ወይም ብቻዋን የምትሄድበት ቦታ ሲኖራት አብሬያት እንድሆንና አብሬያት እንድሄድ ትጠራኝ ጀመር። ከክሱ ጋር በተያያዘም ሆነ በሌላ ጉዳይ በየአጋጣሚው የማወራት ታሪክ ደስ እንደሚላት ትነግረኛለች። ብቻ አብረን የምንውልበት ጊዜ ከቀን ወደቀን እየጨመረ ሄደ።

አንድ ቀን የት እንደምንሄድ ሳትነግረኝ "አንድ ቦታ ደርሰን እንመለስ?" አለችኝ። ተስማማሁ። ትንሽ ራቅ ብለን ከሄድን በኋላ የያዘችው አቅጣጫ ወደ እስር ቤት የሚወስድ መንገድ መሆኑን አወቅሁ። እስር ቤቱ የሚገኝበት መንገድና አካባቢው ከሌላው በተለየ ሁኔታ የሚብስ ገደል፣ በረሐና ጫካ መሆኑን ስለማውቅ በቀላሉ ገባኝ። እና አካባቢውን ስመለከት ፍርሃት ቢጤ ሽው አለብኝ፡፡ "ወዴት ነው የምንሄደው?" አልኳትና ቆምኩ። ሳቅ አለች። ወዲያው ደግሞ ረጋ ብላ በዚያ በለስላሳ ድምፃ* "በአስቸኳይ እስር ቤት ሄጄ ማነጋገር ያለብኝ አንድ ሰው አለ፣ እርሱ ጋ ነው የምንሄደው" አለችና "ምነው ግን?" ስትል ጠየቀችኝ።

"እስር ቤት?" አልኩና ቀለል አድርጌ ጠየቅኋት፣ በውስጤ ግን በጣም ከብዶኛል።

" አዎን ምነው?!" አለች፣ አሁንም ፈገግ እንዳለች ነበር።

በዚያን ጊዜ፣ ሁለታችንም መሣሪያ አልታጠቅንም፤ ያንን አስቤ አንድ ነገር ለማድረግ ወሰኜ ተዘጋጀሁ፣ ለእርሷ ግን ምንም አልነገርኳትም። በውስጤ ጥርጣሬ ስለገባኝና ስለፈራሁ ችግር ውስጥ ከመግባቴ በፊት አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ። በድንገት ቀጥ ብዬ ቆምኩ። እርሷ አሁንም እየሳቀች ቆማ፣ መልሴን ለመስማት ትጠብቃለች።

"ወዴት ነው የምትወስጂኝ?" አልኳት ቢድጋሚ፣ አሁን ግን የጠየቅኳት ኮሰተር ብዬና የቀኝ እጄን መዳፍ አገጬ ላይ አድርጌ በመገረም አስተያየት እያየኋት ነበር። የእውነት ግራ እንደተጋባሁ አወቀች። ፈገግታዋ ከፊቷ ላይ ቀስ ብሎ እየደበዘዘ ሲከስም ታየኝ። ሆኖም ስሜቴን የቀያየረውን ነገር ለመገመት የቻለች አትመስልም። ግራ ተጋብታለች፤ የተከሠተውን ነገር ለማጣራት አካባቢዋን ዞር ዞር ብላ ተመለከተች። ከእርሷና ከእኔ በስተቀር ማንም አልነበረምና የበለጠ የተደናገረች መሰለኝ። ግምባሯን እንደመቋጠር እየከጀላት ትክ ብላ እያየችኝ ያልተፈታ እንቆቅልሽ የሆነባትን ነገር ለመስማት ትጠብቃለች።

እየቆየ ሳላስበው ድንጋጤዬ ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ፤ ከመናገሬ በፊት በተጠንቀቅ ተዘጋጀሁና፣አልህ እየተናነቀኝ "ሰላማዊት ተዴው፣ አወቅኩብሽ! እኔን ለመርዳት ከእኔ ጋር የቆምሽ ረዳቴና ጠበቃዬ ነሽ ብዬ አምኜሽ ነበር። አሁን ግን ቢቃሽኝ! ምን ለማድረግ እንዳሰብሽ አውቄአለሁ። ጭራሽ እስር ቤት ወስደሽ ልትጥይኝ ነው?! ሞኝሽን ፈልጊ!" አልኩና ፊቴን በቅርበት ወደሚታየው ወደ ደንከል በረሀ አዙሬ ቆምኩ። "ስሚ! እኔም አንቺም መሣሪያ አልያዝንም፣ ስለዚህ በኃይል ልታስገድጂኝ አትችይም። ይህ የምታይው በረሐ ሁሉ መውጪያ መግቢያውን በደንብ የማውቀው ሀገር ነው። በዚህ በደንከል በኩል ጠፍቼ ኤርትራ እገባለሁ እንጂ፣ ማንም እጄን ይዞ እስር ቤት ሊከተኝ አይችልም!! ደግሞም፣ አንቺ አይደለሽም፣ ማንም ሰው ቢከተለኝ ሊደርስብኝ አይችልም!!" አልኳትና ለመሮጥ አኮበኮብኩ።

ስሜቴ በደንብ ገብቷታል፤ ንግግሬን እስከጨርስ ጠበቀችኝና መልስ ሳትሰጠኝ በቆመችበት በሳቅ መንከትከት ጀመረች። እኔ ደግሞ በተራዬ በሁኔታዋ ግራ ተጋብቼ ፈዝዤ ሳቋን እስከትጨርስ ጠበቅኋት። ከዚያ ደግሞ መልሳ ኮስተር አለችና "አይ አማኑኤል፣ እኔ አንተን እስር ቤት ልወስድ? እንዴት እንደዚህ ታስበኛለህ? ያሰብከው በፍጹም የሌለና የማይሆን ነገር ነው። እመነኝ! እውነቴን





ነው የምልህ እመነኝ! የመጣሁት ለሌላ ሳይሆን፣ እስር ቤት የማነጋግረው ሰው በመኖሩ ብቻ ነው። ምንም አንቆይም፣ ወዲያውኑ ነው የምንመለሰው" አለችኝ።

ንግግሯን ስትጨርስ ግንባሯ ላይ የነበረው መኮሳተር እየተነነ ገጽታዋን ቅን ፈገግታ ሸፈነው።አንዳች ኃይል የተናገረችውን ሁሉ እንዳምን የሚያስገድድ ስሜት ሲረጭብኝ ተሰማኝ። ውስጤ በአንድ ግዜ ከጥርጣሬ ወደ ማመን ተቀየረና ምንም ሳላመነታ "እሺ" ብየ ተከትያት መሄድ ጀመርኩ። እንደገና ጨዋታ ጀመርንና ስለፖለቲከኞችና ስለአለመተማመን ትንሽ አወራችኝ። ወዲያውኑ ደግሞ ርእሱን ለውጣ፣ ስለከተማና የገጠር ትግል ልዩነት አንዳንድ ነገር ጠቃቀሰችልኝና ወደሌላ ርእስ ገባን። እኔ አብዛኛው ታሪኬን ከትሪቢዩናል ጉዳይ ጋር በተያያዘ አውርቻታለሁ። አንዳንድ ያልነገርኳትንና የሚገርሙኝን ነገሮች ሳነሣ ደስ ብሏት ትሰማኛለች። አንዳንዴ ደግሞ የማወራው ያልቀበኝና የሆነ ያልሆነውን እነግራታለሁ፤ እርሷ ግን ጆሮዎቿን አቁማ በጥንቃቄና በጉጉት ታዳምጠኛለች። እንዲያውም አንዳንዱ ወሬዬ አሰልቺና ተደጋጋሚ እንዳይሆንባት የምነግራት እያመነታሁ ነበር። እርሷ ግን ጊዜ ሳትሰጠኝ የጀመርኩትን እንድቀጥል ወይም አዲስ ታሪክ እንድጀምር ከነገርኳት ታሪክ አንድ ጉዳይ በጥያቄ ትመዝና ታጣድፈኛለች። ይህ ድርጊቷ ደግሞ የማዳመጥ ችሎታዋንና ለሰው ያላትን አክብሮት እንድረዳ አደረገኝ።

በተለይ ስለወሎ ሳወራት በጣም ደስ ብሏት እንደምትሰማኝ አውቄባታለሁ። አንዳንዴ እኔ የማወራው ነገር እንዳለቀብኝና እሷም ደግሞ ከተማ ስላሳለፈችው አንዳንድ ነገር እንድትነግረኝ ስጠይቃት፣ ግድ ይሆንባትና ጥቂት ነገር ጣል አድርጋ እንደገና ተራውን ወደእኔ መልሳ ታዞረዋለች። ብዙ እንደምታውቅና ብዙ ከፉና ደግ የትግል አጋጣሚዎችን ያሳለፈች መሆኗ ይታወቀኛል። በመጀመሪያ ከዓይኖቿ ላይ የሚነበብ አንድ ነገር አለ። አንዳንዴ ከሰው ጋር መሆኗን ረስታ በሐሳብ ጭልጥ ስትል የምታስበው ነገር ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ እገምታለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ በአብዛኛው ከከተማ በተለይ ከአዲስ አበባ

የሚመጡ አንዳንድ ጓዶች ለአደጋ ተጋልጠው መንቀሳቀስ ሲያቅታቸው ምን ያህል አስቸጋሪ በሆነ ፈተና ውስጥ እንዳለፉ፤ እርሷ ደግሞ ከእነዚህ አንዷ ስለሆነች፤ ያላሳለፈችው ሕይወት መስማት ጠቃሚዬ ነበረ። አሲምባ ከመጣች በኋላም ቢሆን በሐላፊነት የተመደበችው ከተማ እያለች ከነበራት የድርጅቱ ሐላፊነት ጋር በሚመጥን ደረጃ ላይ ነበር። በኋላ ካገኘሁት መረጃ ደግሞ የጸሎተ ባለቤት መሆኗን ማወቁ ለግምቴ ማረጋገጫ ሆኖኛል፤ ምክንያቱም ጸሎተ ከጥቂት ነባር የፓርቲው የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት አንዱ ነበርና ነው። ከእነዚህ እውነቶች በመነሣት ሰላማዊት በትግሉ ውስጥ የነበራት ቦታ ከፍተኛ መሆኑ ተሰምቶኛል።

ብዙ ጊዜ ስለራሷ እንድትነግረኝ እንተጉታታለሁ:: አንዳንዴ ሳትወድ በግድ እንደምንም ብዬ "እሺ" አሰኛታለሁ። እሷ ግን ከእኔ ፍላጎት ጋር የሚመጥን ወሬ ነግራኝ አታውቅም። የእርሷ ወሬ በአብዛኛው በአጠቃላይ ነገር ላይ የሚያተኩር ነበረ። ለምሳሌ ስለመንግሥቱ ኃይለማርያም ከማውራት ስለደርግ አንሥታ አጠቃላይ ስለሆነ ከፍ ያለ ጉዳይ ማየት ትመርጣለች። ስለ ከተማ ሕይወቷ፤ ከጓዶቿ ጋር ስላጋጠማቸው ነገር ስጠይቃት፤ ስለ አጠቃላይ ድርጅታዊ ሥራ ወይም ሰፋ ያለውን የከተማ ወጣቶች ጽናት፣ ብርታት መሥዋዕትነትና የእስር ሰቆቃ ነበር የምታወራልኝ። እኔ ደግሞ እንዲህ ዓይነት ነገር አያጠግበኝም። ይህ ሁኔታ ደግሞ አብዛኞቹ ከከተማ የሚመጡ ጓዶች የሚጋሩት ጠባይ ነው፤ ስለራሳቸው ለማውራት ከሚገባው በላይ የሚቆጠቡ ድብቆች ናቸው።

ወደ እስር ቤት በሄድንበት በዚያን ዕለት ግን ርእሱ እንዴት እንደተጀመረ ባላስታውሰውም አንድ ነገር ነገረችኝ። ምናልባት ንዝንዜ አስልችቷት፣ እንዲሁም "ወዴት ልትወስጂኝ ነው?" ብዬ ስለተጠራጠርኳት እንደምታምነኝ ነግራኝ፣ እንዳምናት ልታደርገኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ወይም በእኔ ላይ ያላትን የእምነት መጠን ለመግለጽ፣ ይሁን በሌላ ምክንያት አሰባበትና ወሰና እንደነገረችኝ ነበር የተሰማኝ። ነገሩ ሲጀመር፣ ስለከተማ ድርጅታዊ የምስጢር ሥራ፣ በደርግ እጅ





ስለወደቁ ጓዶች፣ በተለይ ደግሞ ሴት ጓዲቶች፣ በእስር ስለተሰቃዩ፣ ስለተገደሉ ጓደኞቿ ወኔና ስለአሳለፉት የምርመራ ስቃይ፣ እንዲሁም በዚህ ሁሉ ስላለመበገራቸው አጫወተችኝ።

አብረን ያወራንባቸው ብዙ ዕድሎች አሳልፈናል:: ያች ዕለት ግን የተለየ ስሜት ያየሁባት ልዩ ቀን ሆናብኝ ነበር። ያቺ ቀን ለእርሷ ያለኝ ግምት ምን ያህል ትክክል እንደነበረ ያረጋገጥኩባት ቀን ሆነች። ሰላማዊት የአመለካከት ብስለት ያላት፣ ቁምነገረኛ፣ ነገሮችን ቀለል አድርጋ የምታይ፣ የሰው ሐሳብ የሚገባት ብቻ ሳትሆን ለወሳኝ ጊዜ ትግል እሳት ውስጥ ለመግባትና ለመሠዋት ዝግጁ የሆነች ታጋይ እንደነበረች ተረዳሁ።

በአብዛኛው የእርሷን ጥንካሬ የሚያመለክት ነገር ፈጽሞ መናገር እንደማትፈልግ እውቄባታለሁ። የግድ ሆኖ ስታወራ እንኳ ከባዱን ነገር አቅልላ ተራ ነገር መስሎ እንዲታለፍ ነው የምትሞክረው። ስለሌሎች ስታወራ ደግሞ አድናቆቷና ፍቅሯ ከፊቷ ላይ ይነበባል። በተለይ አንዳንዴ ስለተሠው ጓዶቿ ስታነሣ ተናግራ አይወጣላትም፤ በየደቂቃው በእልህ ትተነፍሳለች። ታዲያ ያን ቀን በከተማ ስለሚደረገው ወታደራዊ እንቅስቃሴና በከተማ ታጣቂ ቡድን ውስጥ ሆነው ስለተሰዉ ሴቶች አወራችኝ። በሐሳብ ጭልጥ ብላ ትታኝ የሄደች መስሎኝ ከሄደችበት የሃሳብ መንገድ እንዴት እንደምመልሳት በማሰብ ላይ እያለሁ፤ "ታውቃለህ?" ብላ ጀመረችና መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ለመግደል የተመደበው ቡድን አባል እንደነበረች ጠቅም አድርጋኝ ወሬዋን ቀጠለች። በመጨረሻው ሙከራ ላይ አብረው ከነበሩት ጓዶቿ ጋር የነበረባቸውን የውጥረት ስሜትና ዓላማቸውን የማሳካት ጉጉት አስታውሳ ጠቅለል አድርጋ ነገረችኝ። ከአንዱ ቡድን ጋር በአንድ ቮልስ ዋገን መኪና ውስጥ እንደነበረች፤ ከእርሷ ጋር የነበሩትን ጓዶች ቆራጥነት፣ ወኔና ትዕግሥት፣ ስትነግረኝ የአንድ ልብ አንጠልጣይ ልብ ወለድ መጽሐፍ ትረካ የምሰማ ነበር የመሰለኝ። መኪና ውስጥ ሆነው ሲጠብቁ የነበራቸው ጥንቃቄ፣ ካሁን አሁን ምን ይፈጠር ይሆን? እያሉ በውጥረትና በሰቀቀን

መካከል ያቀባበሉትን መሣሪያ እንዴት አንቀው እንደያዙ፣ ከዚያ በፊት በተደጋጋሚ ወጥተው እንዳልተሳካላቸውና እንደቀደሙት ሙከራዎች ያለስኬት የመመለስ ስጋት የቱን ያህል እያሰቃያቸው እንደቆዩ ተረከችልኝ። የመንግሥቱ ኃይለ ማርያምን እንቅስቃሴ የጠበቁበት የመጨረሻ ሙከራ እንዴት እንደተፈጸመ፤ ተልእኮውን ከጨረሱ በኋላ በመንግሥቱ መሞት እርግጠኞች ሆነው እንደተበታተኑና በተአምር መትረፉን ሲሰሙ እንዴት እንደተናደዱ ነገረችኝ።

በደንብ ባላስታውስም አብረዋት ከነበሩት ጓዶቿ ብዙዎቹ ተሠውተዋል። በትውስታዋ እንደተመሰጠች ንግግሯም እየቀጠለ ሲሄድ በእልህ ቁና፣ ቁና መተንፈስ ጀመረች። ለእነርሱ ስለነበራት ጓዳዊ ፍቅር ስታወራ ውስጧን እያንገበገባት ፊቷ ሲለዋወጥ ሲቃ እየተናነቀ አላናግር አላት። ቢቸግራት ወሬውን አቋርጣ ራሷን ለመቆጣጠር መታገል ጀመረች። ያን ልብ አንጠልጣይ ታሪክ እያጫወተችኝ በድንገት አቋርጣ ራሷን ለመቆጣጠር መሞከር የጀመረችው ለካ እስር ቤቱ የሚገኝበት ቦታ እንደደረስን ስታውቅ ነበር። እኔ ከመመሰጤ የተነሣ የት እንዳለሁ ዘንግቼዋለው።

እስር ቤት እንደደረስን መጀመሪያ ያገኘነው እስረኛ ግሩም ጌታሁን ይባላል። ግሩም አንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ፀሐይ እየሞቀ ነበር። አጠገቡ አንድ ጠባቂ ቆሟል። መጀመሪያ ሳየው እስረኛ አልመሰለኝም ነበር፤ በኃላ ከሁኔታው እስረኛ መሆኑን ስረዳ በጣም ደነገጥኩ። ግሩምን ያየሁትም ሆነ የፓርቲው የማእከላዊ ኮሚቴ አባል እንደሆነ ያወቅሁት በግንቦቱ ስብሰባ ላይ ነበር። ተስፋዬ ደበሳይ በመራው ስብሰባ ላይ ምክትል የስብሰባ መሪ ሆኖ መድረክ ላይ ተቀምጦ ነበር። ግሩምን አንድ ቀን ያየው ሰው መልሶ የትም ቢያየው ሊጠፋው አይችልም፣ ምክንያቱም መልኩም ሆነ የሰውነቱ አቋም ለየት ብሎ ይጎላል። ግሩም መልኩ ብስል ቀይ፣ ረዥም ቁመትና ግዙፍ ሰውነት ስላለው፣ ማንንም አያሳስትም። ግሩም በመጨረሻ ከአንጃዎች ጋር ቢፓርቲው መገደሉን ሰምቻለሁ።





ወደ እስር ቤቱ ደርሰን እንዳየነው ሁለታችንም የተቀመጠበት ቦታ ድረስ ሄደን ሰላም አልነው። ስንገናኝ እንደማውቀውና በዛን ቀን ስብሰባ ላይ ከተስፋዬ ደበሳይ ጋር አብሮ እንዳየሁት ነገርኩት። እሱም ያን ቀን እንዳየኝና እንደሚያስታውሰኝ ሲነግረኝ ገረመኝ። ከዚያም ለሰላምታ ተቃቀፍን፤ ትንሽም አወራን። በተራራዎች መካከል ተከቦ መኖር እንዴት እንደሚያስፈራ እየሳቀ አጫወተኝ። የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ስለነበረ፣ እስር ቤት ሳገኘው "ምን አድርጎ ይሆን?" ብዬ በጣም ነበር የደነገጥኩት። መቼም ሰላማዊት ምክንያቱን ሳታውቅ እንደማትቀር ገምቻለሁ፤ ነገር ግን አልጠይቅኳትም። ብቻ ለራሴ በሆዴ እንዳብሰለሰልኩት ተመለስን።

ስንገዴ ወደ ማደሪያ ቦታችን ከተመለስን በኋላ ዓረፍ አልን። ሰላማዊት የቀኑን ድንጋጤ፣ የሰውነቴን እንቅስቃሴ፣ አቋቋሜንና አጠያየቄን እያነሣች ትሰቅብኝ ጀመር። እንዲሁ እንደያዘችኝ ሳታርፍ ስታበሽቀኝ አመሸች።

ሁሉም ነገር አለቀ። የትሪቢዩናሉ ውሳኔ ብቻ ነበር የሚጠበቀው። በዚያ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ አንድ ቀን ተጠራሁና ከአንድ ጓድ ጋር መልእክት እንድናደርስ ወደ ጾረና ተላከሁ። ከሰላማዊት ጋር ስንሰነባበት ከፍተኛ ቅሬታ ተሰማኝ። ምን ያህል እንደተቀራረብንም ያወቅሁት ያን ጊዜ ነበር። በድንገትና በአንድ አጋጣሚ የተነሳ የተዋወቅን አልመስልህ አለኝ። ለመጨረሻ ጊዜ ብሩህ ፈገግታዋን ተቀብዬ ስመለስ እንደምንገናኝ ተስፋ አድርጌ ተሰናበትኳትና ሄድኩ።

***

ያን ጊዜ የአመራሩ አባላት በሙሉ ጾረና(ኤርትራ) ነበሩ። ከውጪ የመጣ ብዙ የመሣሪያ ክምችት ስለነበረ እርሱን በማሰራጨትና በማከፋፈል ሥራ ላይ ነበሩ። መልእክቱን ይዘን ሄደን ካደረስን በኋላ አብሮኝ የሄደው ጓድ ብቻውን እንዲመለስና እኔ ግን እንድቆይ ተደረግሁ። ጾረና ከኢያሱ ጋር እንደገና ተገናኘን፣ ኢያሱ ሰንገዴ መጥቶ አነጋግሮኝ ስለነበር እንተዋወቃለን። ጉዳዬን እንደሚከታተልና እንዳችም አግባብ ያልሆነ ነገር እንደማይደርስብኝ ነግሮኝ አጽናንቶኝ ስለነበር እንደገና ሳገኘው ደስ አለኝ። እርሱም ስለእኔ በደንብ ሳይነገረው አልቀረም እንደተገናኘን እጆቹን ዘርግቶ ተቀበሎ በጣም አቀረበኝና አብዛኛውን ጊዜ አብረን እናሳልፍ ጀመር። ብቻችንን ስንሆን አንዳንድ ታሪኮች ይነግረኛል፣ በፊት የማላውቃቸውን መዝሙሮችም እያስጠናኝ፣ በቃሌ እንድይዛቸው ያደርግ ነበር። የሚያስተምረኝ መዝሙሮች ለእኔ በሚስማማ ሁኔታ እየመረጠ ነበር። ከመዝሙሮቹ ሁሉ የማልረሳው "በትግል መሞት" የሚለውን መዝሙር ነው። ዜማው አሳዛኝና ቀስቃሽ ስሜት የሚፈጥር ነበር:: ግጥሙም እንዲሁ ገላጭ፣ አጽናኝ፣ አበረታችና አነሳሽ መልእክት የሚያስተላለፍ ነው። የሥነ ጽሑፍን ጥበብ ትልቅነትና የቱን ያህል ስሜትን ለመንካት እንደሚችል ያሳያል። ታዲያ ኢያሱ መጀመሪያ ሙሉ በሙሉ ይዘምርልኝና ቀጥሎ እየተከተልኩት አብሬው እንድዘምር ያደርገኛል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ብቻዬን መዘመር እስከችል ድረስ ያስጠናኛል።

"በትግል መሞት ሕይወት፣ በአመጸ መሞት ሕይወት  
ዳግም ትንሣኤ ልደት። የትግል የድል ጎዳና  
የእነ ቼ የእነ ሆ ፋና  
የፋኖነት ምሥራቹ፣ የታጋይነት ብስራቱ  
ድል ተቀዳጅቶ መሞቱ፣ በሞት ሕይወትን ማግኘቱ።





(ብሎ ዝግ ብሎ የጀመረው መዝሙር ከዚህ በኋላ ከፍ ባለ የድምፅ ደረጃ ወጥቶ በጥሪ ዓይነት ቃና ይቀጥላል። )

እናንት የአብዮት ሰማእታት የነገ ድል ቀን ሕያዎች  
የነጻነት ቀይ ጮራዎች

(እንደገና እዚህ ጋ ደግሞ ዝግ ባለ የድምፅ ደረጃ ዜማው ሲወርድ፣ ግጥሙ ደግሞ በትግል ውስጥ የሚያጋጥመውን ስቃይ ከዚያ በኃላ የሚመጣውን የድል ውጤት አሳይቶ ያበቃል)

የጭቁን ሕዝቦችን ትግል፣ በወህኒ ሲቃ ሰቆቃ፣ በፋሽስቶች ጥይት ጅራፍ  
በመደብደብ በመገረፍ፣ በመገደል በመጨፍጨፍ  
በቆረጣችሁት ስጋ፣ ባዘራችሁት የደም ጎርፍ፣ የትውልድ እድፍ ይጠራል  
ባንዳ በደሙ ይሸቃል፣ ጭቁን ድልን ይቀዳጃል።"

የሚለውን መዝሙርን ስሰማም ሆነ ስዘምረው በዓይኔ የሚመጡት እነዘላለም፣ ግደይ፣ ጁሊያኖና በወሎ እደጋ ላይ የወደቁት ጓዶች በመሆናቸው አንዳንዴ ከእነርሱ ጋር የሚያነጋግረኝ ስለሚመስለኝ በጣም ደስ ይለኛል።

ኢያሱ እንደዚህ ደስ ደስ የሚሉ ሌሎችንም መዝሙሮች እያስጠና፣ ስንዘምር የምንውልበት ብዙ አጋጠሚዎች ነበሩን። ቢሆንም ለሥራ ወዲያ ወዲህ የሚልበት ብዙ ጉዳዮችም ነበሩበት። ጾረና ውስጥ የእኛ አመራሮች፣ ከዘርኡ ከህሸን በስተቀር ሁሉም አንድ ቦታ ነው የሚቀመጡት። ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ዘርኡ ከህሸን ግን የእኛ አመራር ካሉበት ቦታ ፈቀቅ ብሎ በሚገኝ ቤት ውስጥ ለብቻው ነበር የሚቀመጠው።

አንድ ማታ ጂግሳ ጠራኝና በፖስታ የታሸገ ደብዳቤ ሰጥቶኝ፣ "ይህንን ደብዳቤ ወስደህ ለፀሐዬ ስጠው፤ ፀሐዬ ጓዶች ይዞ ወደ እዚህ እየመጣ ነው" ብሎ የሚመጣበትን አቅጣጫ ነግሮኝ" ያልኩህን መንገድ ይዘህ ከሄድክ መንገድ ላይ ትገናኛላችሁ። ደብዳቤውን ግን ለጸሐዬ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ሰው እንዳትሰጥ" በማለት አስጠንቅቆ ላከኝ።

ጊዜው መሽቶ ጨለማ ሆኗል፣ በዚያ ላይ ላኪው ጅግሳ ነው። ጅግሳ ደግሞ በእኛ ክስ ጉዳይ እጁ አለበት። መልእክቱ ስለእኔ እንደሆነ ገምቼ በጣም ጨነቀኝ። ጂግሳ በትሪቢዩናል ክስ ላይ ስሜ በግምገማ ላይ ሳይነሣና ሌሎች እየተቃወሙት ጭምር እንድጠየቅ የሚገፋፋ የነበረው እርሱ ነው ብዬ ስለምገምት፣ በእርሱ ላይ እምነት አልነበረኝም። ትሪቢዩናሉ ውሳኔ አስተላልፎ ሊሆን ይችላልና ላኪው እርሱ በመሆኑ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ገባሁ። ምናልባት በኔ ላይ መጥፎ ትእዛዝ የያዘች ደብዳቤ ልትሆን ትችላለች፣ መታሰርም መገደልም ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩና የበለጠ ሰጋት አደረብኝ።

በዚያ ምክንያት ከጾረና ተነሥቼ ራቅ እንዳልኩ፣ "ለማንኛውም" ብዬ በጥንቃቄ እሽጓን ከፍቼ አነበብኳት። ደብዳቤው በመጨረሻ ላይ "ጓድ አማኑኤል ቤዝ አካባቢ እንዲቆይ" የሚል መልእክት እንደያዘች አየሁ። እንዲህ ከሆነ ምንም ችግር የለውም ብዬ እንደነበረ መልሼ አስተካከልኩና ይዤ ሄድኩኝ። ዛላአንበሳን አልፌ ሰበያ አካባቢ ስደርስ እንደተባለው እነፀሐዬ ሲመጡ አገኘኋቸው።

ስንገኛኝ ቀኑ መሽቶ ነበር። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፣ ደብዳቤዋን አወጣሁና "ፀሐዬ ይቺ ደብዳቤ ላንተ የተላከች ናት፤ ጅግሳ፣ ለፀሐዬ ካልሆነ በስተቀር ለማንም እንዳትሰጥ ብሎ አስጠንቅቆ ነው የላከኝ" አልኩት።

ጨለማ ስለነበር የሲጃራ መለኮሻ ላይተር ለኩሶ ከፈተና አነበባት። አንብቦ ሲጨርስ "ከዚህ በኋላ ወዴትም አትሄድም፣ ከእኔ ጋር ወደ ጾረና ነው የምንሄደው" አለኝ። ምክንያቱም አማኑኤል ቤዝ አካባቢ እንዲቆይ ትላለች። እና ፀሐዬ መልእክቱን ትቶ ለምን ከእኔ ጋር ተመለስ እንዳለ አልገባኝም። ብቻ ስለመልእክቱ ምንም እንደማያውቅ ሰው ሆኜ አብሬው ወደ ጾረና ተመለስኩ።

ከፀሐዬ ጋር የመጡት ጓዶችና ሕዝቡ አዲስ ከገቡት መሳሪያዎች የተወሰነ ብዛት ለማምጣት ተልከው ሲሄዱ፣ ፀሐዬ እኔን እንደገና አመራሮች ወዳሉበት ቦታ ይዞኝ መጣና "ከእነርሱ ጋር እዚሁ ቆይ" አለኝ። አንድ





ሳምንት ያህል ቆየሁ። ከዚያ በኋላ የገባው መሣሪያ ተጓጉዞና የሚከፋፈለውም ተከፋፍሎ፣ እየተገባደደ ሄደ። መጨረሻ የቀረውን ወደ አሥራ ሁለት የግመል ጭነት የሚሆነውን መሣሪያ ይዘን ሁላችንም ወደ አሲምባ ተመለስን።

ጸጋዬ ደብተራው፣ ከኃይል ሦስት ተመልሰን ክስ ሲመሠረትብኝ ኤርትራ ሄዶ ስለነበር አልሰማም። ወደሌላ ቦታ ሄዶ እንደነበረና መመለሱንም የነገረኝ እርሱ ራሱ ነበር። ወደ አሲምባ ስንመለስ የአመራሩ አባላት፡ አበጀ፣ ሮባ፣ ጂግሳ፣ ጸጋዬ ደብተራው፣ ፀሐዬና ሌሎቹም ከእኛ ጋር ነበሩ። የመልስ ጉዞውን ስንጀምር ጸጋዬ ጠርቶኝ እኔና እርሱ አብሪ ሆነን እንደምንሄድ ነገረኝ። "ለብቻችን ከእኔ ጋር እንሂድ ያልኩህ፣ በጎንደር ተልእኮ ላይ ስለደረሰው ችግር እንድትነግረኝ ስለፈለኩ ነው። ስለዚህ ሁሉንም ነገር በደንብ ዘርዝረህ ትገልጽልኛለህ" አለኝ።

አብረን እየሄድን ሁሉንም ነገር ዘርዝሬ ነገርኩት። "እስከአሁን ድረስ ነገሩ ያልተፈታበት ምክንያት እኔን እየጠበቁ ስለነበር ነው። አሁን እኔ መጥቼአለሁና በቅርቡ ሁሉም ችግር ይፈታል። አንተ ከብዙ ችግር የወጣህ ነህ፣ ስለዚህ ምንም ጭንቀት ሊያድርብህ አይገባም" ብሎ ተስፋ ሰጠኝ።

አሲምባ ከደረስን በኋላ የመጣው መሣሪያ በሙሉ ዳያ እንዲከማች ተደረገ። የመሣሪያ ግምጃ ቤቱ የእነ ዘማሪያም ቤት ነበረ፤ ሆኖም ግን በየምሽቱ መሣሪያውን ከቤት በማውጣት የተሠወረ ቦታ እንዲያድር ይደረጋል። ለጥበቃውም አንድ ጋንታ ተመሥርቶ የጋንታ አዛዥ ሆኜ ተመደብኩ። የመሣሪያ ግምጃ ቤቱን ጥበቃ ሐላፊነት ተረከብኩና ዋርድያ የመመደብና የመቆጣጠር ሥራ እየሠረሁ ጥቂት ቀናት ቆየሁ።

በኋላም ወደ ቆለም ሸላ አበጀ ጋ ተላከሁ። ስደርስ አበጀ አድማሱና ሂሩት (መዝገብነሽ) አብረው ቆመዋል። አበጀ ብቻውን ወደ እኔ መጣና "የትሪቡናሉ ውሳኔ ደርሶኛል" አለኝ። ሳላስበው የደነገጥኩ መሰለኝ። "አይዞህ የሚያስደነግጥም የሚያስፈራም የለበትም፣ ሁሉም ነገር በሰላም አልቋል" ብሎ አቅፎ ሳመኝ። ከዚያም አንድ ወረቀት አወጣና "ጓድ አማኑኤል በትሪቢዩናል ከቀረበበት ክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ ስለሆነ፣ ወደ ነበረበት የሐላፊነት ቦታ

እንዲመለስ እንዲሁም ድርጅቱና ሠራዊቱ በሚያምንበት ሐላፊነት ሁሉ ተመድቦ እንዲሠራ....” የሚል ማኅተምና ፊርማ ያለበት ወረቀት አነበበልኝና “ለአሁኑ ጎእተሎ አካባቢ ጥበቃ ኃይል ወደ ነበረችው ኃይል አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ተመድበሀል” አለና ነገረኝ። በማግስቱ ስንቅ ተሰጥቶኝ ወደ ጎእተሎ ሄድኩ።

የኃይል አምስት መቶ ሃምሳ አምስት መሪ ሲራጅ ነበር። ስደርስ በደንብ ተቀበሉኝ። ከሁለት ሳምንት በኋላ፣ ሲራጅ ጠራኝና “አንተ ሞንሰሎ የሚገኘው አመራሩ ዘንድ ተፈልገሀል፤ በዚያውም መአዛን አብረህ ይዘሃት ትሄዳለህ” አለኝ። መአዛ ያኔ ኃይል አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ውስጥ ያለች ብቸኛ ሴት ነበረች። የምትሄደው በአሰፋይቱ የሴቶች የመጀመሪያ ጉባኤ ላይ ለመካፈል ነበር።(የአሰፋይቱ የሴቶች ጉባኤ የተካሄደው በ1969 ዓ.ም ከሐምሌ 21 እስከ 24 ቀን ነበር) በተነሣንበት ቀን ስላልደረስን መሽብንና አንድ ቦታ አድረን፣ በማግስቱ ጠዋት አካባቢ ደረስን። ሞንሰሎ አመራሩ በሚቀመጥበት የኃይሉ ስብሐት ቤት ሄድኩ። እርሷ ደግሞ ጉባኤው ወደሚደረግበት ወደ አሰፋይቱ ሄደች።

ያን ጊዜ ሞንሰሎ የነበሩት ሮባ ፣ ጸጋዬ ደብተራው እና ጂግሳ ናቸው፡፡ ፀሐዬ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። ከእነርሱ ጋር ተገናኝተን ወደ ቤት ስንገባ የኃይሉ ስብሐት ባለቤት “ፀሐዬስ የት ሄደ?” ብላ ጸጋዬ ደብተራውን በትግርኛ ጠየቀችው። ጸጋዬ ደብተራውም ፀሐዬ ሩቅ አገር ነው ያለው ለማለት፣ የአማርኛውን “አገር ቂጥ” ቃል በቃል ወደ ትግሪኛ ተረጎመውና “መእኮር አገር ኢዩ” ብሎ መለሰላት። መልሱን ስትሰማ በሳቅ ተንከተከተችና “ጸጋዬ ደብተራው ምንድነው የምትለው? በትግሪኛ እኮ እንደሱ አይባልም፤ ነውር ነው” አለችው።

ጸጋዬ የሰራው ስሕተት ገባውና ነው መሰለኝ እርሱም ሳቀ። እኔም ከእሱ ተከትዬ ስስቅ “ለምንድነው የምትስቅብኝ?” አለኝ።

“እንዴ ምንአለበት ብስቅ?‘መእኮር አገር’ የምትላት አገር ቂጥ ሄዷል ለማለት ነው? አንተ መእኮር አገር ስትል እኮ ሀገር የሚያከል ቂጥ እንደማለት ነው”





ስለው፣ እርሱ እራሱ እንደገና በጣም ሳቀ። በዚህ ሁኔታ የጀመርነው ጨዋታ ተለወጠና ስለእኔ አንዳንድ ነገሮች ጠይቀኝ። ሁሉም ነገር ሰላም መሆኑን ነገርኩት። መልሴን አዳመጠና “ዋናው ወደዚህ የተጠራህበት ምክንያት ከጅግሳ ጋር እንድትነጋገሩ ስለፈለግሁ ነው” አለኝና ጅግሳን ጠራው።

ከጂግሳ ጋር ስንነጋገር፣ ጂግሳ “በእኔ ላይ ቅሬታ ካለህ ንገረኝ?” አለኝ። በክሱ ጉዳይ ላይ መሆኑ ነው።

“ምንም ቅሬታ የለኝም” አልኩት፣ የእውነቱን ግን አልነበረም።

“እንደሱ ከሆነ እኔም በአንተ ላይ ምንም ዓይነት ቅሬታ የለኝም፤ አይዞህ” አለኝ።

በዚህ ጊዜ እርሱ በእኔ ላይ ቅሬታ እንደነበረውና እኔ ትሪቢዩናል እንድቀርብ ይገፋፋ የነበረው እርሱ ለመሆኑ ማረጋገጫ ሆነኝ። ምክንያቱም ለምን ከጅግሳ ጋር ለብቻችን እንድንወያይ አሰበው ጠሩኝ? በማግስቱ ወደ መጣሁበት ኃይል ተመለስኩ። ልክ እንደተመለስኩ ምክትል ጋንታ መሪ ሆንኩ። ምደባዬ የቆየው ከጅግሳ ጋር እስከምነጋገር ድረስ እንደነበረ ገባኝ።

ወደ ምክትል ጋንታ መሪነት ቦታዬ ከተመለስኩ በኋላ የኃይሏ መሪ ሲራጅ ጥሩ ሰው ስለሆነ በቆየሁበት አጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ነገር የምንሠራው በመግባባትና በመተሳሰብ ነበር። አንዳንዴ ከሲራጅ ጋር ስንጨዋወት የራሺያ ተማሪ እንደነበረ፣ የኦሮሞ ተወላጅ እንደሆነና በቾ አካባቢ እንደተወለደ ይነግረኝ ነበር። ሲራጅ፣ መልኩ ጠይም ዓይኖቹ ትላልቅና ፂማም አብረውት ያሉት ጓዶች እንደ ጓድ ብቻ ሳይሆን እንደትልቅ ወንድምም የሚመለከቱት ነበር ። አንዳንድ ቀን ስናርፍ ብዙ የተቀደዱ ሱሪዎችን ይቀበለንና በመርፌ ጥፎ፣ በመኪና የተሰፋ አስመስሎ ይሰጠናል። ኢሕአሠ ከነበሩት ችግሮች ሁሉ የልብስ ችግሩ ይገርመኝ ነበር። አንዳንዴ ቆየት ያሉ ጓዶች ሳይቀሩ በተቀዳደደ ቁምጣ የሚታዩበት ጊዜም ነበር። ሲራጅ ለሠራዊቱ ልብስ እየሰፋ በግሉ የሚሠራው ሥራ እንዲህ እንደዋዛ የሚታይ አልነበረም፡፡ በሠራዊቱ ውስጥ ትልቅ ቦታ

ለነበረው ችግር መፍትሔ በመስጠት አርአያነት ያለው ሥራ እንዳከናወነ ነው የምቆጥረው። አንዳንዴ ደግሞ የነበረችውን "ሰርቫይቫል" የምትል መጽሐፍ እያነበበ፣ ስለምግብ፣ ስለቅጠላ ቅጠል፣ በችግር ጊዜ ስለሚበሉና ስለማይበሉ የዱር ሥራስርና፣ ፍራ ፍሬ ያስረዳን ነበር።

ከሞንሰሎ በተመለስኩ ሰሞን በነሺፈራው ክስ ላይ የተሰጠውንም ውሳኔ ሰማሁ። ሺፈራው ለስድስት ወራት ትጥቅ እንዲያወርድ፣ ከማንኛቸውም የፓርቲና የሠራዊት ሐላፊነት እንዲታገድና የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዳይኖረው የሚል ውሳኔ ነበር የተላለፈበት።

በኃይሌ ቀጭኑ ላይ የተወሰነው ደግሞ ከነበረው የአመራር ሐላፊነት ጋር የሠራው ሥራ ሲታይ ለአርባያው ችግር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ተጠቅሶ፣ ለአንድ ዓመት ትጥቅ እንዲያወርድ፣ በማንኛውም የፓርቲና የሠራዊት ሐላፊነት ቦታ እንዳይመደብና የመምረጥና የመመረጥ መብቱን እንዲገፈፍ የሚል ነበር።

ኃይል አምስት መቶ ሃምሳ አምስት እያለን አንድ የማልረሳው ነገር ቢኖር እንደ እብድ እየለፈለፈ የሚመላለስ ሰው ነበር። በመጀመሪያ ስናገኘው ምናልባት ሰላይ ሊሆን ይችላል ብለን ስለገመትን ከጥበቃ ጋር አድርገን እንዲያጣሩ ወደ አመራሩ ላክነው። እነርሱ ደግሞ "እብድ የምትልኩብን ምን አድርጉ ብላችሁ ነው?" ብለው ወደ እኛ መለሱት።

"እስኪ እናቆየውና ምን እንደሚያደርግ እንይ" ብለን ስንጠብቀው አንድ ቀን አባተ፣ አብዱ በመንገድ ላይ ሲያልፍ "ማነህ ቁም!!" ብሎ ጮኸበት፣ ሰውዬው አቋቋሙ ሁለት እጆቹና ጣቶቹ ልክ በወታደር አይነት እንቅስቃሴ እንደሆነ አባተ አስተዋለ። የመቶ አለቃ አባተ "ንውስ የደርግ አባል ነበር፣ እውነተኛ የወታደር ሰላይ መሆኑን በእጁ አጨባበጥ መለየት ትችላላችሁ" አለና ነገረን። ከዚያ በኋላ ታስሮ እንዲጠየቅ ተወሰነና ኃይሏ መጀመሪያ መርማሪ ቀጥሎ ደግሞ ትሪቡናል አቋቋመች።





መርማሪዎቹ ወስደው ሲያስፈራሩት "እኔን ፋሽስት እንዳትሉኝ። ከእናንተ ውስጥ አንድ የደርግ ሰው አለ ለካ፣ አገር የምታስጨርሱ ወንበዴዎች" እያለ እንደ እብድ መስሎ ሲናገር የነበረው ሰው አመነና እውነቱን ነገራቸው። ሰውዬው ወደ አራት አምስት ቋንቋዎች ያውቃል። ከአባተ ጋር በኦሮምኛ ቋንቋ ተነጋገሩና ተግባቡ። በኋላ "እኔ ሁሉንም ምስጢር እነግራችኋለሁ፣ አትግደሉኝ" አላቸውና የሠራባቸውን ቦታዎች ተናገረ። እስራኤል እንደሰለጠነ፣ በጌምድር እንደነበረ፣ወሎ ወታደሮችን መሰለሉን ፣ ከተማ ውስጥ የኢሕአፓ አባሎችን ሲከታተልና ሲያሲዝ እንደነበረ ነገራቸው። እነርሱም "እንዴት ታውቃቸዋለህ? በምስጢር ነው የሚሠሩት" ሲሉት ሳቀና "ከተማ ያሉ አብዛኛዎቹ ኢሕአፓዎች እየቸኮሉ ነው የሚሄዱት። አሥር ጊዜ ሰዓት ማየት ይወዳሉ። ጸጉራቸውን ያንፍራሉ ..." አለና ነገራቸው።

ትሪቢዩናል ተቋቁሞ ጠቢቃ ይቁምለት ተባለና ጠበቃ እንዲመርጥ ተነገረው። እሱም ከተሰበሰበው ሰው ለመምረጥ ምንም ሳያመነታና ጊዜ ሳይፈጅ "ሲራጅን መርጫለሁ" አለ። ሲራጅን ስለመረጠ ሁላችንም ተደነቅን። ምክንያቱም ሁላችንም በጣም አስተዋይና ጥሩ ሰው ነው የምንለው፣ ከሌላው በተለየ የምንወደውና የምናከብረው ሲራጅን በመሆኑ ነበር። ይህ ሰውዬም እርሱን ሲመርጥ አስተዋይ ሰው እንደሆነ አወቅን። "እናንተ ካለእርሱ በስተቀር አዋቂና የበሰለ ሰው የላችሁም። እሺ ካላችሁ ለጠበቃነት የምመርጠው እርሱን ነው" አለን።

ሲራጅም ለብቻው ወስዶ አነጋገረውና ለእርሱ ሊሆን የሚችለውን አማራጭ ነገረው፡፡ "የፖለቲካ ትምህርት፣ ለአንድ ወይንም ለሁለት ወር ይሰጥሀ፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ደርግ እንዳትመለስ ወደ ውጭ እወጣለሁ ካልክ እንድትወጣ እኔ እስከመጨረሻ እከራከርልሀለሁ" ብሎ አማከረው።

ሰላዩ ግን "እኔ ለማምንበት እሞታለሁ እንጂ ወደ ውጭ ለመውጣት ፍላጎት የለኝም። የእናንተንም የፖለቲካ ትምህርትም አልፈልግም። እናንተን አውቃችኋለሁ። ስለዚህ ይቅርታ አድርግልኝና እኔ በአቋሜ እንደጸናሁ በአቋሜ

እሞታለሁ እንጂ የምትለውን አማራጭ ሁሉ አልፈልግም"አለ። "እናንተ በእምነታችሁ ጽኑ፣ እኔም በእምነቴ እጸናለሁ። እናንተም በእምነታችሁ ትሠዋላችሁ እኔም በእምነቴ እሠዋለሁ። በመጨረሻ ግን እናንተ እንደምትወድቁና የትም እንደማትደርሱ አውቃለሁ" አለ እንደገና ከጥቂት ቆይታ በኋላ።

"ለምን እንደዚህ አልክ?" ብለን ጠየቅነው። "የእናንተ ዓላማ አይሳካም። እኔ ይሄንን አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ ከእናንተ ጋር አብሬ ለመራራድ አልችልም። ከመጀመሪያም ስነሳ ሞት እንደሚያጋጥመኝ አውቃለሁና ምንም ነገር ቢመጣ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ" አለ። ብዙ ጓዶች እየተቀባበሉ ቢያናግሩትና ቢለምኑትም እንቢ አለ።

ሲራጅ የቻለውን ያህል ተሟገተለትና ፍርድ ተሰጠው። "እኔ አማራጮች ባቀርብለት እምቢ ብሎኛል፣ ለምኜዋለሁ፣ ምንም ማድረግ አልችልም" አለ። ውሳኔውን አስይዘን ከሁለት ጓዶች ጋር ሲምባ እንዲላክ ተወሰነ። ለእርሱ ግን ሁለቱ ጓዶች ሐኪሞች እንደሆኑና ሲምባ እንዲያደርሱት የተመደቡ መሆናቸው ነው የተነገረው።

እኛን "እሺ" አለን። ለራሱ ግን ሞት እንደተፈረደበት ገምቷል። ሌሊት ከታሰረበት ምሰሶ ጋር ጭንቅላቱን እያጋጨ ሕይወቱን አጥፍቶ አገኘነው። ለእምነቱ ያለውን ጽናት ሕይወቱን ያጠፋበትን ሁኔታ አይተን ሁላችንም አደነቅነው።

ከአንድ ወር በላይ ለሚሆን ጊዜ ኃይል አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ከቆየሁ በኋላ በነሐሴ ወር የጉእቶሎ ሠራዊት የመቀየጥ ምደባ ተደረገና ከኃይል አምስት መቶ ሀምሳ አምስት ወደ ኃይል አምስት መቶ ተዛወርኩ።

***





## አምስት

## ኃይል አምስት መቶ

### የጎእቶሎ የሠራዊት ቅየጣ

ነሐሴ ወር 1969 ዓ.ም ጎዕቶሎ ላይ ሠራዊት የመቀየጥ ሥራ ተከናውኖ አዲስ ምደባ ተደረገ። በዚያ ወቅት እኔ ኃይል አምስት መቶ ውስጥ ተመደብኩ። የኃይል መሪ ጌትነት ሲሆን ምክትል መሪ ደግሞ የአቢኢዮ ነበረ። የኃይሏ የፖለቲካ ሐላፊ አሰፋ ምክትል ደግሞ ሰለሞን ሆነው ተመደቡ። የኃይል የፓርቲ ኮሚቴ አባሎች ከሡተ፣ አረፋይኔና ጃቢር ሆነዋል። የፓርቲ ኮሚቴ አባላት መመደብ የተጀመረው በእርማት እንቅስቃሴው ግዜ በተደረጉ የማሻሻያ ውሳኔዎች ሲሆን በአዲሱ አሠራር ሌሎችም ለውጦች ተደርገዋል።

በኃይል አምስት መቶ ውስጥ እንደሚገኘውም ኃይል ሦስት ጋንታዎች አሉ፡፡ እነሱም ጋንታ አምስት መቶ ሦስት፣ ጋንታ አምስት መቶ አራትና ጋንታ አምስት መቶ ስድስት ነበሩ። እኔ የነበርኩበት ጋንታ አምስት መቶ ስድስት ጋንታ መሪው እንግዳ ወርቅ ምክትሉ ደግሞ እኔ ነበርኩ። ድላይ የተመደበችው ጋንታ አምስት መቶ ሦስት ውስጥ ሲሆን፣ የጋንታ መሪው ቴዎድሮስ ባሪያው፣ ምክትሉ ደግሞ እርሷ ነበረች። የሦስተኛዋ የጋንታ አምስት መቶ አራት መሪ ግደይ ጨዳር፣ ምክትሉ ደግሞ ብርሃኑ ሆነው ተመድበዋል።

በጎዕቶሎ ሠራዊቱን በመቀየጥ እንደገና የመመደብ ሥራ በተካሄደ ወቅት ከውጭ የመጣ ብዙ ትጥቅ ስለነበረ ሠራዊቱ በበቂ ሁኔታ ታጥቋል። እያንዳንዱ ኃይልም በየራሱ የተለያዩ ክፍሎች ተዋቅሮ የመረጃ ክፍል፣ የብዙኃን ድርጅት፣ የሚሊሻ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል። አንድ ኃይል አቅሟ በሚፈቅደው መጠን የምታምንበትን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ሥልጣን ተሰጥቷታል። ነገር ግን

በዚያን ጊዜ በአንድ ኃይል ብቻ ሊካሄድ የሚችል ብዙም ነገር ባለመኖሩ ከሌሎች ኃይሎች ጋር በመቀናጀትና በመደጋገፍ መሥራት የግድ ነበር።

በአዲሱ አደረጃጀት ከየቦታው የተወከሉ በፖለቲካዊ፣ በወታደራዊና በሌሎች የሠራዊቱ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ብቃት ያላቸው አባላት እንዲጠቆሙ ተደርጎአል። በሠራዊቱ የተመረጡ ተወካዮችም ወደ አመራር እንዲገቡ በተወሰነው መሠረት መዝሙርና ዳዊት ስዩም ተመርጠዋል። የቀድሞዎቹ የሠራዊቱ ወታደራዊ ጠቅላይ አመራር አባላት ግን ከአንድ የአመራር አባል በስተቀር ሁሉም በሐላፊነት ላይ እንደነበሩ ናቸው።

ሠራዊቱ በአዲሱ የአሠራር ለውጥ እንዲዘጋጅ የተደረገው በአዲስ መስመር፣ በአዲስ አመራር፣ ተጠናክሮ ይንቀሳቀሳል ተብሎ ነው። በዚህ አመዳደብ ደህና የፖለቲካ ብስለትና ጥንካሬ ያላቸው አባላት ተመድበዋል። ለከፍለ ሕዝብ ሥራ ወደ አድዋ፣ እነጽላሎም፣ እነተስፋዬ፣ እነ ጴጥሮስ በመረጃ ክፍል በኩል ደግሞ እነታየ ቶላ፣ ኤልያስ፣ ኪዳነ ኪሮስ፣ አስረስ፣ ተሻገር፣ ፀሐይ፣ ኃይለ ማርያምና ሌሎችም ኀበዝና ጠንካራ አባላት ተመድበዋል።

እንደሌሎቹ ሁሉ የእኛም ኃይል በኃይል፣ በክፍሊታት፣ በመረጃ ክፍልና በሌሎች የሥራ መስኮች በአዲስ አመዳደብ ተደራጅታ ወደ አድዋ በኩል ተንቀሳቀሰች። በኃይል አምስት መቶ የኃይል መሪነት የተመደቡት ጌትነትና የአብኢዮ በፊትም የማውቃቸው ሲሆን ሁለቱም ብቁ የሆነ የአመራር ችሎታና ልምድ ያላቸው ነበሩ።

ከጎእቶሎ ወደ አድዋ ለመሄድ ገና በዝግጅት ላይ እያለን የደርግ ጦር በአዲግራት በኩል እየመጣ መሆኑ ተሰማ፡፡ ኃይል አምስት መቶና ኃይል ሃምሳ አምስት የደርግ ጦር ከአዲግራት እንዳያልፍ ለማገድ ታዘን ምሽግ ይዘን መጠበቅ ጀመርን። ቀኑን በሙሉ እየዘነበብን ምሽግ ይዘን ዋልን። ከኃይል 58 ጋንታ ውስጥ የነበረው ገሬኖቭ ጂ የሚባል ከባድ መሣሪያ ለምናደርገው መከላከል ጠቃሚ





መሆኑ ታምኖበት እኔ ወደነበርኩበት ጋንታ መጥቷል። ዝናቡ በጣም እየበረታ ሲሄድ፣ መሳሪያውን ዝናብ እንዳያበላሸው መሸፈኛው ከተደረገለት በኋላ የተወሰኑ አባላት እንዲጠብቁ ተመድበው የቀረነው ከበታቻችን በሚገኝ ዋሻ ውስጥ እንድንጠለል ተደረገ።

ዋሻ ውስጥ መጠለያ ስናገኝ፣ የአካባቢው ወጣቶች ደግሞ ያለምግብ መዋላችንን አውቀው የምንበላው በለስ ይዘውልን መጡ። የእውነትም ተርበን ነበር። በለስ፣ የአካባቢው ነዋሪ ለምግብነት የሚጠቀምበት በውጭ በኩል ቆዳው እሾህማ የሆነ፣ ውስጡ ግን መቃሚ የምግብ ይዘት ያለው ቁልቋል መሰል ተክል ነው። የበለሱን አበላል የምንችልበት በለሱን እያቀለጥን (እየላጥን) ለራሳችንና አበላሉን ለማያውቁ ጓዶች እንሰጣለን። ውጣቶቹም በመላጡ ያግዙን ነበር።

በለሱን በመመገብ ላይ እያለን መሐመድ የሚባል (ቀድሞ የተሐሓት አባል የነበረ ከአይጋ መጥቶ ወደ ኢሕአፓ የተቀላቀለና በኃይል አምስት መቶ ውስጥ በሀኪምነት የተመደበ) የእኛ አባል፣ አንደኛውን ልጅ “አንተ ልጅ ለራስህም እየበላህ” አለው። የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊው ሳሙኤል ደግሞ የመሀመድን ንግግር ተቀብሎ “ለራስህም ብላ የምትለው፣ ስንቱን የትግራይ ሕዝብ ቀልበን ልንወጣው ነው” አለ ለመቀለድ በመፈለግ።

በዚህ ጊዜ ድላይ በቀልዱ ተናዳ ቱግ አለችና “አንተን ብሎ የፖለቲካ ሐላፊ፤ የትግራይ ሕዝብ አንተን ይቀልብሀል እንጂ አንተ ነህ እንዴ የትግራይን ሕዝብ የምትቀልበው!? እነዚህ የትግራይ ልጆች አይደሉም እንዴ ተርበዋል ብለው፣ አስበው ይሄንን የያዝከውን በለስ ተሸክመው የመጡት?” ብላ ስትቆጣው፣ ሁላችንም እሷን ደግፈን ጮህንበት።

የጋንታ መሪው ቴዎድሮስ ባሪያው ደግሞ “ተሳስተሀል ጓድ፤ ይህ አባባልህ ትክክል አይደለም። እንደዚህ ዓይነት አባባል በተለይ ከአንድ የፖለቲካ ሐላፊ የሚጠበቅ አነጋገር አይደለም። እንደበትህን ብታርም ጥሩ ነው” አለው።

ሳሙኤል ስሕተቱን አምኖ "ይቅርታ አድርጉልኝ፣ እቀልዳለሁ ብዬ፤ እምልጦኝ ነው የተናገርኩት፤ ተሳስቼአለሁ" አለ። ይሁን እንጂ በዚህ አነጋገሩ የተነሣ ብዙዎቻችን ለእሱ የነበረን ግምት እንደመጀመሪያው ሊሆንልን አልቻለም።

መሐመድ ይህንን ሁሉ ነገር ዝም ብሎ ይታዘብ ነበር። ከዚያም ወደ ጆሮዬ ጠጋ በማለት ድምፁን ዝቅ አድርጎ "እንዴ እንደዚህም አለ እንዴ? እኔ በፊት በነበርኩበት ድርጅት ሆነን የምንሰማው፣ አማራዎች የሚሏችሁን ብቻ የምትከተሉና የምትታዘዙ እንጂ እንዲህ ደፍራችሁ ተቃውሟችሁን እንደምትገልጹ አናውቅም ነበር" አለኝ።

"ሁላችንም የራሳችንን ክብር እንጠብቃለን። የምንናገረውና የምናደርገው ሁሉ በመተማመንና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ነው እንጂ አንዱ ያንዱ ገዢ፣ ወይም ተገዢ አይደለም። አንተ እንደምትለውና እንደሚወራው ዓይነት ግንኙነት በእኛ መካከል ቦታ የለውም። የሰው ትልቅነት የሚለካው በአስተሳሰቡ ትልቅነት እንጂ በዘሩ ወይ በጎሳው ማንነት አይደለም" አልኩት። አጋጣሚው አብረውኝ ከነበሩት ከመሐመድና በተለይ ደግሞ ከድላይ ጋር የበለጠ የሀሳብ መቀራረብ ፈጠረልኝ።

ከድላይ ጋር ቀደም ሲል ኃይል ሦስት ውስጥ ሁለት ሳምንታት ያህል በቆየሁበት ጊዜ በመጠኑ ተዋውቀን ነበር። በአዲሱ ምደባ ደግሞ ኃይል አምስት መቶ ውስጥ ተገናኘንና አብረን ቀጠለን። በእንደዚያ ዓይነት የተለያዩ አጋጣሚዎች ስንገናኝ የበለጠ ተግባብተን ተቀራረብን።

***





ወደ አድዋ መንቀሳቀስ ጀምረን ከጥቂት ቀናት በኋላ አንጋፋ ከሚባል በእዳጋ ሐሙስና በሀውዜን መካከል የሚገኝ ተራራ ስር ደረስን። ከፊት ለፊታችን ደግሞ ሌሎች ሁለት ኃይሎች ነበሩ። የእኛ ኃይል በምዕራብ በኩል እንድናርፍ ተደረግን፤ ጋንታዎቹ በሙሉ ቦታ ይዘው እያንዳንዱ ጋንታ ሙከት ወይም ፍየል በማረድ እንዲመገብ ፈቃድ ተሰጠ። የኃይል አመራሮች ለስብሰባ መሄዳቸውንና የእንቅስቃሴአችንን ዕቅድም ጫፍ ጫፉን ሰምተናል። ዕቅዱ ከአዲግራት በስተምዕራብ በኩል ባለው የሙግለት ማይክሮ ዌቭ ጣቢያ ውስጥ በጣም የተጠናከረ የጠላት ኃይልና በርካታ መሣሪያ በመኖሩ እሱን ለመምታት ነበር።

ከስብሰባው በኋላ አመሻሽ ላይ ለወታደራዊ ተልእኮ እንደምንንቀሳቀስ ለጋንታ አመራሮች ብቻ ተነገረን። "ብሉ! ጠጡ!" እያልን አባላቱን ስንጋብዛቸው ቆየን። ምሽት የአመራሩ ስብሰባ ተበተነና የአብኢዮ ወደእኛ መጣ። ተበሳጭቷል፤ ዓይኖቹ ደም ለብሰዋል። ወደእኔ መጣና "ወዲ ሀፍተይ" አለኝ። (በትግርኛ የእኅቴ ልጅ ማለት ነው) ከአሁን በኋላ ሞት የለም። መሥዋዕትነት የሚባል ነገር የለም። ምክንያቱም ሁሉም የሚፈልጉት ላለመዋጋት ነው። ይሄ ድርጅት የፈሪዎች ድርጅት ሆኗል። እንዋጋ እንሠዋ ስንል 'አይቻልም፣ አይሆንም' ብቻ የሚል ድርጅት ሆኗል" አለኝ ።

"ምነው እቅዱ ተሰረዘ እንዴ?" አልኩት "አዎ ተሰረዘ" አለኝ አሁንም ንዴቱ ሳይበርድለት

"ለምን?"

"አመራሩ፤ የተያዘው ዕቅድ መሥዋዕትነት ይበዛበታል ብሎ ስለፈራ በድምፅ ብልጫ እንዲወሰን አደረገ። ይሰረዝ የሚሉት ስለበዙ ተለእኮው ተሰረዘ። ስለዚህ እዚህ አድረን እንደገና ወደ አድዋ ልንመለስ ነው"አለኝ።

የወታደራዊ ተልእኮውን መረጃ ያጠናቀሩት የመረጃ ክፍል አባሎች፣ እነ ታየ ቶላ ነበሩ። እነርሱ ጥናቱን ሲያካሂዱ የየካምፑ ጥበቃ ሁለት ዙር ዋርድያ እንዳለው አውቀዋል። የመጀመሪያው የውጭው ዋርድያ በዚሁ አካባቢ ነዋሪ በሆኑ ሚሊሻዎች ይጠበቃል። ሁለተኛው ወደ ውስጥ ያለው ዋርድያ ደግሞ፣ ነበልባል በሚባለው ጦር እየተጠበቀ ነበር። የአካባቢው የሚሊሺያ ጠባቂዎቹ በእኛ የመረጃ ጓዶች ተይዘዋል። ስለዚህ ለወረራ መግባት የሚቻልበት አንድ ዘዴ አዘጋጅተው ለአመራሩ አቀረቡ። ቀድመው የሚገቡት ጓዶች የሚያውቋቸው ሚሊሻዎች ዋርድያ በሆኑበት ቀን የእነርሱን ልብስ ለብሰው፣ እነርሱን መስለው ወደ ውስጥ ያልፋሉ። ወደ ሁለተኛው የነበልባል ዋርድያ መጠበቂያ አጠገብ ሲደርሱ አፍኖ ይዞ ለሌሎች ጓዶች በር እንዲከፍቱ ለማድረግ እንደሚቻል አስረዱ። አጥሩ ዙሪያውን በፈንጂ የታጠረ ስለሆነ ወደ ካምፑ መግባት የሚቻለው በበሩ በኩል ብቻ ነበር።

ይህንን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ ታዬ ቶላ ራሱ ከአንድ የመረጃ ክፍል ጓድ ጋር ሆኖ ከአንድ ቀን በፊት የሚልሻዎቹን ልብስ ለብሶ ነበልባሎች ወደነበሩበት ቦታ ገብቶ ነበር።ከነበልባሎቹ ጠባቂዎች ጋር ሰላምታ ተለዋውጦ እንደተመለሰም ነግሯቸዋል። ስለዚህ በዕለቱ እነርሱ በተግባር በሞከሩት መንገድ በመግባት ሁኔታዎችን አመቻችተው እኛን ለማስገባት እንደሚቻል ለአመራሩ አስረድቷል። አንድ ጊዜ ውስጥ ከተገባ በኋላ መኮንኖቹ ያሉበትን ቦታና ጦሩ የተከማቸበትን ሥፍራ ስላዩ፣ ድብልቅልቅ ያለ ተኩስ በመክፈት ያለብዙ ችግር ተልእኮውን ማሳካት እንደሚቻል ተገለጸ። ወታደሮች ለመሸሽ ቢፈልጉ እንኳ ግቢው ዙሪያውን በፈንጂ የታጠረ በመሆኑ እጅ ከመስጠት ውጪ አማራጭ ስለሌላቸው ዕቅዱን ማሳካት የሚቻል መሆኑን አስረድቷቸዋል።

ከአመራሩ መካከል "ተልእኮው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፤ በተለይ የፈንጂ ኤክስፐርት ባለበት ካልሆነ በስተቀር ትልቅ አደጋ የሚያስከትልና ከፍተኛ





መስዋእትነት የሚጠይቅ ነው። በእኛ አቅም ሊፈጸም አይችልም፤ ጓዶችንም እናስጨርስም" የሚሉ ነበሩ። በመሆኑም የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ሮባና ምክትሉ አበጀ የሠራዊቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ድምጽን በድምፅ የመሻር ሥልጣናቸውን በመጠቀም ተልእኮው እንዲሠረዝ አዘዙ።

በዚሁ ሳምንት ጠቅላይ ወታደራዊ አዛዡ ሮባ፣ ጠቅላይ ምክትል ኮሚሳሩ ጋዙና የኃይል አምስት መቶ ኮሚሣር አሰፋ የጎንደርን ጦር ለማጠናከር አሲንባን ለቀው ሄዱ። ወሬው እንደተሰማ በተለይም ነባር ታጋዮች ጠቅላይ አዛዡ ሮባ በመሄዱ ከባድ ሐዘን ተሰምቶን ነበር።

***

ተልእኮው ከተሠረዘ በኋላ ወደ ሀውዜን አካባቢ ወረድን። የሀውዜንን ከተማ ወደ ግራ በመተው በስተምዕራብ ወደ አድዋ አመራንና ነበለት አጠገብ የሚገኝ አዲአርጉድ የሚባል መንደር ደረስን። የሀውዜን ጉዞ ዓላማ፣ በየአመቱ በሚከበረው የሙስሊሞች በዓል ላይ ለመገኘት ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጣ ሕዝብ የሚሰበሰብበት በመሆኑ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ ለማካሄድ ነበር።

ሀውዜን በትግራይ ምሥራቃዊ ክፍል በአጋሜ አውራጃ ትገኛለች። ሀውዜን በሰተደቡብ በኩል ሁለት አውላሎን፣ በስተመዕራብ ደግሞ አድዋንና ተንቤንን የምታዋስን ብዙ ታሪክ ያላት ጥንታዊት ከተማ ናት። ሀውዜን፣ አብርሓና አጽብሓ የሚባሉ ሁለት መንታ ወንድማማቾች ሲያስተዳድሯት የነበረች ናት። እነኚህ ሁለቱ ወንድማማቾች የክርስትና ሃይማኖትን ከተቀበሉ በኋላ ስማቸው ተቀይሮ አይዛና እና ሳይዛና ተብለው መናገሻ ከተማቸው ከሀውዜን ወደ አክሱም እስካሸጋገሩበት ድረስ መናኸሪያቸው ነበረች። ከከተማዋ በስተደቡብ በኩል የእነርሱ ታሪክ ያለበት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድነት፣ በየዓመቱ በዓል የሚያከብሩበት አብርሃና አጽብሐ የሚባል ቦታ አለ። ከተማዋ አጋሜን ተንቤንን ሁለት አውላሎን ከማዋሰኗም በላይ ትልቅ የገበያ ማእከልም ነች።

ሀውዜን ከከተማው አጠገብ ስንደርስ ወደ ምዕራብ አመራን። ከሀውዜን አካባቢ መጥቶ የተከዜ ገባር ከሆነው ወረሂ የሚባለው ትልቅ ወንዝ ዳርቻ ላይ አብሩክ ተባልንና ለመጸዳዳት ተፈቀደልን። (አብሩክ ማለት ባላችሁበት ተቀመጡ ማለት ነው)። ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ እያመራን ስለሆነ የፀሐዩ ሙቀት በጀርባችን በኩል ነበረ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ "አማኑኤል ወደፊት" የሚል መልእክት ደረሰኝና ሄድኩ። ከፊት ሁለቱ የኃይል አመራሮች ጌትነትና የአብኢዮ ለትእዛዝ እየጠበቁኝ ነበር። አጠገባቸው ሲደርስ በወታደራዊ ሥነሥርዓት ቆምኩ።

"ከወንዙ ባሻገር ከሚገኘው አዲአርጉድ የሚባል ትልቅ መንደር የሙስሊሞች ዓመታዊ በዓል ይከበራል፡፡ በበዓሉ ላይ ብዙ ህዝብ እንደሚገኝ





ይታወቃል። በሥፍራው ለሚሰብሰበው ሕዝብ የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማድረግ ከሁለት አባላት ጋር በአብሪነት እንድትሄዱ ተመድባችኋል" አሉኝ። መንደሩ ከነበለት ከተማ በጣም ቅርብ ነው፤ ወንዙ ደግሞ በስተምዕራብ በኩል ነው። ከሁለት አባላት ጋር አብሪ ሆነን ፊት ለፊት ወደሚታየው ጋራ በመሄድ ቦታውን እንቆጣጠራለን።መንደሩ ሰላም መሆኑን ስናረጋግጥ ኃይሏ ተንቀሳቅሳ ወንዙን እንደምትሻገር ገለጹልኝ። እኛ ወንዙን እስከምንሻገር ድረስ ኃይሏ ባለችበት ሆና ቦታ ይዘው እንደሚጠብቁንም ነግረውኛል። ትእዛዙን ተቀብዬ ከጨረስኩ በኋላ ሁለቱ አብረውኝ እንዲሄዱ የተመደቡት ብርሃነ ዓባይና ሮምሀ ወደፊት ተጠሩና ከእኔ ጋር በአብሪነት እንደተመደቡ ትእዛዝ ተሰጣቸው።

ሦስታችንም ከላሽን ኮቭ ጠብመንጃ ታጥቀናል። ኃይሏን ወደኋላ ትተን በፍጥነት ወንዙን ተሻገርንና ዳገቱን መውጣት ጀመርን። ዳገቱን ወጥተን እንደጨረስን ከመንደሩ በስተሰሜን በኩል "ቁም! ማነህ?" የሚል ድምጽ ሰማን።

"እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት ነን፤ እናንተስ እነማን ናችሁ?"አልኳቸው።

"እኛ የትግራይ ተጋዳዮች ነን" ብለው መለሱልን። እነርሱ አስቀድመው በሌላ በኩል መጥተው መንደሩን ተቆጣጥረውት ነበር። እኛ የምንገኘው ታች ሲሆን እነርሱ ደግሞ ከበላያችን ከጋራው አናት አካባቢ ሰፍረዋል። ስለዚህ አንድ ነገር ቢመጣ፣ እነሱ ለማጥቃት አመቺ ከፍታ ላይ ከመሆናቸውም በላይ ገዥ መሬት ይዘዋል። አመቺነቱ ለእነሱ ቢሆንም ያለማመንታት በተልእኳችን መሠረት ወደመንደሩ መግባታችንን እንድንቀጥል ወሰንኩ። እነርሱ ቀጣዩን እርምጃችንን ለማወቅ በነበሩበት ሆነው ወደታች ይመለከቱናል። እኛም ለጥንቃቄ ብረታችን ከትከሻችን አውርደን ደገንንና በጥንቃቄ መጠጋታችንን ቀጠልን። መሣሪያ ከትከሻ አውርዶ መደገን ማለት ለመታኮስ በተጠንቀቅ መሆናችንን ማሳየት ነው።

እኛ አስቀድመን እንዳንተኩስ ተነጋግረናል። ከተተኮሰብን ግን መከላከል ስላለብን ተራርቀን በመሄድ እየተጠባበቅን በድፍረት ወደ መንደሩ መጠጋታችንን ቀጠልን። እነሱም ሌላ ነገር ውስጥ መግባት አልፈለጉም ነበርና ያለ ችግር ከመንደሩ ደረስን። ቁሙ ሲሉን ከነበሩት ዘበኞች አጠገብ ደርሰን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ የእኛ ኃይል ከኋላችን እንደምትመጣ ነገርናቸው። እነርሱም የመጡት እንደኛ በበዓሉ ላይ የኪነት ቅስቀሳ ለማድረግ መሆኑን ተረዳን። የእኛ ኃይል ተከትላን ወንዙን ተሻግራ ጋራውን እየወጣች መሆኗን ሲገነዘቡ የያዙትን ቦታ በሰላም ለቀውልን ከመንደሩ በስተሰሜን በኩል ያለው ተራራ ላይ ሄደው ሌላ ቦታ ያዙ።

ከኋላችን የነበሩት ጓዶች ደርሰው በቦታው ላይ ሲተኩሉን ሦስታችን አብሪዎቹ እንደገና ለኃይሏ የሚሆን ቦታ ለመያዝ ወደ መንደሩ ቀድመን ሄድን። ወደ መንደሩ ስንገባ በድንገት ከእነርሱ የኪነት አባሎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኘን። አንዳንዶቹ ሮምህን በማየታቸው አልተደሰቱም። ምክንያቱም ሮምህ ከወያኔ ከድቶ ወደኢሕአሠ የተቀላቀለ አባላችን ስለነበረ ነው። እኔም ነገሩ ገብቶኛል። እርሱን ወደኋላ አድርጌ እኔና ብርሃነ ሰላምታ እየተለዋወጥን እንዳለ ቀድሞ የማውቀው ሙሉጌታ አብርሃ ከሚባል የእነርሱ የኪነት አባል ጋር ተገናኘሁ።

ሙሉጌታ የታወቀ የወያኔ ኪነት አባል ነበር። ካላሰብኩት አቅጣጫ ከበስተግራ በኩል መጥቶ በድንገት ሲነካኝ ደነገጥኩና ልቤ ምቱ ሲጨምር ተሰማኝ። ዞር ብየ ስመለከት ሙሉጌታን አገኘሁ። ተቃቅፈን በመሳሳም ሰላምታ ተለዋወጥን። ሙሉጌታ ጥሩ ጥሩ ባህላዊ ዘፈኖችን የመጫወት ችሎታ ያለው የኪነት ሰው ነበር። እኔ ግን ገና ሳየው በሐሳቤ የመጣውና ያስደነጠኝ ከእርሱ ጋር የነበረን ትውውቅ ወይም ዘፈኑ አልነበረም። ሙሉጌታ ለብሶት የነበረው የወታደር ኮት ከሚያምረው ቀይ መልኩና አፍሮው፣ እንዲሁም ከተስተካከለ ቁመናው ጋር ግርማ ሞገስ አጎናጽፎታል። ገና ቀና ብዬ ሳየው ነበር ፊቴ ተለዋውጦ ሰውነቴ





የተንቀጠቀጠው። መረበሼን እንዳያውቅብኝ አንገቴን ወደጎን ዞር አድርጌ ወደሌላ አቅጣጫ ማየት ጀመርኩ። ትውውቃችን ገና ወደ ትግል ከመውጣታችን በፊት ነበር፤ አዲግራት እያለንም ሆነ በትግል ጊዜ በግሎማከዳ ወረዳ ተገናኝተናል።

ሙሉጌታን ሳየው ሰውነቴ የተረበሸበት ምክንያት፤ ከታላቅ ወንድሙ ከመቶ አለቃ ፍጹም አብርሐሄ ጋር መመሳሰላቸው ነበር። ከአየር ወለድ አባሎች ጋር ወደ ኢሕአሠ የተቀላቀለው የመቶ አለቃ ፍጹም፣ ጎንደር አዲስ ዘመን አውራጃ እብናት ላይ የተሠዋ ምርጥ ጓድ ነበር። ይህንን ግን ታናሽ ወንድሙ ሙሉጌታ አያውቅም።

የመቶ አለቃ ፍጹምና እኔ በኃይል ሶስት ውስጥ አብረን ነበርን። መቶ አለቃ ፍጹምና ወንድሙ ሙልጌታ በመልክም፣ በቁመናም በጣም ይመሳሰላሉ። ሁለቱም በጣም መልከመልካሞችና ቁመናቸው ያማረ፣ እንዲሁም ጥሩ የወታደር ሰውነት ያላቸው ነበሩ። ሙሉጌታን ድንገት ሳየው የተሰዋው ጓድ ከሞት ተነሥቶ የመጣ መስሎኝ ነበር የደነገጥኩት።

መቶ አለቃ ፍጹም፣ ከመሰዋቱ በፊት ከትግራይ ተነሥተን ወደ ጎንደር ለመሄድ በረሐውን ስናቋርጥ በለሳ እስከምንደርስ ድረስ ብዙ ስንጨዋወት ነበር። እርሱ ሰፊ ወታደራዊ ልምድ ስለነበረው ይመክረኝና ያስተምረኝ ነበር። ከአየር ወለድ ጓዶቹ ጋር ወደ ኢሕአሠ እንደመጣ ለብቻው በወታደራዊ ስልጠና አካባቢ እንዲቆይ የመድረጉ ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል አስብ ነበረ። በዚያ የጎንደር ጉዞ ላይ አብረን እያለን ምክንያቱ ምን እንደሆነ ጠየቅኩት።

"ወንድሜ ከወያኔ ጋር ስላለና፣ እንዲሁም ያለሁበት ቦታ ከቤተሰቦቼ መንደር ቅርብ ስለሆነ፣ 'ምናልባት ስለትግሉ ከወንድምህም ሆነ ከቤተሰብህ ጋር ለመመካከር ከፈለግህ በቅርብ ልታገኛቸው ትችላለህ' ብለው ሁኔታዎችን ሊያመቻቹልኝ ነው። እንዲሁም 'ሌላ አማራጭ ካለህም አናስገድድህም፤ በደንብ አስብበት' ብለው ጊዜ ሊሰጡኝ ብለው ነበር" ብሎ በዝምታ ተዋጠ። "እኔ ግን ከመጀመሪያ ከኤርትራ ስወጣ አብረውኝ ከነበሩ የአየር ወለድ አባል ጓዶች ጋር

ለመታገል እንጂ፣ከእነርሱ ተነጥዬ ወደ ሌላ ድርጅት የመግባት ዓላማ አልነበረኝም" አለኝ አፍታ ቆየት ብሎ። ከኢሕአሠ ሌላ ከማንም ድርጅት ጋር እንደማይሰለፍና ከወንድሙም ሆነ ከቤተሰቡ ለመገናኘት ፍላጎት እንደሌለው ለአመራሮች እንዳስታወቃቸው፣ ነገረኝ። ወንድሙም ሆነ እርሱም የየራሳችው ዓላማ አላቸው። የየራሳቸውን እምነት መከተልም ይችላሉ። ይህንኑ እንደነገራቸውና ጉዳዩ በዚያው እንዳለቀ አጫውተኝ ። ከዚያ በኋላ በኃይል ሦስት በምክትል ጋንታ መሪነት ተመድቦ አብረን ቆየን።

ወንድሙን ሙሉጌታን ሳገኘው ፍጹምን አስታውሼ ትካዜና ሐዘን ተቀሰቀሰብኝ።ጌትነትን ጠራሁትና ስለሙሉጌታ ማንነት ነገርኩት። ጌትነትም የአየር ወለድ አባል ስለነበረና የሙቶ አለቃ ፍጹምን በደንብ ስለሚያውቀው፣ ሙሉጌታን ሲያይ ድንግጦ " ቁጭ ራሱን ፍጹምን?! ወይ ጉድ!!" በማለት አብሮኝ ተከዘ።

***





ድላይ

*መቼም ቢሆን መቼም ፍፁም፤*

*ጊዜ፣ ቦታ እና ፍቅር፣ አንድ ላይ ማገበር ከፍለው፣*

*ጸዋ ጠጥተው አያውቁም፡፡*

*ሮበርት ብራውኒንግ*

ከትንሽ ጊዜ በኋላ የመጣንበትን ዓላማ ለመፈጸም እንችል ዘንድ ለእያንዳንዱ ጋንታ ምድብ ቦታ ተሰጠ። እንደታሰበውም እጅግ በርካታ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ከትለያዩ ከተማዎች መጥተዋል። እኛ ከመስጊዱ በስተደቡብ በኩል ስንሆን፣ የወያኔ ኃይል ደግሞ በስተሰሜን በኩል ሰፍረዋል። የእኔ ጋንታ የያዘችው ቦታ ለመስጊዱ በጣም ቅርብ ስለነበረ ከተወሰኑ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ከሌሎች የወያኔ አባሎች ጋር አልተገናኘንም። ሌሎች ጋንታዎችም ቢሆኑ ከአመራሩ በስተቀር መቀራረብናመነጋገር አልነበራቸውም። ዋርዲያ ከተቀመጠበት ትልቅ ድንጋይ ስር ተቀምጬ ስለ ፍጹም አብርሃ እያሰብኩ ነበረ።

ኃይል መሪዎቹ ጌትነትና የአቢኢዮ እኔ ወደነበርኩበት ቦታ ሲመጡ አየኋቸው። አመራሮች ስለሆኑ ሁለቱም የመገናኛ ሬዲዮ ይዘዋል። እኔን ፍለጋ እንደመጡ ሲገባኝ በፍጥነት ተነሥቼ ብረቴን አስተካክዬ ጠጋ አልኩ። የአብኢዮ እየሳቀ "ወድ ሐፍተይ አንድ ነገር ለድላይ ትሰጣታለህ" አለኝ ፈገግ ብሎ በጣም የሚያምሩ ጥርሶቹን እያሳየኝ። ጌትነትም እንዲሁ እየሳቀ በፈገግታ ያየኛል። ጌትነት ረዘም ያለ ቀይ ሆኖ አፍንጫው ሰልካካ ነው። የአብኢዮ ደግሞ ጠቆር ብሎ እግሮቹና እጆቹ በጣም ረዣዥምም ናቸው፤ በረሐ ከመግባቱ በፊት የታወቀ የእግር ኳስና የመረብ ኳስ ተጫዋች እንደነበረ ሰምቻለሁ።

የአቢኢዮ "ወድ ሐፍተይ" ብሎ የሚጠራው በጣም የሚወደውን ሰው ነበር። "ምንድነው የምሰጣት? እየቀለዳችሁ ነው?" አልኩ ሳቃቸው እየተጋባብኝ። "የለም ለመቀለድ አይደለም የመጣነው፣ ድላይ ልብሷን ለማጠብ ወደ ወንዝ ስለምትሄድ የአንተን ሱሪ ለጊዜው እንድትሰጣት ልንጠይቅህ ነው" አሉኝ።

"እኔስ ምን ልልበስ?" አልኳቸው የሚሉት ግራ ገብቶኝ።

"እንደልማድህ ነጠላውን ፍታውና አገልድም" አለኝ የአብኢዮ አሁንም እየሳቀ። (እንደልማድህ ማለቱ ከወሎ ስመለስ በአግልድም ወደ አሲምባ የገባሁትን አስታውሶ ነው።)

ድላይ ለብቻዋ ልብስ ለማጠብ ለምን እንደፈለገችና የእኔን ሱሪ ለምን እንደምሰጣት አሁንም አልገባኝም። በወቅቱ አዲስ የተሰፋ ቁምጣና ኮት ወታደራዊ ልብስ ነበረ የለበስኩት። የአብኢዮና ጌትነት ከጎኔ ቆመው መልሴን እየጠበቁ ነበር።

በመጀመሪያ ሱሪህን ለድላይ አውሳት ሲሉኝ ለቀልድ መስሎኝ ነበር። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ግን ድላይ ራሷ መጣች። ሰውነቷ ደከምከም፤ ፊቷ ጥውልግልግ ብሏል። ጠብመንጃ አልያዘችም፤ ሽጉጥ ብቻ ነው የታጠቀችው። ቀና ብዬ ስመለከታት ፈዘዝ ብላ ታየኛለች። አሁንም ለምን ብቻዋን ሄዳ ልብስ እንደምታጥብ አልተረዳሁም። በተሰጠኝ ትእዛዝ መሠረት ግን ሱሬዬን አውልቄ ሰጠኋትና ለራሴ ነጠላዬን አገለደምኩ።

"በጣም አመሰግናለሁ!" ብላኝ ሱሪዬን ይዛ ወደወንዝ ወረደች።

እኔ አገልድም ታጥቄ ሥራዬን ቀጠልኩ። በመስጊዱ አካባቢ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቧል፤ የወያኔ ኪነቶችም ዘፈን ጀምረዋል። በጣም ደስ የሚል የማሲንቆ ድምፅ ሰማሁ፤ የማሲንቆውን ምት የማውቀው ይመስለኛል እያልኩ በሐሳብ ተመስጬ ቀረሁ። በደንብ ላዳምጠው ፈልጌ ጥቂት ጠጋ ስል በእውነትም የማውቀው ደምፅ ነበር። ዘፋኙ ገብረጻድቅ ይባላል፤ በረሐ ከመውጣቴ በፊት የገብረጻድቅ ዘፈኖች ይማርኩኝ ነበር። ያኔ እርሱ አስመራ ሆኖ ነበር





የሚዘፍነው። ድምፁ፣ ዜማውና የማሲንቆ አመታቱም ጭምር በጣም ያስደስተኛል። ሆኖም ገብረጻድቅን ድምፁን እንጅ በአካል አላውቀውም፤ ስለአየሁት በጣም ደስ አለኝ ።

የበዓሉ ሥነ ሥርዓት ሲፈጸም የእኛ ሰዎች ተፈላጊውን ትምህርት ለሕዝቡ አስተምረውና የቅስቀሳ ሥራ ሠርተው ጨርሰው ነበር። ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ድላይ ከወንዙ መጣችና ሱሪዬን መለሰችልኝ። በጣም እንደደከማት ታስታውቃለች፤ "ጓድ አማኑኤል በጣም አመሰግናለሁ!!" አለች ደጋግማ።

"ለመንቀሳቀስ ተዘጋጁ!" ተባለና ጦሩ ለመንቀሳቀስ ተዘጋጀ። ከአመራሮች በስተቀር ሌሎቻችን ወዴት እንደምንሄድ አናውቅም። የእኛ ጋንታ አባላት፣ ትጥቃችንን ታጥቀን እቃዎቻችንን እንዳንረሳ አጣርተን ስንጨርስ ለመንቀሳቀስ ከጋንታ መሪው ከእንግዳ ወርቅ ትእዛዝ እየተጠባበቅን ነበር። ሁለቱ ከበስተጀርባችን ወንዝ አፋፍ ላይ የነበሩት ጋንታዎች ቀድመውን ተንቀሳቅሰው በፊታችን እያለፉ ወደምዕራብ በኩል ወደ እንባሰነይቲ ተራራ አመሩ። እንባሰነይቲ ተራራ፣ ከነበለት በስተሰሜን በኩል ያለው ትልቅ ተራራ ነው። እነዚያ ሁለት ጋንታዎች ጨርሰው እስከሚያልፉ ድረስ፣ እኛ ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነን ትእዛዝ እየጠበቅን ነበር። ሜዳውን ጨርሰው የነበሉትን ከተማ ወደግራ ትተው ዳገቱን በመያዝ ሲጓዙ እኛም "ተንቀሳቀሱ!" የሚል ትእዛዝ ተሰጠን።

እንደተለመደው ጋንታ መሪው ከፊት፣ ምክትል መሪው ከመካከል ሆነን በሰልፍ ጉዞ ጀመርን። እኔ በምክትልነቴ በመሀል ሰልፍ ሆኜ ከነበለት ወደ ብዘት የሚወስደውን ትልቅ መንገድ ልናቋርጥ ስንል ሁለቱ የኃይል መሪዎች እያወሩ፣ ድላይም በጣም ድክም ብላ አጠገባቸው አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ አየኋቸው። እኛ ግን በመንቀሳቀስ ላይ ነበርን። አጠገባቸው ስደርስ ጠሩኝ።

ከተሰለፍኩበት ወጥቼ ወደ እነርሱ ስሄድ ጌትነት "ድላይን ይዘህ ወደ ነበለት ከተማ ትገባለህ። እዚያ ከተማ ውስጥ እርሷ የምትፈልገው እቃ ስላለ እቃውን ይዛችሁ በቶሎ ወደ ኃይሏ ትመለሳላችሁ። ከእኛ እንደተለያችሁ እንደ

አካባቢው ሕዝብ ተመሳሰሉ፤ ተጋዳላዮች መሆናችሁን ማንም ሰው ማወቅ የለበትም። ወደምትፈልጉት ቤት የምትገቡት በጨለማ ነው። ስለዚህ ከአሁኑ ጀምራችሁ ነጠላችሁን ፍቱና የአገር ቤት አለባበስ ለብሳችሁ ተጓዙ" አለኝ።

የአብኢዮ ደግሞ እንደተለመደው አባባሉ "ወዲ ሐፍተይ ጠንቀቅ በል፤ የክላሽን መጠበቂያህን ሁልጊዜ አውቶማቲክ ላይ አድርገው። ጓዲቷ አሟት ደከማለችና ተንከባከባት" አለኝ።በዚያን ቀን ኃይሏ ማታ የምትሄድበትን ቦታና እንዲሁም ድንገት በጨለማ ከመጣን የምንጠቀምበትን የምስጢር የይለፍ ቃል ነገሩኝ። ይህ የምስጢር ቃል ለአባላት ብቻ የሚሰጥ ዋርድያ "ቁም! ማነህ?" ሲል ጓድ መሆንን ለመግለጽ የሚነገር መጋቢያ የይለፍ ቃል ነበር።

እኔ ካላሽኔን ይዣለሁ፤ ድላይ ግን ሽጉጥና ቦንብ ብቻ ነው የታጠቀችው። ወገቧን ስላመማት የክላሽን ትጥቅ ለጊዜው ስለማትችል አውርዳለች። አሁን ሁለታችን ከኃይላችን ተነጥለን ጉዟችንን ወደነበለት ከተማ አደረግን። በተሰጠን ትእዛዝ መሠረት በአለባበሳችን ከሕዝቡ ጋር ተመሳሰለናል። ከተማው ነጻ የወጣ ነው፣ ነገር ግን ከኛ አባላት በተጨማሪ ብዙ ብረት የያዙ የወያኔ አባላትም ይገኙበታል። ስለዚህም ይመስለኛል አስፈላጊ ወታደራዊ ጥንቃቄ ማድረግእንዳለበኝ የተነገረኝ።

ትንሽ እንደተጓዝን "ልጸዳዳ?" አለችኝ። አሺታየን በአንገቴ ገለጥኩላት። ለጥበቃ እንዲመቸኝ በቀኝ በኩል ወደነበረችው ትንሽ ኮረብታ ወጣሁና እርሷ ከእኔ በስተጀርባ ሆና እንድትጸዳዳ አደረግሁ። ተጸዳድታ እንደመጣች ጉዟችንን ቀጠልን። "ድላይ! ለመሆኑ ወደየት ነው የምንሄደው? እንቺስ የምትፈልጊው እቃ ምንድን ነው?" ብዬ ጠየኳት።

"የምንሄደውማ እንደነገሩህ ወደነበለት ከተማ ነው። የምንሄድበት ምክንያት፣ ከተማ ውስጥ ያሉ ሴት አስተማሪዎችን ፍለጋ ነው። እኔ ለግሌ ከእነርሱ የምፈልገው እቃ ስለአለ እሱን ተቀብለን እንመለሳለን" አለች።





በጣም ግራ ገባኝ " ከሴት አስተማሪዎች የምትቀበዪው ወይም ደግሞ የምታመጪው ምን እቃ ነው?" ብዬ እንደገና ስጠይቃት ሳቀች።

"አንተ አታውቀውም፣ የሴት እቃ ነው፣ አማኑኤል" አለችና እንደገና አከታትላ "አማኑኤል እኔ እኮ አምኛል። ቀኑን በሙሉ ያንተን ልብስ ለብሼ እንደዋልኩ ታውቅ የለ። የእኔ ሱሪ ተበላሽቶ ስለነበረ ለማጠብ ነበር የአንተን ለብሼ ወደ ወንዝ የወረድኩት" ብትለኝም ችግሯን በትክክል አልተረዳሁትም።

"ታዲያ ምንድን ነው የምናመጣው?" እንደገና ጠየቅኋት፤ የማወቅ ፍላጎቴም ጨመረ።

እንዳልገባኝ ተረዳችና "የምናመጣው እቃ ሞዴስ ይባላል" አለችኝ።

"ሞዴስ ምንድነው?"

"ሞዴስ ሴቶች ብቻ የሚጠቀሙበት የሴት እቃ ነው። ወንዶች ብዙም አታውቁትም" አለችና ለአፍታ ያህል ስታስብ ቆየች። "ወንዶች እኮ እንደዚህ ዓይነት ነገር ስለማታውቁ ታድላችኋል" በድምጿ ውስጥ ሐዘን ተሰማኝ፤ ችግሩ ወይም ሕመሟ ቀላል እንዳልሆነ ተረዳሁ። ግን ምን እንዳመማት በትክክል አልተረዳሁም። "ሞዴስ" የሚለውን ቃል ስሰማ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበረ። አሁንም ግን የሴት እቃ ከመሆኑ ሌላ ምን እንደሆነና፣ ለምን እንደሚጠቅም አልገባኝም።

"ታዲያ ሞዴስ ያሽልሻል ማለት ነው?" አልኳት።

"አያሽለኝም፤ ግን ልብሴን ከመበላሸት ይጠብቅልኛል፤ ማለት ይከላከልልኛል። በየቀኑ ልብሴን ለማጠብ እንደማልችል አንተም ታውቃለህ" ብላ ስትገልጽልኝ የእኔን ሱሪ ለምን ተውሳ እንደዋለች ብልጭታ ቢጤ ታየኝ።

ወደ ከተማው ስንዳረስ ቀኑ ጨለምለምአለ፤ አልፎ አልፎም ዳመና ይታያል የነጎድጓድ ድምፅም ይሰማል። የአስተማሪዎች ቤት ከከተማው በስተምስራቅ በኩል ነበር። ሰው እንዳያየን ዳርዳሩን ይዘን አካባቢው ደረስን። ከቤቱ አጠገብ ከመድረሳችን በፊት ቤቱን አመላከተችኝና እርሷን እዛው ቦታ ትቼ ቀስ ብዬ ወደቤቱ ተጠጋሁ። አካባቢውን በሙሉ በጥንቃቄ ተመልክቼ፣ የቤቱን ዙሪያ ገባ

ከአጣራሁ በኋላ አካባቢው ሰላም መሆኑን ስገነዘብ ድላይን ጠራኋት። ድላይን ስጠራት የ ውሾች ጩኸት ተሰማን። "እንግዲህ አንቺ ገብተሽ የምትፈልጊውን እቃ ይዘሽ እስከምትመለሽ ደጅ እጠብቅሻለሁ" አልኳት።

ድላይ ውስጥ ገብታ ምንም ያህል አልቆየችም፤ ፊቷ ከስል ብሶ ወዲያውኑ ተመልሳ መጣች።

"ምነው የምትፈልጊውን እቃ አላገኘሽም?"ብዬ ጠየቅኋት።

"አላገኘሁም፤ አማኑኤል ይሄ ወር የኔ ወር አይደለም። ምንም አልታደልኩም" በማለት በትካዜ፣ በድካምና ተስፋ በመቁረጥ ስሜት መለሰችልኝ።

"ምነው ድላይ" አልኳት ሐዘኗ እየተሰማኝ ።

"እስተማሪዎቹ ደሞዝ ለመቀበል ወደ አድዋ ሄደዋል አሉኝ" አለችኝ አሁንም እንደተከዘች፡፡

ስሜቷ በግልጽ ይታያል፤ አነጋገሯም በጣም ቅዝቅዝ ያለ ነው። እኔም የሐዘኗ ተካፋይ ሆንኩኝ። ነገር ግን እንዴት ብዬ እንደማጽናናት ግራ ገብቶኝ "አይዞሽ በርቺ ድላይ፣ምንም ማድረግ ስለማይቻል ጓዶች ወደአሉበት ቦታ እንሂድ" አልኳትና ኃይሏ ታድርበታለች ወደ ተባለው የኤምባሲኒት ተራራ አካባቢ የመልስ ጉዟችንን ቀጠልን።

ጨለማው ከብዷል፤ ሰማዩና ምድሩ በጨለማ ተውጦ ከመብረቁ ብልጭታ ከሚታየው ብርሃን በስተቀር የሚታይ ነገር አልነበረም። ነጎድጓዱ አላቆመም። በጣም እንደ ታመመችና እንደደከማት በሚገባ አውቄአለሁ፤ ነገር ግን የግድ መመለስና ጓዶች የሚያድሩበት ቦታ ሳይነጋ መድረስ ይኖርብናል። የድላይ ሕመምም አሳሰበኛል፤ ምን ሊከተል እንደሚችል መገመትም አስቸጋሪ ሆኖብኛል። ስለዚህ የግድ ከጓዶች ጋር መገናኘት እንዲሚኖርብን ወሰንኩ። ከከተማ የሚወጣውን ትልቅ መንገድ አቋርጠን ወደግራ በኩል ሄድን። ከዳገቱ ከመድረሳችን በፊት ገና ሜዳው ላይ እያለን "ልጸዳዳ?" አለችኝ። ሕመሟን ስለተረዳሁ





ያለማመንታት ባለሁበት ቦታ ቆምኩ፤ ወደ ትናንሾቹ ቁጥቋጦዎች ውስጥ ገባ ብላ እንድትጸዳዳ ነገርኳት። ተጸዳዳችና ተመለሰች።

በጣም ጨልሟል፤ በዛ ላይ ዝናቡ መጣሁ መጣሁ ይላል። በተለይ ድላይ በዚህ ሁኔታዋ ከፊታችን የሚጠብቀንን ትልቅ ተራራ እንዴት ልትወጣው እንደምትችል ሳስበው ጨነቀኝ። ጥቂት እንደሄድን እንደገና ለመጸዳዳት ጠይቃኝ አልፍ ብዬ ጠበቅኋት። የፈራሁት ዝናብ ነጎድጓዱን የባሰ እያኾጎደጎደና መብረቁን እያብለጨለጨ መጣ። ኃይለኛ ዝናብ መጣል ጀመረ። ድርግም ያለ ጨለማና ሀይለኛ ዶፍ ዝናብ! ከዝናቡ ጋር የሚጋፋው ነፋስ ቅዝቃዜው አካላችንን አቆራመደው፤ ውሽንፍሩን በፊታችን ላይ ሰረጨው ዓይኖቻችንን መግለጥ እንችገር ጀመር። ከድቅድቅ ጨለማው ጋር ፊታችንን የሚገርፈው ውሽንፍር ጉዟችንን የእውር ድንብር አድርጎት ትግል ገጠመን። ከ ቀኑ ድካም አላረፍንም፤ ከፊታችን የሚጠብቀንም ትልቅ የተራራ ጉዞ ነው። እኔስ እንደምንም እችለዋለሁ፤ ለድላይ አዘንኩላት፤ ይህ ጉዞ ባ ጠወሊጋትና ባዳከማት ህመሟ ላይ ሲጨመርበት እንዴት እንደሚያደርጋት እያሰብኩ ከልቤ አሳዘነችኝ።

ወገቧን ስለታመመች ጠመንጃ እንዳትይዝ ተደርጓል፤ ይህን ዝናብና የተራራ መንገድ ግን በምንም መንገድ ልናስቀረው አንችልም። በዚያ ላይ አገኛለሁ ብላ ብዙ የለፋችበትን እቃ እንኳ ልታገኝ ባለመቻሏ ሞራሏን ምን ያህል እንደሰበረውና እቅጭም ብሎ ይነበረውን ፊቷን እንዴት የባሰ እንዳጠቆረው ተመልክቻለሁ። በአጋጠሟት ድርብርብ ችግሮች አካሏም አእምሮዋም ስለተዳከመእንኳንስ በፍጥነት ለመጓዝ በመደበኛ እርምጃም ለመሄድም አልቻልንም። አንዳንዴ እየደገፍኳት አንዳንዴ ደግሞ እጇን ይዤ እየጎተትኳት ተጠጋግተን መሄድ ጀመርን።

ዝናቡ ለአፍታ እንኳ አላቋረጠም፤ በግራ እጄ ክላሼኔን፣ በቀኝ እጄ የግራ እጇን ጨብጫለሁ። ከፊትና ከኋላ ተከታትለን መጓዛችንንም አላቋረጥንም። ከነፋስና ከውሽንፍር ጋር የተቀላቀለው ኃይለኛ ዝናብ እየወረደብን ቢሆንም የምናርፍበት ቦታ በአቅራቢያችን አላገኘንም። ለመፈለግም ጊዜ የለም፤ ሳይነጋ

ጓዶች ከሚያድሩበት አካባቢ ካልደረስን መጠፋፋት ሊመጣ ይችላል። የነበርንበት አካባቢ ጸጥታው አስተማማኝ እንዳልሆነም ተነግሮኛል። እንደምንም ብዬ የድላይን ነፍስ ይዤ መግባት ነበረብኝ። ከዚህ የተሻለ ምንም አማራጭ አልነበረኝም።

የማደርጋት ነገር ጠፋኝ፣ አዝያት ብሄድ ደስ ባለኝ ነበር። ነገር ግን ጠመንጃዬን ከእጄ መለየት እንደሌለብኝ እንዲያውም መጠበቂያውን አውቶማቲክ ላይ እንዳደርገው የአብኢዮ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል። ምንም ነገር ቢመጣ ጠመንጃዬን በፍጥነት ለመጠቀም ተዘጋጅቼ መያዝ አለብኝ። በእርግጥ እጆቼ በዝናብና በቅዝቃዜው ተቆራምደው የሚታዘዙ አይመስሉም፤ ቢሆንም መሞከሬ አይቀርም። ታዲያ ድላይን ምን ላድርጋት?! ምን ልሁንላት?! ጭንቀት ብቻ ዋጠኝ። አልፎ አልፎ በሚያበራው የመብረቅ ብልጭታ ተራራውን ብዙ እንደወጣን አወቅሁ፣ ጓዶች ያሉበት ለመድረስ ምን ያህል እንደሚቀረን ግን ለመገመት ከበደኝ። ድካሙና ብርዱ እየተሰማኝ መጣ፤ እንዲሁም ስለድላይ ጤንነትና ስለደኅንነታችን በጣም በመጨነቄ ይመስለኛል አእምሮዬም ማሰብ እየከበደው መሆኑ ይታወቀኛል። ድካሙን መቋቋም ሲያቅተኝ ደግሞ ድላይን አስባትና ራሴን እወቅሳለሁ፤ እንደምንም አበረታና እርሷንም ለማበረታታት እሞክራለሁ።

ወደተራራው ጫፍ እየቀረብን መጣን፣ ድካሟና ህመሟ ከእርሷም በላይ እየተሰማኝ ሁኔታዋ አሳቀቀኝ። ድካሟን ለማቅለል በማሰብ እየጨነቀኝም ቢሆን "አይዞሽ ድላይ ደርሰናል" እላታለሁ። ይሄ ሁሉ ሲሆን እርሷ "እሺ" ከማለትና የቻለችውን ያህል አቅሟን በማሟጠጥ ከመታገል ውጪ አንዴም ስታማርር አልሰማኋትም። "አይዞሽ ደርሰናል" ስላት ከመቶ ጊዜ በላይ ሳይሆን አይቀርም። እርሷም የጭንቀቴን ያህል እንደምለፈልፍ የገባት ይመስለኛል።





ወደ መዳረሻችን አካባቢ በአጫጭር ጊዜ አከታትላ ለመጸዳዳት እየጠየቀችኝ መቆም ስናበዛ ፈራሁላት። ነፋሱ እና ዝናቡ፣ ውሽንፍሩና ቅዝቃዜው እየበረታ ነው። "አሁን እዚህ ቦታ ላይ ራሷን ብትስት ወይ አንድ ነገር ብትሆን ምንድነው የማደርገው?" የሚል ጭንቀት ወጥሮ ያዘኝ። አቀበቱን ለመጨረስ እየተቃረብን መሆናችንን በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ብቸኛው ባለውለታችን በሆነው የመብረቅ ብርሃን አየሁ። በመብረቁ ብልጭልጭታ ለአፍታ ተመለከትኳት፤ በቃል ባንነጋገርም በዓይኖቻችን የመድረሳችንን የተስፋ መልእክት ተለዋወጥን።

ተራራውን ከጨረስን በኋላስ? መቼም የዚያ ሌሊት ጭንቀቴ ማለቂያ የሌለው ነበረ፤ ከተራራው እናት ወዲያ ጓዶች ለአዳር የሰፈሩበት ቦታ ምን ያህል ርቀት ያስኬድ ይሆን? ወደሚል ሌላ ሐሳብ ተሻገርኩ። ምናልባትም ከወጣነው ተራራ ወዲያ ሌላ ተራራም ይኖር ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ለአዳር የሚመረጠው እንደዚያ ዓይነት ቦታ መሆኑን አውቃለሁ።

ድላይ አቀበቱን መጨረሳችን ሲታወቃት ድካሟ በረታባት መሰለኝ እግሮቿን መዘርጋት እያቃታት ርምጃዋን እየጎተተች እንደመቆም አለች። በግራ እጄ ጠመንጃዬን፣ አስተካከልኩና በቀኝ እጄ እጇን ይዤ ጎተትኳት። በአካሄዷ ላይ ያየሁት አዲስ ነገር ደግሞ አሳሰበኝ፣ በሐሳብ እንደተዋጥኩ በድንገት የውሾች ጩኸት የሰማሁ መሰለኝ፤ የሰማሁትን ለማጣራት ጆሮዎቼን አቁሜ ስጠብቅ ድምፁ ሳይደገም ቀረ። እርሷም ጆሮዎቿን አቁማ የጠፋውን ደምፅ እየጠበቀች እንደሆነ ገብቶኛል። ሁለታችንም ጆሮዎቻችንን አቁመን ትንሽ ቆም ብለን ጠበቅን። ምንም ነገር አልነበረም። የዝናቡና የንፋሱ ድምፅ ይሆን ያሳሳተን? ብዬ አሰብኩ፣ ከጉጉቴ ብዛት እንደሆነ እንጂ እርግጠኛ መሆን አቃተኝ። የድላይን ስሜት መገመት በጣም ቀላል ነበረ፤ ከእኔ በላይ ድምፁን እንድገና ለመስማት እንደጓጓች አውቃለሁ። ከአስቸጋሪው የአየር ሁኔታ በተጨማሪ ህመሙና ድካሙ አቅሟን ሁሉ አሟጦታል። "አፈር ልሁንልሽ፣ የኔ እናት!" አልኳት በውስጤ።

ዳገቱን ጨርሰን የሜዳውን መንገድ ስንጀምር ተመልሶ አልመጣ ያለውን የውሾች ድምጽ ለማጣራት፣ እጇን ለቅቄ ቀደም ብዬ ወደፊት ተራመድኩ። እርሷም ከየት እንዳገኘችው በ ገ ረ መ ኝ አዲስ ኃይል ተራምዳ ተከትላኝ ደረሰችና ጎን ለጎን መሄድ ጀመርን። አቀበቱ በማለቁ የተሰማት ደስታ ሜዳውን እንደልብ እንድትሄድ ኃይል ሳይጨምርላት አልቀረም። ዝናቡ አሁንም እንደቀጠለ ነው።

ድላይ ራሷን ችላ በመበርታቷ፤ ትኩረቴ ጓዶችን ስለምናገኝበት ቦታና ወደውሻው ድምፅ እንዳደርግ ረዳኝ። ያ በጉጉት ስንጠብቀው የነበረ ድምፅ ተደገመ። አሁን አንዴ ጮሆ አልቆመም፤ እንዲያውም የብዙ ውሾች ድምፅ ተከታተለ። የውሻን ጩኸት ትርጉም ሁለታችንም ከልምድ ስለምናውቀው፣ ሳንጠያየቅና ሳናመነታ በቀጥታ የውሾቹን ጩኸት ወደሰማንበት አቅጣጫ አመራን። ነጎድጓዱን እየቀደመ አልፎ አልፎ በሚመጣው የመብረቅ ብርሃን ራቅ ብለው ጉች ጉች ያሉ የገጠር ቤቶች እየታዩን ይጠፋሉ።

ትልቅ እፎይታ ተሰማኝ፤ ዞር ብዬ ስመለከታት በዚያ ሁሉ መከራ ውስጥ ከነበረና ያለ ዕረፍት በጉዞና በህመም ተደራራቢ ስቃይ ከዳመነ ገጽታ ይታያል ተብሎ የማይጠበቅ ፈገግታዋ አስደነገጠኝ። ፈገግታዋ በጭንቀት የወጣ እንደሆነ ባውቅም ጥንካሬዋን አደነቅሁላት። "አይዞሽ ጓዲት፣ ተወጥተሸዋል" ብዬ አንገቷን አቀፍኳት። አቀፈችኝ። ተያይዘን በቅርብ ባገኘነው ቤት ደጃፍ ላይ ቆመን በሩን አንኳኳን።

አንዲት እናት በሩን ከፈቱልንና "ግቡ" አሉን። ልብሳችንና ሰውነታችን በዝናብ መበስበሱን ሲያዩ በጣም አዘኑ። በሚችሉት መጠን አስተናገዱን። እቤቱ ውስጥ ሁለት ሰዎች ተኝተዋል። አንደኛው ወጣት ቀና ብሎ ሰላምታ ከሰጠን በኋላ ዓይኖቹን ገልጦ የምንነጋገረውን ያዳምጥ ጀመረ።





ነጠላዎቻችንን ጨምቀን አራገፍን። ሴትዮዋ እሳት እያይዘው እንድንሞቅ ጠርተውን ወደ እሳቱ ዳር ሄድን። ድላይ ራሷን ችላ መቀመጥ አቅቷት ስትቸገር አይቼ የባስ አንጀቴን በላችኝ። ላግዛት ስንቀሳቀስ እንደምንም ብላ ቁጭ አለችና በኃይል ተነፈሰች። በጣም ነበር የደከመችው።በሴትዮዋ ገጽታ ላይ የነበረው ሐዘን በጉልህ ይታያል። "አይ ልጆቼ ምን በወጣችሁ ነው ይህን ሁሉ መከራ የምታዩት? አባት እናት አሳድገዋችሁ፤ እናንተ ምንም ሳይቸግራችሁ ቤታችሁን ጥላችሁ እንደዚህ በረሐ ለበረሐ መንከራተት ምን ይባላል?!" ብለው በሐዘን ጭንቅላታቸውን ይዘው መልስ የማይጠብቁበትን ጥያቄ አቀረቡ።

በመጀመሪያ ስንገባ የየትኛው ድርጅት አባላት መሆናችንን ስላላወቁ ነበር ብዙ ከመናገር ተቆጥበው እየተጠነቀቁ የቆዩት። በአማርኛ ስናወራ ሲሰሙ ግን ማንነታችንን ለይተዋል። ከዚያ በኋላ ነበር የሴትዮዋ ልጅ ተነሥቶ "የእናንተ ሰዎች እኮ ወደላይ ሊወጡ አሰበው ዝናብ ሲዘንብ እዚህ መንደር ዐርፈዋል" አለ።

"የት?" ሁለታችንም ጠየቅን።

"እዚህ ከእኛ ቤት ፊት ለፊት ያለው ግቢ ናቸው"

"እንዴት አወቅህ?" የማጣራቱን ሥራ ድላይ ለእኔ ተወችልኝ።

"እንግዶች ስለአሉብን፣ ራት አምጡ ተብለን ይዘን ሄደናል"

"ይሄማ በጣም ጥሩ ነው፣ ግን የእኛ ሰዎች ለመሆናቸው እርግጠኛ ነህ?" አልኩት።

"አዎ የእናንተ ሰዎች ናቸው"

"የእኛ ሰዎች መሆናቸውን እንዴት ለየህ?"

"እንዴት አላውቅም? የእናንተ ሰዎች የሚያወሩት አማርኛም ትግርኛም ነው። ልክ እንደናንተ ድብልቆች ናቸው። እንዴት ይሄንን መለየት ያቅተናል? " ብሎ እየሳቀ ጠየቀኝ።

"ታዲያ ጓዶች ያሉበትን ቤት ል ታ ሳየን ትችላለህ?" ስለው ወዲያው ተነሣ።

ሴትየዋ ግን በጣም አዝነውልናል "አረ ልጆቼ ባካችሁ ራት ብሉና ትሄዳላችሁ?!" አሉ፤ አሁንም ሐዘናቸውና ጭንቀታቸው ፊታቸው ላይ እየተነበበ።

"አይ ግዴለም አደይ፡ በጣም መሽቷል፡ ወደጓዶች መሄድ አለብን። ደግሞም ስለደከመን ከተኛን መነሣት እንቸገር ይሆናል፤ እነርሱ ጋ ሄደን ማደር አለብን" ብዬ ከልጁ ጋር ጓዶች ወዳሉበት ሄድን።

ወደ ግቢው ስንጠጋ ዋርድያው "ቁም!" አለን።

የምስጢሩን ቃል ስንናገር እንድናልፍ ተፈቀደልን። ዋርድያው ማንነታችንን ሲለይ ደግሞ ሰላምታ ተለዋወጥንና ወደ ግቢው ውስጥ ዘለቅን። እጋጣሚ ሆኖ የገባንበት ቤት ውስጥ ያገኘናቸው የኔን ጋንታ ጓዶች ነበር።

ጋንታ መሪያችን እንግዳወርቅ መጥቶ አየን። ሌሎቹም ጓዶች እንዴት እንደበሰበስንና እንደደከምን አይተው በጣም አዘኑልን። ወደቤት ገብተን እሳት እንድንሞቅ ተደረገ። ከእሳቱ ዳር ሆነን ልብሳችንም እንዲደርቅ ማሞቅ ነበረብን። በዝናብ መደብደባችንን እንጅ የት ሄደን እንደመጣን ማንም የሚያውቅ የለም። የጋንታ መሪው እንግዳወርቅም የሚያውቅ አይመስለኝም። እኔ እስከማውቀው ድረስ ከኃይል አመራሮች በስተቀር የት እንደነበርን ማንም አያውቅም። በደፈናው ለሆነ መልእክት መሄዳችንን ግን ምመገመቻው አይቀርም።

በኃይሏ ውስጥ ካሉት ሦስት ጋንታዎች ሁለቱ ሌላ ቦታ ናቸው። አንደኛዋ ጋንታ ለማደሪያ የተመረጠው ጋራ ላይ ወጥታለች። ሁለተኛዋ ጋንታ ደግሞ ትንሽ ራቅ ብላ ሰፍራለች። ይህቺኛዋ በመጨረሻ ከኋላ እንድትሄድ የተመደበች ስለነበረች፡ በመንገድ ላይ ዝናብ በጣም ስለበረታባቸው ርቀው ሳይሄዱ ነበር እዚህ መንደር ያረፉት።

ወደጋንታዋ ስንቀላቀል ምሽቱ ገቷል። ጓዶች ራታቸውን በልተው ቦታ ቦታ ይዘው ለመተኛት ተዘጋጅተዋል። ከእንግዳ ወርቅ ጋር ትንሽ ተነጋገርን፡ ከእራት የተረፈ ትንሽ ምግብ ስለነበረ አቀረቡልንና በላን። ቤቱ ለሁሉም የሚበቃ





ስፋ የከብት በረት ነበረው። ሁሉም ለመተኛት ወደበረቱ ሲሄዱ እኔና ድላይ ብቻ ሙቀት አግኝተን እቤት ውስጥ እንድናድር ተደረገ።

እንግዳወርቅ ህመሟንና ድካሟን የተረዳው ይመስለኛል "በሉ እናንተ ልብሳችሁን አድርቃችሁ እዚሁ እቤት ውስጥ ተኙ፤ እኛ ውጭ እናድራለን" ብሎን ሲወጣ ተከተልኩት። ዋርድያ የሚቆምበትን ቦታ በሙሉ ዞረን አካባቢው በሙሉ ሰላም መሆኑን አረጋገጥንና ወደ ዋርድያ ተመለስን። እኔ የእንግዳወርቅ ምክትል ስለሆንኩ አብሬው ለቁጥጥር መውጣት ነበረብኝ።

እንግዳወርቅም ለተረኛው ዋርድያ "አማኑኤልና ድላይ ውስጥ ስላሉ ለሚቀያየሩት ዘበኞች አውስጥ መኖራቸውን እንዲያውቁ አድርግ" በማለት ትእዛዝ ሰጠና ተሰናብቶኝ ወደ መኝታው ሄደ። እኔም ድላይ ወዳለችበት ቤት ተመልሼ ገባሁ።

የተጣበቀውን ነጠላችንን እየተቀባበልን በእሳት እያሞቅን እያገላበጥን አደረቅን። የተቻለንን ያህል ራሳችንን ለማመቻቸት ጥረት አድርገን ለመተኛት ተዘጋጀን። የተኛንበት ቤት በሩ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ነው። ዋርድያ ያለበት የውጪ በር ወደ ሰሜን በኩል ነበር። እሳቱን ትንሽ ቀነስንና በሩን መለስአድርገን ለመተኛት ተቃረብን። በተለመደው ጓዳዊ ሥነሥርዓት የምንተኛባትንና የምንለብሳትን ኩሽክ አነጠፍኩና ድላይ ከወደሙቀቱ እንድትተኛ ነገርኳት።

በገጽታዋ ላይ የሐዘንና የትካዜ ስሜት በመመልከቴ ግር አለኝና "ምነው ድላይ ነጠላዬን ደርቢና እንተኛ እንጂ" አልኳት። "አይ አማኑኤል ለየብቻችን ብንተኛ ይሻላል" አለችኝ።

"ለምን ለብቻሽ ትተኛለሽ? ለብቻሽ ከተኛሽ እኮ ይበርድሻል? ነጠላውም እኮ ገና በደንብ አልደረቀም" ብዬ መለስኩላት።

"የነጠላው ጉዳይ አይደለም፤ አማኑኤል እኔ እኮ ዛሬ ተበላሽቻለሁ። መንገድ ላይ ልጸዳዳ፣ እያልኩ ያስቸገርኩህ ትዝ አይልህም? ስለዚህ ከእኔ

ጋር ከመተኛት ብቻህን ብትተኛ ይሻልሀል" አለችኝ። ምን ማለቷ እንደሆነ አልገባኝም ። "ለምንድነው?" ብዬ እንደገና ጠየቅኋት።

"እኔ ለአንተ ብዬ እኮ ነው! ከእኔ ጋር ከተኛህ ጠረኔ ልክ አይደለምና ይረብሽሃል ብዬ ነው" ስትለኝ በጣም ደነገጥኩ።

"አይዞሽ ጓዲት ምንም አይደለም ይኼ ምንም ሊያስጨንቅሽ አይገባም። አሁን እኩለ ለሊት እያለፈ ነው። ስለዚህ መተኛት አለብን" ብዬ የእኔና የእሷን ነጠላ ደረብንና በግድ ገፉፍቼ እንድተኛ አደረግኋት። የእሳቱ ሙቀት ያለው ድላይ በተኛችበት በኩል ነበር። እኔ ደግሞ ከኋላዋ በኩል ተኛሁ። ከተኛንም በኋላ ግን እንቅልፍ በቶሎ ስላልወሰደን ማውራት ጀመርን።

"አማኑኤል ጠረን አላስቸገረኽም?" አለችኝ

"የለም እኔ ምንም ሽታ አልተሰማኝም። በዚህ ነገር ምንም የሚያሳስብ ነገር እንደሌለ ነግሬሻለሁ፣ ከበረደሽ ግን እሳቱን ልጨምርልሽ" አልኳት።

"እኔማ እሳቱ እያሞቀኝ ነው፤ አንተ ነህ ከወደኋላ ሆነህ የእሳቱ ሙቀት በደንብ የማይደርስህ ስለዚህ በደንብ እንዲሞቅህ ወደእኔ ጠጋ በል" አለችኝ።

የሚታየኝ ህመሟ ድካሟና ብርዱ ነው። የፈለግኩት በተቻለ መጠን እንዲመቻት አድርጌ በደንብ እንድታርፍ ነው። እርሷ ደግሞ ከእሳቱ በመራቁ ተጨንቃ ብርዱ እንዲወጣልኝ "ጠጋ በል" አለችኝ። አሁን በደንብ ተጠጋኋትና አቅፌአት የበለጠ ሙቀት እንድታገኝና እንድትተኛ ፈለግሁ። እጆቼን ከታችና ከላይ በኩል አሳልፌ በወገቧ ዙሪያ እንደመቀነት ሲጠመጠሙ፤ ከፍ አደረገቻቸውና ወደጡቶቿ አስጠጋቻቸው።

ይበልጥ ወደርሷ ተጠጋሁ። ተቃቀፍን እናም መተሻቸቱን ወደድኩት። ምክንያቱም ገና ስጠጋትና ሳቅፋት ምንነቱ ያልገባኝ የተለየ ስሜት ተሰምቶኛል። አሁን ደግሞ ጡቶቿን ስነካቸው ሰውነቴን ወረረኝ። ሙቀቱ በሁሉመናችን ተዘራ።





ልገልጸው በማልችለው ሁኔታ ሰውነታችን ከመሞቅ አልፎ ጋለ። ትንፋሻችን እሳት መትፋትጀመረ።በዚህ ሁኔታ ሁለታችንም ተቃቀፍንና ጥብቅብቅ ብለን ተጣምረን ተኛን። ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነት እንግዳ ስሜት ገጥሞኝ አያውቅም። በሕይወቴ ከሴት ጋር ተቃቅፌ ስተኛ ከድላይ ጋር የመጀመሪያዬ ነው። ትንፋሻችን የሚፋጅ እሳት እየሆነ ይወጣል። ገላዬ ከጀርባዋ በኩል ልክ በገመድ እንደታሰረ አንድ ሆኖ ተጣብቋል። በዝናቡና በነፋሱ ምክንያት የቀዘቀዘው ሰውነታችን ባልተለመደ ሁኔታ ግሎ መፋጀት ጀመረ። በላያችን ላይ የሰፈረው ድካም የት አባቱ እንደገባ አላውቅም። ሁለታችንንም እንቅልፍ አልወሰደንም። ውብ በሆነ ስሜት እየቃተትን ገላ ለገላ ስንተሻሽ አንዳንዴ በተለየ ጉሮሮ የሚወጣ በሚመስል ድምጽ እናቃስት ጀመር።

በዚህ ሁኔታ እንደቆየን ድላይ ገልበጥ አለችና ፊቷን ወደ እኔ አዞረች። የሁለታችንም እሳት የሚተፋው ትንፋሽ ተቀላቀለና በላብ ተጠመቅን። አሁንም ትንሽ ወደእኔ ጠጋ አለችና ሰውነቷ ከደረቴ ጋር ጥብቅ አለ። ከኛ ቁጥጥር ውጪ በሆነ መግነጢሳዊ ሰበት እየተጎተቱ ከንፈሮቻችን በጣም ተቀራረቡ። የከንፈሮቻችን ንክኪ ሙቀቱ፣ ጣዕሙ፣ ስሜቱ፣ ንዝረቱ ልዩ ነው። ፈጽሞ ሰላም የሰፈነበት ሌላ ውብ ዓለም ውስጥ ኾነው ብለን ገባን፤ ይያልበትን ዘነጋነው። ከዚያ በኋላ እንዴትና መቼ እንዳንቀላፋሁ ሳላውቀው እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደኝ፣ የሰሞኑ ተደራራቢ ድካም በጣም ተጫጭኖኝ ነበረ።

ከተኛሁበት የባነንኩት ከለሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ የሆነ ድምፅ ሰምቼ ነው። አንድ ሰው ያለንበትን ቤት ቀስ በሎ ሲከፍት ተሰማኝ። ምንድ ነው ብዬ ስመለከት አታክልቲ ማንጁስ መሆኑን በጥላው ለየሁት። በሩን ቀስ አርጎ ከፍቶ ወደተኛንበት ቦታ አንገቱን ሰገግ አድርጎ ለማየት ይሞክር ነበር። በተኛሁበት ሆኜ ዝም ብዬ አየዋለሁ። ከውጪው የበለጠ ጨለማ ስለሆነበት የውጋጋን ብርሀን ለማግኘት ብሎ በሩን ከፈት አድርጎታል።

“ምነው አታክልቲ ምን ለማየት ፈልገህ ነው የመጣኸው?” ስለው ደነገጠና ምንም ሳይናገር ፈዝዞ አየኝ። “በል በሩን እንደነበረ አድርገህ ዝጋውና ሂድ” አልኩት። ምንም አልተናገረም፤ ወደውጭ ተመልሶ ሄደ።

አታክልቲ ማንጁስ፣ በኃይል አምስት መቶ ውስጥ ከነበርነው ከሁላችንም በዕድሜ ያነሰ ስለነበረ ነው ማንጁስ የተባለው። ምን ጥርጣሬ አድሮበት ወይም ማን እንደላከው አላወቅኩም። ነገር ግን እንዳሰበው ምንም ነገር ሳያገኝ ተመለሰ። አታክልት ማንጁስ በጣም ቀልጣፋና ንቁ ጓድ ነበር። (ከትግል በኋላም ትምህርቱን ጨርሶ ዶክትሬቱን አግኝቷል ሲባል ሰምቻለሁ።)

ሲነጋጋ ሲል ዋርድያ ጓዶችን መቀሰቀስ ጀመረ። ወደእኛ ከመምጣቱ በፊት ውጭ ያሉትን ጓዶች ሲቀሰቅስ ሰምቼ ነቅቻለሁ። ከእንቅልፍ የምንቀሰቀሰው ሁለት ጣቶችን በማጋጨት በሚወጣው ድመጽ ምልክትነት ነው። እሷን ድምፅ ሲሰማ ማንኛውም ጓድ ከተኛበት መነሣት አለበት። እኔም ዋርድያው ሁለት ጣቶቹን አፋጭቶ የሚያወጣትን ድምፅ ከውጪ ስለሰማሁ ተነሣሁና ድላይን ቀሰቀስኳት። ዋርድያው ሊቀሰቅሰን ገና በሩን ሲከፍት መነሣታችን ስለነገርኩት ተመልሶ ሄደ።

***





ከቤት ስንወጣ ማታ ያደረግነውን አስቤ፣ ፍርሃት ተሰማኝ። ድላይ ምን እንደተሰማት ማወቅ ፈለግሁ ሆኖም ደፍሬ ዓይኖቹዋን ማየት አቃተኝ። ጠዋት የተለመደውን የጋንታ ሥነሥርዓቶችና ግዴታዎቻችንን አጠናቀን እንደገና ስንገናኝ ቅሬታ ወይም ግሳጼ ነገር ታሰማለች ብዬ ጠብቄ ነበር። ነገር ግን ምንም የተቃውሞ ምልክት አላሳየችኝም። እኔ ግን ጥፋተኛነት ተሰምቶኛል፤ የፈለገው ይምጣ ብዬ ዓይኖቿን ደፍሬ ሳያቸው ፊቷ ላይ ምንም የቅሬታ ምልክት አልነበረም። እናም የበለጠ ላናግራት ተደፋፈርኩና “ድላይ ማታ ከፍላጎትሽና ከአላማችን ውጪ ሄጄ እንዳስቸገርኩሽ ተሰምቶኛል፤ በህመም ላይ ሆነሽ የወንድነት የተፈጥሮ ስሜቴን በጭፍን ተከትዬ ሳይታወቀኝ እንቅልፍ ነስቼሽ እንዳይሆን ስጋት አድሮብኝ ነበር” እያልኩኝ በማውቀው የተሰባበረ አማርኛዬ ነገርኳት።

ገና ንግግሬን ሳልጨርስ “ምንም ስጋት እንዲያድርብህ አያስፈልግም፤ ከጠዋት እስከማታ ስታስታምመኝና ለእኔ ስትል ያ ሁሉ ዝናብ በጀርባህ ሲወርድ ውለህ አምሽተሃል። እኔ በጣም ደክሞኝና መሄድ አቅቶኝ እጄን ይዘህ ስትጎትተኝ ዋልክ፤ እንደገና ደግሞ ማታ እንዳይበርደኝ ለማድረግ ሌሊቱን በሙሉ ስትንከባከበኝ አደርክ። ይሄ ሁሉ ለእኔ በጣምብዙ ነገር ነው። ስለዚህ ምንም እንዳታስብ። ብዙ ውለታ ጣልክብኝ እንጂ ምንም አላጠፋህም” ብላ በመሽኮርመም ፈገግ ስትልልኝ ታላቅ ደስታ ተሰማኝ።

ያን ጊዜ ልቤ ተረጋጋና ጨዋታ ለመጀመር ገፋፋኝ። “ድላይ! ሌሊት እኮ አታክልቲ ማንጁስ ተጠራጥሮን ነው መሰለኝ በሩን ከፍቶ አንገቱን አስግጎ ወደእኛ ሲመለከት ቆይቶ ተመለሰ” አልኳት። ቀጠል አድርጌም “ምናልባት ልከውት ከሆነ ጠዋት አነጋግረዋለሁ። አለያም የፖለቲካ ሐላፊውን ሊበንን ወይም እንግዳወርቅን አነጋግራቸዋለሁ” አልኳት።

“የለም ዝም በል ማንንም ማናገር አያስፈልግም። እንዲያውም ነገሩ ምንም እንዳልተሰማህ መስለህ ማሳለፍ ነው የሚሻለው። ምንም ያየው ነገር ስለሌለ ተጠራጥሮ ይቀራል እንጂ ምንም የሚያመጣው ነገር የለም” አለችኝ፡፡

ለመንቀሳቀስ ተሰልፍን። "ቢይ ደህና ዋይ፡ አሁን አንቺ ወደጋንታሽ ትሄጃለሽ። እኔ ደግሞ ከጋንታዬ ጋር እቀራለሁ እና አይዞሽ ሌላ ጊዜ እናወራለን" አልኳት፡፡

"ግዴለም ዛሬም እዚሁ ከእናንተ ጋር ሳልውል አልቀርም፤ ገና አልተሻለኝምና ቀኑን ሙሉ አብረን ሆነን በደንብ እንጫወታለን" አለችኝ።

ሁልጊዜ እንደምናደርው ሁሉ ትጥቅና የተጋዳላይ ዝግጅት አድርገናል። እኔ ከላሽኔን ይዣለሁ ድላይ ደግሞ ሽጉጧንና ቦንቧን ታጥቃለች። እንደ ወትሮው እንግዳወርቅና እኔ አካባቢው ሰላም መሆኑን አጣራን። ስንመለስ እቃ እንዳልተረሳና ሁሉም ጓድ መኖሩን ካረጋገጥን በኋላ ከሻፊዎች ወይም ደግሞ አብሪ ጓዶችን አስቀድመን በሰልፍ በሰሜን አቅጣጫ በኩል ወደ አለው የእንባሰነይቲ ተራራ ወጣን።

አንደኛዋ ጋንታ ትላንት ማታ ደርሳለች። የቴዎድሮስ ጋንታ ግን አጠገባችን ነበር የዋለችው።"ዝናብ ስለነበረ ነው እንጂ ትላንትና ነበር መውጣት የነበረብን" አለኝ ጓድ እንግዳወርቅ። እንግዳወርቅ ድላይ መታመሟን ስለአወቀ ይመስለኛል ከጋንታዎቹ ጓድ ከበደ ፊት ለፊት አድርጎ እንድትንቀሳቀስ አደረገ። እኔ እንደምክትል ጋንታ መሪ በመሀል ተሰልፌ እንግዳወርቅ ደግሞ ከፊት ሆኖ ጉዞ ቀጠልን። የገደሉን አፋፍ እንደወጣን " ተጸዳዱ" ተባለ፤ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳያት አትጸዳዳም ዝም ብላ ቁጭ ብላለች። "እየተሻለሽ ነው?" አልኳት።

"ከትላንትና ዛሬ ይሻለኛል ወገቤ ግን ገና አልጠነከረም" አለችኝ። ተራራውን እንደወጣን የአቢዮና ጌትነት ቆመው አገኘናቸው። ሁለቱ ጋንታዎች ቀድመውን ስለወጡ ቦታቸውን ይዘዋል፤ "አብሩክ" ተባልንና ሁላችንም በያለንበት ቦታ ተቀመጥን። ትንሽ እንደቆየን "አማኑኤል ወደፊት" ተባልኩና እየሮጥኩ ደረስኩ። ጌትነትና የአቢኢዮ ከእንግዳወርቅ ጋር እየተነጋገሩ ቆመዋል። "የትላንትና ጉዞ እንዴት ነበር?" ብሎ ጌትነት ጠየቀኝ።





"የተፈለገው ነገር አልተገኘም፤ "ነበለት ሄደን ስንጠይቅ ሴት አስተማሪዎች ወደ አድዋ ከተማ ደሞዝ ለመቀበል ሄደዋል' ስለአሉን ተመለስን። በመንገድ ላይ ግን ዝናቡ ስለወረደብን በቅዝቃዜውና በድካሙ በጣም ተቸግራ ነበር። እንደምንም ብለን ግን ጓዶች ያሉበት ቦታ አደርን" ብዬ ነገርኳቸው፤

የአቢኢዮ "ወዲ ሀፍተይ በጣም ንቁና ጠንቃቃ ነህ። ለዚህ ብለን ነው አንተ ይዘኻት ሂድ ያልንህ። አደራህን ተወጥተሀል። ስለዚህ የቴዎድሮስ ጋንታም ትንሽ ራቅ ብላ ስለሄደች ዛሬም ከእናንተ ጋር ትውልና ማታ ወደጋንታዋ ትቀላቀላለች" የሚል መመሪያ ሰጠ።

እንግዳወርቅም ቀጠል አደረገና "እዎ ትላንትና ማታ በጣም ደክመውና ልብሳቸው በዝናብ ርሶ ሌሊቱን በሙሉ በእሳት ሲያሞቁ ነው ያደሩት። አረፍ ብላ ብትሄድ ይሻላል" የሚል አስተያየት አከለበት።

በውሳኔው በጣም ደስ ብሎኛል፤ ምንም ሳልጨምር ንግግራቸውን እንደጨረሱ ወደነበርኩበት ቦታ ተመለስኩ። እንቅስቃሴ ከፊት ሲጀመር ወደኋላ ሮጥ ብዬ ተመልሼ "አብረን እንውላለን ከእናንተ ጋር ትዋል ብለው ጌትነትና የአቢኢዮ ወስነዋል። ስለዚህ አረፍ ብለሽ ትሄጃለሽ እና እንነጋገር" ብዬ ቀስብዬ ነገርኳት። ደስ እንዳላት ተረዳሁ። ትንሽ ተጉዘን መንደር አገኘንና አረፍን።

እንግዳወርቅ ማረፍ ስለነበረበት እኔ በተራዬ የቀን ዋርዲያ ኃላፊ ነበርኩ። "አብሩክ" እንደተባለ ወደ ፊት ሄድኩና ከእንግዳወርቅ ጋር ተነጋገርኩ፤ ዋርድያ የሚወጣበትንና የሚቆይበትን ቦታ መረጥን። ወደ ቤት ገብተን እቃዎቻችንን እንዳራገፍን ተረኛ ዋርድያ ይዤ የሚቀመጥበትን ቦታ መረጥኩና አስቀመጥኩት። ሁለቱ ዋርድያዎች የት እንዳሉ ነገርኩት ከዋርድያው መቀመጫ ወደ ጎን በኩል ሁለት ተለቅ ያሉ ድንጋዮች ነበሩ፣ ተረኛው የዋርድያ ኃላፊ እኔ ስለነበርኩ ሥፍራየን ከድንጋዩ ስር አደረግሁሁ። ለማንኛውም አስፈላጊ ነገር ከተፈለግሁ የምገኘው እዚያ መሆኑን ለተረኛው ዋርድያ አሳወቅሁ። ተረጋግተን

እንዳረፍን ወደ ድላይ ሄድኩና የቀኑ የ ዋርድያ ኃላፊ መሆኔንና የምገኝበትን ቦታ አመላከቻት ሲመቻት እንድትመጣ ነገርኳትና ተመለስኩ።

ድላይ መታመሟንና መድከሟን አውቀው የጋንታዋ መጋቢዎች እንቁላል ጠብሰው ሰጥተዋት ደስ ብሏታል። በመንፈስም ሆነ በሞራል ጠንከር ብላ ስላየኋት እኔም ደስ አለኝ። ኩሹኬን አንጥፌ ከላሸኔን ድንጋዩ ላይ ደገፍ አደረግሁና ፊቴን ወደ ዋርድያው አዞሬ ጋደም አልኩ። ዋርድያዎቹ በየሰአቱ እየተቀያየሩ ነበሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ድላይ እኔ ወደተቀመጥኩበት ቦታ መጣችና "ጠጋ በል" አለችኝና በቀኝ በኩል ከጎኔ ተቀመጠች። "ተሻለሽ?" አልኳት።

"ከትላንትና ዛሬ ይሻለኛል። እንደአሁኑ ግን ተሰቃይቼ አላውቅም፤ ሌላው ቀርቶ ትጥቄን እንኳን ለመሸከም አልቻልኩም። ወገቤ ሊበጠስ ትንሽ ነበር የቀረው" እያለች ህመሟን በትካዜ ገልጻችልኝ። "እናንተ እኮ ታድላችኋል። እንደዚህ አይነት ህመምአታውቁም" አለች ደግሞ በጣምቀስ ባለ ድምጽ።

"እኔ እኮ 'ድላይ የምትፈልገውን እቃ ይዛችሁ ትመጣላችሁ' ሲሉኝ መጀመሪያ ምንም አልገባኝም። በዚህ ዙሪያ ብዙ የማውቀው ነገር የለኝም። ልጠይቅሽ በጣም እየፈራሁና እያፈርኩኝ ነበር። ትግል ከመግባቴ በፊት እንደዚህ አይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም። ስለተፈጥሮ የነበረኝ እውቀት በጣም የተሳሳተ ነበር። በሕይወቴ ውስጥ ይህ የመጀመሪያ አጋጣሚ ነውና ባለማወቄ ይቅርታ አድርጊልኝ" አልኳት፤ ከልቤ ነበረ።

"ምነው አማኑኤል! ይህ እኮ ይቅርታ የሚያስኝ ነገር አይደለም።" አለችና ችግሩን ቀስ በቀስ ስታስረዳኝ በጣም አዘንኩ። የተሰማኝን ሐዘን ርህራሄ በተሞላው ሁኔታ ስገልጽላት አይኖቼን እየተመለከተች "አማኑኤል አይዞህ ምንም ችግር የለም ከዛሬ ደግሞ ነገ ይሻለኛል ከላሸኔን አንግቼ ታየኛለህ። ቀንና ለሊቱን በሙሉ በጣም ስለተንከባከብከኝ ለእኔ ስትልም ብዙ ስለተጎሳቆልክ በጣም አመሰግናለሁ፤ በፍጹም አልረሳህም። ለእኔም ይህ አጋጣሚ





የመጀመሪያየ ነው በእንዲህ አይነት ሁኔታ ወንድ አይቶኝም ተንከባክቦኝም አያውቅም። አንተ የእውነትም የአደራ ሰው ነህ፤ ጌትነትና የአብኢዮ ከንተ ጋር እንድሄድ ያደረጉበት ምክንያትም ይሄው ይመስለኛል።" በማለት ጓዶች እንዳይሰሙና እንዳይመለከቱን ድምጿን ዝቅ አድርጋ በጥንቃቄ አወራችልኝ።

የወቅቱ ትልቅ ችግሯ በመሆኑ የወገብ ህመሙ የቱን ያህል እንደሚያሰቃያት አስረዳችኝ። ድላይ ስትነግረኝ ነበር ብዙ የማላውቀው ነገር እንዳለ የተረዳሁት። እርሷም አለማወቄን በደንብ ተረዳች። ብዙም ሳልገልጽላት ስላስተዳደጌንና ከትግል በፊት የነበረውን አኗኗሬን ለመገመት ችላለች። "ሞዴስ" የሚለውን ቃል እንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ መስማቴንና ጥቅሙንም የማላውቅ መሆኔን አውቃለች። የአቀራረቤና የአመለካከቴ የዋህነት ካለማወቅ መሆኑን፤ ከብዙ መተቃቀፍና መነካካት የተነሳ ግን ተፈጥሯዊ ስሜቴ ሊመቀስቀስ መቻሉን ተገነዘበች።

"አስቸግሬሽ ከሆነ ግን በጣም ይቅርታ" አልኳት በድጋሚ።

"አይዞህ ምንም የሚያሳስብ ነገር የለም በጣም ከመተሳሰብ የመጣ ሁኔታ ነው እንጂ ሆን ብሎ የተደረገ ነገር አልነበረም። ብቻ የበለጠ ለመቀራረብና ለመተማመን መነሻ ሆኖናል።" አለችኝ ተረጋግታ።

ምሳ መድረሱ ተነገረና ከጓዶች ጋር አብረን በላን። ከምሳ በኋላ ተመልሰን ወደነበርንበት ቦታ ሄድን። ጊዜው ጸሐያማ ስለነበረ ጥላ ወደአለበት ቦታ ቀየርንና መቀማመል ጀመርን። መጀመሪያ ጸጉሯን ቀመልኳት። እርሷም በተራዋ ይህንኑ አደረገች። እያንዳንዱ ንክኪ ከወትሮው ለየት ያለ ስሜት እየፈጠረ ወደመተሻሸት ተቀየረ። "አማኑኤል!" አለችኝ በዝቅተኛ ድምጽ፤ ቀስ ብዬ ስመለከታት አይኖቿ ይርገበገባሉ፤ የምትጨምረው ቃል ግን አልነበራትም። ተያየን፤ በሁለታችንም ዓይኖች ውስጥ ልዩ ስሜት ይነበባል፤ ጓዳዊውን ፍቅር ያሸነፈ ጾታዊ ፍቅር መፈጠሩን ከድላይ ዓይኖች ውስጥ ማንበብ ቻልኩ።

***

ኃይል አምስት መቶ ከኃይል ስልሳ ስድስት ጋር በመሆን በውቅሮ ካምፕ ላይ በቀን ለሚደረግ የወረራ ዝግጅት የተጠራችው ከብዘት ነበር። ብዘት በአድዋ መስመር ከሰሮ ወደ አዲግራት በሚወስደው አቅጣጫ የሚገኝ ቦታ ነው። በዝያን ጊዜ ኃይል አምስት መቶ ከብዘት እስከ አክሱም ጫፍ የመሄድና የፕሮፖጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ የመስራት ኃላፊነት ተሰጥቷት ነበር። በየገበሬው መንደሮች ውስጥ ተመሳስለው እየኖሩ ይሠሩ የነበሩ ጓዶች በየቦታው ይገኙ ስለነበር እነርሱ በቀሰቀሱት ህብረተሰብ ውስጥ ስንንቀሳቀስ ብዙ ችግር እንዲቃለልን አድርገዋል።

ወቅቱ አልፎ አልፎ የደርግ ጦር እንቅስቃሴ የሚታይበት፣ ከወያኔ ጋር የነበረው ቅራኔም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ በጦርነት አፋፍ ላይ የምንገኝበት ነበረ። በተጨማሪም አሲምባ ውስጥ በተፈጠረው የአንጃ እንቅስቃሴ የተነሳ የተወሳሰበ ውስጣዊ ችግር የተከሰተበት ጊዜ ስለነበረ ኃይላችን በዚህ ችግር ውስጥ ሆና ነበር የምትንቀሳቀሰው።

አንድ ቀን የደርግ ጦር ሊመጣ እንደሆነ የሚጠቁም መረጃ ደረሰን። እኛ ደግሞ ምንም አይነት ዝግጅት አልነበረንም፤ በዚያ ላይ የእነግደይ ጋንታ ራቅ ብላ ሄዳለች። ምን ማድረግ እንደአለብን ተነጋግረን መረጃውን ለማረጋገጥ የተወሰኑ ጓዶች እንዲላኩ ተወሰነና የአብኢዮ ሶስት ጓዶችን ይዞ የደርግ ወታደሮች አሉበት ወደተባለው አካባቢ ሔደ።

የተላከው ቡድን መረጃውን አጣርቶ ይመለሳል ተብሎ በተገመተው ጊዜ ውስጥ ሳይመጣ ቀረና ግራ ተጋባን። ጓዶቹ የዘገዩት ምናልባት በጠላት እጅ ወድቀው ይሆናል ብለን ተጠራጠርንናም ስጋት ውስጥ ወደቅን። እነርሱን ለማፈላለግና በዚያውም የደርግንም ጦር ሁኔታም ለማረጋገጥ በጌትነት የምትመራዋ እኔ የነበርኩባት ጋንታ ወደ ሰሮ አቅጣጫ ተላከች።





ከብዘት ሌሊት ተነስተን ሊነጋጋ ሲል ሶሮ አካባቢ ደረስን። ከዚያም አመቺ ቦታ አግኝተን ቅኝት ስናደርግ የደርግ ጦር ከፊት ለፊታችን በቅርበት መኖሩን ተመለከትን። መዝጉበ(ምሽግ) ያዝንና ተመቻችተን ሁኔታዎችን መከታተል ቀጠልን። የሚገጥመንን ወይም የምንገጥመውን ሀይል ለመቋቋም ቢያንስ መትረየስ እንደሚያስፈልገን በመረዳታችን፣ መትረየስ የያዘችው ጋንታ እንድትመጣልን መልእክት ላክን። እስከዚያው ግን ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት አንድ የአመራር አባልና አንድ ጓድ የደርግ ጦር ወደሰፈረበት መንደር ለስለላ እንዲሄዱ ተወሰነ። እኔ ከአመራሩ በፈቃደኝነት ለመሄድ ተነሳሁና ከአትክልቲ ጋር እንድንሔድ ስምምነት ላይ ደረስን።

እኔ የገበሬ ልብስ ለብሼ አትክልቲም ተማሪ ለመምሰል የሐኪማችንን የጓድ ከበደን ደብተርና ወረቀት ይዞ እኔን ተከትሎ እንዲሄድ ተነጋገርን። ሁለታችንም ከእቅዳችን ጋር በሚስማማ አለባበስ ተዘጋጀን። እኔ ሸጉጥና በንብ አትክልቲ ደግሞ የተወሰኑ ቦንቦች ይዟል። እኔ እንግዲህ ልጄን ወይም ወንድሜን ወደ ትምህርት ቤት ለማድረስ እንደምሔድ ገበሬ መስያለሁ።

የምንገባበት መንደር ውስጥ አንድ ቤተክርስቲያንና አንድ ትምህርት ቤት አሉ። ቤተክርስቲያኑ እኛ ባለንበት በኩል በመንደሩ ዳርቻ ላይ ከፊት ለፊታችን ቁልቁለቱ ላይ ይገኛል። እናም ትምህርት ቤት ከመድረሳችን በፊት ቤተክርስቲያኑን ስለምናገኝ እዚያ ከምናገኛቸው ሰዎች መረጃ ለመሰብሰብ ነበር ያሰብነው።

ቤተክርስቲያን ስንደርስ የቅዳሴ ስነ ሥርአት አብቅቶና ተአምረ ማርያም ተሰምቶ አብቅቶ ቄሱ ምእመናኑን በመባረክ ላይ ነበሩ። እኛ ቀስ ብለን ሰዎችን ለማነጋገር ጠጋ ስንል፣ ቄሱ አዩንና ወደ እኛ መጡ። "እናንተ ተጋዳዮች አይደላችሁም እንዴ፣ እዚህ ምን ታደርጋላችሁ" አሉን።

"አዎን አባ፣ ልክ ነዎት፣አሁን ግን ሰው እንዳይሰማ ዝም ይበሉ" አልናቸው።

"ታዲያ እዚህ ምን ፈልጋችሁ መጥታችሁ ነው፣ ደርግ ያለው እኮ እዚህ ቅርብ ማዶ ነው"

"ደርግ እዚህ አካባቢ ለምን መጣ፣ ምን እየሰራ ነው?" አልናቸው።

"ምን ፈልገው እንደሆነ አላውቅም፤ ግን ሌሊቱን በሙሉ እዚህ ምሽግ ይዘው ነው ያደሩት፣ ከባድ መሳሪያዎች ጭምር ይዘው ነው የመጡት፤ ከዚህ ቦታ ትንሽ እልፍ ብትሉ ግን ስለሚያገኟችሁ ችግር ላይ ትወድቃላችሁ" አሉን።

ከዚህ በኋላ ማለፍ ስላልቻልን፣ ቄሱ የነገሩንን መረጃ ይዘን ጓዶቻችን ወደነበሩበት ቦታ ተመለስን። እኛ ከጓዶቻችን ከመቀላቀላችን በፊት፣ ታንኮች መብራት አብርተው መንቀሳቀስ ጀመሩ። ጌትነት እኛን እስኪያገኝ ድረስ ምንም አይነት ትእዛዝ ሳይሰጥ እኛን ይጠብቀናል። ስንደርስ የሰማነውን ነገርነው። ከዚህ በኋላ ተኩስ እንዲከፈት አዘዘ። ለአርባ አምስት ደቂቃዎች ያህል በነበርንበት ሆነን ስንታኮስ ቆየንና የደርግ ጦር ምሽግ የያዘንበትን ቦታ ለይቶ በማወቁ ለመከበብ ቦታውን እያሰፋ መሄድ ጀመረ። ለበለጠ አደጋ እየተጋለጥን ነበርን፤ አፈግፍጎ ለመሰወር እንኳ የማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ልንገባ ትንሽ ሲቀረን በግደይ ጨጓር የምትመራው ጋንታ ደረሰችና ተጨማሪ ሽፋን አግኝተን ተጠናከርን። ያን ጊዜም በአስተማማኝ ሁኔታ ሳይከቡን አስቀድመን እያፈገፈግን መታኮስ የምንችለበት እድል ስለተፈጠረልን ተኩሱን አጋግለን ማፈግፈግ እንደጀመርን፣ ወደ ብዘት አቅጣጫ በመጓዝ ላይ የነበሩትን ሁለቱን የደርግ ጦር ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች የተቀበረ ቦንብ አፈነዳቸው። በዚህ የተደናገጠው የደርግ ጦር ተኩሱን የበለጠ አባብሶ ይለቀው ጀመር። እኛ የእነርሱን መረበሽ ማወቃችን በአስተማማኝ ሁኔታ ያለምንም ችግር እንድናፈገፍግ አገዘንና በሰላም ወደ ብዘት ተመለስን።

***





ወደ ብዘት ተመልሰን ትንሽ እንደቆየን በ1970 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት አካባቢ ከአሲምባ ወደ እኛ ከመጣ በክፍለ ሕዝብ ውስጥ ከሚሠራ አባል ጋር ተገናኘሁ። ስለ አሲምባ ጠየቅሁትና ስንጨዋወት ሰላማዊት ትዝ አለችኝ፤ ያውቃት እንደሆነ አለያም ስለእርሷ የሰማው ነገር እንዳለው ጠየቅሁት። ከሰላማዊት ጋር የተለያየነው የፍርድ ቤቱ (የትሪቢዩናሉ) ውሳኔ ከመሰማቱ በፊት ስለነበረ ውሳኔው ከሰማሁ በኋላ አግኝቼ ላመሰግናት በጣም እፈልግ ነበር። አልተገናኘንም፤ እንደምንም ብየ አገኛታለሁ የሚል እምነት ግን ነበረኝ። ወደ አሲምባ ሳልመለስ ደግሞ ኃይል አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ተመደብኩ። እናም አመስግኜ ለመሰናበት ይቅርና ወሬዋን እንኳ መስማት ሳልችል ቀረሁ።

ከሰላማዊት ጋር የተለያየነው ወደ ጾረና ተልኬ ከሄድኩ ጀምሮ ነበር። ጾረና አንድ ወር ቆይቼ ስመለስ ስንቅና ትጥቅ ያለበት ቦታ እንደትጠብቅ የተመሠረተችውን ጋንታ ዋርድያዎች የምመድበውና የምቆጣጠረው እኔ ነበርኩ። ያኔ ደግሞ አዳዲስ መሣሪያ መጥቶ ስለነበረ፣ ከተወሰኑ ሰዎች በስተቀር ወደዚያ ማንም አይመጣም ነበረና ወሬ አላገኘሁም። እኔም ስንገዴ ለመሄድአልቻልም ነበር።

ለጓዱ ከእርሷ ጋር የነበረኝን ቀረቤታ ነገርኩት። ትንሽ ዝም ብሎ ቆየ፤ እኔም እንደማያውቃት እያሰብኩ ተስፋ ወደመቁረጡ አዘነበልኩ። እርሱ ግን እንዴት እንደሚነግረኝ ግራ ገብቶት ነበር። ምናልባትም ከእርሷ ጋር ስለነበረኝ ቀረቤታ መጀመሪያ ባልነግረው ኖሮ እንዲህ አይጨነቅ ይሆናል። ይህንን የተረዳሁት በኋላ ነበር። አንገቱን ወደ መሬት ደፍቶ ቆየና ጉሮሮውን አጸዳድቶ ቀና ብሎ ሲያየኝ ልቤ ደነገጠ። ሰላማዊት ታማለች፣ ወይ ታሥራለች አለያም ቆስላለች፤ ብቻ መጥፎ ነገሮች በሙሉ ተሰብስበው በሐሳቤ መጡና አሸበሩኝ።

"ምነው ምን ሆናለች? ደኅና አይደለችም እንዴ?" ብዬ ጮህኩበት።

"ብቻ እኔም በዓይኔ አላየሁም ወሬ ነው የሰማሁት ታማ ለትንሽ ጊዜ ተኝታ ነበር" አለኝ።

"እና!" አልኩት በድንጋጤ።

"በሽታዋ በእኛ ህክምና ደረጃ የማይቻል ሆኖ ወደሌላ ቦታ ሊወስዷት እየሞከሩ ሳለ ....." ብሎ አልጨረሰም ወይም እኔ መጨረሻውን አልሰማሁትም። ብቻ ራሴን ይገፍ መጮህ ጀመርኩ። በነበርኩበት ቦታ ላይ ቁጭ ብዬ ብዙ አለቀስኩ። ዕንባዬ አልቆም አለኝ። በብዙ ትግል ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩ። ቁምነገሯና ጨዋታዋ፣ በተለይ በቀይ ክብ ፊቷ ላይ የሚበራው ደማቅ ፈገግታዋ ትዝ ሲለኝ የቆመው ዕንባዬ እንደገና ይወርድ ነበር።

***





## ዳንግለት

"በጦርነት ሕይወት ውስጥ ቀልጣፋ እንቅስቃሴ ሁልጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም እውነተኛ መልኩ የሚታየው ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ነው።"

ያልታወቀ ተዋጊ፤ 1850ዎቹ

በኅዳር ወር 1970 ዓ.ም. የውቅሮን ካምፕ በቀን ለማጥቃት ዕቅድ ወጥቶ ከኃይል ስልሣ ስድስት ጋር ተቀላቅለን ተንቀሳቀስን። የተልእኮው ዓላማ ዳንግለት ላይ ሶስት የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎችን አስገድዶ በመያዝ ውቅሮ በሚገኘው የደርግ ጦር ካምፕ ላይ በቀን ድንገተኛ ወረራ መፈጸም ነበር። ዳንግለት ከውቅሮ በስተሰሜን አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሥፍራ ነው። ከዳንግለት አምስት ኪሎሜትር ያህል ወደ ደቡብ ሲጓዙ አልነጋሽ የሚባለው ታሪካዊው መስጊድ ይገኛል።

በዚያ ተልእኮ የተሳተፍነው ከኃይል ስልሣ ስድስትና ከኃይል አምስት መቶ በድምሩ ወደ መቶ ሀምሣ የምንሆን ታጣቂዎች ነበርን። የኃይል አምስት መቶ መሪ ጌትነት ምክትሉ የአቢኢዮ ሲሆኑ የፖለቲካ ሐላፊና ምክትል የፖለቲካ ሐላፊዎች ደግሞ ሰለሞንና ከሡተ ነበሩ።

ሁለቱ ኃይሎች ወደዚያ ተልእኮ ከመሰማራታቸው አስቀድመው የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ነበር። የተልእኮው ዓላማው ምንድነው? ምን መደረግ አለበት? የሥራ ክፍፍሉ ምን ይሁን? በቅንጅትስ መሠራት ያለበት የትኛው ነው? ከጥቃቱ በኋላ የማፈግፈጉ ዕቅዱ እንዴት ይሁን? የሚሉትን ጉዳዮች በዝርዝር ተወያይተውበታል።

በሁለቱም ኃይሎች ወታደራዊ ሥልጠና የወሰዱና ጥሩ ልምድ ያላቸው ጓዶች ነበሩባቸው። ለምሳሌ የውትድርና ሞያና ልምድ ካላቸው መካከል ሻምበል አስረስ፣ ሻምበል ዮሐንስና ሌሎች የመቶ አሊቃዎችም ነበሩበት። በመረጃ ክፍል በኩል ደግሞ ታየ ቶላ፣ ኪዳነ፣ ኪሮስ፣ ኤልያስና ሌሎችም ሰፊ ልምድ ያላቸው አባላት ነበሩ።

በአቅዱ የመጀመሪያ ምእራፍ ላይ የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች ከሚተላለፉበት ከነጋሽ በፊት በዳንግለት በኩል የሚገኝ አንድ ድልድይ አለ። ድልድዩ ካለበት መንገድ አጠገብ ከሚገኝ ኮረብታ ላይ የኃይል አባላቱ ሰፍረው እንዲጠባበቁ ተደረገ። የተወሰኑ ጓዶች ወደ ድልድዩ ስር ወርደው መኪናዎችን እንዲያስቆሙና ዝግጁ እንዲያደርጉ ሲመደቡ፣ አንድ ሌላ ቡድን ደግሞ ከመኪና የወረዱትን ተሳፋሪዎች ከድልድዩ ስር ወስዶ እንዲሰበስብ ተመድቧል። ከዚያ በኋላ የኃይል አባላቶቹ በሦስት መኪኖች ተሳፍረን ወደ ውቅሮ እንጓዛለን። ውቅሮ ላይ በሦስቱ መኪናዎች የሚሳፈሩት የሠራዊት አባላት ሦስት የተለያዩ የሥራ መደቦች ነበሯቸው። በመጀመሪያው መኪና እንዲሳፈሩ የተመደቡት ከመቀሌ ወደ ውቅሮ ለዕርዳታ ሊመጣ የሚችለውን ጦር ይመክታሉ። በሁለተኛው መኪና የሚሳፈሩት በቀጥታ ወደ ውቅሮ የደርግ ወታደራዊ ካምፕ ሄደው ዋናውን ተልእኮ ይፈጽማሉ። ሦስተኛው መኪና ውስጥ ያሉት ደግሞ ከአዲግራት ወደ ውቅሮ ሊመጣ የሚችል ረዳት ጦር ገድበው የሚያስቀሩ ናቸው።

በዳንግላት የመኪና መተላለፊያ (መንገድ) ዳር ካለው ኮረብታማ ቦታ በታሰበው ሰዓት ደረስን። መኪናዎችን የሚያስቆሙና ተሳፋሪዎችን ወደ ድልድዩ ስር የሚወስዱ ጓዶች የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያለ ምንም ችግር አጠናቀቁ። አሁን ሦስት መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ መኪኖች፣ ተሳፋሪዎቻቸው ወርደው ጓዶቹ እንደየምድባቸው ወደታገቱት መኪኖች መግባት ጀምረዋል። የእኔ ቡድን የሥራ ምድብ ከመኪናው የወረዱትን ተሳፋሪዎች ወደ ድልድዩ ስር አስገብቶ መጠበቅ ስለሆነ ከጓድ ሳሙኤል ጋር ሆነን ሥራችንን ያለችግር አጠናቀቅን። እኛ ድልድዩ ስር ቆመን ሌሎቹ ተሳፋሪውን አስወርደው እስኪጨርሱ ጠብቀን ሰዎቹን እዛው በመተው ከጓዶቻችን ጋር ወደየምድብ መኪናችን ሄደን ለመሳፈር ተዘጋጅተናል። የእኔ ምድብ ወደካምፕ የሚገባው ቡድን የሚሳፈርበት መኪና ነው።





ሁኔታዎች በታቀዱበት ሁኔታ እየተፈጸሙ እያለ እኔና ሳሙኤል ድልድዩ ስር እንደቆምን አውቶማቲክ መሣሪያ ሁለት ጊዜ ተተኮሰ። መጀመሪያ ምናልባት የባረቀ መሣሪያ ይሆናል ወይም ቀላል ችግር ሊሆን ይችላል ብለን ስላሰብን ሁሉም ጓዶች መኪና ውስጥ መግባታቸው እስኪነገረን እየተጠባበቅን ነበር።

እንደጠበቅነው አልነበረም፤ ተኩሱ ትንሽ ቆም ካለ በኋላ እንደገና ቀጠለ፣ ከበድ ያለ ችግር መሆኑን ተረዳን። ሁኔታውን ለማጣራት ያለንበትን ቦታ ለቀን ጓዶች መጀመሪያ ተሰብስበው ወደነበሩበት ኮረብታ ላይ በፍጥነት እየሮጥን ወጣን።

ነገሩን ስንጠይቅ፣ በአንደኛው መኪና ውስጥ መጨረሻ ላይ እንዲገቡ ሲጠብቁ የነበሩት የአብኢዮና ታየ ቶላ ለመግባት እየተዘጋጁ እያሉ ከፊት ለፊታቸው የሚመጣ መኪና ያያሉ፤ መኪናው የጫነው ወታደሮች መሆኑን እንዳረጋገጡ መጀመሪያ የተሰማው የአውቶማቲክ መሣሪያ ለማስጠንቀቂያ ተኮሱ።

ዋርድያ እንዲቆም የተደረገበት ቦታ ከሁለቱም አቅጣጫ የሚመጣውን መኪና ለማየት የሚቻልበት ቦታ ነበር። መኪናው ከመጣበት አቅጣጫ በዋርድያነት ይጠብቅ የነበረው ጓድ ምናልባትም ትኩረቱን ወደመሳፈሩ አድርጎ መኪናውን ሲመጣ ሳያየው ቀርቷል። እናም ተኩስ በተከፈተበት ወታደሮቹን በጫነው መኪና እና በታገቱት መኪኖች መካከል የነበረው ርቀት በትንሽ ሜትሮች የሚለካ ነበረ። መኪና ውስጥ የገቡት የእኛ አባላት ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ሊወድቁ ሆነ። ከሕዝብ ማመላለሻ መኪናው ውስጥ በፍጥነት መውረድ አላመቻቸውም። ሁለቱ መኪናዎች ፊት ለፊት ቆመው ፍጥጫ ላይ እንዳሉ እየተገፋፉ በበሩና፣ መስታወቶችን በመስበር በመስኮቶችም በኩል እየዘለሉ እስኪወርዱ ጊዜ ፈጁ። ቀድመው የወረዱት ደግሞ መኪና ውስጥ የቀሩትን በፍጥነት እንዲወጡ ወደማገዝ አተኮሩ። በዚህ መካከል ወታደሮቹ

ቀድመው ቦታ ይዘው መተኮስ ጀመሩ። ከአውቶቡሱ ወርደው ሁሉም ከለላ ለመፈለግ በየአቅጣጫው ሲሮጡ ቅንጅት ጠፋና ተበታተኑ።

እኔና ሳሙኤል ኮረብታው ላይ ወጥተን ስንመለከት መኪና ውስጥ የነበሩት በሙሉ ወርደዋል። የአቢኢዮና ጌትነት ሬድዮ ይዘው ተነጣጥለው በየግላቸው የሚሮጡትን አባሎች ለማረጋጋትና ለማሰባሰብ ወዲህና ወዲያ እያሉ ይጣደፋሉ። እኔና ሳሙእኤል ወደነርሱ ሄድን።

እኛ ስንደርስ ጌትነት ከሲራጅና ከየአቢኢዮ ጋር በሬዲዮ እየተነጋገረ ወደፊት የሄዱትን አባላት ለመመለስ ወዲያና ወዲህ በመሮጥ ላይ እያለ ወታደሮቹ በመነጋገሪያ ሬድዮው አንቴና አቅጣጫ አስተካክለው ተኮሱበትና ጌትነት ተመትቶ ወደቀ ። እርሱን አንስተን ይዘውት እንዲሄዱ ለጓዶች ከላክነው በኋላ እንደገና ወደ ተኩሱ ቦታ ስንመለስ ብዙዎቹ ጓዶች የሉም። ታየ ቶላ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ ጭንቅላቱን በእጁ ይዞ "ጉድ ሆንን! - ጉድ ሆንን!" እያለ ይጮህል።

እኔ፣ የአቢኢዮ፣ ብርሃነ ዓባይ፣ ብርሃኑ የሚባል የደጀን (የጎጃም) ልጅ አጠገቡ ቆመናል "አሁን ተመልሰን ምን እንናገራለን? እንዴት የአሲምባን መሬት እንረግጣለን?! በዚህ ላይ ደግሞ ሸሻችሁ ይሉናል!!" ይላል ታየ ራሱን ይዞ።

"ታዲያ ለምን አንዋጋም፣ ለምን ውጊያውን አንቀጥልም?" አልነው።

"ኋላ ደግሞ ያለፍቃድ ጦር አንቀሳቅሳችሁ ብለው ወቀሳ እንዳይመጣብን ነው እንጂ ..."አለና ዝም አለ።

በዚህ ጊዜ ተከሥተ አጠገባችን ደርሶ ነበር "እንዳትወቀሱ እንኳን እኔ አለሁኝ። ጦርነት ለመፍቀድ ሥልጣን አለኝ። ስለዚህ ለእናንተ ሙሉ ሐላፊነት እሰጣችኋለሁ!!" ሲለን ሁላችንምተደሰትን። ተከሥተ የኃይል አምስት መቶ ምክትል የፖለቲካ ሐላፊ ስለነበረ ውጊያ ለመፍቀድ ሥልጣን ያለው በመሆኑ ጥሩ ጊዜ ደረሰልን።





"በዚህ ከተስማማን፣ ለጊዜው ወታደራዊ መሪ ሁነን" ብለን ሻምበል ዮሐንስን ጠየቅነውና "እሺ" አለን። እየተነጋገርን መታኮሳችንን ቀጥለናል።

ቢራራ መትረየስ ይዞ ሽፋን እንዲሰጠን ተመደበ። ሌሎቻችን ደግሞ ወደ ጠላት ኃይል ለመጠጋት መንቀሳቀስ እንደጀመርን ሻምበል አስረስ "የመንግሥት ኃይሎች ድንጋይ ይወረውራሉ፣ ድንጋይ በሚወረውሩበት ጊዜ ቦንብ መስሏችሁ ቦታ ለመቀየር ስትሉ አነጣጥረው ይተኩሱባችኋልና እንዳትታለሉ። እንዳየነው ይሄ ጦር ተራ ጦር አይደለም፤ ከፍተኛ ልምድ ያለው ጦር ሳይሆን አይቀርምና ተጠንቀቁ" አለን። ወደ ተኩስ ውስጥ ስንገባ ሻምበል አስረስ እንዳለው ተጠግተው ቆይተው በእኛ ላይም ጥቃት ለመፈጸም ሞከሩ።

ቢራራ "የኢሕአፓ ጦር ነን! እጃችሁን ስጡ!!" እያለ የፓርቲውን ቀይ ባንዲራ እያውለበለበ እየጮኸ ሊያናግራቸው እየሞከረ ነበረ። እነርሱ ግን በማጥቃት መተኮሳቸውን ቀጠሉበት። ከዚያ በኋላ ቢራራ የያዘውን መትረየስ ደግሞ የሽፋን ተኩስ ይሰጠን ጀመረ። እርሱ ሽፋን ሲሰጠን እኛም ቦታ እየያዝን ማጥቃት ጀመርን። እነርሱ ደግሞ ቀስ እያሉ በማፈግፈግ ቦታ መልቀቅ ያዙ። በዚያ ጊዜ እየተከታተልን አጣደፍናቸው። አስፋልቱን ቆርጠን ወደፊት ስንገፋ አንድ ላይ የነበሩት በሁለት በኩል ተከፈሉ።

እኔ፣ ታዬ ቶላ፣ ብርሃነ ዓባይ፣ ብርሃኑ፣ ተመስገን፣ረደአይ፣ አዳዩና፣ ሌሎችም እነርሱን ከቆረጥን በኋላ ገደል ላይ ሆነን ወደፊት ተኩስ ቀጠልን። በዚህ ጊዜ ከበስተግራ በኩል መንቀሳቀሻ አጥተው የነበሩት የአቢኢዮ፣ ሲራጅ፣ አስማማውና ከእነርሱ ጋር የነበሩት፤ እንዲሁም ከኋላ የነበሩ የእኛ ጓዶች ነጻ ሆኑ። ከዚያ በኋላ ወደ ውጊያው መቀላቀልና ማጥቃት ሲጀመሩ ኃይላችን ተጠናከረ ። በመጨረሻው የጠላት ጦር አፈግፍጎ ወደ አዲግራት ሸሽቶ ሲሄድ፣ ወደፊት የሄደው ደግሞ በዚያው ተበታተኖ ጠፋ።

በውጊያው ከወታደራዊ ሥልጠና የመጣ አንድ መቶ አለቃ ሲሠዋብን፣ ብርሃነ ዓባይ ቆሰለ። በኋላ ቆይተን እንደሰማነው ብርሃነም

የቆሰለው በእነርሱ ወታደሮች አልነበረም። ጉዳዩ ሊታወቅ የቻለው ከወራት በኋላ ሲሆን ኃይል ስልሣ ስድስቶች አንድ ሽፍታ በሌላ ምክንያት ይዘው ሲመረምሩ ነበር። በዚያ የተኩስ ልውውጥ ላይ አስፋልቱን ቆርጠን ሄደን ሳለን ብርሃነ አንድ ትልቅ ቤት ተሸኪል(ምሽግ) ተከልሎ ነበረ። እዚያ ቤት ውስጥ የነበረው ሽፍታ ደግሞ በድንገት ተኩስ ሲሰማ ደንግጦ በመተኮሱ ብርሃነን ግራ እጁ ላይ አቆሰለው። ተይዞ ሲመረመር ይህንኑ ተናገረ።

በመጨረሻእንደገና ተመልሰን ከኋላ የነበሩ ጓዶችን አደራጅተን ማፈግፈግ አደረግን። በማግስቱ የተወሰንን ሰዎች ከሡተ፣ እኔ፣ ታየ ቶላ፣ ኪዳነ ኪሮስና ሌሎችም በጠቅላላው ወደ ሰባት ሆነን ሁኔታውን ለመሰለል ተመልሰን ዳንግላት ሄድን። ደርግ ሌላ የተደራጀ ጦር ለአሰሳ ልኮ ስለነበር ያ ጦር ፊት ለፊታችን እስኪቀርብ ድረስ አንድ ቦታ ተደብቀን አየነው። ያን ቀን አሰሰው ምንም ሳያገኙ ተመለሱ። ማታውን ደግሞ ከአዲግራት አቅጣጫ ብዙ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች መብራት እያበሩ ሲመጡ ተመለከትን።

***





በዚያው ዓመት በኅዳር ወር መጨረሻ እንደገና ከአድዋ ወደ ደብረ ዳሞ ተንቀሳቀስን። ከገዳሙ አጠገብ መዛምር ዳሞ የሚባል ትልቅ መንደር አለ። ወደ መንደሩ የመጣንበት ምክንያት፤ ቀደም ሲል ከውጭ ሀገር በኤርትራ ነጻ አውጪ ድርጅት በኩል የመጡ የራሳችን የሆኑ መሣሪያዎች ጾረና ገብተው ከዚያም ወደ መዛምር ዳሞ መጥተዋል የሚል መልእክት ስለደረሰን ነበር። ጾረና ኤርትራን ከትግራይ የሚያዋስን ነጻ የወጣ በረሀማ አካባቢ ነው። መሣሪያዎቹን ከመዛምር ዳሞ ወደ አሲምባ መውሰድ ነበረብን።

ከኤርትራ መዛምር ዳሞ የመጡትን መሣሪያዎች ተሸከመን አጋሜ አውራጃ ለመድረስ በሌሊቱ ተነሣንና ተራራውን በመውጣት ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ጉዟችንን ቀጠልን። ምን ጊዜምቢሆን ከአጋሜወደ አድዋ ወይም ከአድዋ ወደ አጋሜ በምንሄድበትጊዜ በመካከል የሚገኙትን ታላላቅና አስቸጋሪ ተራራዎች መውጣትና መውረድ የግድ ነበር። የተነሣነው በሌሊትም ቢሆን መሣሪያዎቹንና ትጥቃችንን ተሸክመን ተራራዎቹን ስንወጣና ስንወርድ ተዳከመን ነበር። ከፊት "ማውንቴንስ አር ፔፐር ታይገርስ" የሚል የእንግሊዘኛ ቃላት የያዘ መልእክት መጣ። ከመጀመሪያ የመጣው መልእክት እየተቀባበለ መጨረሻ ሰልፍ ላይ እስካለው ሰው ድረስ ይሄዳል። እንደሚመስለኝ "አይዞዋችሁ! በርቱ! ተራራውን አይታችሁ አትፍሩት!" ለማለት ነበር።

ከአዲግራት ወደ ዛላንበሳ የሚወስደውን አስፋልት መንገድ በጥንቃቄ አለፍንና ሊነጋ ሲል ሰግላት ገባን። ሰግላት እንደገባን ያረፍነው የቄስ ካባ ቤት ነበር። ከሰግላት ደግሞ መሣሪያውን ተቀብላ ወደ አሲምባ የምትወስድ ሌላ ኃይል ስለሆነች ኃይሉዋ እየጠበቀችን ነበር። ሌሊቱን በሙሉ እቃ ተሸክመን በአሸቻጋሪ መንገድ ስለመጣን እንደምንደክም አውቀው የምትጠብቀን ኃይል አባላት ቄስ ካባ ቤት ውስጥ ምግብ አዘጋጅተውልን ነበር።

ቄስ ካባ የዚሁ የሰግላት መንደር የግሎማከዳ ወረዳ ተወላጅ ናቸው። ከመጀመሪያጀምሮ የኢሕአሥን ሥራዎች ተቀብለው ለድርጅቱና ለሠራዊቱ

ከፍተኛ አስተወዋጽኦ ያበረከቱ ሰው ናቸው። ቤታቸው የሠራዊቱ ትጥቅና ስንቅ ማእከል ከመሆኑም በላይ ቄስ ካባ ሁለት ልጆቻቸውን ለትግሉ የሰጡ በኢሕአፓ ዓላማ ትልቅ እምነት የነበራቸው የተከበሩ አባት ነበሩ። ቄስ ካባ በጣም ረዥም ቁመት፣ ደልዳላ ሰውነት ያላቸውና ጢማቸውን የሚያሳድጉ ስለነበሩ አንዳንድ ጓዶች የኩባውን መሪ ፊደል ካስትሮን ይመስላሉ ይሉ ነበር። አሜሪካን መጥቼ ካስትሮን ቢጋዜጣና በቴሌቭዥን ሳየው እውነትም ጢማቸው፣ ቁመናቸውና ግንባራቸው የካስትሮን እንደሚመስል አረጋገጥኩ። ቅላታቸውም፣ አቋቋማቸውና ደረት ሰፊነታቸውም ሁሉ ከካስትሮ ጋር የሚመሳሰል ነበር። ቄስ ካባ ጠንካራ ሰው፣ ጥሩ ተናጋሪና ከፍተኛ የማሳመን ችሎታ የነበራቸው የድርጅቱ ዋና ደጋፊ ሲሆኑ ምናልባትም የፓርቲ አባል ሳይሆኑ አይቀሩም።

በነጋታው ያመጣናቸውን መሣሪያዎች ለምትጠብቀን ኃይል አስረክበንና ዐረፍ ብለን እንደገና ወደ ዳሞ ወረዳ ሄድን። ብዙት ከመድረሳችን በፊት ዓሙስ የሚባል መንደር አጠገብ ስንደርስ በርከት ያሉ አርሶ አደሮች እኛን ለማናገር ተከትለውን መጡ። ቦታው ዓሙስ ከመግባታችን በፊት ወደቀኝ በኩል ያለ መንደር ነው። በዚህ ጊዜ ብዙ የዳሞ ነዋሪዎች የሚተዳደሩት በኢሕአሠ ስር ነበር ። በአካባቢው ጠንካራ ካድሬዎች ስለነበሩ፣ በመጀመሪያ መሬት ያከፋፈልንበትም ቦታ ስለሆነና ከፍተኛ ድርጅታዊ ሥራዎች ስለሠራንበት በአካባቢው ጥሩ ተቀባይነት ነበረን። በዚህ ቦታ ላይ ብዙ ጊዜ ከሠሩ ካድሬዎች መካከል ገብረ ጻድቃን ነጋሽ ፣ ኤሊያስ፣ ጥሪት፣ ሀጎስ፣ ራሄል እና የመሳሰሉ ጎበዝ ጓዶች ይገኙበታል።

እኛ ስንደርስ ግን ከሊፋ የሚባል አንድ የአዲግራት ልጅ በካድሬነት ተመድቦ ይሠራ ነበር። የከሊፋ አመራርና አሠራር ግን ህሕቡን አላስደሰተም ነበረና የከሊፋን አስተዳደር በመጥላት ለ ወያኔ አመልክተው እነርሱ እንዲያስተዳድሯቸው የጠየቁ ሰዎች ነበሩ። በነበረው አሠራር ሕዝቡ ወያኔና





ኢሕአፓ ወይም ተወካዮች በተገኙበት ድምፅ መስጠት ነበረበት። አብዛኛውን ድምፅ ያገኘው ድርጅት አመራሩን ይረከባል። በዚያ ሁኔታ ሕዝብ በፈለገበት መንገድ ለመስተዳደር ይችላል። ስለዚህ በከሊፋ ያልተደሰቱ ሰዎች ወያኔዎችን ጠርተው የህዝቡ ድምጽ እንዲጠየቅ ቀጠሮ ይዘዋል። የድምፅ መስጫው ቀን ከመድረሱ በፊት የእኛ ደጋፊዎች ኃይል አምስት መቶን አነጋግረዋል። ለዚህ አስፈላጊ ቀን ጠንካራ ሰዎች እንዲላኩላቸውና በዚህ ሁኔታ ከሊፋ በሌለበት ሕዝቡን ለማነጋገር አቅደው ነበር ወደ እኛ የመጡት።

ኃይል አምስት መቶ የሕዝቡን ጥያቄ በመቀበል ሦስት ሰዎች እንዲመደቡ ወሰነ። በዚህ መሰረት እኔ፣ አሰፋና ሮምሀ ተጠርተን ጉዳዩ ተነገረንና በተባለው መሠረት ለማስፈጸም ሄድን። አሰፋና ሮምሀ ቀድሞም በደንብ የሚተዋወቁ የመቀሌ ልጆች ናቸውና። አሰፋ መቀሌ ውስጥ ቻይና ግሩፕ ተብሎ ይጠራ የነበረው የጎረምሶች ቡድን አባል የነበረና ደልዳላ የስፖርተኛ ሰውነት ያለው ነበር። እኔና አሰፋ ለመልእክት አብረን ተመድበን ብዙ ጊዜ ወደተለያዩ ቦታዎች በመሄድ አብረን ሠርተናል። አሰፋ በማታ የማየት ችግር ስለነበረበት ትንሽ ከጨለመ የሰው እግር እየተለከተለ ነበር የሚራመደው። እንደቻይና ግሩፕ አባልነቱ ሳይሆን በጣም ሲበዛ ትዕግሥተኛ ነበር። ሮምሀ ደግሞ መጀመሪያ የወያኔ አባል የነበረ ሲሆን፣ እጁን ለደርግ ሰጥቶ ከበረሀ ወደ ከተማ ገብቶ ነበር። እንደገና ከአዲስ አበባ በኢሕአፓ ተመልምሎ የከተማ ታጣቂ ሆኖ ሲሠራ ከቆየ በኋላ ሲጋለጥ ነበር ወደ አሲምባ የመጣው። ሁለቱም ጥሩ ተናጋሪዎች ሲሆኑ ምናልባትም የፓርቲ አባሎች የነበሩ ይመስለኛል።

ሮምሀ በመጀመሪያ የወያኔ አባል ስለነበረ እርሱን ከወያኔ ጋር በሚያገናኝ ስራ ውስጥ ማስገባት ብዙ ንትርክ የሚያስከትል ነበር። ይህ እየታወቀ በዚያን ቀን ለምን እንደተመደበ ባላውቅም በትእዛዙ መሠረት ሁለቱም በስብሰባው እንዲካፈሉ ተደረገ። እኔ በወታደራዊና ጸጥታ በኩል ሐላፊነት ተሰጥቶኝ ተልእኮውን ለመፈጸም ከመጡት ደጋፊዎቻችን ጋር ወደ መንደሩ አመራን።

መጀመሪያ ወደመንደሩ በድብቅ በመግባት፤ ከሊፋን ወደ ስብሰባ እንዳይመጣና ከኃይል አምስት መቶ የተመደቡ ጓዶች ነገሩን ለመፍታት እንደተላከን መልእክት አስተላለፍንለት። በሁለተኛ ደረጃ ጠንካራ የሆኑ አባሎችን ስብሰባ በሌሊት ጠራን። ሦስተኛ ደግሞ የስብሰባውን ቀን ቀይረን፣ በማግስቱ ሕዝቡ እንዲጠራ ጠየቅን። ይህን ያደረግንበት ምክንያት ሁኔታውን ለማጥናትና ደጋፊዎቻችንን በደንብ ለማጠናከር ነበር። የሚሰበሰበው የሦስት መንደር ሕዝብ ስለነበር የሕዝቡም ቁጥር በርካታ ነበር ።

በማግስቱ መመለስ ሲገባን ምንም ማድረግ ስላልቻልን ቆይታችንን በአንድ ቀን አራዘምነው። በማግስቱም እኛ ሦስታችን ከሁለት የወያኔ ካድሬዎች ጋር ሆነን ቀኑን ሙሉ ስብሰባ ዋልን። በስብሰባ ውስጥ የነበሩ ሁለት ወያኔዎች ከሮምህና ከአሰፋ ጋር ቀድሞም ይተዋወቁ ስለነበር፣ አለመግባባት ተፈጥሮ አሰፋ በስሜታዊነት ከሥነሥርዓት ወጭ የመሄድ አዝማሚያ አሳየ። ነገሩ የወጣትነት ስሜትና፣ ካለማስተዋል የተከሠተ መሆኑን ስለተሰማኝ አካሄዱ አስፈላጊ አለመሆኑን ለአሰፋ አስረዳሁት። ከወያኔ ካድሬዎች‧አንደኛው በሰል ያለና ችግሩን ሊረዳ ይችላል ብየ በመገመት አነጋገርኩትና ያለመግባባቱ በርዶ ስብሰባው በሰላም ተጠናቀቀ።

በመጨረሻም ድምፅ እንዲሰጥ ተደረገና በተቆጠረው ድምፅ የእኛ ድርጅት በለጠ። መንደሩ በእኛ ድርጅት እንደሚተዳደር ተገልጾ አብዛኛው ሕዝብ በጭብጨባ ውጤቱን አጽድቆ ስብሰባው ተበተነ። በዚያን ዕለት ከነበሩት የወያኔ ካድሬዎች መካከል ያነጋገርኩት አዲስ ዓለም ባሌማ ነበረ። በዚያ አጋጣሚ ዓዲስ አለም በሳልና ትዕግሥተኛ ሲሆን ጥሩ የቅራኔ አፈታት ችሎታ የነበረው ሰው መሆኑን ተመልክቻለሁ።

ያንን በሕዝብ ድምፅ ለመዳኘት በሁለት የተለያዩ ድርጅቶች መካከል የነበረውን ስምምነት ሳስታውስ፣ ምንም እንኳ ለአጭር ግዜ ቢሆንም፣ በሀገራችን





ደረጃ ካየሁትና ከሰማሁት የመጀመሪያውና ታሪካዊው ሕዝባዊ ዳኝነት ሳይሆን አይቀርምእያልኩ ብዙ ጊዜ አስባለሁ።

በአስገኘነው ውጤት የተደሰቱ የእኛ ደጋፊዎች "ማደር አለባችሁ" ብለው እንደገና አንድ ሌላ ተጨማሪ ለሊት አሳደሩን። የኃይሏ እንቅስቃሴና አቅጣጫ ለእኔ ስለተነገረኝ፣ ሲነጋ ተነሥተን ኃይላችን ወደምትጓዝበት ቦታ መንገዳችንን ቀጠልን።

ረፋዱ ላይ አንድ መንደር አልፈን ስንሄድ በመንደሩ ብዙ ሰው ሲገባና ሲወጣ አየን። እኛ በቶሎ ኃይላችን ጋ ለመድረስ እየተጣደፍን ነበርን። በመንደሩ ውስጥ አንድ ትልቅ ሰርግ ነበርና መንደሩን አቋርጠን ማለፋችንን ደጋሾቹ ሲሰሙ በሩጫ ተከትለው ደረሱብን። "ሰርጋችንን ረግጣችሁ እንዴት ትሄዳላችሁ? ምሳ መብላት አለባችሁ" በማለት ጋበዙን። ግብዣቸውን መቀበል ግድ ቢሆንብንም ብዙ ሕዝብ በሚሳተፍበት ድግስ ውስጥ መታየት ደግሞ አልፈለግንም። ሰዎቹም ሁኔታችንን ተገንዝበው ከነበርንበት አቅራቢያ በሚገኝ ቤት ውስጥ አስገቡንና ዐረፍ እንድንል አደረጉ። ለድግሱ ከተዘጋጀው ምግብ የነበርንበት ቤት ድረስ አመጡልንና ምሳችንን በልተን አመስግነን ጉዟችንን ቀጠልን።

ከኃይላችን ጋር ከደብረ ዳሞ በስተደቡብ በኩል ወደ ሰሮ መውረጃ ላይ ከሚገኝ አንድ መንደር አጠገብ ተገናኘን። መጀመሪያ ያገኘናት የአሰፋን ጋንታ በመሆኑ ተቀላቀልን። አሰፋ ድላይ የነበረችበት ጋንታ አባል ነው። እኔና ሮምሀ ደግሞ ወደ የጋንታችን አመራን፤ ሮምሀ የጋንታ ምድቡ ከእነ ግደይ ጨዓር ጋር ነበር። አሰፋ ወደ ጋንታው እንደተቀላቀለ ድላይ መመለሳችንን ሰምታ እየሮጠች መጣችና ከኋላችን በኩል ሆና ስሜን ስትጠራ ሰማኋት። መለስ ብዬ ሳያት ድላይ ወደ እኔ እየመጣች ነበረች። ልጠብቃት ስቆም ሮምሀን ወደ ጋንታው እንዲቀላቀል ነገርኩት። አጠገቤ ደርሳ ሳያት በጣምተቆጥታለች፤ በጣም ከመናደዷ

የተነሣ ፊቷም ዓይኖቿም በንዴት ቀልተዋል። ስትናደድ ለአደን የተዘጋጀች አንበሳ ትመስላለች። የንዴት ድምፅ አታሰማም፤ ገጽታዋ ግን ይናገራል።

"የት ሄዳችሁ ነው ለሁለት ቀን የቆያችሁት?!" ብላ ጠየቀችኝ።

"የሕዝብ ጉዳይ እንድናይ በአመራሩ ተልከን ነበር ምነው?" አልኳት ቁጣዋ አስደንግጦኝ።

"ብዙዎቻችን ደንግጠናል! ወያኔዎች ሮምህን ፈልገው ችግር ፈጥረውበት ወይም የታፈናችሁ መስሎን ነበር። አንዳንዶች ደግሞ ጠፍተው ነው እያሉ ሲነጋገሩ ነበር" አለች። ከጥቂት ዝምታ በኋላ ደግሞ "ስማ - አማኑኤል!" አለችና ድምጿን ዝቅ አደርጋ "እኔ እኮ አንዳንድ ጊዜ እርስ በእርሳችሁ በትግርኛ ስታወሩ እሰማችኋለሁ! የሆነ ውሳኔ ስትወስን ግን አደራ! እኔን ሳታማክር እንዳትወስን!" አለችኝ።

ቁጣዋና ንዴቷ ረበሸኝ። ነገሯን ሁሉ ከሐሳቤ ሳላወጣው ዋልኩና አመሸሁም። "ምን ሰምታ ይሆን? ወይስ የካዳሁ መስሏት ደንግጣ ነው?" እያልኩ አባባሏን ደጋግሜ አብሰለሰልኩት። "እኔን ሳታማክር እንዳትወስን" ያለችው ነገር በነቃሁ ቁጥር ሲያንቃጭልብኝ ነበር ሌሊቱን ያነጋሁት። በሚቀጥለው ቀን አግኝቻት እስከጠይቃትም በጣም ጉጉት ያዘኝ።

***





ስመኝ

ፍቅርና ትግል የተዋሐዱ ለት

ተመሪው ብስለት ነው፣ መሪው የዋህነት::

(ነቢይ መኮንን ለ60ዎቹ)

የኅዳር ወር አልቆ ታህሣሥ እንደገባ በብዘትና በእንትጮ መካከል በሚገኘው በሰሮ ገጠር አካባቢ አደረግንና የመረብ ወንዝን ተፋሰስ ተከትለን አዕሰአ ወደተባለው የአድዋ አውራጃ ከፍል ሄድን። ወደዚያ ወረዳ ስንሄድ የመጀመሪያ ጊዜያችን ነበር። አዕስአን በሰሜን በኩል የሚያዋስነው የመረብ ወንዝ ነው፤ መረብን ተሻግሮ ሰራዬ የሚባለው የኤርትራ አውራጃ አለ። ኤርትራ ለመግባት መረብ አፋፍ ላይ በሚገኘው የራማ ከተማ በኩል ቅርብ ነው። ራማ ነጻ የወጣ ከተማ ነው። ኃይል አምስት ሙቶም ራማ ከተማ አጠገብ ደርሳ በአረፋይነ የሚመሩ የተወሰኑ አባላት ቀድመው እንዲገቡ ተልከዋል። አረፋይነ የእነድላይ ጋንታ አባልና የኃይሏ የፓርቲ ኮሚቴ ንቁና ጥንቁቅ አባል ነው።

ጊዜው ደርግ ነበልባል የተባለውን ጦር አቋቁሞ በራማ በኩል መረብን እያሻገረ ወደ ኤርትራ ለማዝመት የተነሳበት ወቅት ነው። በአንጻሩ ደግሞ የጦሩ አባላት መሹለኪያ ባገኙ ቁጥር ይጠፉ ነበር። ከጦሩ ጠፍተው ለኤርትራ ተቃዋሚ ኃይል ሠራዊት እጃቸውን ሰጥተው ከገቡ በኋላ ደግሞ በጥያቄያቸው መሠረት ከኢሕአሠ ጋር ለመቀላቀል ወደ ኃይል አምስት ሙቶ የመጡ ሁለት ወታደሮች ነበሩ። ለወታደራዊ ሥልጠና ወደ አሲምባ እስከሚሄዱ ድረስ ከጋንታ አምስት ሙቶ ሦስት ማለትም በቴዎድሮስ ባሪያው ከሚመራው ድላይም ከነበረችበት ጋንታ ጋር እንደማንኛውም የሠራዊቱ አባል እየተንቀሳቀሱ እንዲቆዩ ተደርገዋል።

የተነሣ ፊቷም ዓይኖቿም በንዴት ቀልተዋል። ስትናደድ ለአደን የተዘጋጀች አንበሳ ትመስላለች። የንዴት ድምፅ አታሰማም፣ ገጽታዋ ግን ይናገራል።
"የት ሄዳችሁ ነው ለሁለት ቀን የቆያችሁት?!" ብላ ጠየቀችኝ።

"የሕዝብ ጉዳይ እንድናይ በአመራሩ ተልከን ነበር ምነው?" አልኳት ቁጣዋ አስደንግጦኝ።

"ብዙዎቻችን ደንግጠናል! ወያኔዎች ሮምህን ፈልገው ችግር ፈጥረውበት ወይም የታፈናችሁ መስሎን ነበር። አንዳንዶች ደግሞ ጠፍተው ነው እያሉ ሲነጋገሩ ነበር" አለች። ከጥቂት ዝምታ በኋላ ደግሞ "ስማ - አማኑኤል!" አለችና ድምጿን ዝቅ አደርጋ "እኔ እኮ አንዳንድ ጊዜ እርስ በእርሳችሁ በትግርኛ ስታወሩ እሰማችኋለሁ! የሆነ ውሳኔ ስትወስን ግን አደራ! እኔን ሳታማክር እንዳትወስን!" አለችኝ።

ቁጣዋና ንዴቷ ረበሸኝ። ነገሯን ሁሉ ከሐሳቤ ሳላወጣው ዋልኩና አመሸሁም። "ምን ሰምታ ይሆን? ወይስ የካዳሁ መስሏት ደንግጣ ነው?" እያልኩ አባባሏን ደጋግሜ አብሰለሰልኩት። "እኔን ሳታማክር እንዳትወስን" ያለችው ነገር በነቃሁ ቁጥር ሲያንቃጭልብኝ ነበር ሌሊቱን ያነጋሁት። በሚቀጥለው ቀን አግኝቻት እስከጠይቃትም በጣም ጉጉት ያዘኝ።

***





## ስመኝ

ፍቅርና ትግል የተዋሐዱ ለት

ተመሪው ብስለት ነው፣ መሪው የዋህነት::

(ነቢይ መኮንን ለ60ዎቹ)

የኅዳር ወር አልቆ ታህሣሥ እንደገባ በብዘትና በአንትጮ መካከል በሚገኘው በስሮ ገጠር አካባቢ አደረግንና የመረብ ወንዝን ተፋሰስ ተከትለን አዕስአ ወደተባለው የኢድዋ አውራጃ ክፍል ሄድን። ወደዚያ ወረዳ ስንሄድ የመጀመሪያ ጊዜያችን ነበር። አዕስአን በሰሜን በኩል የሚያዋስነው የመረብ ወንዝ ነው፤ መረብን ተሻግሮ ሰራዬ የሚባለው የኤርትራ አውራጃ አለ። ኤርትራ ለመግባት መረብ አፋፍ ላይ በሚገኘው የራማ ከተማ በኩል ቅርብ ነው። ራማ ነጻ የወጣ ከተማ ነው። ኃይል አምስት መቶም ራማ ከተማ አጠገብ ደርሳ በአረፋይነ የሚመሩ የተወሰኑ አባላት ቀድመው እንዲገቡ ተልከዋል። አረፋይነ የእነድላይ ጋንታ አባልና የኃይሏ የፓርቲ ኮሚቴ ንቁና ጥንቁቅ አባል ነው።

ጊዜው ደርግ ነበልባል የተባለውን ጦር አቋቁሞ በራማ በኩል መረብን እያሻገረ ወደ ኤርትራ ለማዝመት የተነሳበት ወቅት ነው። በአንጻሩ ደግሞ የጦሩ አባላት መሹለኪያ ባገኙ ቁጥር ይጠፉ ነበር። ከጦሩ ጠፍተው ለኤርትራ ተቃዋሚ ኃይል ሠራዊት እጃቸውን ሰጥተው ከገቡ በኋላ ደግሞ በጥያቄያቸው መሠረት ከኢሕአሠ ጋር ለመቀላቀል ወደ ኃይል አምስት መቶ የመጡ ሁለት ወታደሮች ነበሩ። ለወታደራዊ ሥልጠና ወደ አሲምባ እስከሚሄዱ ድረስ ከጋንታ አምስት መቶ ሦስት ማለትም በቴዎድሮስ ባሪያው ከሚመራው ድላይም ከነበረችበት ጋንታ ጋር እንደማንኛውም የሠራዊቱ አባል እየተንቀሳቀሱ እንዲቆዩ ተደርገዋል።

ኃይሏም ከራማ ተመልሳ ወደ ደቡብ በመንቀሳቀስ በፈረስ ማይ በኩል ተጉዛ ወደ ምዕራብበመዞር አድዋ ከተማ አጠገብ በስተምሥራቅ በኩል አባ ገሪማ ወረዳ ውስጥ ከሚገኝ ገዲባ የሚባል መንደር ገባን። እኛ እዚህ መንደርም ስንመጣ የመጀመሪያ ጊዜያችን ቢሆንም በድብቅ የሚሠሩና ሕዝቡን የሚያደራጁ ካድሬዎቻችን ይንቀሳቀሱበት ነበር። ገበሬ መስለው የሚሠሩ ሴት ካድሬዎች ጭምር አግኝተናል።

ከመንደሩ ፊት ለፊት አድዋ ውስጥ የሚገኘው እምባ ስሎዳ የተባለው ትልቁ ተራራ ይታያል። መንደሯ ለአድዋ ከተማ ቅርብ ስለሆነች ከአድዋ ከተማ የሚመጡ ዘማች ተማሪዎችንለመገናኘት የወያኔም የእኛም አባላት ወደዚያ ቦታ ይመላለሳሉ። በመሆኑም የሕዝቡ የፖለቲካ ንቃት ያደገበት አካባቢ ነው።

አንድ ቀን በጋራዎች መካከል በሚገኘውና ገድባ በሚባለው መንደር ወርደን ዐረፍን። ከጋንታ አምስት መቶ ሦስት ወደ ኃይል አመራሮች አንድ መልእክተኛ ተልኮ መጣ። መልእክቱም "ከኤርትራ መጥተው ተቀላቅለው የነበሩት ሁለት የነበልባል ጦር አባላት በሌሊት ጠፍተው ወዴት አቅጣጫ እንደሄዱ አልታወቀም" የሚል ነበር።

መልእክቱ እንደደረሰ የኃይሏ ወታደራዊ መሪና የፖለቲካ ሐላፊ የአቢኢዮና ሰለሞን ተረብሸው ይነጋገራሉ። መንገዱ ለአድዋ ከተማ ምን ያህል ቅርብ እንደሆነ ለመገመት እንደሚሞከሩ ገብቶኛል። የእኔ ጋንታ የነበረችበት ቦታ ከአድዋ በስተጀርባ ካሉ ተራራዎች ማዶ ትታያለች። ከተራራዎቹ እኛ ወደነበርንበት ቦታ ያለውን መንገድ ለመቆጣጠር አንድ ዋርድያ ራቅ አድርገን አቁመናል። እኔ የቀኑ ዋርድያ ሐላፊ ስለነበርኩ ከዋርድያው በስተጀርባ የሚገኝ ገደል አፋፍ ላይ ቁጭ እንዳልኩ ነበር የአቢዮና ሰለሞን የመጡት።

እነርሱ በመነጋገር ላይ እንዳሉ ድላይ እየተቻኮለች ወደ እነሱ መጣችና ስለጠፉት ወታደሮች መነጋገር ጀመረች። እኔ አፋፉ ላይ እንደተቀመጥኩ ነው።





የጠፉት ከነድላይ ጋንታ ስለነበረ እነርሱም ስለአጠፋፋቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመሩ። ትንሽ ከተነጋገሩ በኋላ ድላይ አንድ ሐሳብ ስታቀርብላቸው ይሰማኛል። "ትናንትና የዋልንበት ሰፈር አንድ ቤት ገብተው ሰዎችን ያነጋግሩ ነበር። እዛ ሰፈር ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ጥርጣሬ አለኝ፤ ከሰዎቹ ጋር ምን እንደተባባሉ አላውቅም። አማኑኤልን መድቡልኝና ከሰዎቹ ምን እንደተነጋገሩ ጠይቀን አካባቢውንም ፈትሸን ብንመጣ ጥሩ ነው" አለቻቸው።

የአቢኢዮና ሰለሞንም በሐሳቧ ተስማምተው "ጥሩ ሐሳብ ነው፣ እንዲያውም አማኑኤል አብሮሽ ከሄደ ሌላ ተጨማሪ ሰውም አያስፈልገሽም። አሁኑኑ ፈጥናችሁ ተነሡ" አሉ። ከዚያም ከድላይ ጋር እንድሄድ ነገሩኝና፣ ኃይሏ የምታድርበትን ቦታና የሌሊት የምስጢር ቃል አሳወቁን። የአቢኢዮ እኔንም ጨምሮ የሚወደውን ሰው በሚጠራበት በተለመደው አነጋገር "ወዲ ሐፍተይ" አለኝና "አይዞህ ጠንቀቅ በል፣ በተቻለ መጠን የወያኔ ካድሬዎች ዘማች ተማሪዎችን እያነጋገሩ ስለሆነ፣ እነሱን ሳትጠጉ ድላይ የምታሳይህ ቦታዎችን ፈትሻችሁና፣ ያገኛችሁትን መረጃ ይዛችሁ ቶሎ ተመለሱ" በማለት ትእዛዝ ሰጠኝ።

ለጥቂት ቀናት እኔና ድላይ እንደልብ የምናወራበት ዕድል አልነበረንም። ብንገናኝም ከሰላምታ አልፈን የግል ሐሳባችንን ለመጫወት ዕድሉንም ጊዜውንም አላገኘንም። ከዳም ከሮምሀና ከአሰፋ ጋር ሁለት ቀን አድረን የመጣን ጊዜ፣ እየሮጠች መጥታ በንዴትና በድንጋጤ ስለተናገረችኝ ሆዴን እየበላኝ ቆይቻለሁ። ለመጠየቅም አንድ አጋጣሚ እየጠበቅሁ ነበር። አሁን በዚህ አጋጣሚ ለመጠየቅና የፈለግነውን ምስጢር ለማውራት ጥሩ ዕድል በማግኘታችን ደስ አለኝ። ወደታዘዝነበት ቦታ ለመሄድ መንገድ ስንጀምርና ገደሉን ስንወርድ በሁለታችንም ገጽታ ላይ ደስታ አረብቦበት ነበር።

ሁለታችንም የለበስነው የሠራዊቱን የደንብ ልብስ ነበር። የደንብ ልብሱ ቀለም ሰማያዊ ሲሆን ከታች የለበስነው ቁምጣ ሆኖ ትንሽ አደፍ ስላለ ወደ አፈርማ መልክ ያደላል። የሁለታችንም ጸጉር ጎፈሬ ነው። ሁለታችንም ክላሽን ይዘናል።

እንዲሁም የሰውነታችን ቅርጽ ስለሚመሳሰል ፊትና ኋላ ሆነን ስንሄድ ምን እንደምንመስል አሰብኩ። የምንፈልገውን ቦታ የምታውቀው እርሷ ስለነበረች ጠመንጃዋን በቀኝ ትከሻዋ አንግታ የግራ እጇን እያወዛወዘች ከፊት ከፊት ትሄዳለች፤ እኔ ጠመንጃዬን በግራ በኩል አንግቼ የቀኝ እጄን እያወዛወዝኩ ከኋላዋ እከተላለሁ።

ከተነሣንበት የገደሉ አፋፍ ጀምሮ ብዙ እስከምንሄድ ድረስ ሰው የሚሄድበትን የእግር መንገድ አቅጣጫ አልተከተልንም። ያን መንገድ የመረጥንበት ምክንያት ምናልባትም ብቻችንን ለመሆን ከነበረን ትልቅ ጉጉት የመጣ ይሆናል የሚል ግምት አድሮብኛል። ገደሉን እየዘለልንና ጥሻውን እየጣስን ብዙ ከሄድን በኋላ ነበር የእግረኛ ዱካ ምልክት ያለውን መስመር መያዝ የጀመርነው።

ከዓመታት በኋላ የዚያን ቀን አካሄዳችንን፣ የፍቅርና የኩራት እንዲሁም በራስ የመተማመን መንፈሳችንን ሳስበው "ዘ ላየን ኪንግ" ከተሰኘው ዝነኛው የካርቱን ፊልም ላይ ካለ አንድ ትእይንት ጋር አመሳስዬ አሰብኩት። የግዛቱ የዱር እንስሳት ንጉስ ሙፋሳ ይባላል። የሙፋሳ ልጅ ደግሞ ሲምባ አለ። ሲምባ የንጉሥ ልጅ ስለሆነና እንደአባቱ ታላቅ የመሆን ፍላጎት ስላደረበት ያን በተግባር የሚመለከትበትን አጋጣሚ ይፈልግ ነበር። "እራሴን ችዬ ለማደንም ሆነ ለመንቀሳቀስ እችላለሁ" ብሎ ከጓደኛው ናላ ከምትባል እንስት አንበሳ ጋር ተያይዘው ይወጣሉ። ሁለቱም ፍቅር ኩራትና በራስ መተማመን አድሮባቸው በደስታ እየፈነደቁ ጫካውን አቋርጠው ሲጓዙ ከነበራቸው ስሜት ጋር የሚመሳሰል ስሜት ነበር በእኔና ድላይም ላይ የነበረው።

ሲምባና ናላ እየፈነጠዙ በጫከው ውስጥ እንደሚቦርቁት፣ እኔና ድላይም ገደሉን እየዘለልን ጥሻውን እየጣስን እየተያየንና በቅልጥፍና እየተራመድን የግል ነጻነታችንን በማግኘታችን እየቦረቅን፣ በየንግግራችን መሐል እየተሳሳቅን





እየተፍለቀለቅን ነበር የምንጓዘው። የፍቅርና የጓድ እንዲሁም የጓደኝነታችንን ልዩ ጥማት ለመወጣት ያስቻለንንዕድል በስሜት እንጂ በቃላት ለመግለጽ እንደማይቻል በደመነፍስ ታውቆን እየፈነጥዝን ወደፊት ገሰገስን።

ከተነሣንበት ቦታ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ተጉዘን ማይ ምሻም የሚባል ተራራ አጠገብ ደረስን። እዚያ ቦታ ቀደም ሲልም መጥተንበታል፤ አንድ የፕሮቴስታንት ክርስቲያን ሚሽን ያቋቋመውና የሚያስተዳድረው መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አለ። ከተራራው ስር ደግሞ ወደ እዳጋ አርቢ ከተማ አቅጣጫ የሚያመለክት ቅስት አለ።

አካባቢው ወልቃይት ውስጥ የተሠዋው ፋኑስ የሚባል ጓድ የትውልድ ሀገር ነው። ፋኑስ ወልቃይት ውስጥ ከኪዳኔ ኪሮስ ጋር ለሠራዊቱ ተልእኮ እየተንቀሳቀሱ እያሉ አንድ መንገድ ከሚመራቸው ገበሬ ጋር ሆነው ሊታጠቡ ወደ ወንዝ እንደወረዱ ጠመንጃቸውን ለመውሰድ በፈለገው በመንገድ መሪው ገበሬ የተገደለ ጓድ ነበር። ፋኑስ፣ ወልቃይት አካባቢ በመረጃ ክፍል ሥራ ብዙ ውጤት ያስገኘ ጠንካራ ጓድ ነበር። እናም በትውልድ ቦታው ውስጥ ስናልፍ ፋኑስን አስታወስኩት።

ቁልቁለቱን ወርደን እንደጨረስን የማይ ምሻምን ተራራ ከመውጣታችን በፊት ውኃ መጠጣት ነበረብን። ከአገኘናቸው ጥቂት ቤቶች ውስጥ ወደ አንደኛው ጎራ አልን። ቤት ውስጥ ሦስት ሴቶች ነበሩ፤ ውኃ ሰጥተውን ከጠጣን በኋላ "የደከማችሁ ትመስላላችሁ ትንሽ ዐረፍ በሉና ትሄዳላችሁ" አሉን። እኔ በሩ አጠገብ ድላይ ደግሞ በስተቀኜ በኩል ተቀመጠች። ሴቶቹ ለእኛ ወጥ ለመሥራት ማድቤት ውስጥ ገብተው መንጎዳጎድ ሲጀምሩ ይታዩናል።

"ትንሽ ለማረፍ ፈልገን ነው እንጂ እንቸኩላለን" አልኳቸው ድምጼን ከፍ አድርጌ።

"ኧረ ግዴለም ትደርሳላችሁ፣ ሽሮ ነው የምናፈላላችሁ፤ ጊዜ አይወስድም" አለች እሳት በማቀጣጠል ላይ ያለችው ሴት።

ዘና ብለን ተቀመጥን፣ የተጠጋጋነው ትከሻ ለትከሻ ብቻ ሳይሆን ጎኖቻችንም ተጣብቀው ነበር። በድንገት ሦስት ጥይት ተከታትሎ ተተኮሰ። እኔ ዘልዬ ወደ ውጪ ወጣሁና ከላሽኔን አቀባብዬ ፊት ለፊት ወደነበረው የፈራረሰ ቤት ጀርባ ሄጄ ከለላ ያዝኩ። ድላይም መሣሪያዋን አቀባብላ ተከትላኝ መጥታ ጎን ለጎን ሆነን ግራ ቀኝ ተመለከትን፤ ምንም ነገር አልነበረም። ድላይን ባለችበት እንድትቆይ አድርጌ ወጣሁና ቤቱን በጥንቃቄ እየዞርኩ ሌላ ታጣቂ ካለ ለማየት ወይም ደግሞ ተኩሱ ከየት አቅጣጫ እንደመጣ ለማጣራት ሞከርኩ። ነገር ግን ምንም ፍንጭ አጥቼ ግራ ገብቶኝ ቆምኩ።

ግራ መጋባቴን ካዩት እቤት ውስጥ ካሉት ሴቶች አንደኛዋ ወጣችና "ተኩሱ እኮ ከእናንተ ነው የወጣው። ከእናንተ ብረት እኮ ነው የተተኮሰው" አለችኝ።

"እንዴ፣ ምን ማለትሽ ነው?" ብዬ አሁንም ግራ ገብቶኝ ጠየቅኳት።

"ማለቴ፣ ተኩሱ ከውጪ ሳይሆን ከቤት ነው የተሰማው፤ ከሁለት በአንዳችሁ ብረት ነው የተተኮሰው እንጂ ከውጪ የመጣ አይደለም" አለች ሴትዮዋ በእርግጠኝነት።

ደነገጥኩ። ለማረጋገጥ ወደቤት ገባሁና ወደተቀመጥንበት ቦታ ስመለከት ሶስት ቀልሆዎች መሬት ላይ ወድቀው አገኘሁ። አሁን ከድላይ ከላሽ የወጣ ተኩስ እንደሆነ አወቅኩና ወጥቼ ወደ ድላይ ሄጄ "ድላይ ነይ እስቲ፣ መሣሪያሽን አንዴ ስጪኝ?" አልኩና መሣሪያዋን ተቀበልኳት። ሳየው መጠበቂያው ክፍት ነው። ወደ አፍንጫዬ አስጠግቼ ሳሸተው፣ ባሩድ ባሩድ ይሸታል። የበለጠ ደነገጥኩ። "ምነው ድላይ?! እንዴት ሊባርቅብሽ ቻለ? ተጠጋግተን እንደተቀመጥነው ቢሆን እኮ ጥይቶቹ ወይ አንቺን ወይ እኔን ሊመቱ ይችሉ ነበር?!" ብዬ የወደቁትን ቀለሆዎች ሳሳያት በድንጋጤ ራሷን ያዘች። ሁለት ልጆች ተኩሱን ሰምተው መጥተዋል። በነበርንበት አካባቢ የሚንቀሳቀሱ





ጓዶችም በቅርብ ስለአሉ እንዳይረበሹ ብለን፣ በድንገት የተተኮሰ እንደሆነና እኛም ሰላም እንደሆንን እንዲነግሯቸው ልጆቹን ላክንባቸው።

ተመልሰን ስንቀመጥ ድላይ አሁንም ድንጋጤው አልለቀቃትም፤ ፊቷ ቀልቷል፤ ዓይኖቿ ፈጥጠው እንባ ቋጥረዋል። ሳያት በጣም አሳዘነችኝ። "አይዞሽ፣ ብቻ ለሁለተኛው ተጠንቀቂ" አልኳትና አቅፌ አረጋጋኋት። ተመልሰን ከተቀመጥን ብዙም ሳንቆይ ሽሮው ደርሶ ምሳ ቀርቦልን በላንና ሴቶቹን በጣም አመስግነን ጉዞ ቀጠልን፤ የማይ ምሻምን ተራራ ለመውጣት ዳገቱን ተያያዝነው።

ዳገቱን ጨርሰን ከመውጣታችን በፊት አንዲት ትንሽ መንደር አግኝተን የተላክንበትን ጉዳይ ለመፈጸም በየቤቱ እየተዘዋወርን ፈተሸን፣ ምንም አላገኘንም። ተራራውን ወጥተን ከጨረስን በኋላ በምዕራብ አቅጣጫ ፣ ለማረፍ የሚመች ቦታ ፈልገን ከአንድ ዛፍ ስር ካለ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀመጥን።

ድንጋዩ ትልቅ ስለሆነ የሁለታችንም እግሮች አየር ላይ ተንጠልጥለዋል። ድላይ ኮፍያ አድርጋለች እኔ ደግሞ ኩሽኬን ጠቅልዬ አንገቴ ላይ ጠምጥሜዋለሁ። ሁለታችንም የ ከላሾቻችንን አፈሙዞች ወደ ላይ አድርገን በትከሻችን እንዳንጠለጠልናቸው ነው ጎን ለጎን ተጠጋግተን የተቀመጥነው። የተቀመጥንበት ቦታ ደስ ይላል፤ ጸጥ ያለ ቦታ ነው። የሚሰማ ድምጽ ቢኖር የወፎች ጫጫታና ራቅ ብለው ቅጠላ ቅጠል እየበጠሱ የሚበሉ ፍየሎች ጩኸት ብቻ ነበር። ከፊታችን የአከሱም ሜዳ ተዘርግቷል። ወደላይ በኩል የጸለምትና የሰሜን ተራራዎች ይታያሉ። ሰማዩ አልፎ አልፎ ዳመና አዝሏል። ከበድ ያሉ ደመናዎች ወደራስ ዳሸንና ወደ ቡሀይት ተራራ ሲጓዙ ከሩቅ ይታያሉ። በስተግራ በኩል፣ የተንቤን ተራራዎችና የተንቤን በረሀ፣ እንዲሁም በቀኝ በኩል የአድዋ ተራራና እምባ ሰሎዳ ይታያሉ። ቁጭ እንዳልን እነዚህን በሩቅና በቅርብ የሚታዩ የተፈጥሮ ጸጋዎች እያየን ትንፋሽ ከወሰድን በኋላ ማውራት ጀመርን።

አሙቿ ሁኔታ አጥቼ ሳልጠይቃት የቀረሁትን ጥያቄዬን እያስታወስኩት ነበረ። "በቀደም፡ምን ሰምተሽ ነበር ጠፍተው ይሆናል ብለሽ የተጠራጠሽው?" ብዬ ጠየቅኋት።

"እኔ እንጃ ሁለት ሌሊት ሳትመጡ ስትቀሩ፡ ሰውነቴ ተረብሾ ነበር። "አማኑኤል የት ሄደ?" ብዬ የአቢኢዮን ልጠይቀው ፈልጌ እንዳይጠረጥረኝ ፈራሁ" አለችና ዓይን ዓይኔን በትካዜ ትመለከት ጀመር።

"እኔ ደግሞ ሳታማከረኝ ለመሄድ ምንም አይነት ውሳኔ እንዳታደርግ ስትይኝ፡ ምን አዲስ ነገር አለ፡ ሊጠፋ ነው የሚል ወሬ ሰምተሽ እንደሆን ብዬ ተረብሼ ስነበትኩ፡ የሚሙች ጊዜ እግኝቼ እስከምጠይቅሽ ጨንቆኝ ነበር። አሁን ግን ሐሳብሽ ስለገባኝ ተረጋግቻለሁ" አልኳትና ርእስ ቀይሬ "ወገብሽ እንዴት ነው፡ አሁንም ያምሻል ወይስ ድነሻል?" ብዬ ጠየቅኋት።

"ከዚያን ቀን በኋላ ብዙም አሞኝ አያውቅም፡ ያው በየወሩ ህመሙ አይቀርም፣ ድካምም ይሰማኛል፤ እንደዚያን ቀን ግን ብሶብኝ አያውቅም። ያን ቀን በሰራኸው ግን አንተን በጣም አመስግንኩህ። የዛን ቀን ህመሜ እኮ ነው እኔና አንተን በጣም ያቀራረበን" አለችና ፈገግ አለች።

"አንቺ በመታመምሽ እንጂ ያን ቀን ማታ ደስ ብሎኝ ነው ያደርኩት" አልኳት ፈገግ ብዬ።

"እንዴት?" አለችኝ ፈገግታዋ በፊቷ ላይ እንዳለ።

"ከሴት ልጅ ጋር ተቃቅፌ ስተኛ የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለሆነ፡ ልዩ ስሜት ነበር የተሰማኝ" ስላት ከት ብላ ሳቀች። "ምን ያስቅሻል፡ የተናገርኩት ነውር ነው እንዴ? እውነቴን እኮ ነው! ከዚያ በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ከሴት ልጅ ጋር ያደርኩት ከመአዛ ጋር ነበር። መአዛ ለአሰፋይቱ ጉባኤ ስትሄድ እኔ ነበርኩ የሸኘኋት። (የአሰፋይት ጉባኤ፡ አሰፋይት ውስጥ የተደረገ የኢሕአሠ ሴቶች ጉባኤ





ነበር) ቦታው ከመድረሳችን በፊት ስለመሸብን ደገይቶ አብረን አደርን። ያን ቀን ማታም ኃይለኛ ብርድ ነበረ።

ምንም እንዳይሰማት ከጎኗ ሆኜ ፊቴን አዙሬ ስተኛ፡ በጣም እንደተሳቀቅኩኝ ገባትና 'ጓድ አማኑኤል፡ አይዞህ! ጠጋ በል! አትፍራ! ጓዲት ነኝ። ከተማ እያለን እኮ ከጓዶች ጋር ባልና ሚስት ነን እያልን አብረን እንተኛ ነበር። ግን ምንም አይነት ሌላ ስሜት አይሰማንም ነበር ብላ አደፋፈረችኝ። ከአንቺ ጋር ያደርኩ ቀን ግን ሰውነቴን መቆጣጠር አቅቶኝ ደሜ ሞቆ ነበር" አልኳት።

"ሌላ ጊዜ ዝምተኛ ነህ ፣ ዛሬ ደግሞ አፍ ለቀቀብህና ለፈላፊ ሆንክ" አለችኝ። ከቃላቱ ይልቅ ዓይኖቿ ልዩ መልእክት ነበራቸው።

"አዎእ! ዛሬማ ለመናገር እደፍራለሁ" አልኳት ፊት ለፊት እያየኋት።

"ምን የሚያስደፍር ነገር አገኘህና?"

"እዚህ ያለነው እኔና አንቺ ብቻችንን ነዋ! ከዚህ ከዐረፍንበት ዛፍ፣ ከእነዚህ ከሚንጫጩት ወፎችና ከአንቺ በስተቀር ማን ይሰማኛል? ሌላ ጊዜ ግን ጓዶች ይሰሙናል እያልኩ ነበር የምፈራው። እውነቱን ለመናገር እኔ ከሴት ጋር ስሆን ምን እንደምል አላውቅም ነበር። ልምዱ የለኝም ብዬ ሐቁን ብናገር ይሻለኛል" አልኳት አሁንም እያየኋት።

"ለጫወታ ብዬ ነው እንጂ እኔም ዝምተኛ ነኝ። ከአንተ ጋር ስሆን ግን መጫወት ደስ ይለኛል። ከአንተ ጋር በንጽሕና በመተሳሰብ ነው እንጂ በተንኮል ምንም ያደረግነው ነገር የለም"

"እውነትሽን ነው፤ እኔ መጀመሪያ ሳቅፍሽ ብርዱን ልከላከልልሽ እንጂ ለሌላ አልነበረም። ካቀፍኩሽ በኋላ ግን የተፈጥሮ ስሜቴ ወደሌላ ገፋኝና አስቸገርኩሽ። ቢሆንም ግን ዓላማችንን አስቀድመን፡ ገደቡን ሳናልፍ ሁለታችንም ስለተቆጣጠርነው ደስ አለኝ" አልኳት። አሁንም ፈገግ እንዳለች ራሷን እየነቀነቀች አዎንታዋን ገለጸችልኝና ዝም አለች። እኔም ዝም አልኩና ቀና

ብዬ ጥላውን እየለገሰን ያለውን ዛፍ አየሁት፤ ትልቅ ዛፍ ነው። ዙሪያ አካባቢያችን በሙሉ በጣም ያምራል፤ ከዳር ዳር በአድናቆት መመልከት ጀመርኩ።

ደስ ብሎኛል። ምናልባት ከድላይ ጋር ስለሆንኩ እንደሆነም እንጃ ብቻ የተፈጥሮው ውበት ስሜቴን ነካው። ጥላ የሚሰጠን ዛፍ እየተወዛወዘ አየሩን ያናፍስልናል። አልፎ አልፎ ደግሞ ቅጠሎቹን እያንሳፈፈ ከ፡ላይ ወደ እኛ ይለቃቸዋል። ለሙሽሮች እንደሚበተን አበባ ፍቅራችንን ለማድመቅ ሆነ ብሎ የሚያደርገው ነው ብዬ አሰብኩ። ከዛፉ ላይና በአካባቢው ካሉ ዛፎች ወዲህ ወዲያ የሚሉት አእዋፍም እንደየዝርያቸው የተለያዩና የሚማርኩ ዜማዎቻቸውን ወደ ጆሮዎቻችን እየላኩ ደስታችንን ጨምረውታል።

እኔ በዚህ ጊዜ የሀያ አመት ወጣት ነኝ። ድላይም ብትሆን እኩያዬ ብትሆን እንጂ የዕድሜ ልዩነት የለንም። ሁለታችንም በአፍላ ዕድሜ ውስጥ ነበርን። በጣም ተጠጋግተን ሰውነታችን ተነካከቶአል በእያንዳንዱ ትንንሽ እንቅስቃሴያችን እንተሻሻለን። በውስጤ የነበረው ሐሳብ ፈጥሮት ሊሆን ይችላል፤ ብቻ የሰውነቷ ሙቀት የተሰማኝ ስለመሰለኝ የእኔም ስሜት መነሣሣት ጀመረ። ሰውነቴ ሙቀቱን ጨመረና ጋለ፤ ራሴን ለመግታት አልቻልኩም። የቀኝ እጄን ዘረጋሁና አጠገቤ ያለውን የግራ እጇን ሳብ አድርጌ ሳምኩት።

"አማኑኤል በትግል ውስጥ እንዳለን አትርሳ፤ ስሜትህን ተቆጣጠር። እኔም እኮ እንደ አንተ ስሜት አለኝ። ያለነው ግን በትግል ውስጥ ስለሆነ ስሜቴን በግድም ቢሆንእየተቆጣጠርኩ ነው። አለበለዚያ ሁለታችንም ልንታገል አንችልም። ስለዚህ ትግልን ወይም ፍቅርን መምረጥ አለብን። የአቢሊዮና ሰለሞን ለብቻችን የላኩን እኮ አምነውን ነው። ስንታመን ደግሞ እምነታችንን ማጉደል አይገባንም" አለችኝ።

"ድላይ..." ብዬ ገና መናገር ስጀምር አቋረጠችኝ።





"ምነው አማኑ! አልተዋጠልህም እንዴ?" አለችና "አሁን አንድ ነገር ካደረግን እንዴት ብለን ወደጓዶች እንመለሳለን። ካልተመለስንስ ወደሌላ ወደ የት እንሄዳለን። ሕይወታችን በሙሉ ከድርጅቱና ከጓዶች ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ መጽናት አለብን" በማለት ሐዘን በተሞላው የሚጣፍጥ አንደበቷ ልትገታኝ ሞከረች።

"ድላይ፤ የምትናገሪው በሙሉ ትክክል ነው። ነገር ግን እኔ ደጋግሜ እንደነገርኩሽ በሕይወቴ ውስጥ ወድጄም ተወድጄም አላውቅም። ወደ በረሐ የገባሁት ለፍቅር ሳይሆን ለትግልና ለመስዋዕትነት ነው። አሁን ግን ያጋጠመኝ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ነገር ነው" ብዬ እውነቱን ነገርኳት።

"አማኑኤል፤ እኔ ሳውቅህ ዝምተኛና የዋህ ነህ። እንደዚህ ዓይነት ቃላቶች ካንተ የሚወጡ አይመስለኝም ነበር። ዛሬ ምን ነካህ? ብቻ አደራህን እንዳታሳስተኝ" ካለች በኋላ አንገቷን ደፋችና መተከዝ ጀመረች። ትንሽ ከቆየሁ በኋላ ደሜ እንደገና መሞቅ ጀመረ። ቀኝ እጄን በትከሻዋ አሳልፌ አንገቷን አቅፌ ላስጠጋት ስሞክር ግን ኮስተር ብላ ፊቷ ሲለዋወጥ ደነገጥኩና እጄን መለስኩ።

"አንተ ልጅ ተው እንጂ" ብላ መደንገጤን ስታይ እሷም ደነገጠችና ወዲያውኑ ቁጣውን ለውጣ በትንሹ ፈገግ አ ለች "አማኑኤል፤ እስቲ አንዴ ረጋ እንበል" በማለት አለሳለሰችኝና ነገሩን አበረደችው ስል ከዓይኖቿ የዕንባ ዘለላዎች ዱብ ዱብ አሉ። እኔም ሳላስበው ዕንባ በዕንባ ሆንኩ።

ሁለታችንም ለቅሷችንን ለማቆም እየሞከርን ነበርን። መነጋገር ስላልቻልን በምልክት ብቻ እንንሳ ተባብለን ከተቀመጥንበት ድንጋይ ላይ እየዘለልን ወረድንና አጠገብ ለአጠገብ ቆምን። ሳናስበው በደመነፍስ ተቃቀፍንና ጉንጮቼን ሳመችኝ። እኔም ጉንጮቿን ሳምኳቸው። ቀጠልንና ግንባሮቻችንን ተሳሳምን። ተሳስመን ስንጨርስ ሁለት እጆቿን ያዝኩና "ለመጀመሪያ ግዜ ፍቅርን ያወቅኳት

በአንቺ ነው። ከትግል በኋላ በሕይወት ከቆየን ከአንች በቀር ሌላ ሴት አላገባም። ይሄ የማልለውጠው ቃሌ ነው" አልኳት።

ዓይን ዓይኔን እያየች ዕንባዋ በግራና በቀኝ ጉንጮቿ ኩልል እያለ ንግግሬን ስጨርስ ጠብቃ በልቅሶ መሐል እንደምንም ፈገግ ለማለት እየሞከረች "እንዴ! እግሬ እጄ ቢቆረጥስ፣ አይኔ ቢጠፋስ" ስትል፣ ለመቀለድ እያስመሰለች ቃሌን በቁም ነገር ለማጣራት የፈለገች መሰለኝ።

"እኔ አንቺን በሕይወት እስካገኘሁ ድረስ ምንም ነገር ቢደርስብሽ የምፈልገው አንቺን ነው እንጂ ሌላ አይደለም። ዛሬ የዋልነው ውሎ፣ ዛሬ የተነጋገርናቸው ቃላት ምንጊዜም አይረሱኝም። ብቻ ሁሉም ነገር አልፎ በሕይወት ለመገናኘት ያብቃን" አልኳት።

"እኔም ብሆን በቀደም እኮ ነግሬሀለሁ። ትዝ ካለህ ነበሩት እያለን የማምንህና የምወድህ ጓዴ አንተ እንደሆንክ ነግሬሀለሁ። ባላምንህ ኖሮ የአንተን ቁምጣ ለብሼ አልውልም ነበር። ባልወድህ ኖሮ አንተን ለብቻዬ ይዤ ለመምጣት አልሞክርም ነበር። ብቻ እንዳልከው በሕይወት ለመገናኘት ያብቃን እንጂ እኔም ካንተ በስተቀር ሌላ ወንድ አልፈልግም" አለች። ሳናስበው ተቃቅፈን በቃላት ሊገለጽ የማይችል ስሜት ውስጥ ሰመጥንና ለጥቂት ደቂዎች ቆየን። እኔም ሆንኩ እሷ ምን ያህል እንደምንዋደድ አረጋገጥን። ዕንባችንን ጠራርገን ለመሄድ ተዘገጃጀን።

አካባቢው ጸጥ እረጭ እንዳለ ነው። ጥላው ዞሮ ደስ የምትል ለሰስ ያለች የማታ ፀሐይ በሙቀቷ እየዳበሰን ነው። ቀደም ብሎ ያየናቸው ፍየሎች ቀኑ እየመሸ ስለነበረ ሄደዋል። በዚያ ደስታና ልዩ የፍቅር ዓለም ውስጥ ሆነንና ማለቂያ የሌለው ፈተና ውስጥ ገብተን ነገር ዓለሙን ሁሉ ረሳነው። ቀኑ እንደመሸብን ዘንግተነዋል። አሁን ፀሐይቱ ለመግባት በስተምዕራብ በኩል በደማቅ ቀይና ብጫ ቀለም ተከባ ታምራለች። በጣም ዘግይተን ስለነበር በታውን ለቀን በፈጣን እርምጃ





መጓዝ ጀመርን። እጅ ለእጅ ተያይዘን ገደሉን መውረድ ስንጀምር "አማኑኤል" አለችኝ ድላይ።

"ምነው?" አልኳት

"አንድ ልነግርህ የምፈልገው ነገር አለ!" "ምንድነው?"

"ለማንኛውም እውነተኛ ስሜ ሰመኝ እንደሚባል እንድታውቀው እፈልጋለሁ። አንዳንዴ ብቻችንን ስንሆን ሰመኝ ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ" አለችኝ።

"ምነው ምን አሳሰበሽ? በእኛ አሠራር እኮ እውነተኛ ስም መናገር አያስፈልግም?" አልኳት። ከሠራዊቱ በተቀላቀልኩበት ቀን ግደይ " እውነተኛ ስምህን ለማንም እንዳትናገር! ካሕሳይ ቢሉህ ወይ እንዳትል! ካሕሳይ ነህ ቢሉህ እንኳ፣ አይደለሁም ነው ማለት ያለብህ! እኛ ሁላችንም የምንጠራው በሌላ ስም ነው።" ያለኝ ትዝ አለኝ። ከንግግሩ ትውስታ ቀጥሎ እሱ ራሱ ትዝ አለኝ። ግደይን ሳስታወሰው ደግሞ እነሐዋዝና ዘላለም ትዝ አሉኝና ዓይኖቼ ዕንባ አቀረሩ፣

"ምነው ምን ሆንክ?! እኔ እኮ፣ ዝም ብዬ ለማንኛውም ብታውቀው ጥሩ ነው ብዬ ነው" አለችኝ።

"እሺ" አልኳትና ዝም ተባብለን መንገዳችንን በመቀጠል የሰሜኑን አቅጣጫ ያዝን።

ጠዋት ስንላክ ጓዶቻችን ያሉበት አቅጣጫ ተነግሮናል። በትክክል ያሉበት ቦታ ግን አልተነገረንም። የተፈቀደልን ደርሰን እንድንመለስ እንጂ እንድናድር አይደለም። በትክክልም የተላክንበትን ጉዳይ ጨርሰን በዕለቱ መመለስ እንችል ነበር። ነገር ግን ትንሽ ብቻችንን ሆነን ለማውራት ተቀመጥንና በፍቅርና በትግል ስሜት ማእበል ውስጥ ሆነን ወዲያና ወዲህ የሚያላጋ ፈተና ውስጥ ገብተን ቀኑ ሳናውቀው መሸብን።

ትንሽ እንደተጓዝን ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ያለበት ትንሽ መንደር ደረስን። ኃይሏ ለአዳር የምታርፍበት መንደር ደግሞ ከቤተ ክርስቲያኑ ባሻገር በአድዋ በኩል ሆኖ ብዙም እንደማይርቅ እናውቃለን። መንደሩን ከመልቀቃችን በፊት እዚህ እንደር ወይስ እንሂድ ብለን ለመመካከር ተቀመጥን። ትንሽ ከተወያየን በኋላ ለብቻችን ለማደር ወሰንን። ነገር ግን ወደአሉበት አካባቢ ተጠግተን ለማደርና ጠዋት መንቀሳቀስ ሳይጀምሩ ሄደን ለመቀላቀል ተስማማን።

ቀኑ ሙሉ በሙሉ አልጨለመም፤ መንደሩን መጥተንበትም ስለማናውቅ የምናድርበትን ቦታ ሌላ ሰው እንዳያውቅ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን። እስኪጨልም ቆይተን የምናድርበትን ቦታ መፈለግ ይሻላል ብለን እስኪጨልም ድረስ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተጠግተን ቆየን። ሲጨልም ጓዶች ለሰፈሩበት መንደር ወደሚቀርቡት ቤቶች ሄደን አንዱ ጋ ለማደር ነበር የፈለግነው። እስከዚያ ድረስ በተጠንቀቅ ሆነን አካባቢያችንን በዓይናችን እየተቆጣጠርን ጠመንጃችንን አዘጋጅተን ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ተቀመጥን።

አካባቢያችን ችግር እንደሌለው በደንብ ካጣራን በኋላ፣ ድምፃችንን ዝቅ አድርገን ማውራት ጀመርን "ዓየሀ አማኑኤል፣ ገና ምንም ሳንጀምር ከጓዶች ጋር መቀላቀል እየቻልን ከእነሱ ተደብቀን ለማደር ወሰንን። ብንጀምር ኖሮስ ምን ልናመጣ እንችል ነበር?!" አለችኝ ድላይ።

እኔም በትግሪኛ "ባእልኪ ትፈልጢ"(ግድ የለኝም) ስላት ድምፅ አውጥታ ሳቀች። "አንቺ ልጅ ተይ እንጂ፣ እዚህ የተደበቅነው እኮ ሰው ሳያየንና ሳይሰማን በምስጢር ለማደር ነበር" አልኳትና ሳቋን ለመቆጣጠር ሞከረች።

ለሁለት ሰዓታት ያህል ከቆየን በኋላ መንደሩ ውስጥ ይሰማ የነበረው ድምፅ እየጠፋና ጸጥ እያለ ሄደ። ከቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ካለው ቤት ሄደን አንኳኳን። አንድ ወጣት ልጅ በሩን ከፈተልን፤ ተጋዳዮች መሆናችንንና ለማረፍ ስለፈልግን ፈቃድ ልንጠይቅ እንዳንኳኳን ስንነግረው ደነገጠና





እናቱን ጠራ። እናትየውም ድምፃችን እየሰሙ ስለነበር ውስጥ እንዳሉ "ከፈተሎም መሲኢዮም ኢዩ" (ከፈትላቸው መሽቶባቸው ነው) አሉና ወደውስጥ ገባን። ለመተኛት እየተዘጋጁ ይመስላሉ፤ አሁን ደግሞ ለእኛ እራት ሊያዘጋጁ እሳቱን እየቆሰቆሱ ከኛ ጋር ወሬ ጀመሩ። ድላይ አማርኛና ትግሪኛ በደንብ ታውቃለች። የሚቀናት ግን አማርኛ ነው፤ በትግሪኛ ስታወራ አነጋገሯ ደስ ይላል። ድምጿም ለስለስ ስለሚል ለጆሮ ይጣፍጣል።

የሁለታችንም አለባበስ ተመሳሳይ ስለሆነ ይመስለኛል፣ ሴትዮዋ ሲያናግሩን በትግሪኛ እሷንም እኔንም አንተ እያሉ በወንድ ጾታ ይጠቀሙ ስለነበረ እኔ እየሰማሁ እስቃለሁ። ድላይም ችግራቸው ገብቷታል፤ ግን ጫወታቸውን ላለማደናቀፍ ዝም ብላ ታዋራቸዋለች። በጣም ሲደጋግሙት፣ እኔ ጣልቃ ገባሁና "ኢደይ እሳ ጓል ኢያ፣ ወዲ አይኮነትን"(እደይ፣ እርሷ እኮ ሴት ናት ወንድ አይደለችም) አልኳቸው።

"እዋይ፣ ወደይ አሪጋ ኢልካ ዲኻ ትቕልደሊይ? ግደፍባ" (ወይ ልጄ፣ እርጅታለች ብለህ ነው የምትቀልድብኝ፣ ተው እንጂ) አሉ። እኔ አሁንም እስቃለሁ።

"ቀልዲ አይኮነን ሐቀይ ኢዩ እሳ ጓል ኢያ" (ስቀልድ አይደለም፤ እውነቴን ነው ሴት ነች) አልኳቸው። ሁኔታቸውን ስታይ ድላይም ቀጠል አድርጋ "እደይ እሱ እውነቱን ነው የነገረዎት። እኔ ወንድ አይደለሁም ሴት ነኝ" ስትላቸው ደንግጠው አዲስ እንደመጣ ሰው ትኩር ብለው አይተዋትም ለማመን ተቸገሩ።

እኔም ተጨመርኩና እንደገና "ሐቀይ እዩ፣ ጓል ኢያ። ወዲ ዝመስለትክን ከም ተጋዳላይ ስለዝተከደነት ኢዩ" (እውነቴን ነው፣ ሴት ናት። ወንድ የመሰለችዎ፣ እንደ ተጋዳላይ ስለለበሰች ይሆናል) አልኳቸው። እሳቸው ግን አሁንም ለማመን ከበዳቸው። ድላይ፣ ለመቀበል እንደከበዳቸው ስትመለከት እንዴት ለማሳመን እንደምትችል ጨነቃትና ቢቸግራት፣ ልብሷን በግራ በኩል ከፍታ ጡቷን አውጥታ እያሳየቻቸው "ኢደይ እነ ጓል ኢየ፣ እንድሕር

ዘአይአመንክናኒ ጡበይ ርአይአ" (አደይ ከላመኑኝ ይኸው ጡቴን ይመልከቱ፤ እኔ ሴት ነኝ) አለቻቸው።

እውነት መሆኑን ሲረዱ፤ ደንግጠው "ውይ! ውይ! አደኺ ጓል ወሊዴ ኢላ ከምዚልኪ ኢንተትርእየኪ እንታይ ምበለት? ጓለይ እንታይኮን ኮይና ኢላ እንድሓሰበት፤ እስኺ ግና ከምዚይ ጫካ ንጫካ፡ በረኻ ንበረኻ ምስ አወዳት ኪርተት እናበልኪ፣ እንዳገዛ ሰብ፤ በብሜድኡ ከምትሐድሪ አዴኺ እንታትሰምዕ እንታይኮን ምውሐጣ?" (ውይ ውይ!! እናትሽ ሴት ልጅ ወለድኩ ብላ፤ እንደዚህ ብታይሽ ምን ትል ነበር? ልጄ እንዴት ሆና ይሆን ብላ ስታስብ፤ አንቺ ግን እንዲህ ጫካ ለጫካ በረሐ ለበረሐ ከወንዶች ጋር እየተንከራተትሽ በየሰው ቤት፤ በየሜዳው እንደምታድሪ እናትሽ ብትሰማ ምን ይውጣት ነበር?!) ብለው አንገታቸውን ደፋና በእንጉርጉሮና በዜማ አድርገው ማልቀስ ጀመሩ።

እኔንም እናቴን ስላስታወሱኝ ሌላ ሐሳብ ውስጥ ገባሁና ቅዝዝ አልኩ። አንደገና ደግሞ ቀና አሉና፤ በሚቆራረጥ ድምፅ "ንምኳኑ ቤተሰብኪ እንታይ በዲሎምኺ እዮም ገዛኺ ገዲፍኪ ከምዚ ዝኾንኪ?" (ኧረ ለመሆኑ ቤተሰቦችሽ ምን በድለውሽ ነው እንዲህ የሆንሽው?!" ብለው መልሷንም ሳይጠብቁ ለቅሷቸውን ቀጠሉ።

እኛ እንዲህ ዓይነት ከፍተኛ ሐዘን ውስጥ ይገባሉ ብለን ስላልገመትን በትካዜ ተይዘን እንዴት እንደምናጽናናቸው ግራ ገባን። እንዲተው እንደምንም እያባበልን ርእስ እየለዋወጥን በብዙ ጥረት ወደሌላ ጫወታ ከአስገባናቸው በኋላ ራት አቅርበውልን በላንና ለመተኛት ስንዘጋጅ ጋቢ ሊያመጡልን ሄዱ ።

"ከዚህ በላይ አይቸገሩ እኛ ምንም ተጨማሪ ልብስ አያስፈልገንም፤ የያዝነው ነጠላ ይበቃናል" አልናቸው።

"ንአኻ ከይኮነስ ንዓአ እዩ፤ እስቲ ንሐንቲ ለይቲኳ፤ አነ አዶ ከኾነላ" (ላንተ ሳይሆን ለእርሷ ነው፤ እስቲ ለአንድ ለሊት እንኳ እኔ እናት ልሁንላት?) አሉ።





አይሆንም ብንልም ሊቀበሉን ፈቃደኛ አልሆኑም። ቅር እያላቸው ጋቢውን አመጡ ።

ተኝተን ብቻችን ስንሆን ሁኔታቸው በጣም ውስጤን ስለነካው "አንቺ ለምን እንዲህ ታደርጊያለሽ?"አልኳት።

"ማመን ስላቃታቸው፤ የግድ ማሳመን ስለነበረብኝ ነው። ይሄም እኮ አንዱ የትግል ዓይነት ነው። እኛ ሴቶችም ለራሳችንና ለሌሎችም መብት በእኩልነት መታገል እንደምንችልና መታገል እንዳለብንም ማሳወቅ ስላለብኝ ነው እንጂ ጡቴን ላሳያቸው፤ ወይም ለአንተ ላሳይህ ብዬ አይደለም!" አለችኝ።

እዚህም እንደመጀመሪያው ቀን አቅፍቀፍ ብለን በፍቅር ስሜት የጋለው ሰውነታችን አንዴም ሳይላቀቅ እንደእሳት የሚፋጅ ትንፋሻችንን እየተለዋወጥን አደርን። ስሜታችን አይሎ ሊገነፍል አፋፍ ደርሶ ሌሊቱን ያሳለፍነው ያለእንቅልፍ ነበረ። የገባነው ከባድ ፈተና ውስጥ ቢሆንም፤ በተስማማነው መሠረት ከፍቅር ትግል መቅደም እንዳለበት በማመን በጣም ተጠንቅቀን ስሜታችንን ተቆጣጠርነው።

ሲነጋ ሲል ተነሣን፤ ወደየጋንታችን ለመቀላቀል ጓዶች ያድሩብታል ብለን ወደገመትነው መንደር ሄድን። ወደ መንደሩ ከመግባታችን በፊት የሚጓዙበትን አቅጣጫ ተመለከትንና በሌላ አቅጣጫ አድርገን ከፊታቸው ቀደምንና ከሚመጡበት ገደላማ አፋፍ ደርሰን ጠበቅናቸው። በመጀመሪያ ከገደሉ የወጡት የእነድላይ ጋንታ አባላት ነበሩ። እኔ እዚያው እንደቆምኩ እያየኋት ሄዳ ተቀላቀለች። ከነበርኩበት ቦታ ሆኜ ድምፃቸው ይሰማኛል።

"የት ይዛው ጠፍታ ነበር" የሚሉ ቃላት ወደ ጆሮዎቼ ሲደርሱ፤ መጀመሪያ አላመንኩም ነበር። በኋላ ግን ጥርጣሬ ውስጥ እየገባን መሆኑን ሳውቅ ደነገጥኩ። ጥርጣሬውም በብዙዎች አእምሮ ውስጥ የሚብላላና የሰፋ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ። ብዙዎቹ ራሳችንን ተቆጣጥረን፤ ፈተናችንን እንደተወጣንና

ለዓላማችንና ለትግል ተገዝተን በንጹሕነት እንዳለን ሊያምኑ አይችልም ብዬ አሰብኩ።

በሐሳብ ውስጥ ሆኜ ትንሽ እንደቆየሁ የእኔዋም ጋንታ አባላት ከገደሉ ብቅ ብቅ ሲሉ ከገባሁበት ሐሳብ ወጣሁና ተቀላቅዬ አብሬ መጓዝ ጀመርኩ።

***





ኃይል አምስት መቶ በምትንቀሳቀስባቸው ቦታዎች ከወያኔ ጋር ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ ለጦርነት የተቃረበው አዳጋ አርቢ ነበር። አዳጋ አርቢ የሚገኙት የወያኔ ሚሊሺያዎች በከፍለ ሕዝብ የሚሠሩ አባሎቻችንን ከወረዳው ውጡ ብለው አላስቀምጥ ከማለታቸውም በላይ የእኛ ሰዎች እንዳያልፉ መከልከል ጀመሩ። ኢነየአቢኢዮ ሰምተው ከበላይ አመራሮች ጋር እየተነጋገሩ ቆይተው በመጨረሻ እኔን ጨምሮ ከሶስት ጋንታ የተውጣጣን ስድስት ሰዎች ተላክን። እምቢ ካሉ እንድተኩስና የኃይል እርምጃ እንድወስድ ትእዛዝ ተሰጥቶኝ ነበር ወደዚያው ያመራነው።

አዳጋ አርቢ ወደ ተከዜ የምንተላለፍበትና ከጸለምት ጋር የምንገናኝበት ቁልፍ መገናኛ መስመር ስለሆነ ነበር ጠበቅ ያለ ትእዛዝ የተሰጠኝ። በዚያ መሠረት "ችግር ከተፈጠረ አንተ ቀድመህ ተኩስ መከፈት አይኖርብህም፤ እንዳትቀድም ተጠንቀቅ" ተብያለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ኃይሏ ተዘጋጅታ እንደምትጠብቅና ልክ ተኩስ እንደተሰማ እንደምትደርስልንም ተነግሮኛል። ነገሩ ወደ ተኩስ ከደረሰ ከሚሊሺያዎቹ በተጨማሪ የወያኔም ኃይል ከችግሩ በስተጀርባ እንዳለ ስለተገመተ፣ ውጊያው በወያኔ ኃይልና በእኛ ኃይል መካከል እንደሚሆንና ውጤቱም ወደ አስከፊ እልቂት ሊሄድ እንደሚችልም ተገምቷል።

ስንደርስ ከተማዋ ወያኔ ባስታጠቃቻቸው ብዙ ሚሊሺያዎች ዙሪያዋን ተከባለች። የወረዳው የወያኔ ሚሊሻዎች መሪ ከፊታችን ትንሽ ራቅ ብሎ ከጥቂት ሰዎች ኋላ ቆሞአል። እኛን አትገቡም ብሎ አስቆመን። ማንነታችንን እንዲያውቅ አድርገን የወሰደው እርምጃ ትክክል እንዳልሆነና ሌላ ችግር ውስጥ እንዳንገባ ብንነግረውም ሊሰማን አልቻለም።

"ወደከተማ አትገቡም እዚህ ሕዝቡ እናንተን አይፈልጋችሁም" እያለ ይደነፋ ጀመር።

"አሁንም ይህንን አባባልህን ተውና ተነጋግረን በሰላም ብንፈታው ይሻላል" ብንለውም እምቢ ብሎ ያልሆነ ነገር መናገር ቀጠለ።

ከዚያ በኋላ አብረውኝ ያሉትን ጓዶች ቦታ እንዲይዙና መሣሪያቸውን አዘጋጅተው በተጠንቀቅ እንዲሆኑ ነግርኳቸው። ከለላ ይዘን ተኩስ ከተጀመረ ለመመለስ መሣሪያየን አነጣጥሬ ጣቴን ቃታው ላይ አድርጌ በተጠንቀቅ እንደቆምኩ "ተው አትተኩስ!" የሚል ድምፅ ሰማሁ፤ ገብረ ሐዋሪያ ነበረ።

"አማኑኤል ተው! መታኮስ የለብንም የእኅቴ ባል ነው! የእኅቴ ባል ነው!" እያለ በመጮህ ምሽግ ከያዘበት ቦታ ወጣና እየሮጠ ወደ እነርሱ ሄደ። ሰውዬው አወቀውና ሰላም ተባባሉ።

"ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?" አለው ገብረ ሐዋርያ ሰውየውን። በዚህ ሁኔታ እንድንገባ ተፈቀደልንና ያንን ጓድ ከእኅቱ ጋር ሊያገናኘው ወደ ቤቱ ሊወስደው ሲል ሁለት ጓዶች አብረውት እንዲሄዱ ሰጠሁት። አብረው ሄደው እኅቱንም አይቶ ተመለሰ።

*እናንተ ሁለት ወንድማማቾች የያዛችሁትን አፈሙዝ እንድትገዳደሉበት ሳይሆን እንድትተቃቀፉበት ነው።* (እንዲት ዘማች ተማር ባለታሪኩ እና የሕወሐት አባል የሆነ የትምህርት ቤት ጓደኞቿ ተገናኝተው በድንገት ሲተቃቀፉ አይታ የተናገረችው።)

***





**የመከፋፈል ምልክቶች**

"....እየፈላ ካልሰከነ

ትግል ምኑን ትግል ሆነ!"

(የኢሕአፓ ልጆች ግጥም)

በ1970 ዓ.ም. በታህሣሥ ወር ነበር ወደ አድና የተመለስነው። ነበለት አካባቢ ስንደርስ የኃይሏ አባላት ተሰበሰብን። አሰፋ ወደ በጌምድር ከሚሄዱ ጓዶች ጋር ስለተመደበ የኃይል የፖለቲካ ሐላፊ ሰለሞን ሆኗል። ምክትል የኃይል የፖለቲካ ሐላፊ ደግሞ ከሡተ ነው። ሁላችንም ከተሰበሰብን በኋላ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚነገሩን ተገለጸልን። በፓርቲው ውስጥ አንጃ እንደተፈጠረና ፓርቲው ለሁለት እንደተከፍለ ተነገረን። የአንጃውን ቡድን የሚመሩት "ሀ" እና 'ለ" የሚባሉ መሆናቸውም ተገለጸልን። ብርሃነ መስቀል ከፓርቲው እንደተገለለ በሐሜት ስንሰማ ቆይተናል። ሰምኑን በእነርሱው ቡድን መዘጋጀቱ የተወራለት፣ "ልዩነታችን" የሚል ጽሑፍ የያዘ ወረቀት ተበትኖ ነበር። ወረቀቱ ከተበተነ በኋላ አንዳንድ ነገሮች መስማታቸው አይቀርም ብለው ይመስላል ሊነግሩን የፈለጉት።

"ሀ" እና "ለ" የሚባሉ ስማቸው ያልተጠቀሱ የፓርቲው አመራር አባላት አንጃ በመፍጠራቸው ምክንያት ከድርጅቱ የተባረሩ መሆኑ ተገለጸ። የአንጃው ቡድን ፓርቲውን ለሁለት እንዲከፈል እያደረገና በከተማው መዋቅር ውስጥ በጓዶች ላይ ወንጀል እየፈጸመ መሆኑ ተነገረን። የሠራዊቱ አባላትም አፍራሽ ተልእኮ ካለው ከዚህ የአንጃ ቡድን ቅስቀሳ እንድንጠነቀቅ ማሳሰቢያ ተሰጠን። ከስብሰባው በኋላ ከነበርንበት ቦታ ተንቀሳቅሰን ወደ ሀውዜን ስንሄድ እንደገና በሌሎች ስብሰባዎች ውይይቶች ቀጠሉ። በቡድን ሆነን መወያየት ጀመርን። በውይይቶቹ ከተነሡት ጥያቄዎችም 'ለምንድነው የትጥቅ ትግል የሚያስፈልገው? ድርጅቱ ገበሬ ለመልመል ለምንድነው ፍላጎት ያነሰው? ገበሬ ያልተደባለቀበት የገጠር ሠራዊት

የያዝነው ለምንድነው? ገበሬውን ሳናስታጥቅና ሳናደራጅ እንዴት አድርገን ነው በገጠር የምንታገለው? ፓርቲው የገጠሩን ትግል ነው ወይስ የከተማውን ትግል በቀዳሚነት የሚያየው? አሁን ፓርቲው ድል አድርጎ ሥልጣን ቢይዝና ሠራዊቱ ወደከተማ ግባ ቢባል፤ ዝም ብሎ መግባት አለበት ወይስ የተራዘመ፣ ከገጠር ወደከተማ የሚደረግ ትግል የግድ ያስፈልጋል?" የሚሉ ጥያቄዎች ይገኙባቸዋል።

ከዚያ በኋላ ቀስ በቀስ በቡድን የመከፋፈል ስሜት እየጎላ መጣ። ሁሉም በየጎራው ሆኖ አንድ ከሚያደርገን ዓላማ ይልቅ የሚለያዩንን ትናንሽ ነገሮች እየተያዙ የመከፋፈል ዝንባሌ ያላቸው ድርጊቶችና ወሬዎች ተስፋፉ። እኔና እኔን መሰል የገበሬ ልጆች የሆንንና ገና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያልጨረስን አባሎች በአንዳንዶች የመናቅ ዝንባሌ ባላቸው ምሁራን የንቀት ትችት ውስጥ ወደቅን።

አንድ ቀን መንገድ እየሄድን እያለን "እንጸዳዳ" የሚል ጥያቄ ከኋላ መተላለፍ ጀመረ። እኔ ደግሞ "ከወደፊት ላሉ ጓዶች እንጸዳዳ" ይላሉ ብዬ ለእንግዳ ወርቅ አስተላለፍኩኝ።

እንግዳ ወርቅ ጋንታ መሪ ስለነበር "ቆዩ በላቸው" አለኝ። "ቆዩ ተብላችኋል" አልኳቸው።

ትንሽ ቆየት ብለው "ለመቆየት ስለማንችል፤ መጸዳዳት አለብን። አስቸኳይ ነው" ብለው ከትእዛዙ ውጪ መጸዳዳት ጀመሩ። ስመለከት የተወሰኑ ጓዶች ከሰልፍ ተቆርጠዋል። እኔም ሁኔታውን እየሁና "ለምንድን ነው ተጸዳዱ ሳትባሉ ከሰልፍ የወጣችሁት?!" አልኳቸው።

"ታዲያ እናንተ ተጸዳዱ እስከምትሉን እንጠብቅ እንዴ?! በጣም ተቸገርን እኮ!!" አለ የኃይሏ ምክትል የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊ።

"ጓድ፣ ይህ አናርኪዝም ነው" አልኩት። ዝም አለና ሄደ።





በጊዜው በየጋንታችን ራሳችን የምናወጣቸው ጽሑፎች ነበሩ። **የእኛ ጋንታ** የምታወጣው ጎትመት "ጎሕ" የምትባል ነበረች። አንድ መንደር ላይ **ቆሞ** ስንል የተለያዩ ጽሑፎችን እናመጣና ተሰበስበን ማታ ማታ ይነበባል። የፓርቲው ኮሚቴ አባል ደግሞ ጥሩ የጽሑፍ ችሎታ ነበረው። ያን ማታ ታዲያ የጻፈው ስለአናርኪዝም ነበር።

በአናርኪዝም ላይ ብዙ ትንተና እና የብዙ ሀገሮች ልምድ ጨምሮበታል። የራሺያ፣ የአውሮፓ፣ የላቲን አሜሪካ፣ የቬትናም፣ የቻይና . . . ብቻ ያልተጠቀሰ ሀገርና አብዮት አልነበረም። "ስለዚህ አናርኪስት ማለት" ብሎ፣ በየሀገሩ ትንታኔ ላይ የተጠቀሱ ቡድኖችና ግለሰቦችን አንሥቶአል። "ስለአናርኪዝም ሳያውቁ፣ ለመጸዳዳት መስረዕ ያቋረጠውን ሰው ሁሉ አናርኪስት ለሚሉ የአናርኪስትን ትርጉም እኛ እናስተምራቸዋለን" ብሎ ደመደመ።

ይሄ ለእኔ ስድብ ነበር። አንተ "የአናርኪዝምን ትርጉም ሳታውቅ፣ አናርኪስት አልከኝ" ማለቱ ነበር "ትልቁ ስሕተትህ የሠራኸው ሥራ ሳይሆን፣ የተናገርከው ንግግር ነው" ለማለት ስለሆነ ገረመኝ።

በአቀራረቡም አንዳንድ ጓዶች ተናደዱበት። የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊ አባላትም ጭምር በአካሄዱ ያልተደሰቱ ነበሩ። ብርሃኑና ሊበን "አይዞህ ግደለም አትበሳጭ፣ እርሱ ዝም ብሎ ነው!" አሉኝ። እኔም ነገሩን ተውኩት፤ ብስጭቴንና ቁጭቴን እንደያዝኩ ዝም አልኩ።

በሌላ ጊዜ የዋርድያ ምደባና ቁጥጥር ስናደርግ በአንድ ጊዜ ሁለት ዋርዲያዎች እንዲቆሙ የሚያስፈልጉበት ቦታና ጊዜ ነበረ። ሁለት ዋርድያዎች በአንድ ላይ ሆነው ለሁለት ሰዓት ይጠብቃሉ። አንድ ቀን ሁለት ዋርዲያዎች በምናስወጣበት ጊዜ አንድ የፓርቲ ኮሚቴ አባልና አንድ ሌላ ጓድ አብረው ዋርዲያ ተመደቡ። ሁለቱ የቅርብ ጓደኞች ነበሩ። ጓዱ በጣም ጥሩ ሰው ሲሆን ተጫዋች፣ ትግስተኛ፣ ሲናገር ረጋ ያለ ብስለት ያለው ነበረ።

ታዲያ ሁለቱ በአንድ ላይ ነበር ዋርድያ የሚቆሙት። ጥበቃውን የሚረከቧቸው ተረኞች በሚቀያየሩበት ጊዜ አንዱን ብቻ በጥበቃ ላይ እንደሚያገኙት ነገሩኝ። በዋርድያ ላይ የሚመጣ ቸልተኝነትና ስህተት ሁሉንም ጓዶች አደጋ ውስጥ የሚከት ችግር ሊፈጥር ስለሚችል በቀላሉ የሚታለፍ አይሆንም። መረጃውን ይገፍ በደንብ አጠናሁና እነርሱ በሚወጡበት ጊዜ ከሚቀይሯቸው ዋርዲያዎች አንዱ እንዲቀሰቅሰኝ ነገርኩት። እንዳልኩትም ቀሰቀሰኝ፤ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ስሄድ፣ አንደኛው ጓድ እየጠበቀ የፓርቲው ኮሚቴ አባል ግን ተኝቶ ደረስኩ። " የታለ ካንተ ጋር የተመደበው ጓድ፣ በየተራ ሳይሆን ሁለታችሁም በአንዴ እንድትጠብቁ ነው የተመደባችሁት" ብዬ ጓዱ ላይ አፈጠጥኩበት።

"እኔ ተነሥቼ እየጠበቅኩኝ ነው፣ እሱ አልተነሣም ታዲያ እኔን ምን አድርግ ትለኛለህ?" አለኝ ጓዱ። ከዚያም እሱን ትቼ "ያን ጓድ ሄጄ አንተ ለምንድ ነው ዋርዲያ ጠብቅ ተብለህ፣ ዝም ብለህ የምትተኛው? ለምን አልተነሣህም?" ብዬ ጠየቅሁት።

"ማንም አልቀሰቀሰኝም!" አለኝ።

"ያም ሆነ ይህ ሁለት ሰዎች በአንድነት እንድትጠብቁ ተመድባችሁ አንተ ለብቻህ እሱ ለብቻው እየተቀያየራችሁ እንደምትጠብቁ በደንብ አውቀነዋል!!"አልኩት።

"እባክህ ዝም በል!' ጋኖች አለቁና ምንቾቶች ጋን ሆኑ" ብሎ ተረተብኝ። ግልጽ ስድብ ነበር።

ጠዋት ያንኑ ለሰለሞንና ለየአቢኢዮ ነገርኳቸው። ጌትነት በዳንግላት ተኩስ ላይ ስለተመታና ቁስለኛ ስለሆነ የአብኢዮ ኃይል መሪ ሆኗል። ሌላ ምክትል የኃይል መሪ ግን አልተመደበም። ማታ እንደምንነጋገርበት ተነገረኝ። ማታ ሂስና ግለ ሂስ ይደረጋል ብዬ ስጠብቅ ምንም ነገር አልነበረም። በእዚህና በመሳሰሉት





በሁለታችን መካከል ትልቅ ቅራኔ ተፈጠረ። ሊያሾፍ ሲሞክር ብርሃነ ዓባይ (ብርሃነ ወልቃይት ላይ የኃይል አመራር ሆኖ በውጊያ ላይ ተሠውቷል) በጣም ተናደደና "እሁንስ አበዛኸው!" ብሎ የክላሽኑን አፈሙዝ አፍንጫው ላይ አድርሶ ሊሰካበት ምንም አልቀረውም፤ ሁለታችንም በጣም ተናደድን። ምክንያቱም ሂስ እንኳ እንዲሰጠው አልተደረገም። ሌሎቹ ለምን ዝም እንዳሉ ወይም ለምን እንደፈሩ አልገባኝም። እኔን የበለጠ ያበሳጨኝ ይሄ ነበር። ምክንያቱም ህግና ደንብ የሚባለው ነገር በሁላችንም ላይ እኩል ነው መተግበር ያለበት፣ እያደር ግን ነገሮች መስመራቸውን ስተው እየወጡ መጥተዋል።

እንደዚያ ዓይነት የመናናቅ ችግር በእኔና በእርሱ መሀል ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎችም መካከል መታየቱ እየተዘወተረ ሄዷል። ችግሩ ተባብሶ በየጋንታው ስለተስፋፋ በኃይል አምስት መቶ ውስጥ ከፍተኛ መከፋፈል ተፈጠረ።

ለምሳሌ እንደዚያ ዓይነት ሁኔታ ከማያስደስታቸው ጓዶች መሃል ጸዳለ፣ አዳል፣ እንግዳ ወርቅ፣ሊበንና ብርሃኑ እባካችሁ ይሄ ትክክል አይደለም፤ ጓዶችን አትከፋፍሉ፤ እነርሱም ዕድል ቢያገኙ ኖሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጨርሰው ዩኒቨርሲቲ ይገቡ ነበር፣ ነገር ግን ከትምህርት ቤት በቀጥታ ወደትግል ስለመጡ ነው፣ ስለዚህ እነርሱን ማግለል ትክክል አይደለም" በማለት የተሳሳተ አቅጣጫ የያዙትን የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎች ለማረም ይታገሉ ነበር። ይሄ ዝንባሌ በሌሎች ኃይሎችም የታየ ቢሆንም ፣በኃይል አምስት መቶ ግን በጣም ጎልቶ ወጣ። ቅራኔው በጣም እየከረረ ሲሄድ ችግሩ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎቹንም መከፋፈል ጀመረ።

ችግሩ እየከረረ በመጣበት ጊዜ እኛም እራሳችንን የማግለል ብቻ ሳይሆን ራሳችንን የማሰባሰብ እንቅስቃሴ የማድረግ አዝማሚያ ያዝን። ሁኔታዎች ጥሩ አልነበሩም፤ ድርጅቱ እንደፈለግነው አይንቀሳቀስም የከተማው ትግል ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን እንሰማለን የገጠሩ ግን በጣም ተዳክሟል፡፡ ከገጠር ገጠር፣ ከመንደር መንደር እየሄድን መብላት ሰልችቶናል። ትግል ካለ

መሞትም መቁሰልም አለ፤ ጠላት ወደአለንበት ቦታ ካልመጣ እኛ መሄድ እንጂ እስከሚመጣ መጠበቅ ትክክል አይደለም። ስለዚህ "እስከመቼ ነው እንደዚህ የምንሆነው?" የሚል ማጉረምረም ነበረ ።

እንዲያ በትንሽ በትልቁ መከፋፈልና አለመግባባት እንዲሁም መፈራራት እያደገ ሲመጣ ተስፋ መቁረጥና ጭንቀት በብዙዎች ላይ የሚታይ ችግር ሆነ። "አልታዘዝም፣ መሀይም የገጠር ልጅ፣ የደርግ ወታደር፣ የአመራር ተላላኪ..." እያለ ቅጽሉ ሌላ ቅጽል እየጨመረ ሲሄድ ሁሉም በትናንሽ ቡድንና ሐሳብ ውስጥ መዋጥ ጀመረ። ይህ ስሜት ወደየክፍሉ ለመዛመት ጊዜ አልወሰደበትም። የክፍለ ህዝቢ ወይም ደግሞ የደኅንነት ጓዶች በምናገኝበት ጊዜ "እናንተ ዝም ብላችሁ ነው እንጂ፣ ድርጅቱ ፈርሷል የከተማ መዋቅሩ ተበትኗል" ብለው የሚነግሩን ጓዶች ነበሩ።

የትግል ስሜታችን እየቀነሰ በሄደ ቁጥር እንዳንዶቻችን የመሰናበት ጥያቄ ማንሳት ጀመርን። አንድ ቀን አንድ የእኛ ክፍለ ሕዝቢ ደከም ያለበት ቦታ ከወያኔ ጋር ስብሰባ በሚያደርጉበት ወቅት ከኃይል አምስት መቶ ለሕዝቡ ንግግር ለማድረግ እኔ፣ ሮምሀና አሰፋ ተላክን። የሄድንበት ሥራ እንዳሰብነው ስላልተቃና የግድ ማደር ነበረብንና አደርን። ጋንታዎች የሶስት ቀን መንገዳቸውን ነግረውን ስለነበር፣ በማግስቱ ረፋድፋድ እንዳለ ወደአሉበት ቦታ ሄድንና ተደባለቅን። እንደደረስን ድላይ መጣችና "ና እስቲ" አለችኝና "የት ነው ያደራችሁት?" ብላ ጠየቀችኝ።

"ውይይቱ በጣም ስለቆየና የሕዝቡ ሁኔታ ጥሩ አዝማሚያ ላይ ስላልነበረ፣ ሁኔታውን ለማረጋጋት የወያኔ ሰዎችም በመምጣታቸው ከእነርሱ ጋር መነጋገር ነበረብን፤ እዚያው አመሸን። ሲመሽ ደግሞ ገበሬዎች አድራችሁ ሂዱ ብለው አስገደዱን" አልኳት።





"ጠዋት፣ ሦስቱም ከዱ ተብሎ ሹክሹክታው በዝቶ ነበረ። አሁን ስትመጡ እኮ፣ ሁሉም እፍሮ ዝም አለ። ስለማ በጣም ነበር ያዘንኩት። እንዴት አማኑኤል ሳይሰናበተኝ ዝምብሎኝ ይሄዳል ብዬ ግራ ገባኝ" አለችኝ።

"ምነው እስከዚህ ድረስ፤ ዝም ብለው ይከዳሉ የሚሉን" አልኳት።

"በታ እየተበሳጫችሁ እንደሆነ ሁሉም ያውቃል፣ ለዚህ ነው" አለችኝ።

ከክፍለ ህዝቢ ጓዶችም "ይሄ ድርጅት ችግር ውስጥ ነው፣ ሊመራን የማይችል ከሆነ አንድ ነገር ለምን አናደርግም? ለምን የራሳችን ድርጅት ፈጥረን እዚህ ትግራይ ውስጥ አንንቀሳቀስም?" የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳት የጀመሩበት ሁኔታም ነበር። ለአንድ ቀን የተላከንበት ቦታ ለሁለት ለሦስት ቀን ቆይተን ምን ማድረግ እንዳለብን መነጋገር ጀመርን።

በዚያው ሰሞን በመንገድ ላይ እያለን፣ ጴጥሮስ የሚባል የብዙሀን ድርጅት አባል የነበረ ወደ ብዘት አካባቢ መጣና ለብቻዬ አነጋገረኝ። "ድርጅቱ እየፈረሰ ነው፤ ይህ ድርጅት እኛን መርቶ ወደ ድል ሊያደርሰን አይችልም እኛ አምስት፣ ስድስት ሆነን ለመክዳት አስበናል። ሁሉም የብዙኃን ድርጅት አባሎች በሙሉ የትግራይ ልጆች ናቸውና ችግር የለብንም፣ አንተም አብረኸን ለመሄድ የምትፈልግ ከሆነ ብዬ ነው ላነጋግርህ የመጣሁት" አለኝ።

ብዙ ተነጋገርንና "እኔ በአሁን ጊዜ ድርጅቱን ለቅቄ ለመሄድ ገና አልወሰንኩም" አልኩት። ከጥቂት ቀናት በኋላ መጥፋታቸውን ሰማሁ።

ወደ አሲምባ ስንሄድም በጉሎ ማከዳ አካባቢ የነበሩ ጓዶችም እየጠፉ ነበር። ክፍለ ሕዝብ የነበሩ ጓዶችም ጠፍተዋል። ብቻ በሚታየው ነገር ሁሉ በጣም እየተበሳጩ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብዙ የትግራይ ጓዶች እየከዱ ወደ ኤርትራ ሄዱ። የተደረገው የእርማት እንቅስቃሴ ግቡን አልመታም ተብሎ በብዙ የሠራዊት አባላት ጥያቄዎች ተነሥተው ነበር። በተለይ ኃይል አራት መቶ የእንጃ ሁኔታ ጎልቶ ወጥቷል። ኃይል አራት መቶ ማለት የፖለቲካና የወታደራዊ ትምህርት ሥልጠና የሚወስዱ አባላት የያዘች ኃይል ነች። ሥራቸው ሁሉ

ውይይት ስለሆነ ሁሉንም ነገር ይወያዩበታል፡፡ "ድርጅቱ እንደሚፈለገው አይንቀሳቀስም፣ የተሳሳተ መንገድ እየተከተለ ነው፣ በዚህ ሁኔታ ደግሞ ድል ሊያደርግ አይችልም" የሚሉ ሐሳቦች አንስተዋል።

ታህሣሥ 1970 ዓ.ም ላይ በአመራሩ ጸጋዬ ደብተራው፣ አንበርብር፣ ፀሐይና ጌዲዎን ያሉበት፣ ኮሚሽን ተቋቁሞ፣ የኃይል አምስት መቶን ችግር ለመፍታት ወደ አድዋ መጡ። ችግሩን ለመፍታት ለተወሰኑ ቀናት ከእኛ ጋር ቆይተው ከጋንታ ጋንታ እየዞሩ ሁሉንም አነጋገሩና ያለንበትን ሁኔታ ጠይቀውን ነገርናቸው። በመጨረሻም ችግሩ እንደሚፈታ ገልጸው፣ ይሁን እንጂ መፍትሔ ላይ እስኪደረስ ድረስ ሁላችንም በትዕግሥት መጠበቅ እንዳለብን ነገሩን።

በመካከል እኔና አሰፋ ወደ አሲምባ ተላክን። ከመሄዳችን በፊት ጸጋዬ ደብተራው ለብቻዬ ጠራኝና "አሁን ሁሉንም ነገር አሻሽለሀል፣ ያላሻሻልካት ነገር አንድ ብቻ ነች። እሷም የጓደኝነትና የድርጅት ፍቅር አለመለየትህ ነው። ጓደኞችህን ትወዳለህ፣ ድርጅትህንም ትወዳለህ፣ ጓደኞችህ እየመጡ አብረኻቸው እንድትከዳ ይጠይቁሃል አንተ ግን " አልወጣም አልሄድም" ትላቸዋለህ። እነርሱ ሲሄዱ ግን ዝም ትላለህ እንጂ አሳልፈህ አትሰጣቸውም። ስለዚህ ከድርጅቱና ከጓደኝነት ፍቅር ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት እንዳለብህ ካሁን በኋላ እንድታስብበት እፈልጋለሁ። አንተን ለወደፊቱም በጣም እንፈልግሀለን" አለኝ።

"እሺ አንግዲህ አስብበታለሁ፣ ከአሁን በኋላ አስተካክላለሁ" አልኩት።

ጸጋዬ አላበቃም "በአንተና በፓርቲ ኮሚቴ አባሉ መካከል ያለው ቅራኔ በፍጹም መኖር የሌለበት ቅራኔ ነው። ሁለታችሁም ያላችሁት በአንድ መስመር ውስጥ ነው። የሚያጣላ ነገርም የላችሁም። እርሱን አነጋግሬዋለሁ፣ ችግራችሁ በጣም ቀላል ሲሆን የሚያስፈራም የሚያሰጋም ነገር የለበትም፤ ስለዚህ በእሱ





ላይ ያለህን ቅሬታ እንዣ። እርሱም ባንተ ላይ ቅሬታ የለውም። በሁለታችሁ መካከል ምንም መሠረታዊ ልዩነት የለምና በዛ በኩል እንዳታስብ" አለኝ።

***

በማግስቱ ወደአሲምባ ትሄዳለህ ተብዬ የማደርሰው ደብዳቤ ተሰጠኝ። ወደ አሲምባ ይገፍው ከምሄደው ደብዳቤ ሌላም የተሰጠኝ ሐላፊነት ነበረ። እንደአጋጣሚ ሆኖ ከፈረስ ማይ ወረዳ የወያኔ ሚሊሻ ሐላፊ የነበረ አባዲ ደስታ የሚባል የወያኔ አመራር አስሮት ነበረ። እሱ ግን ከእስር ቤት አምልጦ ሸፍቶ ቆይቶ ወደ እኛ መጣ። እርሱንም ወደ አሲምባ እንድናደርስ ነበር ሁለተኛው ሐላፊነት።

ወደ አሲምባ ለመሄድ እየተዘጋጀን እያለ ምክትል የፖሊቲካ ጉዳይ ሐላፊው ብርሃኑ ደቦጭ መጣ። አማኑኤል አንድ ጊዜ ላነጋግርህ አለና ለብቻየ ጠራኝ። " ነገ ወደ አሲምባ እንደምትሄድ ታውቃለህ?" አለኝ።

"አዎ አውቃለሁ"

"አባዲን ይዘህ እንደምትሄድ ታውቃለህ?"

"አመራሩ የሚሰጥህ ደብዳቤም አለ እሱንም ይዘህ ነው የምትሄደው"

"አዎ"

"ለነማን እንደምትሰጥ ታውቃለህ? እሱን እነሱ ይነግሩሃል። አሁን ግን እኔ አንድ ምስጢር እነግርሃለሁ። ይዘህ የምትሄደው ሰው ወንጀለኛ ነው፤ ወንጀሉን እርሱ አያምንበትም። እኛ ግን ትክክል መሆኑን አውቀናል። ወያኔዎች እርሱን ያሰሩበት ምክንያት ባሏ የሞተባት፣ የቄስ ሚስት ስለደፈረ ነው። ሴትዮዋ ሁለት ልጆች ታሳድጋለች፣ በሀገሩ ባህል የቄስ ሚስት ካላፈረሰች በስተቀር ለቄስ የሚሰጠው ግብርና መሬት ይሰጣታል፣ በዛ ልጆቿን ታሳድጋለች። ካመነዘረች ወይም ሌላ ባል ካገባች ግን አይሰጣትም። ስለዚህ እርሱ ጥቂት ሚሊሻዎችን አስከትሎ ሄዶ ቤቱን ከቦ ቢደፍራትም፣ ለእነርሱ ግን አልደፈረኝም ብላለች። ምክንያቱም ደፈረኝ ካለች መሬቷን ትነጠቃለች። እነርሱ ግን እንደ ደፈራት በደንብ ስላወቁ አስረውት ነው የሄዱት። ሴትዮዋ ለእኛ እንደደፈራት ነግራናለች። ነገር ግን ለሰው ከተናገራችሁ መሬቴ ይወሰድብኛል፣ ልጆቼን እንዴት አሳድጋለሁ ብላ አለቀሰች። ስለዚህ ይህ ይዘኸው የምትሄደው ሰው ወንጀለኛ ነው።





መንገድ ላይ ወያኔዎች ካገኙህና እርሱን እንወስደዋለን ካሉህ፣ ስጣቸው፤ ይግደሉት። እንዲያውም አንተ ራስህ ግደለው። እኔ ድርጅቱ ለምን እንደተቀበለው አላውቅም፤ እና ለእርሱ ብለህ ከወያኔዎች ጋር ተጣልተህ አደጋ ውስጥ እንዳትገባ" አለኝ።

በማግስቱ ደብዳቤዎቹ ተሰጡኝና ለፀሐዬ ወይም ደግሞ ለዳዊት እንድሰጥና በምንም ምክንያት ግን ለመዝሙር እንዳልሰጥ ተነገረኝ። ከአሰፋ ጋር ተጉዘን ብዘት ስንደርስ በገበያ ቀን የኃይል አራት መቶ ጓዶችን አገኘናቸው። ከእነሱ ጋር ሰላምታ ተለዋውጠን ወደ ኢጋሜ ስንሄድ ደግሞ፣ ሰግላት እንደደረስን ከኃይል ሃምሳ ስምንት አባላት ጋር ተገናኘን። እነርሱ ጋ የአመራር አባል (የጠቅላይ ፓርቲ ኮሚቴ አባል) የሆነው፣ ዘለቀ እየጠበቀኝ ነበርና ጠርቶ "አማኑኤል አንተ ነህ?" ብሎ ጠየቀኝ። ከዘለቀ ጋር ከዚህ በፊት ተገናኝተን አናውቅም ነበር።

"አዎ" አልኩት።

"አንድ ጊዜ ወደቤት እንሂድና ላነጋግርህ እፈልጋለሁ" አለኝና ቤት ውስጥ ይዞኝ ገባ።

"ያመጣሃቸው ደብዳቤዎች አሉ?"ሲል ጠየቀኝ።

"አዎ"

"ላነበው ፈልጌያለሁና ትሰጠኛለህ?"

"አንተ ማን እንደሆንክ አላውቅህም፣ እንዴት እሰጥሃለሁ?" አልኩት።

ሳቅ አለና "እኔ ዘለቀ እባላለሁ። የአመራር አባል ነኝ" በማለት ነገረኝ።

"እኔ ግን ለአንተ ስጥ አልተባልኩም"

"ግድየለም፣ ለእኔ ልትሰጠኝ ትችላለህ" ሲለኝ፣ እሺ ብዬ ሰጠሁት።

ደብዳቤዎቹን ቀዶ አነበበና እንደገና አሽጎ መለሰልኝ። ከእነርሱ ጋር አድረን፣ በቀጣዩ ቀን ከኃይል ሃምሳ ስምንት ሦስት ጓዶች ተሰጡንና እርሱም ከኛ ጋር አብሮን ሆኖ ወደ ዳህዋን ሄድን። በመንገዳችን ላይ ዘለቀ "የትግራይ ጓዶች ድርጅቱን እየለቀቁ ናቸው። እኛ በማናውቀው መንገድ ያስቀየምናቸው ነገር ይኖር ይሆን?" ብሎ ጠየቀኝ።

"ያልተማረ የተማረ እየተባለ ነው ልዩነት የተፈጠረው" አልኩት።

"እንደሱ ከሆነ ግዴለም እናስተካከለዋለን፤ አይዟችሁ" አለኝ

ዳህዋን እንደደረስን፣ ዘለቀም ከእኔ ጋር እንዳለ " ራስህ ቀደህ እንዳነበብከው ንገራቸው" አልኩትና ለተባሉት አመራሮች በፊቱ ደብዳቤውን ሰጧቸው።

ደብዳቤውን ባደረስኩ በማግስቱ ደግሞ መዝሙርን አገኘሁት። መዝሙር ወፈር ያለና ቁመቱ ረዥም ነው። ፈገግታ አይለየውም፤ በአነጋገሩም የመማርከ ችሎታ አለው። "ወንዝ እግራችንን ታጥበን እንመለሳለን" ብሎኝ አብረን ሄድን። ወንዝ እግራችንን እየታጠብን በኃይል አምስት መቶ ውስጥ ስላለው ሁኔታ ጠየቀኝና አንዳንድ ችግሮች እንዳሉ ነገርኩት። እርሱም "እኛም ጋ አንዳንድ ችግሮች አሉ፤ ችግሮችን ለመፍታት እናንተም በየበኩላችሁ የየድርሻችሁን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባችሁ" አለኝ -በደፈናው። በዚህ ጊዜ ለመዝሙር ደብዳቤዎቹን እንዳትሰጠው ያሉኝን አስታውሼ፣ ከነገረኝ ነገር ጋር ሳዛምደው በመካከላቸው ትልቅ ችግር እንዳለ ገባኝ።

ወደ አሲምባ እንድናደርሰው የተሰጠንን አባዲ ደስታን ለአመራሩ ከአስረከብን በኋላ ከእኛ ድርጅት ጋር አልቆየም፤ ይልቁንም አመራሩ ሰውየውን ከእኛ ዓላማ ጋር ሊጣጣም የሚችል ሆኖ ስላላገኘው አካባቢውን ለቅቆ እንዲሄ ፈቃድ ሰጥቶታል።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከአመራሩ አባላት አንዱ ጋይም (ገብረ እግዚአብሔር ኃ/ሚካኤል) አሲቴና አብረን እንድንሄድ እኔን እየጠበቀ ነበርና ስንገናኝ እዚያ ወደሚገኘው የልደታ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ተነሣን። ቤተ ክርስቲያን ከመድረሳችን ጋይምም ልክ ከመዝሙር ጋር እናወራ ስለነበረው ስለ ኃይል አምስት መቶ ችግርና እንቅስቃሴ ጠየቀኝ። በሠራዊቱ ጦር ሰፈር ውስጥ ከሚወራው መጥፎ ነገር እንድጠነቀቅ፣ ከአንጃ እንቅስቃሴና ከወሬ ራሴን እንድጠብቅ





አስጠነቀቀኝ። ጋይም የፈለገኝ ምናልባት ከመዝሙር ጋር አብረን እንደነበርን ስላወቀ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።

ቤተ ክርስቲያን ከመድረሳችን በፊት ወደ አንድ ቤት እንደምንሄድ ነግሮኝ ወደዚያው አመራን። እኔ ጋይም እዚያ ቤት ውስጥ ምን እንደሚፈልግ አላወቅኩም። ከቤቱ ደጃፍ ላይ እንደቆምን፣ "የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ቤተሰቦች ቤት ነው" አለኝና፣ እዚህ ውስጥ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር የሆነው ዘርኡ ክህሸን እንደሚኖርና ከእርሱ ጋር እንደሚያስተዋውቀኝ ነገረኝ። እኔም ከአንድ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር ጋር ለመተዋወቅ ዕድል በማግኘቴ በጣም ደስ ብሎኝ እስከማየው ድረስ ቸኰልኩ።

የቤቱ ዋና በር በአለበት በሰሜን አቅጣጫ በኩል ነበር የሄድነው። ከመድረሳችን በፊት ትልቅ ጥቁር ፊት ያለውና ጸጉሩን ያጎፈረ ሰው አንገቱን በመስኮት አወጣና ተመለከተን። ከዚያም ዘርኡ ጋይምን አየውና ፈገግ ብሎ ሰላም ሊለው ወጣ። ዘርኡ እኛ ጋ ሲደርስ ጋይም ከእኔ ጋር አስተዋወቀው። በዚህ ጊዜ እኔ ለፓርቲያችን ከፍተኛ አመራር የሚገባውን በወታደራዊ ተጠንቀቅ አቋቋም ሆኜ ሰላምታ ሰጠሁት። በቀኝ እጄ የያዝኩትን ጠመንጃዬን በፍጥነት ወደ ግራ እጄ በማዞር ጨበጥኩት። ዘርኡ በቅልጥፍናዬ መደሰቱን በሚያሳይ ማራኪ ፈገግታ ጋር ጨበጠኝ።

ከጋይም ጋር ለአጭር ግዜ እስኪነጋገሩ እኔ ወደኋላ ትንሽ ራቅ አልኩና ጠበቅኳቸው። ሲጨርሱዘርኡ ሊሰናበተኝ ወደ እኔ ሲመጣ አሁንም ለመሪ በሚገባ አክብሮት ቀልጠፍ ብዬ ጨበጥኩትና በድጋሚ በተጠንቀቅ ቆምኩ። አሁንም ፈገግ አለ።

ጋይም ባሳየሁት ወታደራዊ ቅልጥፍናና አክብሮት እንደተደሰተ እየነገረኝ መንገዳችንን ቀጠልን። የመጣነው በቤተ ክርስቲያኑ ዋና ቄስ ራት ተጋብዞ እንደሆነ ጋይም ወደቤተክርስቲያኑ አካባቢ ስንደርስ አጫወተኝ። ከእራት ግብዣው በኋላ የጸሎት ሥነሥርዓት እንደሚደረግም ነገረኝ።

ልደታ ካቶሊክ ቤተ ክርስትያን የብዙ ዓመታት ዕድሜ ያላትና በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት። ስንደርስ ዋናው ቄስ ተቀበሉንና ወደ ምግብ አዳራሹ እየመሩ ይዘውን ገቡ። አዳራሹ ውስጥ ሦስት በረዥም ቁመት የተደረደሩ ጠረጴዛዎች ይታያሉ። በግራና ቀኝ በኩል ካሉት ወንበሮቻቸው ላይ፣ የደንብ ልብስ የለበሱ ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ ተማሪዎችና የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ተቀምጠዋል። በአንድ ጥግ በኩል በየዓይነቱ ምግብ የተደረደረበት ጠረጴዛ አለ። ተረኛ አስተናጋጆቹም ዝግጅታቸውን ጨርሰው የእራት ሥነሥርዓት እስኪጀመር በአንድ በኩል ተሰልፈው ቆመዋል።

እኔና ጋይም ከዋናው ቄስ አጠገብ ስለተቀመጥን ብፌውን ለማንሣት ከመጀመሪያዎቹ ውስጥ ሆነን ቄሱን ተከትለን ሄድን። ወደ ጠረጴዛው ጠጋ ብዬ የተደረደረውን ምግብ ሳይ ዓይኖቼን ማመን አቅቶኝ ነበር። እንኳንና ምግብ ያረረበት አንድ ተራ ታጋይ ይቅርና በከተማ ያለ ሀብታም ቤት ሊገኝ የማይችል ዝግጅት እንደሆነ ምንም አያጠራጥርም። ከተወለድኩ ጀምሮ እንደዚያ ያለ ምግብ አይቼ አላውቅም። እንጀራው ከንጹህ ነጭ ጤፍ የተጋገረ ነው። ወጡ እጅግ ብዙ ዓይነት ነበረ። አትክልቱና ፍራፍሬው ተደርድሮ ለመብላት ብቻ ሳይሆን ለማየትም ያጓጓል። ምግብ ተነሥቶ ካለቀ በኋላ የምስጋና ጸሎት ተደርጎ መመገብ ተጀመረ። ሳህኔ የቻለውን ያህል አንሥቼ ብሄድም ገና ሁለቴ የጎረስኩ ሳይመስለኝ አጣራሁት። ሁኔታዬን የሚከታተሉት ዋናው ቄስ እንዲጨምርልኝ አዝዘው ጨምሬ ብበላም በደንብ ልረካና ሊወጣልኝ አልቻለም፣ ግን ከዚያ በኋላ ይሉኝታ ስለያዘኝ እንደበቃው ሰው ሆንኩ። የታዳሚው ዓይን በሙሉ እኔ ላይ እንደሆነ ተሰምቶኛል። በአበላሌ ብቻ ሳይሆን የለበስኩት ካኪ ጉርድ ጃኬትና ቁምጣ፣ የጎፈረው ጸጉሬና የያዝኩት ጠመንጃ ከሁሉም የተለየሁ መሆኔን ይናገራሉ።

የራት ሥነሥርዓቱ ካበቃ በኋላ ጋይም ነግሮኝ የነበረው ረዥም የጸሎት ሥነሥርዓት ተጀመረ። እኔን የገረመኝ የጋይም ጠንቅቆ ማወቅ ነበር።





ምናልባት የዚያ ቤተ ክርስቲያን አባል እንደነበረ ተጠራጠርኩ። የሚባለውን **አኩል** ይላል፣ ዜማውን ከእነርሱ እኩል ያውቀዋል። ብቻ እያንዳንዱን ስነስርአት አንድም ሳያዛባ ነበር ጸሎቱ ያበቃው። በመጨረሻ ዋናውን ቄስ አመስግነን ተሰናበትንና ወጣን። ቀኑ መሸቷል፤ ግን አሊቴና ለአሲምባ ቅርብ ነው በዚያ ላይ ነጻ የወጣ አካባቢ ስለሆነ ምንም አስጊ ነገር የለም። ይሄንን ሳስብ ጋይም እኔን ይዞ የመጣው ለደኅንነት ሲል እንዳልሆነ ገምቻለሁ። ምናልባት መዝሙር ጠርቶ ይዞኝ እንደሄደና አብረን እንደቆየን ስላወቀ አንዳንድ ነገሮች ሊጠቁመኝና እንድጠነቀቅ ስለፈለገ ይመስለኛል። አሲምባ ደርሰን እስክንለያይ ድረስ ጋይም ስንሄድ ጠቆም ካረገኝ ነገር ሌላ አብሬው እንድሄድ የፈለገበትን ምክንያት አልነገረኝም። የእርሱ ምክንያት ምንም ይሁን ምን የዚያ ቀን አጋጣሚ ግን በሕይወቴ የማላገኘውና የማልረሳው፣ ትልቁ የጋይም ማስታወሻ ትዝታዬ ሆኖ ዕድሜ ልክ አብሮኝ ይኖራል።

***

እኔና አሰፋ አሲምባ ሁለት ቀን ዐረፍንና ወደ ሁለት አውላሎ ተላከን። ወደዚያ የምንሄድበት ምክንያት ግደይ ጨዓር ከኃይል አምስት መቶ ወደ ሁለት አውላሎ ለዕረፍት ብሎ እንደሄደ በዚይው ስለቆየ እነጸጋዬ ደብተራው "ሄደህ አነጋግረውና እንዲመለስ አድርገው" ብለውኝ ነበር። "እኛ መጥተን ኃይል አምስት መቶ ውስጥ ያለውን ችግር እንደፈታነው ንገረው"። እኛ ወደ እርሱ ስንሄድ ሳዕሲዕ ላይ ግደይን ከኃይል ስልሣ ስድስት ወደ አሲምባ እየመጣ አገኘነው። እርሱን ይዘን ወደ ብዘት ስንሄድ ታሪኩን አገኘነው።

ታሪኩን ስናናግረው በድርጅቱ ውስጥ ስለተፈጠረው ችግር በግልጽ ነበረ ያስረዳን፤ የእርምት እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ ግን የድርጅቱ መውደቅ አይቀሬ መሆኑንም አጠንክሮ ነገረን። "ኃይል አምስት መቶም ውስጥ የእኛ ሰዎች አሉ፣ ያነጋግሩሀል። ብዙ ችግሮች አሉ ድርጅቱ ግን ትልቅ ትግል እያደረገ ነውና ይፈታል" ብዬ አግባባሁት። የታሪኩ ዕውነተኛ ስም ከድር ነበር፤ በኋላ ላይ በአንጃነት ምክንያት በሠራዊቱ ተገደለ። ብዘት እንደደረስን ከኮሚሽን አመራሮች እና ከኃይል አምስት መቶ ጋር ተገናኘን። የጠፓአኮ አባል ከሆነው ከጌዲዎን ጋር አንድ ሻይ ቤት ገብተን ሁሉም ነገር እንደተፈታና ችግሩ እንደተቃለለ ነግሮኝ የስንብት ጥያቄዬን እንዳነሳ ጠይቆኝ ተስማማሁ።

***





1970 ዓ.ም. የካቲት ወር መጀመሪያ ላይ የፖለቲካ ኮሚሳሩ ሰሎሞን በከተማው የፓርቲ ኮሚቴ ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ነበለት ይሄድ ነበረ። እኔና ብርሃኑ ሰሎሞንን አጅበን እንድንሄድ ተመደብን። ወደ አመሻሹ ላይ ነበር የተነሣነው፤ እኔ ከፊት ሰሎሞን ከመሐል ብርሃኑ ደግሞ ከኋላ ሆኖ ነበር ጉዞ የጀመርነው። ሰሎሞን ስብሰባው ላይ ተሳትፎ በሰላም እስኪመለስ ድረስ ሐላፊነት ነበረብን። እኩለ ሌሊት ሊሆን ትንሽ ሲቀር ነበለት ደረስንና ሰለሞንን ስብሰባው የሚካሄድበት ቤት አስገብተነው እኛ በሁለት አቅጣጫ ቆመን አካባቢውን መጠበቅ ያዝን። እኔና ብርሃኑ ወደቤቱ ውስጥ አልገባንም፣ ተሰብሳቢዎቹንም አላየናቸውም። ስብሰባው ረዘም ያለ ጊዜ ውስዶባቸው ከሌሊቱ አስር ሰዓት አካባቢ ተጠናቀቀና ሰለሞንን አጅበን ተመለስን።

ከነበለት ስንመለስ አሲምባ ደርሶ የመጣውን አስፍሃን አግኝቼ ሳናግረው፣ ሠራዊት የመቀየጥ ምደባ እንደተደረገና ምድቡ እንደተነገረው ገልጾ "አንተም ወደ ሌላ ኃይል ተቀይረሀል" ብሎ ነገረኝ። የተመደብኩበትን ኃይል እንዲነግረኝ ጠየቅሁት።

ጋንታ ሀያ ስድስት የምትባል ወደ በጌምድር በምትሔድ ጋንታ ውስጥ እንደተመደብኩ ነገረኝ። ደነገጥኩና "ለምንድነው ካለሁበት ኃይል ቀይረው ያውም ወደ ጎንደር ሊልኩኝ የፈለጉት?" የሚል ሐሳብ ገባኝ። ከኃይላችን የፖለቲካ ሐላፊ ከሰለሞን ጋር በጣም ስለምንግባባና ስለምንቀራረብ፣ የሰማሁትን ነገርኩትና ሐሳብ እንደገባኝና ነገሩም ደስ እንዳላለኝ ገልጬለት የሚያውቀው ነገር እንደአለ ስጠይቀው "ማን ነገረህ?" አለኝ።

"አስፍሀ ከአሲምባ ሰምቶ ነው የነገረኝ" አልኩት

"የአንተ ምደባ እውነት ከሆነም ለጥሩ ነው እንጂ፣ ለመጥፎ አይደለም። ስለዚህ ምንም አትስጋ። ምክንያቱን ቀስ ብለህ ታውቀዋለህ፣ መቸኮል አያስፈልግም" አለኝ። ይኼን ስሰማ ተረጋጋሁና ሄድኩ።

ስድስት

# ስድስት
# የውቅሮ ተልእኮ

## አራት ኃይሎች በክልተ አውላሎ

«ንፁሕ ወርቅ እሳት አይፈራም!!»

ያልታወቀ ጸሐፊ - የቻይናዎች የጀግንነት ምሳሌ

ጥር 13 ቀን 1970 ዓ.ም. ኃይል አምስት መቶ በአመራሩ ተጠርታ ወደ ክልተ አውላሎ ተንቀሳቀሰች። ሌሊቱን የፍጥነት ጉዞ አድርገን ጥር 14 ቀን ክልተ አውላሎ ስንደርስ ሌሎች ኃይሎችም ደርሰው እየጠበቁን አገኘናቸው። በጠቅላላው አራት ኃይሎች ሆነን አንድ ላይ ሰፈርን። የዚያን ቀን ሌሊቱን የኃይል አመራሮች ስብሰባ ተጠርተው፣ ሲነጋገሩ አደሩ።

በቀጣዩ ቀን ደግሞ የጋንታ አመራሮችንም የሚጨምር ሌላ ስብሰባ ተጠራ። ጋንታዎቻችንን ቦታ አስይዘን ሁላችንም ሰፊ አዳራሽ ወዳለው ቤት ውስጥ ገባንና ተሰበሰብን። ቆሎ እየበላን ወደ አመሻሹ ላይ ስብሰባው ተጀመረ። መጨለም ሲጀምር ስለሞን የቀለኮሰ ኩራዝ ይዞ መጣ። በስብሰባው ላይ በውቅሮ ጦር ካምፕ ላይ በማግስቱ ወረራ ለማድረግ እንደተወሰነ ተነገረን። የወረራው ዕቅድ ቢፓርቲውና በአመራሩ ብዙ ጥናትና ቅንጅት ተደርጎ በጥንቃቄ መዘጋጀቱንና ወረራውም የሚካሄደው በሚቀጥለው ቀን እንዲሆን የተወሰነ መሆኑንም ስለሞን ገለጸልን።

ስለሞን በሰጠው ማብራሪያ መሠረት፣ በውቅሮ ካምፕ ሁለት መቶ ሰማንያ አምስት የታጠቁ ወታደሮች ነበሩ። ካምፑን ለማጥቃት አራት ኃይሎች እንደተመደቡ ገልጾ "አጠቃላይ ውጊያውን እንዲመራ የተመደበው ወርቂ ሲሆን የፖለቲካ ሐላፊ ደግሞ እኔ ነኝ" በማለት ራሱን አስተዋወቀ።





ስለጦርነቱ አጠቃላይ መረጃ ከተሰጠ በኋላ፣ የእያንዳንዳችን ምደባና ሐላፊነት ሲነገር፣ በመጀመሪያ ካምፑን በበምብና በቀላል መሣሪያ የሚያጠቃው ቡድን ዝርዝር፣ ቀጥሎ ደግሞ ከተማ የተመደቡ እንዲሁም ለጠላት ድጋፍ ሰጪ ኃይል እንዳይገባ መንገድ የሚዘጉ ክፍሎች ዝርዝር ተገለጸ።

የማጥቃቱ ዕቅድ የተነደፈው በአራት ቡድን በመከፋፈል በአራት አቅጣጫ ለመሰማራት ነበር። አንደኛው በየአቢኢዮ የሚመራ ቡድን ከከተማ ደጋፊ ኃይል እንዳይመጣ ለማገድ፣ ወደ ከተማው ወስጥ ገብቶ በከተማው ቁልፍ ዒላማዎችን በማጥቃት፣ እዚያ ያለው ኃይል በከተማው ችግር እንዲጠመድ በማድረግ እንዳይወጣ ባለበት የሚያስቀር ነበር። ሁለተኛው ቡድን ከመቀሌ አቅጣጫ ደጋፊ እንዳይመጣ ዘግቶ የሚከላከልና የሚያግድ ሲሆን፣ ሦስተኛው ቡድን ከአዲግራት ወደ ውቅሮ ረዳት እንዳይመጣ የሚያግድ በሲራጅ የሚመራ ቡድን ሆነ። አራተኛው ቡድን ግን በቀጥታ ወደ ካምፑ የሚገባና ዋናውን አላማ የሚፈጽም ነበር። የአጥቂው ቡድን እንዲገባ የታቀደው በሁለት አቅጣጫ ማለትም በደቡብና በምሥራቅ በኩል ሲ ሆ ን የደቡቡን አጥቂ ቡድን ሕብስቱ፣ በእደማሪያም ደግሞ የምስራቁን አጥቂ ቡድን እንዲመሩ ተመድበዋል።

በዚያ መሠረት ዋናውን ዒላማ የሚፈጽምና በቀጥታ ወደ ጦር ሰፈሩ ሄዶ ጦርነት ለሚከፍተው ቡድን በአዛዥነት የተመደበው የአየር ወለድ ጦር አባል የነበረውና የኃይል ሀያ ሰባት አዛዡ ሕብስቱ እንደሆነ ተነገረን። ወደ ከተማ የሚገባውን ቡድን የሚመራው ደግሞ የኛ ማለትም የኃይል አምስት መቶ አዛዥ የአቢኢዮ እንደሆነ፣ በተጨማሪ አንድ በድላይ የምትመራ ጋንታ በተወርዋሪነት ልትጠባበቅና የቆሰሉ አባላትን እንድታነሣና እንድታሸሽ ተመድባለች።

የአቢኢዮ በንዴት ፊቱ ተለዋውጦ ከተቀመጠበት ተነሣ። "የአቢኢዮ ፈሪ ነው፣ ያላችሁ ማነውና ነው ከተማ የተመደብኩት?! ከተማ መግባት ማለት እኮ የቀበሌ ቢሮዎችን መፈተሽና መዝገብ ማቃጠል ማለት ነው። እኔ ተወልጄ ያደግሁት ውቅሮ ከተማ ውስጥ ነው፤ የውቅሮን መውጫያና መግቢያው ከእኔ

የበለጠ የሚያውቅ ማንም የለም። ስለዚህ እኔ ወደጦር ሰፈሩ ከሚገባው ቡድን ጋር ነው መመደብ ያለብኝ እንጂ ሌላ ቦታ ሊሆን አይችልም!" በማለት ተቃውሞውን ገለጸና አኩርፎ ተቀመጠ።

የተወለደበትና ያደገበት ቦታ ስለሆነ አንድ አደጋ ቢያጋጥመው፣ ለቤተሰቦቹ፣ ለጓደኞቹም ሆነ ለሚያውቀው ሰው ሁሉ መጥፎ ሐዘን እንደሚሆንና ሌላም ጦስ ሊያስከትል እንደሚችል በመግለጽ፣ የተለያዩ ምክንያቶችን ዘርዝሮ ሰለሞን በተቻለ መጠን ሊያስረዳውና ሊያግባባው ሞከረ። የአቢኢዮ ግን አልቀበልም ብሎ ድርቅ አለ። ሰለሞን ነገሩን ለማብረድ ብሎ የአቢኢዮም ጊዜ ወስዶ ቢያስብበት ምናልባት ሐሳቡን ሊለውጥ ይችላል ብሎ ይመስላል ለትንሽ ጊዜ ለዕረፍት እንድንወጣና ስንመለስ ስብሰባው እንደሚቀጥል አስታውቆ እረፍት ሆነ።

ሁሉም በየፊናው ለዕረፍት በየቦታው ተሰማራ። እኔ፣ ድላይና ብርሃኑ ግን የአቢኢዮን በጣም ስለምንቀርበው ወደእርሱ ነበር የሄድነው። በስብሰባው ላይ ያነሳውን ሐሳብ እንዲለውጥ ለማደረግ እየተፈራረቅን ስናናግረውና ስንለምነው ቆየን። በተለይ እኔና ድላይ በእርሷ ጉዳይም ሆነ፣ ከዚያ በፊት ከእርሱ ጋር በነበረን ግንኙነት ለእርሱ የተለየ የፍቅር ስሜትና ቅርበት ስለነበረን፣ በጣም ለመንነው። የአቢኢዮ ግን ልመናችንን አልሰማም።

ብዙ ጊዜ ለብቻችን ስንሆን ስለእርሱ ጥሩነት እያነሣን አውርተናል። በተለይ እኔ ፈገግ ብሎ "ወዲ ሐፍተይ" ሲለኝ የሚሰማኝ ደስታ ልዩ ነበር። ከድላይ ጋር ነበለት ስንሄድም እንዴት እንደተጨነቀልንና የድላይ ችግር እንዴት እንደተሰማው አስታውሳለሁ። ስንሄድ ደግሞ እንዴት መጠንቀቅ እንዳለብን ሲመክረን የነበረውን እያነሣንም ብዙ ጊዜ አውርተናል።

ስለየአቢኢዮ አንዳንድ የሰማሁትና ያየሁትን እንዲሁም ቅድመ ታሪኩንም መለስ ብዬ ሳስበው ለወደደው ሟች እንደሆነ ተረድቻለሁ።



የአሲምባ ፍቅር

የየአቢኢዮ እውነተኛ ስም ታፈረ ተድላ ነበር፤ እናቱ የወለዱት ሁለት ልጆች ነው ፤ እርሱና እንዲት እኅቱ ማለት ነው። የአቢኢዮ እናቱንና እኅቱን በጣምይወዳቸዋል። የሚወደውን ሰው የሚያቆላምጠው "የእኅቴ ልጅ" በማለት ሲሆን ሲምል ደግሞ በእናቱ ነበር። የአቢኢዮ አንዴ የእናቱን ስም ጠርቶ "ከለላ ትሙት!" ካለ ያ ጉዳይ ያለቀለት ነው ማለት ነው። እኔም ታዲያ "ወዲ ሐፍተይ" ሲለኝ ደስ የሚለኝ ለእናቱና ለእኅቱ ያለውን ልዩ ፍቅር ስለማውቅ ነበር።

ሦስታችንም ለእርሱ ካለን ፍቅር የተነሣ ነበር ሀሳቡን ለማስቀየር የምንታገለው። "ወደ ካምፑ ከሚገባው ቡድን ጋር ካልተመደብኩ" ማለቱ ትክክል እንዳልሆነ፣ ለሕይወት በጣም የማያስጋውን የአመራሩን አመዳደብ እምቢ ብሎ እሳት ውስጥ ካልገባሁ ማለቱ፣ በእርሱም ላይ ሆነ ከቤተሰቡ ጋር በተያያዘ ሊከተል የሚችለውን ችግር እንዲያስበው በማድረግ ለማሳመን ሞከርን። አመራሩ የእርሱን ምደባ ከዋናው ውጊያ ወደራቀ ቦታ ያደረገው ሆን ብሎ እንደሆነ ሁላችንም እምነንበት ትክክለኛ ውሳኔነቱን ተቀብለናል። እርሱ ግን ምንም አልሰማ አለን። ብዙ ሞከርንና ስብሰባው ሊጀምር ሲቃረብ ተስፋ ቆርጠን ወደ ስብሰባው ተመልሰን ገባን። በተለይ ድላይ ድርቅ በማለቱ በጣም ነበር የተናደደችው። ወደ ስብሰባ ስንመለስ በጣም አዝና፣ ፊቷ ተቆጣጥሮና ተለዋውጦ ስሜቷ ይታወቅባት ነበር።

ስብሰባው እንደገና ሲጀመር እነሰሎሞንም የአቢኢዮን ሐሳብ ለማስለውጥ ሞክረው አልተሳካላቸውም። በመጨረሻ ውሳኔው ተቀይሮ ድልድሉ ተለወጠና የአቢኢዮና ሕብስቱ ወደካምፕ በሁለት አቅጣጫ የሚገቡትን ቡድኖች እንዲመሩ ተደረገ።

የአጥቂው ቡድን እንዲገባ የታቀደው በሁለት አቅጣጫ ማለትም በደቡብና በምሥራቅ በኩል መሆኑ እንደተጠበቀ ነው። የደቡቡን አጥቂ ቡድን ሕብስቱ፣ የአቢኢዮ ደግሞ የምስራቁን አጥቂ ቡድን እንዲመሩ ተመደቡ። የየአቢኢዮን የቀድሞ ምድብ ማለትም ወደ ከተማ የሚገባውን ቡድን ደግሞ የአየር ወለድ

ጦር አባልና የኃይል ሰልሳ ስድስቱ ምክትል መሪ በአደ ማሪያም እንዲተካው ተደረገ።

በስብሰባው ከነበርነው የጋንታ አመራሮች መካከል እኔ፣ ግደይ ጨዳርና ብርሃኑ ወደካምፑ ከሚገባው ቡድን ውስጥ ተመደብን። ድላይ ደግሞ ተወርዋሪ ቡድን ይዛ ድጋፍ ሰጪ ሆና ተመደበችና ስብሰባው ተጠናቀቀ። በማግስቱ ጠዋት ለየጋንታችን አባላት ማብራሪያ እንድንሰጥ ይጠበቅብናል። ከሰዓት በኋላ ደግሞ ወደውቅሮ ጉዞ ይጀመራል።

ስብሰባው ካበቃ በኋላ ለመተኛት ሁሉም ወዲያ ወዲህ ማለት ጀመረ። ቤት ውስጥ ያለነው የአመራር አባላት ብቻ ስለሆንን እንደፈለገን መተኛት እንችላለን። አስተኛኘታችን እንደተለመደው ሁለት - ሁለት ሰው እየሆንን ነበረ። ከስብሰባው አዳራሽ ውጪ ከብቶች የሚያድሩበት ቤት አለ። እኔ ከየአቢአዮና ከግደይ ጋር እያወራሁ ወደውጪ ስንወጣ ገና በሩን አለፍ እንዳልን፣ ድላይ ከኛ ቀድማ ወጥታ ኖሮ ሁሉም እየሰሙ "አማኑኤል፣ ቦታ ይዣለሁ! ና አብረን ነው የምንተኛው!" ብላ ጠራችኝና ሄደኩ።

የያዘችው ቦታ ከስበሰባው ክፍል በራፍ በስተምዕራብ በኩል ትንሽ ራቅ ብሎ በነበረው ጥግ ነበር። መኝታችንን አንጥፈን ከተኛን በኋላ፣ ወሬ ለማውራት ከኛ ትንሽ ራቅ ብለው የተኙ ጓዶች እንዳይሰሙን ለትንሽ ጊዜ በዝምታ መጠበቅ ያስፈልገናል። በአቅራቢያችን የነበሩት ጓዶች እንቅልፍ ወስዷቸዋል ብለን ስንገምት መነጋገር ጀመርን። ተደጋጋሚ ምሽቶችን በሥራ ማሳለፍና ድካም በሚደራረብብን ወቅት የመኝታ ጊዜው ሲገኝ ወዲያው እንቅልፍ ጭልጥ አርጎ ይወስደናል። ከድላይ ጋር ብቻችንን የመተኛት እድል ባገኘን ቁጥር ግን ድካሙቢኖርምየእንቅልፍ ጊዜያችንን እየቀነስን ስናወራ መቆየት ለምደብናል።

ቆየት እንዳልን ጠራችኝና እንዳልተኛሁ ስታረጋግጥ "የአቢአዮ እንደዚህ ድርቅ ያለ መሆኑን አላውቅም ነበረ። እሺ ብሎ የተመደበበትን ቦታ እንደመቀበል





እምቢ ብሎ ይከራከራል እንዴ?! እኔ መቼም በጣም ነው የገረመኝ። ይሄ የእብደት ነው እንጂ የጤና አይመስለኝም" ብላ ወሬ ጀመረች።

"እንግዲህ እኛ የቻልነውን ያህል ሞከረናል፤ ምንም ማድረግ አይቻልም" አልኳት።

"በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ጦርነት ውስጥ መግባት ጥሩ አይደለም። አማኑኤል! እኔ በበኩሌ የአሁኑ ጦርነት ነገር አላማረኝም" አለች።

"ሁላችንም እኮ ለመንነው፤ ግን እምቢ አለ ምን ማድረግ ይቻላል?" አልኳት ወሬውን ለማሳጠርና ለመተኛት ፈልጌ።

"እኔ እንጃ! በውስጤ ግን መጥፎ ነገር ተሰምቶኛል። ይኼ የውቅሮ ጦርነት ምንም ደስ አላለኝም፤ ብዙ እልቂት የሚያስከትል ይመስለኛል። በተለይ አንተና የአቢአዮ በሕይወት የምትመለሱ አይመስለኝም። ካንተም ጋር ዛሬ አብረን የምንተኛው ለመጨረሻ ጊዜ ይመስለኛል። በጣም ነው የፈራሁት!" አለችኝ።

"ተይ እንጂ ድላይ፤ ለምን እንደዚህ ትያለሽ? ልክ አይደለሽም። ደግሞስ ሁላችንም ትግል ውስጥ የገባነው ለመሠዋት አይደለም እንዴ?" ብዬ እንደመገሠጽም አድርጌ ላረጋጋት ሞከርኩ።

"እኔ እንጃ! ብቻ በተለይ እናንተ ጨበጣ እንድትገቡ ከተመደባችሁት፣ ማናችሁም የምትመለሱ አይመስለኝም። አንተም ራስህ አሁን ሬሳ-ሬሳ ነው የምትሸተኝ" ብላ በለሆሳስና በሚያሳዝን ዜማ ተናግራ ዝም አለች።

"እኔ እንደሆነ ብዙ ጊዜ እሳት ውስጥ ገብቼ የወጣሁ ነኝ። እናንተም እኮ እኛን ለመርዳት ስትመጡ በተኩስ ውስጥ ነው የምታልፉት። ሁላችንም አደጋ ሊገጥመን ይችላል። ጦርነት ላይ ደግሞ ለመሰዋት ተዘጋጅተን መሄድ አለብን። እኔ፣ አንቺ ወይ የአቢአዮም ሆነ ሌሎቻችንም ብንሠዋ፣ የቀረነው መቀበልና ትግሉን መቀጠል ብቻ ነው ያለብን። ይሄን አንቺም የምታውቂውና የኖርንበት እውነት ነው። ዝም ብለሽ ተጨነቂ ሲልሽ ነው እንጂ!" አልኳት።

"ሊሆን ይችላል። የእኛና የእናንተ ግን በጣም ይለያያል። እናንተ እኮ የጋለ እሳት ውስጥ ነው የምትገቡት!"

"ተይ እንጂ ድላይ በእናትሽ! አሁን ምን አዲስ ነገር መጣና ነው እንዲህ የሆንሽው? እኔ መቼም አንቺ በጀግንነት ወደ ውጊያ ስትገቢ ነው እንጂ ፈራሁ ስትዪ ገና ዛሬ መስማቴ ነው። ለማንኛውም ተልእኮ ስንሄድ መሠዋት ሊኖር እንደሚችል የታወቀ ነው። ደግሞም እኔም አንቺም የምናውቃቸው ብዙ የተሠው ጓዶች ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጥተው እንዳለፉ አይተናል። ሁላችንም ተራችን ከደረሰ ለመስዋዕትነት መዘጋጀት አለብን እንጂ፤ ለምን ይሄን የተለየ ነገር አድርገሽ ታይዋለሽ?" በማለት ብዬ ላረጋጋት ሞከርኩ።

"ይሄ መፍራት ወይም አለመፍራት አይደለም። አንዳንዴ ውስጥህ የሚነግርህ ነገር አለ። ብቻ የሆነ ነገር ይሰማኛል" አለችና እየደጋገመች አንተና የአቢኢዮ ... እያለች ስትደጋግም፤ ፍርሀቷ፣ አነጋገሯና የድምጿ ቅላጼ እያባባኝ ቀስ በቀስ ፍረሀት ሲወርረኝ ተሰማኝ።

እንዴ! ከድላይ ጋር የመጨረሻ መኙታችን ሊሆን ነው ማለት ነው? ብዬ አሰብኩ። ድንገት እቅፍ አደረግኳትና "አይዞሽ ድላይ፣ ምንም አንሆንም! በሕይወት እንመለሳለን! ድሉም የእኛ ይሆናል" ብዬ ከጀርባዋ በኩል ትከሻዋን ሳምኩት። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህን የተናገርኩት እርሷን ለማጽናናት ሳይሆን በያዘኝ ፍርሀት ምክንያት ይመስለኛል።

የዚያን ዕለት አስተዳደራችን ከሌላው ጊዜ የተለየ ሆነብን። እንተቃቀፍ እንጂ የሁለታችንም ሐሳብ ከጦርነቱ ጋር ስለነበረ ምንም የተለየ ስሜት ሊፈጠር አልቻለም።ከሚጠብቀን ተልእኳችን በቀር ሌላ ነገር በፍጹም አልተሰማንም።

በተለምዶ ማናችንም እንደነገ ጦርነት ልንሄድ ማታውኑ ስንጫወትና ስንሳሳቅ አምሽተን ነበር የምንተኛው። መሥዋዕትነቱን ተቀብለን ያለፍርሀት





ስለምንዘጋጅ ምንም አይሰማንም ነበር። ያን ቀን ግን ተለየብኝ። ፍቅር ይሆን ፍርሀት ያደረብኝን ስሜት ማወቅ ተሳነኝ።

ድላይ የተኛችው በግድግዳው በኩል ነበር፤ እኔ ከጀርባዋ በኩል ነኝ። የቀኝ እጄን በቀኝ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጌዋለሁ። ሌላ ጊዜ ወሬ ጨርሰን ስትተኛ ወዲያው ነበር እንቅልፍ የሚወስዳት። በዚያን ማታ ግን አሁንም አሁንም መገላበጥ አበዛች። እንቅልፍ እምቢ እንዳላት ገባኝ። እኔ ትንሽ ሸለብ አድርጎኝ ነበር፣ እየተገላበጠች ስታቃስት ያመማት መስሎኝ ቀና አልኩና "ምነው ድላይ አመመሽ እንዴ?" ብዬ ጠየቅኳት።

"አይ አላመመኝም፣ ደኅና ነኝ። ብቻ የየአቢኢዮና የአንተ ነገር እያሳሳበኝ ነው" በስንት መከራ ያስተውኳትን ርእስ እንደገና አነሣችው።

"አንቺ እኮ ልክ ትናንትና ወደ ትግል እንደገባና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደውጊያ እንደሚሄድ ሰው ነው የሆንሽው። ደግሞም እርግጠኛ ነኝ በመጀመሪያ የውጊያ ውሎሽም ፍርሀት ያልነበረብሽ ቆራጥ ተዋጊ ነበርሽ። ዛሬ ግን ምን እንደነካሽ አልገባኝም። በቃ ተይው፣ ምንም ነገር አንሆንም አንቺም እኮ ያለንበት ቦታ ድረስ ትመጪልናለሽ። በዛሬው ዕለት እንለያያለን ብለሽ ተስፋ መቁረጥ የለብሽም" አልኳት። የእርሷም የጭንቀቷ መነሻ፣ ምናልባት የጀመርነውና ስር እየሰደደ የሄደው የፍቅር ግንኙነታችን ውጤት እንጂ ሌላ አልመሰለኝም።

"ለእናንተ ፈራሁላችሁ ስልህ እኮ ለራሴም ብቻዬን እንዳልቀር ፈርቼ ነው"

" የአቢኢዮም፣ እኔም አንቺም ብትሆኚ ለዓላማችን እስከ መሥዋዕትነት ለመታገል ቃለ መሀላ አድርገን የገባንበት ጉዳይ ነው። ከተሠዋንም የቀሩት ጓዶች የኛን ዓላማ ይዘው የክብር ሞት እስከሚሞቱ በመታገል ይቀጥላሉ" አልኳት ባለመታከት።

"እሺ ግን አማኑኤል" አለችና ወይ እስከላት ንግግሯን አቋማ ጠበቀችኝ።

"አቤት!" መለስኩላት ምን ልትለኝ እንደነበር ለመገመት እየሞከርኩ።

"አንተ አንድ ነገር ከሆንክ ግን እኔ እንዴት እሆናለሁ?" አለች። አባባሏ አስደነገጠኝ። ብደነግጥም ግን ምንም የተለየ ስሜት እንዳልተሰማኝ ለመሆን እየሞከርኩ "እዚህ ያሉት ሁሉ ጓዶችሽ አይደሉም እንዴ? ከእነርሱ ጋር ትሆኛለሽ። ሁላችንም ለአንድ ዓላማ የቆምን፤ በዓላማ የተሳሰርን አይደለንም እንዴ? ከእኔስ የተዋወቅነው በዚህ ትግል አይደለም እንዴ? ቅርርባችንም እኮ የአጋጣሚ ነገር ነው። እዚህ ያሉት ሁሉ የበለጠ የምትቀራረቢበት አጋጣሚና ምክንያት እስኪደርስ ነው እንጂ፣ አብዛኞቹ እንደእኔ ከእኔም የበለጠ የሚሆኑልሽ እውነተኞች ናቸው"አልኳት።

"እንደአንተ ለእኔ ጉዳይ የሚንገላታ። የወር አበባዬ ላይ ሆኜ፣ ጠረኔ ሳይሰማው አብሮኝ የሚተኛ ንጹሕ፣ ለሰው አሳቢ የትም የሚገኝ እንዳይመስልህ። እኔ አንተን አጥቼ፣ ከሌላ ወንድ ጋር ነጻ ሆኜ መኖር የምችል አይመስለኝም። ፈራሁ ስልህ ለአናንተ ብቻ አይደለም፤ ለእራሴም ነው የፈራሁት። እርግጥ እኔ እራሴ ብሞት ግድ የለኝም። አንተን አጥቼ መኖር ግን ያስፈራኛል። ሁሉም ነገር ጨለማ እየሆነብኝ ነው የጨነቀኝ"

"አየሽ ያ የፈራነው ነገር እየደረሰ ነው። ፍቅር ውስጥ መግባታችን ከመሥዋዕትነት እንድንሸሽ ሊያደርገን ነው፣ ፈሪ እያደረገን ነው ማለት ነው" ስላት ዝም አለች። ምናልባት ሐሳብ ውስጥ ገብታ ይሁን በፍቅራችን ጥያቄ ላይ ስለመጣሁባት አላውቅም፣ ብቻ ዝም አለች።

እኔም አጋጣሚውን በመጠቀም "ቢቃ አሁን ትንሽ እንተኛ"ብዬ ነጠላውን ተከናነብኩና ተኛሁ። እርሷም ለመተኛት የምታደርገው ሙከራ ይታወቀኛል። እንቅልፍ ይውሰዳት አይወሰዳት አላውቅኩም። እኔ ግን ጋንታ መሪና ምክትል ጋንታ መሪዎች የሚያበራ ሰዓት ስለሚሰጠን በየመሐሉ ሰዓት እየተመለከትኩ





የጊዜው መድረስ አለመድረሱን እከታተላለሁ። እርሷም በተነሣሁ ቁጥር "ሰዓቱ ደረሰ?" እያለች እንደጠየቀችኝ ነጋ።

***

በማግስቱ ጥር 15 ቀን 1970 ዓ.ም. የአራቱም ኃይል አባላት በሙሉ አንድ ላይ ምሳ በላንና እዚያው ዋልን። ለጦርነት ወይም ለረዥም ጉዞ ስንዘጋጅ ሁልጊዜም እንደሚደረገው፣ በደንብ እንድንመገብ ለእያንዳንዱ ጋንታ ፍየሎች ተገዝተው ተሰጥተውናል። አጋጣሚ ሆኖ በዚያን ቀን የአቢኢዮ የዋለው ከእኛ ጋንታ ጋር ነበር። ከሌሎች የኃይል አመራሮች ጋር የሚገናኝበትን የመገናኛ ሬድዮ ከፊቱ አስቀምጦ እየተጫወተ ነው። ትኩር በዬ ሳየው ድላይ ማታ የተናገረችው ትዝ ብሎኝ ትካዜ ተሰማኝ። እርሱም ፊቴን አንብቦ ነው መሰለኝ "አይዞህ አማኑኤል፣ ዛሬ ማታ ውቅሮ ያለውን ጦር እንደመስሰዋለን፣ ድሉ የኛ ነው። እግረ መንገዳችንንም ከለላን ሰላም ብለናት እንመጣለን" እያለ እየሳቀ አወራኝ (ወይዘሮ ከለላ እናቱ ናቸው) ጥርሶቹ ነጫጭና የሚያምሩ ናቸው። በጥቁር መልኩ ላይ የጥርሶቹ ንጣት በጣም ይደምቃል።

ከየአቢኢዮ ጋር ያለን ትውውቅ ከመጀመሪያው ከሰንገዴ ሥልጠና አንስቶ ነው። ዘወትር ፈገግታ ስለማይለየው፣ ብዙ ጊዜ ሲስቅ አይቼዋለሁ። የዚያን ዕለት አሳሳቁ ግን በጣም የተለየ መሰለኝ። ።

ድላይ ማታ የተናገረችው እየረበሸኝ ስለነበረ የእርሱ ንግግር ስሜቴን አልቀየረውም። በተለይ የአቢኢዮ ወደ ጦር ሰፈር መድቡኝ ብሎ መግባቱ ደስ እንዳላሰኛት ደጋግማ የነገረችኝ አእምሮየ ውስጥ እያስተጋባ አሰቸገረኝ። "ካሁን በኋላ ሁለታችሁንም በሕይወት የማያችሁ አይመስለኝም" እያለችና እኔንም ሬሳ ሬሳ ትሸተኛለህ እንዳለች ነበር ያደረችው። የአቢኢዮን በጣምስለምትወደው በአንድ ቀን በጣም የምትወዳቸውን ሁለት ጓዶቿ እንዳታጣ ፈርታለች። አሁንም የአቢኢዮ እንደገና "ምነው አማኑኤል?! ዛሬ ልክ አይደለህም ተከዘሀል። እንደማትመለስ አውቀሀል መሰለኝ?" አለኝ። አሁንም ያንን የማይለየውን ፈገግታውን በግማሹ እያሳየኝ።





"የለም የአቢኢዮ ትንሽ ደክሞኝ ነው። ሌሊት ስብሰባ ነው ያደርኩት። ዛሬ ደግሞ ተረኛ መጋቢዎች ስለሆንን ድካም ተጫጭኖኝ ነው እንጂ ሌላ አይደለም" ብዬ ለመሸፋፈን ሞከርኩ።

ወደ ማምሻው ላይ የአራቱም ኃይሎች አባላት፣ በአንድ ላይ ተሰበሰብን። ጥይት ወደ ካዝና ለመሙላት ጊዜ ስለማይኖር ለእያንዳንዳችን ጥይት የተሞሉ ስድስት ካርታዎችና ሁለት ሁለት ቦንብ ተሰጥቶናል። (አንድ ካርታ ሰላሳ ጥይት ነው የሚይዘው።)

ሰሎሞንና ወርቁ አጠር ያለ ገለጻ አደረጉልን። ቀጥሎም የየምድቡ ወታደራዊ መሪዎች ድልድላችንን ለመግለጽ መጀመሪያ ሕብስቱ ስም ሊጠራ ወረቀት ይዞ ቆመ። አብዛኞቻችን በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚ ካልሆነ በስተቀር ለመገናኘት ስለማንችል በዚያ አጋጣሚ የተገናኘንና የምንተዋወቅ ጓዶች እርስ በእርስ መነጋገር ጀመርን። ለረዥም ጊዜ ተገናኝተን የማናውቅ ደጋግመን እየተቃቀፍን ስንሳሳምና ሰላም ስንባባል ጫጫታ ተፈጠረና ሁካታ ሆነ። በዚህ ጊዜ ሰሎሞን ተነሣና "ጓዶች!! እባካችሁ ምድብ ምድባችሁ ሲነገር ስለሆነ ጫጫታውን አቁሙና ስማችሁን አዳምጡ! "Remember we are at a war zone!" (ያለነው በጦር ቀጠና ውስጥ መሆኑን አስቡ!) ሲል ሁሉም ጸጥ አለ።

ጸጥታው እስኪመለስ ወረቀት እንደያዘ ይጠብቅ የነበረው ሕብስቱም ስም ዝርዝራችንን ማንበብ ጀምረ። በመጀመሪያ የኔ ስም ተጠራ። ብድግ ብዬ ሄድኩና ከበስተጀርባው ቆምኩ።ከእኔ ቀጥሎ ስማቸው የተጠሩት በሙሉ እየመጡ ከሕብስቱ ኋላ ተሰበሰብን። ከእኔ ጋንታ ውስጥ ወደ ካምፕ ጨበጣ ከሚገባው ቡድን ጋር የተመደበው አንዶም ብቻ ነው።

የተሰበሰብንበት ቦታ እንደቆምኩ፣ ረድኢይ መጣና ጠራኝ። ረድኢይ የኃይል ስልሣ ስድስት የፖለቲካ ሐላፊ ነበር። ኃይል ስልሳ ስድስት ደግሞ በውቅሮ አካባቢ የምትንቀሳቀስ ኃይል ነበረች። ወደ ረድኢይ ስሄድ "ምድብህን አውቀኸዋል?" ብሎ ጠየቀኝ።

"አዎ ምነው?" አልኩት።

"በል ቀስ ብለህ ተከተለኝ" አለኝ።

ተከትዬው ስሄድ ወደፊት ቀደም አለኝና ፍሱሕ ገብራይንም ጠራው። ሁለታችንን ነጥሎ ወስዶ "አስቀድመን የምንሄድበት ቦታ ስላለ አሁን እንነሣለን፤ ሠራዊቱም እኛን ተከትሎ ይመጣል" ሲል በአብሪነት የተመደቡትን ለብቻቸው ከፊት ተሰልፈው በማየታችን፤ እኔና ፍሱሕ ግራ ተጋባን። ረድኢይ ግራ እንደገባን አውቆ "እኛ አብሪዎች አይደለንም። ነገር ግን ቀድመን ወደውቅሮ የምንሄድበት ጉዳይ አለ" አለን።

እኔም ከመሄዴ በፊት ድላይን ፈቷን እንኳ አይቼ ብሄድ ተመኘቼ ወደ ኋላ ዞሬ በዓይኔ ፈለግኳት። ግን አላገኘኋትም። ምንም አማራጭ ስለአልነበረኝ ረድኢይና ፍሱሕን ተከትዬ መንገዴን ቀጠልኩ።

ረድኢይና ፍሱሕ የኃይል ስልሣ ስድስት አባላት ስለሆኑ ሁለቱም መንገዱን በደንብ ያውቁታል። ፍሱሕ ከፊት ረድኢይ ከመሐል እኔ ከኋላ ሁኜ ለስምንት ሰአታት ያለማቋረጥ ከተጓዝን በኋላ እኩለ ለሊት አካባቢ፡ ከውቅሮ ከተማ በስተሰሜን ምስራቅ በኩል ያለው ተራራ ላይ ደረስን። የከተማው መብራት ይታየናል።

ረድኢይ "እዚህ መረጃ የሚሰጡን ጓዶች ይጠብቁናል። ከእነርሱ መረጃውን ወስደን ስንመለስ፤ ሌሎቹን ጓ ዶ ች ወደዚህ እየመጡ ስለምናገኛቸው እናንተም ወደየምድባችሁ ትመለሳላችሁ" አለን።

ኃይል ስልሳ ስድስት በወቅቱ የምትንቀሳቀሰው በውቅሮ አካባቢ ስለሆነ ከውቅሮ የድርጅቱ የከተማ መዋቅር ጋር የሚገናኘው ረድኢይ እንደነበረ እገምታለሁ። የነበርንበት ተራራ ስር አንድ ትልቅ ዋርካ አለ። እርሱን ተከትለን ዋርካው ጋ ስንደርስ ዋርካው ላይ ከነበሩ ሁለት ሰዎች ጋር





የምስጢር ቃል ተነጋገሩ። ትክክል መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ሁለት የከተማ ሰዎች ወረዱና መነጋገር ጀመሩ። እኔና ፍሱሕ ከረድኢይ አጠገብ ቆመናል።

"ምን አዲስ መረጃ አላችሁ?"ብሎ ጠየቃቸው ረድኢይ።

"በእኛ መረጃ መሠረት ደርግ ጥቃት ለማድረስ እንደምትመጡ ሰምቷል። ስለዚህ ከአሥራ ሁለት ሰዓት በኋላ ከተማ ውስጥ ያለው ወታደር በሙሉ ወደ ካምፕ እንዲገባ ታዟል።በካምፑም ዙሪያ ምሽግ ተቆፍሯል። ከዚህም በተጨማሪ ከአዲግራት ረዳት ኃይል መጥቷል እናም በደንብ ተዘጋጅተው እየጠበቋችሁ ነው። እኛ ያገኘነው መረጃ ይኸው ነው። ከዚህ በኋላ ያለው ውሳኔ የእናንተ ጉዳይ ነው" ብሎ አንደኛው ነገረውና ከጓደኛው ጋር ሄዱ። ከእነዚያ ሰዎች አንደኛውን ሌሊት ተመልሰን ጋራውን ስንወጣ አየሁት። ስለዚህ ሁለቱም ተመልሰው ከኛ ጋ ተቀላቅለዋል ብየ አሰብኩ።

በሰማነው መረጃ እኔና ፍሱሕ ግራ ገብቶን ተያየን። ረድኢይምሁኔታችን ገብቶት ወደ እኛ ዞር ብሎ "ይህ ተልእኮ የፓርቲውና የሠራዊቱ አመራሮች የወሰኑት ስለሆነ፤ በእኛ ሥልጣን ልንሽረው የምንችለው አይደለም። ስለዚህ የፈለገው ቢሆን መፈጸም አለበት። የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት ከፍለንም ቢሆን መግባት አለብን። ስለዚህ አሁን የሰማችሁት ሚስጥር ስለሆነ ለማንም ሰው መናገር የለባችሁም!" አለን። መቼም ድርጅታዊ ምስጢር ነው ብለን "እሺ" ብንልም እኔም ፍሱሕም ደስ አላለንም። ነገር ግን ከመታዘዝ ውጪ፤በኛ አቅም ምንም የምናደርገው ነገር ስለሌለ "አይዞህ! አይዞህ!" ተባብለን ተቃቀፍንና እርስ በእርሳችን ለመበረታታት ሞከርን። ስንመለስ እኔ ድላይ የተናገረችው ነገር በሐሳቤ እየመጣ አስጨነቀኝ። "ያለችው እውነት ሊሆን ነው?" እያለኩ አሰላስላለሁ፤ ምክንያቱም ጠላት ቀድሞ ተዘጋጅቶ እየጠበቀን የግድ መፈጸም አለበት በመባሉ አደጋው ከፍተኛ እንደሚሆን ተሰምቶኛል።

ብዙም ርቀን ሳንሄድ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሠራዊቱ ጋር ተገናኘንና ሦስታችንም ወደየምድባችን ገባን። እኔና ፍሱሕ ምድባችን በሕብሰቱ ከሚመራው

ዋናው አጥቂ ቡድን ውስጥ በመሆኑ አንድ ላይ ነው የገባነው። ዞር ብዬ ረድአይን ሳየው ከሆኑ ሰዎች ጋር ይነጋገራል። ማንነታቸውን ግን ለመለየት አልቻልኩም፤ ለአመራሩ ወይም ለዚያ ጦርነት ዋና መሪ ለወርቁ መንገርና ያለመንገሩን አላወቅሁም። ፍሱሕ ገብራይ ዛሬም በሕይወት አለ፤ ከአመራሩ ብዙዎቹ ዛሬም በሕይወት መኖራቸውን አውቃለሁ። ረድአይን ግን ከዚያ ጊዜ በኋላ አግኝቼው አላውቅም።

***





**የአደገኛው ትልዕኮ ፍጻሜ**

ወደካምፑ ከሚገቡት ሁለት ቡድኖች አንዱ በሕብስቱ **የሚመራው እኔ** የነበርኩበት ቡድን የመጀመሪያውን ተኩስ መክፈት ነበረበት። ጋራውን ተከትለን ከጦር ሰፈሩ በስተደቡብ በኩል አሸምቀን ወደ ካምፑ መጠጋት ጀመርን። በተሰጠን መመሪያ መሰረት የካምፑ ዘቦች አጥሩ ዙሪያ ባሉ የጥበቃ ቦታዎች እንደሚገኙ አውቀናል። ዕቅዳችን ወደ አጥሩ ተጠግተን በንቦች ወደውስጥ እንድንወረውርና አከታትለን በቀላል መሣሪያ ማጥቃት ነበር።

በየአቢኢዮ የሚመራው ቡድን ከካምፑ በቀኝ በኩል ይገባል። ከካምፑ በስተጀርባ በሚገኘው ጣሊያን በሠራው ግንብ ላይ ወጥተው በመትረየሶች ሽፋን የሚሰጡን የተወሰኑ መትረየስ ተኳሾች በሁለት በኩል ተመድበዋል።

ወደ ጦር ካምፑ ለመጠጋት ዳገቱን ወጥተን ስንጨርስ ግን ከካምፕ ውጪ ሆኖ ወዲያና ወዲህ እያለ የሚጠብቅ አንድ ዘብ ተመለከትን። በነበርንበት ቦታ ተኛንና ለመተኮስ የሕብስቱን ትእዛዝ መጠባበቅ ያዝን፤ " ትንሽ እንጠጋ አሁን አትተኩሱ" አለን ሕብስቱ። ትንሽ ተጠጋን። በካምፑ መግቢያ ላይ ደግሞ ሌላ ጠባቂ እንዳለ አየን። ከዚያ በላይ ከተጠጋን ልንታይ እንችላለን በሚል በከፍተኛ ጥንቃቄ ነበር ጥቂት በጥቂት የምንጠጋው። ሕብስቱ የእጅ ቦንብ መወርወር እስከምንችልበት ርቀት ድረስ በጥንቃቄ እንድንጠጋ ነገረን።

በሌላ ጊዜ ዋርድያ የሚቆመው ካምፕ ውስጥ አጥር ላይ ባለ የጥበቃ ማማ ላይ ነበር። በ ዚ ያን ዕለት ግን መምጣታችንን ስላወቁ ይመስላል ጥበቃው ወጥቶ ነበር የሚጠብቀው። ዋርካው ጋር ያገኘናቸው ሰዎች እውነታቸውን ነበር አልኩ በልቤ።

እንዳደፈጥን ወደ ዋርዲያው ትንሽ ጠጋ ብለናል "እንምታው?" በማለት በሹክሹክታ ጠየቅሁት።

"የለም የለም አትምቱት! ዝም ብላችሁ ተጠጉ፣ የእጁ ቦንብ ለመወርወር እንድንችል ትንሽ እንቅረብ" አለ ሕብስቱ።

እኛ ከአሁን አሁን ሊያየን ይችላል በሚል ልንቀድመው ነው የፈለግነው። ቢሆንም ሕብስቱ በፈለገው ርቀት ለመቅረብ ተዳርሰናል። ነገር ግን የቀረችንን ርቀት ለመጠጋት ስንሞክር ዘቡ አየን። ልክ እንዳየን በድንጋጤ እየጮኸ ወደ ኋላ በሩጫ ተመለሰ። እኛም እየሮጥን ተከተልነው፤ ልንደረስበት ስንል ግን እነርሱ ቀድመው ተኩስ ከፈቱብን።

በመትረየሶች የለቀቁብን የተኩስ ዝናብ በአንድ ጊዜ አካባቢውን አናወጠው። የኃይል ሀያ ሰባት መትረየስ ተኳሾች ከበስተጀርባችን ሽፋን እየሰጡን ነበር። አጠገባችን የተከመሩ ድንጋዮችና የእንጨት ግድግዳ ያላቸው ጎጆዎች ስለነበሩ እኔና ሮምሀ በአንዱ ጎጆ ተከለልን። ጎጆው የእነርሱ ዘብ ይጠብቅበት የነበረው ቦታ መሆኑ ነው። ያለነው ከእነሕብስቱና ከነየአቢኢዮ መካከል ነበር። የሚተኮስብን ተኩስ በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ በፍጹም መንቀሳቀስ አልቻልንም። ከእኛ በስተጀርባ አር.ፒ.ጂ እና መትረየስ የያዙ ጓዶች ምሽግ ይዘዋል። አር.ፒ.ጂውን የያዘው ብርሃነ ነበር። መትረየስ ተኳሹ በተቻለው መጠን ሽፋን መስጠቱን ቀጥሏል።

በሁሉም አቅጣጫ ተኩስ ተከፍቷል። ከእነ የአቢኢዮ ጋር የተመደበው መትረየስ ተኳሽ ቢራራ ከፊት የሚተኮስበት የወታደሮቹ መትረየስና ከባድ መሣሪያ በጣም ስለአየለበት ምንም ለማድረግ አልቻለም። እኛ ከለላ ያደረግነውን ጎጆ በባዙቃ ሳቱት። ከእኛ በታች ያሉት ሕብስቱና ጌታሁን የተከለሉበት ቤት በባዙቃ ተመትቶ መንደድ ጀምሯል።

በዚህ መሀል አንድ ጓድ ጎንበስ ብሎ በአጠገባችን ውልብ ሲል አየሁ። ለምን እንደሆነና ወዴት እንደሚሄድ አሰብ አድርጌ ገርሞኛል፤ ነገር ግን የጦፈ ውጊያ ውስጥ ስለገባን ፋታ አላገኘሁም። ወዲያው ደግሞ ወታደሮቹ "ወደ ማን ላይ ነው የምትተኩሰው?" ሲባባሉ ተሰማኝ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደግሞ የካምፑን በር ከፈቱና "ጎትተህ አስገባው! ጎትተህ አስገባው!" ሲባባሉ ሰማሁ።





ነገር ግን የሚናገሩትም ሆነ የሚያደርጉት ነገር አልገባኝም። **ምናልባት ተመትቶ** የወደቀ የእነርሱ ሰው እንዳለ ነበር የገመትኩት። በበሩ ለወጡት **የሽፋን ተኩስ** ለመስጠት ፈልገው ነው መሰለኝ ኃይለኛ ተኩስ አከታተሉ።

እኔና ሮምሀ በቀኝና በግራ በኩል ሆነን ስንታኮስበት የነበረ ጎጆ ቤት በብዙ ጥይቶች ተመታ። የተደገፍኩበት እንጨት በጥይት ተመትቶ ሲሰነጠቅ እኔ የተመታሁ መስሎኝ "ተመትቻለሁ" አልኩት ለሮምሀ፡፡

"ምንህን ነው የተመታኸው?" አለኝ።

እልፍ ብዬ በጨረቃ ሳይ ያለመመታቴን አወቅሁ እና "እንጨቱ ሲመታ የተመታሁ መስሎኝ ነው እንጂ አልተመታሁም አይዞህ" አልኩት

ከነበርንበት ቦታ ወደ ፊት ለመግፋት ብናስብም ለመንቀሳቀስ ስላልቻልን የግድ ቦታ ቀይረን የተሻለ ምሽግ መያዝ ነበረብን። በጎናችን በኩል በነበሩት የተከመሩ ድንጋዮች ጀርባ መሽገንለመታኮስ ወሰንን።

"መጀመሪያ እኔ ልሂድና አንተ ሽፋን ስጠኝ" አልኩት።

ሮምሀ ግን "ቦታው ለእኔ ስለሚቀርብ፣ መጀመሪያ እኔ እሄዳለሁ አንተ ሽፋን ስጠኝ" አለና ለመሄድ ተዘጋጀ። እሺ ብዬ ሽፋን ሰጠሁት። ድንጋይ ጀርባ መሽጎ እኔ ወደ እርሱ ልሄድ ስዘጋጅ ሽፋን ሊሰጠኝ ቀና ብሎ ሲተኩስ ወደ አፉ አካባቢ ተመታና "እ!!" ብሎ አንዴ ብቻ ድምፅ አሰምቶ ወደቀ። (ሮምሀ እውነተኛ ስሙ ሀድጉ ለማ ነበር)" ሮምሀ! ሮምሀ!" እያልኩ ደርሼ ሳየው ሕይወቱ አልፋለች። እኔ በግራ በኩል ሆኜ የእርሱ ሬሳ በቀኜ ወድቆ የሚዘንብብኝን ተኩስ ለማሳለፍ ጎንበስ ብዬ አጠብቃለሁ። መሞቱን ልቤ መቀበል አልቻአለም፤ እየተኮስኩ በየመሃሉ በእጄ እየነቀነቅኩት "ሮምሀ! ሮምሀ!" እላለሁ እርሱ ግን አይመልስልኝም። ወዲያውኑ ነበር የተሠዋው።

የሚዘንብብኝን ተኩስ ለማሳለፍ ጎንበስ ብዬ ስጠብቅ ብርሃነ የያዘውን አር.ፒ.ጂ. አነጣጥሮ ሲተኩስ ሳተ። ለሁለተኛ ጊዜ አነጣጥሮ ሲተኩስ ደግሞ ግንቡን መታው። አር.ፒ.ጂ. ከባድ መሣሪያ ስለሆነ ግንቡን ሲመታው ደንግጠው

ለትንሽ ጊዜ ተኩሳቸውን አቆሙ። ብርሃነ የተሰጠው አራት የአር.ፒ.ጂ. ጥይት ሲሆን የምትጠቀምበት ሁለቱን ጥይት ብቻ ነው ተብሏል፤ እናም ከሁለተኛው በኋላ አልተኮሰም። ስለዚህ አር.ፒ.ጂ.ውን ለረዳቱ ሰጥቶ የሮምሀን ክላሽ አንስቶ መታኮስ ጀመረ።

መኮንንን ጠራሁና እርዳታ እንዲሰጡን ወደ ኋላ ተመልሶ ለእነድላይና ለእነወርቁ እንዲነግር ላከሁት። ከእርሱ ጋር የነበረው ሀጎስ ማንጁስ አብሮኝ መከላከል ጀመረ። ሀጎስ ማንጁስ የአዲግራት ልጅ ነው። በጣም ጎበዝ ተዋጊ ሲሆን፣ በእኔ ቦታ ኃይል አምስት መቶ ተመድቦ ከሌላ ኃይል የመጣው የውቅሮን ካምፕ ለማጥቃት ስንዘጋጅ ነበር። ከእኔም ጋር የተገናኘነው ያን ቀን ነው። በመጨረሻ ወደ በጌምድር ተመድቦ ሄዶ ድብ ባሕር ላይ ተሰዋ።

ካምፕ ውስጥ ያሉት ወታደሮች ከካምፑ ወጥተው ለማጥቃት መሞከር ጀመሩ። በነበርንበት ቦታ ሆነን በጣም ስለተኮስንባቸው መውጣት አቃታቸው። የመኮንን መልእክት ምላሽ ስለዘገየብን ሌላ ሰው እንደገና ወደ እነወርቁ ላከን።

አር.ፒ.ጂውን ልንጠቀምበት ስለማንችል፣ ብርሃነ ወደ ኋላ ይዞት ሄደ። አንዶም ደግሞ ከእኛ በስተግራ ወደነበሩት ወ ደ እነግደይ ጨዳር ጋ ሊሄድ ሲል እንገቱን በጥይት ተመታና ወደቀ፣ ግን አልሞተም። ጌታሁን የግራ እጁን በከባድ መሣሪያ ጥይት ተመትቶ እጁ ተንጠልጥሎ ሊወድቅ ምንም አልቀረውም። በዚህ ተኩስ መካከል ከመግቢያው አጥር ላይ መትረየስ የሚተኩሰው ወታደር ምንም አላንቀሳቅስ አለንና በጣም አስቸገረን። እኛ በዚህም በዚያም ብንል ምንም ልናደርግ አልቻልንም።

እነ ሕብስቱ የተከለሉበት ቤት በባዙቃ ተመትቶ እንደተቃጠለ፣ ሕብስቱን ከቃጠሎው ቦታ ወደፊት ሲሄድ አይቼዋለሁ፤ ነገር ግን በዚያው እንደሄደ ቀርቷል። አብረውት የነበሩት ጌታሁንና አንዶም ተመትተው ቆሰለዋል። ግደይ ጨዳርና





ፍሱሕ የቆሰሉትንና ራሳቸውን እየተከላከሉ እየተታኮሱ ናቸው። ብርሃነ የሮምሀን ክላሽ ይዞ ሊረዳቸው ወደ እነርሱ ሄደ።

የተሙቱና የተሠውትን ለማውጣት እነድላይን እንዲጠራ የተላከው ጓድ "አልቀዋል" ብሎ ሳያስደነግጣቸው አልቀረም መሰለኝ፣ እነድላይ ከበስተኋላችን ኃይለኛ ተኩስ እየተኮሱ መጡ። ተኩሱ ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ እኛ እንኳ ቀና ለማለት ሳንችል እንዳጎነበስን ነበር አጠገባችን የደረሱት። ድላይ እየበረረች ወደእኔ መጣችና "አንተ ደኅና ነህ? ተርፈሀል? ምንም አልሆንክም?" ብላ ጠየቀችኝ።

"እኔ ደኅና ነኝ። ሮምሀን፣ ጌታሁንንና አንዳንድ የቆሰሉ ጓዶችን እንድናወጣ ነው ያስጠራሁሽ" አልኳትና እኔ የሮምሀን አሬሳ ተሸክሜ ለመሄድ ተነሣሁ። ሮምሀ ስሸከመው በአፍና በአፍንጫው ብዙ ደም ፈሰሰውና ከጸጉር እስከእግሬ ደም በደም ሆንኩ። ተሸክሜው ትንሽ እንደሄድኩ ብርሐነ አየኝና ተቀበለኝ።

የሮምሀን አስከሬን ለብርነአ እንደሰጠሁ ቢራራን አየሁትና ወደ እርሱ ሄድኩ። ትንሽ ቆይቶ በአጠጋባችን ውልብ ብሎ ያለፈው ሕብስቱ እንደነበረ ሰማሁ። ሕብስቱ በስር በኩል አጎንብሶ ወደፊት ሄዶ በሃምሳ ካሊበር እየተኮሰ አላፈናፍን ያለንን ወታደር ባለበት ቦታ ላይ ወጥቶ ዘረረው፡ ከዚያም የሃምሳ ካሊበሩን ወደእነርሱ አዙሮ ሊተኩስ ሲል ተመትቶ ከአጥሩ ስር በሩ አጠገብ እንደወደቀ ሰማሁ። ቀደም ብሎ ሲነጋገሩ የሰማኋቸው ቃላት ትርጉማቸው ገባኝ። ጎትተው ያስገቡት የሕብስቱን አስከሬን ነበር ማለት ነው።

ከእኔና ከቢራራ ፊት ሁለት ጓዶች አንድ አስከሬን በቃሬዛ ይዘው እያለፉ ነው። ቢራራም "አማኑኤል.." አለኝና "ይሄ በቃሬዛ የሚሄደው የማን አስከሬን እንደሆን ታውቃለህ?" አለኝ፤ በጣም አዝኗል።

አልመለስኩለትም፤ የአቢኢዮና ቢራራ አንድ ቡድን ውስጥ እንደነበሩ ትዝ አለኝ፤ ምን እያለን እንደነበረ ተረድቻለሁ፣ ሰውነቴ የባሰውን ሲግል ተሰማኝ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ደረሰ። ግን በተቻለኝ መጠን የሆነውን ላለማመንና ከራሴ ጋር

ለመታገል ፈለግሁ። ጠጋ ብዬ "ቢራራ! የአብኢዮ ነው?" ብዬ ጠየቅኩት፤ "አይደለም" የሚል መልስ እንዲሰጠኝ አምላኬን እየተማጸንኩ ነበረ።

ዝቅ በላ ድምፅና፣ ጉትት ባለ አነጋገር "ኢ.ኢ.ዎ.ዎ" አለኝ። የፈራሁትን ቃል ስሰማ ጀርዬ ስር እንደፈነዳ የቦንብ ድምፅ ጭንቅላቴን በጠበጠው። በቆምኩበት ቦታ ራሴን ይገፍ ቁጭ አልኩና ድንዝዝ ብዬ ለአፍታ ቆየሁ። ቀስ እያሉ እምባዎቼ ዱብ ዱብ አሉ፣ በተቀመጥኩበት አንገቴን ወደ መሬት ደፍቼ አለቀስኩ። ቢራራ እንደነገረኝ የአቢኢዮ ሁለት የእጅ ቦንብ ወርውሮ ከባድ ጉዳት አድርሶባቸው ለሶስተኛ ጊዜ ለመወረውር ሲሄድ ነበር የተመታው።

እንባዬን እንደምንም ገትቼ ቀና ስል ድላይና ፍሱሕ፣ ጌታሁንንና እንዶምን ተሸክመው ሲወጡ አየኋቸው። ድላይ እያለቀሰች ጌታሁንንተሸክማ እየወሰደችው ነበር። በኋላ የራሱን ስቃይ ትቶ "አይዞሽ ጓዲት፣ በርቺ አይዞሽ!" እያለ አንጀት በሚበላ ንግግር በማበረታታት እርሷን ለማጽናናት ይሞክር እንደነበር ነገረችኝ።

በመጀመሪያ ሁለቱም አልሞቱም ነበር፤ ጥቂት ሄደት እንዳልን ግን ጌታሁን አበቃለት፣ ሕይወቱ አለፈች። እንዶምን ግን ቃሬዛ ሠርተን ይዘነው ሄድን። የየአቢኢዮን አስከሬን ከውጊያው ቦታ አውጥተናል። የሕብስቱን አስከሬን፤ ጎትተው ወደካምፕ ውስጥ ስላስገቡት ምንም ማድረግ አልቻልንም።

ሮምህን የቀበርነው ራቅ ብለን ወደ ተራራው ከመድረሳችን በፊት ባለው ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ቢሆንም ለ ወታደሮቹ ስለምንታያቸው እየተኮሱብን ነበርና በደንብ እንኳ መቆም ተቸግረን ነበር። ራሳችንን አጎንብሰንና ፈጠን ፈጠን እያልን ለጓዶች የሚደረገውን የስንብት መዝሙር እንደነገሩ ዘምረን ቀበርነው።

ከዚያም ወደምሥራቅ በኩል የበረሐውን አቅጣጫ ይዘን ስንሄድ ሌሎች ጓዶችን ሰብሰብ ብለው ቆመው አገኘንና "አንተን እየጠበቅን ነበር" አሉኝ።





አጠገባቸው ጉድጓድ ቆፍረው ጎን ላይ የየአቢኢዮ አስከሬን ለቀብር ተዘጋጅቶ ተመለከትኩና "ምነው ምንሆናችሁ?" አልኳቸው።

"አንተን እየጠበቅንህ ነበር" አለኝ አንዱ ጓድ።

"የአቢኢዮ የውቅሮ ልጅ ነው። አስከሬኑን ከዚህ በላይ ርቀት ይዘን ልንሄድ አንችልም። ጉድጓድ ቆፍረናል፣ እዚህ ከቀበርነው ግን በውቅሮ የደርግ ሰዎች ማንነቱ ስለሚታወቅ አስከሬኑን ሊያወጡት ይችላሉ ብለን ሰጋን። ከዚያም በላይ ሌላም መዘዝ ሊያስከትል ይችላል። ይህ ደግሞ ለቤተሰቦቹ፣ ለዘመዶቹና ለሚያውቁት ሁሉ ጥሩ አይሆንም። ስለዚህ ምን እንደምናድርግ ቸግሮናል" አለ ቀጠለና፤ "አስከሬኑ እንዳይታወቅ አንገቱን ቆርጠን እንውሰደው የሚል ሐሳብ መጥቶ ነበር። ከበደን፤ መስማማትም አቃተን። "አማኑኤል በቅርብ ስለሚያውቀውና የኃይል መሪውም ስለሆነ እርሱን ብናማክር ይሻላል በማለት ነው የፈለግንህ" አለኝ።

የየአቢኢዮ እናትና አጎት ትዝ አሉኝ። እናቱ አንዳች ነገር ቢሰሙ ወይም ቢያዩ የሚከተለውን አሰቤዋለሁ። ነገር ግን ዓይናችን እያየ በገዛ እጃችን አንገቱን መቁረጥ ... ውስጤ እንቢ አለኝ። እናቱን ሳስብ ደግሞ ግራ ገባኝ፣ ጭንቅላቴ ጭው አለብኝ። መጀመሪያ መሞቱን ስሰማ የተሰማኝ ስሜት አሁንም እየሞከረኝ ነው። የፈለገው ይምጣ ብዬ "በፍጹም አንገት መቁረጥ አይደረግም! እንዲሁ እንዳለ ቀብረነው ብንሄድ ነው የሚሻለው" አልኩና ከስሬ ወደተንጋለለው የየአቢኢዮ አስከሬን በርከክ አልኩና ተመለከትኩት።

የተመታው በስተግራ በኩል ከአይኑ ትንሽ ዝቅ ብሎ ነበር። ትንሽ የደረቀ ደም ፊቱ ላይ ከመታየቱ በስተቀር ሰውነቱ በሙሉ ደም የለበትም። የግራ እጄን በአንገቱ በኩል አስገብቼ አንገቱን ቀና አደረግኩና ግንባሩን ሳምኩት። አይኖቹ እንደሞተ ሰው ሳይሆን እንቅልፍ እንደወሰደው ሰው ተከድነው ፊቱ ላይ የጸጥታ መንፈስ ሰፍሯል። ማስታወሻእንዲሆነኝ ብዬ ቀበቶውን አውጥቼ ወሰድኩ። አሁንም እንደገና አየሁትና ቀኝ ጉንጬን ጎንበስ ብዬ ስስመው "ወዲ

ሐፍተይ፣ ወዲ ሓፍተይ" የሚል ድምጽ ጆሮዬ ላይ ይጮህብኝ ጀመር። ዕንባ በአይኖቼ ሞላ። የልቤ ምት ጨመረ፣ ሆዴ ተንሰፈሰፈ። ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም። አስከሬኑን እንዳቀፍኩ ስቅስቅ ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ። የቆሙት ጓዶች ምን እንደሚያደርጉኝ ግራ ገብቷቸዋል፣ ቢጠብቁኝም አልነሣ ብያቸዋለሁ።

በኋላ ቢራራ ጎንበስ ብሎ ትከሻዬን ያዘና "ብቃ፣ በቃ ተነሥ" አለኝ፣ እሺ አላልኩትም። በሁለት እጆቹ ግራና ቀኝ ትከሻዬን ይዞ ሊያነሣኝ ሞከረ፣ አልተነሣሁም። በመጨረሻ ከአንድ ጓድ ጋር ተጋግዘው በግድ እየጎተቱ አነሡኝና ወደ ኋላ አድርገውኝ አስከሬኑን መቅበር ጀመሩ። አስከሬኑን ወደ ጉድጓድ ጨመሩና አፈር አለበሱት። ሁላችንም በተጠንቀቅ ቆመን የኢሕአሠን የስንብት መዝሙር በአንድ ድምፅ ዘመርን።

የአቢዮን ቀብረን ስንሄድ በፍጥነት እንድንደርስ ስለተነገረን እየሮጥን የቀደሙትን ጓዶች ደረስንባቸው። ስንደርስ አንዶም በሕይወት ነበረ፤ ይነጋገራል። የተመታበትን ቦታ በጨርቅ አስረን በተቻለን መጠን ደሙን ለማቆም ሞከርን። ያፈገፈግንበት ቦታ ከውቅሮ በስተምሥራቅ በኩል የሚገኘው አጽበ ደራ ወረዳ ይባላል። ተራራዎቹን ከወጣን በኋላ ሜዳ ነው። ከሜዳው በሰተምሥራቅ በኩል ያሉት ዳሎልና የደንከል በረሐ ናቸው።

እኔ ሮምሀን ስሸከመው በአፉና በአፍንጫው የፈሰሰው ደም ከላይ እስከታች ድረስ አልብሶኛል። ሮምሀን ተሸክሜ ትጥቁን ለመያዝ ስላልተመቸኝ ለአንድ ጓድ ሰጥቼው ይዞ ቀድሞ ሄዶ ነበር። ድላይና ፍሱሕ ገብራይ ደግሞ ጌታሁንን ሲሸከሙ ሰውነታቸውም ልብሳቸውም እንደኔ በደም ተነክሯል። እነርሱ ከእኔ በፊት ተራራውን ወጥተዋል። እኔና ብርሃኑ ምክትል ጋንታ መሪዎች ስለሆንን የተወሰኑ ጓዶችን አሰባስበን እየተጓዝን ነበር።

***





ማይ መሳኑ

«ለጓድ ሞት አያለቅሱም፣ አርማውን ያነሷል እንጂ»

ተራራውን ወጥተን አጽቢ ከተማ ስንደርስ ጸኃይ ጮራዋን መፈንጠቅ ጀመረች። በህይወት የተረፉት የአመራር አባላት ቀድመው የመጡትን በየጋንታቸው እያሰባሰቡ ደረስን። የእኛ ጋንታ መሪ እንግዳወርቅም የሚመራውን ጋንታ አባላት እያሰባሰበ ነበር። ስንደርስ እነእንግዳ ወርቅ እኔን ሲያዩ ድንጋጤአቸውን መሸፈን ሳይችሉ ሁሉም ወደ እኔ ዞሩ። ሁኔታቸውን ስመለከት ምን ተፈጠረ ብዬ ግራ ገብቶኛል። ለካስ ትጥቁን የሰጠሁት ጓድ የኔን መሳሪያ ሲሰጣቸው አማኑኤልም ተሰውቷል ብለው ተጠራጥረው ነበር። ትንሽ ከተረጋጉ በኋላ መሣሪያየን የሰጠሁበት ምክንያት ተነግሯቸዋል፤ ስደርስ ግን የመጀመሪያው ድንጋጤያቸው አልለቀቃቸው ኖሮ ሁሉም አፍጥጠው ተመለከቱኝ።

አንዶምን ይዘነው ስንደርስ ሀኪሞች እየጠበቁን ነበር። አንዶምን ለሀኪሞቹ ሰጥተን እኔም ወደ ጋንታዬ ገባሁና ትንሽ እንደሄድን ከአመራሩ መልእክት መጣ። እንግዳ ወርቅ መልእክቱ እንደደረሰው፣ ወደእኔ መጣና ትጥቁን ሰትጥቶኝ "አማኑኤል፣ ዛሬ በጣም የምትወዳቸውን ጓዶችህን አጥተሀል። አንተም ከእነርሱ ጋር ብትቀር ይሻልህ ነበር። ከአሁን በኋላ ምን ህይወት ትኖራለህ?" አለኝ ፊቱ በሀዘን እንደተጨፈገገ። "ለማንኛውም አሁን ፍሱሕና ድላይ ስለሚጠብቁህ ከእኛ ጋር ሳይሆን ከእነሱ ጋር እንድትሄድ ከአመራሩ መልእክት ደርሷል" አለኝ።

ትንሽ ወደፊት እንደሄድኩ ነበር ፍሱሕንና ድላይን ያገኘኋቸው። አልተነጋገርንም፤ በፍሱሕ መሪነት ወደ ወንዝ ወረድን። ቦታውን እኔና ድላይ አናውቀውም። ፍሱሕ የነበረባት ኃይል ሰልሳ ስድስት በዚያው አካባቢትንቀሳቀስ

ስለነበረ አካባቢውን በሚገባ ያውቀዋል። ወንዙ ከከተማው በስተሰሜንይነሳና ጥቂት ወደ ደቡብ ከወረደ በኋላ ወደ ቆላ ይፈሳል፤ እኛም ፍሱሕን ተከትለን እንሄዳለን።

በመጀመሪያ ጥሻ ውስጥ ገባንና ወደ ወንዙ የሚያወርደውን ቁልቁለት ያዝን። በምንሄድበት በኩል ምንም የእግር መንገድ ምልክት አይታይም። ሰው ሄዶበት የሚያውቅም አይመስልም። ቦታው በዛፎችና በትናንሽ ቁጥቋጦዎች የተሞላነው። ቁልቁለቱን ወርደን ስንጨርስ የወራጅ ወንዝ ድምጽ ይሰማ ጀመር። ትንሽ ከሄድን በኋላ ቁልቁለቱን ጨርሰን ጥሻውን አለፍንና ወደ ወንዙ አፋፍ ካለው ገላጣ ቦታ ላይ ደርሰን። እይታው መንፈስን ይሰርቃል፤ እኔና ድላይ በአድናቆት ፈዘን ቆምን።

ሁለታችንም አይኖቻችን ማመን እስኪያቅተን ድረስ በአግራሞት ተውጠን አድናቆታችንን በአንደበታችን መግለጽ ተስኖን እንተያያለን። ፍሱሕ ሁኔታችን ፈገግ አሰኝቶት አድናቆታችንን እስክንጨርስ የሚጠብቀን ይመስላል። እኛ ከነበርንበት እልፍ ብሎ በከተማውና በወንዙ መካከል አንድ ትንሽ ኮረብታ አለ። ወንዙ ማይ መሳኑ፣ ኮረብታው ደግሞ ባርካ እንደሚባል ፍሱሕ ነገረን። ማይ መሳኑ ማለት የመስኖ ውሀ ማለት ሲሆን፣ ባርካ ማለት ደግሞ አካባቢውን ማሳየት የሚችል ከፍተኛ ቦታ እንደማለት ነው።

ሰአቱ ከጠዋቱ ሁለት ወይም ሶስት ሰአት አካባቢ ይሆናል። "ወደ ወንዝ እንድንወርድ የተደረገው የሶስታችንም ገላና ልብስ በደም ስለተበላሸ እንድንታጠብ ነው" አለ ፍሱሕ። ነጠላውን ነጥሎ የልብሱን ደም እንዲሸፍንለት አርጎ ከለበሰ በኋላ ሳሙና ሊያመጣ እኔና ድላይን ብቻችንን ትቶን ወደ ከተማ ሄደ። ሳሙና ካመጣልን በኋላ ሰውነቱን ታጥቦ ትንሽ ቆየና ምሳ ሊያመጣ እንደገና ወደከተማ ተመለሰ።

እኔና ድላይ ጸሀይ ለመሞቅ ብለን ወደ ኮረብታው ላይ ወጣንና ተቀመጥን። ከሁለቱም የበለጠ የእኔ ሰውነትና ልብስ፣ ጸጉሬም ጭምር በሮምህ





ደምና ከሆዱ በወጣ ነገር ከላይ እስከታች ተበላሽቷል። ድላይ ፍዝዝ ብላ ስታየኝ ቆይታ አይኖቿ እንባ እያቀረሩ "እንዴት ሆነህ ከዚህ ሁሉ መዓት ወጣህ?" አለችኝ።

"በህይወት እተርፋለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም። ግን መኖርስ ምን ዋጋ አለው?! ብሰዋ ይሻለኝ ነበር!" ብዬ ድምጼ ተቆራረጠና ራሴን ታግዬ መቆጣጠር አቃተኝ። አንገቴን ወደ መሬት ደፍቼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። ጥቂት ቆይቼ ደግሞ ላወራላት ጀመርኩ "በወሎ የእነጁሊያኖን አሟሟት አይቻለሁ። በ1969 ዓ.ም. ደግሞ ጎንደር በለሳ ላይ እነያደቴ፣ ምትኩ፣ አለማየሁ ሊቁና፣አብሮ አደጌ ዳዊትና ብርሐነ በርሔ ሕይወታቸው ሲያልፍ አይቼ ጥያቸው መጥቻለሁ። ከበለሳ ስንመለስ ለመጸዳዳት የሚወጣ በመምሰል እነዳዊትንና ሙቶ አሊቃ ፍጹምን እያስታወስኩ ብዙ ግዜ ለብቻዬ አለቅስ ነበር። አሁን ደግሞ የአቢኢዮን ሞት ተመለከትኩ። ትናንት አብረን ነበርን እኔ ስተከዝ አይቶ እየሳቀ ሲያበረታታኝና ሊያጫውተኝ ሲሞክር ነበር። ዛሬ ግን ሜዳ ላይ ቀብሬው መጣሁ። ሮምህ አጠገቤ ሆኖ እየተመካከርን ስንትኩስ ቆይተን በደቂቃ ውስጥ አንዲት ቃል እንኳ ማውጣት ተስኖት፣ አይዞህ ጓዴ አጠገብህ ነኝ በርታ እንኳ ለማለት እድል አጥቼ..." ንግግሬን ልጨርስላት አልቻልኩም፤ የሆዴን መተረማመስ ማቆም አቃተኝ፤ የጀገኑት ዓይኖቼ ብቻ ነበሩና እንባቸውን በመንታ አወረዱት። ድላይ መጀመሪያ ልታባብለኝ ሞከረችና ከዚያ በኋላ ግን እርሷም ባሰችና ማልቀስ ጀመረች።

ድላይ "እንዴት ከዚያ መዓት ወጣህ?" ማለቷ ወደ ውቅሮ ከመሰማራታችን በፊት "አንተና የአቢኢዮን በሕይወት የማገኛችሁ አይመስለኝም" ያለችውን ስጋት አስታወሳ ነበር። በጦርነቱም ውስጥ እያለን ቀድማ ወደ እኔ የደረሰችው ከዚያው ስጋቷ ጋር ተያይዞ በተሰማት ጥርጣሬ ነበር።

በእርሷ ጋንታ ውስጥ በተጠባባቂ የነበሩ ጓዶችን ይዛ፣ አዋጊ ሆና ስትመጣ፣ ከኋላችን የነበረ አንድ ጓድ ተኩስ በዝቶበት፣ አቀርቅሮ ጠመንጃውን ወደታች ሲተኩስ አይታው ተናደደችበት። "ጓድ ቀና በል እንጂ፣

የምትተኩሰው ጥይት ወዴት መሆኑን ማወቅ አለብህ" ብላ ጠመንጃውን ከእጄ ነጥቃ እንዴት እንደሚተኮስ አሳይታው መልሳ ጠችው። መቼምጀግንነቷ ለዩ ነበር።

እንደምንም ለቅሷችንን አቆምንና ተነስተን ወደ ወንዙ ዳርቻ ወርደን ድንጋይ ላይ ቁጭ እንዳልን "አማኑኤልን ሬሳውን እንጂ በሕይወት አላገኘውም እያልኩ ነበር የመጣሁት" አለችኝ።

"አዎ እኔም እወጣለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም። ሮኩሱ ከጠበቅነው በላይ ነበር። እናንተ መጥታችሁ ባትረዱን ኖሮ እኛም በሕይወት አንወጣም ነበር" አልኳት። የምናወራው አይን ለአይን እየተያየን እጆቻችንን በወንዙ ውሀ ውስጥ ከትተን ከውሀውም ጋር እየተጫወትን ነበር።

"እና ወደ በጌምድር የምትሄደው መቼ ነው?" አለችኝ ደግሞ። ቀስ ብላ እርእስት መለወጥ እንደፈለገች ገባኝ።

"መቼ እንደሆነ ገና አላወቅኩም። የጋንታ ሀያ ስድስት አባሎች፣ ምክትል የጋንታ መሪው ይዟቸው መጥቶ ጦርነቱ ላይ ተካፍለዋል። ነገ ወይንም ከነገ ወዲያ ከእነርሱ ጋር ወይንም ለብቻዬ ወደ አሲምባ እወርዳለሁ" አልኳት።

"አሁንስ ኃይል አምስት መቶ አስጠላኝ። እኔም ብሆን ወደ ሌላ ኃይል ቢቀይሩኝ ደስ ይለኝ ነበር። ጌትነት የለም፣ አሁን ደግሞ የአቢኢዮና ሮምሀ ተሰውተዋል። አንተ ብርሀኑና ግደይ ጨጓር ደግሞ ወደሌላ ቦታ ተመድባችኋል። የቀረነው እኔ ቴዎድሮስ ባሪያውና እንግዳ ወርቅ ብቻ ነን" አለችና በሀዘን ተዋጠች።

"እኔም እኮ ትእዛዝ ሆኖብኝ ነው እንጂ፣ ከእናንተ ለመለየት አልፈልግም ነበር። በተለይ እኔና አንቺ ሁልጊዜ አንድ ኃይል ውስጥ ብንሆን ደስ ይለኝ ነበር" አልኳት።

"አይ አማኑኤል፣ እንደዚያማ አይሆንም። ግን ትግራይና በጌምድር ሆኖ መለያየቱ በጣም ደስ አይልም..." ተናግራም ሳትጨርስ እኔም መልስ





ሳልሰጣት የከባድ መሳሪያ ድምጽ ሰማሁኝና ከተቀመጥኩበት ፍንጥር ብዬ ተነስቼ ጠመንጃዬን አንስቼ ግራ ቀኝ ስል፣ እርሷ በጣም ሳቀች። እንደዚያ ስትስቅ አይቻት አላውቅም፤ በጣም ሳቀች። "ምን ያስቅሻል? ጠመንጃሽን ያገርና ተነሺ እንጂ" አልኳት። ያሳቃት የግልድም አለባበሴና ከእነ ብረቴ መነሳቴ ነበር። " ግልድም አለባበሱን በደንብ አውቀህበታል። ከግልድምህ ጋር ደግሞ ጠመንጃ እያያዝ ያምርብሀል፣ ልክ ያገሬን ሰዎች መሰልከኝ" አለችኝ።

"አለባበስ እኮ በደንብ አስተምረውኛል። ከሁለት አመታት በፊት ከወሎ ሮቢት አሲምባ ድረስ አገልድም ለብሼ ነበር የተጓዝኩት" አልኳት።

"አዎ፣ ሰምቻለሁ። ታዲያ እንዴት አልረሳኸውም?" " "እንዴት ይረሳኛል?"

"እሺ ዘለህ የተነሳኸው ምን ሆነህ ነው?"

"የከባድ መሳሪያ ድምፅ!"

"የከባድ መሳሪያ ድምፅማ አልሰማህም" አለችና ጥቂት ዝም አለች።

"የለም አልሰማህም። አንተ ብትሰማ ኖሮማ እኔም እሰማ ነበር" አለችኝ በማረጋገጥ። እንግዲያውስ የሌሊቱ የተኩስ ድምጽ ጭንቅላቴ ውስጥ ተቀርጾ ይሆናል ብዬ አሰብኩና ገረመኝ።

"በል እሱን ተወውና ና ተቀመጥ" አለችኝ ደግሞ። ከፊት ለፊቷ ድንጋይ ላይ ተቀመጥኩ።ስቀመጥ እያየችኝ ሳቋን እንደገና ጀመረች። " ምነው?" ስላት

"አሁንስ ሚዶና ቂቤ ብቻ ነው የቀረህ እንጂ እሱ ቢጨመርልህ ደንበኛ ራያ፣እንዲያውም የወሎ ራያ ትመስላለህ" አለችና ሳቋን ለቀቀችው።

ፊት ለፊት ተቀምጠን ዓይን ለዓይን እየተያየን ስለነበር ገጽታዋ ብሩህ ሆኖ ይታየኛል። ጥርሶቿ ተከርክመው እንደተስተካከሉ ሁሉ መስመር ይዘው የተደረደሩ ናቸው። ጉንጮቿ ወጣ ወጣ ብለው ዓይኖቿ ወደ ውስጥ ገባ ገባ በለዋል። ገላዋን በሳሙና ስለታጠበች ፊቷ ያንጸባርቃል። አጠር ያለ ሉጫ ጸጉሯ በነፋሱ ወዲህ ወዲያ እያለ ይወዛወዛል። ሰውነቷ በሙሉ የተስተካከለ ነው።

ሁሉ ነገሯ አምሯል። ትክክለኛ የሴትነት ውበቷን ያየሁት ያን ቀን ይመስለኛል።

በሌላ ጊዜ በደልዳላ አቋሟ ጠመንጃ ይዛ፣ በተለይ ደግሞ ኮፍያ አርጋ ስትሄድ ወንድ ነው የምትመስለው። ፊቷን ኮስተር ስታደርገው ደግሞ ታስፈራለች። በዚያ ቀን ግን ተጣጥባ፣ መናፈሻ ውስጥ ሆና ንጹሕ አየር እየተነፈሰችና ነጻ ሆና ስትስቅ ሳያት ድላይ መሰላ ታየችኝ። "እሁንስ በእውነት ሙሽራ መስለሻል፤ ዛሬ በጣም ነው ያማረብሽ፣ አብረውኝ ያደጉ የአዲግራት ልጃገረዶችን መስለሻል። እንዲህ ከሆን ሁልጊዜ ወንዝ እየወረድሽ በሳሙና መታጠብ አለብሽ" ብዬ ቀለድኩባት።

"አንተ 'አናርኪስት' ሥነሥርዓት!! የአዲግራት ልጃገረዶች ቆንጆዎች እንደሆኑ አውቃለሁ" አለችና እንደገና መሳቅ ጀመረች። ማራኪ ውበትና የሚያምር ሰውነት እንዳላት በዚያ ቀን ዓይቻት ምስክር ለመሆን በመቻሌ ትልቅ ደስታ ተሰማኝ።

***





ጠዋት ስናለቅስ ቆይተን አሁን ደግሞ በሳቅ ልንሞት ደርሰናል። እንደገና ወደዚያ ሀሳብ ስገባ ፊቴ ተለዋውጦ በሐዘን ጨለመ። እርሷም ወዲያውኑ መለወጤን አይታ "ምን ሆንክ፣ አማኑኤል?" አለችኝ፤ የእርሷም ፊት እንደኔው መለወጥ እየጀመረ ሲሄድ ይታየኛል። "ምንም አይደለም፤ ግን እኮ ድላይ፣ እኔና አንቺም ከዛሬ በኋላ ላንገናኝ እንችላለን። እንዲህ ዓይነት ዕድልም ሁለተኛ ላያጋጥመን ይችላል" አልኩ ሐዘን የበለጠ ልቤን እየሰበረው።

"አዎን ሊሆን ይችላል። እኔ፣ ዛሬ በሕይወት እንደማላገኝህ ነበር ትናንት ማታ ያሰብኩት። አጋጣሚ ሆኖ ግን ዛሬ አብረን ውለናል። የሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ ምን እንደሚመጣ ምን ይታወቃል" አለችና እ ር ሷ ም አንገቷን ወደመሬት ደፋችው።

የሚወረደውን የወንዝ ውኃ እየተመለከትኩ ቅዝዝ ብዬ ቀረሁ። ቀና አለችና "ምነው አማኑኤል ምን እያሰብክ ነው?" አለችኝ።

"ምንም! ብቻ የምንወዳቸውን ጓዶች ቀብረን ዳግም ላናገኛቸው መለያየታችንን ሳስበው ውስጤ ይረበሻል። በተለይ ሮምሀ አጠገቤ እንደተመታ ወዲያውኑ ነበር የሞተው። ትናንትና መጀመሪያ የተሠዋው እሱ ይመስለኛል። እንደተመታ በዚያው ወድቆ ቀረ። አንዲት ቃል እንኳ ለመተንፈስ ዕድል አላገኘም። እኔ ግን ነፍሱ ሳትወጣ አንድ ቃል እንኳን ይናገር እንደሆን ብዬ ስሙን እየጠራሁ ትከሻውን እነቀንቀው ነበር። እሱ ግን እስከወዲያኛው ሄዷል፣ አልሰማኝም። የሆነ ነገር ተናግሮ ቢሞት ይሻለኝ ነበር። ምንም ቢሆን ሐዘኑ የሚወጣልኝ አይመስለኝም። እርሱ አንድቃል ለመተንፈስ ዕድሉን አጣ። እኔና አንቺ ደግሞ እዚህ ልዩ የተፈጥሮ ውበት በታደለ በአበቦች በተንቆጠቆጠ፣ በአእዋፍ ዝማሬ በደመቀ፣ ንጹሕ አየር፣ ጥርት ያለ የወንዝ ውኃ ባለበት ቦታ ላይ ገላችንን ታጥበን፣ በነጻነት ሆነን እየሳቅን ለማውራት የማይታለም ዕድል አገኘን። ዓለም ምንድናት? እንዲህ የ ሰማይና ምድርን ያህል የሰውን ልጅ እየለየች የማይገናኝ

ኢጋጣሚ የምትሰጠው፣ ዕድልስ የሚወሰነው እንዴት ነው? እያልኩ ራሴን እየጠየቅሁ ሁሉም ነገር ግራ ይገባኛል" አልኳት።

"ደግሞ ትናንት በጣም ያሳዘነኝ ነገር ምን እንደነበር ታውቃለህ? ጌታሁንን ተሸክሜው ስሄድ እኔ እንደሆንኩ አውቋል። የተመታው በከባድ መሣሪያ ግራ ደረቱ ላይ ስለነበረ በጣም ተጎድቷል። የግራ እጁ ተበጥሳ ልትወድቅ ደርሳ አንድ ጓድ የግራ እጁን እየደገፈልኝ ነበር የምሄደው። እኔ ስለእርሱ መትረፍና አለመትረፍ ነበር የምጨነቀው። እርሱ ግን እንዲያ ሆኖ የራሱን ሁኔታ ትቶ እኔን ሊያበረታታ "አይዞሽ ጓዲት፣ አይዞሽ ጓዲት!" ይለኝ ነበር፤ ከሞት ጋር እየታገለ። ትከሻዬ ላይ እንዳለ መተንፈስ እያቃተው ሲታገል ይሰማኝ ነበር። እርሱ ሞት አፋፍ ላይ መሆኑን እያወቀ እኔን አይዞሽ ሲለኝ አንጀቴ አልችል ብሎ ይንሰፈሰፍ ነበር። እንደዚህ ዓይነት ሰቆቃ ማሳለፍ እንኳን በምትወደው ሰው በጠላትም ላይ ቢታይ ከባድ ነው። ግን ትግል ስለሆነ ለመርሳት መሞከር ነው እንጂ ምንም ማድረግ አይቻልም" ብላ በሐዘን ስትዋጥ የኔን ሐዘን ትቼ እሷን ማጽናናት ጀመርኩ።

***





ድላይ ተወርዋሪውን ኃይል ይዛ ወደ ጦርነቱ ስትገባ መጀመሪያ የመጣት እኔ ወደ ነበርኩበት ምሽግ ነበር። ከወታደሮቹ ፊት ለፊት ስለነበርን በጣም የተጠቃነው እኛ ነን። የእነርሱን ዘብ ቦታ አስለቅቀን ነበር የምንታኮሰው። ወደ ግምቡ አጥር ለመጠጋት ግን አልቻልንም። እንደመጣች የተገናኘችው መጀመሪያ ከእኔና ከሀጎስ ማንጁስ ጋር ነው ። ሁኔታውን በደንብ ገለጽኩላት። ከእኛ በስተግራ በኩል ምሽግ ይዘው የሚታኮሱት ሕብስቱና ጌታሁን ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ይተኮስባቸው ስለነበረ እነርሱ ወደአሉበት ቦታ እንድትሄድ ነገርኳት። እነርሱ ወደእነሕብስቱ ሲሄዱ እኛ ሽፋን እየሰጠናቸው ነበር።

ድላይ ይህንን አስታውሳ፤ "እኛ ወደታች ስንወርድ እናንተ ከፍተኛ ተኩስ ከፍታችሁ ሽፋን ባትሰጡን ችግር ላይ መውደቃችን አይቀርም ነበር። እነፍሱሕና እነግደይ በጣም ገረማቸው። አንዶምና ጌታሁን ቆስለው ወድቀዋል። ሕብስቱ ብቻውን ተነሥቶ ወደፊት ሄዶ በዚያው ቀረ። ሕብስቱ አጥሩ ስር እንደተመታ ከተረዱ በኋላ ወደፊት ሄደው ሕብስቱን ለማውጣት ሞክረው ነበር። ነገር ግን ወታደሮቹ የሕብስቱን ሬሳ ወደ ውስጥ ጎትተው አስገብተውታል። በመጨረሻ የነበረን አማራጭ በሕይወት ያሉትን ቁስለኞች ማስወጣት ነበር። አንዶም በሕይወት ተርፏል። ጌታሁንን ግን በትከሻዬ ተሸክሜው እየሄድኩ በላዬ ላይ ሆኖ፤ "አይዞሽ" ሲለኝ ቆይቶ ነበር ያረፈው። በአሰብኩት ቁጥር ድምፁ ጆሮዬ ላይ ይደውላል፤ እስካሁን ድረስ ትከሻዬ ላይ ያለ ይመስለኛል፤ ሐዘኑ የቀን ያህል ልቤን እንደሰበረው ልነግርህ አልችልም። ነገር ግን ትግል ስለሆነ እኛም እንከተላቸዋለን።

"አሁን ያለን አማራጭ መጠንከር ብቻ ነው እንጂ የአቢኢዮ፣ ሮምሀ፣ ሕብስቱ፣ ጌታሁን ፣ ዩሱፍ ሌሎቹም አይመለሱም። በሕይወት እስከአለን ድረስ በጀግንነታቸው እንኮራለን።መሥዋዕትነት ሁላችንም ወደ ትግል ስንገባ የተቀበልነው ነገር ነው። ሁላችንም ወደፊት በመታገል መቀጠል ብቻ ነው ያለብን። ትግል እኮ ለተሠውትም ላለነውም መራራ ነው። ይህን ሐዘናችንን ልንረሳው ካልቻልን ወደፊት ለመራመድ እንቸገራለን። ስለዚህ እሱን ረስተን

ስለወደፊቱ ዓላማችንና ትግላችን እናውራ፤ ድላችንን በተስፋ የሚጠብቀውን የትግራይንና የመላው ኢትዮጵያን ሕዝብ ስናስብ ብቻ ነው ሐዘናችንን መርሣት የምንችለው" አለች በተመስጦ።

ሁለታችንም ስናወራ ወደ ወንዙ ጎንበስ ብለን ወራጁን ውኃ እያየን ስለነበር፣ ዕንባችን ወደ ወንዙ እየተንጠባጠበ ከወንዙ ከውኃው ጋር ተቀላቅሎ ይወርዳል። ትካዜና ሐዘናችን ከብዶ ከቁጥጥራችን ውጪ ነበር።

ፍሱሕ ገብራይ ምሳ ሊያመጣልን እንደሄደ አልተመለሰም። የሄደበት ከተማ ካለንበት ቅርብ ነው። ነጻ የወጣ አካባቢ ስለሆነ የሚጠበቀው በእኛ ሚሊሺያዎች ነበር። በአካባቢው የምትንቀሳቀሰው ኃይል ስልሣ ሰድስት ብዙ ስለሠራችበት በርካታ ደጋፊዎች ያሉባት ከተማ ነች።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ፍሱሕ ገብራይና ሁለት ሚሊሻዎች ዳቦ አመጡልን፤ በልተን ከወንዙ ውኃ በእጃችን እየጨለፍን ጠጣን። ፍሱሕ ገብራይ "እመጣለሁ" ብሎ ከሚሊሻዎቹ ጋር ተመልሶ ሲሄድ እኔና ድላይ እንደገና ለብቻችን ቀረን። ያለንበት ቦታ ከከተማው ቅርብ ሲሆን የሚከልለን አንድ መለስተኛ ኮረብታ ነው። ወደ ወንዙ መውረጃ ገደላማ እየሆነ ይሄዳል። ትላልቅ ዛፎችም ይገኙበታል። ቀሪዎቹ ጓዶች ያሉበትን ቦታ በግምት ነው እንጂ በደንብ አናውቅም። ከነበርንበት ቦታ በምን ያህል ርቀት ላይ እንዳሉ መገመትም ከባድ ነው። "የምትሄዱበት ቦታ ለጸጥታ አስጊ አይደደለም በእኛ ሰዎች ቁጥጥር ውስጥ ነው" ብቻ ነው የተባልነው።

ሁለታችንምአገልድምለብሰን መሣሪያችንን ከነሙሉ ትጥቁ ይዘን ልብሳችንን እያደረቅን ነበርን። ከምሳ በኋላ አገልድም እንደለበስኩ ድንጋይ ላይ ቁጭ አልኩ። ከወገቤ በላይ ራቁቴን ነበርኩ። ድላይ ግማሽ ራቁቴን ስታየኝ የመጀመሪያዋ ነው። ቀና ብላ ተመለከተችኝና "አማኑኤል ለካስ በጣም ቀጭን ነህ፡ አጥንቶችህ ይታያሉ" አለችኝ።





"አዎን፣ እኔ እኮ በድህነት ነው ያደግኩት። አሁን ደግሞ ትግል ላይ ስለሆንን የተገኘውን ነው የምንበላው፤ ጦም ውሎ ጦም ማደርም የተለመደ ነገር ነው፡ በፊትም በችግር አሁንም በባሰ ሁኔታ በመኖሬ የነበረው ይብሳል" አልኳት።

"አይዞህ ምንም አይደለም። ሁላችንም በድህነት ነው ያደግነው" ስትል እኔን ለማጽናናት መሰሎኝ ነበር።

"እኔ በድህነት ማደጌን መደበቅ አልፈልግም። አንዳንድ እንዲታወቅባቸው የማይፈልጉም እንዳሉ አይቻለሁ" አልኩ በመቀጠል።

"ልክ ነህ! ሁሉም እንዳንተ ንጹሕ መሰለህ እንዴ? ለዚህ እኮ ነው ትግሉ ከውስጥም ከውጪም ነው የሚባለው" በማለት ድህነት የሚያሳፍር እንዳልሆነ በሚማርክ አነጋገር ገለጸችልኝ።

ልብሳችን መድረቁን ለማየት ወደ ኮረብታው ላይ ወጣሁ። ባልደረቀው በኩል ፀሐይ እንዲመታው ልብ ሳችንንን ለበጥኩና ተመሼ ከፊቷ ተቀመጥኩና እየተያየን ማውራት ጀመርን። "ዛሬ ታዲያ የመጨረሻችን ቀን ነው ማለት ነው?" አለችኝ፤ ድላይ የተናገረችው እስባ አይመስልም።

"አዎ፤ ከየአቢኢዮና ከሮምሀ ጋር በሞት ተለያየን። እኔና አንቺ ደግሞ በሕይወት ልንለያይ ነው። ለምን እኔን ብቻ ከኃይል አምስት መቶ ነቅለው ወደ ጎንደር እንደመደቡኝ አላውቅም። ትግራይ ውስጥ ካሉት ሌሎች ኃይሎች ውስጥ ቢመድቡኝ እንኳ በእንደዚህ ዓይነት ጦርነት ጊዜ ወይም ሠራዊት በሚቀየጥበት ምደባ ልንገናኝ እንችል ነበር። በጌምድር ከሄድኩ ግን ላልመለስም እችላለሁ። ብመለስም በጣም ቆይቼ ነው የሚሆነው። ምንም ማድረግ አንችልም፤ ብቻ በያለንበት በትግል መጽናት ነው" አልኩዋት።

"አዎ፤ አንተ ግን ህመሜንና ስቃዬን መካፈልህን አልረሳውም። ወደማይ ምሻም ተራራ ሄደን በፍቅር ያሳለፍናቸውን ቀናትም አልረሳቸውም። ጠመንጃው እኮ የባረቀብኝ ልቤ ተደፍኖ ነበር። እንዴት ሳላስበው ቃታውን እንደሳብኩትም አላውቅም። ጥይቱ እኮ በሁለታችን መካከል ነው ወደ ጣራው

የሄደው። ጠመንጃው ዘንበል ብሎ ቢሆን ኖሮ ጉድ ሆነን ነበር" አለችና ፈገግ ብላ ሐሳብ ውስጥ ገባች።

"ያን ቀን ግን የጠረጠሩን ይመስልሻል" "ለምን እንደዚህ አልክ?"

"ታዲያ እኔን ብቻ ለይተው ወደ በጌምድር ለምን ይልኩኛል? አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ግደይ ጨዳር ብቻችንን ስንሆን ቺኮዝ ብሎ ይጠራኛል"

"ችኮዝ ማለት ምን ማለት ነው?

"ቺኮዝ የጠመንጃ አይነት ነው። ነገር ግን በድርጅታችን ሰላይ ተብሎ ሞት የተፈረደበት ሰው የተገደለው በቺኮዝ ጠመንጃ ስለነበር "ሞት አዳይፈረድብህ" ብለን ስንቀላለድ " ቺኮዝ" እንባባላለን። እንግዲህ ግደይም በጾታ ግንኙነት ተከሰህ ሞት እንዳይፈረድብህ ብሎ መቀለዱ ይሆናል" ስላት ሆዷን ይዛ ከት ብላ ሳቀች።

"ግደይ እኮ የመሰለውን ከመናገር ወደኋላ አይልም። እኔን ግን የአቢኢዮም ሆነ ሰሎሞን ምንም የተናገሩኝ ነገር የለም"

ግደይ ቀልደኛ ነው። ከዚህ በፊትም ኃይል ስምንት ውስጥ ሆኖ ወደ ራስ ዳሽን አካባቢ ሲወጡ የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊው በከር ዳገቱን ለመውጣት በጣም ደከሞት እየው፣ ግደይ ጨዳር ከላይ ሆኖ " ጓድ በከር አይዞህ ሳብ ሳብ አድርግ፤ ዳገት መውጣት እንደ ፖለቲካ ውይይት አይደለም" ብሎ ቀለደበት። በዚህ የተነሣ መንገድ የደከመው የፖለቲካ ሐላፊ እንደ በከር አትሁን ይባል ጀመር። የከተማ ልጆች መናገር እንጂ ዳገት አይሆናችሁም ማለቱ ነው።

"መስሎሀል! ድርጅቱ እኮ ውስጥ ለውስጥ ነው የሚሠራው። ጠርጥረውንም ሊሆን ይችላል። የለያዩንም በዚሁ ምክንያት ይሆናል። ከእንግዲህ መለያየቱ አልቀረልንም። ከአሁን በኋላ ፍቅራችንን መቀጠል የምንችለው በሕይወት ተርፈን ለመገናኘት ከበቃን ብቻ ነው። ከአሁን በኋላ ተራርቀን ነው የምንኖረው" አለች ትካዜ በገጽታዋ ላይ እያንዣበበ።





"ብንራራቅም እስከምንጊዜውም ድረስ እንደምወድሽ እንድታውቂልኝ እፈልጋለሁ። ሕይወታችን በፍቅር ተሳስሯል። ትናንት ሌሊት ጦርነት ላይ ያ ሁሉ ጥይት እየዘነበ፣ "አማኑኤል የት አለ?" እያልሽ በቀጥታ ወደእኔ ስትመጪ ምን ያህል እንደምትወጂኝ አወቅሁ። ይሄን ደግሞምንጊዜም አልረሳውም። ከዚህም በተጨማሪ በአድዋ በረሐ በማይ ምሻም ተራራ ለብቻችን ያሳለፍነውና የተነጋገርነው ሁሉ ትዝታው እስከሕይወቴ ፍጻሜ አብሮኝ ይኖራል። ለፍቅር እንግዳ መሆኔንና ምንም እንደማላውቅ እያወቅሽ ሁሉንም ነገሬን በትዕግሥትና በፍቅር እያየሽ ተቀብለሽኛል" በማለት ለእሷ ያለኝንም ፍቅርና ክብር ምንም ሳልደብቅ በግልጽ ነገርኳት።

"አንተ ልጅ አባክህ ተወኝ፣ አታስለቅሰኝ። ዛሬ ግን ምን ሆነህል? አነጋገርህ ሁሉ ተለይቶብኛል፤ ትዛዜ አስመሰልከው እኮ" አለችኝ።

"ከአሁን በኋላ የምንገናኝ አይመስለኝም፤ ከየአቢኢዮና ከሕብስቱ የበለጠ ጀግና የለንም። አየሽ ትናንት አብረን ነበርን ዛሬ ተለይተውናል። የእኛም መገናኘት የመጨረሻው ይመስለኛል። የአዲሱ ጋንታ መሪ ከምሆን እዚሁ ምክትል ጋንታ መሪ ሆኜ ብቀመጥ ይሻለኝ ነበር" ብዬ መሬት መሬቱን እያየሁ ዝም አልኩ። እሷም በኃሳብ ተውጣ ዝም አለች። ለትንሽ ጊዜ በመካከላችን ጸጥታ ነገሰ። የሁለታችንም አእምሮ የመጨረሻ ቀናችን መሆኑን የተቀበለ መሰለኝ።

ቀድማ ጸጥታውን የሰበረችው እሷ ነበረች። ምንአልባት ወሬ ለመቀየር ብላ ይሆናል። "አማኑኤል! እስቲ ኮረብታው ላይ ውጣና የከተማውን ርቀት እየው። ደግሞም አካባቢውንም መቃኘት ጥሩ ነው። የኢሕአፓ ነገር እኮ አይታወቅም፤ ተደብቀው ሊሰልሉንም ይችላሉ" አለች።

እኔም ደነገጥኩና ወዲያው ከላሸኔን አንሥቼ ኮረብታው ላይ ወጣሁና ዙሪያውን መመልከት ጀመርኩ። ከተማው እኔ ከገመትኩት በላይ ትንሽ ራቅ ብሎ ይታያል። ካለንበት ቦታ በቅርበት የሚታይ ምንም መንደር የለም። የሚታዩት መንደሮች ሁሉም ራቅ ያሉ ናቸው። የሚሰልልም የሚመለከትም የለም። ከኮረብታው ላይ ሆኜ የከተማውንና የመንደሮችን መራቅ ነገርኳት። በዙሪያችን

የሚንቀሳቀስ የሰው ፍጡር የሚባል ነገር ምንም እንደሌለ አረጋገጥኩላትና ተመልሼ ወደ እርሷ ሄድኩ። ሙሉ ፈገግታ እየሰጠችኝ በዝምታ ታየኛለች።

ስሙን የማላውቀው አንድ አበባ አለ፤ ፀሐይ ሲያገኝ ይፈካል። ድላይም ከእኔ ጋር ነጻ ሆነን ከተገናኘን እንደዚህ አበባ ነው ፊቷ የሚፈካው ብዬ አሰብኩ። ደስታዋና ሳቋ በጣም ያምራል። ልብሶቻችንን እንደገና አገላበጥንና ቅማሎቹን አራግፈን፣ የቅማል መሸሸጊያ ቦታዎችን ከፋፍተን ፀሐይ እንዲመታቸው መልሰን አሰጣናቸው። ከዚያም ከወንዙ በስተቀኝ በኩል የወንዙን መውረጃ አቅጣጫ ተከትለን፣ ወደታች ወረድን።

በግራና በቀኝ በኩል ትላልቅ ዛፎች አሉ። በለምለም ቄጠማ የተዋበውን አካባቢ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው አበቦች አፍከትውታል። ቄጤማዎችም በርካታ ናቸው። ውሃው እኛ ከነበርንበት ቦታ ላይ ይጠራቀምና ታች ሲደርስ ፏፏቴ ሆኖ እየዘለለና ድምፅ እያሰማ ይወርዳል። ትንሽ ራቅ ሲል ደግሞ ጥቅጠቅ ያለው ደን ወደገደሉ ይዘልቃል። ከዚያ በኋላ ብዙ ርቀን እንዳንሄድ ሰግተን በፏፏቴው አጠገብ ጎን ለጎን ተቀመጥን።

ስለጉዟችን መነጋገር ጀመርን። “ጎንደር መሄድህ ጥሩ ስሜት አልፈጠረብህም?” አለች።

“በአንድ በኩል ድርጅቱ በእኔ ላይ ትልቅ እምነት አሳድሮብኝ ነው፣ ለብቻዬ ጋንታ ይዤ እየመራሁ እንድሄድ የወሰነው፣ ብዬ ሳስብ ደስ ይለኛል። ደግሞ ሮባና ጌራም እዚያ ስላሉ እነሱን እንደማገኝ ሳስብም ደስ ይለኛል። በጣም ቅር የሚለኝ ግን ከአንቺ መለያየቱን ሳስበው ነው”

“እንዴት?”

“እንዴት፤ እንዴት ትይኛለሽ?! የእኔና አንቺ እምነትና አንድነታችን እኮ ከትግል በላይ ሆኗል። እንደዚህ ከቀረቡት ሰው ጋር ደግሞ መለያየት ስሜትን ይነካል” አልኳት። ቆጣ ማለቴ ታውቆኛል።





“አሁንስ እንደ ፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎቹ ለፍላፊና ፖለቲከኛ ሆነህል” አለችና መሳቅ ጀመረች።

“እኔ የምለፈልፈው አንቺ ፊት ስሆን ነው እንጂ፣ እነሱ ጋማምንም አልናገርም፤ አፌን ዘግቼ ጸጥ ነው የምለው። እኔ እንዲያውም ውይይት ሲጀምሩ ጥበቃ ወይም ዋርድያ መውጣት ነው የምመርጠው። ሁሌም ከነገራቸው መራቅ ነው የምፈልገው” አልኩ ቀልዷን በቀልድ ለመመለስ።

“ለመሆኑ በየት በኩል ነው የምትሄዱት?”

“ሁለቱንም መንገዶች አውቃቸዋለሁ። በሰቆጣና በተንቤን በኩል ያለ ችግር መሄድ ይቻላል። ነገር ግን አመራሩ በሚወስነው መንገድ ነው የምንሄደው”

አሁን ጥያቄዋን አቁማ ዝም አለች። ሳያት ገፅታዋ ተረጋግቶ ዓይኖቿ ፍዝዝ ብለው በዝምታ ቆየች። እንደገና ወደእኔ እየተመለከተች ለመናገር የፈለገችው የጠፋባት ወይም የጨነቃት በሚመስል ሁኔታ በረዥሙ ተነፈሰች። “ብዙ ነገር ስላስለመድከኝ መለያየቱ ለእኔ የሚከብደኝ ይመስለኛል። ትግል ውስጥ ከገባሁ ጀምሮ እንደአንተ ያመንኩትና የወደድኩት ሰው የለም”

“ናፍቆትና ትዝታውማ ካንቺ የባሰ ለእኔ ይከብደኛል”

“ለእኔ የበለጠ የሚከብድብኝ ይመስለኛል”

“እኔ እኮ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያፈቀርኩሽ አንቺ ብቻ ነሽ። በፍቅር፣ሌላ ሴት አላውቅም። ሴት ልጅ ትወደኛለች የሚል እምነትም አመለካከትም አልነበረኝም። ራሴን ከሰው በታች አድርጌ ነበር የምገምተው…” ብዬ ንግግሬን ሳልጨርስ ተቆጥታ ፊቷ ተለዋወጠ ።

“አማኑኤል! እንዲህ ዓይነት አመለካከትማ ኋላ ቀር ነው። አንተ ምን ይጎድልሀልና ነው!? በድህነት ማደግህ ከሆነ እሱ ወንጀል አይደለም። ድህነት ሥርዓቱ ያመጣብን ችግር ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሀ መሆኑን መርሳት የለብህም። ደግሞስ ወደትግል የወጣንበት ዋናው ምክንያት በሥርዓቱ

ምክንያት አልላቀቅ ያለንን የሀገራችንን ድህነት በመቃወም አይደል። ትናንት ባደረግነው ጦርነት፣ የተሠውት ጀግኖች በሙሉ እኮ ለድህነታችን ተጠያቂ ከሆነው የመንግሥት ሥርዓት ጋር በመፋለም ነው። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ሥርአቱ የጣለብህን የአስተሳሰብ በሽታ ከጭንቅላትህ አውጥተህ መጣል አለብህ። በድህነትህ እንድታፍር ያደረገህ እኮ ያደግክበትና ዛሬም ያለው አስተሳሰብ በተዘዋዋሪ መንገድ ለድህነትህ እኔ ሳልሆን አንተ ነህ ተጠያቂ ብሎ ለማሳመን የፈጠረው የስነ ልቦና ጦርነት ክፍል ነው። ስለዚህ ሁለተኛ እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ መተውና ከሌሎችም ላይ እንዲጠፋ መታገል ነው ያለብን" በማለት ስለድህነት ተንትና አዲስ አስተሳሰብ እንድይዝ መስመሩን አሳየችኝ።

ከተቀመጥንበት ተነሣንና እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደ ኮረብታው ሄድን። ልብሶቻችንን አነሣንና መለባበስ ጀመርን። አሁን በጣም ስለተለማመድን ልብሷን ለመቀየር ከለላ አልፈለገችም። ዘና ብላ ምንም ሳይመስላት ሰውነቷ እያየሁት አጠገቤ ሆና መለባበስ ጀመረች።ሰውነቷን ስመለከተው ልቤ ስትመታ ይሰማኛል። አከላቷ በጣም ይማርካል።

ከለበስን በኋላ እጅ ለእጅ ተያይዘን ስንወርድ የሰውነቷ ሙቀት በእጇ በኩል አልፎ ወደ ሰውነቴን የተለየ ሙቀት ዘራበት። ጎተት ሳደርጋት ተጠጋችኝ፤ ሳቅፋትም አቀፈችኝና በጣም ተጠጋግተን ቆምን። በመካከላችን ምንም ያህል የቦታ ርቀት ቢኖር እንደማንረሳሳ ተማማልን። ጉንጪን ሳምኳትና ያሳለፍናቸውን ሁኔታዎች እያስታወስን አወራን።

"በጣም ነው የማፈቅርሽ፤ ከአሁን በኋላ በሕይወት ባንገናኝ እንኳ እስከ ዕለተ ሞቴ አስታውስሻለሁ፤ ፍቅርሽም እስከመጨረሻው አብሮኝ ይኖራል" ስላት እንደማፈር አይነት ሳቅ አለች። አይን አይኔን ስታይ የእኔ አይኖች ወደ ከንፈሮቿ ወረዱ። ጠጋ አልኩና ሳምኳት። ለደቂቃዎች ያህል ወደ መንግሥተ ሰማያት የገባሁ እስኪመስለኝ ድረስ የት እንዳለሁ ዘነጋሁት ሌላውን ዓለም





ትቼ ከከንፈሮቿ የሚመጣልኝን ልዩ መልእክት በስሜት እያጣጣምኩ በፍቅር ጥልቅ ስሜት ወስጥ ሰመጥኩ።

"አማን! በጣም ነው የምወድህ!! ፍቅርህ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ምንም ነገር ላይሽረው ልቤ ውስጥ ታትሟል" ብላ ልዩ ስልት ባለው የፍቅር ቋንቋ ቀስ እርጋ ከሄድኩበት መለሰችኝ "ከዚህ በላይ ለአንተ ያለኝን ከባድ ፍቅር እንዴት ልገልጽልህ እንደምችል አላውቅም" አለች በሹክሹክታ።አፏን ጆሮዬ ስር አስጠግታ የተስለመለሙትን ዓይኖቿን ለመመለስ እየሞከረች።

"ድላይ! ምን መግለጽ ያስፈልጋል?! ይኸው በተግባር እያየሁት አይደለም እንዴ!! በድላይ ምንም ጥርጣሬ የለኝም። ብቻ በሕይወት ለመገናኘት ያብቃንና መጨረሻችንን ያሳምረው እንጂ!!" አልኳት።

ቀድመን ደጋግመን ያነሣነውን ፍርሃታችንን አሁንም ደገመችውና "ከአሁን በኋላ እኮ ላንገናኝ እንችላለን" አለችና መልሴን ሳትጠብቅ "ከአሁን በኋላ ባንገናኝም እንኳ፣ እኔና አንተ በዚህ ትግል ውስጥ የማይረሳ ታሪክ አሳልፈናል። ለፍቅራችንም በመጠኑም ቢሆን ቦታ አግኝተንለታል። አብሮ መዋል፣ አብሮ ማደር፣ አብሮ በፍቅር ማሳለፍ፣ አብሮ ጦርነት መዋል፣ አብሮ መሳቅ፣ አብሮ ማልቀስ፣ ልብ ለልብ መቀራረብና መተማመኑን ይህን ሁሉ ሌሎች ጓዶች ለማግኘት ያልቻሉትን ዕድል ነው ያገኘነው።

"የዛሬውም ዕድል እኔና አንተ ሆን ብለን የፈጠርነው አይደለም። ጓዶቻችን ለማዳንና ሬሳቸውን በጠላት እጅ እንዳይወድቅ ስንል ተሸከመን ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ስለማስንንና ደም በደም በመሆናችን የተሠውት ጓዶች የሰጡን ልዩ ስጦታ አርገን ነው መውሰድ ያለብን።

"የነበለትም ቢሆን የታወቀው የሴትነት ተፈጥሮ ያስከተለው ሁኔታ ነበር ዕድሉን የሰጠን እንጂ ሆን ብለን ያደረግነው አልነበረም። ጓዳዊ መተሳሰቡ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በፍቅር አጀበን። ይህ ደግሞ የበለጠ የምንተሳሰብና

የምንተማመን አደረገን። የጀመርነው ፍቅር የተመሠረተው ትግሉና ለትግሉ ባለን ፍቅር ላይ ስለሆነ ደስ ሊለንና ሊያበረታን ይገባል።

"ስለዚህ ብንገናኝም ባንገናኝም እኔ እንደማልረሳህና አንተም እንደማትረሳኝ አምናለሁ። በያለንበት ሆነን መጠንከር ይገባናል። እኔ አማኑኤል ተሠውቷል ካልተባለ በስተቀር ካንተ ሌላ ማንንም አላስብም" በማለት እየተናገረች እንደገና ሐዘን ውስጥ ገባችና ዓይኖቿ ዕንባ ቋጠሩ።

"አይዞሽ" አልኩና አቀፍኳት

"አማኑኤል ጀግና ነው ሲሉ እሰማ ነበር። በደንብ ያረጋገረጥኩት ትናንት በዓይኔ አይቼ ነው። አንተና ሀጎስ ማንጁስ ጦር ሰፈሩ አፍንጫ ስር ሆናችሁ፣ የሮምሀን ሬሳ ላለማስነካት እኛ እስከምንደርስ ድረስ ጥይት እንደዝናብ እየወረደባችሁ ስትታኮሱ ቆይታችሁ ጠላትን አላፈናፍን ብላችሁ ሳታስጠጉ ነበር እስከመጨረሻው የተጋፈጣችሁት። አሁን ደግሞ ለብቻህ ጋንታ እየመራህ ጸለምት ድረስ መሄድ ቀላል አይደለም። ድርጅቱ ይህን ሐላፊነት የሰጠህ ጀግንነትህንና ጽናትህን አምኖ እንደሆነ ምንም አያጠራጥርም። ለኔ ይሄም ሌላ የጀግናነትህ ምስክር ሆኖኛል። ስለዚህ ጀግና በማፍቀሬ ትልቅ ኩራት ይሰማኛል" አለች።

"አሁን ደግሞ አንቺ የቁም ኑዛዜ እያደረግሽ ትመስያለሽ። ሞት ማንን እንደሚያስቀድም፣ ማንን እንደሚያስከትል፣ አናውቅም። ቢሆንም ግን እኔ የአንቺን መሠዋት መስማት አልፈልግም።በተለይ ይህቺ ቀን የመጨረሻችን ከሆነችና "ድላይ ተሠዋች" የሚል ወሬ ከሰማሁ ሐዘኑን አልችለውም። በሕይወቴ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደወንድ እንድኮራ ያደረግሺኝ አንቺ ነሽ። ፍጹም የሆነ እውነተኛ የጾታ ፍቅር ባንቺ አይቻለሁ። ነገር ግን ሕይወታችን በሙሉ ከድርጅታችንና ከጓዶቻችን ጋር የተሳሰረ ነው ያልሽኝ እውነት ነው። ዓላማችንን ባናስቀድም ኖሮ እንዲህ ዓይናችን እያየ በዚህ ቦታ ለመጨረሻ ግዜ አብረን ሆነን ለመለያየት አንፈቅድም ነበር" አልኳት። ቢሆንም ግን ሳለመላቀቅና ቢቻል





የዛሬዋን ግንኙነት ለማራዘም መሞከር ፈልገናል። ስለዚህ ከቻልን የዛሬን ማታ አብረን አድረን በማግስቱ ወደጓዶች ለመሄድ የሚቻልበትን መንገድ ለመሞከር ወሰንን።

ቀኑ ሊመሽ ፀሐይ መጥለቅ ጀምራለች፤ ፍሱሕም ተመልሶ አልመጣም። ለማንኛውም ወደ ኮረብታው ወጥተን የአካባቢውን እንቅስቃሴ እንይ ብለን ኮረብታውን መውጣት ስንጀምር ሁለት የእኛ ሚሊሻዎች መጡ። ፍሱሕ አልነበረም። አንደኛው ሚሊሺያ ቀን ምሳ ሲያመጡልን ከፍሱሕ ጋር አብሮ ነበረ። ቀረብ አለና "መልእክት ይዘን ነው የመጣነው" አለ።

"ምን መልእክት ነው?"አልኩት።

"ሠራዊቱ ወደሰሜን እየተንቀሳቀሰ ስለሆነ፣ ቶሎ ብላችሁ ወደአሉበት መንደር እንድትደርሱ ተብላችኋል"

"አሁን በቶሎ ካልተነሣችሁ ሠራዊቱ ስለተንቀሳቀሰ ያላችሁበት ቦታ ጸጥታው አስተማማኝ አይሆንም" አሉን።

መልእክቱን ተቀብለን ከተማ ውስጥ ሳንገባ ወደሠራዊቱ ለመሄድ ያለንን አማራጭ ለማወቅ ፈለግን። ከሚሊሺያዎቹ አስፈላጊውን መረጃ ወሰድንና እንደምንሄድ ነግረን አሰናበትናቸው። እኛ ግን ያ ዕለት የመጨረሻችን ነው ብለን ስለአሰብን አብረን አድረን ለመሄድ ወስነናል። ጓዶቻችንም ከዚህ በፊት ጠፍተን አድረን እንደተመለስን ያወቃሉና ብዙም እንደማይረበሹ ገመትን። ወደ ሰሜን በኩል ከሄድን ከሠራዊቱ ጋር እንገናኛለን፤ ስለዚህ፣ ትንሽ መሸት አድርገን ጨለማው ሲጀምር ወደ ምሥራቅ በኩል ሄደን ባገኘነው መንደር እንድናድር ተስማማን። እስኪመሽ ድረስ ሙሉ ትጥቃችንን ይዘን ተዘጋጅንና ኮረብታው ላይ ወጥተን ተቀመጥን። ከዚህ በፊት አብረን ያደርንባቸውን ለሊቶች እያስታወስንና፣ በናፍቆት የተሞሉ ወሬዎችን እያወራን ቀኑ እስከሚጨልም ጠበቅን።

"ዛሬ በመጨረሻው ቀናችን አብረን ስናድር እንቅልፍ ይወስደን ይሆን?" አልኳት።

"እኔ እንጃ! እኔ ግን የሚወስደኝ አይመስለኝም። እንዲያውም ቶሎ የሚነጋብን ይመስለኛል። አማኑኤል! ዛሬ ግን በደንብ አቅፈኸኝ ነው የምናድረው" አለችኝ።

"እኔም አቅፌሽ የሚወጣልኝ፣ እንቅልፍም የሚወስደኝ አይመስለኝም። እኔ እንደሆንኩ እዚህ ያለንበት ኮረብታ ላይ ብናድርም ምንም አይመስለኝም" ስላት የሚያማምሩ ትናንሽ ጥርሶቿ ተፈልቅቀው በፍቅር ፈገግታ ፈካች። ዓይኖቿ ከብለል ከብለል እያሉ በስስት ይመለከቱኝ ነበር። ቀኑ አልጨልም ብሎን ትንሽ እየመሸ በሄደ ቁጥር ልባችን ትር ትር እያለ፣ አይን ለአይን በስስት እየተያየን፤ ኮረብታው አናት ላይ ተቃቅፈን እንደቆምን ከኛ ጋር እልህ የተጋባውን እንደ ሌሊ የሚነትት ምሽት እንጠብቃለን። ለእኛ መጪው ሌሊት የመጨረሻ የናፍቆታችንን ምሽት ነበር ብቻችንን አብረን ሆነን ለማሳለፍ በጉጉት የምንጠብቀው ልዩ ጊዜ ሆኖብናል።

ኮረብታው ላይ ሆነን ተቃቅፈን እየተላፉንና እያወራን ግማሽ ሰዓት ያህል እንደቆየን ፍሱሕ ገብራይ መጣ። የመጣበትም ምክንያት ቶሎ ተንቀሳቀሱ ተብለን መልእክት ተልኮብን ስላልሄድንላቸው ሁኔታችንን ለማረጋገጥ ነበር።

መልእክቱ እንደደረሰን አረጋግጠንለት፣ ዛሬ ግን ለመለያየት የመጨረሻ ቀናችን ስለሆነ አብረን እየተጫወትን ለማደር እንደፈለግንም ነገርነው። "እሺ" ብሎ ተስማማና "እኔም እኮ የእኛ ሚሊሺያ ጓዶች ራት ጠርተውኝ፣ አብረውኝ የዋሉ ሁለት ጓዶች እንዳሉ ስነግራቸው ይዣችሁ እንድሄድ ነግረውኛል" ብሎን በሃሳቡ ተስማማን። በምሥራቅ በኩል አድርገን ወደ ሰሜን በመሄድ ወደከተማ ለመግባት ተነሣን። "እራት ከበላን በኋላ ወይ ለብቻችን እናድራለን ወይም ወደ ጓዶች





እንሄዳለን" አለን። ፍሱሕ ከፊት ድላይ ከመካከል እኔ ደግሞ ከኋላ ሆነን እንደተጋዳይ በተፈናተት ሆነን መንገድ ጀመርን።

ፍሱሕ ገብራይ ኃይሎች የነበሩበትን ቦታ ያውቃል። በጸጥታው በኩል ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ተረድተናል። ትንሽ እንደተጓዘን ምሽቱ በደንብ ጨለመ። አንድ ሰአት ላይ ነበር። በቅርብ ካልሆነ በስተቀር ሰውን ለማየት ያስቸግራል።

አሁን የሰዎች የኮቴ ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ። በእኛ ግምት ጓዶች ቀድመው ወደ ሰሜን አቅጣጫ አልፈዋል። ነገር ግን አንድ ጋንታ ወደ ኋላ ቀርታ እየተጓዘች ነበር። እኛ ወደ ምሥራቅ ስንሄድ እነሱ ወደሰሜን እየሄዱ እያሉ ፊት ለፊት ተገናኘን። ይቺ በመጨረሻ ላይ በመጓዝ ላይ የነበረችው የእነ ድላይ ጋንታ ነበረች። የገባንበት መስመርም በቀጥታ ወደ ጋንታ መሪው ወደ ቴዎድሮስ ባሪያው ጋ አደረሰን።

ቴዎድሮስ ባሪያውም ወደአለንበት ወደ ግራው ዞር ብሎ ድላይን "ወደጋንታሽ ግቢ!" አላት። በጣም ደነገጥኩኝ። ምክንያቱም ባላሰብንበት ወቅትና ባልገመትነው ሁኔታ ነበር ያገኘናቸው።

ድላይም እንደኔው ደንግጣ ቴዎድሮስ ያለውን ሰማችና "እናንተ ሂዱ፣ እኔ ከአማኑኤልና ከፍሱሕ ጋር አብረን ስለዋልን አብረን እንመጣለን" አለችው።

"ቀን አብራችሁ ውላችኋል፣ አሁን ግን መሽቷልና ወደጋንታሽ ግ ቢ፣ ካሁን በኋላ ከእነሱ ጋር የምትሄጂበት ጉዳይ የለሽም" ብሎ ጥያቄዋን በትእዛዝ ገታው።

ምንም ማድረግ ስለማትችል ወደ ጋንታዋ እየገባች ወደ ኋላ መለስ ብላ የግራ እጇን እያወዛወዘች ምንም ቃል ሳትናገር በምልክት ብቻ ተሰናበተችኝና ፊቷን በንዴት ኮስተር አድርጋ ወደ ጋንታዋ ተቀላቀለች።

እኔ ምንም ሳልንቀሳቀስ ባለሁበት ቦታ በድን ሆኜ ፍዝዝ ብዬ አያታለሁ። ምንም ቃል አልተናገርኩም። ከቴዎድሮስ ጋር በቀጥታ ባትገናኝ

ኖሮ ምክትል ጋንታ መሪ ስለሆነች ሌላ አባል ትእዛዝ ሊሰጣት አይችልም ነበር። ፍሱሕ ገብራይ ቀጥታ ወደ ጋንታዋ ቀጥሎምቴዎድሮስ በነበረበት ቦታ ላይ የወሰደን አውቆ ይሁን በአጋጣሚ እሱና ቴዎድሮስ ባሪያው ብቻ ናቸው የሚያውቁት። ቴዎድሮስ ባሪያውና ፍሱሕ ገብራይ ዛሬም በሕይወት አሉ።

ቀኑን ሙሉ አብረን ውለን የመጨረሻውን ሌሊታችንን አብረን ለማሳለፍ ብዙ ተመኝተን ነበር። ጉጉታችን እንደዋዛ በአፍታ ውስጥ፣ ባላሰብነው ሰዓትና ቦታ ውኃ በላውና የህልም እንጀራ ሆነ። ከውቅሮ ከተማ በሰተምሥራቅ በኩል ያሉ ተ ራራዎችን አልፎ የሚገኘው አጽቢ የሚባለው ትንሽ መንደር ከድላይ ጋር ዱብ እዳ የወረደብን ቦታ ስለሆነ በሕይወቴ ሁሉ አልረሳውም።

ድላይ ከጋንታዋ ጋር ተቀላቅላ ስትሄድ ከዓይኔ እስኪጠፉ ድረስ ተመለከትኳቸው። ፍሱሕ ሁኔታዬን ስለተረዳ አጠገቤ ቆሞ ምንም ሳይናገር ይጠብቀኛል። እስከሚታዩኝ ድረስ በአይኔ ሸኝቼያቸው ሳበቃ ወደ ፍሱሕ ዞሬ ለመሄድ ተዘጋጀሁ።

ምሽቱ በጣም ጨልሞ ነበር፤ ከተማ እንደደረስን ተኩስ ሰማን። ፍሱሕን የከተማው ሰዎች ስለሚያውቁት፤ ተደናግጠን ተኩስ ወደሰማንበት ቦታ ሄድንና ሁኔታውን አረጋግጠን እራት ወደተጋበዝንበት ቤት ሄድን። እንደገባንም በአገሩ ባህል ጥሩ የሚባል ምግብ ተዘጋጅቶ ነበረና ቀረበልን። እኔ ግን ከድላይ ጋር ባልፈለግንበት ቦታና ጊዜ ስለተለያየን በጣም አዝኜ ስለነበረ የምግብ ፍላጎቴ ተዘግቷል። በሐዘን ላይ ሌላ ሐዘን ተጨምሮብኝ ከፍቶኛል፤ ያን ስሜቴን ሁሉም ከፊቴ ላይ አንብበዋል። እንደምንም ብዬ ትንሽ ጎራረስኩና ኃይሎች ያሉበትን ቦታ ፈልገን ከእነርሱ ጋር ለማደር ተነሥተን ወጣን።

ከከተማው የአንድ ሰዓት መንገድ እንደተጓዝን አንድ ጋንታ አገኘን። የኃይል ስልሣ ስድስት ጋንታ ነበረች። ስንደርስ ምሽቱ ገፍቶ ከእኩለ ለሊት





አልፏል። ከጋንታዋ ጋር ለሊቱን አሳልፈን፣ በነጋታው ጠዋት ወደኃይል አምስት መቶ ሄጄ ከጋንታዬ ጋር ተቀላቀልኩ።

***

## *ጋንታ ሀያ ስድስት*

ወደ ኃይል አምስት መቶ ተመልሼ ወደ ጋንታዬ በሄድኩ በማግሥቱ የኃይሏ የፖለቲካ ሐላፊ ሰሎሞን መጣና "ወደ ጎንደር ከምትሄደው ጋንታ ስለምትገባ፣ ትጥቅህን ለነበርክበት ጋንታ አስረክብ" አለኝና በእኔ ቦታ ለተመደበው ለሀጎስ ማንጁስ አስረከብኩ። የግደይ ጋንታ ምክትል መሪ የነበረው ብርሃኑም በጋንታ መሪነት ተመድቦ ወደ ኃይል አርባ አምስት መሄድ ነበረበት። የኃይል አምስት መቶ ምክትል የፖለቲካ ሐላፊ የነበረው ከሡተ ደግሞ ወደ አሲምባ የሚሄድበት ጉዳይ ነበረው። እኔም ጋንታ ሀያ ስድስትን ለመቀላቀል አሲምባ መድረስ ነበረብኝ።

ስለዚህ ሦስታችንም ከኃይል አምስትመቶ ወጥተን አብረን ተጉዘን ከሁለት ቀናት በኋላ አሲምባ ደረስን። አሲምባ ስንደርስ አመራሩ ዳህዋን ስለነበረ እኔ ወደ ዳህዋን ሄድኩ። የጋንታ ሀያ ስድስት አባላት ብዙዎቹ በውቅሮ ተልእኮ ተካፍለው ስለነበር ከልአሳ ላይ እየተሰባሰቡ እንደሆኑ ተገረኝ፡፡ የተሰባሰቡትንና የቀሩትንምጨምሬ ይዣቸው እንድመጣ ታዘዝኩና ከዳህዋን ወደ ከልአሳ ተጓዝኩ። ከልአሳ የጋንታዋ ምክትል መሪ አንተነህንና እንዲሁም ከቡልጋሪያ መጥቶ ሠራዊቱን የተቀላቀለውን · የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊውን ሽርሳዊን አገኘኋቸው። እነርሱም የሚጠብቁት እኔ ከኃይል አምስት መቶ እስክመጣ ነበርና ጥር 20 ቀን፣ ከአዲሷ ጋንታ ሀያ ስድስት ጋር ተቀላቀልኩ።

ከሦስት ቀናት በኋላ ከለአሳ ሕክምና ከሚሰጥበት ጣቢያ ወደ አቦይ ምስግና ቤት ጌትነትን ለመጠየቅ ሄድኩ። ጌትነት እኔ የነበርኩበት የኃይል አምስት መቶ ኃይል መሪ ነበረ። እንዲሁም ከኃይል ሦስት ጋር ወደ ጎንደር ስንሄድ፣ ጌትነት ምክትል ኃይል መሪና እኔ የነበርኩበት ጋንታ መሪ ሆኖ እኔ ምክትሉ ነበርኩ። በውጊያ ላይ ቆስሎ ሕክምና ሲደረግለት ቢቆይም ህመሙ በጣም እንደጸናበት ስለሰማሁ ነበር ልጠይቀው የሄድኩት።





ከዳውሃን ወደ ከልአሳ ብቻዬን እንዳልሄድ ብዬ የእኔ ጋንታ አባል የሆነውን አዋሽ ኃይለ ማርያምን ይዤ ሄድኩ። አቦይ ምስግና ቤት ሄጄ ህመምተኞቹ መሐል ብፈልገው አጣሁት። "የት ሄደ! ሞተ እንዴ?" ብዬ ስጠይቅ በሕይወት መኖሩን ተረዳሁ። ነገር ግን በጣም ስለደከመ ወደታችኛው ቤት እንደተዘዋወረና ማንም ወደ እሱ እንዳይገባ መከልከሉን ነገሩኝ። ወደነበረበት ቤት ስሄድ ከልካይ የሚባል ነርስ ሲያስታምመው ደረስኩ። ከልካይን አላውቀውምለመጀመሪያጊዜ ነበር ያየሁት። "መግባት ክልክል ነው" አለኝ ከልካይ።

"ከእኔ ጋር አብሮ የነበረ ጓዴ ነው! አጠገቤ ሆኖ ነው የቆሰለው! ለምንድነው ለማየት የማልችለው?!" ብዬ ስቆጣ፣ ዝም አለ። እኔም አልፌው ገባሁ።

ወደተኛበት ፍራሽ ጠጋ ብዬ ጌትነትን ሳየው ሰውነቱ አልቆ በአጽም ቀርቷል። እርሱ መሆኑን የሚናገረው መልከ መልካም የፊቱ ገጽታ ብቻ ነበር። በግማሽ እንደሚስቅ ሰው አፉ ከፈት ብሏል። ጎፈሬ የነበረ ጸጉሩ ተላጭቷል። ቁስሉ በጣም በርትቶበት ሊቋቋመው አልቻለም። በድንጋጤ ፈዝዤ እያየሁት የበፊቱ ጌትነት ፊቴ ላይ ድቅን ሲል ዓይኖቼ ዕንባ አቀረሩ። ያ ጥይት የማይፈራው ጀግናው ጌትነት፤ አስተዋይ፣ ረጋ ያለና በሳል የአመራር ችሎታ የነበረው ጌትነት፣ ከእባብና ከዘንዶ ጋር እየተሯሯጠ ድብብቆሽ መጫወት የሚወደው ጌትነት ታየኝ።

የማየው ጌትነት ደግሞ ኮስምኖ፣ ከሰውነት ጎዳና ወጥቶ፣ በሰው እጅ እየተገላበጠ ለመሞት ደቂቃዎችን የሚቆጥር ጌትነትን ነበር። ግንባሩን ለመሳም ጎንበስ አልኩ፣ ከንፈሮቼ ግንባሩ ላይ ሲያርፉ የዕንባዬ ጠብታዎች የበሽተኛ ልብሱ ላይ ዱብ ዱብ አሉ፤ ከዚያም የሚተናነቀኝ ሲቃ ጥሶ ወጣና ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ።

ከልካይም ሁኔታዬን እንደተመለከተ "ጓድ ማልቀስ አይፈቀድም!" ብሎ ለመኮሳተር እየሞከረ፣ ከንዴን ይዞ አስወጣኝ።

ያን ቀንና ሌሊት ጌትነት ዓይኔ አልጠፋ ብሎ ስለርሱ ሳስብና ስጨነቅ ውዬ አደርኩ። ጌትነት ወደ አሲምባ የመጣው ከአየር ወለድ ጓደኞቹ ጋር ነበር። በ1969 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ጌትነት የኃይል ሦስት የኃይሌ ቀጮት ምክትልና በተጨማሪም እኔ የነበርኩበት ጋንታም መሪ ስለነበረ በቅርበት አውቀዋለሁ። በአርባያ ውጊያ ላይ ብዙ ትርምስ ሲከሠት በጌትነት የምትመራው ቡድን አንድም ጓድ ሳይሠዋባት ግዴታዋን ፈጽማ ለመውጣት የቻለችው በጌትነት ብቃት ነበር።

ጌትነት ለተሠዉ ጓዶች ያዝንና ይተክዝ የነበረባቸውን ጊዜያት አስታወስኩና አሁን እርሱ ያለበትን ሁኔታ ሳስበው ሆዴን በላኝ። ምነው እንዲህ እየተሰቃዩ ከማየው እዚያው ውጊያ ላይ በተገላገለ ኖሮ! ብዬ አሰብኩ። ለጌትነት ያለኝ ትዝታ ብዙ ነው። እኔን ከድላይ ጋር የበለጠ እንድቀራረብ ያደረጉኝ እሱና የአቢኢዮ ነበሩ። ዛሬ የአቢኢዮ በሕይወት የለም፤ ጌትነትም ያለበት ሁኔታ ከመኖር አይቆጠርም። የአቢኢዮ ዳንግላት ላይ ተርፎ ውቅሮ ላይ ተሠዋ። ጌትነት ግን ዳንግላት ላይ እንደቆሰለ ታምሞ ቆይቶ አሁን ሕይወቱ መጨረሻ አፋፍ ላይ ነች። ከዚያ ከዳንግላት ጦርነት በኋላ ሕክምና ላይ እንዳለ ሰማሁ እንጂ ላየው ባለመቻሌ ቅር ተሰኝቼ ነበር። ዛሬ በዚህ አጋጣሚ ሳየው ደግሞ "ምነው ባላየሁት" አሰኘኝ። በጭራሽ የሚተርፍ አይመስልም፤ መትረፍ አይደለም አንድ ቀንም የሚያድር አይመስልም። በመጨረሻም ከ ሦስት ቀናት በኋላ ጥር 26 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

እንግዲህ የምወዳቸውን ጓዶቼን መሥዋዕትነት ነጥቆኛል፤ ዛሬ በሕይወት ብንኖርም ከድላይም ጋር ተለያይተናል፤ ነገ ለመገናኘትም ዋስትና የለንም፤ እንዲያውም የሚያመዝነው ተለያይተን መቅረታችን ነው። ልቤን ሐዘን አስቃየው።

***





በማግስቱ የጋንታ ሀያ ስድስትን የጎንደር ጉዞ አስመልክቶ እኔ፣ አብደላ፣ ጸጋዬ ደብተራውና ጌዲዎን ሆነን ስብሰባ ተቀመጥን። ጌዲዎን ስለጋንታ ሀያ ስድስት ተልእኮና ስለምትሄድበት ቦታ ነገረን። ጋንታዋ የምትሄደው የፓርቲ ሰነዶች (ዶክመንቶች)፣ የክላሽን ጥይቶች እንዲሁም ከጀብሀ እጃቸውን ሰጥተው የመጡ ዘጠኝ ሰዎችን ይዛ ጎንደር ለማድረስ ነው። ዘጠኙ ሰዎች በጎንደር አድርገው ከሀገር ውጪ የሚሸኙ ናቸው። በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ በጌምድር የተመደቡ ጓዶችም ስላሉ እነርሱም ከእኛ ጋር ወደ በጌምድር ይሄዳሉ። ስንቅና ትጥቅን በሚመለከት ደግሞለምለምናዳዊት እንደሚያደራጁልንና እኛም ተዘጋጅተን እንድንቆይ ተነገረን።

ከዚያም ጸጋዬ ጠራኝና የጋንታ ሀያ ስድስት አባላትን ዝርዝር ሰጠኝ። ሳየው የእያንዳንዱ አባል የፖለቲካ ሐላፊነትና የአባልነት ዝርዝር አለው። ስለእያንዳንዱ አባል ዝርዝር የፖለቲካ ድርሻ ሳይቀር የሚያትተውን ሰነድ ሳነብ ደነገጥኩኝ። ወደ ጸጋዬ ደብተራው ሄጄ "ይሄ መረጃ ለፖለቲካ ሐላፊ የሚሰጥ ነው፤ ለኔ የሰጠኸኝ ተሳስተህ ነው?" አልኩት። እኔ እንደዛ ማለቴ በአሠራራችን እኔ የሠራዊት አባል እንጂ የፓርቲ አባል ስላልሆንኩ፣ የፓርቲ አባላትን ማወቅ ስለሌለብኝ ነበር። እርሱ ግን "ይሁን፣ አውቄ ነው የሰጠሁህ። ግዴለም አንተ ያዘውና ለሸርሳዊ ትሰጠዋለህ" አለ።

አብደላም ከእኛ ጋር የተሰበሰበበት ምክንያት፣ ለየት ያለ ተልእኮ ተሰጥቶት አብሮን ስለሚሄድ መሆኑን ጸጋዬ ከስብሰባው በኋላ ነገረኝ። "አብደላ ለየት ያለ የፓርቲ ተልእኮ አለው፣ መንገዱንም በደንብ ያውቃል፣ የፓርቲ ግንኙነቱም ስለነበረው በመንገድ የሚረዷችሁን ሰዎችም ሊያገኝ ይችላልና ከእናንተ ጋር እንዲሄድ የተደረገውም በዚህ ምክንያት ነው" አለኝ። አብደላ ከኃይል ሦስት ጋር ወደ በጌምድር ስንሄድ ከእኔ ጋር በፈታውራሪ ጣሰው የተነሣ የተጣላውና የፖለቲካ ጉዳይ ሀላፊዬ የነበረው ነው።

"አሁን ግን አንተን ጠርተን ያነጋገርንህ፣ እስከአሁን ድረስ አንዳንድ ድክመቶች ነበሩብህ። የፓርቲ አባል ያልሆንከው በእነዛ ድክመቶችህ ምክንያት ነበረ። ከአሁን በኋላ ግን በፓርቲ አባልነት እንድትመለመል ተወስኗል እና በጌምድር ከመድረስህ በፊት የፓርቲ አባል ትሆናለህ።

"በመጀመሪያ በተሰጠህ ምድብ ወደበለሳ ከሚሄዱት ጓዶች ጋር ወደዚያው ትሄዳለህ። አንተ በለሳን ታውቀዋለህ እንዲሁም ከበለሳ ወደሌላ አዳዲስ ቦታዎችም ለመሄድ ይታሰባል። ምናልባት ከገበሬዎች ጋር ጦርነት ሊያጋጥም ስለሚችል አንተ ያለህ ልምድ እንደሚጠቅም ስለታመነበት ነው። በለሳን ዋና የጦር ሰፈር ለማድረግ ስለታሰበ ነው ለዚህ ተልእኮ የፈለግንህ" አለኝ።

ጸጋዬ ደብተራውን በጣም ስለምወደው "አሁን ጎንደር ከሄድኩ ላንገናኝ እንችላለንና አንተን ማስታወሻ የሚሆነኝ አንድ ነገር ስጠኝ" አልኩት። እሱም ሳቅ አለና ትንሽ ካሰበ በኋላ "እንካ ጠመንጃዬን ልቀይርህና ማስታወሻ ይሆንሀል" ብሎ ሰጠኝ። የእርሱን ወስጄ የእኔን ሰጠሁትና ተቃቅፈን ተሳሳምን። ሁለቱም የከላሽን ኮቭ ጠመንጃዎች ነበሩ፤ ምንም ልዩነት የላቸውም። ቢያንስ አንዳንዴ ጠመንጃዬን ሳይ ግን እሱን ያስታውሰኛል ብዬ በጣም ደስ አለኝ።

***





ጋንታ ሀያ ስድስት ከከልአሳ ዳህዋን መጥታ አመራሩን ለመጠበቅ እነርሱ ካሉበት ቤት ፊት ለፊት እንድትሰፍር ተደርጋለች። ከትንሽ ቀናት በኋላ በወርቁ የምትመራው ኃይል ወደ ከልአሳ መጣች። ወርቁ የውቅሮ ውጊያ ጠቅላይ መሪ የነበረ ነው። ከልአሳና ዳውሃን የሚለያዩት በመካከላቸው በሚያልፍ ወንዝ ነው። ከወንዙ በስተሰሜን በኩል ከልአሳ ሲሆን፣ በስተደቡብ ያለው ደግሞ ዳህዋን ነው። ስንቅና ትጥቅን በሚመለከት ከለምለም ጋር ተነጋገሩ ተብዬ ስለነበር ከዳህዋን ወደ ከልአሳ ሄድኩ። ከልአሳ እያለሁ ከአመራር አባሎች በአንዱ "ስለውቅሮ ውጊያ ሂስና ግለሂስ ይደረጋልና አንተም ውጊያው ላይ ስለነበርክ ስብሰባው ላይ መካፈል አለብህ" ተብዬ ወደ ስብሰባው ቦታ ሄድኩ።

ስብሰባው የተደረገው ከልአሳ ከአቦይ ገብራይ ቤት ፊት ለፊት በሚገኘው ትልቅ ቤት ውስጥ ነበር። ስብሰባውን የመሩት የአመራር አባሎች፤ አበጀ፣ ዳዊት ስዩምና ጋይም ነበሩ። በውጊያው ላይ በወገንም በጠላትም በኩል የነበሩት ጠንካራ ጎኖች ተዘረዘሩ። ወደ መጨረሻ አካባቢ የውጊያው ጠቅላይ ዋና መሪ ወርቁ መናገር ጀመረና በውጊያው ቅር እንደተሰኘ ተናገረ።

ወርቁ ምን ለማለት እንደፈለገ አልገባኝም። ጦርነቱ በጣም አስከፊ ነበር። ወደጦር ሰፈር በቀጥታ እንዲገቡ ከተመደቡት ጓዶች ወደ ኋላ ያፈገፈገ አልነበረም። ሁላችንም ፊት ለፊት ካለው እስከ ጦር ካምፑ ግንብ አፍንጫ ድረስ ደርሰናል። የተሰውት ጓዶች በሙሉ በደፈጣ ላይ ከእኛው ጋር ሆነው ነበር የወደቁት። የሞቱት ሞቱ የቆሰሉት ቆሰሉ፤ የቀረነው ደግሞ ደፈጣችንን ይዘን ያለምንም ፍርሀት እስከመጨረሻ፣ እስኪነጋ ድረስ ስንከላከል ቆይተናል። የጠላት ኃይሉ ከጦር ሰፈሩ ወጥቶ ለማጥቃት ብዙ ሙከራ ቢ ያ ደ ር ግ ም በተኩስ ፋታ ሳንሰጣቸው ገትረን ስላስጨነቅናቸው ማጥቃት ሳይችሉ ቀርተዋል። ከጦር ሰፈሩ ሊወጡ ቢችሉ ኖሮ፣ እኛን ጨርሰው ወይም አሳደው ከተማ የገባውንም ሠራዊት ይፈጁት ነበር።

እንደ ኃይል መሪና እንደ አጠቃላይ አዋጊ የነበረውን ተኩስ አይቶታል። በመጨረሻም ራሱ ወርቁ አፈግፍጉ የሚል ትእዛዝ ሰጠ ከተባለ በኋላ ነበር መመለስ የጀመርነው። እስኪነጋና የቆሰሉና የተሰውት ጓዶች እስከሬን በጠቅላላው እስኪወጣ ድረስ ጠላትን ሳናነቃንቅ ተዋግተናል።

በዚህ አነጋገሩ ብዙዎቻችን ቅር አለን። ቅር መሰኘቴን ሲመለከቱ ሐሳቤን እንዳቀርብ ተጠይቄ ነበረ። ምንም ሐሳብ አለሰጠሁም፤ እውነቱን ለመናገር ቢፈልግ የወገንና የጠላት ኃይል ጠንካራና ደካማ ጎን ሲዘረዘር ጠላት ተዘጋጅቶ እየጠበቀን እንደነበረ መነገር ነበረበት። መቼም ረድኢይ ለእኛ "ምስጢር ነው" ያለንን ጉዳይ ለአመራሩና ለጠቅላይ የውጊያው ዋና መሪም የሚደብቀው ምስጢር ይሆናል ተብሎ አይገመትም። ስለዚህ ትክክል ያልሆነና ድብብቆሽ ያለበት ነገር እንደነበረ ስለተሰማኝ መናገር አስፈላጊ ሆኖ አልታየኝም። ብናገርም ረድኢይ፤ "ም ስጢር ነው" ያለንን ነገር እዚያ መናገር እንደማልችል አውቃለሁ። አዝኜ ዝም አልኩ።

ጥይት እንደዝናብ እየወረደብን፣ ተዘጋጅቶ ከሚጠብቀንና በሰው ቁጥር፣ በመሣሪያ ዓይነትና ብዛት፣ ከእኛ ከሚበልጥ ኃይል ጋር ተጋፍጥን ሳናልቅ መመለሳችን ራሱ ተአምር ነበር። ለሦስት መቶ የጠላት ወታደሮች በጠቅላላው የተመደብነው አንድ ኃይል ማለትም በቁጥር ሀምሣ ወይም ስልሣ ብቻ ብንሆን ነበር። የተቀሩት ኃይሎች ወደ ከተማ የተላኩትና በሁለት አቅጣጫ ያሉ መንገዶችን ዘግተው የሚይዙ ነበሩ።

ወደጦር ካምፕ እንድንገባ ከተመደብነው ውስጥ ደግሞ በተለይ እኔ የነበርኩበት መካከለኛው ቡድን፣ ከሁሉም የበለጠ ለጦር ካምፑ ቅርብ ነበርን። በጣም ከመቅረባችን የተነሳ መጀመሪያ ላይ ንግግራቸውና ጨዋታቸውን ሁሉ ይሰማን ነበር። ከዚህ የበለጠ ሁሉ ለመቅረብ ሞክረን ተኩስ ስለተከፈተ አልቻልንም። ግን እስከመጨረሻው ድረስ ጥይት





እንደዝናብ ቢያወርዱብንም ቦታችንን ሳንለቅ ነበር የተዋጋነው። እናም ወርቁን ቅር ያሰኘው ምን እንደነበረ አልገባኝም። ወርቁ በጣም የማደንቀው አዋጊና ተዋጊ ነበር፣ በዚያ ቀን የተናገረው ግን የሆነ የማላውቀው ምክንያት አሳስቶት ይሆናል ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል። ምናልባትም ጠላት አስቀድሞ መምጣታችንን ማወቁን ረዳኢ ላይነግረው ይችላል ብዬ ገመትኩ።

***

ጋንታ ሀያ ስድስት ከዛሬ ነገ በጌምደር ትሄዳለች ተብለን እየጠበቅን እያለን ካለንበት ቦታ በቅርበት ባለው በሰበያ አካባቢ በወያኔና በሠራዊታችን መካከል ጦርነት መጀመሩን ሰማን። ጦርነት እንደተጀመረ ያወቅነው አንድ የሌሊት ዋርዲያ ቀሰቅሶን የከባድ መሣሪያ ተኩስ እንደሚሰማ ሲነግረን ነበር። ተኩሱን ስንሰማ አዲ አውሊዕ ይሆናል ብለን አሰብን፤ ብዙ ጊዜ የደርግ ጦር በዚያ አካባቢ ሲመጣ ስለሚተኮስ እንደዚያው መስሎን ነበር። ከግማሽ ሰአት በኋላ ግን የተኩሱ ድምፅ እየቀረበ የከባድ መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆን የቀላል መሣሪያዎችም ድምፅ መሰማት ጀመረ። "ተኩሱ ወደዚህ እየቀረበ ነው፤ ምንድነው?" እየተባባልን መጠያየቅ ጀመርን።

ረፋዱ ላይ አንድ ጓድ በፈረስ እየጋለበ መጥቶ ጦርነቱ ሰበያ ላይ በወያኔ መጀመሩንና እየተካሄደ መሆኑን ለመሪዎቻችን ነገረ። በጦርነቱ መጀመር መሪዎች አልተደሰቱም፤ አላስፈላጊ ደም መፋሰስ እንዳይደርስ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። በዚህ ሁኔታ ላይ እንደነበርን በግምት ከአንድ ሰዓት በኋላ ደግሞ ጦርነቱ ቦታ ላይ ከነበሩት ወያኔዎች ደብዳቤ የያዘ አንድ ገበሬ ዳህዋን ደረሰ። መሪዎቹ ከነበሩበት ቤት ወጣ ገባ እያልኩ ስለነበረ ገበሬው ያመጣውን ደብዳቤ ይዘት ለመረዳት ችያለሁ። ወያኔዎቹ በዛን ወቅት ጦርነቱን ለማካሄ የማይፈልጉ መሆናቸውንና በሁለቱም ወገን የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በጦርነቱ ግንባር ላሉት የሠራዊት አባላት ጦርነቱን እንዲያቆሙ መመሪያ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ነበረ። መሪዎቹም ሠራዊቱ ጦርነቱን አቁሞ እንዲያፈገፍግ ተእዛዝ አስተላለፉ። ጦርነቱ የተካሄደው ለእኛ ቤዝ ቅርብ የሆነ ቦታ ላይ ስለነበረ የእኛ ሠራዊት የወያኔን ጦር በቀላሉ መከበብና ማጥቃት እንደሚችል ይታወቃል። ሆኖም ጦርነቱን ለማካሄድ በሁለቱም በኩል ፍላጎት ስላልነበረ ከሰዓት በኋላ ላይ ጦርነቱ ቆመ። በዚያም መሠረት የወያኔ ጦር ወደ ደቡብ ሲያፈገፍግ የእኛ ደግሞ ወደ ምሥራቅ አፈገፈጉ። በዚያ ጊዜ አመ ራሩ ተነጋግሮ ዳዊትና ፀሐዬ ወደ ሰበያ ሄዱ። ጦርነቱ ያልታሰበ





ስለነበር እኛም ለከባድ ጥበቃ እንድንሰማራ ታዘዝንና የጎንደሩ ጉዞ በዚያም ሳምንት ሳይሳካ ቀረ።

እኔ የምመራት ጋንታ ሃያ ስደስት ዳህዋን ውስጥ ስለነበረች በየትኛውም ደቂቃ ትእዛዝ ለመቀበል ዝግጁ ነበርን። በሚቀጥለው ቀን የእኛ ኃይል አይጋ ውስጥ የምትገኘውን ትንሽ የወያኔ ቤዝ በቁጥጥር ስር ማዋሉ ተሰማ። ያ የወያኔ የጦር ቤዝ እንዲያዝ የተደረገው ለእኛ በጣም ቅርብ ስለነበረ ቦታውን ለመቆጣጠር ሲባል ነበር። የነበሩት ጥቂት የወያኔ ጦር አባላት ወዲያውኑ በማፈግፈጋቸው ምንም ዓይነት ጉዳት አልደረሰም። ከዚያ በኋላ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ሆነው ከወያኔ ጋር የነበረው ጦርነት ወደ ነበለት ተዛመተ።

ከዘጠኝ ቀናት በኋላ ደግሞ ነበለት ላይ በኃይል ሰባ አራት እና በወያኔ መካከል ሌላ ጦርነት ተጀመረ። የኃይል አባላቱ ሰበያ ላይ ስለተካሄደው ጦርነት ምንም መረጃ አልነበራቸውም። ከኃይሏ ሦስቱ ጋንታዎች አንዷ ተከባ አራት አባላት ብቻ ሲወጡ፣ ሌሎቹ በዚያው ቀሩ። ሁለቱ ጋንታዎች ግን እስከሚመለሱ ድረስ ደንና ምሽግ ይዘው ሲከላከሉ ዋሉና በመጨረሻ ተመልሰው መጡ። ጦርነቱ ነበለት ላይ አላቆመም ወደ ብዘትና አጋሜም ቀጥሎ ነበር።

ጋንታ ሀያ ስድስት ዳውሃን እያለች፣ ከአንጃ ችግር ጋር በተያያዘ እዚህም እዚያም ጎልቶ የወጣ ችግር ይታይ ነበረ። የታሰሩ ጓዶች ነበሩ፣ በጋንታ ሀያ ስድስት ስር ሁለት እስረኞች ነበሩ። ሌሎች ሁለት ደግሞ በዓይነ ቁራኛ የሚጠበቁ ነበሩ ከእነርሱም አንደኛው ታዬ የሚባል ነበረ። ቀን ቀን እንደ አመራር አባል ተሰብስቦ ይውላል፣ ማታ ማታ ግን ለብቻው ያድራል። በዓይነ ቁራኛ እንድንጠብቀውና ከእርሱ የሚገናኙ ሰዎችን ማሳወቅ እንዳለብን ከአመራሩ ተነግሮኛል። እርሱ ግን እንደምከታተለው አያውቅም፤ ወደ እርሱ የሚሄድ ሰው ሁሉ፣ ማንን ፈልጎ እንደገባ? ማን እንደጠራው? ጭምር እያጣራን ሪፖርት እንድናደርግ ታዘን ነበር። ለምን

ቀን ከእነርሱ ጋር ተሰብስቦ እንደሚውል ግን አላውቅም፤ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ይሄ ሥራ የኔ ድርሻ ሆኖ ነበረ። ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ከእኛ ጋ ሄደ፤ የት እንደሄደ ግን አላውቅም። ታዬ በጣም ረዥም ጸጉረ ሉጫ ጥቁር ህንድ የሚመስል ነበረ።

ሁለተኛው እስረኛ ደግሞ በአንጻ ተጠርጥሮ ለብቻው እንዲቀመጥ ተደርጎ፣ እኛ ምግብ እንድንሰጠው ታዘን እንሰጠው ነበረ። አንድ ቀን ከአዳል ጋር ስናወራ "ይሄ እኮ ወንድሜ ነው" ብሎ ነገረኝ። በጣም ደነገጥኩና "አዳል! ምንድነው የምትለው፣ እውነትህን ነው እንዴ?" ስለው።

"አዎ እውነቴን ነው። ወንድሜ ነው" አለኝ።

"የአንተ ወንድም ከሆነ ታዲያ በዓይነ ቁራኛ ይሚጠበቀው ምን አድርጎ ነው?"

"ከተማ እያለ፣ አንጃ ተብሎ ስለተጠረጠረ 'የፈለጋችሁትን አድርጉኝ እንጂ፣ እኔ ግን አንጃ አይደለሁም' ብሎ እራሱ ነው የመጣው። እስከሚያጣሩ ድረስ ነው እንጂ አንጃ አይደለም" አለኝ።

በጣምያሳዝናል በአባትም በእናትምወንድሜነው ሲለኝ በጣም ገርሞኝ "ምን ዓይነት ነገር መጣ?" እያልኩ አስብ ነበር። ሆኖም ከትንሽ ቀናት በኋላ ወጣና ወደ ወታደራዊ ሥልጠና ገብቶ ሠራዊቱን እንዲቀላቀል ተደረገ። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ሁኔታዎች ወደ መጥፎ አቅጣጫ እየሄዱ መሆናቸውን በደንብ ያመላከቱ ነበረ።

ለምሳሌ ገረይና ኃይለ ማሪያም ከሠራዊት ከድተው እዚያው አዲ ኢሮብ ውስጥ ለብቻቸው ሸፍተው ነበር። የዚያው አካባቢ ተወላጅ ስለነበሩ የአዲ ኢሮብ





ሕዝብ አሳልፎ እንደማይሰጣቸው የታወቀ ነው። በምን እንዳኮረፉ ባላውቅም፣ ከፀሐዬ ጋር ውስጥ ለውስጥ ይገናኙ ነበርና ተነጋግረውና ተማምነው እንደገና ወደ ድርጅቱ ተመለሱ።"ፎርማሊቲ ስለሆነ ተነጋግራችሁ ነገ ይመለስላችኋል" ብላችሁ ብረታቸውን አስወርዷቸው አሉን። ሲመጡ እኔና አበጀ ብረታቸውን እንዲያወርዱ አደረግናቸውና በማግስቱ ተመልሶ ተሰጣቸው። አንዳንዶቹን ለመመለስ ቢታገሉም፣ ከሠራዊቱ የሚከዱ አባላት ቁጥር እየጨመረ ሄደ። በሌላ በኩል ደግሞከሕዋሐት ጋር የሚደረጉ ጦርነቶችም እየተባባሱ ሄደዋል።

ለሁለተኛ ጊዜ ለመሄድ ተዘጋጁ ተብለን ተዘጋጅተን እየጠበቅን እያለ ዘውዱ መጣ። ዘውዱ የኃይል አሥራ አራት መሪ የነበረ የአየር ወለድ አባል ነበረ። እኔ፣ ዘውዱና አመራሮቹ በየትኛው መንገድ እንደምንሄድ ለመምረጥ ተቀመጥንና ተወያየን። ከዚያም በብዘት በኩል እንድንሄድ ተወሰነ። ነገር ግን ከወያኔዎች ጋር ጦርነት ስለነበረ፣ ሁለት ኃይሎች እስከተወሰነ ርቀት እንዲሸኙን ሆነ። ከዚያም መጀመሪያ ከኃይል አሥራ አራት እኛን ለመውሰድ አንድ ጋንታ ስለምትመጣ እንድንጠብቅ ተነገረን።

የተባለችውን ጋንታ በመጠበቅ ላይ እያለን ደግሞ ሌላ ችግር ተከሠተ። በመረጃ ክፍል ይሠራ የነበረው ኪዳነ ኪሮስን ሳገኘው "ከየት መጣህ?" አልኩት።

"አልሰማችሁም እንዴ?!" አለኝ

"ምኑን?!" አልኩት

"የብዘትን ወሬ አልሰማችሁም?"

"ምንም አልሰማንም"

"ብዘት ላይ እኮ ተደበደብን"

"መቼ?"

"ዛሬ የመጣሁት እኮ፣ እዚያ አድሬ ነው። ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ጦርነት ላይ ነበርን። አሁንም ከዚያ አምልጬ ነው የመጣሁት። እና ይሄ ሁሉ ሲሆን አመራሮች አላወቁም ማለት ነው!?"

"አዎ፣ አላወቁም። በል ግባና ንገራቸው" አልኩትና ሊነግራቸው ሄደ።

በአንድ በኩል የአንጃ ችግር የሚባለው ከመፈታት ይልቅ በአባላት ላይ የፈጠረው ውጥረትና አለመተማመን ተባባሰ። በሌላ በኩል አመራሩ ከሕወሐት ጋር የነበረውን ችግር በሰላም አልፈታውም ወይም የመከላከልም ሆነ ሌላ አማራጭ መፍትሔ አላደረገለትም። የአመራሩ አባላት ከወያኔ ጋር ደም ባንፋሰስና ቢቀዘቅዝ ጥሩ ነበር፤ ሲሉ ብቻ ነው የሚሰሙት። በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የነበረው ግንኙነት ከቀን ወደቀን እየተበላሸ መሄዱ ለሁሉም ግልጽ ነበር። ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝም መገመት አስቸጋሪ አይደለም፤ ሆኖም አመራሩ ሁኔታውን በማጤን ምንም ዓይነት ርምጃ አልወሰደም። ሠራዊቱ ቦታውን ጁስቀድሞ እንዲለቅ አለያም እራሱን እንዲከላከል ከመሪዎቹ መመርያ አልተሰጠውም። አመራሩ ለምን ችላ እንዳለ ግራ የሚያጋባ ነበረ። በመሆኑም በውጪም በውስጥም ባልተፈቱ ሁለት ትልልቅ ችግሮች ስለተተበተበ የሠራዊቱ እምነት እየተሸረሸረ ሄዶ ተስፋ መቁረጥ ነገሠ። ሠራዊቱ በአመራሩ ላይ የነበረው እምነት እየተሸረሸረ ሄደ። በቅርብ የሚተዋወቁና የሚተማመኑ አባላት ሲገናኙ የሚማከሩት ስለመከዳት እንደሆነ ያስታውቅ ነበር። እኔም በቅርብ የማውቃቸው ጓደኞቼን ባገኘሁ ቁጥር ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ፣ አብረን እንጥፋ የሚሉ ወይም ሠራዊቱን ትቼ እንድወጣ በራሴ እንድወስን የሚመክሩኝ እየበዙ ሄዱ።

ኤልያስ አንድ ቀን መጣና "ምን ታደርጋለህ?" አለኝ።





"ምነው?" አልኩት።

"ድርጅቱ ፈርሷል፣ ድሮም ነግረንሃል፤ ፓርቲው ቀድሞም ፈርሷል። አሁን ደግሞ ሠራዊቱ እየፈረሰ ነው። እዚህ አንተ የእነርሱ አሽከር ነህ እየተባልክ ትታማለህ። ከዚህ ቦታ ውጣና አብረን እንሂድ" አለኝ።

"እኔ ለመሄድ ዝግጁ አይደለሁም፡። እንዴት ዝም ብዬ ተነሥቼ እሄዳለሁ? እንደምታውቀው ግን የአንተን ምስጢር እጠብቅልሀለሁ" አልኩት።

ቀስ ብሎ ተነሣና ሄደ። ብዙም አልቆየም ከዓለም መስፍን ጋር ሆነው ለብቻቸው ሹፈቱ ተባለ። ሁለቱም የመረጃ ክፍል አባላት የነበሩ ናቸው።

ከኤልያስ በኋላ ብርሃነ ዓባይም አነጋግሮኝ ነበር፡፡ በል እንዳያሳስቱህ ተጠንቀቅ አለኝ። ሌላ ፍጹም የማልረሳው ጋንታ ሀያ ስድስትን ለመውሰድ ወደ ከልአሳ እንደሄድኩ ኃይል አምስት መቶ ከልአሳ መጥታ በነበረ ጊዜ ያጋጠመኝን ነው። ያን ጊዜ ኃይል መሪም አልነበራትም የአቢኢዮ ከተሠዋ በኋላ ፍሱሕ ገብራይ ኃይሏን እንዲመራ ተጠይቆ እንቢ ብሎ ተቀምጧል። መስፍን ኃይል መሪ ተደረገ። መስፍን ብቃት ያለው ኃይል መሪ ነበረ። ከነበሩ ጓዶች ሁሉ በመችረየስ አተኳኮስ ይታወቃል። ሲተኩሱ ድምፁን እንደ ሙዚቃ ይቃኙ ከነበሩ ሰዎች በጣም የሚታወቁት መስፍን፣ ቢራራና ግደይ ጨጓር ነበሩ። ተኩሱን ስንሰማ ሁላችንም የማን እንደሆነ በዜማው ብቻ እንለየው ነበር።

ኃይል አምስት መቶ እያለሁኝ ሊበን የጋንታ አምስት መቶ ስድስት የፖለቲካ ሐላፊ፣ ብርሃኑ ደቦጭ ደግሞ የሊበን ምክትል የፖለቲካ ሐላፊ ነበር። በጣም የምንግባባና የምንዋደድ ነበርን። ታዲያ ኃይል አምስት መቶ ወደ ከልአሳ መጥታ በነበረ ጊዜ ብርሃኑ ደቦጭ አገኘኝና "አንድ ጊዜ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ" አለኝ። ብርሀኑ ደቦጭ ኃይል አምስት መቶ ስድስት እያለን የእኔ ጋንታ ምክትል

የፖለቲካ ሀላፊም የነበረ ነው። "እንግዲህ አማኑኤል እኔና አንተ ካሁን በኋላ ላንገናኝ እንችላለን ብዬ ነው የመጣሁት" አለኝ።

"ምነው?" የኔ ጥያቄ ነበረ።

"አሁን እንግዲህ እንደምታየው ድርጅቱ የተሳሳተ መስመር ይዟል። አንጃ ግራንጃ እያለ ጓዶችን በመደዳ አስሯል። አሁንም ገና ለማሰር እየተዘጋጀ ነው። ይሄን እኔ አላምንበትም፣ ትክክል አይደለም። ድርጅቱ ስሕተት አለው ብሎ ስሕተቱን የጠቆመ ሁሉ አንጃ እየተባለ ነው። ስለዚህ አንተ ያለህን የወታደራዊ ችሎታና የትግል ፍቅር ለዚህ ድርጅት ሳይሆን ለሚመጣው ሀቀኛ የላብ አደር ፓርቲ፣ ሕዝቡን ለሚወክል፣ ሕዝቡን ሊመራ ለሚችል ድርጅት ማድረግ አለብህ እንጂ፣ ለዚህ ድርጅት መሥዋዕትነት እንድትከፍል አልፈልግም" አለኝ።"ስለዚህ እኔና አንተ ምናልባት ላንገናኝ እንችላለንና ይቺን ግን ልነግርህ እፈልጋለሁ" አለኝ።

"እሺ እኔም አስብበታለሁ" አልኩትና ተቃቅፍን ተሳስመን ተሰነባበትን። ከብርሃኑ ጋር እንደተለያየን እኔም ወደ ጋንታዬ ተመለስኩ። በማግስቱ ብርሃኑ ደቦጭና ሊበን ተያይዘው ከሰግላት ጠፍተው አዲግራት ለሚገኘው የደርግ ጦር እጃቸውን መስጠታቸውን ሰማሁ።ኃይል አምስት መቶ አብሮን የነበረው ጎይቶም መጥፋታቸውን ሊናግር ረፉድ ላይ ወደ አመራሩ ሲመጣ ከእኔ ጋር ተገናኘንና ለእኔም ነገረኝ።

"የፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊና ምክትሉ፤ሊበንና ብርሃኑ ሌሊት ጠፍተው ወደ አዲግራት ሳይሄዱ አይቀሩም። ምክንያቱም አቅጣጫቸው ወደ እዚያ በኩል ነበረ። ተከታትለናቸው ነበር፤ ሆኖም ልንደርስባቸው አልቻልንም" አለኝ።

"በል እንግዲህ አንተ ራስህ ሄደህ ንገራቸው" አልኩትና ሄዶ ነገራቸው።

እኔ ብዙ ጊዜ ነበር የምወቀሰው። " አሁን ደግሞ ከልአሳ ከብርሃኑ ጋር መነጋገሬን ያየ ሰው ካለ" እያልኩኝ በጣም ነበር ተጨንቄ ያደርኩት። ብርሃኑ





በጣም የማምነው ሰው ነበር፤ ሁለቱም ጥሩ ጓዳዊ ፍቅር ነበራቸው። በተለይ እኛ ኃይል አምስት መቶ ከአንዳንድ ጓዶች ጋር በነበረን ቅራኔ እኔን በደንብ ነበር የሚያበረታቱኝ።

***

በዚያው ሰሞን በአንዱ ቀን ዳህዋን እያለሁ አንድ ድንደተኛ ነገር አጋጠመን። አንድ ቀን ጸጋዬ ደብተራው መጣና "ጸሎተና ደጀኔ ወደ ወንዝ ልብስ ለማጠብ ሄደዋልና ዋርዲያ ቦታውን እንዲያይ አድርግ" አለኝ።

"እሺ" አልኩት። ቦታውን ሁልጊዜ ሁለት ዘቦች ከላይና ከታች አቁመን የምንቆጣጠረው ቦታ ነበረ። እንደገና ደግሞ ትንሽ ቆየት ብሎ ተመልሶ መጣና "እኔና ዳዊት እናንተ ከሄዳችሁ ብለን ቤት ለመቀየር እያሰብን ነው። ስለዚህ አሁን ከፊታችን ባለው ጋራ ላይ የሚገኘውን ቤት አይተን ለመመለስ ልንሄድ ነውና ጥበቃዎች እንዲከተሉን አድርግልን" አለኝና ሄደ።

በዚህ መካከል፣ ከቀኑ አሥር ሰዓት አካባቢ ሲሆን ከወንዙ አቅጣጫ በማከታተል የሁለት አውቶማቲክ መሣሪያ ድምፅ ሰማሁ። ወደ ወንዙ በኩል ሮጠን ወጣንና ተኩሱ ይቀጥላል ብለን ብንጠብቅ አልቀጠለም። ጋንታችን የሰው ብዛት ከሌሎች ጋንታዎች በላይ ነበረችና በሦስት በአራት ተከፋፍለው ቦታ እንደያዙ፣ እኔ ተኩሱ ወደነበረበት ወደ ወንዙ አቅጣጫ አንድ ስድስት ጓዶች ይዤ ሄድኩ። ስደርስ ጸጋዬ ደብተራው ከወንዝ እየወጣ ሽጉጥ ወደ ሰማይ ሲተኩስ አየሁት።በጣም ስለምወደው እያሳደዱት ስለመሰለኝ በድንጋጤ ከያዝኩት ከለላ ወጥቼእርሱን ለማዳን እየሮጥኩ ወደ ነበረበት ሄድኩ፡፡

ጸጋዬ ደብተራውን ሳየው እነጸሎተም እዚያው ነበሩና የሆነ ሰው እነርሱን ገድሏል ብዩ አሰብኩ። መጀመሪያ ዳዊት ከጸጋዬ ደብተራው ጋር ነበረ። አሁን ጸጋዬ ደብተራውን ብቻውን ሳየው ምንአልባት ዳዊትም ተገድሎ ጸጋዬ ደብተራውን እያሳደዱት ይሆናል ብቻውን የሆነው ብዬ፣ "ጸጋዬን የሚከተል ሰው ካያችሁ አነጣጥራችሁ ምቱ" ብዬ ትእዛዝ ሰጠሁ። ከዚያም ጸጋዬ ደብተራው ወደ ነበረበት ወደታች ወረድኩና ምን እንደተፈጠረ ስጠይቀው "ደጀኔ ጸሎተን ገደለው፣እኛ ደግሞ ደጀኔን ገደልነው" አለኝ።





በሩጫ ወደ ወንዙ ሄጄ ስመለከት፣ ደጀኔ ከግራ አይኑ በታች አፍንጫው ላይ ተመትቶ ሞቷል። ጸሎተ ደግሞ የግራ ደረቱ ላይ ነው ተመትቶ የወደቀው። ጸሎተ አጠር ያለ በጣም ቀይና ጢማም ነበረ። አጠገቡ ዳዊት ቆሞ "ወንድሜ! ወንድሜ! ጓዴ! ጓዴ!" እያለ እየጮኸ ያለቅሳል። እኔ ስደርስ ጸሎተ ነፍሱ አልወጣችም ነበርና ተሸክመን ከፀሐይ ወደ ጥላ ወሰድነው። ትንሽ ቆይቶ የሆነ ነገር ለመናገር ሞከረ። መናገር አቃተውና ወዲያው ስሩ ተገታትሮ ምንም ቃል ሳያወጣ በዛው ሕይወቱ አለፈች።

ከእኔ በኋላ ተከትሎ የደረሰው አበጀ ነበረ። ከዚያም በቅርብ ያሉ ገበሬዎች ሰምተው መጡ። ገበሬዎቹ ሬሳውን ገነዙት። ነጠላ አልነበረውም።ና የእኔን ነጠላ አውጥቼ ሰጠኋቸውና ገንዘው ይዘውት ሄዱ።

የጸሎተና የዳዊት ጠመንጃዎች እንደተተኮሰባቸው አሸተትንና አወቅን። ከልአሳ ሕክምናላይ የነበሩ ጓዶች የጸሎተን መሞት እንዳወቁ መጡ። እነ አምዴም አለቀሱ። ጸጋዬ ደብተራው መጣና "ወደዘርኡ ከህሸን ሰዎች ልከን ጸሎተ መሞቱን እንድንነግር ሁለት ጓዶች ስጠኝ" አለኝ። ሁለት ጓዶች መደብኩለት። እንደገና ቆየት ብሎ ሐሳቡን ቀየረና "አንተ ራስህ ሂድና ንገረው" አለኝ።

እንተነህን ጠራሁትና እኔ ከአንድ ሰው ጋር ለዘርኡ ከህሸን የጸሎተን መሞት ለመንገር ወደሚኖርበት ወደ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ቤተሰቦች ቤት ልሄድ እንደሆንና እርሱ የቦታውን ጸጥታ እንዲቆጣጠር ነግሬው ተነሣሁ። ወዲያው ግን ለምለም እየሮጠች መጣችና "ቢቃ አማኑኤል እዚሁ ቆይ፣ ራሴ ሄጄ እነግረዋለሁ" አለችና ሄደች።

***

## ሰባት
## የመጨረሻዎቹ ቀናት

### ማአቢኖን

«ከምሮ እየናደ፣ ንዶ እየከመረ
ዘመንና ዘመን እየተባረረ
ይኸው ጅምሩ አልቆ ማለቂያው ጀመረ!»

(ጌትነት እንዬው)

በብዘት በኩል ጦርነቱ እየቀጠለ ነው ወያኔም ወደኢጋሜ መንቀሳቀስ ጀምራለች፤የእኛም ጋንታ ወደ ጦርነቱ እንድትሄድ ተወሰነና ወደ ማአቢኖን ልታቀና ሆነ። ያኔ ፍሱሕ ገብራይ "በቃኝ" ብሎ ከኃይል ስልሣ ስድስት ተሰናብቶ ወደ ቤተሰቦቹ ሄዶ ነበር። አሁን ግን አግባብተውት ተመለሰና ከእኛ ጋር እንዲሄድ ተደረገ፤ ከእኔ በላይ እርሱ ወታደራዊ አዛዥ እንዲሆንና እኔ ምክትል ሆኜ ማአቢኖን እንድንከላከል ተላክን።

ከፍሱሕ ገብራይ ጋር አብረን ብዙ ችግሮችን አሳልፈናል። በሠራዊቱ ውስጥ ሆነን ስለሚደርሱብን ችግሮችም በተደጋጋሚ ሰንወያይ ቆይተናል። የተለያዩ ምስጢሮችን ተጋርተናል። በውቅሮ ተልእኮ ጊዜ የደርግ ኃይል ስለእኛ ዕቅድ መረጃ ማግኘቱን አመራሩ እያወቀ ወደ ውጊያ እንዳስገባን እኔ፣ እርሱና ረድኢይ ብቻ ነበርን የምናውቀው። ፍሱሕ ሠራዊቱን ጥሎ ወደ ቤተሰቡ የሄደበትም ምክንያት በውቅሮ ጦርነት ላይ በሆነው ነገር መቀየሙ ነበር። ቤተሰቦቹ ያሉት አዲ ኢሮብ ውስጥ ስለሆነና አካባቢው ከደርግ ነጻ የሆነ ስለነበረ ወደ ቤተሰቦቹ ለመመለስ ምንም ችግር አልነበረበትም።





እኔ ግን የቱንም ያህል ብናደድ ምንምእርምጃ አልወሰድኩም። እንደ እርሱ ወደ ቤተሰቦቼ ልሂድም ብል አልችልም። ምክንያቱም የዛላ አንበሳ አካባቢ በደርግ ቁጥጥር ስር ነበረ። ተመልሼ ወደ ቤተሰቦቼ ከሄድኩኝ ለደርግ እጄን መስጠት ይኖርብኛል። ያንን ማድረግ ደግሞ በፍጹም አልፈልግም።

እነሕብስቱን የመሰሉ "ካልተሠዋሁ" እያሉ በጨበጣ የጠላትን መትረየስ በእጃቸው ለመንጠቅ የሚሽቀዳደሙ ምትክ የማይገኝላቸው የጦር መሪዎችን ያጣነው በውቅሮ ተልእኮ ነበር። እነየአቢኢዮን የመሰሉ ግንባር ካልተመደብኩና ካልተሠዋሁ እያሉ "ኡኡ!" የሚሉ መሪዎችን አጥተናል። እንዲሁም እነጌታሁን ለመሞት እያጣጣሩ እንኳን የራሳቸው ሕይወት ሳይሆን ተሸከመው የሚያሸሹዋቸው ጓዶቻቸው ጭንቀት ይበልጥ የሚሰማቸው ጀግኖች ውቅሮ ላይ ያለአግባብ መሠዋታቸው ያንገበግበኝ ነበር። እነርሱን ሳስብ ሁልጊዜ ሞራሌ እንክትክት እያለብኝ እምነቴ እየተሸረሸረ ሲፈታተነኝ ቆይቷል።

በዚህ ሥነ አእምሮአዊ ችግር ውስጥ እያለሁ ነበር ከብርሃኑ ደቦጭ ጋር የተገናኘሁት። ከልአሳ እያለሁ ብርሃኑ ደቦጭን አግኝቼው የተናገረኝ ነገር ከዚህ ቁስሌ ጋር ተያይዞ ውስጤን ነካው። "በምንም ተአምር ከአሁን በኋላ ለዚህ ድርጅት መሥዋዕትነት እንዳትከፍል! ይህ ድርጅት የያዘው አካሄድ እየተበላሸ ነው። በአሁኑ ጊዜ አንጃ ግራንጃ እያሉ ጓዶችን እየፈረጁ ነው፤ ያመኑበትን የሚናገሩ ታጋዮችን በየምክንያቱ እያሰሩ ነው ! ..."

ኃይል አምስት መቶ እያለንም እኛ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት ሳንጨርስ ሜዳ የገባን ልጆች፣ በአንዳንድ ምሁር ነን በሚሉ አባላት የማግለል፣ የንቀትና የማንጓጠጥ በትር ይሰነዘርብን ነበር። የደረሰብን የሥነልቦና ተጽእኖ ሲጨመርበት ውስጤ በጣም እየተጎዳ ስለሄደ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማሰብ ጀመርኩ።

መጀመሪያ አንዳንዶች በዚያ የተነሳ ሠራዊቱን ጥለው ለመሄድ እንደተነሣሱ እየነገሩኝ ጠፍተው ሲሄዱ አብሬ መሄድ ትክክለኛ መንገድ ነው

ብዬ አልተቀበልኩም ነበር። ምክንያቱም አመራሩ ችግሩ ትልቅ መሆኑን ካወቀ መፍታት አያቅተውም ብዬ አስብ ነበረና ነው። ስለዚህ ብዙዎች የዚህ ዓይነት ችግር ያስመረራቸው ጓዶች ሁለት ሦስት ሆነው እየተማከሩ ጥለው ለመሄድ ሲወስኑ አብሬያቸው እንድሄድ ጠይቀውኝ እምቢ እያልኩ ስመልሳቸው ቆይቻለሁ።

አሁን ግን የማየው ነገር ሁሉ ተስፋ የሚሰጥ ሳይሆን በአንዱ ችግር ላይ ሌላ ችግር እየተጨመረ፣ ከመሻሻል ይልቅ ከቀን ቀን እየባሰበት ነው። በአመራሩም ላይ የነበረኝ እምነትም እየቀነሰ ሄዷል። ሳውቃቸው የአመራሩ አባላት ብዙ ነገሮችን ቀድመው የሚያስቡ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ለሚፈጠሩ ነገሮች ቀድመው ተዘጋጅተው እርምጃ ለመውሰድ የሚችሉ ነበሩ። ወደ ኋላ ግን ሁሉም ነገር የተገላቢጦሽ ሆነ። በጊዜው በአካባቢው በቅርብ የነበረ ኃይል እንደሌለ ስሰማ ተናደድኩ። በዚህ አጋጣሚ የተረዳሁት ነገር የአመራሩ ችግር ከባድ እንደሆነና ሊፈቱትም መቻላቸው በጣም አጣራጣሪ መሆኑን ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ መቆየትም ሆነ መሥዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀት ምንም ጥቅም የለውም ብዬ የመጨረሻ ውሳኔ አደረግኩና ድርጅቱን ጥዬ ለመውጣት ወሰንኩ።

ከወያኔ ጋር የነበረው ግንኙነት እየተበላሸ እንጅ እየተሻሻለ እንደማይሄድ ይታይ ነበርና በማንኛውም ግዜ ጦርነት ሊጀመር እንደሚችል መገመት ይቻላል። በእኛ በኩል የሚታየው ነገር ግን አመራሩ ሁኔታውን ያገናዘበ ምንም ዓይነት ዝግጅት እያደረገ ያለመሆኑን የሚያመላክት ነው። የሠራዊቱ አመራርም ሆነ ሠራዊቱ ባዶ ሜዳ ላይ ለአደጋ እንደተጋለጠ የሚጠቁም ነበር። ይሄንን ሳይ የድርጅቱ ነገር እያበቃለት እንደሆነ ተሰማኝ።

በአካባቢው በጊዜው የነበረው አማራጭ አንድ ብቻ ነው። እኔ የምመራትና ጎንደር እስከትሄድ ለአመራር አባላት ጥበቃ በማድረግ ላይ የነበረችውን ጋንታ ሀያ ስድስትን ማንቀሳቀስና ማእቢኖን እንድትሄድ ማዘዝ። ፍሱሕ ከሄደበት





ጋንታ ሀያ ስድስትንና በኋላም ለማጠናከር የሚላኩትን ጋንታዎች ጭምር እንዲመራ ተመድቦ አብረን ወደ ማእቢኖን ሄድን።

በሌሊት ተነሥተን ዳውሃንና የአዎን ተራሮችን ወጣንና ጋራቢኖ ደረስን። እዚያ እርሱ የሚያውቃቸው ሰዎች ነበሩና ማእቢኖን መያዙንና አለመያዙን ሰልለው እንዲመጡ ላካቸው።ምክንያቱም መጀመሪያ በነበረው ግርግር ማን የት እንዳለ ምንም አይታወቅም ነበርና ነው። ሰዎቹ ማእቢኖን እንዳልተያዘ አረጋግጠው ተመለሱ። ስለዚህ ከሻፊዎች እንላክ አለኝና መጀመሪያ ስድስት ጓዶች ልከን ቦታውን እንዲይዙት አደረግን። ሥፍራውን ከተቆጣጠሩት በኋላ ጋንታችን ሄዳ ቦታ ያዘች። በዚያን ወቅት የወያኔ ኃይል ከጎእተሎ አልተንቀሳቀሰም ነበር። በማግስቱም ሌላ ሰላይ ስንልክ ወያኔዎች ከሁለት ቀን በኋላ እንደገና መንቀሳቀሳቸውን ነገሩን።

በየቀኑ ሁለትና ሦስት ጊዜ፣ የወያኔዎችን እንቅስቃሴ ሰላዮችን እየላክን እየተከታተልን ቆየን። ጦርነቱ በሰበያም በምድረባም በኩል በሁለት አቅጣጫ ቀጠለና ሰበያንም መልቀቅ ተጀመረ። ሰበያ ሲለቀቅ ብዙ ጓዶች ወደ ቆሎምሽላ ምሽግ እንዲይዙ ተደረገ። የተወሰኑት ደግሞ ወደ ማእቢኖን እኛጋ እንዲመጡ ሆነ። አሁን ማእቢኖን ላይ ሠራዊት እየተጨመረ እየደረሰልን ነው። ከኃይል ስልሣ ስድስትና ከኃይል ሰባ አራት የመጡ የተወሰኑ ጋንታዎችም ማእቢኖን ደረሱ። ወደ ማእቢኖን ስንላክ ምንም ዝግጅት እንዳልነበረ ያዩና እንደኔ ስሜታቸው የተነካ ብዙ መሆናቸውን ታዝቤአለሁ። እርግጥ ሁሉም ከሚቀርበው ጋር ነበረ ስሜቱን የሚገላለጸው። ፍሱሕ ከማንም በላይ የማምነው ሰው ነበረ፤ ስለዚህ ከሚታየው ሁኔታ ድርጅቱ ምንም ተስፋ እንደሌለውና በዚህ ዓይነት መቀጠል ስለማይቻል እኔ ለቅቄ ለመሄድ እንደወሰንኩ ነገርኩትና እርሱም በሐሳቤ ተስማማ። ከእኔ ጋር ለመሄድ መወሰኑን ነገረኝ። እዚያ ወሳኝ ቦታ ላይ እርሱን ማግኘቴ ለእኔ እንደልዩ ዕድል የሚቆጠር ነበር። ፍሱሕን ከሄደበት አግባብተው እንዲመለስ ያደረጉትና

ያመጡት በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነበር። ያመጡትም አካባቢውን ስለሚያውቅ፣ ልምድ ስላለውና ከአከባቢውም ኅብረተሰብ ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበረው ነው።

በአንድ ሐሳብ ከተስማማን በኋላ፡ የእኛን ጋንታዎች ቦታ ቦታ አስይዘን ለከፋም ለደጉ መሸሸጊያ የሚሆነን ቦታ ለማየት አብረን ከጋራው ወደታች ወረድን። አንድ እርሱ የሚያውቀው በዱር የተሸፈነ ቦታ ነበረና እዚያ ስንደርስ በቦታው ከነበሩ ሰዎች ጋር በሁኔታው ላይ ተነጋገሮ ወደ ምሽጋችን ተመለስን።

በማግስቱ ከኃይል ስልሣ ስድስት ጋር የእነግደይ ጨጓር ጋንታ መጣች። ይህች ጋንታ በኃይል ስልሣ ስድስት ውስጥ ሆና ከወያኔ ጋር ብዙት ላይ በመጀመሪያው ጦርነት የተዋጋች ጋንታ ነበረች። ከግደይ ጨጓር ጋራ ኃይል አምስት መቶ ውስጥ አብረን ስለነበርን በደንብ ነው የምንግባባው። ግደይም ራሱ በአመራሩ ቅሬታ ተሰምቶትና ተበሳጭቶ ስንብት ጠይቆ ከሄደ በኋላ ነበረ እንደገና አግባብተው የመለሱት። ስለዚህ እርሱም ያሰብነውን ልንነግረው የምንችለው ታማኝና ያለውንም ችግር የሚያውቅ ስለሆነ በመምጣቱ እኔና ፍሱሕ ደስ አለን። ከእርሱ ጋር ለመነጋገር ችግር ስላልነበረብን ያሰብነውን በቀላሉ ነገርነው። በሐሳባችን መስማማቱን ስናረጋግጥ መፍትሔ ለመፈለግ ሦስታችንም መመካከር ጀመርን።

በመጀመሪያ ፍሱሕ ገብራይ አዲ ኢሮብ ወደታች በኩል ባለው አካባቢ ለተወሰነ ጊዜ ሽፍተን ለመቆየት እንችላለን ስላለ በዚሁ ተስማማን። ከዚህ በኋላ ፍሱሕ ከአንድ ገበሬ ጋር ሆኖ ፊት ለፊታችን ያለው ተራራ በወያኔ ኃይል መያዝ አለመያዙን ለማጣራት ሊሄድ ስለሆነ ከዚያ ሲመለስ ወደምንሸፍትበት ቦታ ጠፍተን እንሄዳለን ብለን ወሰንን።





ፍሱሕ ከሄደ በኋላ እስኪመለስ ድረስ እኛ ተዘጋጅተን ጠበቅነው። መንገድ ላይ ምን እንደአጋጠማቸው ባናውቅም ሳይመለስ ሙሉ ቀን ቆየ። በዚያ መካከል በነጋታው ጠዋት ከኃይል ሰባ አራት አድሀኖም (እውነተኛ ሥሙ ፍስሐየ ሃጎስ ይባላል) መጣ። እርሱንም በደንብ ስለምናውቀውና ስለምናምነው ልናማክረው ተስማማን። አድሀኖም የብዘትና የነበለት ጦርነት ላይ የተሳተፈችው ጋንታ መሪ ነበረ። እኔና ግደይ ስለዕቅዳችን ለአድሀኖም ነገርነውና መስማማቱን ገለጸልን። ዐቅደን የነበረውንና ፍሱሕ ሄዶ በመቅረቱ ግራ መጋባታችንን እንዲሁም ከዚያ በኋላ እዚያ ቦታ መቆየቱ አደጋ እንደሚሆን ለአድሀኖም ነገርነው።

በመጨረሻ አውጥተን አውርደን፡ 'ወደደርግ መግባት አንፈልግም፡ ያለን አማራጭ ወደ ኤርትራ መጥፋት ነው" የሚል ውሳኔ ላይ ደርስናል። ስለዚህ ፍሱሕ በዚያኑ ዕለት ካልመጣ በሚቀጥለው ቀን ወደ ኤርትራ ለመሄድ ውሳኔ አደረግንና ወደየጋንታችን ተመልሰን ሄድን።

በስልሳ ስምንት ዓመተ ምሕረት ወደ ሜዳ ስገባ ከማእቢኖን መቶ ሜትር በምትርቀው በጋራቢኖ በኩል ነበር። ስወጣም በዚያው በኩል ልወጣ መሆኑን አስቤ በአጋጣሚው እየተገረምኩ በጣም ተከዝኩ። እነዚያ በአዲኢሮብ የሚገኙ አሲምባ፡ ወረአትሌ፣ ሰንገዴ፣ ዳያ፣ ከልአሳና ሌሎቹም ሁሉ ቦታዎች እንዳደግንበት ቦታ የሚቆጠሩ፣ ጥዋት ማታ የምንመላለስባቸው፡ የምንውልባቸውና የምናድርባቸው፣ ብዙ ትዝታ የጣሉብንን ቦታዎች ሁሉ ትተን መሄዳችንን አሰብኩና ውስጤ ተሸበረ። ሰው የሚወደውንና ተወልዶ ያደገበትን ቀዬ ለቆ ሲሰደድ የሚሰማው ጭንቀት ስለተፈጠረብኝ ሆዴ አልችል አለኝ።

ከእነዚያ ቦታዎች ጋር ተያይዞ አብረን ብዙ ያሳለፍን ጓዶቻችንንም ትተን መሄዳችንን ሳስብ ጨነቀኝ። በሕይወት ያሉ ጓዶቻችንን ወደፊት የሚያጋጥማቸውን አናውቅም። ምናልባት እንገናኝ ይሆናል፤ የሞቱትን ጓዶች አደራ በልተን ልንሄድ ነው! የተሠዉ ጓዶቻችንን "እንከተላችኋለን" እያልን የገባነውን ቃል ልናፈርስ ነው! እንግዲህ እነሱን ከድተናቸዋል! ትግል ሲባል ለካስ እንደዚህም አለ? እኛም

እስከ ማታ ድረስ ፍሱሕን ጠበቅነው፣ አልመጣም። ስለዚህ ሦስታችንም የጋንታ መሪዎች ስለሆንን፣ ጋንታዎቻችን ወደነበሩበት ቦታ ሄደን ለየምክትል ጋንታ መሪዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ትእዛዝ ሰጥተን፣ እኛ አንድ ቦታ ደርሰን እንደምንመለስ ነግረናቸው እንደገና ተገናኘን።

በውሳኔያችንም መሠረት የሰሜን ምዕራብን አቅጣጫ ይዘን ወደ መንሰ ቦሎ ጉዞ ጀመርን። መንሰቦሎ እንደደረስን፣ የኪንኪታን ወንዝ ተሻገርንና በቆሎ ምሽላ በኩል አድርገን ሌሊቱን ሙሉ ስንሄድ አደርን። ሲነጋጋ ሲል ኤርትራ ውስጥ የምትገኘው መነኩሲቶ ገባን።

ልክ የኤርትራን መሬት ስንረግጥ ፊታችንን ወደ ደቡብ ምሥራቅ አዞርን። የአዲ ኢሮብ ሶስቱ ታላላቅ ተራራዎች አሲምባ፣ አይጋና ማእቢኖን ናቸው። አይጋ፣ ከአሲምባ ተራራ በስተሰሜን፣ ማእቢኖን ደግሞ በስተምዕራብ በኩል ይገኛሉ። የአሲምባን ተራራ ሐዘንና ሰቀቀን በተሞላበት ስሜት ውስጥ ሆነን ለመጨረሻ ጊዜ በወታደራዊ ሰላምታ ልንሰናበት ነው።

በዚያ ጊዜ ስሜቴ በጣም ተነካና መሪር ሐዘን ወደቀብኝ። ከዓይኖቼ የሚመነጩ የዕንባ ዘለላዎች ጉንጮቼን እየዳበሱ ሲወርዱ ተሰማኝ። ጩሀ - ጩሀ አለኝ። ዞር ስል ግደይና አድሀኖም ወታደራዊ የስንብት ሰላምታውን ቀድመውኝ ጨርሰው ፊንጠር ብለው እየጠበቁኝ ነበር። እንደተረበሽኩ ገብቷቸዋል። እነርሱም ቢሆኑ ከእኔ ባልተናነሰ ሁኔታ ተረብሸው ስለነበር ማንም ማንንም ሊያጽናና አልሞከረም። አጠገባቸው ስደርስ ዞር ብለው መንገድ ጀመሩ። ሦስታችንም አንገታችንን እንደደፋን ሳንነጋገር፣ ሳንተያይ ዝም ብለን መራመድ ብቻ ሆነ። ያ ዝምታችን የት ስንደርስና እንዴት እንደተሰበረ እስከዛሬም አላስታውስም። ልቤ ሁሉን ነገር ትቶ አሲምባ ቀርቷል። የዚያ ጽኑ ዓላማ ምንጭ፣ የቃል ኪዳናችን መሠረት፣ የልቤ ክፋይ በዚያው በአሲምባ ምድር ተቀብሮ ትቼው የምሄድ መሰለኝ፤ አሲምባን ብቻ ነበረ የማሰላስለው።





መነኩሲቶ ተጋድሎ ሀርነት ኤርትራ ወይም ጀበሀ በመባል የሚታወቀው ድርጅት የሚቆጣጠረው ቦታ ነው። ሦስታችንም ወደ ጀብሀዎች ሄደን እጃችንን ሰጠንና ተቀበሉን። መነኩሲቶ ከመግባታችን በፊት ቀድመው የገቡ ብዙ የእኛ ልጆች ነበሩ። ኤርትራ ከገባን በኋላ በሦስተኛው ቀን ቅናፍና የሚባል አከለ ጉዛይ አልፈን ሰራዬ እንደደረስን የአካባቢው የጀብሀ አስተዳዳሪ መጣ። "ሠራዊታችሁ በአጠቃላይ ከአሲምባ ወጥቶ ኤርትራ ገብቷል፤ ጥገኝነት እንድንሰጠውም ጠይቋል" ብሎ ነገረን።

ኤርትራ ገብተን ከጀብሀ ወታደሮች ጋር ወደ መጠለያ ቦታ በመሄድ ላይ እያለን እኔና መቶ አለቃ በሪሁን በወባ ትንኝ ተነደፍንና ታመምን። እኔ እንደምንም እየታገልኩ ባገግምም በሪሁን ግን በጣም ስለባሰበት በጀብሀዎች ሕክምና ወደሚገኝበት ቦታ ተላከ። የቀረነው ጉዟችንን ቀጥለን ለመቆያ ወደተዘጋጀልን ቦታ እንደደረስን መቶ አለቃ በሪሁን እንደሞተ አረዱን። ከዚህ በኋላ በኤርትራ ቆይታችን ጊዜ የወባ በሽታ እየተነሣችብኝ አልፎ አልፎ ታ ሰቸግረኝ ነበር።

ኤርትራ መጠለያ ሰፈር ከደረስን በኋላ ከእኛ በፊት ቀድመው ወደ ጀብሀ መጥተው ከነበሩትም ጋር ተገናኘን። ከእኛ በኋላ የመጡም እየተጨመሩ፣ በአጠቃላይ ወደሰባ አምስት ደርሰናል። ቢደንብ የምንተዋወቀው በሠራዊቱ ውስጥ ስለነበረን ሕይወት፣ በሠራዊቱና በድርጅታችን ውስጥ መጨረሻ ላይ ስለተፈጠረው ችግር መነጋገር ጀመርን።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ድላይ እግሯ ላይ ተመትታ እንደቆሰለች አብራት የነበረው የማነ የነገረኝ መንደፈራ ስንገናኝ ነው። የማነ ከድላይ ጋር አብሮ ሕክምና ላይ ነበረ። እርሱ ትንሽ ቆስሎ ሕክምናውን ጨርሶ መምጣቱ ነው። መቁሰሏን ከሰማሁ ጀምሮ ስለድላይ ምንም ወሬ አላገኘሁም ነበርና የማነ "እኔና ድላይ ሕክምና ላይ አንድ ላይ ነበርን" ብሎ ሁኔታውን ሲነግረኝ በጣም ደስ አለኝ።

"እንዴት ነች? በጣም ተጎድታ ነበር?" ብዬ ጠየቅኩት።

"ደኅና ናት፣ የተመታቸው እግሯ ላይ ነው። በጣም አልተጎዳችም" አለኝና ቅዝዝ አለ።

"ምነው?" አልኩት

"ምንም አይደለም። ግን እሷ ሁሌ የምታወራው ስለአንተ ብቻ ነበር። 'አማኑኤል ከድርጅቱ ከድቶ ሄደል' ሲባል ስምታ 'አማኑኤል በፍጹም ድርጅቱን አይከዳም። ምናልባት ድርጅቱ በምስጢር ለሌላ ሥራ ልኮት ይሆናል። እኔ ግን እንደሚመለስ እርግጠኛ ነኝ' እያለች ሁሌ ስለአንተ ነበረ የምታወራው። ሁልጊዜ እያስታወሰች ታነሣህ ነበር" ብሎ ነገረኝ።

የማነ ይሄንን ሲነግረኝ ድላይ ለምን እንደዚህ እንዳሰበች ገብቶኛል። በሌላ አነጋገር "አማኑኤል እኔን ሳያማክር ለቅቆ አይሄድም" ማለቷ ነበር። እውነት ነበራት፤ ምክንያቱም ዳሞ ወረዳ ላይ እንደተገናኘን "እኔን ሳታማክር ምንም ዓይነት ውሳኔ እንዳትወስን" ስትለኝ "እሺ" ብዬ ቃል ገብቼላት ነበር። እኔ ግን እርሷን ለማማከር ጊዜውና ሁኔታው ያልተመቸኝ ቢሆንም አሁን ግን እንደገና ከሰው ስሰማው ትልቅ ጸጸት ሆነብኝ።

ከአረፋይነ ጋርም ለመጀመሪያ ጊዜ ከድላይ ጋር ስለነበረን ግንኙነት ያወራነው ኤርትራ ውስጥ ከገባን በኋላ ነው። አረፋይነ ከድላይ ጋር ስለነበረን ግንኙነት እንሥቶ እርሱና በጋንታዋ ውስጥ ያሉት ጓደኞቹ በጣም ይጠረጥሩን እንደነበረ ነገረኝ።

አረፋይነ የእርሷ ጋንታ የፓርቲ ኮሚቴ አባል ስለነበረ ሁኔታውን በደንብ ተከታትሏል። "አሁን ሁሉም ነገር አልፏል። ከድላይ ጋር ስለነበረህ ግንኙነት እናማችሁ ነበር። በድርጅቱ ም በኩል ይሁን በግል ስለ ግንኙነታችሁ በደንብ ነበር የምናውቀው። አሁን እስቲ እወነቱን ራስህ ንገረኝ" አለኝና ሐቁን ስነግረው በጣም ተደነቀ።





"በፍጹም አናምናችሁም ነበር። ምክንያቱም የምታደርጉት ነገር ሁሉ የፍቅር እንደሆነ ከሁኔታችሁ ያስታወቅ ነበር። እጅ ከፍንጅ ስለአልተያዛችሁ ምንም ልንላችሁ አልቻልንም እንጂ ሁለታችሁም በፍቅር ክንፍ ብላችሁ እንደነበረ ሁሉም ሰው አውቋል። በተለይ ጠፍታችሁ አድራችሁ የመጣችሁ ጊዜማ የሁሉም ሹክሹኪታ ስለናንተ ብቻ ሆኖ ነበር።

"አሁን እንግዲህ ከሠራዊቱ ወጥተናል፣ ምንም የምትፈራው ነገር የለህም፣ ነጻ ሆነህ፣ ምንም ዓይነት የወሲብ ግንኙነት አልፈጸምንም ብለህ ስትነግረኝ አመንኩህ። ምክንያቱም አሁን የሚያስደብቅህ ምንም ምክንያት የለምና። ደግሞም ሁለታችሁም ወጣቶች ስለነበራችሁ ምንም ነገር ብታደርጉ የሚያሳፍር ነገር እንደሌለው አውቃለሁ። አንተ፣ እውነቱን የምትናገር፣ ንጹሕና ሐቀኛ እንደሆንክ አወቃለሁ፤ ስለዚህ አምንሀለሁ።ማመን ብቻ አይደለም ዓላማችሁን አስቀድማችሁ የወጣትነት ስሜታችሁን ተቆጣጥራችሁ በማሳለፋችሁ፣ ስለሁለታችሁም የተሰማኝን ትልቅ ከብርና አድናቆት ልነግርህ እፈልጋለሁ" አለኝ። ኤርትራ ውስጥ በነበርንበት ጊዜ ከድርጅቱም ጋር በተያያዘ አንዳንድ ውይይቶችን እናደርግ ነበረ። እኛን ያልተማርነውን ልጆች ዝቅ አድርጎ በመመልከት ስለተፈጠረው ችግር "አገለሉን" የሚል ስሜት ያደረባቸው ልጆች አጋጥመውኝ ከእነርሱ ጋር ተወያይቻለሁ።

እኔ ችግሩን እንዴት እንደምመለከተው ነግሬያቸው ከብዙዎቹ ጋር ተስማምተናል።"እንደ እኔ አመለካከት፣ ድርጅቱ በኅብረ ብሔራዊ ትግል የሚያምን ስለሆነ የሁሉንም ብሔር አባላት በእኩል የሚመለከትና የሚቀበል ዓላማ ይዞ የሚራመድ ነበር። ሠራዊቱም፣ ከሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የተውጣጣ ሠራዊት ሆኖ ነው የተደራጀው። የተለያዩ ቋንቋዎች የምንናገር ግን በጓዳዊ ፍቅርና ስሜት አንድነት ያለን ነበርን። በብሔር፣ በቋንቋ፣ በባህል ወይም በሃይማኖት ምክንያት እርስ በእርሳችን ተጣልተን አናውቅም። ልክ ከአንድ ቤተሰብ እንደተወለድን ሆነን ነበር እርስ በእርሳችን የምንተሳሰበው።

"የአካሄድ ልዩነት እየተፈጠረ ሲመጣ ግን በርእዮተ ዓለማዊ ጥያቄዎች ላይ ሲጨቃጨቁ እንደነበረ እናውቃለን። እኛ ኢፍትሐዊነትንና ጭቆናን በማስወገድ ሕዝብን ነጻ ማውጣትን ዓላማችን አድርገን የደርግን ግፈኛ መንግስት ከማስወገድ ተልእኮአችን በቀር ብዙ የምናውቀው ነገር አልነበረንም። በእርማት እንቅስቃሴው ከተገለጸው በቀር በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረውን መሠረታዊ ልዩነት፤ በተለይ ልዩ ሐሳብ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ዓላማ ጠልቀን አናውቅም። በዚህ ምክንያት አንዱ አንዱን ሲከታተል፣ አንዱ ከሌላው ሲጠነቀቅ፣ በኋላም ማሰር ሲመጣ በድርጊት ብቻ ነበር የልዩነቱን ነገር ያየነው።

"ብዙ የምናምናቸውና ተሰሚ የነበሩ ልጆች ሲታሰሩ ብዙዎቻችን ደስ አላለንም። እኛ ደግሞ ከበፊትም አመራሩ የሚያዘንን ስለምናደርግና ስለእነሱ ልዩነት እንደማናውቅ ስለሚያውቁ እኛን ነበር የሚያምኑን። በአመራሩ ላይ ቅሬታ ያላቸው ደግሞ በዚህ የተነሣ በእኛ ላይ ቅሬታ ስለተሰማቸው በነበረብን ድክመት ገብተው ሞራላችንን በመንካት ስሜታቸውን ለመግለጽ ይሞክሩ እንጂ በትምህርታችን ቢሆን ኖሮ ድሮውንስ ለምን እንደዚያ ዓይነት አመለካከት አልተንጸባረቀም ነበር? ብዬ አስባለሁ።

"እኛን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስላልጨረስን "እነኝህ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያልጨረሱ፣ ወታደራዊ ካልሆነ በስተቀር ፖለቲካዊ ብስለት የሌላቸው፣ ያልነቁ፣ የድሮ አመራሮች የሚሉዋቸውን ብቻ የሚሰሙ፣ የድሮ አመራር ቡቹሎች" እያሉ የሚተቹንና የሚነቅፉን በዚሁ ምክንያት እንጂ በሌላ አልነበረም ብዬ ነው የማምነው። ስለዚህ በድርጅቱ የአካሄድ ልዩነት ከተፈጠረ በኋላ የመጣ ከራሳቸው ልዩነት ጋራ የተያያዘ እንጂ ከብሔር ጋር የተያያዘ መሠረት አልነበረውም ባይ ነኝ።

"ከዚህም በተጨማሪ የማግለል ዝንባሌው በእኛ ላይ ብቻ የመጣ ሳይሆን በአየር ወለዶችም ላይ ይሰነዘር እንደነበረ እናውቃለን። አየር ወለዶችንም አንዳንድ





ጊዜ "እነኝህ ነጭ ሠራዊት ያሠለጠናቸው ናቸው፣ ቀይ ሰራዊት አይደሉም" እያሉ የሚተቹ ነበሩ። አየር ወለዶች ግን በወታደራዊም ሆነ በፖለቲካዊ አስተሳሰብ በጣም የበሰሉና ለድርጅቱ ትልቅ ጉልበት የሰጡ እንደነበሩ ማንም አይክድም። በማሠልጠን፣ በመዋጋትና በማዋጋትም፤ በሁሉም በኩል ትልቅ ድርሻ የነበራቸው እንደሆኑ ማንም አይዘነጋም። ስለዚህ አየር ወለዶችም እንደእኛ ሁሉ የመወቀስና የመገለል መከራ ተደርጎባቸው ነበር። ይሄ በስተኋላ በመካከላችን የተከሠተ አነስተኛ መራራቅ የነበረውን ፍቅርና መተሳሰብ በምንም ተአምር ሊሽር የሚችል መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ መታየት የሚገባው አይደለም" ብዬ ስሜቴን ገለጽኩላቸው።

በዚህ ዓይነት ስንወያይ ያጋጠሙኝ በሙሉ በሠራዊቱ ውስጥ እያሉ ስለአሳለፉት የትግል ሕይወት ፍቅርና አንድነት እያነሱ የሚኮሩ ነበሩ። እንዲያውም ያሳለፏቸውን ውጊያዎች፣ የሞቱትን ጓዶች እያስታወሱ የሚያለቅሱም ነበሩ። አንዳንዴ እንዲህ ዓይነት ውይይቶችን እያደረግንና በተለያዩ መንገዶችም ጊዜያችንን ለማሳለፍ እየሞከርን 'መጨረሻችን ምን ይሆን?" እያልን ቀናትን፣ ሳምንታትንና ወራት መቁጠር ጀመርን።

ጀብሀዎች ይቀበሉን እንጂ መጨረሻችን ምን እንደሆነ አላወቅንም። ድርጅቱ ከጀብሀም ሆነ ከሻቢያ ጋር ያለው ግንኙነት እንደተበላሸ እናውቃለን። ከኤርትራ ድርጅቶች ጋር ያለው ግንኙነት በጣም ከመበላሸቱ የተነሣ፣ ኤርትራ ውስጥ የነበሩ ጓዶች አከባቢውን ለቅቀው እንዲወጡ ተደርገው እንደነበር ብዙዎቻችን ሰምተናል። ጌትነት እንደተመታ "እባካችሁ አሳክሙልን" ተብለው ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ከልእሳም እንደዚሁ ሰላስ (የዘርኡ ከህሸን ሚስት) ከፍተኛ ሕክምና አስፈልጓት በሸክም ወደ ኤርትራ፣ ጸሮና ተወስዳ "እናክምም ቦታ የለንም" ብለው መልሰዋታል። ይሁን እንጂ እስከ አሁን እኛን ከፉ ፊት አላሳዩንም። ደግሞም ከድተን የመጣን ስለሆነ በጥላቻ አይተው ከፉ ነገር ሊያመጡብን ይችላሉ የሚል ግምት የለንም።

መውደቃቸውን መስማቴ ነበር። "ምነው አንገቱን ቆርጠን በቀበርነው ኖሮ!" ብዬም እስከ መጸጸት ደረስኩ። ወሬውን ከሰማሁበት ቀን ጀምሮም ከራሴ ጋር ቀን ከሌት በመሟገት የኅሊና ዕረፍት አጣሁ። አሁንም ግን ራሴን ስፈትሸው የምወደውን ጓዴን አንገት ተቆርጦ ማየት ለመቻሌ እርግጠኛ አይደለሁም። በሌላ በኩል "ምነው እርሱ እምቢ ባይልና መጀመሪያ በተመደበበት ቡድን በቆየ ኖሮ" እላለሁ። እንደዚያ ቢሆን እርሱም እናቱም ይተርፉ ነበር የሚል ባዶ ሐሳብ ይመጣብኛል። በሌላ በኩል እኔ ከመድረሴ በፊት የነበሩት ጓዶች በራሳቸው ውሳኔ እንዳሉት ቢፈጽሙት ምን ነበረበት? እንዲያ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ቢያንስ እናቱን አእምሮአቸውን ከማጣት ማትረፍ ይቻል ነበረ እያልኩ ፋይዳ በሌለው ሐሳብ ስዋልል ከርሜአለሁ። በዚያ ሰሞን ስለ የአቢኢዮና ስለ እናቱ እያሰብኩ ለብዙ ቀናት እንቅልፍ አጥቼ እያለቀስኩ ቀን ከሌት በጭንቀት ማሳለፍ አልለቅህ ብሎኝ ስቸገር ከረምኩ። አዎ! ሁሉም አለፈ - ከእኔ ጸጸት በስተቀር።

ገዳሪፍ ወሬ የሚመጣው ከዚህም ከዚያም ነው። ገዳሪፍ ከሚመላለሱ ነጋዴዎች ጋር ከሚተዋወቁት ሰዎች ሊሆን ይችላል። እነርሱ "ከአካባቢያቸው፣ ከእኛና ከቤተሰብ ጋር የተያያዘ ወሬ አግኝተው ሲያመጡ ወደ እኛ ይደርሳል። በሌላ በኩል በየጊዜው ከሠራዊቱ እየከዱ በሚመጡ አባላትም በኩል የሚደርሱን ወሬዎች ነበሩ። ከሠራዊቱና ከፓርቲ ሥራ ጋር በተያያዘ ወደ ገዳርፌ የሚመጡና ሱዳን ውስጥ የሚቀመጡ የድርጅት ሰዎች በየጊዜው እኛ ወደአለንበት ብቅ እያሉ ያነጋግሩን ነበር።

ተስፋዬ ኢዲዩ፣ ሱዳን ውስጥ ለድርጅቱ ሥራ ከተቀመጡ የድርጅት ሰዎች አንዱ ስለነበር፣ አንዳንዴ እየመጣ ስለአለብን ችግርና በድርጅቱ ላይ ስለነበረን ቅሬታ እየጠየቀን ወደ ድርጅቱ እንደገና እንድንመለስ ለማሳመንና በሌላም ጉዳይ እኛ ዘንድ ይመላለስ ነበር። አንድ ቀን ምን እንደሰማ አላውቅም መጣና "ለድላይ ደብዳቤ መላክ ከፈለግክ ጻፍና እኛ እናደርስልሀለን" አለኝ። የምጽፈውን





ደብዳቤ ድርጅቱ ሊያነበው ስለሚችል፣ ምንም ጥቅም የለውም ብዬ ደብዳቤ ለመላክ እንደማልፈልግ ነገርኩትና ከእሱ ጋር ያለን ግንኙነትም በዚሁ አበቃ።

በሱዳን ቆይታችን ከነበረብኝ የጤና ችግር አንዱ ኤርትራ የያዘኝ ወባ አልፎ አልፎ እየተነሣብኝ መቸገሬ ነው። እንደምንም በመድኃኒት ኃይል እየተሻለኝ ደኅና እሆንና ትንሽ ወራት ቆይቶ እያገረሸ ይመለስብኝ ነበር። በዚያን ጊዜ ሜዳ እያለን በሐኪምነት ስትሠራ የነበረችው ጀዝ በሕክምናውም በመድኅኒቱም እየተባበረችኝ ትረዳኝ ነበር።

አንድ ቀን ለድርጅት ሥራ ሱዳን ካሉና ከሜዳ ከሚመጡት መካከል አንድ ከንፉ የሚባል የሠራዊት አባል ለድርጅት ሥራ መጥቶ ተዋውቀን "አማኑኤል እባላለሁ" ስለው ደነገጠና ትክ ብሎ አይቶኝ

"አንተነህ እንዴ አማኑኤል፣ ስለአንተ ብዙ ነገር ሰምቻለሁ" አለኝ።

"ሳቅ እልኩና ከማነው የሰማኸው?" ብዬ ጠየቅኩት። ምናልባት ከድላይ ወይም ደግሞ ከሌሎች ከድላይ ጋር ስለነበረን ግንኙነት ሰምቶ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።

"ጸጋዬ ደብተራው ሁል ጊዜ ነው የሚያነሣህ። በጣም ነው የሚወድህ። በጣምም ነበር የሚተማመንብህ" አለና እንደገና በደንብ አጥንቶ ተመለከተኝ።

ጸጋዬ ደብተራውን በጣም እንደምወደውና እሱም ለእኔ ጥሩ አመለካከት እንደነበረው ባውቅም ያን ያህል ያስታውሰኛል ብዬ ገምቼ አላውቅም። ከከንፉ አፍ ያን በመስማቴ ደስ አለኝ። "ደኅና ነው ጸጋዬ?" ብዬ ጠየቅኩት።

"ደኅና ነው" ብሎ መለሰልኝና የጀመረውን በመቀጠል "ወሎ፣ ጎንደር፣ ብዙ ችግር እንዳሳለፍክ፣ በውጊያም ላይ ብዙ ቦታ እንደተካፈልክና ብዙ ልምድ እንዳለህ ይናገር ነበር። በዓላማህ ጠንካራ እንደነበርክና ለሠራዊቱ የነበረህን ፍቅር፣ ሌላም ሌላም ሲናገር ሰምቸው፣ "አማኑኤል ምን ዓይነት ልጅ ነው?" እል ነበር። ዛሬ ላገኝህና ልተዋወቅህ ዕድል ስላገኘሁ በጣም ደስ ብሎኛል። ከተመለስኩና ጸጋዬን

ካገኘሁት መቼም ስለአንተ ስነግረው በጣም ደስ እንደሚለው እርግጠኛ ነኝ' አለኝ - ፈግግ ብሎ።

የድርጅት ሰዎች አግኝቼ ባወራሁ ቁጥር ሁኔታዎች እየተሻሻሉ እንደሆነ ይነግሩኛል። ወደ ትግል ዓለም እንድመለስም ለማሳመን ሲጥሩ ቆይተዋል። ቀስ በቀስም ወደሥራዊቱ የመመለሱ ነገር በአእምሮዬ መጉላላት ጀመረ። ሁኔታዎች እየተሻሻሉ ናቸው ወደሚል አመለካከት አዘንብዬ ከእራሴ ጋር መነጋገርም ጀመርኩ። ለማናቸውም ግን "እሺ! ጊዜ ስጡኝና ላስብበት" ከማለት ያለፈ ሌላ ፍንጭ ልሰጣቸው አልፈለግሁም።

ከእነርሱ ጋር ሳወራ እነዚያ ያለፉ የሚያስቆጩኝና የሚያቃጥሉኝ ነገሮች ቀስ እያሉ እየደበዘዙ ሲሄዱ ይሰማኛል። አሁን ደግሞ ስለጸጋዬ ደብተራው ስሰማ ለመመለስ ውስጤ የሚገፋፋበት ተጨማሪ ምክንያት አገኘ። ስለጸጋዬ ደብተራው ሳስብ "ምነው ሄጄ አጠገቡ በሆንኩ። ምነው እንደበፊቱ በቀመለኝና ሲጨርስ ፊቱ ላይ የሚነበበውን የእናትነት ስሜት ባየሁ። ምነው አጠገቡ ሆኜ ከፉ እንዳይነካው በጠበቅኩት" እላለሁ። በዚያ ላይ ሳልሰናበታትና ሳላገኛት በድንገት የተለየኋት ድላይ እዚያ አለች። ዓይኗን እንኳ ባየሁ የሚል ጉጉት ደግሞ በውስጤ ይብላላል። ስውል ሳድር ውስጤ የበለጠ እየተገፋፋ በየቀኑ መነሣሣቱ እየጨመረብኝ ሄደ።

ከእውነቱ ጋር ላለመፋጠጥ ነው እንጂ እኔ በወጣሁበት ጊዜ ድርጅቱ የነበረበት ውጪያዊም ሆነ ውስጣዊ ችግር እንዲህ በዋዛ የሚሻሻል እንዳልሆነ ልቦናዬ ይነግረኛል። ልቦናዬ የሚነግረኝን መስማት አልፈለግኩም። እንዲያውም ሳባብለው ቆይቼ "እምቢ አልሰማህም! እመለሳለሁ!" በማለት በልቦናዬ ማመጽ ጀምሬያለሁ።

ከሠራዊቱ ተሰናብተውና ወይም ጠፍተው የሚመጡ አባላትን ሳገኝ ስለሁኔታው ሳልጠይቅ አላልፍም። ሁሉም የድርጅቱ ሁኔታ ጥሩ እንዳልሆነ





እንዲያውም እየባሰበት በመሆኑ በፍጹም እንዳልመለስ ነበር የሚነግሩኝ። አንዳንድ በአመራሩ ያልተደሰቱ ጓዶች ቅሬታቸውን እንዳቀረቡና ከአመራሩ ጋረ እየተፋጠጡ እንደሆነም ሰምቻለሁ። እንዲያውም በከፉ መተያየት እንደበዛና ውጥረት እንደነገሠ ሲነግሩኝ ግራ ገባኝ። ሆኖም ግን ላለማመን ሰበብ እየፈለግሁ ከራሴ ጋር እታገላለሁ። ከከዱ አባላት መቼም ብዙ አዎንታዊ መረጃ መጠበቅ እንደማይቻል አውቃለሁ። በሚናገሩት ውስጥ ግን ብዙ እውነታ እንደነበረ ተሰምቶኛል። ውስጤን ግን "እምቢ" አልኩት።

በዚያ መወላወል ላይ ሆኜ ሐዲሽ በየነ ገዳሪፍ መጣና ተገናኘን። ከሐዲሽ ጋር የምንተዋወቀው አሲምባ እያለሁ ሲሆን ያኔ ከፍተኛ የመረጃ ክፍል ባለሥልጣን እንደነበረ አውቃለሁ። ሐዲሽ ገዳሪፍ የመጣው ድርጅቱን ከድቶ ሳይሆን ለድርጅቱ ሥራ ነበር። "አማኑኤል እንኳን አገኘሁህ" አለኝ ሐዲሽ ከሰላምታ በኋላ። በመገናኘታችን ደስ መሰኘቱን ፊቱ ይናገራል። ሞቅ ያለ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስለገዳሪፍ ኑሮ፣ አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለሁና ስለጤንነቴ ጠየቀኝ። ስለጤንነቴም ሆነ ስለጀመርኩት ትምህርት በጠቅላላ ስለሕይወቴ ሁሉንም ነገር ነገርኩት። ስለጤንነቴ ማድረግ ያለብኝን ጥንቃቄ መከሮኝ ትምህርት በመማሬ ደግሞ በጣም መደሰቱን ነገረኝ።

እኔም በተራዬ ወደ ድርጅቱ ለመመለስ መፈለጌን ሳልነግረው፤ ሁልጊዜ ከድርጅቱ ጠፍተውም ሆነ ለሥራ ሲመጡ ለማንኛውም የማቀርባቸውን ጥያቄዎች በደፈናው፣ ጠየቅሁት። ከዚያም የበለሳ ሁኔታ እንዴት እንደንበረ ጠየቅሁት።

"ሁኔታዎች ጥሩ አይደሉም፤ ነገሮች ሁሉ የባሰ እየተበላሹ ነው" ብሎ ሲመልስልኝ ጆሮዬን ማመን አቅቶኝ፣ በጣም ደነገጥኩ። እኔ እንደዚያ ዓይነት መልስ የምጠብቀው ከድተው ከመጡ አባላት እንጂ እንደእርሱ በድርጅት ሥራ ላይ ካሉት አልነበረም። ከዚያ ቀደም ካነጋገርኳቸው መካከል

እንደዚያ ዓይነት ያልተጠበቀ ምላሽ አላገኘሁም። የሀዲሽ ምላሽ ግን የመጀመሪያዬ ነበረ።

"ታዲያ መጨረሻው ምንድነው። ሁሉም ነገር አበቃለት? ድርጅቱ ከፈረሰ ሠራዊቱም ሊበተን ነው ማለት ነው?" አልኩት ድንጋጤዬ እያስታወቀብኝ። ዝርዝሩን እንዲነግረኝ እየጠየቅኩት ነበር።

"አይታወቅም፡ ምናልባት አንዳንድ ነገሮች ከተለወጡ እንደገና መስመር ለማስያዝ የሚቻልበት ሁኔታም አለ። ቢሆንም በቅርቡ ሳይሆን ጊዜ የሚጠይቅ ይመስለኛል" አለኝ ገጽታው ላይ ተስፋ መቁረጥ እየታየበት። ብዙ ካወራን በኋላ እሱን ባላገኝ ኖሮ ልመለስ እያሰብኩ እንደነበረ ገለጽኩለት።

"በጭራሽ! አሁን ለመመለስ እንዳታስብ! አንተ ብዙ አስተዋጽኦ ያደረግክና ብዙ ልምድ ያለህ ነህ። ሁኔታዎች እስኪሻሻሉ ትምህርትን ተማር በኋላ ብዙ ልትጠቅመን ትችላለህ። እንደእኔ፣ እዚሁ በተቻለህ መጠን በርትተህ ብትማርልን እመርጣለሁ" አለኝ።

"እንዲህ መጥፎ ከሆነ አንተስ ለምን በዚሁ አትቀርም?" ብዬ ጠየቅኩት።

"እኔ ዕድሜዬም ገፍቷል፣ ካሁን በኋላ የከተማ ኑሮ እንደ አዲስ መጀመር አልችልም። እዚሁ ብሞት ነው የሚሻለኝ። ሁሉ ነገር ተበላሽቶ ድርጅቱ ቢበተንና ብቻዬን ብቀር እንኳ ጫካ ገብቼ ቀሪ ዕድሜዬን እገፋለሁ እንጂ የከተማ ኑሮን አልሞክረውም" ሲለኝ በጣም አሳዘነኝ።

ሐዲሽን ካገኘሁ በኋላ የመመለስ ሐሳቤን እርግፍ አድርጌ ተውኩትና ስለወደፊቱ መደበኛ ሕይወቴ ማሰብና ማቀድ ጀመርኩ። ማታ ወደ መኝታዬ ስሄድ ቀን ከሰማሁት ተነሥቼ የማስታውሳቸውን ነገሮች ወደ አእምሮዬ እያመጣሁ አብላላለሁ። ድርጅቱ በአመራሩ ውስጣዊ ችግር የተነሣ ከማይወጣበት ችግር ውስጥ ገብቶ ከፊቱ ያለውን አደጋ እንኳ ለማየት እያቃተው ነበር። በዚህም ራሱን ጠልፎ የጣለው ራሱ እንደሆነ አስባለሁ። በዚያን ጊዜ ቅሬታ የነበረው





ከወያኔ ጋር በተነሣው ጦርነት ብቻ ሳይሆን በፊትም የነበረ ነው። ለምሳሌ እርግት እንቅስቃሴ ግቡን አልመታም። ሁኔታዎች እየተበላሹ ለመምጣታቸው አንዱ ምልክት ወታደራዊ ዲሲፕሊን ጭምር እየላላ መሄዱ ነበር። ወታደራዊ ዲስፒሊንና ሞራል ከሌለና ከተበላሸ ጦርነትን በጀብደኝነት ብቻ ለመዋጋት አይቻልም።

በዚያን ጊዜ ከከተማ ወደ ሠራዊቱ ሲገቡ የነበሩ ጓዶች ከተማ ለቀይ ሽብር የተጋለጡ እለያም ከደርግ ሠራዊት ከድተው የሚመጡ አባላት ነበሩ። ከዚያ ውጭ እርሶ አደሩን ለሠራዊት አባልነት አልመለመለም። እርሶ አደሩ ደግሞ ከእኛ ጋር ለመሰለፍ ብዙ ፍላጎት ነበረው፤ እኛ ግን በደንብ አልቀረብነውም። እናም ድርጅቱ የምሁራን ብቻ ሆነ። እንደዚያ ዓይነቱን አካሄድ ይመስለኛል ብዙዎቹ የተቃወሙት። የውስጥ ችግሮቹ ሲባባሱ ደግሞ በተለያየ መልክ ይገለጹ ነበረ። ለምሳሌ የውቅሮ ተልእኮ አለመሳካቱ ጠላት ቀድሞ መረጃው ስለደረሰው ነበር። ጠላት መረጃ ሊያገኝ የቻለው ደግሞ ፓርቲው በወታደራዊ ተልእኮው ተሳትፎ ስለነበረው ከፓርቲው ውስጣዊ ልዩነት ጋር በተያያዘ መረጃ አሳልፎ የሰጠ አካል በመኖሩ እንደሆነ ይገመታል። ሠራዊቱን ለማስመታት ወይም ማጥቃቱን እንዲተው የፈለገ ወገን ያደረገው ነገር ነበረ። አለበለዚያ ግን ምስጢሩን የሚያውቁት የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ስለነበሩ መረጃው በሰፊው የተዳረሰ ባለመሆኑ ሊወጣ አይችልም።

መረጃውን ያወጡት የሠራዊቱ አባላት ነበሩ ለማለት በፍጹም አይቻልም። መረጃ ለጠላት በመንገር ሕይወታቸውን ለጠላት አጋልጠው ሰጥተው ከእኛ ጋር ጦርነት ውስጥ እንዴት ይገባሉ? ነገር ግን መረጃውን ጠላት እንዳወቀ ሲሰሙ ዕቅዱን ይሰርዙታል ብለው የከተማው ሰዎች አስበው ይሆናል። አሁንም ድረስ ብዙዎቹ አባላት የሠራዊቱ አመራር መረጃው መውጣቱን ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ሰምተው እንደነበረ አያውቁም። እኔም ይሄንን ምስጢር እስከ አሁንም ድረስ ለማንም አልተናገርኩም።

በ1972 ዓ.ም. የመጀመሪያ ወራት ውስጥ መሐመድ እንድሚፈልገኝ ነግሮኝ አንድ ሻይ ቤት ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝን። በቀጠሮው ሰዓት መሐመድ የመጣው ከገብረ ጻድቃን ነጋሽ ጋር ነበር ። ከተቀመጥኩበት ተነሥቼ ተቀበልኳቸው። ሁለቱም ከባድ የሐዘን ስሜት ይታይባቸዋል፣ የተፈጠረ ችግር እንዳለ ተሰማኝ። እንደተቀመጡ ተጨማሪ ጊዜ ሳልሰጣቸው "ምነው፣ ደኅና አይደላችሁም እንዴ?" ብዬ ጠየቅሁ። "እኛ እንኳን ደኅና ነን። አንድ የሚያሳዝን ነገር ገብረ ጻድቃን ሰምቶ ነገረኝና እሱን ልንነግርህ መጣን" አለ መሐመድ።

"ሰሞኑን ከበለሳ የመጣ ሰው በአጋጣሚ ስለ ድላይ አንድ ወሬ ነገረኝና..." አለና ገብረ ጻድቃን ዐረፍተ ነገሩን ሳይጨርሰው፣ አንገቱን ወደመሬት ደፋና ዝም አለ።

ግራ ገብቶኝ ወደ መሐመድ ዞር ስል እርሱም ፊቴን ማየት የፈራ ይመስል አንገቱን ወደታች አቀርቀረና ዝም አለ።

"ምንድነው የሰማኸው? ድላይ ምን? ድላይ ምን ሆነች አሉህ?!" ብዬ ገብረ ጻድቃን ላይ አፈጠጠኩበት። እርሱ ግን አንገቱን ወደታች እንዳቀረቀረ ዝምታውን ቀጠለ።

"ምን ሆናችኋል?! ምንድነው የሰማችሁት?! ድላይ ምን ሆነች? ንገሩኝ እንጂ! ድላይ ምን ሆነች? ታመመች? ቆሰለች?! ብቻ ሞተች እንዳትሉኝ?" ትዕግሥት አጥቼ በጥያቄ አጣደፍኳቸው። ልሰማ የመረጥኩትን ማስቀደሜና ልሰማ የማልፈልገውን ማራቄ ነበር። ውስጤ ግን እውነተኛው በመጨረሻ የተናገርኩት እንደሆነ ነግሮኛል። ብቻ ላለመቀበል እየታገልኩ መልሳቸውን መጠበቅ ጀመርኩ።

መሐመድ ቀና አለና አንገቱን በአዎንታ ነቀነቀ። ገብረ ጻድቃንም ተከተለና ቀና ብሎ በትካዜ እየተመለከተኝ እርሱም አንገቱን በአዎንታ ነቀነቀ። "ትናንት





ነው የነገሩኝ። ኃይሏ ከነበረችበት ቦታ ወደሌላ መንደር ስትሄድ ያደቡ ሽፍቶች ሳታያቸው ተኩሰው እንደመቷት ነው የነገሩኝ" አለ።

"እና ማንም አልደረሰላትም!?"

"እንደነገሩኝ ከሆነ ተኩሱ እንደተሰማ በቅርብ የነበሩ ጓዶች ደርሰውላት ነበር። ግን የተመታችው መጥፎ ቦታ ላይ ስለነበረ ልትተርፍ አልቻለችም"" አለ።

የምናገረውና የምሆነው ነገር ጠፋኝ። ክንዶቼን ጠረጴዛ ላይ ተከልኳቸውና፤ ጉንጮቼን በመዳፎቼ ይዤ አንገቴን ወደታች ደፋሁና ጸጥ አልኩ። እነርሱ ቀና ብለው በስቀቀን እየተመለከቱኝ ነበር፤ አንገት የመድፋቱ ተራ ደግሞ የኔ ሆነ። ከሰውነቴ አንድ አካሌ ተቆርጦ እንደተወሰደ ያህል የሆነ ጎዶሎነት ተሰማኝ።

"ከአሁን በኋላ አንገናኝም ዛሬ የመጨረሻ ቀናችን ነው" ብላ የተናገረችበት ድምፅና ፊቷ ላይ የነበረው ስሜት ዓይኔ ላየ መጣ። ራሴን መቆጣጠር ሊያቅተኝ ደረሰ። ሰውነቴ እንደመንቀጥቀጥ አደረገው፤ ሆዴ ውስጥ የሚተረማመስ ነገር ተሰማኝ። ዕንባየ ገደቡን ጥሶ መውረድ እንደጀመረ የታወቀኝ በጉንጮቼ ላይ በተሰማኝ ለስ ያለ ሙቀት ነበር። ድንዝዝ ብየ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ አላውቅም፤ ሁለት እጆች የግራና ቀኝ ትከሻዬን ሲዳብሱኝ፤ የመሐመድና የገብረ ጻድቃን የማጽናናት ቃላት ወደጆሮዎቼ ሲፈሱ ከሩቅ ይሰማኛል። " በቃ ምንም ማድረግ አይቻልም፤ ሞት ያለ ነገር ነው። አንተ ደግሞ ብዙ ክፉ ነገር ያየህ ሰው ነህ፤ ቻል አድርገው ... " የተለመዱ የማጽናኛ አረፍተ ነገሮች ነበሩ። ቢሆንም ግን በቅርቤ ስረዳና ውስጤ ድረስ ሲዘልቁ የማበረታታት አቅም ነበራቸው። የተለመዱ ቢሆኑም ቃላቱ በተወረወሩ ቁጥር ውስጤ "አዎ! አዎ!" እያለ እንድቀበል ሲታገል ታወቀኝ። በእውነትም በተወሰነ ደረጃ ቀስ በቀስ ራሴን ለመመለስና ቀና ለማለት አገዙኝ።

ከዚያ በኋላ በቀዘቀዘ ስሜትም ቢሆን ፊት ለፊት እየተያየን ማውራት ጀመርን። መሐመድ፣ እኛ በነበርንበት ኃይል ሐኪም ሆኖ ሲሠራ የእኔንና

የድላይን የቅርብ ግንኙነት በሚገባ ያውቃል። በቴዎድሮስ ባሪያው የሚመራው የእነ ድላይ ጋንታ አባልም ስለነበረ፣ ድላይ ከጋንታዋ ተለይታ በተለያየ ጊዜ ከእኔ ጋር ስንሄድ አይቷል። ከሁኔታችን ግንኙነታችን ምን ያህል እንደነበረ እንኳን እንደ መሐመድ ቀርቦ ያየበወሬ የሰማሁሉ የሚያውቀው ነበረ። ሱዳን ከመጣን በኋላ ከእርሱ ጋር በጣም ተቀራርበን ምናልባትም ሱዳን ከእርሱ በላይ ድላይን የሚያውቃት ሰው ስላልነበረ ስለድላይ ለማውራት በነበረኝ ፍላጎት ሳይሆን አይቀርም። መሐመድ በሱዳን የምስጢር ጓደኛዬ ሆኗል፤ ሁሉንም ነገር የማማክረውም ለእርሱ ብቻ ነበር። ስለኃይላችን ስናወራ ድላይ ሳትነሣ ቀርታ አታውቅም። በዚያ ላይ ከድላይ ጋር ብቻችን ስላሳለፍናቸው ጊዜያትም የነገርኩት እነግረው ነበረ። ከበለሳ ብዙ አባላት እየጠፉ ሲመጡ ድላይም ትመጣና እንገናኝ ይሆናል ብዬ እንዴት በጉጉትና በተስፋ እጠብቃት እንደነበርም ያውቃል። ገብረ ጻድቃን ወሬውን እንደሰማ መሐመድን የፈለገው ይህንን ጥብቅ ግንኙነታችንን ስለሚያውቅ ይመስለኛል።

ወደ ገብረ ጻድቅን ዞር አልኩና ወሬው ምን ያህል እርግጠኛ እንደነበር ጠየቅኩት። በቦታው የነበረ፣ በደንብ የሚያውቀውና የሚያምነው ሠራዊቱን ለቆ የመጣ አባል እንደነገረውና ሱዳን ለድርጅቱ ሥራ ከሚመላለሱ ሰዎችም ማረጋገጫ እንዳገኘ ነገረኝ። ገብረ ጻድቃን ዝም ብሎ ያልተረጋገጠ ወሬ የሚቀበል አይነት ሰው እንዳልሆነም አውቃለሁ። የድላይ መርዶ ግን በጣም ስለከበደብኝ በቀላሉ ልቀበለው የምችለው ስላልሆነ ነበር እርግጠኛነቱን ልጠይቀው የተገፋፋሁት።

ከእነመሐመድ ጋር ከተለያየሁ በኋላ ለብቻዬ ከድላይ ጋር ያሳለፍናቸውን ጊዜያት እያሰብኩ መንገድ ለመንገድ ዕንባዬን እያዘራሁ ወደ መኖሪያዬ ቦታ ደረስኩ። ማንንም ሰው ማናገር አልፈለኩም፤ ሰው የሚባል ፍጡር አስጠላኝ። ፍላጎቴ ብቻዬን መሆን ነበርና ከሰው ሁሉ ሸሸሁ። ለወራት





ያህል እንዲሁ ከሰው ጋር መነጋገር እንዳቃተኝ፣ ከድላይ ጋር ስላሳለፍናቸው ጊ ዜያት ብቻ እያሰብኩ በሀዘን አረንቋ ውስጥ እንደሰመጥኩ ሰነበትኩ።

***

ሌላው የማልረሳው ሱዳን ውስጥ ያገኘሁት አንተነህን ነበር። አንተነህ ቀይ ጸጉረ ሉጫ ዓይኖቹ በጣም የሚያምሩ መልከ መልካም፣ በጠባዩም በጣም ጥሩ ልጅ ነው። ተዋውቀን ብዙ ግዜ አብረን ባንቆይም፣ በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ ተግባብተን ልብ ለልብ ተገናኝተን ነበር። ከአንተነህ ጋር የተዋወቅነው ወደ ጎንደር ትሄዳለች የተባለችውና መጨረሻ ላይ መሪ ሆኜ የተመደብኩባት ጋንታ ሀያ ስድሥት ውስጥ ነው። እርሱ በምክትል ጋንታ መሪነት ነበር የተመደበው። ኢጋጣሚ ሆኖ ሱዳን ከገባሁ በኋላ ካርቱም ውስጥ በሩቅ አየኝና እየሮጠ መጥቶ "አማኑኤል! አማኑኤል!" ብሎ ጠራኝ። የጠራኝን ሰው ለማረጋገጥዞር ብዬ ስመለከት አንተነህን አየሁት። እየሮጠ መጥቶ አቅፎ ሳመኝና ሻይ ቡና እንጠጣ ተባብለን፣ ካዛብላንካ የሚባል ካፍቴሪያ ገባንና አይስክሬም እየበላን መጫወት ጀመርን።

ልንለያይ ስንል "እንግዲህ መቼ እናደምንገናኝ ቀጠሮ እናድርግ" አልኩት። "እንኳን ዛሬ አገኘሁህ እንጂ፣ እኔማ መሄዴ ነው" አለኝ።

"እንዴ! መቼ መጥተህ ነው መሄዴ ነው የምትለኝ?"

"ከመጣሁማ አንድ ወር ይሆነኛል"

"እንዴት በአንድ ወር አለቀልህ? ደግሞስ ወዴት ሀገር ነው የምትሄደው?"

"ወደ እንግሊዝ ሀገር ነው የምሄደው"

"ያውም እንግሊዝ?! እንዴት ነው በአንድ ወር ሊያልቅልህ የቻለው?"

"አይ እዚህ እንደገባሁ ለቤተሰቦቼ ደውዬላቸው ፓስፖርትና ትኬት ይዘውልኝ ስለመጡ ነው"

"እንዴ አንተ የእነዚያ የቤተ መንግሥቶች የአምስት መቶዎቹ ዘር ነህ እንዴ?" ስለው ከት ብሎ ሳቀና አቀፈኝ፤ በዚያው ተለያየን።





ቀስ በቀስ ጊዜው ሲደርስ ለእኛም ወደ ውጪ የመሄድ ዕድል ስለመምጣቱ ወሬ መናፈስ ጀመረ። በዚያ ጊዜ የወባ በሽታ ተቀስቅሳብኝ ስተኛ ስነሣ ነበረ የከረምኩት። እንዲያውም በየጊዜው እየተመላለሰች የሕክምና እርዳታ ያደረገችልኝ ጆዝ ባትኖር ኖሮ እጎዳ ነበር። በተለይ የአሜሪካ ዕድል ከመጣልኝ በኋላ በሕመሜ ምክንያት ዕድሉን እንዳላጣ ስትል በቶሎ እንዳገግምና ለበረራ እንድዘጋጅ በጣም ተጨንቃ ነበር ጤናዬን የምትከታተለው። በመጨረሻም ሁሉም ነገር ሲሳካ ምን ያህል እንደተደሰተች አልረሳውም፤ ውለታዋን ሁሌ አስታውሰዋለሁ።

የአየርላንድ የበጎ አደራጎት ድርጅት ሠራተኛ የነበረችውን አልማዝንም በፍጹም አልረሳትም። ልዩ ድጋፍ እንድናገኝ ለተባበሩት መንግሥታት የስደተኞችና መልሶ ማቋቋም መሥሪያ ቤት ደብዳቤ እያጻፈች እኔንም ጨምሮ ብዙ ጓደኞቻችን እንድንመዘገብና ተቀባይነትም እንድናገኝ ብዙ አግዛናለች። አልማዝን አሜሪካ ከገባሁ በኋላ የሕክምና ባለሙያ ሆና ካናዳ ውስጥ አግኝታለሁ።

***

## ካሕሳይ አብርሃ ብስራት

### አሜሪካ

"ስለሞቱት ማዘን ስለኖሩት አለማዘንና አለማወደስ አይደለም። ሁሉንም ታሪክ ያስተሳስራቸዋልና"

ያገሬ ፀሐፊ

አሲምባ፣ በለሳም፤ የኢሕአፓ የገጠር ሠራዊት በሆነው፣ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠ ራዊት (ኢሕአሠ) አማካይነት፣ ስንዋጋና ስንፋለም ቆይተን፣ በመጨረሻ ወደ ሱዳን መሄድ ግድ ሆነና ሱዳን ገባን።

ሱዳን ለሁለት ዓመታት ያህል እንደቆየሁ፣ በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ የመልሶ ማስፈር ፕሮግራም አማካኝነት እንቀበላለን ወደሚሉ ሀገሮች ስደተኞችን መላክ ተጀመረ። በተለይ ወደ አሜሪካ፣ ካናዳና ጀርመን ለመሄድ አንዳንድ ዕድሎች እየተመቻቹ ነበር። እኔም አጎቴ ዶክተር ክንፈ ረዳ ፖርተሪኮ በሚባለው የአሜሪካ ግዛት ይኖር ነበር። በእርሱ በኩል ይህን ዕድል አገኘሁና የዩናይትድ ስቴትስ የካቶሊክ ኮንፈረስ የሚባል ድርጅት በዋንኛነት ስፖንሰር አድርጎኝ ኅዳር 14 ቀን 1973 ዓ.ም. አሜሪካ ገባሁ።

ፖርተሪኮ ስደርስ አጎቴ ተቀበለኝ።ፖርተሪኮ በጣም ውብ ደሴት ናት። ከተማዋ ሳንዋን ይባላል። ለብዙ ዓመታት በእስፓኒሽ ቅኝ ግዛት ተይዛ ስለነበረ አብዛኛው ነዋሪዎቿ የስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው። ፖርተሪኮ፣ ከሚያሚ አልፎ፣ ኩባን አልፎ ወደ ታችኛው የአሜሪካ ክፍል የምትገኝ ሀገር ናት።

ከአጎቴ ጋር ከተገናኘሁ በኋላ "ምንድነው ዓላማህ? ምንድነው የምትፈልገው?" ብሎ ጠየቀኝ።"እኔ የምፈልገው መማር ነው" አልኩት። በረሐ እያለሁ ባለመማሬ ይደርስብኝ የነበረው መንኳሰስ ያሳደረብኝ የቁጭት ስሜት በአእምሮየ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ እንደያዘ ነበረ፡፡ ስለዚህ "እማራለሁ" አልኩና እዛ በከተማው በሚገኘው ወርልድ ዩኒቨርሲቲ አመልክቼ የመጀመሪያ ፈተና ወሰድኩ።





የዩኒቨርሲቲውም ሰዎች ውጤቴን አይተው መውሰድ ያለብኝን ኮርሶች ነገሩኝ፤ በሚገባ ተከታትዬ በጥሩ ውጤት አለፍኩ።

ያመጣሁት ከፍተኛ ውጤት የዕድል በሮችን ይከፍትልኝ ጀመር፤ መልካም አጋጣሚዎቹም ተበራከቱ። ቢሆንም ደሴቷ የስፓኒሽ ተናጋሪዎች የሚበዙባት ስለሆነች የቋንቋ ችግር ነበረብኝ። ጥረትና ዕድል ከጎኔ ነበሩና ውጤቴ ነጻ የትምህርት ዕድል እንዳገኝ ረዳኝ። በእንግሊዝኛ መማር ወደምችልበት ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ወዳለው የዚሁ ዩኒቨርሲቲ ቅርንጫፍ ተላክሁ። ዋሺንግተን ዲሲ የሚገኘው ኮሌጅ ትንሽ እንደቆሁ አንድ ናይጀሪያዊ ፕሮፌሰር ተዋወቅሁ። አንድ ቀን ፕሮፌሰሩ ወደ መሥሪያ ቤቱ ጠራኝና "እዚህ ምን ለማድረግ ነው የመጣኸው?" አለኝ።

"እዚህ የመጣሁት በእንግሊዘኛ ለመማር ፈልጌ ነው። የነበርኩበት ትምህርት ቤት አብዛኞቹ ስፓኒሽ ናቸው፤ መጠቀሚያ ቋንቋቸውም ስፓኒሽ ነው። ዲኑ ዶክተር ባወር ጥሩ ውጤት እንዳመጣሁ አይቶ፤ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብማር የተሻለ እንደሚሆን በማሰብ ነጻ የትምህርት ዕድል እንዲሰጠኝ በማድረግ ነው ወደዚህ የላከኝ" አልኩት።

"በጣም ጥሩ አድርጓል። የትምህርት ማስረጃህንም አይቼዋለሁ፤ ጥሩ ውጤት አለህ። ግን ይህ ትምህርት ቤት አዲስ ትምህርት ቤት ነው። ከተከፈተ ገና ሦስት ዓመቱ በመሆኑ እውቅና አላገኘንም። አንተን የመሰለ ጥሩ ተማሪ ደግሞ እውቅና የሌለው ትምህርት ቤት መግባት የለበትም። ስለዚህ ከዚህ ትምህርት ቤት ማስረጃህን ይዘህ ወጥተህ ሌላ እውቅና ያለው ትምህርት ቤት ብትሞክር ይሻልሃል" ብሎ መከረኝ።

ለስድስት ወራት ተምሬ ከዎርልድ ዩኒቨርሲቲ የምሥክር ወረቀቴን (ሰርተፍኬቴን) ይዤ ወደ አሌክሳንድርያ፤ ቨርጂኒያ ሄድኩ። አሌክሳንደሪያ ዝነኛው የጆርጅ ዋሺንግተን መታሰቢያ ማእከል የሚገኝበት ቦታ ነው። በማግስቱ የምስክር ወረቀቴን ይዤ ቨርጂኒያ፤ አሌክሳንድርያ የሚገኝ ኖቫ ወደሚባል የማኅበረሰብ ኮሌጅ ሄድኩና አመለከትኩ። ተቀበሉኝና መማር ጀመርኩ።

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1974 ዓ.ም የፈረንጆች የገና በዓል ነበር። ቨርጂኒያ ውስጥ የእነ ከፍሌ ጓደኞች ቤት ዝግጅት ተደርጎ በአሉን እዚያ ለማክበር ተሰባሰብን። ከዋሺንግተን በስተደቡብ በኩል ፖቶማክ የሚባል ወንዝ አለ፤ ይህንን ወንዝ ተሻግሮ ቨርጂኒያ ስቴት ይገኛል። ከወንዙ ባሻገር ወደ ቀኝ በኩል ክሪስታል ሲቲ የምትባል ትንሽ ከተማ አለች። በዓሉን ለማክበር ዝግጅት የተደረገበት ቦታ እዚህች ከተማ ውስጥ በሚገኝ ቤት ነበር። በአሜሪካ ባህል ቤተሰብና ጓደኛሞች ተሰባስበው የደስታ ጊዜ ከሚያሳልፉባቸው ትላልቅ በዓላት አንዱ ገና ነው።

እኔና ከንፉ የምንኖረው አሌክሳንድርያ ውስጥ ነበር ። ከንፉ ሜዳ የነበረ ቢሆንም ከእርሱ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘነው ሱዳን ውስጥ ነው። ከንፉ ቨርጂኒያ ውስጥ ከታናሽ እኅቱ ከአሌኒ ጋር ይኖራል። አሌኒ ሜዳ አልነበረችም፤ ነገር ግን በከተማው ትግል ውስጥ ተሳታፊ ስለነበረች የምታወራቸው ከትግል ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ ያስደስተናል። እርሷም እኛ ስለሜዳ የምናወራውን የመስማት ፍላጎቷ ከፍ ያለ ስለነበር በጣም ተቀራረብን።

በዚያ የገና በዓል አንጀሎ የሚባል ጓደኛችን መኪና ይዞ መጥቶ እኔን፣ ከንፉንና የከንፉን ታናሽ እኅት አሌኒን ይዞ ወደ ዝግጅቱ ቦታ ሄድን። በድግሱ ላይ ወደ ሃያ የምንሆን ኢትዮጵያውያን ተሰባሰብን። ከምናውቃቸው ውስጥ ከፍሌና ጌድዮን ነበሩ። ሌሎች ሜዳ ያልነበሩ ወንዶችም ሴቶችም በድግሱ ላይ ተገኝተዋል። የድግሱ ሥነሥርዓት ተጀምሮ የሚበላውና የሚጠጣው በየዓይነቱ ቀርቦ ፤ ሙዚቃው ተለቆ ቤቱ ሞቅ አለ።

አንዲት ቆንጆ ልጅ አጠገቤ መጥታ "ምሥራቅ እባላለሁ" ብላ ተዋወቀችኝና አብረን መጫወት ጀመርን። ምሥራቅ ረዥምና ጠይም ቆንጆ ነች። ዓይኖቿ በጣም ትላልቅ፣ ጥርሶቿ ነጫጭ ናቸው። ስታወራ ለዛ ያላትና ጨዋታ አዋቂ ናት። አሳሳቋ ሁሉ በጣም ደስ ይላል። ቅርጿ ድንቅ ነው፡፡ አለባበሷም በጣም የተስማማ ነበር፤ ብቻ ሁሉ ነገሯ ይማርካል።





ድግሱ እየተሟሟቀ ሲሄድ ሳላስበው መጠጥ አበዛሁና ሞቅ አለኝ። ከሞቅታም አልፌ ሰከርኩ። ስካር መንፈስ ውስጥ ከገባሁ በኋላ ግን በድንገት ድላይ ትዝ አለችኝ፤ ወዲያው ሁሉም ነገር አስጠላኝ። ብቻዬን ቁጭ ብዬ መተከዝ ጀመርኩ። ምሥራቅ ሁኔታዬን አይታ «ካሕሳይ፣ ምነው ተከዝክ? ና ተጫወት» ብላ እጄን ይዛ ትጎትተኝ ጀመር።

እኔም «ስሚ፤ ድሮ የማውቀው የአንቀጸ ብርሃን ግእዝ ላይ ማርያም የምትወደስበት አባባል ምን ይላል መሰለሽ "ወትወልዲ ኮከበ ወታጸግቢ ርሁበ ወትመስሊ ምሥራቅ» ይላል ብዬ ጠቀስኩላት። "አንቺ ልጅ ስምሽ ምሥራቅ ነው። ፊትሽም ምሥራቅ ነው። ነገር ግን ዛሬ ማታ ተዋውቀናል፣ ተግባብተናል፣ ተጨዋውተናል ብለሽ፣ ሌላ ነገር እንዳታስቢ። በጣም የማፈቅራት ድላይ የምትባል ልጅ አለች። ዛሬ ግን አጠገቤ የለችም። ይቅርታ አድርጊልኝና ከድላይ በኋላ ሌላ ሴት የማፈቅርበት ልብ ስለሌለኝ ቅር እንዳይልሽ» በማለት ቆንጆዋንና ተግባቢዋን ልጅ በማታውቀው ነገር ወረድኩባት።

እነ ከንፉ፣ አሌኒ፣ ጌዲዎንና ከፍሉ የድላይ ስም ከንደበቴ ሲወጣ ሰምተው በያሉበት ደንግጠው በሐዘኔታ ያዩኝ ጀመር። የበዓሉን የደስታ ስሜታቸውን እንደ አበላሸሁባቸው ጥርጥር የለውም። ጌዲዎን ወደእኔ መጥቶ «አይዞህ አማኑኤል፣ አይዞህ» ሲለኝ በድብርትና በሰካር መንፈስ ውስጥ ሆኜ ነበር የማዳምጠው።

ልጅቱ በሁኔታዬ በጣም ስለተደናገጠች እነአሌኒ ተሰብስበው ምክንያቱን ሊያስረዷት ሲሞክሩ ይታዩኛል። ከትንሽ ጊዜ በኋላ መጠጣቴን እንዳቆም አደረጉና ሁላችንም ወደቤት ተመለስን። ወደቤት እየሄድን ትዕግሥቱ፣ ከፍሉና ሌሎቹም መከሩኝ። አልኮል መጠጥ መጠጣት መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ሊያስገባኝ እንደሚችል አስረድተውኝ ከዚያ በኋላ ርግፍ አድርጌ እንድተው አስጠነቀቁኝ። «ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል» እንደሚባለው ነው፤ ስትጠጣ ሐዘንህ ይቀሰቀሳል፤ እናም ሁለተኛ ባትጠጣ ይሻልሃል አሉኝ። ምክራቸውን ተቀበልኩና ከዚያን ቀን በኋላ ከመጠጥ መቆጠብ ጀመርኩ።

ስለ ድላይ ማሰቤንና መረጃ የማግኘት ጥረቴን ግን በጭራሽ አቋርጬ አላውቅም:: በቅርብ ከማውቃቸው አንዳንድ የሜዳ ጓደኞቼ ጋር የሚያገናኘን አጋጣሚ በተፈጠረ ቁጥር ሆነ ብዬም ይሁን ሳላስበው የእርሷን ስም ሳላነሣ ያሳለፍኩትን ጊዜ አላስታውስም። ስለእኔ የሜዳ ሕይወት ከሚያውቁት አብዛኞቹ ወይ ከእርሷ ጋር ስለነበረን ግንኙነት ያውቃሉ አሊያም ታሪካችንን ሰምተዋል። ስለዚህ አንዳንዴ ሳወራና ስተክዝ ስለሚያዩኝ በተቻላቸው መጠን የምረሳበትን ዘዴ ለማመላከት ይሞክራሉ። በዚያ ከቀጠልኩ ግን በጤንነቴ ላይ ጉዳት ሊፈጥርብኝ እንደሚችልም ያስጠነቅቁኝ ነበረ።

ብዙዎቻችን ሜዳ የነበርን ጓዶች ከአሲምባ በኋላ አሜሪካ ተገናኝተናል፤ የጌራ ሰርግ ደግሞ ብዙዎቻችን የተገናኘንበት አንዱ አጋጣሚ ነበር። ሰርጉ በ1983 ዓ.ም. የደርግ መንግሥት በወደቀ በሦስተኛው ቀን መዋሉ ደግሞ አጋጣሚውን ልዩ ያደርገዋል።

ስንገናኝ ወሬያችን በሙሉ ካለፈው ሕይወታችን ጋር የተያያዘ ይሆንና ሁሉን እንረሳለን፤ ያን ሁሉ አልፈን በሕወት መገናኘታችን ይገርመናል። ጌራ ራሱ ለዚያ መብቃቱ ተአምር ነው። ከሱማሌ የእስር ቤት ሰቆቃ ተርፎ፤ ከኤርትራ ተዋጊዎች ጋር አብሮ የእነርሱን ጦርነት ተዋግቶ፣ አሲምባ ብዙ ዓመት ቆይቶ ስንቱን ከፉ ነገር አሳልፏል። እርሱ ሞት አልፈልግህም ብሎ የተፋው ጉድ ነው::

አይ ጌራ! ሙቼም ያኔ ሕክምና ሲያሠለጥን መለማመጃ መርፌ ሲያስጠቀጥቅብን የነበረው አይረሳኝም። ሌላም የማልረሳው የጌራ ትዝታ አለብኝ። ሳንባ ታመህል ተብዬ ብቻዬን ስገለል፤ "አይዞህ ምንም አትሳቀቅ፣ የሚያሰጋ ነገር አይደለም" እያለ ያበረታታኝ የነበረውን ሙቼም አልረሳውም።

በጌራ ሰርግ ላይ ካገኘኋቸው መካከል አንዱ  ጀማል ነበር፤ ጀማል ትዝታው ባይለየኝም መልኩ ጠፍቶብኝ ነበር። የጌራ ሰርግ ጀማልን ብቻ ሳይሆን አግኝቻቸው የማላውቅ ብዙ የአሲምባ ጓደኞቼን ያገኘሁበት ልዩ አጋጣሚ ነበር።





ቴዎድሮስ ባሪያው፣ ሮባ፣ ለምለም፣ አምበርብር፣  አድማሱ፣ ጥበበ፣ አበጀ፣ ሰለሞን፣ ጸዳለ . . .

ከጌራ ሰርግ በፊት ስለጀማል ሰምቼ ስለማላውቅ በሕይወት ይኑር አይኑር፣ አላውቅም ነበር። በአጋጣሚ ያን ቀን ሲመጣና ከሩቅ ሳየው አይኔን ማመን አቃተኝ። እየተጠራጠርኩ  አጠገቡ ሄጄ ሰላም አልኩት፤ አላወቀኝም። "ማነኝ? ታስታወኛለህ?" ስለው ለደቂቃ ያህል ግር ብሎት ሲመለከተኝ ቆየና "እንዴ፣ አማኑኤል!" ብሎ በመጮህ አንገቴ ላይ ተጠመጠመ።

"የአርባያው ጉዳችን ትዝ ይልሀል" ብዬ ጠየቅኩት በጨዋታችን መሃል።

"እንዴ! እንዴት እረሳዋለሁ" ብሎ ታሪኩን ራሱ መተረክ ጀመረ። እሱ ወድቆ ሌሎቹ ታዘው ጥለውት ሄደው እንደነበረና እኔ ተሸክሜው እንዳወጣሁት ተናግሮ "አማኑኤል እኮ ነው ነፍሴን ያዳናት። እሱ ባያወጣኝ ዛሬ በሕይወት አታገኙኝም ነበር" አለና ስሜትቱ ገጽታው እያሳየበት።

***

**ዴንቨር ኮሎራዶ**

አንድ ዓመት አሌክሳንድርያ ከቆየሁ በኋላ ትምህርቱም ሆነ ሥራው አላስደሰት አለኝ። ኖቫ የማኅበረሰብ ኮሌጅ ሁለት ሰሚስተር ከተማርኩ በኋላ ከአሌክሳንድሪያ፣ እንደገና ሀገር በመቀየር ወደ ዴንቨር ኮሎራዶ ሄድኩ።

ዴንቨር፣ በጣም የምትታወቀው እንደሰንሰለት በተያያዙት ድንጋያማ ተራራዎቿ ነው። ተራራዎቹ ተያይዘው እስከካናዳ የሚዘልቁ ናቸው። አየሩ በጣም የሚስማማና ደስ የሚል ሆኖ አገኘሁት።ተራሮቹን ሳይ ደግሞ የበለጠ ደስ አለኝ። አንዳንዴ ጊዜ ሳገኝ ወደ ተራራሮቹ ሄጄ ስንሸራሸር ልክ አገር ቤት ያለሁ ይመስለኛል። ዴንቨርን በጣም ወደድኩት። ተራሮቹን አሲምባ እያለሁ ከማውቃቸው ተራሮች ጋር እያመሳሰልኩ "ይሄ ዳያን ይመስላል፤ ይሄ አሲምባን ይመስላል፤ ይሄ ደግሞ ጻለምት ያለውን የሰሜን ተራራ ይመስላል" እያልኩ አመሳስላቸዋለሁ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ወደሌላኛው ሰፈር እሄድና ይሄ ቃሌምን ይመስላል፤ ያ አገሌን ይመስላል እያልኩ ኢትዮጵያ በትግል ውስጥ እያለሁ በማውቃቸው ቦታዎች እሰይማቸዋለሁ።

ዴንቨርን አገሬ ብዬ ሰፈርኩና ኮሎራዶ ዩኒቨርስቲ ተመዝግቤ ትምህርቴን ቀጠልኩ። ያኔ አሲምባ እያለሁ ኮሌጅ ተምረው የጨረሱት ብቻ ሳይሆኑ ደጃፉን የረገጡት ሁሉ ዩኒቨርስቲ ባልገባነው ላይ የበላይነት ስሜት ሲያንጸባርቁ መመልከቴ ቁጭት አሳድሮብኛል። በምንም ተአምር ትምህርቴን ሳልጨርስ እንደማላቋርጥ ለራሴ ቃል ገብቻለሁ። ትምህርቴን ጨረስኩኝና ከኮሎራዶ ዩኒቨርስቲ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1995 በፋርማሲ ትምህርት በዲግሪ ተመረቅኩ።

ዴንቨር ውስጥ ቅርንጫፍ ያለው ክሮገር የሚባል ኩባንያ ገና ከመመረቁ ከሁለት ዓመት በፊትም ቀጥሮኝ ነበርና በዚሁ ኩባንያ ውስጥ በፋርማሲ ዲፓርትመንት ሥራ እስኪያጅነት መሥራቴን ቀጠልኩ።





## ስምንት

## ከአሥራ አራት ዓመታት በኋላ

**ከዴንቨር አዲስ አበባ**

1984 ዓ.ም. የደርግ መንግሥት ከወደቀ ከአንድ ዓመትና እኔ ከሀገሬ ከወጣሁ ደግሞ ከአሥራ ሦስት ዓመታት በኋላ ወደ ኢት፡ጵያ ለመመለስ ተነሣሁ። ከአሜሪካ ወደ እንግሊዝ በአሜሪካ አየር መንገድ በርሬ፣ ከለንደን ደግሞ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ይዤ ወደ ሀገሬ ለመግባት ቸኩያለሁ።

ከሱዳን ወደ አሜሪካ ሄጄ ኑሮ ከጀመርኩ በኋላም የአሲምባ ትዝታዬን የሚቀሰቅሱብኝ አጋጣሚዎች ነበሩ። ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ስወስን ደግሞ ትዝታና ናፍቆት ጠናብኝ። ሀገሬ፣ ከዚያም ከአሲምባ ሕይወቴ ጋር የተያያዙ አጋጣሚዎቼ ተራ በተራ እየመጡ በሐሳብ ያዋልሉኝ ጀመር።

እነዚያ አጋጣሚዎች ወይ ከቦታ ወይ ከሰዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። ዴንቨር ውስጥ ያሉት ጠዋት ማታ የማያቸው ሰንሰለታማ ተራራዎች አንዱ የትዝታዬ ቀስቃሽ ናቸው። ምናልባት ኑሮዬን በዴንቨር አድርጌ እንድረጋጋና ሀገሩን እንድወደው ያደረገኝ የእነዚህ ሰንሰለታማ ተራራዎች መኖር ሊሆን ይችላል። ሀገሬ የትግል ሕይወቴን ያሳለፍኩባቸው የአሲምባ ዙሪያ ተራሮች ከዴንቨር ጋር መመሳሰል የፈጠረብኝ ፍቅር ሳላስበው ዴንቨርን ሙጥኝ ብየ ለመቅረቴ ምክንያት እንደሆነ አስባለሁ።

ለንደን ደርሼ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ውስጥ ስገባ፤ የማየው፣ የምሰማው፣ የማነበው እያንዳንዱ ነገር በውስጤ ተቀብሮ የኖረውን ትዝታ የሚቀሰቅስ ሆኖ አስቸገረኝ። ተፈታተነኝ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ከሆንኩ፣

አእምሮዬን ላሳርፍ ብዬ ለመተኛት ብሞክርም ገና ሽለብ ሲያደርገኝ ያው ህመሜን የሚቀሰቅስብኝ አንድ ነገር አይጠፋም።

ሰላምታ የሚለውን የአየር መንገድ መጽሔት ብድግ አድርጌ ለማንበብ ሞከርኩ። የአፋር የባህል ልብስ የለበሱ ሰዎች ፎቶግራፍ ስመለከት የዳሎል ጉዞ ትዝ ብሎኝ በሐሳብ አሰመጠኝ። ከዚያ እንደምንም ሐሳቤን ጎትቼ አወጣሁና ገለጥ ሳደርግ ስለወሎው ላሊበላ የሚያወራ ነገር ያለበት ጽሑፍ አየሁ። ለእኔ ወሎ ማለት ውድዬ፣ ቃሌም፣ ቆቦ፣ ናቸው። እነሱ ትዝ አሉኝ። የወሎ ተልእኮ፣ ጦርነቱ ሰቆቃው... "ኡፍ!" አልኩና መጽሔቱን አስቀምጬ ሌላ ነገር ለማሰብ ሞከርኩ።

አጠገቤ ያለው ሰው እንቅልፍ ሸለብ አድርጎታል። ከፊት ለፊቴ አንድ ሰው ከመጸዳጃ ቤት ተመልሶ ወደ መቀመጫው ሲሄድ በአጠገቤ አለፈ፤ ቀና ብዬ አየሁትና ልቤ ደነገጠብኝ። «የት ነው የማውቀው» ሳስተውለው ልክ ጀማልን ነው የሚመስለው። አንዳንዴ የሰው መመሳሰል ይገርማል። ከዚያ ሌሎቹ የሜዳ ጓዶቹ አንድ በአንድ መጡብኝ፡፡ ድላይ ትዝ ስትለኝ ደግሞ ዓይኖቼም ጨለሙብኝ።

ድላይ በጣም ዝነኛ ከመሆኗ የተነሣ እዚህ አሜሪካ ያሉ አንዳንድ የቀድሞ ጓዶች ለሴት ልጆቻቸው ድላይ ብለው ስም እንደሚያወጡ አውቃለሁ፡፡ በለሳ ውስጥም በስሟ የተሰየመ ተራራ መኖሩን አንዳንድ ጓዶች አጫውቶኛል።

ይህን ታሪክ በመጽሐፍ መልክ ለመጻፍ ስጀምር በታሪኩ ውስጥ ድላይ ብዙ ቦታ ስለነበራት እንደገና ትዝታ እየተቀሰቀሰብኝ ችግር ላይ ወድቄ ነበር። ሆኖም አንዴ ስለወሰንኩ ወደ ኋላ ለመመለስ አልፈለግኩም። በመሐል አንዳንድ መረጃዎችን ለማሟላትና አንዳንዶቹን ደግሞ ማረጋገጥ ስለነበረብኝ ከሚመለከታቸውና ላገኛቸው ከምችላቸው የሜዳ ጓደኞቼ ጋር ያለኝ ግንኙነት እየጠበቀ መጣ። እነርሱም ቢሆኑ መጽሐፍ ለማውጣት ሥራ እንደጀመርኩ ስነግራቸው በጣም ደስ ብሏቸው ባላቸው አቅም ይተባበሩኝ ጀመር።





ነገሮች እየተስተካከሉ ቀስ በቀስ መልክ እየያዙ መሄድ ጀመሩ። ነገር ግን አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ መረጃ ቀርቶኛል። የድላይን መጨረሻ፣ ትክክለኛ የአሟሟቷን ሁኔታ በቦታው ከነበረ የዓይን ምስክር መረጃ ማግኘት አለብኝ።

የድላይ መሠዋት የተረጋገጠ ነገር ቢሆንም በመጨረሻው ሰዓት ቦታው ከነበረና ካየ ሰው መስማት በጣም የምመኘው ነገር ነበረ። እስካሁን ግን አንድም በቦታው የነበረ ወይም የነበረን ሰው የሚጠቁመኝ አላገኘሁም፤ ቢሆንም ስለድላይ መጠየቄን አላቋረጥኩም። ድንገት የሚገኝ ጫፍ ቢኖር በሚል ተስፋ እጠይቃለሁ። "የድላይን መጨረሻ አይቻለሁ" የሚለኝ ሰው አግኝቼ ለኅሊናዬ ዕረፍት ለማግኘት እጓጓለሁ። ሜዳ የነበሩ ሰዎችን ባገኘሁ ቁጥር ስለድላይ መጠየቅን ልምዴ አድርጌዋለሁ። ግን ምንም እተለየ መረጃ አላገኘሁም። ምናልባትም ያለሁበት አካባቢ ወጣ ያለ መሆን የግንኙነቴን አድማስ አጥብቦት የእርሷን መጨረሻ እንዳላውቅ አድርጎኛል ብዬ እገምታለሁ።

ዴንቨር ከገባሁ ከሁለት ዓመት በኋላ ይፍጠር ከሚባል የኢሕአሠ አባል ከነበረ ጓድ ጋር በአጋጣሚ ተገናኘን፤ በጨዋታ መካከል በለሳ እንደነበረ ነገረኝ። እኔም በ1969 ዓ.ም በለሳ ሄጄ እንደነበረና ቦታውን እንደማውቀው አጫወትኩት። የተለመደ ጥያቄየን ለእርሱም አቀረብኩ።

ይፍጠር ድላይን እንደሚያውቃት አልተጠራጠርኩም፤ ምክንያቱም እንኳን በለሳ የነበሩ ያልነበሩትም በዝና ያውቋታልና ነው። ድላይ በለሳ እንደተሠዋች ማወቄን ነገርኩትና ስለእሷ አሟሟት የሰማው ወይ የሚያውቀው ነገር እንዳለ ጠየቅኩት -ምን ይታወቃል ልሞክር ብዬ። ይፍጠርን ስለድላይ ከጠየቅኩት በኋላ ሐሳብ ውስጥ ሰምጬና ፊቴ ጠቁሮ ሲያይ ነው መሰለኝ ሁኔታዬን ገምቶ ከሄድኩበት እስክመለስ በትዕግሥት እየጠበቀኝ ነበረ። ቆይቼ ወደራሴ ስመለስ ይቅርታ ጠየቅኩት።

«ድላይ ሕይወቷ ሲያልፍ» አለና ትንሽ ዝም አለ፤ እንደማመንታት ብሎ።

"«እ!» አልኩት የጓጓሁለትን ወሬ ሊነግረኝ እንደሆነ ገምቼ።

«ድላይ ሕይወቷ ሲያልፍ ቦታው ላይ ነበርኩ»

«እውነትህን ነው» አልኩ በርግጌ።

«እውነቴን ነው። በእርሷ መሞት ሠራዊቱ በሙሉ ነበረ ያዘነው። በአካባቢው በጣም ታዋቂ ስለነበረች የአካባቢው ገበሬዎች ጭምር ነበሩ ያዘኑት።» አለና ምን ያህል እወዳት እንደነበረ ከሁኔታዬ ተገንዝቦ ይመስለኛል ወሬውን አሳጥሮ እኔን ማጽናናት ቀጠለ። በዚያው ተለያየን።

ለዚህ መጽሐፍ መረጃ ማጠናቀር ስጀምር ይፍጠርን በድጋሚ አግኝቼው ዝርዝሩን ይነግረኛል የሚል እምነት ነበረኝ። እርሱን ግን በአድራሻው ለማግኘት ሞክሬ አቃተኝ። በመጨረሻም ምንም እንኳን ዕድሉ ጠባብ ቢሆንም ሌላ አማራጭ ልሞክር ብዬ ድላይ ስትሠዋ አጠገቧ የነበረ ሌላ ሰው ማፈላለግ ጀመርኩ።

ይህን ችግሬን ለሺፈራው አማከርኩት፡፡ ሺፈራው ሜዳም እያለን በከፉ ጊዜ መካሪዬና ቁምነገረኛ ወዳጄ ነበር። ሌላ አማራጭ ለመሞከር እንደሚጥር ቃል ገባልኝ። ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራትም አለፉ፤ ሺፈራው የቻለውን እየሞከረ ቢሆንም ከተስፋ በቀር ምንም የተጨበጠ ነገር ሳይገኝ ቀረ። እርግጥ ከሰላሣ ዓመት በፊት የሆነን ታሪክ ያውም ከሩቁ አገር ከአሜሪካ በመልእክትና በስማ በለው መፈለግ ክባድ እንደሆነ ለመረዳት አይከብድም። ነገር ግን ውስጤ እንደገና ስለተነሣሣብኝ ትዕግሥት አጣሁ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ አንድ ቀን ስልክ ተደወለ፤ ሺፈራው ነበረ። ያን ቀን ድምፁ ለወጥ ብሎብኛል፣ ወይም ተለውጧል ብዬ አስቤ ይሆናል። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ «ምን አዲስ ነገር አለ?» ብዬ ጠየቅኩት።

«ምንም አዲስ ነገር የለም ምናልባት አንድ ፍንጭ ሊሰጥ የሚችል ጥቆማ አግኝቻለሁ። እውነት ከሆነ አረጋግጬ እነግርሀለሁ» አለኝ። ሺፈራውን ለሙከራው አመሰገንኩትና ስልኩን ዘጋሁት። ምንም እንኳ የአሜሪካ ኑሮ ፋታ የሚሰጥ ባይሆንም እርሱ ግን ከጠበቅኩት በላይ እየታገለ ነበረ። ከተለያየንም በኋላ





ለሚያውቃቸው ሁሉ እየነገረ ደውለው የጠየቁኝም ነበሩና ሙከራዬን በጣም ትልቅ ቁም ነገር አድርጎ እንደያዘው ተረዳሁ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ እንደገና ደውሎ ድላይ ሕይወቷ ሲያልፍ አብራት የነበረች የቅርብ ጓደኛዋን ማግኘቱን ነገረኝ።

"ማን ትባላለች? የት ነች?" ብየ በጥያቄ አጣደፍኩት።

"ማስረሻ ትባላለች፤ የምትኖረው እዚሁ አሜሪካ ነው" አለኝ።

ጉዳዩን በዝርዝር እንደነገራትና ከእኔ ጋር ለመገናኘትም ፈቃደኛ መሆኗን አስረድቶኝ የስልክ ቁጥሯን ሰጠኝ። ደወልኩና ማስረሻን አገኘኋት። እውነት ነበር፤ ማስረሻ ድላይ በክንዷ ላይ ማረፏንና በጊዜው የነበረውን ሁኔታ አስታውሳ ነገረችኝ።

በ1972 ዓመተ ምሕረት ድላይ ምክትል ኃይል መሪ ሆና በለሳ በነበረችበት ጊዜ ድርጅቱ በውስጥና በውጪ ችግር ተጠምዶ ውጥረት ላይ ነበር። ወቅቱ ከውጪ ከደርግ ጋር ኃይለኛ ጦርነት ተደርጎ ጉዳት የደረሰበት ጊዜ ሲሆን፤ በውስጥ ደግሞ እርማት እንዲደረግ የሚፈልጉ አባላት በድርጅቱ አመራር ላይ ሂስ በማቅረባቸው አለመግባባት ነግሦ አጣብቂኝ ውስጥ የተገባበት ጊዜ ነበር። ሌሎች ጥቂት የማይባሉ አባላት እየከዱ መሄድ ቀጥለዋል። እንዲሁ የሠራዊቱን መዳከም የተመለከቱ አባላት በተናጠል በሚሄዱበት ጊዜ አንዳንድ የታጠቁ የአካባቢው ሽፍቶች ግለሰቦችና የደርግ ሚሊሻዎች ተኩስ እየከፈቱባቸው ጥቃት ያደርሱ ነበረና በሁሉም አቅጣጫ ውጥረቱ ተባብሷል። በዚህ መካከል የኃይል አመራሮች ተሰባስበው በአመራሩ ላይ አሉ ስላሏቸው ግድፈቶችና ጉድለቶች በመነጋገር ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወያየት ጀምረው ነበር።

ድላይም በአመራሩ ላይ ቅሬታ ካላቸው ውስጥ አንዷ ስለነበረች በድርጅቱም ላይ እምነቷ እየመነመነ መሄድ ጀምሯል። በዚያው መካከል የነበረችበት ኃይል ከሰፈረበት ቦታ ተነሥታ ወደሌላ ኃይል ሄደች። በመንገድ ላይ እያለች በአጋጣሚ በአካባቢው የነበሩ የደርግ ሚሊሺያ አባላት ባልታሰበ ሰዓት ተኩሰው አንገቷ ላይ በጥይት መቱዋት፡፡ ወደቀች። ብዙም ሳትቆይ በአካባቢው ከነበሩ ጓዶቿ አንድ

የሠራዊቱ ሐኪምና ሌላ የሠራዊቱ አባል የሆነች ማስረሻ የምትባል ጓዲት ደረሱ። ጓዲቷ የድላይ የቅርብ ጓደኛዋም ጭምር የነበረች ናት።

እነርሱ በወደቀችበት ቦታ እንደደረሱ ከአንገቷ ቀና አድርገው ደግፈው የተመታችበትን ቦታ በመለየት ለመርዳት ጥረት አደረጉ። የተመታችበት ቦታ ለሕይወቷ አስጊ ነበር፤ እነርሱም ምንም ለማድረግ ሳይችሉ ግራ ተጋብተዋል፡፡ ድላይ ከአንገቷ ቀና አድርጋ ለያዘቻት ጓደኛዋ "ውኃ ስጪኝ! ውኃ፣ ውኃ!» የሚሉ ቃላት ካሰማች በኋላ በክንዷ ላይ እንዳለች ሕይወቷ በበለሳ ወረዳ ውስጥ እንዳለፈች ማስረሻ ዝርዝር ታሪኩን ነገረችኝ።

አስከሬኗን አንሥተው ሲወስዱ በቦታው የነበሩት ጓዶቹዋ የቱን ያህል በሐዘን ተውጠው እንደነበር ስትነግረኝ ስሜቷ ድምጿን እየቆራረጠው ነበረ። በአካባቢውም በጣም ትታወቅ ነበረ። የመሞቷ ወሬ ወዲያውኑ ተዳርሶ ከጓዶቿ በተጨማሪ ብዙ የአካባቢው ነዋሪዎች በቀብሯ ሥነሥርዓት ላይ እንደተገኙም ገለጸችልኝ።

ዋ ድላይ!

አድዋ ማይ ምሻም ተራራ ላይ ብቻችንን ሆነን፤ «ስመኝ ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ» ያለችኝን አስታውሼ ማስረሻን «እውነተኛ ስሟንስ ታውቂያለሽ?» ብዬ ጠየቅኳት።

«እውነተኛ ስሟን እንኳዋን አላስታውስም፡፡ አብሮ አደጎቿን አስጠይቄ እነግርሀለሁ» አለችኝ። «ለእኔ ግን አንድ ቀን ብቻችንን ስንሆን 'ስመኝ ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ' ብላኝ ነበር፤ እውነተኛ ስሟ ከሆን እስኪ አጣሪ» አልኳትና ተለያየን።

ከማስረሻ ጋር እንደገና በስልክ ተገናኘን፡፡

«አዎን! ስመኝ እውነተኛ ስሟ ነበር» አለችኝ።

«የአባቷስ ስም? ማለቴ ምናልባት ከጠየቅሽ» አልኳት።





«የአባቷ ስም፣ ምንአለ ነው። ስመኝ ምንአለ ነው የምትባለው» አለችኝ።

ከልቤ አመሰገንኩዋት፡፡

ይህን ስትነግረኝ የተሰማኝን ደስታ በቃላት መግለጽ ይከብደኛል። በደስታ እንደተሞላሁ ማስረሻ ስለግል ሕይወቷም ተጨማሪ መረጃ እንደምታውቅ ገምቼ፤ «የተወለደችው የት ነው? ስለተወለደችበትና ስላደገችበት ሀገር የነገሩሽ ነገር ካለም ብትነግሪኝ በጣም ይጠቅመኛል» አልኳት።

"ብዙ ዝርዝር ባላውቅም፤ የተወለደችው ቆቦ እንደሆነና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን የተከታተለችው ወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደነበረ አውርታኛለች። የእድገት በህብረት ዘማች ተማሪ የሆነችውም ከዚህ ትምህርት ቤት ይመስለኛል።» አለች።

«አሁን እንግዲህ የድላይን ታሪክ ከሞላ ጎደል የሚገልጹ መረጃዎች አግኝቻለሁና ስለማንነቷ፣ ታጋይነቷ፣ መሥዋዕትነቷ፣ ለእኔም ውድና የመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ስለመሆኗ የተሟላ ነገር ማቅረብ እችላለሁ። የመጽሐፌ ሥራ በግማሽ ወደፊት እንደተራመደ እቆጥረዋለሁ» አልኩና ማስረሻን በጣም አመሰግኛት ተሰነባበትን።

ሀሳቤ ወደ ድላይ ትዝታ የኋሊት ሸምጥ ጋለበ፡፡

«አማኑኤል፣ ካሁን በኋላ አንገናኝም። ያሳለፍናቸው ጊዜያት ግን የማይረሱ ናቸው፤ ሁል ጊዜ አስታውስሀለሁ! አንተም እንዳትረሳኝ!»

መጀመሪያም ከሆዴ አልወጣ ብሎ ያስቸገረኝ ንግግሯ ነበር። አሁንም ትዝ እያለኝ ይረብሸኛል። አሁን ግን ድላይን እስከ መጨረሻው እንዳስታውሳት የሚያደርገኝ ነገር ላገኝ ነው። ይህ ሥራዬ እውን ሲሆን አእምሮዬ፤ ምናልባትም ከሠላሳ ዓመት በኋላ ስለድላይ ከሚመላለስብኝ ሐሳብ በመጠኑም ቢሆን ዕረፍት ሊያገኝና እውነቱን ለመቀበል ይችል ይሆናል ብዬ ተስፋ አደረግሁ።

ከለንደን አዲስ አበባ የምናደርገው ጉዞ አላለቀም፤ አእምሮየን ከሐሳቤና ከድካም ለማሳረፍ የተለየ ሙዚቃ እየሰማሁ ጋደም ለማለት ፈለግሁ። የጥላሁን ገሰሰን ዘፈኖች መርጬ፤ ማዳመጫውን ጆሮዎቼ ላይ ሰካሁና ጋለል ብዬ ዓይኖቼን ከደን አደረግኳቸው። ለስለስ ያለው የጥላሁን ዜማ በጣም ደስ ብሎኛል። የጥላሁን ልዩ ድምፅና ችሎታ። የዜማው፣ የግጥሙ ይዘትና የአጃቢው ሙዚቃ ውሕደት በጣም የተስማማ መሆኑ እየገረመኝ ነው የማዳምጠው። “«በምሽት ጨረቃ በንጋት ፀሐይ ጮራ» ብሎ ይጀምርና ይቀጥላል ጥላሁን።

“ ...እኔና አንቺ፣ ሆነን፣ ፍቅርን ቀመስናት

በዓለም ተሸከርከረን፣ ውበትን አየናት...

.... በየተራራው ላይ፣ በየሸንተረሩ......››

የጥላሁን ዘፈን እንደገና ወደ ድላይ ትዝታ ይዞኝ ጭልጥ አለ፡፡ ሙዚቃውና የትውስታዬ ሥዕል ተደበላለቁብኝ።

... ፊት ለፊታችን የአክሱም ሜዳ ተዘርግቷል። ከላይ በኩል የጻለምትና የሰሜን ተራራዎች ይታያሉ።

. . . ጎን ለጎን ተጠጋግተን ነው የተቀመጥነው። የተቀመጥንበት ቦታ ደስ ይላል፤ ጸጥ ያለ ቦታ ነው። የሚሰማ ቢኖር የወፎች ጫጫታና ራቅ ብለው ቅጠላ ቅጠል እየበጠሱ የሚበሉ ፍየሎች ጩኸት ብቻ ነው። ሰማዩ አልፎ አልፎ ዳመና አዝሏል። ከበድ ያሉ ደመናዎች ከራስ ዳሸን ወደ ድልበዛና ወደ ቡሀይት ተራራ ይጓዛሉ። በስተግራ በኩል፣ የተንቤን ተራራዎችና በረሐ፣ እንዲሁም በቀኝ በኩል የአድዋ ተራራና እምባ ሶሎዳ





ይታያሉ። ቁጭ እንዳልን እነዚህን በሩቅና በቅርብ የሚታዩ የተፈጥሮ ጸጋዎችን እያየን ትንሽ ትንፋሽ ወሰድን።

“ . . . በእዚህ በአድዋ በረሐ በማይ ምሻም ተራራ ለብቻችን ያሳለፍነውና የተነጋገርነው ሁሉ ትዝታው እስከሕይወቴ ፍጻሜ አብሮኝ ይኖራል። «ለፍቅር እንግዳ መሆኔንና ምንም እንደማላውቅ እያወቅሽ ሁሉንም ነገሬን በትዕግሥትና በፍቅር እያየሽ ተቀብለሽኛል»

«አንተ ልጅ እባክህ ተወኝ፣ ኢታስለቅሰኝ። ዛሬ ግን ምን ሆነህል? አነጋገርህ ሁሉ ተለይቶብኛል፤ ኑዛዜ ነው እኮ የሚመስለው»...

ዕንባ ዓይኖቼን አቃጠላቸው፣ ትናንትን በትዝታዬ ምስል ውስጥ ስመለከት የምቋቋምበት አቅም አጣሁ፤ ሆዴንም ባር ባር አለኝ። እኔ የራሴን ትዝታ ለራሴ እነግረዋለሁ። ጥላሁንም ለእኔና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በዜማው የራሱን ድርሰት ያንቆረቁረዋል። ሁለቱ ለእኔ በጣም የሚመሳሰሉና አንድ ታሪክ ሆኑብኝ። እንዲያውም ለኔ የዘፈነው ሁሉ መሰለኝ።

«ብዙ ተጫውተናል፣ ፍቅር

ልባችንን ገልጸን፣ ተስማምቶን አየሩ

አንቺን በማግኘቴ፣

ታደሰች ሕይወቴ ።......»

ስለድላይ ማሰብ እጀምርና ደግሞ ሌሎቹም ጓዶች ይመጡብኛል። ይገርማል! ወደበረሐ ለመግባት አብሮኝ ተነሥቶ ከመነኩሲቶ የተመለሰው ታደሰ አጽብሃ ከየት መጣ ሳልለው ተደቀነብኝ። እውነት የት ደርሶ ይሆን? ታደሰ አጽብሃን ሳስብ የአዲግራት ልጆችና አብረን ያነበብናቸው ጽሑፎች ሳይቀሩ መጡብኝ። ስንቶቹ

ይሆኑ በሕይወት ያሉት? ታደሰን ባገኘውና ስለሁሉም ብጠይቀው ተመኘሁ። ፍሱሕና ንጉሤ እንዲሁም ግደይ ተራ በተራ በዓይነ ኅሊናየ ታዩኝ። ከኢሕአሠ ጋር የተቀላቀልኩበት የመጀመሪያው ቀን... ሥልጠና፣ ጉዞ፣ ጦርነት፣ ጅግንነት፣ መሥዋዕትነት፤ ጁሊያና፣ ሐዋዝ፣ እነየአቢኢዮ፤ አእምሮየ ሲፈነዳ ደረሰ። ደግሞ የጓዶች የሚገርም መተሳሰብና ፍቅር፣ ማንም ለሕይወቱ የማይሳሳበት ጊዜ! ያ ወቅት አንድ እንኳ የሚረሳ ነገር የለውም። በየመሐሉ ግን ድላይ ጎልታ ወደሐሳቤ መምጣቷ የማይቀር ነው፤ አይ ድላይ!

......ፏፏቴው አጠገብ፤ የወፎቹን ዜማና የፏፏቴው ሿሿታ በጆሮዬ እየተሰማኝ ነው።

.......ከወንዙ በስተቀኝ በኩል የወንዙን መውረጃ አቅጣጫ ተከትለን፣ ወደታች ወረድን። በግራና በቀኝ በኩል ትላልቅ ዛፎች ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው አበባዎችና ለምለም ቄጠማዎች አካባቢውን አስውበውታል። ወንዙ ካለንበት ቦታ ላይ ይጠራቀምና ታች ሲደርስ ፏፏቴ ሆኖ እየዘለለና እየደነፋ ይወርዳል። ትንሽ ራቅ ሲል ደግሞ ደኑ ጥቅጠቅ እያለ ወደገደል ይሄዳል። ከዚያ በኋላ ብዙ ርቀን እንዳንሄድ እንመለስ ተባባልንና ፏፏቴው አጠገብ ጎን ለጎን ሆነን ተቀምጠን ማውራት ጀመርን።

እርሷ ከፊቴ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብላለች። እኔም ከፊቷ ያለው ድንጋይ ላይ ቁጭ ብዬ ዓይን ዓይኗን አያታለሁ። እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴት ልጅን ፍቅር ያየሁት በእርሷ ነው። ከፊቴ ግጽታዋ መልኳ ፈክቶ ይታየኛል። ጥርሶቿ ተከርክመው እንደተስተካከሉ መስመር ይዘው ተደርድረዋል። ጉንጮቿ ወጣ ወጣ ብለው ዓይኖቿ ወደውስጥ ገባ ገባ ብለዋል። ያን ቀን ገላዋን በሳሙና ስለታጠበች ፊቷ ያንጸባርቃል። አጠር ያለ ሉጫ፣ አፍሮ ጸጉሯ በነፋሱ ወዲያ ወዲህ ይወዛወዛል። ሰውነቷ በሙሉ የተስተካከለ ነው። ሁሉም ነገሯ ይማርካል። ትክክለኛ የሴትነት ውበቷን ያየሁት ያን ቀን ነው።





በዚያን ቀን ተጣጥባ፣ ንጹሕ አየር እየተነፈሰች፣ ነጻ ሆና ስትስቅ ሳያት ሌላ ድላይ መሰለችኝ። «አሁንስ በእውነት ደንበኛ ሙሽራ መስለሻል። ዛሬ በጣም ነው ያማረብሽ፣ አብረውኝ ያደጉ የአዲግራት ልጃገረዶችን መስለሻል፣ እንዲህ ከሆነ ሁልጊዜ ወንዝ እየወረድሽ በሳሙና መታጠብ አለብሽ» ብዬ ቀለድኩባት።

«አንተ አናርኪስት ሥነሥርዓት!! የአዲግራት ልጃገረዶች ቆንጆዎች እንደሆኑ አውቃለሁ» አለችና እንደገና መሳቅ ጀመረች። እውነትም ማራኪ ውበትና የሚያምር ሰውነት እንዳላት በዚህ ቀን በማየት ምስክር ለመሆን በመቻሌ ትልቅ ደስታ ተሰማኝ።

« ...... ከአሁን በኋላ ተራርቀን ነው የምንኖረው። ብንራራቅም ግን እስከ ምን ጊዜውም ድረስ እንደምወድሽ እንድታውቂልኝ እፈልጋለሁ። ሕይወታችን በፍቅር ተሳስሯል። ልቦቻችን ተጣምረዋል። ትናንት ሌሊት ጦርነት ላይ ያ ሁሉ ጥይት እየዘነበ፣ አማኑኤል የታለ እያልሽ በቀጥታ ወደእኔ ስትመጪ ምን ያህል እንደምትወጂኝ አወቅኩኝ። ይሄን ደግሞ ምንጊዜም አልረሳውም። »

........በአድዋ በረሐ በማይ ምሻም ተራራ ለብቻችን ያሳለፍነውና የተነጋገርነው ሁሉ ትዝታው እስከሕይወቴ ፍጻሜ አብሮኝ ይኖራል።

«......"አሁንስ እንደፖለቲካ ጉዳይ ሐላፊዎቹ ለፍላፊና ፖለቲከኛ ሆነሃል» አለችኝና መሳቅ ጀመረች።

«እኔ የምለፈልፈው አንቺ ፊት ስሆን ነው እንጂ እነርሱ ጋማ ምንም አልናገርም፣ አፌን ዘግቼ ጸጥ ነው የምለው። እኔ እንዲያውም ውይይት ሲጀምሩ ጥበቃ ወይም ዋርድያ መውጣት ነው የምመርጠው። ሁሌም ከነገራቸው መራቅ ነው የምፈልገው»

እሁን ጥያቄዋን አቁማ ዝም አለች። ሳያት ፊቷ በተረጋጋ ሁኔታ ዓይኖቿ ፍዝዝ ብለው ቆዩና እንደገና ወደእኔ እየተመለከተች ለመናገር የፈለገችው የጠፋባት ወይም ለመናገር የጨነቃት በሚመስል ሁኔታ በረዥሙ ተነፈሰች። «ብዙ ነገር

ስላስለመድከኝ መለያየቱ በጣም የሚከብደኝ ይመስለኛል። ትግል ውስጥ ከገባሁ ጀምሮ እንዳንተ ያመንኩትና የወደድኩት ሰው የለም»

«ናፍቆትና ትዝታውማ ካንቺ የባሰ ለእኔ የሚከብድ ይመስለኛል»

«እኔ ደግሞ የበለጠ የሚከብድብኝ ይመስለኛኝል»

«እኔ እኮ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ያፈቀርኩሽና ያፈቀርሽኝ አንቺ ብቻ ነሽ፣ በፍቅር፣ ሌላ ሴት አላውቅም። ሴት ልጅ ትወደኛለች የሚል እምነትም፣ አመለካከትም አልነበረኝም። ራሴን ከሰው በታች አድርጌ ነበር የምገምተው» ብዬ ንግግሬን ሳልጨርስ ተቆጥታ ፊቷ ተለዋወጠ።

«እማኑ፣ እንዲህ ዓይነት አመለካከትማ ኋላ ቀር ነው። አንተ ምን ይጎድልሀልና ነው!» በድህነት ማደግህ ከሆነ እሱ ወንጀል አይደለም። ድህነት ሥርዓቱ ያመጣብን ችግር ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሀ መሆኑን መርሳት የለብህም። ደግሞም ወደትግል የወጣንበት አንዱ ምክንያት በሥርዓቱ የተነሳ አልላቀቅ ያለንን የሀገራችንን ድህነት ለማስወገድ ነው። ......ሁለተኛ እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ መተውና ከሌሎችም ላይ እንዲጠፉ መታገል ነው ያለብን» በማለት ስለድህነት ተንትና በአዲስ አስተሳሰብ እንድሄድ መስመሩን አሳይታኛለች።

ከተቀመጥንበት ተነሥተን እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደኮረብታው ላይ ሄደን የተሰጡትን ልብሶቻችንን አነሣንና መለባበስ ጀመርን። አሁን በጣም ስለተለማመድን ልብሷን ለመቀየር ከለላ አልፈለገችም። ዘና ብላ ምንም ሳይመስላት ውብ ገላዋ እየታየኝ አጠገቤ ሆና መልበስ ጀመረች። ሰውነቷን ስመለከተው ልቤ በጥድፊያ ዱ... ዱ.... እያለ መታ። አካላቷ በጣም ይማርካል። ከለበስን በኋላም እጅ ለእጅ ተያይዘን ስንወርድ ለምን እንደሆነ ባላውቅም የሰውነቷ ሙቀት በእጇ በኩል ተላለፈና በሰውነቴ ውስጥ የተለየ ሙቀት ዘራበት።

የጥላሁን ዜማ ከሩቅ ቦታ እንደሚመጣ ድምፅ በጆሮዎቼ እየተንቀረቀረ ልዩ እንግዳ ነገር ሆኖ ይሰማኛል። በሰውነቴ የተለየ ሙቀት ኢዳረስ የተሰማኝ መሰለኝ።





ልክ ያን ቀን ድላይን ሳብ አድርጌ ስጎትታት ወደእኔ ስትጠጋ የተሰማኝን ዓይነት ስሜት። ያቀፍኳትና ያቀፈችኝ መሰለኝ። ጉንጯን የሳምኳትና፤ በመካከላችን ምንም ያህል የቦታ ረቀት ቢኖርም እንደማንረሳሳ የተማማልነው ሁሉ በእዝነ ልቡናየ ናኙብኝ። የማወራትም መሰለኝ "...በጣም ነው የማፈቅርሽ ከአሁን በኋላ በሕይወት ባንገናኝ እንኳ እስከዕለተ ሞቴ አስታውስሻለሁ ፍቅርሽም እስከመጨረሻው አብሮኝ ይኖራል» አልኩዋት፡፡ እኔ ግን እነሆ ኑሮየን እየኖርኩ ነው።

ጥላሁን ዜማውን ጨረሰ.... ከሄድኩበት የሰመመን ጉዞ ተመልሼ ግራና ቀኜን ተመለከትኩና ያለሁበትን ቦታ አስታወስኩ።

አሁንም ወደኢትዮጵያ በመብረር ላይ ባለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ነኝ። በሐሳብ የሚያንገላታኝ፤ ከዕንባዬ ጋር የሚያታግለኝ የትዝታዎቼ ሁሉ ምንጭ የተሳፈርኩበት አውሮፕላን ይመስለኛል። ለደቂቃ እንኳ አእምሮዬ ሌላ ነገር ማሰብ አልቻለም፤ ድላይና ያሳለፍኩት የትግል ሕይወት፣ የምወዳቸው ጓዶቼ፣ ሕዝቡና የአሲምባ ተራራዎች...አእምሮዬን እንዳተራመሱት ናቸው፤ ልክ ትላንት እንደሆን ሁሉ ያልደበዘዘ ትውስታ! ይገርመኛል።

አውሮፕላኑ፣ የሱዳንን የአየር ክልል አልፎ ወደኢትዮጵያ ሲገባ፣ የራስ ዳሽን ተራራ በስተግራችን በኩል የሚታየው ተራራ እንደሆነ አብራሪው ተናገረ። በዚህ ጊዜ በለሳ የሚገኘው ከራስ ዳሽን በስተቀኝ በኩል እንደሆነ ትዝ አለኝ። በለሳ ደግሞ ድላይ የተሠዋችበትና የተቀበረችበት ቦታ ነው። እንዲሁም ሌሎች በለሳ የተሠዉ ጓዶቼን አስታወስኩና ሐዘን ገባኝ።

የወደቁበት ተራራ በስማቸው የተሰየመላቸው አንዳንድ ጓዶች እንዳሉ ሰምቻለሁ። ዳዊት ተራራ፣ ጃሯ ተራራ፣ ግደይ ተራራ፣ ድላይ ተራራ!!... "በድላይ ስም የሚጠራው ተራራ የትኛው ይሆን?" እያልኩ እኔ ከሰማይ ላይ ሆኜ ዓይኖቼ ጓዶች የተቀበሩባቸውን ተራሮች ቁልቁል ለማየት እየሞከሩ ሳለ ድንገት ነስረኝና ደም ከአፍንጫዬ ሲጎርፍ ደንግጬ ከገባሁበት ሐሳብ ወጣሁ። የአፍንጫዬን ደም

በፊት ማበሻ ወረቀት እየጠረግሁ፣ ተነሥቼ ወደመጸዳጃ ቤት ሄድኩ፡፡ ደሙ እስኪቆምልኝ ጠብቄ ተጣጥቤ ወደቦታዬ ተመለስኩና ቁጭ አልኩ።

ትንሽ ዕረፍ ካልኩ በኋላ የጆሮ ማዳመጫውን አነሣሁና እንደገና የሀገር ባህል ሙዚቃ ማዳመጥ ጀመርኩ። ሁለት ዘፈኖች ካለፉ በኋላ በሦስተኛው ዘፈን ላይ የሰማሁት አንድ ስንኝ ቀልቤን ያዘው።

«ምን ያለው ጉሬዛ ከዛፍ ይሟገታል፣
ከሚወዱት ጋራ ማን ሲኖር አይቶታል»

ድላይን እያስታወስኩ "ከሚወዱት ጋራ ማን ሲሞት አይቶታል!" ቢባልም እኮ ያስኬዳል አልኩኝ በሆዴ፡፡

የአውሮፕላኑ አብራሪ አዲስ አበባ መድረሳችንን ነግሮን ቀበቷችሁን እሰሩ የሚል መልእክት አስተላለፈ። አዲስ አበባ ከሰራችን ተዘርግታ ወደመሬት እስከምንወርድ ትጠብቃለች። እኔ አዲስ አበባን የማያት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፤ ከተወለድኩበት ከዛላ አንበሳና ከተማርኩባት አዲግራት ከተማ በስተቀር፤ ሌሎች ቦታዎች በሙሉ ከኢሕአሠ ጋር በተያያዘ የማውቃቸው ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ ለሕክምና ከሄድኩበት የጎንደር ከተማ በስተቀር ሁሉም ገጠርና የገጠር ከተሞች ሲሆኑ፤ አብዛኞቹ ትግራይ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው።

አዲስ አበባ ብዙም አልቆየሁም፤ ቤተሰቦቼንና የትውልድ ሥፍራየን እንዲሁም ያችን የወጣትነት ዕድሜየን በትግል ያሳለፍኩባትን አሲምባንና አካባቢዋን ለማየት ፈጥኜ ሄድኩ። የተሰዉ ጓዶቼ ትዝታ ሲያንገላታኝ ስነበተ፤ አእምሮዬ ማረፍ ተሣነው፤ ማልቀስና መተከዝ ከቶውንም ርካታ ሊሰጡኝ አልቻሉም። ስለእነዚያ በንጹሕ የአገር ፍቅር ስሜት መሥዋዕትነት ስለከፈሉ ጀግኖች አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ኀሊናየ ጎተጎተኝ። ቢያንስ ታሪካቸውን መናገር እንዳለብኝ አሰብኩ፤ መጽሐፍ ለመጻፍ የነበረኝን ውጥን አጠነከርኩ። ታሪካቸውን ለመጻፍ ቁርጥ ውሳኔ





ላይ ስደርስ ማረፍ አቃተኝ፤ ሥራው ግን ቀላል እንደማይሆን አውቄዋለሁ። ቢሆንም እነዚያ ዛሬም አጠገቤ ያሉ የሚመስሉኝ፤ ለሕዝብ ሲሉ ደማቸውን ላፈሰሱና አጥንታቸውን ለከሰከሱ፤ እኔ በሕይወት ቆይቼ ከቆምኩበት ምድር በታች ለቀሩት ለምወዳችው ጓደኞቼ ታሪካቸውን መጻፍ በትዝታ የሚያዋልል ቢሆንም ለእኔ ክብር ሆኖ ተሰማኝ።

## እንደገና አሲምባ

«እናንተ ኢሕአፓዎች ይሄንን አሲምባን እንዴት አትረሱትም?»

« ወዳጄ! የልጅነት ፍቅር ይረሳል?!»

አንድ የኢሕአፓ ሰው የመለሰው መልስ

...............................................

ማንንም ያልፈራ፣ ማንንም ያላታለለ

እዚህ ወድቋል፣ የታደለ!!

ጀምስ ዳግላስ - የመቃብር ላይ ፅሁፍ

..............................

እነሆ ከገዳሪፍ አሜሪካ ከገባሁ ከ29 ዓመታት በኋላ በ2002 ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ተጓዝኩ። እንደተለመደው ሁሉ ከዋሽንግተን ዲሲ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ነው የምበረው። የጉዞው ዓላማ ወደዚያ ወደ ልጅነቴ ዓለም፣ ወደምወዳቸው ሰማእታት ጓዶቼ ዘላዓለማዊ የዕረፍት ሥፍራ አሲምባ! መሄድ ነው። አሲምባ! ለአንደበቴ ልዩ ዜማ፣ ለጆሮዎቼ ልዩ ቃና ያለው ቃል ነው። ንጹሕ የሀገርና የሕዝብ ፍቅር ሲገለጽ የተመለከትኩበት፤ ለዓላማ የመኖርን "ሀ ሁ" የቆጠርኩበት፣ ራስን ለሌሎች መሥዋዕት የማድረግን ቁርጠኝነት በተግባር ያየሁበት፤ የብርቅና ድንቅ ጓዶችን ሞት ለሕዝብ ሲባል በጸጋ መቀበልን የተማርኩበት፤ አሲምባ! የፍቅሬና የስብእናየ መሠረትና መታሰቢያ የሁለንተናየ ሥፍራ!! እናም የዚያ ጉዞዬ ዓላማ እንደገና አሲምባየን ማየት ሆነና ከጉዞዬ ዕለት በጣም ቀደም ብየ በሐሳብ መጓዝ ጀመርኩ።

ዕለቱ ደረሰና ገና ወደ አየር መንገዱ ሳመራ ሐሳቤ መተረማመስ ጀመረ፤





ልቤም ምቷን ጨምራለች፣ ትንፋሼም ፈጠን ብሏል፣ አእምሮየም ሥራ በዝቶበታል። ታዲያ በምናቤ የሚመጡት፣ በዓይነ ኅሊናየ የሚታዩኝ፣ እዝነ ልቡናየም የሚያዳምጠው እነኛኑ ሁልጊዜ አብረውኝ ያሉ የሚመስሉኝን ጓዶቼን ነበር። በሐሳብና በትዝታ ሠላሳ ዓመታት ወደኋላ የምመለስ ሳይሆን ትናንት አብሬአቸው የነበርኩ ያህል ይሰማኛል። በሐሳብ ማእበል እንደተንገላታሁ፣ እንዳንዴም ከዕንባየ እንደታገልኩ ረጂሙን በረራ ተወጣሁት።

አዲስ አበባ አየር ማረፊያ ዘመዶቼ ይጠብቁኝ ስለነበር አገኘኋቸው። ከዘመዶቼ ጋር ለአንድ ሳምንት ያህል ከቆየሁ በኋላ በመኪና ወደ ትግራይ ሄድኩ። ትግራይ ከመቀሌ በቀጥታ ወደ ውቅሮ ነበር የሄድኩት።አቤት! እንዴት ያለ ስቃይ ነበር! እንዲያ እሆናለሁ ብየ በፍጹም
አላሰብኩም። ሁልጊዜም ባሰብኩት ቁጥር ልቤ በሐዘን እንደሚሰበር ባውቅም፤ ያን ዕለት ወደ ውቅሮ ስሄድ የተሰማኝን ዓይነት ሐዘን፤ በፍጹም ቃላት ሊገልጹት የማይችሉት ስሜት ግን አልጠበቅሁም። ውቅሮ ከተማ ስንደርስ መኪናውን አስቆምኩና ወደ ውቅሮ የጦር ሰፈር በእግሬ ወጣሁ።

ውቅሮ የሚገኘው የጦር ካምፕ እንዳለ ነው። ያኔ ከለላ አድርገን ስንዋጋባቸው የነበሩት ቤቶች ፈራርሰዋል። ምሽግ አድርገን የተጠቀምንባቸው ድንጋዮች ግን እንዳሉ ናቸው። ሮምሀ የወደቀበት ቦታ ላይ ቆሜ ለደቂቃዎች አስታወስኩት፤ ሮምሀና የአቢኢዮ የተቀበሩበትን ቦታ ለማየት ሄድኩ። ሮምሀ የተቀበረባት ቦታ ከጦር ካምፑ ወደ ምስራቅ በኩል እልፍ ብላ የምትገኝ ኮረብታ ላይ ወጣሁና አየሁት። የአቢኢዮ የተቀበረበት ሜዳ ግን ቤቶች ተሰርተውበት ከተማ ሆኗል። ጌታሁን የተቀበረበት ወደ ምሥራቅ በኩል ያለውንም ሸለቆ ቃኘሁት።

በዚሁ በምሥራቅ በኩል ያለውን ተራራ እልፎ የሚገኝ እጽቢ የሚባል ከተማ አለ። እዚህ ከተማ ነበር እኔና ድላይ ለመጨረሻ ግዜ

የተለያየነው። ወደ ላይ ለመውጣት አልቻልኩም። ስለዚህ ወደ መኪናችን ተመለስኩና ለአዳር ወደ አዲግራት ሄድኩ።

በማግስቱ ከአዲግራት በጠዋት ተነስተን በስተሰሜን አቅጣጫ ወደምትገኘው ወደዛላ አንበሳ ጉዟችንን ቀጠልን። ከአዲግራት አስር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የጉሎ ማከዳ ወረዳ ውስጥ የሚገኙት ተራራዎች አጠገብ ደረስን። መኪናውን አስቁሜ ወረድኩና ወደ ምሥራቅ በኩል ዞሬ ተመለከትኩ፣ የአሲምባን ተራራና የአዲ ኢሮብን በረሐ እንዲሁም የጎእቶሎ፣ የደገይቱና የማእቢኖን ተራራዎችን አየኋቸው። በእነዚህ ተራራዎችና በአካባቢያቸው ጓዶች ሲንቀሳቀሱና ሲታኮሱ በሐሳቤ ታዩኝ። ትዝታቸው እንደገና ወደኋላ ወሰደኝ፤ ያሳለፍነው ሕይወትና ሥራችን ሁሉ ድቅን አለብኝ። ወደመኪናው ተመለስኩ፤ ቅድም ከወረድኩበት ቦታ አምስት ኪሎ ሜትር እንዳለፍኩ ደግሞ በስተግራ በኩል የዳሞና የአደዋ ተራሮች ታዩኝ። እነዚህ ተራራዎች ኃይል አምስት መቶ ውስጥ ሆኜ ብዙ የተመላለስኩባቸው፣ ከድላይ ጋር ሆነን በችግር፣ በደስታና በፍቅር ሐሳብ ለሐሳብ ተዋሕደን፤ ልብ ለልብ ተጣምረን ልዩ ታሪክ ያሳለፍልንባቸው ተራራዎች ናቸው። በነበለትና በእምባሴኒት ተራሮች ሳስታምማትናበማይ ምሻም አካባቢ ልብ ለልብ የተነጋገርንባቸውን ጊዜያት በሙሉ አስታወስኳቸውና ትካዜና ሐዘን ተሰማኝ።

ቤተሰቦቼን ለአሥራ ስድስት ዓመታት ሳላያቸው ቆይቻለሁ፤ ለእኔ ግን ከማንም በላይ የሚናፍቁኝ ጓዶቼ ነበሩ። አብረን ቀን ከሌት፣ ተጉዘን በድካም ሳንሸነፍ ዓላማችንን ለመሙላት የነበረን ስሜት፣ አብረን ስንራብ፣ ስንጠማ፣ ስንሰበሰብ፣ ስንዋጋ፡... የነበረን የእርስ በእርስ ፍቅር፣ መተሳሰብና ጓዳዊ አመለካከት በቀላሉ ከጭንቅላት ሊወጣ የሚችል ስላልሆነ ከእኔም ጋር





እስከሕይወቴ ፍጻሜ አብሮኝ ይኖራል።

መንገዳችንን በመቀጠል ትንሽ እንደተጓዝን ከዛላ አንበሳ በስተምሥራቅ በኩል የተዘረጋውን የመኪና መንገድ ይዘን በአሲምባ መንገድ ምድርባ የሚባል መንደር ደረስን። ይህ መንደር ሁለት ነገሮችን ያስታውሰኛል። አንደኛው ትውስታየ የዚህ መንደር ተወላጆች የነበሩ ሁለት የተሠው ጠንካራ ታጋዮች ስሙር ተስፋ ሚካኤል እና ብርሃነ መስቀል ሐጎስ ናቸው። ብርሃነ መስቀል የመረጃና ደኅንነት ክፍል አባል የነበረ ነው። ከአእምሮየ የማይጠፋው ሌላ ትውስታ ደግሞ ዛላ አንበሳን ከጠላት ኃይል በመጠበቅ ላይ እያለ፣ የተበላሸ ጠመንጃ ለመጠገን ሲሞክር እራሱን በስሕተት የገደለው ሰለሞን ታፈሰ ነበር። የምድርባ ሕዝብም በጥሩ የቀብር ሥነሥርዓት እዚያ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀበረው።

ከምድርባ ተነሥተን ሰበያን በማቋረጥ ኢሮብ ለመግባት ኪኒኪንታ በር ላይ ደረስን። ኪንኪንታ ላይ ሆኖ ኢሮብ ሙሉ በሙሉ ይታያል። የመንሶብሎን፣ የአሰፋይቱን፣ እንዲሁም የአይጋን ተራራ ተመለከትኩ። ከዚያም አሁን ድልድይ የተሠራለትን የኪንክንታን ወንዝ ተሻግረን ወደ ዳህዋን ገባን። ዳህዋን አሁን ከተማ ሆኖ ትምህርት ቤት ተከፍቶባታል። የአሲምባው ጓዴ ፍሱሕ ገብራይ የዚያ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሆኗል ሲባል ሰምቼ በጣም ደስ አለኝ። ለማግኘት ብዙ ብሞክርም ከከተማ ወጥቶ ስለነበረ ላገኘው አልቻልኩም።

ዳውሃን የአመራሩ መኖሪያ የነበረበትና እኔ ጋንታ ሃያ ስድስት እያለሁ ጋንታዋ የሰፈረችበት ቦታ መካከል ላይ የአውቶብስ መቆሚያ ሆኗል። እዚህ ቦታ ላይ ቆሜከል አሳን፣ ዳውሃን፣ ዳያን ስመለከት ጓዶች በሥራ፣ በወታደራዊ

## የቃላት ትርጉምና ምኅፃረ - ቃላት

በወቅቱ ይነገሩ የነበሩና በሁሉም አንባብያን ላይታወቁ የሚችሉ ቃላት ትርጉም

ተአሊም ---------------------- ወታደራዊ ሥልጠና

ኢንተለጀንስ ክፍል --------------- የመረጃ ክፍል

ኩሽክ ------------------ የአቡጀዲ ነጠላ

አብሩክ --------------- ----- የአሳርፍ ትእዛዝ

ተቅሊጥ ----- ------- ----- ሠራዊት የመቀየጥ ምደባ...

ኮሚሳር ------------------ የጋንታ፣ የኃይል፣ የሠራዊት የፖለቲካ ሐላፊ

ኮማንድ ------- ከፍተኛ ወታደረዊ አመራር

ትሪቢዩናል ------- የሠራዊቱ ወታደራዊ ፍርድ ቤት

ክፍለ ሕዝቢ ------- የሕዝባዊ ድርጅት ሥራ ክፍል

ከሻፊ (አብሪ) ------- ከሠራዊቱ ፊት ፊት አካባቢዉን እያጣራ ቀድሞ የሚሄድ ቡድን (ቃኝ)።

ተሸኪል ——— ምሽግ መያዝ

ተበገስ ——— ተንቀሳቀስ

ተዳሎ ——— ተጠንቀቅ





# ምኅጻረ ቃላት

ኢ.ሕ.አ.ፓ.. ---- የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ

ኢ.ሕ.አ.ሠ.. ---- የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት

ግ.ገ.ት. ---- ግንባር ገድሊ ትግራይ

ሕወሐት ---- ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ

ኢ.ፒ. ኤል.ኤፍ. (ሻቢያ) ---- የኤርትራ ሕዝብ ነጻ አዉጪ ድርጅት

ኢ.ኤል.ኤፍ. (ጀብሀ) ---- የኤርትራ ነጻ አዉጪ ድርጅት

ኢ. ዲ.ዩ. ---- የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ዩኒየን

ጠ.ፓ.አ.ኮ. ---- ጠቅላይ የፓርቲ አመራር ኮሚቴ

ጠ.አ.ኮ. ---- ጠቅላይ አመራር ኮሚቴ



የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን ታሪክና የትግል ጉዞ አስመልክተው ብዙ ሰዎች ፅፈው አንብቤአለሁ - በያገባኛል ባይነትም በታሪክ ንባብ ፍቅርም:: ሁሉም የሚስማሙበት አንድ ፍሬ-ነገር፤ የኢህአፓ ታሪክም ሆነ የሌሎች ፓርቲዎች ታሪክ፤ በየአቅጣጫው መፃፍ አለበት የሚለው ይመስለኛል:: በቃል ያለ ይረሳል፣ በፅሁፍ ያለ ይወረሳል ይሏልና::

እኔም፤ ‹‹የታሪክ መኖር ደርዙ፣
ሁሉ መፃፉ በወዙ፤ (''መ'' እና '' ፃ'' ይጠብቃል)
ስህተት የማረም መቅረዙ፤
መጪውን ትውልድ ማገዙ!››

ነው እላለሁ::

እስካሁን ካነበብኳቸው በኢሕአፓ ላይ ያተኮሩ፤ በተለይ በአማርኛ ከተፃፉት መፅሐፍት መካከል፤ የካህሳይን መፅሐፍ ለይቼ ወድጄዋለሁ:: ቀና ነው:: በህፃን የየዋህነት ቀለም የተፃፈ ነው:: ስለራሱ ለራሱ ለመንገር ብሎ እንጂ ለሌሎች ለመንገር ብሎ የፃፈው አይመስልም:: ፅሁፉ ያን ዘመን እንደገና ከሌሎች ጋር እንድወያይበት አድርጎኛል::

የካህሳይ አብርሃም መፅሐፍ በአሲምባ የግል ታሪኩ ላይ ያተኮረ ነው:: የታሪክ-ኩርባዎቹም :- ወላጆቹ፣ ከሱ ጋር ነብስ የተቀባበለው ይመር ንጉሤ የተባለው ገበሬ ፤ እና አሲምባ የወለደለት ድላይ የተባለች ጓድ-ፍቅረኛው፤ ናቸው:: መፅሐፉ የአሲምባ ጓዶቹ ታሪክ ላይ ያተኮረ ነው:: ባለታሪኩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (የኢሕአፓ የታጠቀ ክንፍ) ውስጥ እስከነበረበት ወቅት ድረስ፣ ያሳለፈውን ሁኔታ በመንተራሱ፤ አንድም በዚያው አካባቢ የተወለደ በመሆኑ፣አንድም እዚያው የታገለ በመሆኑ፤ ስለትግራይ ልዩ ልዩ ሥፍራዎችም በቅርበት ያስረዳናል:: በኢሕአሠ ዐይን በመመልከት፤ በዚያ ክልል ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ሌሎች ድርጅቶች ሁኔታም ያገናዝብልናል:: ከቦታው፣ ከፖለቲካው እንቅስቃሴ እና ከሕዝቡ አኳያ ያ ጊዜ ምን አይነት ስዕል ይታይበት እንደነበር ያፀኸያል::

ካህሳይ በትግል ውስጥ ፍቅር እንዳለ ያሳየናል:: ፍቅር ከትግል ያዘናጋል ብሎ ከማፍቀር አልተቆጠበም:: ሲያፈቅርም ተፈጥሮን አልዋሸ፤ ሲፅፍም ተፈጥሮን አልዋሸ:: ነብሱን ለትግሉ ሲሰጥ፤ አልሳሳም:: ለሰው ነብስ ግን በንፁሕ ልቦናውና ለህዝብ ካለው ፍቅር በመነሳት ሳሳ:: ይህንኑም ሳይሳሳ ፃፈ:: መፃፍ፤ ሳይሳሱ ለራስ ታማኝነትን መግለፅ ነውና!

የህይወትን ውጣ ውረድ አዎንታዊውንና ገንቢውን ገፅ ማየት የብዙዎቻችን ችግር ሳይሆን አይቀርምና፤ ይህ መፅሐፍ ትልቅ ውለታ ይውልልናል ብዬ አስባለሁ:: ለማንኛውም፤ መፅሐፉና ታሪኩ የራሱን ሕይወት ይኖራል - che sera, sera!

ነቢይ መኮንን (ገጣሚ፣ ፀሐፊ፣ ተርጓሚ፣ ጋዜጠኛ...)

ዋጋ 100.00 ብር

ህትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር 0111565352